የሃበሻ ጀብዱ

አብርሆት የኢንተርኔት
ቤተ-መጻህፍት



አዶልፍ ፓርለሳክ

ተጫኔ ጆብሬ መኰንን (ተርጓሚ)

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ

የሃበሻ ጀብዱ

አዶልፍ ፓርለሳክ

1989 ዓ.ም.

ተርጓሚ ተጫኔ ጆብሬ መኰንን

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ
ፖስታ ሣጥን ቁጥር፣ 1176
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
ስልክ፣ ቀጥታ + 251-011-123 97 46
ፋክስ፣ + 251-011-124 32 91
ኢ-ሜል፣ aau.press@ethionet.et

© አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ ፪ሺህ፲፩ ዓ.ም.

ISBN 978-99944-52-36-1

በድጋሚ ፪ሺህ፬ ዓ.ም.፣ ፪ሺህ፯ ዓ.ም.፣ ፪ሺህ፱ እና ፪ሺህ፲፩ ዓ.ም. ታተመ።

ብራና ማተሚያ ድርጅት ታተመ።

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

መታሰቢያነቷ

ለወንድሜ ለንጉሡ ጆብሬ መኰንን
ለእናቴ ለአበበች ሺበሺ (እመዋ)

እና

ለመላው ቤተሰቦቼ

ከሁሉም በላይ

ለዚያ ኩሩና ጀግና ትውልድ
ትሁንልኝ።

ተጫኔ ጆብሬ መኰንን

ምስጋና

በዚህ መጽሐፍ ዙሪያ መጽሐፉን ተርጉሜ ለኢትዮጵያ ህዝብ እንዳቀርበው ለአበረታቱኝ የኢትዮጵያና የህዝቦቿ ወዳጆች በሙሉ፣ ለፓቬል ሚኬሽ ! ለፍራንቲሼክ ሞሽና፣ ለየመናዊው ጓደኛዬ ለጋላል ራሺድ አብዶ፣ ለዮሴፍ ተካ እና ለሌሎችም፣

ይሄ መጽሐፍ ለህትመት ከመቅረቡ በፊት አብዛኛውን ቴክኒካል የሆኑ ነገሮችን ማለትም ያረጁ ጥንታውያን ፎቶግራፎችን በዘመናዊ መሳሪያ በማጽዳት፣ የእጅ ሥዕሎችን ልክ በ1948 ዓመተ ምህረቱ አይነት በማስተካከል እና ሌሎች ዝርዝሬ የማልገፋቸውን ጥቃቅን ነገሮች ሁሉ በማስተካከል ለረዳኝ ጓደኛዬ ለኦንድርዤይ ቱማ፣

ስለጦርነቱ የዓይን ምስክር የነበሩትና በተለይም ስለንጉሠ ነገሥቱ ባሕርይ በሰፊው ላጫወቱኝ ለክቡር አቶ ያሮስላቭ ክሮብ (ከ1989 ዓ.ም. በኋላ ኮሎኔል ያሮስላቭ ክሮብ)፣

በመጨረሻ እንዲህ እጅግ በጣም ሲበዛ የፊደል ግድፈቶች የበዛበትን ጽሑፍ በታላቅ ትዕግስት አርሞ ለህትመት ላበቃልኝ ለተወዳጁ አጎቴ ለአቶ አያሌው ሺበሺ ከልብ የመነጨ ልዩ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

ተርጓሚው ተጫነ ጀብሬ መኮንን

ማውጫ

.... ix
መግቢያ 1
1. የሃበሻ በር 11
2. ድሬዳዋ 20
3. አዲስ አበባ 27
4. በአዲሱ ቤተ መንግሥት 37
5. ከአዲስ አበባ ወደ ደብረ ታቦር 46
6. በራስ ካሣ ቤተ መንግሥት 56
7. ጦርነቱ ተጀመረ 62
8. ራስ መንገሻ ሥዩም 67
9. የደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ክህደት 71
10. ጦራችን በጉዞ ላይ 75
11. ዝቅ ካለ ሰማይ ስር 80
12. ዋድላ 90
13. ከአፄ ቴዎድሮስ የልጅ ልጅ ጋር 97
14. በአሸንጌ ሐይቅ 102
15. የጠላት ጦር ከፊታችን 110
16. የብረት ዝናብ 118
17. በእሳትና በጎራዴ 124
18. ተንቀሳቃሹ ከተማ 131
19. ሶስቱ ንጉሦች 140
20. የጣልያኖች ብቀላ 143
21. በነጋሪት ድምፅ 152
22. የአውሮፕላን ቀብር 158
23. ጠላት አፋፍ ላይ 168
24. የፋሽስቱ ጦር ሽንፈት 179
25. ከድል በኋላ 191
26. የጣልያኖች ጭካኔ 206
27. ያልሞቱ ሬሳዎች ዋሻ 206

28. ከሽፍቶች ጋር ግብ ግብ 216
29. ለሁለት ቀን የአርበኞች መሪ 227
30. የራስ ሙሉጌታ ሞት 242
31. የራስ ካሣ ወጥመድ ውስጥ 247
32. የብረቱ አጥር መሰበር 264
33. ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር በኮረም 284
34. የእንግሊዞች ቀይ መስቀል 298
35. ተስፋ ቢስ ቀኖች፣ የግዳጅ ፍጻሜ 309
36. የልጅ ጦር ፍጻሜ 315
37. የአዲስ አበባ (የሸገር) እሳት 320
38. ስደት 322

መግቢያ

ትንሽ ስለደራሲው

የቼክ ሪፐብሊክ ተወላጅ የሆኑት ክቡር ኢንጂነር አዶልፍ ፓርለሳክ በ07/04/1908 ዓ.ም. በዱሮዋ ቼኮዝሎቫኪያ፣ ብርኖ በምትባል ከተማ ተወለዱ። በ18 አመታቸው በብርኖ ከተማ የ2ኛ ደረጃ ትምህርታቸውን አጠናቀው በመቀጠል ከቪሶካ ሽኮላ ኢኮኖሚትስካ ዩኒቨርስቲ [ትርጉሙ የኢኮኖሚክስ ዩኒቨርስቲ እንደማለት ነው] የኤሌክትሮ ቴክኒካል ፋኩልቲ በኢንጂነርነት ተመርቀዋል። ቆየት ብሎም ከፕራግ ዩኒቨርስቲ ኢኮኖሚክ ፋኩልቲ በዲግሪ ተመርቀዋል።

አዶልፍ ፓርለሳክ ገና በ14 አመት እድሜያቸው በብስክሌት የቼኮዝሎቫኪያን አዋሳኝ አገሮች ማለት ኦስትሪያ (ነምሳ)፣ ሃንጋሪ፣ ሩማኒያ፣ ፖላንድንና ጀርመንን ጎብኝተዋል። በ17 አመታቸው ደግሞ ጣልያንና ሳንማሪኖን የመጎብኘቱ እድል ገጥሟቸዋል። በ1926* ዓ.ም. ከጓደኛቸው ከአልዮስ ፖላክ ጋር ወደ ባልካን ሀገሮች በመውረድ ዩጎዝላቪያን፣ አልባኒያን፣ ግሪክን፣ ቱርክንና ሩማንያን ጎብኝተዋል ።

ገና በ19 አመታቸው በአንድ ሊዮድ ትሬስቲኖ (Lioyd Triestino) በምትባል የጣልያን መርከብ ላይ እንደ መርከበኛ ተቀጥረው ሲሪያን፣ ፍልስጥየምን (ፓለስታይን)፣ ግብፅንና ሌሎች አገሮችንም ጎብኝተው ወደ ሀገራቸው ወደ ቼኮዝሎቫኪያ ከተመለሱና፣ ከጓደኛቸው ከአሊዮስ ፖላክ ጋር ለሌላ አዲስ ጉዞ ጥቂት ከተዘጋጁ በኋላ የጉዞ መስመራቸውን ወደ አረብ አገሮችና አፍሪካ አዙረው በርካታ የአረብ ሀገሮችን ጎበኙ። ከዚያም ወደ ግብፅ በመመለስ የአባይን ወንዝ ተከትለው በሱዳን በኩል አድርገው ወደ ኢትዮጵያ ከገቡ በኋላ፣ በሰሜን ኢትዮጵያ ረዘም ላለ ጊዜ ሲዘዋወሩ ቆይተው ወደ ኤርትራ ተመለሱ። በኋላም ቀይ ባህርን በመርከብ ተሻግረው ወደ ሰሜን የመን ገብተዋል። ከሰሜን የመን በፈረስና በግመል ሰንዓ ገብተው፣ ከሰናዓ በመርከብ በቀይ ባህር ያሉ ብዙ ደሴቶችን ሲጎበኙ ቆይተው

---

* በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሱት የቀን አቆጣጠሮች በሙሉ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ነው።

በመጨረሻ በየመኑ ንጉሥ እንግድነት ዓደን (ዔደን) ሰነባብተው፣ ከዔደን ወደ ሀገራቸው ወደ ቼኮዝሎቫኪያ ተመልሰዋል።

አዶልፍ ፓርለሳክ ጉዟቸውን ቀጥለው ሩቅ ምስራቅን፣ ቻይናን፣ ታይዋንንና የጃፓን ደሴቶችን፣ የአፍሪካ ደሴቶችን ጨምሮ ጎብኝተዋል። ደረጃ በደረጃም 12 የአለም ቋንቋዎችን መናገር ችለዋል። ከሁለተኛው የአለም ጦርነት በኋላ በርካታ የትርጉም ስራዎችን ሰርተዋል። ለጥቂት አመታትም ለቼኮዝሎቫኪያ አውቶ ክለብ ካምፓኒ ሰርተዋል። ለዚሁ ድርጅትም መጽሐፍ ጽፈዋል።

አዶልፍ ፓርለሳክ በ1935 ዓ.ም ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው በንጉሠ ነገሥቱ ፊት ቀርበው ትልቅ የሚባለውን የኢትዮጵያን መኰንንነት ማዕረግ ተሾሙ። ከዚያም በካፒቴን ማዕረግ በጣልያን ወረራ ጊዜ (በ1935/1936 እ.ኤ.አ.) በወቅቱ የሰሜኑ ጦር ጠቅላይ አዛዥ ከነበሩት ከራስ ካሣ ኃይሉ፣ የሰላሌው ወታደራዊ አማካሪና፣ በመቶ ሺዎች ከሚቆጠሩት ጀግኖቹ የኢትዮጵያ ልጆች ጎን ሆነው እስካፍንጫው ታጥቆ የመጣውን ወራሪውን የሞሶሎኒ ጦር እስከመጨረሻዋ ቀን ድረስ የታገሉና ያታገሉ ታላቅ፣ ጀግና የጦር መኰንን ነበሩ ።

እኚህ ጀግና ሰው በታላቅ ጀግንነትና ወደር በማይገኝለት የሀገር ፍቅርና ወኔ የእናት ሀገር ፍቅሩን በደሙ ለከፈለው ለዚያ ጦር የታሪክ ገድል *ሃበሽስካ ኦዴሳ* (Habešská Odyssea) ***የሃበሻ ጀብዱ*** የተባለውን እውነተኛ የታሪክ ማስታወሻ ፅፈው ታህሳስ 1 ቀን 1981 ዓ.ም. በቼኮዝሎቫኪያ ዋና ከተማ ፕራግ አርፈዋል፤ አልፈዋል።

በመሆኑም ይህንን ከሰባ አመታት በላይ ያለፈውን እውነተኛውን የአያቶቻችንንና የቅድመ አያቶቻችንን ታሪክ፣ ለታሪክ ተመራማሪዎች፣ ለተማሪዎችና ለአንባቢያን ወደ አማርኛ ተርጉሞ ማቅረቡ ተገቢ መስሎ ስለታየኝ፣ የዚያን ትውልድ የእናት ሀገር ፍቅርና እውነተኛ ታሪክ እንደሚከተለው ለማቅረብ ሞክሬያለሁ።

ትንሽ ስለመጽሐፉ

"ቴክገለሚክ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ወታደር" ብሎ የሚጀምረው የአዶልፍ ፓርለሳክ የሃበሻ ጀብዱ መጽሐፍ ለመጀመሪያ ጊዜ በቼኮዝሎቫኪያ የታተመው እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ1948 ዓ.ም. ሲሆን፣ ለሁለተኛ ጊዜ ይዘቱ እጅጉን በጣም አጥሮ በብዛት የታተመው ግን በ1989 ዓ.ም. ነው።

ይኼንኑ በ1989 ዓ.ም. በብዛት የታተመውን የሃበሻ ጀብዱ መጽሐፍ እኔም ገና የቼክ ቋንቋ ትምህርት አጠናቅቄ በቻርልስ ዩኒቨርስቲ የህግ ፋክልቲ ተማሪ በነበርኩበት ጊዜ ነበር እንደአብዛኛው ኢትዮጵያዊ ሁሉ ገዝቼ በመጽሐፍ መደርደሪያዬ ላይ ያኖርኩት።

ምናልባት የአጋጣሚ ነገር ሊሆን ይችላል፣ ምናልባትም ጊዜ ከማጣትም ሊሆን ይችላል፣ ብቻ ይሄን መጽሐፍ ገዝቼ በቅጡ ሳላነበው እንዲሁ እንደተቀመጠ ብዙ አመታት ተቆጠሩ። ከአመታት በኋላ በአንድ ኮንፍረንስ ላይ ስለ ጣልያን ወረራ ጥናታዊ ጽሑፍ እንዳቀርብ ተጠየኩና ለዚሁ ስራ በየቤተ መጽሐፍቱ እየተመላለስኩ በወቅቱ የተጻፉ ጋዜጦችን ሳይቀር እያነበብኩ ብዘጋጅም ለራሴ ባለመርካቴ እንዲሁ በኢንተርኔት የተጻፉ ነገሮች ባገኝ እያልኩ በፍለጋዬ ገፋሁበት። ይሁንና ለዚያ በርካታ የታሪክ ተመራማሪዎች ለሚሰበሰቡበት ኮንፍረንስ ግን በቂ መረጃዎችን ያገኘሁ ያገኘሁ አልመስል እያለኝ ተቸግሬ ተቀመጥኩ።

ምንም እንኳን በአንድ ወቅት አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያን ታሪክ ለሁለት ሴሚስተር የተማርኩ ቢሆንም ያ ውሱን እውቀት ለኮንፈረንሱ ዝግጅት ብዙም ሳይረዳኝ እንዲሁ መላው ጠፍቶኝ እቤቴ እንደተቀመጥኩ፣ ያቿን ከጥቂት አመታት በፊት ገዝቼ በመጽሐፍ መደርደሪያዬ ላይ አቧራ የጠገበችውን የአዶልፍ ፓርለሳክን "የሃበሻ ጀብዱ" አስታወስኩና አቧራዋን አራግፌ ማንበብ ጀመርኩ።

እውነቱን ለመናገር ይኼን የመሰለ እውነተኛ የታሪክ እንቁ መጽሐፍ እቤቴ አስቀምጬ በየመጽሐፍ ቤቱ መንከራተቴ እጅጉን አናደደኝ። ቢሆንም ከዚያች ቀን ጀምሮ ከዚች መጽሐፍ ጋር ለዘላለሙ የማንነጣጠል ጓደኛሞች ሆንን። በሄድኩበት ቦታ ሁሉ ሁሌም ይገኖት እሄድ ጀመር። ባገኘሁት አጋጣሚ ሁሉ እየገለጥኩ ዝም ብዬ በፍቅር አነብባት ጀመር።

በፕራግ ኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያ ወዳጆች ማህበር በወር አንድ ጊዜ ወሩ በገባ በመጀመሪያው አርብ እየተገናኘን እንጫወት ነበር። በዚህች አርብ አሁን አሁን

ሁሌም ከእጄ የማትለየዋን መጽሐፌን እንደያዝኩ ወደዚያች ቢራ ቤት እሄድ ነበርና በኋላ ወደ ትርጉም አለም ደፍሬ እንድገባ ብዙ ያበረታታኝ ጓደኛዬ ጋቬል ሚኬሽ ይቺ እኔ የያዝኳት መጽሐፍ በጣም አጥራ የተጻፈች እንደሆነችና ሙሉ በሙሉ አዶልፍ ፓርለሳክ የጻፈውን እንደማታጠቃልል ነገረኝ። ቃሉን ጠብቆም በሚቀጥለው ወር ስንገናኝ የ1948 ዓ.ምህረቱን እትም ከአርጌ ተራ ገዝቶ አምጥቶ ሰጠኝ።

እናም ከዚያች የአርብ የቢራ ቤታችን እንደተመለስኩ ሌሊቱን ሙሉ በታላቅ ጉጉት የ1948 ዓ.ምህረቱን እትም አነበብኩት። ምንም እንኳን ጋቬል ሚኬሽ ያመጣልኝ መጽሐፍ በጣም ያረጀና ጥቂት ገጾች የሚጎድሉት ቢሆንም ጋቬል ሚኬሽ እውነት ነበረው። የ1989 ዓ.ምህረቱ እትም ለኮሚኒስቶች በሚመች መልኩ የተዘጋጀ አጭር ታሪክ ነበር። በመጨረሻ ሙሉ በሙሉ ልተረጉመው ቆርጬ ስነሳ ፕሮፌሰር ፍራንቲሼክ ሞሽና አንድ በደህና ሁኔታ ላይ ያለ የ1948 ዓ.ም. መጽሐፍ ከግለሰብ ላይ በውድ ዋጋ ገዝቶ ሰጠኝ።

ይኼ የ1948 ዓ.ም. እትም እጄ ከመግባቱ በፊት የ1989 ዓመተ ምህረቱን እትም ወደ አማርኛ እየተረጎምኩ በwww.cyberethiopia.com...warka... የባህልና ስነጹሁፍ ድረ-ገጽ ላይ አወጣው ነበር። በዋርካ ያሉ በአካል የማንተዋወቅ የሀገሬ ልጆች መጽሐፉ ለኢትዮጵያ ህዝብ ታትሞ መድረስ እንዳለበት ደጋግመው እያስታወሱኝ እና እያበረታቱኝ፣ ይቺኑ የ1989 ዓ.ም. ቁንጽል ታሪክ እስከጨርስኩበት ጊዜ ድረስ የኢትዮጵያ የገበሬ ወታደር በወጣው ተራራ እየወጡ፣ በተሻገረው ወንዝ እየተሻገሩ፣ በገባው ጉድጓድ እየገቡ፣ አብረውኝ ዘምተዋልና በዚህ አጋጣሚ ለዋርካ ልጆች ከፍ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

በመጨረሻ ይኼን የፊደል ግድፈት የበዛበትን የትርጉም ስራዬን ለአጎቴ ለአቶ አያሌው ሺበሺ ላኩለትና በእሱ ከፍተኛ ድጋፍ እነሆ ለህትመት በቃ። ትልቁም ምስጋናዬ ለእሱ ይሁንልኝ።

የአርሲዋ ትንቢተኛ አሮጊት

ከድሬዳዋ በአውራሪስ ባቡር ተሳፍረን ለገሃር ስንገባ የሀገሬ ልጅ አቶ ሉድቪክ ካልቮዳ ተቀብሎን፣ ቤት እስክንከራይ ድረስ በእንግድነት እንድናርፍ በዋናው አደባባይ ወደሚገኘው መኖሪያ ቤቱ ወሰደን።

ደከም ያለ ንፋስ በመተኛት ላይ ያሉትን ለምለሞቹንና ረጃጅሞቹን የአዲስ አበባ የባህር ዛፎች ያወዛውዛቸዋል። ራቅ ብሎ የተራቡ ጅቦች ጩኸት ይሰማል። ለጅቦቹ ጩኸት የአዲስ አበባ ውሾች ከየጎጆው ከፍ ባለ ጩኸት ይመልሳሉ። በዚህ መኻል አንዲት ደረቅ ጥይት ጮኸች። ወዲያው ጅቦችም ውሾችም ዝም አሉ።

የሀገሬ ልጅ ሉድቪክ ካልቮዳ እንዲን ሲጻራ አጥሶ ይተረኩሳትና አንዲት ቃል ሳይተነፍስ ሁለተኛዋን ይለኩሳል፣ ሶስተኛዋን፣ አራተኛዋን። ብቻ በዝምታ ያስባል፤ ይተክዛል። እንዲህ መተከዙ አይፈረድበትም። እነሆ የሰኔ ወር መጨረሻ 1935 ዓ.ም. ነው። የወልወል ግጭት ጣጣ በጠቅላላው ነፃዋ የኢትዮጵያ ምድር ላይ የጦርነት ዳመናውን ከባለ ሰነባብቷል። ይኼ የጦርነት ዳመና መብረቅ ከወለደ ጦርነት መፈንዳቱ ነው። ጦርነት ተጀመረ ማለት ደግሞ ሉድቪክ ካልቮዳ ለረጅም አመታት በአዲስ አበባ ጉልበቱንና ገንዘቡን አፍስሶ የገነባው ድርጅት ፍሬ ማፍሪያው ሲቃረብ በጦርነት እሳት መንደዱ ነው። ከዚህ ትካዜው ድንገት ብንን ብሎ "ስለ አርሲዋ ትንቢተኛ ሰምተሃል?" ሲል ድንገት ጠየቀኝ። "አልሰማሁም" አልኩት።

ወዲያው የአርሲዋን ትንቢተኛ አሮጊት አስገራሚ ትንቢት ያወጋኝ ጀመር። ከንግሥት ዘውዲቱ ሞት በኋላ "ሬገንት ባለ ሙሉ ስልጣን እንደራሴ ራስ ተፈሪ መኮንን" ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ተብለው ዘውድ ሲጭኑ አዲስ አበባ ከምንጊዜውም በላይ ደምቃና አምራ ነበር። በንግሥናው ስነ ስርዓትም ላይ በርካታ የባህር ማዶ ነገሥታትና መሳፍንት፣ ፕሬዝደንቶች፣ ጠቅላይ ሚኒስትሮችና ሌሎች ታላላቅ ሰዎችም ተገኝተው ነበር።

ከንግሥናው ስነ ስርዓት በኋላ በአዲስ አበባ የተለያዩ ትንቢቶች በሰፊው መወራት ጀመሩ። የአርሲዋ አሮጊት ትንቢት ግን ከሁሉም ትንቢቶች በልጦ ከአዲሱ ንጉሥ ጆሮ ደረሰ። ትንቢቱም፣ "ኃይለ ሥላሴ የመጨረሻው የኢትዮጵያ ንጉሥ ነው። ለረጅም ጊዜ አይገዛም። በጠላት እጅም ይሞታል። ዘውዱም እስከመጨረሻው ይወድቃል" የሚል ነበር።

ይህንና ሌሎችንም የአርሲዋን አሮጊት ትንቢቶች የሰሙት አዲሱ ንጉሥ ለመንግሥታቸው ጥሩ መሰረት እንደማይሆኑ ተረድተው አሮጊቷን የአርሲ ትንቢተኛ ፈልገው እንዲያመጧት ወታደሮቻቸውን ወደ አርሲ ቢልኩም፣ አሮጊቷን ትንቢተኛ እንዲያመጡ የተላኩት ወታደሮች አንዳቸውም ሳይመለሱ ቀሩ።

የአዲስ አበባ ከፋ ወሬኞች እንዳወሩት አሮጊቷ ትንቢተኛ ሰማያዊ ኃይል ያላትና የዱር አራዊትንም የማዘዝ ኃይል ስለነበራት ንጉሠ ነገሥቱ የላኳቸውን መልክተኛ ወታደሮች አባቦች እየነደፉ፣ አንበሶች እየበሉ በዚያው አስቀሯቸው እያሉ አወሩ።

የአርሲዋ ትንቢተኛ አሮጊት ትንቢቶች ከስድስት አመት በኋላ ሙሉ በሙሉ ባይሆንም በከፊል ተፈጸሙ። ነው ወይስ በዚያን ጊዜ የጣልያኖች ፕሮፓጋንዳ እስከመሀል ሀገር ድረስ ዘልቆ ገብቶ ነበር?

1

ሃበሻ በር

"ማንን ነው የምትፈልገው መሲዮ?"

"የባቡር ጣቢያውን ሃላፊ" ስለው፣

በፀሐይ ብዛት ከሰማያዊነት ወደ ዳለቻነት የተለወጠችውን የኢትዮጵያና የፈረንሳይ ባቡር ጣቢያ ሰራተኞች የደንብ ልብስ የለበሰ አንድ በጣም ረጅምና ጠብደል፣ ጥቁር፣ ባዶ እግሩን የሚሄድ የጣቢያው ዘበኛ ትከሻውን እያወዛወዘ፣ "እዚህ የለም መስዮ:: ወደእዚህ ብቅ የሚለው ባቡሩ ለመሄድ ሲዘጋጅ ብቻ ነው" አለኝ::

"በስንት ሰዓት ነው ባቡሩ የሚሄደው?"

"አላውቅም መሲዮ:: ግን ዛሬ አንድም ባቡር አይኼድም:: ምናልባት ነገ ወይም ከነገ ወዲያ ይኼድ ይሆናል::"

ራሱ ዋናው የባቡር ጣቢያው ሃላፊ ባቡሩ ወደ አዲስ አበባ የሚሄድበትን ሰዓት ቀርቶ ቀኑን እንኳን ማወቁን እግዜር ይወቀው:: ታዲያ ይኼ ምስኪን ዘበኛ እንዴት አድርጎ ነው የሚያውቀው?

ምናልባት ነገ በጂቡቲ ወደብ የመንገደኞች መርከብ ከመጣ ድርጅቱ ልዩ ባቡር ወደ አዲስ አበባ ያዘጋጃል:: አለበለዚያ ከነገ ወዲያ ቋሚው ባቡር ከጂቡቲ ወደ አዲስ አበባ ይኼዳል:: ችግሩ ታዲያ አዲስ አበባ እስኪደርስ ሶስት ቀን ይፈጅበታል::

ጂቡቲ የበረሃ ቅኝ ግዛት:: ይቺ ሃሩር የበዛባት ምድረ በዳ መሳይ አነስተኛ የወደብ ከተማ ሁለት ሦስት ሰፋፊ ግን አጫጭር የአስፓልት መንገዶች ሲኖሯት፣ በነዚሁ የአስፓልት መንገዶች ግራና ቀኝ የዚቺው የበረሃ ቅኝ ግዛት ገገርዎች የመኖሪያ ቪላ ቤቶች ፈንጠር ፈንጠር እያሉ ጉች ጉች ብለዋል:: ከነዚህ ቪላ ቤቶች በተጨማሪ ይቺ የበረሃ የወደብ ከተማ በአረቦቹ ነጫጭ የቦረንቅ ቤቶችና ውሽቅሽቅ ያሉ የሱማሌዎች የሳር ጎጆዎች የሞሉባት ናት::

ይኼ ጉዳይ ሃሩር ፈረንሳውያንን ትኝ ገበሮች ደማቸውን ከሰጋቸው መጥጦ በቆዳ ብቻ የተሸፈኑ አጽሞች አስመስሏቸዋል። እነዚህ ትኝ ገበሮ ፈረንጆች በዚች በረሃ የሚኖሩት ወይ በትጣት ነው፤ አለያም የፈረንሳይ ሀገር ኑሮ የመረራቸውና ጥቂት ፍራንኮች ብናጠራትም በሚል ባዶ ተስፋ የፈረንሳይን መንግሥት ለማገልገል በወዶ ገባ ትብተው በሃሩር የሚነዱ ምስኪኖች ናቸው።

በዚች በረሃ ከፈረንሳይ ትኝ ገበሮች በተጨማሪ የግሪክና የአርመን ዜጎች በንግድ ሥራ ላይ ተሰማርተው እየነገዱ ሲኖሩ ይታያሉ። እነዚህ ነጋዴዎች አብዛኛዎቹ ከመጠን በላይ ሲበዛ ሃብታሞች ሆነዋል። እነዚህ ሃብታም የግሪክና የአርመን ነጋዴዎች ባላቸው ሃብት በፈረንሳይ ሀገር ባሉ ድሎት የበዛባቸው የወደብ ከተሞች ተንደላቀው መኖር ሲቻላቸው፤ በሆነ ምትሃታዊ ምክንያት እንዲሁ በዚች በረሃ እየነደዱ ይኖራሉ፤ ለምደውታል። የሰው ልጅ በእንዲህ ዓይነት በረሃ ለረጅም ዓመታት ሲኖር ይደነዝዛል፤ እና ሌላ ምንም ነገር አይታየውም።

እንደ ገሃነም እሳት የሚፋጀው የጂቡቲ ፀሐይ የህይወትን ጥላ መጥጦ፣ አይምሮንም አደንዝዞ፣ ማሰብን አስቁሞ፣ ተስፋ አስቆርጦ እንዲሁ መና ያስቀራል። በቀን በዚያ ጠራራ ፀሐይ ፈጽሞ መስራት አይቻልም። እና አዲስ መጤ ፈረንጆች የሀገሬውን ሰው ስንፍና ከሁሉ ቀድመን እናወግዛለን። ግን ለጥቂት ዓመታት በዚች በረሃ የኖረ ፈረንጅ ችግሩ በደንብ ይገባውና እሱም ከነሱ በላይ ሰነፍ ሆኖ ይቀራል።

የቅኝ ግዛት ቢሮዎች ከጠዋት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ክፍት ናቸው፤ ማለት እንዳው ለነገሩ የሚሰራ ነገር ካለ ማለት ነው። ከሰዓት በኋላ ደግሞ ከአስር ሰዓት ጀምሮ እስከ ምሽቱ ድረስ ቢሮዎች ክፍት ናቸው። እንዲህ ዓይነቱ የሥራ ሰዓት በጠቅላላው በምስራቅ አፍሪካ የቅኝ ግዛቶች በሙሉ ተግባራዊ ነው።

እዚህ «መስራት» ማለት ቢሮ ውስጥ ተቀምጦ የቀዘቀዘ ውስኪ በበረዶ መጠጣት ማለት ነው። በእውነቱ የሆነ ነገር ተቀምጦ መስራት ፈጽሞ አይቻልም። እንዲያው አንዱ የዚህ ዓይነት የቅኝ ገበሮች የቢሮ ሰራተኛ የሆነ ነገር ልስራ ብሎ ቢነሳና እርሳስ ቢያነሳ፣ ከመላ ሰውነቱ እንደ ጎርፍ የሚወርደው ላብ በእጁ በኩል ወርዶ ወረቀቷን በሰከንዶች ልዩነት ከጠረጴዛው ጋር አርሶ ያጣብቃታል።

ምንም እንኳን በኤሌክትሪክ የሚሰራው አዙሪት አውሎ ንፋስ ቀረሽ ንፋስ ቢያስነሳምና የቢሮዋ መስኮቶችም ሆነ በሯ ወለል ብለው የተከፈቱ ቢሆኑም፣ በእውነቱ ለሰዓታት ተቀምጦ መስራት የማይታሰብ ጉዳይ ነው። ኤሌክትሪክ ባልገባባቸው ቢሮዎች ውስጥ በዚያ የኤሌክትሪክ አዙሪት ፈንታ ሁለት ሱማሌዎች ከቢሮው ሰራተኛ ጀርባ ቆመው የቅኝ ግዛቱ ሰራተኛ እንዳያልበው ሲያራግቡ ይውላሉ።

ዛሬ በጅቡቲ ያ ጉዳይ ሃሩር ከተማዋን አስጨንቆ ይዟታል። ምንም እንኳን ከሰዓት በኋላ ቢሆንም የጅቡቲ መንገዶች በሙሉ ባዶ ናቸው። ሰው ቀርቶ ዘዋሪ ውሻ እንኳ አይታይም። ማንም ሰው ወደ ውጪ መውጣት አልደፈረም። የኒም ሾፌር

በባቡር ጣቢያው አጠገብ የሆነች ጥላ ነገር ስላገኘ በዛፎቹ ጥላ ስር መኪናዋን አቁሞ ውስጧ ተኝቷል። እኔ የመኪናዋን የፊት በር ከፍቼ ስገባ ከእንቅልፍ ነቅቶ፣

«ወዴት መሄድ ነው የምትፈልገው መሲዮ?» አለኝ።

«ወደ ሆቴል መልሰኝ» አልኩት።

እነዚህ የጂቡቲ ሶማሌዎች አንቱታ ብሎ ነገር አያውቁም። ለምን? ሶማሌዎችና አረቦች ሲበዛ ብልጣብልጦች ናቸው። በየቀኑ የተወሰኑ የፈረንሳይኛ ቋንቋ ቃላትን ያጠኑና በጥቂት ጊዜ ውስጥ አቀላጥፈው ፈረንሳይኛ መናገር ይጀምራሉ። ችግሩ ታዲያ ያገኙት፣ የሚያናግራቸው ፈረንጅ ሁሉ አንተ ብሎ ስለሚጠራቸው እነሱም ባጠኗት ፈረንሳይኛ መልሰው ትልቁን ጌታ ሳይቀር «አንተ» እያሉ ይዘረጥጣሉ። ለማኙ ሳይቀር «እባክህ ቸገረኝ» ብሎ አስተዛዛኝ ከመለመንና ሆኖ በሀገሬው፣ በተወላጁና በቅኝ ገዢዎቹ ፈረንጆች መካከል ሰላም የወረደ ከማስተዛዘን ይልቅ እንዲሁ ዝም ብሎ «ፍራንክ ስጠኝ መሲዮ» ይላል። እንደዚህም ይመስላል።

ጅቡቲ የፈረንሣዮች የቅኝ ግዛት የወደብ ከተማ ነች እየተባለች ተጋኖ የሚወራላት ሀገር «እግዜሩ የረሳት» ትመስላለች። ጅቡቲ ምንም የማይበቅልባት፣ ምንም የሌለባት፣ ምድረ በዳ ናት። በዚች የወደብ ከተማ ምንም ነገር አይበቅልም፤ ህይወት ያለው ነገር ሁሉ ሳይውል ሳያድር ይበላሻል፤ ይጠፋል። ታዲያ እንዴት በዚች እግዜሩ በረሳት ምድር ላይ የሰው ልጅ መኖር ይቻለዋል? እንኳን ሰው የግሪኮቹ፣ የአርመኖቹና የአረቦቹ ቤቶች ሳይቀሩ በሚነፍሰው ጨዋማ ንፋስ ተስነጣጥቀው የሥጋ ደዌ በሽታ የወረራቸው ይመስላሉ። እነዚያ የሀገሬው ተወላጆች እንደ ባህላቸው ቤት እንኳን እንዳይሰሩ በአካባቢው ዛፍ ለምልክት እንኳን አይታይም።

ስለ ጅቡቲ በሰፊው ከሚወሩ ቀልዶች የመጀመሪያዎቹ የቅኝ ገዢዋ የፈረንሳይ ወታደሮች ጅቡቲ ሲገቡ፣ ዛፍ አይደለም የሳር ዘር ቀርቶ ፋንድያ የሚመስል ነገር እንኳን ባለማግኘታቸው ሰው የማይኖርበት ምድረ በዳ መስሏቸው ሊመለሱ መንገድ ጀምረው ነበር ይባላል።

ሌላው ትኩስ ቀልድ ደግሞ፣ አዲሱ የጅቡቲ ቅኝ ግዛት ገገር በጅቡቲ ቤተ መንግሥት ቅጥር ግቢ የተወሰኑ ዛፎች ለመትከል በተደጋጋሚ ቢጥርም፣ አንዲት ዛፍ እንኳን ማጽደቅ ሳይቻለው ልፋቱ ከንቱ ሆኖ ይቀርበታል። በርግጥ ይኼ አዲሱ ገገር ያን ሁሉ ዛፍ በተደጋጋሚ ከአረብ አገሮች ድረስ እያስመጣ ለማጽደቅ ቢሞክርም ዛፎቹ በተተከሉ በጥቂት ቀናት ውስጥ ጠውልገው እየደረቁበት ሲቸገር ከርሞ፣ በመጨረሻ በጅቡቲ ዛፍ ተክሎ ለሚያጸድቅ ማንኛውም ሰው ከፍተኛ ሽልማት እንደሚሰጥ በይፋ ያስደነግጋል።

ገዢው ይኸን ቃል በአዋጅ ካስነገሩ ከጥቂት ወራት በኋላ አንድ ግሪካዊ ነጋዴ መኖሪያ ቤቱን በዘንባባ ተክል አሳምሮ በጅቡቲ አሉ የሚባሉ ባለስልጣኖችንና ታላላቅ ሰዎችን በሙሉ ለራት ግብዣ ይጠራል፤ በዚህ የራት ግብዣ ላይ አዲሱ አገረ ገዢም ተገኝቶ ነበር።

ወደ ራቱ ግብዣ የገቡት ተጋባዦች፤ ራሱ አዲሱ ገዢ ሳይቀር፤ የግሪካዊውን ነጋዴ ግቢና የዘንባባ ተክሎቹን ገና ከመግባታቸው ሁሉም ሲያደንቁለት፤ ብልጡ ግሪካዊ ነጋዴ ሁሉንም በፈገግታ ተቀበላቸው።

አብዛኛው የዚያች ምሽት ተጋባዥ እንዴት እነዚህን የዘንባባ ተክሎች ማልማት እንደቻለ ምስጢሩን እንዲነግራቸው ደጋግመው ቢወተውቱት የግሪኩ ነጋዴ እንዲሁ እየሳቀ ብቻ ምስጢሩን ሳይነግራቸው ዝም አለ። ከነዚህ ተጋባዦች መካከል ለነዚህ የዘንባባ ዛፎች ታላቅ ትኩረት ሰጥቶ ምሽቱን በትኩረት ሲመራመር ያመሸው አዲሱ ገዢ፤ በሚነፍሰው በበጋው የምሽቱ ንፋስ እነዚህ የዘንባባው አረንጓዴና ለጋ ቅጠሎች ያለመጠውለጋቸው ከባድ ጥርጣሬ ውስጥ ስለከተተው፤ ከተቀመጠበት የክብር ቦታ ተነስቶ ሄዶ አንዱን የዘንባባ ዛፍ ግንድ ሲነካ የግሪኩ ነጋዴ ከባድ ምስጢር ለሰው ተገለጠለትና እየሳቀ ወደ ቦታው ተመለሰ እንጂ ብልጡን የግሪክ ነጋዴ በእንግዶቹ ፊት አላጋለጠውም። ምስጢሩ የዘንባባው ግንድ ብረት ሲሆን እነዚያ የማይጠወለጉ ግን በጣም የሚያምሩ አረንጓዴዎቹ የዘንባባው ቅጠሎች ደግሞ አረንጓዴ ቀለም የተቀቡ ቆርቆሮዎች ነበሩ። ብቻ ግሪካዊው ነጋዴና አዲሱ ገዢ ስለተግባቡ እየተያዩ ተሳሳቁ። ይቺ ቀልድ ምናልባት እድሜን ተጋና ተወርታ ሊሆን ይችላል። ቢሆንም የጅቡቲን የአየር ጸባይ በትክክል ትገልጻለች።

የሶማሊው ተወላጅ ሾፌሬ መኪናዋን ድንገት ከሆቴሏ በራፍ ላይ ሲያቆማት ከዚህ የቀን ቅዠት ባነንኩ። አዎ ይቺ ሆቴል ለሚቀጥሉት ሁለት ወይም ሶስት ቀናት መጠለያዬ፤ ማደሪያዬ፤ ቤቴ ናት። በሆቴሏ በረንዳ አንድ ወፈርና ፈርጠም ያለ ፈረንጅ ሰፊ፤ ረጅምና ነጭ ሥሥ ሱሪ ታጥቆ እጅ ጉርድ ነጭ ሸሚዙን እንደለበሰ ተቀምጦ በትልቅ መሃረብ መሳይ ጨርቅ ነገር አስር ጊዜ ላቡን ከግንባሩና ከማጅራቱ ላይ ይጠርጋል። የማውቀው የቼክዝሎቫኪያ ተወላጅ፤ ወዳጄ፤ የሀገሬ ልጅ መሆኑን ከሩቅ ለየሁት፤ እሱም አወቀኝ መሰለኝ ከሩቅ፤

«የት ነው ስትንቀዋለል የዋልከው?» ሲል እየሳቀ ጠየቀኝ።

«ባቡር ጣቢያ ነበርኩ» ስለው፤ አሁን ከቅድሙ በላይ ጮክ ብሎ ሳቁን ለቀቀው። ሳቁን እንደምንም ተቆጣጥሮ፤ «ባቡሩ የሚሄድበትን ሰዓት ለማየት ነበር?» አለኝ አሁንም ያንኑ ሳቁን እየሳቀ፤ አብሬው እንድቀመጥ በእጁ ምልክት እያሳየ ጋበዘኝ። ቀጥሎም ወደ አዲስ አበባ በሳምንት ሁለት ጊዜ ብቻ ባቡር እንደሚሄድ ገና ሳልቀመጥ በፊት መርዶውን አረዳኝ።

ትንሽ ስንጓጠት ቆይተን ከተማዋን እየተዘዋወርን እንድንጎበኛ ያቀረበልኝን ግብዣ ተቀብዬ ይቺን አግዜሩ የረሳት የምትመስለውን ምድረ በዳ የጠይብ ከተማ ለመጎብኘት ሆቴሏን ለቅቀን ወጣን፡፡

በእነዚያ የአረቦች፣ የግሪኮችና የአርመኖች ነጫጭ የድንጋይ ቤቶች መካከል ባለች ሸለቆ በምትመስል ጠባብ መንገድ ቢጋባገር ትንሽዬ የቤት መኪና ስንጓዝ ቆይተን ከከተማዋ ዳርቻ ደረስን፡፡ በመንገዳችን ላይ ጋባገሯ ይቺን ትንሽዬ አሮጌ መኪና በ900 ፍራንክ እንደገዛት ደጋግሞ ነገረኝ፡፡

ከከተማዋ ዳርቻ እንደደረስን የዕፅዋት ዘር የማይታይበት መጨረሻ የሌለው የሚመስል የበረሃ ሜዳ ከፊታችን ተዘረጋ፡፡ በዚህ የበረሃ ሜዳ ላይ የጠጠሩ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ቁርጥራጭ የጨው ስባሪዎች እንደ አልማዝ ከሩቅ ያበራሉ፣ ያብረቀርቃሉ፡፡

እንዲህ የተፈጥሮን ምስጢራዊ ድራማ ስናደንቅ ቆይተን ፀሐይ ጀንበር ወደቤቷ ስትገባ እኛም ወደ ከተማ ተመለስንና ከአንድ መናጢ የግሪክ ሆቴል ደጃፍ ላይ መኪና ተብዬዋን አቁመን ወደሆቴሏ ገባን፡፡

በጠረጴዛዎች ዙሪያ ወንበሮች ተደርድረውና ጥላ ተዘርግቶላቸው እንግዶችን ለመቀበል የሆቴሏ በረንዳ ዝግጁ ቢሆንም፣ ያቺ የግሪኩ ሆቴል የሰው ዘር አይታይባትም፡፡ ጭር እንዳለች ነው፡፡ አንዲት ጥግ ላይ ግን አንድ አንገቱን ደፍቶ የተቀመጠ ፈረንጅ ጋባገሩ ከሩቅ አየና ወደዚሁ ፈረንጅ ሄድን፡፡ ከፈረንጁ አጠገብ እንደደረስን ከፈረንጁ ጋር ልባዊ ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ እኔንም አስተዋወቀኝ፡፡ ይኼ ፈረንጅ ኦላፍ ሄንድሪክ ይባላል፡፡ ዝርያው ሲውዲናዊ ሲሆን ዜግነቱ ግን ማለት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ፈረንሳዊ ነው፡፡

ኦላፍ ሄንድሪክ በሁለመናው እውነተኞቹን የቅኝ ገገር ፈረንጆችን ይመስላል፡፡ ምንም ነገር ሳይናገር ትንሽ በረዶ ጣል የተደረገባትን ሙሉ ውስኪ የያዘች ብርጭቆውን እንደጨበጠና አንገቱን እንደደፋ ጥቂት ሲተክዝ ቆይቶ ወደአንዳችንም ሳይመለከት የብርጭቆዋን ግማሽ ያህል በአንድ ትንፋሽ ይጎነጭና ተመልሶ ያቀረቅራል፡፡ ምናልባት ማሰብ ቀርቶ ህልም ማየትም ሳይተው አይቀርም፡፡ ብቻ ደንዝዟል፡፡ አሁን ያጋመሳትን ብርጭቆ በአንድ ትንፋሽ ጨልጦ ፍፁም ለኔ ባዘነ ወይም በተቆረቆረ በሚመስል አስተያየት ትክ ብሎ ሲያየኝ ቆይቶ «ምን ሰይጣን ቢይዝህ ነው ወደዚች የተረገመች ወደብ የመጣኸው?» ሲል ጠረጴዛዋን በቡጢ ደለቃት፡፡ የኔ ጋባዥ ፈጠን ብሎ «እዚህ ብዙ አይቆይም፣ ወደ ኢትዮጵያ ዘልቆ ለመሄድ ነው የመጣው» ሲል የዚህን ስዊድናዊ ንዴት ለማረጋጋት ሞከረ፡፡ ኦላፍ ሄንድሪክ አሁን ትንሽ ፈገግ ብሎ «ታዲያ እንደሱ አትለኝም እንዴ? ኢትዮጵያ?» ኦላፍ ሄንድሪክ ልክ ለብቻው እንደሚያወራ ሰው ደጋግሞ ኢትዮጵያ እያለ እኛን ጥሎን እሱ በሃሳብ በትዝታ በጣም በጣም ርቆ ሄደ፡፡

ከዚያም አላፍ ሄድሪክ አሳላፊው ያመጣለትን ትንሽ በረዶ ጣል የተደረገባትን ሙሉ የውስኪ ብርጭቆ በደመነፍስ እጁን ብቻ ወደጠረጴዛዋ ልኮ ካነሳ በኋላ ግማሽ ያህሉን ተጎንጭቶ ወደኔ ቀና ብሎ እያየ «ኢትዮጵያ የተቀደሰች ሀገር ናት፤ አይዞህ በኢትዮጵያ እንዲህ በሃሩር ነደህ፣ ደንዝዘህ ሞትን ብቻ እየጠበክ ተስፋ ቆርጠህ አትቀርም። ኢትዮጵያ ጥሩ ሀገር ናት። ከኢትዮጵያ እግሬን ነቅዬ የወጣሁበትንና ለፈረንሳይ ቅኝ ገገርዎች የማይረባ ፍራንክ ስል ውል የፈረምኩባትን ቀን እድሜ ልኬን እንደረገምኩ እኖራለሁ። ለሰይጣን መንፈስን አሳልፎ እንደመሸጥ ነው የምቆጥረው! እኔ በዚች አጭር ህይወቱ የሰራሁትን ስህተት እንዳትሰራ አደራ» አለኝና ቀሪዋን ግማሽ ብርጭቆ አሁንም በአንድ ትንፋሽ ጨልጦ መልሶ አንገቱን ደፋ።

ፈጣኑ አስተናጋጅ ያቀረበለትን አዲስ ተቀድቶ የመጣ ውስኪ አሁንም እንዳቀረቀረ በደመነፍስ እጁን ወደጠረጴዛዋ ልኮ ብርጭቆዋን ከጨበጠ በኋላ እንደመሳቅ እያለ ቀና አለና «አየህ ወዳጄ፣ በዚች ምድረ በዳ የሚበቅል ነገር ቢኖር ድንጋይና አሸዋ ብቻ ነው» አለና ብቻውን እንዳበደ ሰው ድምጹን ከፍ አድርጎ መሳቅ ጀመረ። ምናልባትም እብደቷ እየጀማመረቸው ሳይሆን አይቀርም።

እንዲህ እኔና ጋባገር ከአላፍ ሄንድሪክ ጋር ተቀምጠን ስንቆዝም ከፊት ለፊታችን በተዘረጋው አስፓልት ላይ አንድ ትንሽ የስፖርት መኪና በከፍተኛ ፍጥነት እየከነፈች መጣች። በፈለጉት ፍጥነት ቢበሩ ትራፊክ ቀርቶ ዘዋሪ ውሻ እንኳን በሌለበት አስፓልት ላይ አደጋ አደርሳለሁ ብሎ ባይፈራም ይቺኛዋ የስፖርት መኪና ግን መሀል አስፓልቱን ለቅቃ፣ አንዴ ወደ ግራ አንዴ ደግሞ ወደ ቀኝ እየተወላገደች ከፍ ብሎ ከተሰራው የእግረኞች መንገድ ጋር ትላተም ጀመር። በመጨረሻም በዚያው ፍጥነቷ ስትከንፍ ሄዳ ከቴሌግራሙ እንጨት ጋር ተላተመችና በጀርባዋ ተፈነገለች።

«ጆርጅ ነው» አሉ ሁለቱም በአንድ ድምፅ። አዎ በትክክል ጆርጅ ነው። ወጣቱ ጆርጅ የአንድ የንግድ መርከብ ሰራተኛ ነው። ዛሬ ጠዋት በቢሮው በኩል ሳልፍ ሰላምታ ተለዋውጠን፣ ተዋውቀን አብረን ሻይ ጠጥተናል። ጠዋት አብረን ሻይ ስንጠጣ ከፊቱ ትልቅ አላማ ያለው ሰው መሆኑና ተስፋዎቹ ሁሉ ጎልተው ይታዩ ነበር፤ በጣም በሚያማምሩ ቃላት በሰሜን ፈረንሳይ ስላለችው ውድ ፍቅረኛው ማለት እጮኛው ውበትና ታማኝነት ብቻ ሳይሆን ከጂቡቲ ወደ ሰሜን ፈረንሳይ ሲመለስ እዚህ ባጠራቀመው ገንዘብ ምን ምን መስራት እንዳቀደ ሁሉ በሰፊው ተርኮልኛል።

እነሆ አሁን ከገለበጣት መኪና ውስጥ በራሱ ደም ተነክሮ እንደሰከረ ሰው እየተወላገደ ወጣ። የተወሰኑ ሰዎች ይህንን በደም የተነከረ ወጣት ለመርዳት እየሮጡ ቢሄዱ፣ ወጣቱ ጆርጅ ፍፁም ቁጡ ሆኖ በኃይለኛ ቃል ጮክ ብሎ «Allez-vous-en! Allez-vous-en!» እያለ ከአጠገቡ እንዲርቁ «ዞር በሉ!» እያለ በደም የተነከሩ እጆቹን

ሲሮጡና ጭፍ እነዚያን ነጫጭ የአረቦች ቤቶች በደመ ፍንጣቂ የቀይ ቡሬ አስመሰላቸው።

«ተያላችሁ፤ አሁንም አንዱ አበደ!» አለ አላፍ ሄንድሪክ ጮክ ብሎ። ቀጠለናም «ምስኪን ጆርጅ! አሷም ተራዋ ደርሶ አበደች? አዎ፤ የጆርጅ ሎተሪ ዛሬ ወጣ» አለ አላፍ ሄንድሪክ። አሁን ግን ከልቡ እጅግ በጣም አዝንና ትክዝ ብሎ ቆየና በመቀጠል «ሰሞኑን ሁኔታው ሁሉ አላምር ስላለኝ ሳጠናው ነበር። የሀገር፣ የፍቅረኛው ፍቅርና ናፍቆት ከሚችለውና ከሚሸከመው በላይ ሆኖበት ነበር። በተደጋጋሚ ወደ ፈረንሳይ ሀገር ለአጭር ጊዜ እረፍት እንኳ እንዲለቁት ቢጠይቅም ሳይፈቅዱለት ቀሩ። አሁን ግን እረፍቷን ያገኛል። እስከመጨረሻው» አለና አይኑን ከጆርጅ ላይ ሳይነቅል እጁን ብቻ ወደ ብርጭቆው ዘርግቶ የቀረቺውን አልኮል በአንድ ትንፋሽ ጨለጣትና በመቀጠል፣ «አየህ ጌታው፣ ተመሳሳይ እድል ሁላችንንም ይጠብቀናል። አንዳንዱን ገና ከመድረሱ ይይዘዋል፤ ሌሎችን ደግሞ ቀስ እያለ በደማቸው ገብቶ አንድ ቀን በድንገት ይነሳና ያሳብዳቸዋል። አየህ ጌታው፣ እብደት ሲነካካቸው እንዲሁ ዝም ብለው በአንድ ቦታ ተቀምጠው በባዶ አየር ላይ ለረጅም ሰዓታት ሲያፈጡ ይውላሉ፤ ማሰብ ያቆማሉ። አዎ ጌታው፣ እብደት ሲጀምር እንዲህ ነው።» «ምስኪን ጆርጅ! በመጨረሻ የፈራው ነገር ደረሰበት። የጂቡቲ በረሃ ለነጆርጅና ለኡ መሰል ወጣቶች አይሆንም።»

አላፍ ሄንድሪክ ለተወሰነ ጊዜ በትካዜ ዝም ብሎ ቆይቶ ድንገት የሚያስበረግግ ቀዝቃዛ ሳቅ መሳቅ ጀመረ። «በዚች ጅቡቲ በምትባል ምድር ላይ መሞት አልፈልግም፤ እዚህ የረባም የቀብር ቦታ እንኳ የላቸውም። እንደምንም የሚቆፈር የቀብር ጉድጓድ በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ በውሃ ይሞላል። ከጥቂት ቀናት በፊት አንድ የጥንት ጓደኛዬ ድንገት ሞተና ሬሳውን ለመቅበር ጉድጓድ ቆፍረን ሬሳውን ልናመጣ ለጥቂት ደቂቃዎች ሄደን ብንመለስ ያ የቆፈርነው ጉድጓድ ውሃ ሞልቶ አገኘነው። ምን ይደረግ፣ ውሃ በሞላው ጉድጓድ ውስጥ ቀበርነው። ታድያ ይኼ የቀይ ባህር ውሃ ውስጥ ውስጡን ሰርስሮ ሬሳውን ይወስድና ለባህር አውሬዎች ያቀብላቸዋል» እያለ ያንን ቀዝቃዛና አስፈሪ ሳቁን መሳቅ ቀጠለ።

በዚህ መሀል በርከት ያሉ ፈረንጆች ተረባርበው ወጣቱንና ትኩሱን እብድ ጆርጅን፣ በግድ ይዘው ቁስሉን ካከሙለት በኋላ ለጥቂት ጊዜ ጋደም እንዲል ቢመክሩትም ምክራቸውን ሳይሰማ ተነስቶ ምንም ትርጉም የማይሰጡ ቃላትን እየተናገረ ሄደ።

«ቦይ!» ሲል አላፍ የሱማሊውን አስተናጋጅ ጠራው። ባዶ እግሩ ሱማሌ ነጭና ረዘም ያለ ቀሚስ መሳይ ነገር ለብሶ በአንገቱ ላይ ነጭ አንገት ልብስ አጣፍቷል። ይኼ የሱማሌ ልጅ ባዶዋን የቀረችውን የአላፍን ብርጭቆ አንስቶ፣ በሄደበት ፍጥነት ተመልሶ ብርጭቆዋን ሞልቶ ለአላፍ በጠረጴዛዋ ላይ አስቀመጠለት። ይኼ የሱማሌ

ልቶ አሳፍና መለኪያዎቹ ምን እንደሚፈልጉ ጠንቅቆ ስለሚያውቅ «ምን ልታዘዝ?» ብሎ እንኳን ቆሞ አላለም::

አዲስ መጤ ፈረንጆች ስለ ጅቡቲ የወደብ ከተማ የሚያውቁት ምንም ነገር የለም:: የሚያውቁት ነገር ቢኖር ከፍተኛ ደሞዝ እንደሚከፈላቸው ብቻ ነው:: ይቺ ከፍተኛ ደሞዝ እንደነሱ ዓይነት ወጣትና ልምድ የሌላቸውን ወጣቶች እያጓጓች፣ ከሞቀ ቤተሰባቸው ጉያ እያስወጣች በዚች የምድር ላይ ገሃነም ትወረውራቸዋለች:: እነዚህ ልምድ የሌላቸው ወጣት ፈረንጆች ለንዘብበት ሲሉ የሚከፈላቸው ይኼ ከፍተኛ ደሞዝ፣ ምንም እንኳን የአልኮሆል መጠጦች ዋጋ በጣም ርካሽ ቢሆንም፣ ፍጹም እንደማይበቃቸው ይረዳሉ::

«ምን ቢሉ ጌታው መልሱ በጣም ቀላል ነው:: አዎ! እውነት ነው፤ በጣም ሲበዛ እንጠጣለን:: አዎ ጌታው! ራሳችንን ለመርሳት እንጠጣለን፤ ብቸኝነታችንን ለመርሳት እንጠጣለን፤ ናፍቆታችንን ላለመናፈቅ እንጠጣለን፤ አዎ ጌታው ህይወታችንን በዛ ፈቀዳችን ማበላሸታችንን ለመርሳት እንጠጣለን:: እናም ጌታው ያቺ ያንንችን ከፍተኛ ደሞዝ ለዚች ለርካሿ መጠጥ እንኳን አትበቃንም::»

እንዲህ አፋፍ ሲናዘዝ ሰማሌው አሳላፊ ሌላ አዲስ ሙሉ ብርጭቆ አልኮሆል ስላመጣለት ብርጭቆውን አንስቶ ግማሽ ያህሉን ከተንነጨ በኋላ «አዎ ጌታው፣ የኛ የከንቱዎቹ ህይወት ይኼን ይመስላል:: ዛሬም እንጠጣለን፤ ነገም እንጠጣለን፤ አንድ ቀን ይኼ የበረሃ በሽታ አናታችን ላይ ወጥቶ ወባ ወልዶ ሲረታን፣ በሁለትና በሶስት ቀን ውስጥ ሲደፋን፣ ጠሪያ ውሃ በሞላው ጉድጓድ ውስጥ ይቀብሩናል::»

ምንም እንኳን ጀንበር ከጠለቀች የቆየች ቢሆንም ያ የታፈነ አድካሚ ሙቀት እንዳለ ነው:: እውነቱን ለመናገር ከልብሳችን ላይ የራሳችንን ላብ መጭመቅ እንችላለን:: አፋፍ አሁን ከኛ ጋር ማውጋቱን አቁሞ አንገቱን እንደደፋ ከብርጭቆው ጋር መጫወት ጀምሯል::

«ተነስ እንሂድ!» ሲል ጋባዤ የሀገሬ ልጅ ጎሰም አደረገኝ::

«ወዴት ነው የምንሄደው?» ስል ግራ ቢገባኝ ጠየኩት::

«የትም፣ ብቻ ዝም ብለን በመኪና እንዞራለን:: ሁሉም በጂቡቲ ያሉ ፈረንጆች ሁልቀን የሚያደርጉት ጉዳይ ነው» አለኝና ቀጥሎ «ቀስ እያልን እየነዳን ይኼንን የምሽቱን ደካማ ነፋስ ለመጠቀም እንሞክራለን» አለኝ::

ከዚያ አፋፍን ከነመለኪያውና ድብርቱ እዚያው ጥለነው እኛ በዚያች ሚጢጢ መኪናው ተሳፍረን ከመኪናዎች ሰልፍ ውስጥ ገብተን ማዝገም ጀመርን:: ምንም እንኳን ነፋስ የሚባል ነገር ባይኖርም፣ ያንን ከባድና አድካሚ የታፈነ አየር እየሰነጠቅን ስንሄድ፣ በመጠኑም ቢሆን ቀዝቀዝ ያለ አየር ማግኘት ጀመርን::

እውነትም አንድ ቦታ ተገልቶ በላብ ከመዘፈቅ የተሻለ ነበር:: እንዲህ በጂቡቲ የወደብ ከተማ ሸለቆዎች እየተሽሎከለክን ስንዝገ ቆይተን ከከተማዋ ወጣ ብለን ካንድ ባለ አንድ ፎቅ ቡና ቤት ፊት ለፊት መኪናችንን አቁመን ወደ ቡና ቤቷ ገባን::

ሁሉም የአዳራሹ መስኮቶችና በሮች ወለል ብለው ተከፍተዋል:: ቢከፈቱም በአዳራሹ ውስጥ ያለው አየር ግን በሲጃራ ጭስና በአልኮሆል መጠጥ ትንፋሽ የተበከለ ነበር:: በዚያ አዳራሽ ውስጥ ላሉ ሰዎች ግን ይኼን ያህል የከበዳቸው አይመስልም::

ከበሩ ፊት ለፊት ባለው ረጅም ጠረጴዛ ዙሪያ በአሉት በአግዳሚ ወንበሮች ላይ በርካታ መርከበኞች ተደርድረው ተቀምጠዋል:: ዛሬ ማለዳ በጂቡቲ ወደብ ካረፈችው የፈረንሳይ የጦር መርከብ ውስጥ የወጡ መርከበኞች ናቸው:: እነዚህ የፈረንሳይ የጦር መርከብ መርከበኞች በመጠጥ ኃይል እየተገፉ ይጫወታሉ፤ ይዘፍናሉ፤ ይደንሳሉ፤ ብቻ እንዲሁ ላያቸው ሰው ደስተኞች ይመስላሉ::

ግራማፎኑ የሚያሰማው ሙዚቃ ከነዚህ የጦር መርከብ መርከበኞች ጩኸት ጋር ተቀላቅሎ ቤቷን ቅዳሜ ገበያ አስመስሏታል:: እነዚህ መርከበኞች በግራማፎኑ የዳንስ ሙዚቃ እየታጀቡ ጥንድ ጥንድ እየሆኑ ይደንሳሉ፣ ጢማም ጨበሬ ወታደር ከጢማም ጨበሬ ወታደር ጋር ወንድ ለወንድ ተያይዘው ዳንሱን ያስነኩታል::

በዚህ መልኩ በሀገሬ ልጅ ጋባዥነትና መሪነት ጥንድ ጥንድ ሆነው ደስታቸውን ከሚቀጩ የፈረንሳይ የጦር መርከበኞች በሚዝናኑባት በዚች የግሪካዊው ቡና ቤት ቁጭ አልኩ:: አዎ በጂቡቲ የሚኖሩ ፈረንጆች እነዚህን መርከበኞች እንደሚጠሯቸው የ«መርከበኛ ባልና ሚስቶች»ን የዳንስ ትርኢት ለማየት በቃሁ::

በጅቡቲ የሚኖሩ የቅኝ ግዛት ሰራተኞች በአብዛኛው ወንደ ላጤዎች ናቸው:: ወደ ጅቡቲ ከመምጣታቸው በፊት ባለትዳሮች ቢኖሩም፣ በጅቡቲ በረሃ ደንዝዘው፣ ትዳራቸው ፈርሶ፣ ወንደላጤነትን አሜን ብለው የተቀበሉም ጥቂቶች አይደሉም:: ለዚያም መሰለኝ የፈረንሳይ የቅኝ ግዛት ገገርዎች በጅቡቲ ከተማ ዳርቻ ላይ ይቺን ባለ አንድ ፎቅ ቡና ቤት «የፍቅር ቤት» ያቆሙት:: በዚች «የፍቅር ቤት» ሁለት ወጣት ፈረንሳውያን ሴተኛ አዳሪዎች ይኖራሉ:: አሁን ከፎቁ በደረጃዎች ላይ አንዲት ቀጭን ፈረንጅ ልጅ ከሃር የተሰራ ነጭ የውስጥ ልብስ ብቻ ለብሳ ወደአዳራሹ መውረድ ጀመረች:: ልጂቷ የተኳኳለችው ፊቷ ወደዚች የተረገመች ምድረ በዳ ከመምጣቷ በፊት ቆንጆዬ ልጅ እንደነበረች ይመሰክራል:: አዎ የጂቡቲ በረሃ አጥንቷ እስኪቀር ድረስ አመንምኗታል::

«ወደዚህ ስትመጣ ጤነኛና ጠንካራ ነበረች» ሲል ከጎኔ የተቀመጠው የሀገሬ ልጅ በጆሮዬ ሹክ አለኝ:: ቀጠለናም «አሁን ከምታያት ሁለትና ሶስት እጥፍ ጠንካራ ልጅ ነበረች:: እዚህ ከመጣች ገና ወር እንኳን አልሞላትም፤ ይኼው እንደምታየው መንምና አጽም መስላለች:: አንድ ሁለት ወር ጠንክራ ከቻለች ወደሀገሯ መመለስ ትችላለች:: አለበለዚያ ያው ያቺ ውሃ የሞላት ጉድጓድ የዘላለም ቤቷ ትሆናለች»

አለች፡፡ ልጆቹ ፊደሎቹን እንዲያ ሳተምስ አንዱ መርከበኛ ወታደር ጓደኞቹን እየገፈተረ በኩል ፊደሎቹን በጥንቃቄ ከልጆቿ ጋር ተያይዘው ወደ ክፍሏ ሄዱ፡፡ ሌላው ጓደኛውም ተከትሎት ወደ እንፋሎት ብቻ እንኳን ያላለፈውን ሁለተኛዋን ቤት ፍለጋ ሄደ፡፡ ሌሎች በእንፋሎት ውስጥ ያሉት መርከበኞች ጓደኞቻቸው ቁርስ ጨርሰው እስኪመለሱ ድረስ በትዕግስት ይጠብቃሉ፡፡

እያንዳንዱ መርከበኛ 15 ደቂቃ የተወሰነ የቁርስ ሰዓት አለው፡፡ አስራ አምስቱ ደቂቃ ዋጋው 30 የፈረንሳይ ፍራንክ ሲሆን፣ ከአስራ አምስቱ ደቂቃ በተጨማሪ ለአንድም ይሁን ለሁለት ደቂቃ በቁርስ ጨዋታው ቢቀጥል ሌላ ተጨማሪ 30 የፈረንሳይ ፍራንክ ይከፍላል፡፡ ጠረጴዛ የቁርስ ቤት ልክ በፖስታ ቤት ቴሌግራም እንደሚልክ ሰው ደቂቃዎቹ በትክክል ይቆጠራሉ፡፡

በጣም ከመሸ በኋላ ወደ ሆቴል ተመለስኩ፡፡ በመኝታ ቤቱ ከባድ ሙቀት ስለነበረ ተንቀሳቃሽ አልጋዬን ይዤ ወደ በረንዳዋ ወጣሁ፡፡ እውነት ለመናገር ምንተፍረቴን ከመሸፈኛ የውስጥ ሱሪ በስተቀር እርቃኔን ነኝ፡፡ እንዲህም ሆኖ ፈጽሞ መተኛት አልቻልኩም፡፡ በጣም በጣም ሲበዛ ይወብቃል፡፡ በዚያች የሆቴሏ በረንዳ ላይ በተደጋጋሚ ከአንዷ ጥግ ወደ ሌላዋ ጥግ ቦታ እየቀያየርኩ ለመተኛት ሞከርኩ፣ በራሴ ላይ ከመታጠብ በስተቀር ምንም ፋይዳ ሳላገኝ፣ አይኔ ሳትከደን፣ እንቅልፍ ርቆኝ እንዳይነጋ የለም ነጋ፡፡



2

ድሬዳዋ
የብረቱ አውራሪስ

በአንድ የፀደይ ማለዳ 1814 ዓ.ም. ሽማግሌው ስቴፈንሰን ለአመታት አምጦ አምጦ የወለደው የፈጠራ ልጁ የመጀመሪያውን አዝጋሚ ጉዞ መጀመር ሲያይ በፊቱ ላይ ታላቅ ደስታና የወደፊት ተስፋ ይነበብበት ነበር፡፡ ምናልባትም በዚያች ማለዳ ዓለምን ወደ አንድ ሌላ ከፍ ወዳለ ስልጣኔ የሚወስድ ትልቅ ነገር ለዓለም ህዝብ መፍጠሩንና ማበርከቱን የተገነዘበው እሱ ብቻ ነበር፡፡

ሌሎችማ በዚያች ማለዳ የሽማግሌውን ስቴፈንሰንን ግኝት ወይም ፈጠራ ለማየት የተሰበሰቡት በርካታ ወሬ አዳማቂ ሰዎች የፈጠራ ስራውን የመጀመሪያ አዝጋሚ ጉዞ ሲያዩ ሳቁበት፣ ቀለዱበት፣ አላገጡበት፡፡ እነዚህ ሰዎች ከብዙ አመታት በኋላ ነበር ሽማግሌው ስቴፈንሰን እውነት እንደነበረውና እነሱ ግን ተሳስተው እንደነበረ አምነው የተናገሩት፡፡

አዎ የባቡር መንገድና ባቡር ባይኖሩ ኖሮ ዛሬ የመላው አለም ህዝብ ይኼን ያህል ባልተቀራረበና ባልተዋወቀ ነበር፣ ባቡር ባይኖር ኖሮ ዛሬ ከደረስንበት የስልጣኔ ደረጃ ላይ ባልደረስን ነበር፣ ባቡር ባይኖር ኖሮ በሌላው በሞቃቱ የዓለም ክፍል የሚበቅሉትን ፍራፍሬዎችን እንኳን ሳይቀር ለመብላት ባልቻልን ነበር፣ ባቡር ባይኖር ኖሮ በመላው ዓለም የሚኖሩትን ህዝቦች ባህል፣ ሃይማኖትና አኗኗር ባላወቅን ነበር፡፡

እዎ እነዚህ ሁለት እድሜ ልካቸውን እንዳይነጣጠሉ ሆነው ጎን ለጎን የተዘረጉ ሁለት ጠፍጣፋ ብረቶች የዓለምን ህዝብ አገናኝተውታል ብሎ በድፍረት መናገር ይቻላል።

ከጂቡቲ እስከ ድሬዳዋ ድረስ ባለው ክልል ውስጥ የሚኖሩ ህዝቦች "ፈረስ አል ሼይጣን" በብረት ላይ የሚሄድ የሰይጣን ፈረስ ይሉታል። ለእነዚህ ሰዎች ባቡር እንደማንኛውም የቤት እንስሳ ማለትም አህያ፣ ፈረስ፣ ግመልና በቅሎ ሁሉ ፍጡር ነው። በሳርና በቅጠል ፈንታ ከሰል በልቶ ውሃ ጠጥቶ እንፋሎት የሚተፋ፣ በሁለት ብረቶች ላይ የሚጋልብ፣ መንፈስ ያለው ፍጡር፣ የሰይጣን ፈረስ ነው።

በእኔ ግምት የነዚህ ባላገሮች አስተሳሰብ ከእውነት የራቀ አይደለም፤ ባቡር እስካሁን የሰው ልጅ ከፈጠራቸው ግኝቶች ሁሉ ልዩና ተወዳዳሪ የሌለው፣ የነገሮች ሁሉ ንጉሥ ሆኖ ቀዳሚውን ቦታ ይዞ ይገኛል። ለዛም መሰለኝ እያንዳንዱ ባቡር የራሱ የሆነ ልዩ ስምና ቁጥር ያለው። ለምሳሌ፣ የኢትዮጵያና የፈረንሳይ የባቡር መንገድ ድርጅት ንብረት የሆኑት ባቡሮች እያንዳንዳቸው የራሳቸው የሆነ ልዩ ስም አላቸው።

ኤሊ ምንም እንኳን ከረጅም ዓመታት አገልግሎት በኋላ በጡረታ የተገለለች ቢሆንም አሁንም አልፎ አልፎ በባቡር ጣቢያ ከዝሆን ጋር በመተባበር ፉርጎ በመግፋት ትረዳለች። ግመል ትናንትና በርካታ ሙሉ ጭነት የተጫኑ ፉርጎዎችን እየጎተተ ከአዲስ አበባ ወደ ጂቡቲ ሲወርድ አይተነዋል።

የኛ ባቡር ማለት እኛን አሳፍሮ ከጂቡቲ ተነስቶ እስከ አዲስ አበባ ድረስ ከ800 ኪሎ ሜትር ርቀት በላይና ከባህር ወለል ወደ 2,500 ሜትር በላይ አሻቅቦ መውጣት ያለበት ባቡራችን የተከበረ ኩሩ ስም አለው "አውራሪስ"። አውራሪስ፣ በርካታ ፉርጎዎች ሲኖሩት ከመጀመሪያዎቹ ሁለቱ ፉርጎዎች በስተቀር የቀሩት የሀገሬውን ሰዎች (በሱማሌዎች፣ ኢሳዎች፣ አፋሮች) እና ቋጠሮዎቻቸው የተሞሉ ናቸው።

የመጀመሪያውና ሁለተኛው ፉርጎ አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ መሆናቸው ሲሆን አንደኛ ደረጃው ከሁለተኛ ደረጃው የሚለይበት ብቸኛ ነገር ቢኖር ዋጋው መወደዱ ብቻ ነው። ለዛም መሰለኝ በርካታ ባዶ ቦታዎች ያሉት።

በኛ ፉርጎ ውስጥ አንድ ወፍራምና በርጫም ፈረንጅ ነጭ ሸሚዝ እና ዳልቻ ቁምጣ ለብሶ የቡሽ ባርኔጣውን እንደደፋ ተደላድሎ ተቀምጧል። ሰላምታ ሰጠሁት። "ካል ኢሚራ" አለኝ ላቀረብኩለት ሰላምታ ሲመልስልኝ። ይኼ የሶሉና ሰው ግማሽ እድሜውን ያህል ያሳለፈው በምስራቅ አፍሪካ ሲሆን ለበርካታ ዓመታትም በኢትዮጵያ ኖሯል።

"ሁሉም መንገዶች ወደ ሮማ ይወስዳሉ፤ ወደ ኢትዮጵያ የሚወስደው መንገድ ግን አንድ ብቻ ነው። ያቺም መንገድ ይቺ የባቡር ሃዲድ ብቻ ነች" እያለ ኘ ከመቀመጤ ጨዋታ ጀመረ።

"ከእርግጥ በግመልም፣ በፈረስም፣ ከከፋም በእግርም ወደ ኢትዮጵያ ዘልቆ መግባት ይቻላል። ችግሩ ግን ዋጋው ከመወደዱ በላይ ይኼ የሶስቱ ቀን የባቡር መንገድ ከሳምንት በላይ ከመውሰዱም በላይ መንገዱ በአደጋ የተሞላ መሆኑ ነው። እናም ጌታው ብቸኛውና አስተማማኙ መንገድ ይኼ የባቡር መንገድ ብቻ ነው። ይገባዎታል ጌቶች ምን ማለቴ እንደሆነ?" ብሎ ጠይቆ መልሴን እንኳን ሳይጠብቅ በመቀጠል፣ "ከኢትዮጵያ የሆነች ነገር ወደ ውጪ ለማስወጣት ቢፈልጉ መጠቀም ያለብዎት ይቺኑ ብቸኛዋን የባቡር ትራንስፖርት ብቻ ነው። የባቡር መንገዱ ድርጅት በጥቂት የአክሲዮን ባለቤቶች እጅ ወድቋል። ጌቶቹ የአክሲዮን ባለቤቶች አንዲት ድንጋይ ሳይፈነቅሉ ዋጋውን እንደፈለጋቸው ከጣሪያ በላይ እያወጡ በማይሞላው የገንዘብ ከረጢታቸው ውስጥ ስንት ለፍተንና ጥረን ያመጣነውን ገንዘብ ያለ አንዳች ይሉኝታ ያጭቃሉ።"

"ይኼንን ጌቶቹ ባለ አክሲዮኖች የጫኑትን ከፍተኛ ዋጋ አልከፍልም ቢሉ፣ ከኢትዮጵያም ይሁን ወደ ኢትዮጵያ አንዲት ቁራጭ ነገር ማስወጣትም ይሁን ማስገባት አይችሉም። እናም ጌታው በዚህ መልኩ ፈጽሞ መነገድ የማይቻልበት ጊዜ ላይ ደርሰናል። ሌላ ስራ ደግሞ ፈረንጅ በኢትዮጵያ ፈጽሞ ማግኘት አይችልም። እዎ ጌታው የባቡሩ መንገድ ድርጅት በመንግሥት እጅ ገብቶ መንግሥት ተመጣጣኝ ዋጋ ወስኖ ቢቆርጥልን ምናኛ በስራችን ተግተን በተገኘን ነበር። በዚህ መልኩ ከቀጠለ ግን መክሰራችን ሳይታለም የተፈታ ነው" እያለ ብሶቱን አንጎደጎደልኝ፤ አነባልኝ።

ይኼው ቀኑን ሙሉ በፈረንሳይ ሱማሌ አሸዋማ ምድር ላይ እየተጓዝን ነው። ባዶ መሬት ነው። ምንም አይነት የውሃም ይሁን የእጽዋት ዘርያ አይታይም። በጣም ይሞቃል። ብቻ እንዲሁ ሳስበው አግዜሩ የረሳት መሬት ሳትሆን አትቀርም። እንደ ገሃነም እሳት እየነደደች የሰው ልጆችን አንድዶ አንድዶ የሚፈጅ የሚመስል ሙቀት ትተፋለች።

እንዲህም ሆኖ የሰው ልጆች ይኖሩበታል። በዚህ እንደ ገሃነም እሳት በሚፋጅ የበረሃ መሬት ላይ ሶማሌዎች፣ ዳንከላዎች፣ ኢሳዎች፣ አሳይታዎች እና ሌሎችም በርካታ ጎሳዎች ተበትነው ይኖሩበታል።

አልፎ አልፎ በባቡሩ መስኮት አሻግሮ ላየ ሰው አነስ አነስ ያሉ በቡድን በቡድን የተከፋፈሉ ሰዎች ሰብሰብ ብለው ጦራቸውን እንደያዙ ወደ ቀመው ያወራሉ፤ አልያም በዝግታ የሚያዘግሙ ጎሳዎችን ማየት ይቻላል። እኔም በጉዞዬ ላይ እነህን መሰል ጎሳዎች በተደጋጋሚ አይቻለሁ።

ይኼ የባቡር መንገድ ከጂቡቲ እስከ አዲስ አበባ ድረስ በሚዘረጋበት ጊዜ እነዚህ የአካባቢው ነዋሪዎች እጅጉን በጣም የሚፈሩ ጠላቶች የነበሩበት ጊዜ ሩቅ አይደለም። አንድ አሁን ስሙን የረሳሁት ሰው በወቅቱ በጻፈው ማስታወሻ "እያንዳንዷ የምንዘረጋት ሃዲድ አንድ የሀገሬውን ተወላጅ ህይወት ስትጠይቅ፤ እያንዳንዷ አንድ ኪሎ ሜትር የተዘረጋች የባቡር ሃዲድ ደግሞ አንድ የፈረንጅ ህይወት መስዋትነት ተከፍሎባታል" በማለት ከትቧል።

ምናልባት ይኼ ሰው አጋኖ ዕሮት ሊሆን ይችላል። ቢሆንም ይኼ የባቡር ሃዲድ (መንገድ) በሚዘረጋበት ጊዜ በበረሃ በሽታ በርካታ ሰው እንዳለቀና እነዚህ የአካባቢው ነዋሪዎችም ብዙ ሰው እንደገደሉ ግን ጥርጥር የለውም።

ዛሬም ቢሆን የባቡር መንገድ እስከዚህ ከአደጋዎች ሙሉ በሙሉ ነፃ ነው ማለት ፈፅሞ አይቻልም። የባቡር ጣቢያዎች በጣም ተራርቀው ከመሰራታቸውም በላይ የባቡሩ መንገድ ፈፅሞ አይጠበቅም። እዎ ሶማሌዎች የባቡሩን ሃዲድ ነቃቅለው ባቡሩን በግድ በማስቆም ተሳፋሪውን እየገደሉ ንብረቱን የዘረፉበት ጊዜ የሩቅ ጊዜ ትዝታ አይደለም።

አሁን አሁን ባቡር ለመዝረፍ ብዙም አይዳፈሩም። ይሁን እንጂ ሃዲዱን እየነቀሉ በመውሰድ ተጓዡን አደጋ ላይ መጣላቸው ግን አልቀረም። እንዲህ አንድ ሁለቱን የሃዲድ ብረት ነቅለው በመውሰድ በጎሳው ብረት አንጣሪ መሃንዲስነት ከሳምንታት አስቸጋሪ የብረት ቆረጣና ቅጥቀጣ በኋላ እነዚህ ጎሳዎች በመቶዎች የሚቆጠሩ አዳዲስ ጦሮች ባለንብረቶች ይሆናሉ። በነዚህ አዲስ ነጥረው በተሰሩ ጦሮች አጊጠው በሌሎች ጎሳዎች ላይ የኃይል የበላይነታቸውን ለማሳየትና ለማሳመን ሲጥሩም ይታያሉ። ለዚህም መሰለኝ ባቡሮች በቀን ብቻ የሚጓዙት። ሌሊቱን ካሉት የባቡር ጣቢያዎች በአንዱ ያሳልፋሉ። እናም ከጂቡቲ አዲስ አበባ የባቡር መንገድ ሦስት ቀን ይፈጃል።

በዚህ መልኩ እየተጓዝን ከሰዓት በኋላ በደወሌ የባቡር ጣቢያ ለእረፍት ቆምን። ደወሌ የመጀመሪያዋ በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ያለች የባቡር ጣቢያ ነች። በደወሌ የባቡር ጣቢያ ያ የፈረንሳይ ባቡር ጣቢያን የደንብ ልብስ ለብሶ የነበረው ሰው እጅጉን በጣም በሚያስደንቅ ፍጥነትና ቅልጥፍና ልብሶቹን ቀይሮ ኢትዮጵያዊ ሆኖ "Vous passeports, Messieurs" እያለ እጅግ በሚገርምና በሚጥም ፈረንሳይኛ ፓስፖርታችንን ጠይቆ ከተቀበለ በኋላ በጂቡቲ የኢትዮጵያ ቆንስል የፈረመበትን ቪዛ በጥንቃቄ አገላብጦ ከመረመረ በኋላ አመስግኖ መለሰልን። በጣም ከመሸ በኋላ ድሬዳዋ ገባን። እንግዲህ የዛሬው አዳራችን በድሬዳዋ ስለሆነ ከባቡር ጣቢያው ወጥተን ሆቴል ፍለጋ ወደ ድሬ ዘልቀን ገባን።

ከአምስት ዓመት በፊት ድሬደዋ በነበርኩበት ጊዜ የተዋወቅሁት የሀገሬ ልጅ አቶ ሸሴክ፣ አሁን በድሬ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሰራተኛ፣ ከዚያች የግሪኩ ቆሻሻ ሆቴል አዳር ገላገለን።

ብቻዬን አይደለሁም፣ በግብፅ ፖርት ሳይድ የሚገኘው የፈረንሳይ ቆንስል ቢሮ በሄድኩ ወቅት በአጋጣሚ ከሀገሬ ልጅ ከቪሌም ብረየር ጋር ተዋወቅሁ። ቪሌም ብረየር ልክ እንደኔው እሱም ከፖርት ሳይድ በጂቡቲ በኩል አልፎ ወደ ኢትዮጵያ መግባት እንዲችል የይለፍ ፈቃድ ቪዛ ከፈረንሳዩ ቆንስል ይጠይቅ ነበር። ከቪሌም ብረየር ጋር ከፖርት ሳይድ እስከ ጅቡቲ ብሎም እስከ አዲስ አበባ ድረስ መንገዝ ብቻ ሳይሆን በተጓዤን ያየሁትን ፍዳ ሁሉ አብሮኝ የተካፈለ ሰው ነው።

ድሬደዋ በምሽት በጣም ትቀዘቅዛለች። የድሬን ነፋሻማና ቀዝቃዛ አየር እየሳብን በድሬ የመንገድ ላይ መብራቶች ብዙም ስለሌሉ ከጨለማው ጋር እየተጋፋን ለሽርሽር ወጣን። እንዲህ በድሬ ዋና አደባባይ ስንሽራሽር ቪሌም ብረየር ናዚዎች ወደ ስልጣን ከወጡባት ቀን ጀምሮ በጀርመን ሀገር ስላለው ሁኔታ ያጫውተን ጀመር። እዎ ናዚዎች ስልጣን ከመያዛቸው በፊት ቪሌም ብረየር በጀርመን ሀገር ጥሩ ስራ ነበረው። ናዚዎች ስልጣን ከያዙ በኋላ ግን የውጪ ሀገር ሰዎች በጀርመን ሀገር እንደልባቸው መንቀሳቀስም ሆነ መስራት አስቸጋሪ እየሆነ መጣ።

ቪሌም ብረየር የአዶልፍ ሂትለር አካሄድ ስላላማረው ስለ የወደፊት ህይወቱ እና እድሉ ሲያስብ፣ ሲያወጣና ሲያወርድ በአጋጣሚ በኢትዮጵያ የነገሰው አዲሱ ንጉሥ አውሮፓውያንን በሙያቸው እየተቀበለ ስራ ይሰጣል የሚል ወሬ በመስማቱ፣ እሱም እድሉን በኢትዮጵያ ለመሞከር ከግብፅ ፖርት ሳይድ ወደ ኢትዮጵያ መግቢያ ፈቃድ ሲጠይቅ እስከተገናኘንባት ቀን ድረስ ያለውን ታሪኩን አጫወተን።

እንዲህ ቪሌም ብረየር ስለ ጀርመንና ሂትለር እያጫወተንና የድሬን ነፋሻማ አየር እየሳብን ስንሽራሽር አንድ የሞተር ብስክሌት ከባድ መብራቱን አብርቶብን ካለፈ በኋላ የጉዞ መስመሩን በፍጥነት ቀይሮ ወደኛ እየበረረ፣

"የቶ ኦን" አለ ሞተረኛው በቼክ ቋንቋ።

"እሱ ነው" እንደ ማለት ነበር።

"የቶ ኦን" የሚለውን በሞተሩ ድምፅ መሀል ለይቼ ሰምቼ ዞር ስል የቼኮዝሎቫኪያ ተወላጅ ከሆኑት ከሁለቱ ወንድማማቾቹ የክሮብ ልጆች ጋር ግንባር ለግንባር ተገጣጠምን። ከነዚህ ወንድማማቾች ጋር ተቃቅፈን ተሳሳምን።

እዎ እነዚህ ወንድማማች የክሮብ ልጆች እነሆ በንግድ ሙያ ተሰማርተው በኢትዮጵያ ሲኖሩ ከአስር ዓመት በላይ ሆኗቸዋል። እናም እነሆ ከአምስት አመታት ቆይታ በኋላ እንደገና በድሬደዋ ስንገናኝ እንዳው ዝም ብሎ ተሳስሞና ሰላምታ ተለዋውጦ መለያየቱ ተገቢ አልነበረምና፣ ምሽቱን ከነዚህ ወንድማማቾች ጋር ለማሳለፍ ያቀረቡልንን ግብዣ ተቀብለን ወደ ሆቴል ቦሎላኮስ (Bololakos) በመሄድ

ዋናም የተገናኘንበትን ምሽት በሚገባ ምርጦቹ የፈረንሳይ ዘና እየተንከባከብን አዘጋጅተን፡፡

ወንድማማቾቹ "እዋቂዎቹ ትንሽ ጊዜ በድሬዳዋ አብሬችሁን ስንብት፤ ቢያንስ እስከሚቀጥለው ጥቅር ድረስ" እያሉ ይለምኑን ጀመር፡፡ ቀጥሎም ከወንድማማቾቹ እስከሚቀጥለው ጥቅር ድረስ እያሉ ይለምኑን ጀመር፡፡ ቀጥሎም ከወንድማማቾቹ ትንሹዬው ያርስላቭ ክሮብ "ነገ ከኛ ጋር አብረን አደን መውጣት እንችላለን" ሲል ለመነኝ፡፡ ይሄን ልመናውን እምቢ ማለት አልተቻለኝምና በድሬዳዋ ቢያንስ እስከሚቀጥለው ጥቅር መጨረሻ ድረስ ለመቆየት ወሰንኩ፡፡ ሁሉም ብረየርም ስለተስማማ የወንድማማቾችን ግብዣ ተቀብለን ቀጠሮ ይዘን ወደ ማደሪያችን ወደ ቫሴክ ቤት በእሳዳሪያችን ታጅበን ሄድን፡፡

እንግዲህ ቢያንስ ለሚቀጥሉት ሦስት ወይም አራት ቀናት በድሬ መሰንበታችን ነው ማለት ነው፡፡ ቢሆንም በነዚህ በድሬ በቆየሁባቸው ቀናት ምንጊዜም የማልረሳቸው በርካታ ትዝታዎችን ቋጥሬባቸዋለሁ፡፡

ሎም በትራንስ ጆርዳን፣ በኬራክ አገሬ ገበር ግብዣ በሶሪያ በረሃ የተካፈልኩበት ፀመኪና የሚዳቋ አደን ትዝታ እስከዛሬ ከልቤ አልወጣምና የወንድማማቾችን የአደን ግብዣ ሳላንገራግር ተቀበልኩ፡፡

ኀ ከመንጋቱ ሁለቱ ወንድማማቾች ሞተር ብስክሌታቸውን እያስጓሩ መጥተው የቫሴክን ትንሽ የድንጋይ ቤት በር ማንኳኳት ጀመሩ፡፡ ተኝተው ይሆናል በሚል የተሳሳተ ግምት ነው የቫሴክን በር ያንኳኩት፡፡ እንዳልኩት ወንድማማቾቹ ተሳስተው ነበር፡፡ ማለትም እኛ ገና ጴሮ ተነስተን ለባብሰን እየጠበቅናቸው ነበርና ጊዜ ሳናጠፋ ወንድማማቾችን ተከትለን አቶ ቫሴክን ተሰናብተን ለአደን ወጣን፡፡

ወንድማማቾቹ ለኛም አንድ አንድ ሹራብና አንድ አንድ የአደን ጠመንጃም ይዘውልን መጥተዋል፡፡ በአንድ ሞተር ብስክሌት አራት ሰው አሳፍረው እንዴት መሄድ እንደፈለጉ ሞተሯን እየዞርኩ ስፈላሰፍ ትንሹ ያሮስላቭ ክሮብ ገላገለኝ፡፡ ትልቅየው የሞተሯን መሪ እንደጨበጠ ከፊት ተቀምጧል፡፡ በሞተሯ ወገብ ግራና ቀኝ ጎን ለጎን እንድንቀመጥ ያሮስላቭ እየጋበዘን እሱ ጀርባውን ለኛ ሰጥቶ ከኋላ ተቀመጠ፡፡

በዚህ መልክ በአንድ ሞተር ብስክሌት ላይ አራት ሆነን ተቀምጠን ድሬን ወደኋላ ጥለን ወደ አደኑ ሜዳ ገሰገስን፡፡ ጥርጊያው የድሬ መንገድ ምቹ ነበር፡፡ ልክ ድሬዳዋን ለቀቀን እንደወጣን የጥርጊያውም መንገድ አድራሻው ስለጠፋ በአባጣ ጎባጣው መንገድ መላ ሰውነታችን እየተርገፈገፈ በፍጥነት ቀጠልን፡፡ እውነቱን ለመናገር ሞተሯ ልክ እንደ ደንበረ ፈረስ ትዘል ነበር ማለት ይቻላል፡፡

ግራ አድለ ቢሶች ነን አለን ያርስላቭ ክሮብ (ከወንድማማቾቹ ትንሹዬው) ከሁለት ሰዓት በላይ በደኑ ውስጥ ስንዞር ቆይተን አንድም የሚታይን የዱር እንስሳ ባለማየታችን ትንሽ ቅር ብሎት፡፡

እንዲህ የሚታደን አውሬ ፍለጋ ስንዞር ያርስላቭ ክሮብ ባለፉት ወራት በድሬዳዋና አካባቢዋ ስላሳለፈው የአደን ትዝታዎች እያነሳ ብዙ ብዙ አጫወተን፡፡ እዋ በኋላ ወደ መኖሪያ ቤታቸው ስንመለስ ያሳዩን የተለያዩ የዱር አራዊት ቆዳዎች እና ቀንዶች በድሬደዋና አካባቢዋ በርካታ የዱር አራዊት እንዳሉ ትልቅ ምስክር ነው፡፡ ድሬዳዋና አካባቢዋ ከተለያዩ የሜዳ ፍየል ዝርያዎች በተጨማሪ የዱር አሳማ፣ ቀበሮ፣ ተኩላ፣ ጅብና የዱር አውሬዎች ንጉሥ አንበሳ ሳይቀር ይሄንን ቆላማ ሀገር ደስ በሰፋው ይኖሩበታል፡፡

እንዲህ በጫካ ውስጥ ስንሽሎኮሎክ አንዲት ከፍ ያለች ሚዳቆ በመንገዳችን ገባች፡፡ ሚዳቆዋ እኛን ስታይ እየዘለለች ወደፊት ሜዳ ሜዳውን መርጥ ጀመረች፡፡ ትልቁ ክሮብ የሞተር ብስክሌቷን ፍጥነት በጣም ጨምሮ በሚዳቆዋና በኛ መካከል ያለው ርቀት በጣም አንሶ ሚዳቆዋ ኢላማችን ውስጥ ልትገባልን በምትችልበት ርቀት ላይ ሞተሯን አቆማት፡፡ እንግዶቻቸው ነንና ቅድሚያውን ለኛ ሰጡን፡፡ ሁለት ጥይቶች ተከታትለው ተተኮሱ፡፡ ሚዳቆዋ ግን አሁንም ትሮጣለች፡፡ ሶስተኛዋ ጥይት ከመሬጮ ያቺ ሚዳቆ ተንከባላ ወደቀች፡፡ እዎ እኛ ተኩሰን የሳትናትን ሚዳቆ ያሮስላቭ ክሮብ በአንድ ምት ጣላት፡፡ ኀበዝ አልሞ ተኳሽ ነው፡፡

የሚዳቆዋን አንገት ቆርጠው ለገና ሲወስዱ፣ ከሚዳቆዋ ስጋ ደግሞ ጥሩ ጥሩ ስጋ ያለውን እግሮቿን ብቻ ወስደን የቀረውን ለጅቦች ተውንላቸው፡፡ ከሌላ ተጨማሪ ሁለት ሰዓት በኋላ የምኒልክን ድክ ድክ አገኘናት፡፡

ይቺ ድክ ድክ፣ ትንሽዬ የሚዳቆ ወይም የሜዳ ፍየል ዘር፣ እንደ መርፌ በቀጠኑ እግሮቿ እየተፈናጠረች ከአይናችን እይታ በጣም ርቃ እስክትሄድ ድረስ ሁላችንም ባለንበት ቆመን አየናት፡፡ ከሰዓት በኋላም በርካታ ድክድኮች አይተናል፡፡ ግን በጣም ድንጉጥ እንስሳ ስለሆነች በትንሽ ኮሽታ ፈርጥጣ ትጠፋለችና "እለሁ፣ እኔ ነኝ ለሚል አልሞ ተኳሽ እንኳ ኢላማ ውስጥ ከመግባቷ በፊት ሁሌም ወይ ቶሎ ትሰወራለች፤ አልያም በነዚያ መርፌ እግሮቿ ፈርጥጣ ርቃ ትሄዳለች፡፡

ትልቁ የክሮብ ልጅ ዶሚኒክ ክሮብ ሞተሯን አቁሞ በየት በኩል መሄድ እንዳለበት አካባቢውን ሲያጠና ከጀርባችን በጣም የተቆጣ አውሬ ድምጽ ሰማን፡፡ ከመቅጽበት ሁላችንም ድምጹን ወደሰማንበት አቅጣጫ ስንዞር አንድ በጣም ትልቅና ጥቁር አውሬ ከበርካታ ግልገሎቿ ጋር አየን፣ የዱር አሳማ ነበረች፡፡ ወዲያው ሁላችንም ተበታትነን ወደ ቁጥቋጦዎች ውስጥ ገባን፡፡ እሾኩ፣ ጋሬጣውና ደረቁ ጭራሮ ሳይቀር ልብሶቻችንን እየገነጣጠለ ደም በደም ቢያደርጉንም፣ በዱር አሳማ ከመገደል አይከፋምና ሁሉንም ችለን በቁጥቋጦዎች ውስጥ ስንሽሎኮሎክ

ከወንድማማቾቹ ትንሽዬው ያርስላቭ ክሮብ አከታትሎ ሁለቱ ሲተኩስ አሳማዋ የጣር ድምጿን ከፍ አድርጋ ማንጓራት ጀመረች።

«ተጠንቀቁ! ተጠንቀቁ! ከቁጥቋጦዎች ውስጥ ውጡ!» እያለ ያሮስላቭ ድምጹን ከፍ አድርጎ አስጠነቀቀን። የተመታችው የዱር አሳማ ገና አልሞተችም። «የቆሰለ የዱር አሳማ ከቤንጋል ነብር የከፋ ነው» አለን ትልቅየው እየሳቀ። ምናልባት ዶሚኒክ እውነቱን ሊሆን ይችላል። ግን እኛ እውነታውን ማረጋገጫ እድሉ አልነበረንም። ብቻ አልሞ ተኳሹ ያሮስላቭ አሳማዋን በአንድ ምት ጠቅልሎ ጥሏታል። ብቻ ከቁጥቋጦዎቹ ውስጥ ወጥተን ወደ ግዳዩ ብንሄድ፣ እስካሁን ትልቋ የዱር አሳማ ነች ብለን የገመትናት አውሬ ተራ ግልገል ሆና አገኘናት።

አዋሽ

የአዋሽ ወንዝ ከሸዋ ተራሮች ተነስቶ በርካታ ኪሎ ሜትሮች ወደሰሜን ምስራቅ ኢትዮጵያ ተጉዞ የተጠሙትን የደንከል በረሃዎች ውሃ ጥም እየቆረጠ ሄዶ በአውሳ በረሃ ዱካው ይጠፋል።

የአዋሽ ከተማ ምናልባት የተቆረቆረችው፣ ይኼ የፈረንሳይና የኢትዮጵያ መንግሥታት የጋራ ንብረት የሆነው ባቡር ሌሊቱን በአዋሽ ስለሚያሳልፍ ብቻ ሊሆን ይችላል። ምናልባትም የአዋሽ ከተማ አቆራቆር ታሪክ ሌላ ሊሆን ይችላል። ብቻ ዛሬ አዳራችን በአዋሽ ከተማ ነው።

አብዛኛው ተሳፋሪ አዳሩን በየፉርጎው ውስጥ አድርጓል። አዋሽ ከተማ ዘመዶች ወይም ወዳጆች ያሏቸው ደግሞ በየዘመዶቻቸውና በየወዳጆቻቸው ቤት አዳራቸውን ለማድረግ ጓዛቸውን ይዘው ሄደዋል። እኛ ፈረንጆቹና ጥቂት ባለሃብት ኢትዮጵያውያን ደግሞ አዳራችንን በአዋሽ ባሉ ሆቴሎች ለማድረግ ወደሆቴል ፍለጋችን ሄድን።

ከባቡር ጣቢያው ሃምሳ ሜትር ሳንርቅ አንዲት ሆቴል አገኘን። የዚች ሆቴል ባለቤት ማን እንደሆነ መገመቱ ከባድ አይደለም። ለብዙ ዓመታት በኢትዮጵያ የኖረ ግሪካዊ ነው። ኢትዮጵያውያን ሆቴል ከፍቶ አልጋ ማከራየትና እንጀራ በወጥ መሸጥን እንደነውር ይቆጥሩታልና አብዛኛዎቹ ሆቴሎች በግሪኮችና በአርመኖች እጅ ናቸው።

ይቺ ዛሬ ለአዳራችን የመረጥናት የግሪክ ሆቴል ትንሽዬ የምግብ አዳራሽ የምትመስል ነገር አላት። ግሪኩ የምግቧን አዳራሽ ሁለት ቦታ በሳጠራ ክፍሎ እንደነገሩ እንግዶቹን ለመቀበል ተዘጋጅቷል። ሆቴሏ ከዚች የምግብ አዳራሽ ተጨማሪ አንድ ሶስት የሚሆኑ የመኝታ ክፍሎችም አሏት። በመኝታ ክፍሏ ውስጥ አንዲት ተራና መናኛ አልጋ ተዘርግታ እንደነገሩ ተነጥፋ በወባ መከላከያ መረብ ተሸፍናለች። በቃ በዚች የመኝታ ክፍል ውስጥ ያለ ነገር ቢኖር ይኼ ብቻ ነው።

የምግብንና የመጠጥን ዋጋ በተመለከተ ረገድ ኢትዮጵያ በአለም ላይ ካሉ ሀገሮች ሁሉ በጣም ርካሽ ሀገር ነበረች። አሁንም ነች። ይሁን እንጂ ይቺ የዚህ ብልጣብልጥ ግሪክ የአዋሿ ሆቴል ያለ አቅሚ ዋጋዋን ወደድ አድርጋዋለች።

የአዋሹ ሆቴል አዳራችን አዳር አይበለው። በአንድ ቁንጫ አንድ ቤሳ የሚከፍል ቢገኝ በአንድ ሌሊት የሰማግለውን የሮክ ፌለርን ጠቅላላ ንብረት ገዘፎው ባደርጉ ነበር። ከሁሉ የሚገርመው ደግሞ የአዋሽ የቁንጫ ሰራዊትና የአዋሽ የወባ ትንኞች ጦር የጋራ ስምምነት የተፈራረሙ ይመስል፣ በወባ መከላከያ ከተሸፈነችው አልጋ ውስጥ ያንን ምስኪን የሆቴሏን ደንበኛ በሚሊዮን የሚቆጠሩ የቁንጫ ሰራዊቶች መድረሻ አሳጥተው ከመረቡ ሲያስወጡት በውላቸው መሰረት የወባ ትንኞች ይቀበሉና መከራውን ያሳዩታል።

በሶስተኛው ቀን የብረቱ አውራሪስ ባቡራችን የመጨረሻውን ጉዞ ከአዋሽ ተነስቶ አሻቅቦ ከ2,450 ሜትር ከባህር ጠለል በላይ እየወጣን መስመሩን ወደ አዲስ አበባ አቀና። አሁን ከቆላማው ቀበሌ ወደደጋው ስንወጣ አካባቢው ደረጃ በደረጃ ወደ አረንጓዴነት እየተለወጠ መጣ። በቁጥቋጦዎች፣ በግራሮችና በቁልቋሎች (Euphorbia Canadelabra) ፈንታ ቀጭኖቹና ረጃጅሞቹ የባህር ዛፎች አካባቢውን አድምቀውት ማየት ጀመርን። በዚህ የደጋው መሬት ላይም የደገኞቹ ጎጆዎች በባህር ዛፎች ተከበውና ደምቀው እዚህም እዚያም ፈንጠርጠር ብለው ቆመው ይታያሉ።

በአዋሽ የባቡር ጣቢያም የተሳፈሩት አዲሶቹ ተሳፋሪዎች በአመዛኙ ደገኞቹ አማራዎችና ኦሮሞዎች ናቸው። እነዚህን ደገኞች ከቆላው ሰው በነጩ ሸማቸው ብቻ ሳይሆን በመልክ ገጻቸው ለይቶ በትክክል ማወቅ ይቻላል። ቀላ ከማለታቸው በተጨማሪ መልከ መልካሞችም ናቸው። ምንም እንኳን ዋናው መለያቸው ነጩ ሸማቸው ቢሆንም በሁለመናቸው ከቆላው ህዝብ እንደሚለዩ ማንም ሰው ቢሆን ለይቶ ያውቃቸዋል።

አዎ እውነተኞቹ ጦረኞቹ «ሃበሾች» እነዚህ ናቸው። ለምን እንደሆነ ባላውቅም እነዚህ ሰዎች በምግብና በመጠጥ ሰዓት ራስ ቅላቸውን በሸማቸው ይሸፍናሉ። የአዋቂነት ፊታቸው ላይ ያ ጎፈሬያቸው ሲጨመርበት፣ ማንም ሰው ቢሆን እነዚህ ሰዎች እውነተኞቹ ጦረኞች «ሃበሾች» መሆናቸውን ሊክድ አይችልም። ወደፊት እንደምናየው ጦረኝነታቸውን፣ ጀግንነታቸውን በተንቤን የጦር አውድማ ሲያሳዩ በአይኔ በብረቱ አይቻለሁና አሁንም ስለነዚህ ሰዎች ማውራቱ ታሪክን መቅደም ይሆናልና በዚሁ ላቁም።

3
አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ከዛሬ ስድስት ዓመት በፊት ካየኋት ብዙም አልተለወጠችም:: ይሁን እንጅ እዚህም እዚያም የሚታዩት የለውጥ ሙከራዎች የውጤታማነት መንገድ እየያዙ መሆኑ ይታያል::

“አዲስ አበባ” ድንቅ ስም:: በ1889 ዓ.ም እምዬ ምኒልክ በባለቤታቸው በእቴጌ ጣይቱ ምኞት በአቃቂና በቀበና ወንዝ መካከል ተቆረቆረች::

መካከለኛው ከተማ ባለ አንድና ሁለት ፎቅ የድንጋይና የእንጨት የመኖሪያ ቤቶችና የግሪክ ነጋዴዎች ሱቆች እንዲሁም የሌሎች አውሮፓውያን መኖሪያ ቤቶች ተሰርተውበት ደመቅመቅ ብሏል:: ከነዚህ የቆርቆሮ ቤቶች ዙርያ ጥንታውያኑና ክቦቹ የኢትዮጵያውያንም ጎጆዎች በረጃጅሞቹ የባህር ዛፎች ተከበውና ተውጠው ቦታ ቦታቸውን ይዘዋል::

አዲሱ ንጉሥ ሬጀንት ራስ ተፈሪ (ልዑል ራስ ተፈሪ መኰንን ባለ ሙሉ ስልጣን እንደራሴ) በነበሩበትና አውሮፓን በሰፊው በጎበኙበት ወቅት ስልጣኔ የቱን ያህል ጠቃሚ እንደሆነ ጠንቅቀው ስላወቁ ለሀገራቸው እድገት ሌት ተቀን ሲጥሩ ይታያሉ::

ምንም እንኳን አውሮፓውያን ከመቶ ዓመት በላይ በፈጀባቸው ስልጣኔ ላይ በጥቂት ዓመታት መድረስ ባይቻልም ቢያንስ ጫፉን ለመያዝ ለሚጥሩት አዲሱ ንጉሥ ጠንካራው የኢትዮጵያ ባህል፣ ሃይማኖትና ልጆቿ ላዲሱ ስልጣኔ እንቅፋቶች እየሆኑ አዲሱ ንጉሥ ወደ ስልጣኔ እንደፈለጉት አገራቸውን ይዘው እንዳይሮጡ መሰናክሎች ሆኑባቸው::

አዲሱ ንጉሥ በ1930 ከነገሱበት ቀን ጀምሮ ዘላለማዊ እንቅልፍ የተኛች የምትመስለውን ውዷን ሀገራቸውን ከዚህ እንቅልፏ ለመቀስቀስና ወደፊት መራመድ እንድትችል የውጪ ዲፕሎማሲ ምን ያህል ከፍተኛ ሚና እንደሚጫወት ጠንቅቀው ያወቁት ንቁውና ብልሁ ንጉሥ፣ የዲፕሎማሲ ስራውን ከሁሉም ነገር በፊት አስቀድመው አጠናከሩት:: ይሁን እንጂ ኢትዮጵያ ከእንቅልፏ መነሳት በጀመረችበት በአሁኑ ሰዓት የጦርነት ዳመና በመላው ሰማይዋ ላይ ተዘረጋባት ::

አዲስ አበባ በርከት ያሉ ሰፋፊና ጥሩ ሆነው የተሰሩ የአስፓልት የመኪና መንገዶች አሏት:: በሁሉም መስቀለኛ መንገዶች ላይ የኢትዮጵያ ፖሊሶች ቆመው ባለ መኪናውንም፣ እግረኛውንም ስርአት ባለው መንገድ እንዲጓዝ ይረዳሉ::

እነዚህ ፖሊሶች የፖሊስ የደንብ ልብስ የለበሱና መለዮ የደፉ ቢሆኑም ለእግራቸው ግን ጫማ አልነበራቸውም:: ባዶ እግራቸውን አስፓልት ላይ ቆመው ስራቸውን በታላቅ ትግስትና ንቃት ያከናውናሉ:: እነዚህ ፖሊሶች ከአዲስ አበባው ከንቲባ በተሰጣቸው ጥብቅ ትዕዛዝ መሰረት መኪኖችም ሆኑ እግረኞች በቀኝ በኩል በትክክል መሄዳቸውን በጥብቅ ይከታተላሉ::

ይሁን እንጂ ለእግረኞች የተሰራው መንገድ ጠባብ ከመሆኑም በላይ ኮረኮንች ስለሚበዛው የአዲስ አበባ እግረኛ የኮረኮንቹን መንገድ ትቶ በለስላሳዋ አስፓልት ላይ ከመኪና ጋር እየተጋፋ ይኼዳል:: ይኼም ለነዚያ የከተማ ፖሊሶች ትልቅ አበሳ ነበር:: አንዳንዶቹ ፖሊሶች አስፓልት መሀል ገብቶ የሚሄደውን የሸገር አራዳ አቁመው በሰላምና በትግስት ሊያስረዱት ይሞክራሉ:: ትግስት የሌላቸው ፖሊሶች በመንገደኛው ላይ ጉማሬያቸውን ያስቀድማሉ:: የአዲስ አበባ ፖሊሶች አበሳ የሰው ልጅ ከሚችለው በላይ ሸክም የተሸከሙ አስመስሏቸዋል::

ባዶ እግሩ ፖሊስ ዛሬ ቢያንስ ከመቶ እግረኛ በላይ በቀኝ በኩል ባለው የእግረኛ መንገድ እንዲሄዱ ሲያስረዳ ውሏል:: አንድ እግረኛ የአስፓልቱን መሀል መንገድ ይዞ ሲሄድ ከኋላው የሚመጣ አውቶሞቢል ክላክስ ሲነፋበት ተደናግሮ የሚሄድበት ጠፍቶት እንደቆመ፣ ይኼው ፖሊስ ወደ ባላገሩ ጠጋ ብሎ “በንጉሥ ኃይለ ሥላሴ! በቀኝ በኩል ይሂዱ” ይለዋል::

ምስኪን ባላገር ለምን በቀኝ በኩል ብቻ መሄድ እንዳለበት ሊገባው አልቻለም:: ተወልዶ ባደገበት መንደሩ ከልጅነቱ ጀምሮ ባሻው መንገድ ሲሄድ ኖሯል:: ምናልባትም ቀኙ መንገድ እንኳን የትኛው እንደሆነም አልገባውም ይሆናል:: እና ይኼን የተረዳው ባዶ እግሩ ፖሊስ ባላገሩን ሰው እጁን ይዞ ወደ ቀኝ በኩል ይዞት ሄዶ በዚህ በኩል ለወደፊቱ እንዲሄድ ያስረዳውና ይለቀቀዋል:: ባላገሩ ፖሊሱ ባሳየው መንገድ ለራሱ ብቻውን እያወራ ወደፊት ሄደ:: ከጥቂት ጊዜ በኋላ በዚያችው መንገድ ተመልሶ መጣ::

"አንተ የውሻ ልጅ! በቀኝ በኩል ሂድ አላልኩህም?" አለ ባዶ እግሩ ፖሊስ በንዴት ጉማሬውን እያወናጨፈ::

"ዝምኒልክ አምላክ! በንጉሥ! አንተው ራስ ነህ በዚህ በኩል ሂድ ብለህ ያሳየኸኝ እያለ ባላገሩ በምኒልክ ስም ይምላል፤ ይገዘታል::

አልፎ አልፎ ፈረሰኞች አስፓልቱን ሞልተው ሲሄዱ ይታያሉ:: እነሆ ባሬ በሰንጋ ፈረስ ላይ የተቀመጠ ሰው ፊት ለፊት እየሄደ ከኋላው ጥቂት የታጠቁ ፈረሰኞች አጅበውት የአስፓልቱን መሀል ይዞ አለፈ:: እነዚያ ባዶ እግር ፖሊሶች ፈረሰኞች ሲያቀርቡ ፈረሰኛው ፈገግታ በማሳየት በተጠንቀቅ ቆመው ወታደራዊ ሰላምታቸውን ሲያቀርቡ ፈረሰኛው ፈገግታ በማሳየት እጁፋውን መለሰላቸው:: ንጉሠ ነገሥቱ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ነበሩ::

ከጠዋት ጀምሮ በየቀኑ ከአዲስ አበባና አካባቢዋ ገበያተኞች ወደገበያ ይወጣሉ:: ምንም አይነት ሱቅም (መደብርም) ሆነ በረንዳ የለም:: ብቻ እንዲያው ባዶው ሜዳ ላይ ነጠላቸውን ዘርግተው እቃዎቻቸውን ይዘረግፉና ይገበያያሉ:: ሁሉም የራሱ የሆነ የተወሰነ ቦታ አለው:: ጨርቅ ተራ፣ እህል ተራ፣ እንጨት ተራ፣ ከብት ተራ፣ በግ ተራ ወዘተ. እየተባለ ተከፋፍሏል:: ከነዚህ ገበያተኞች አመዛኞቹ በአዲስ አበባ እና በዙሪያዋ የሚኖሩኦሮሞዎች ናቸው::

በገበያው መጨረሻ ላይ የአልጋ ተራ አለ:: በአልጋ ተራ በአብዛኛው አራቱም እግራቸው እኩል እንኳን ያልሆኑ አልጋዎች ይሸጣሉ:: አሮጌ አልጋ በጣም በርካሽ ዋጋ መግዛት ይቻላል:: ይሁን እንጂ የነዚህ አሮጌ አልጋዎች ባለቤቶች ወደ መቃብር የወረዱ ስለሆኑ፣ ብዙ ጊዜ የሟች ቤተሰቦች ሟችን በራሱ አልጋ ወስደው ከቀበሩ በኋላ የሟችን አልጋ በጥቂት ቤሳዎች ለመሸጥ ወደገበያ ይሮጣሉ:: እናም ገገርው ሟች በሞተበት በሽታ የመለከፍ እድሉ ያመዝናል::

በእንዲህ አይነት ገበያዎች በምንም ተአምር የገበያ ዳኛ መቅረት የለበትም:: በገበያተኞች መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን ሁለቱንም ወገን በሚያስማማ መልኩ የሚዳኝ ዳኛ መኖር አለበት:: እንዲህ አይነት ችሎቶች ወይም ዳኝነቶች በአውላላ ሜዳ ላይ ይካሄዳሉ::

አውሮፓውያን ሲያሽሟጥጡ ይሁን የምራቸውን ብቻ ኢትዮጵያውያን ዳኞች ከንጉሥ ሰለሞን ዳኝነት የማይተናነስ እውቀት አላቸው እያሉ ያወራሉ:: ምናልባት እውነታው ሌላ ቦታ ሊሆን ይችላል:: በኢትዮጵያ እስካሁንም ብትን ጨርቆች የሚለኩት በክንድ ነው::

በጨርቅ ተራ ሁለት ገበያተኞች ይጨቃጨቃሉ:: ጨርቁን የሚገዛው ሰውየ እጁግ በጣም ረጅም ሲሆን ሻጩ ደግሞ በጣም አጭር ነው:: እናም ገገር በሚችለው መልኩ ክንዱን ዘርግቶ፣ ጣቶቹን ወጥሮ አስር ክንድ ለካና ምልክት አደረገ:: ሻጩ ደሞ በሚችለው ሁሉ ጣቶቹን ሳይወጥር እሱም አስር ክንድ ለካና እሱም ምልክት

አደረገ:: ሁለቱ በለኩት መካከል ከአንድ ክንድ የሚበልጥ ልዩነት መጣ:: ገገርው ሻጩን አውቆ ክንዱን ሳይወጥር ይለካል ሲል አመረረ:: ሻጩ በምኒልክ እየማለ ነቀፋ ሻጩን አውቆ ክንዱን ሳይወጥር... ነጋዴ መሆኑን እግዚአብሔርን ምስክርነት ጠራ:: በዚህ መሀል ብዙ ወሬኛ ጠያቶኞች ከበቧቸው:: በነዚህ ወሬኞች ፊት ሁለቱም ደጋግመው ቢለኩም ልዩነቱ ተመሳሳይ ነበር:: እናም መግባባት ባለመቻላቸው ያላቸው ብቸኛ አማራጭ ዳኛ ፍለጋ መሄድ ብቻ ነበርና፣ ሸማቸውን እያይዘውና አቀላልፈው፣ ጎን ለጎን ግራና ቀኝ እጆቻቸውን በነጠላቸው ጫፎች ሸብ አድርገው አስረው ከቋጠሩ በኋላ ወደ የገበያው ሽምጋይ ዳኛ በብዙ ወሬኞች ታጅበው ሔዱ::

ብቸኛው የገበያዋ ፈላጭ ቆራጭ ዳኛ ከፍ ብላ ከተሰራች አንዲት ባለ ሁለት ቆርቆሮ መደብር ላይ ተከፍሶ ተቀምጧል:: የሚንጫጫውን ወሬኛ ፀጥ ካሰኘ በኋላ በትግስት ሁለቱንም ባለጉዳዮች አዳመጠ:: ሁለቱም በአምየ ምኒልክ እየማሉና እግዜሩን ምስክርነት እየጠሩ ችግራቸውን ለዳኛው አስረዱ:: ገገርም ሻጭም ድምፃቸውን ከፍ በማድረግ እየጮሁ ዳኛውን ለማሳመን ሞከሩ:: ዳኛው ሁለቱንም በትግስት ካዳመጠ እና ከቦ የሚያወራውን የገበያ ወሬኛ ዝም ካሰባለ በኋላ፣ ወደ ሁለቱ ባለጉዳዮች እያየ መጀመሪያ ገገርውን አስር ክንድ እንዲለካና ምልክት እንዲያደርግ አዘዘው:: ወዲያው ሻጩንም አስር ክንድ እንዲለካና ምልክት እንዲያደርግ አዘዘው:: ሁለቱም ጨርቁን ለክተው ምልክት አድርገው እንደጨረሱ ዳኛው ጨርቁን ተቀብሎ፣ መጀመሪያ ገገርው ለክቶ ምልክት ያደረገበት ቦታ ላይ በመቀስ ቆረጠው:: ወዲያው ቀጥሎ ሻጩ ለክቶ ምልክት ያደረገበት ቦታ ላይ ቆረጠውና ሁለቱም እውነታ አላቸው፤ እግዚአብሔር ያውቃል አለና ፍርዱን ሲሰጥ፣ በአምዬ ምኒልክ ሁለታችሁም እውነት አላችሁ:: ግን እንዳትጣሉ:: ገገርው በሻጩ አጭር ክንድ መስማማት ስላለበት፣ ነጋዴውም ከዚህ ትርፍ እንዳያገኝ ልዩነት ያመጣውን ጨርቅ ለዳኝነቱ ዋጋ ለራሱ አስቀርቶ ሁለቱን ባለጉዳዮች አሰናበታቸው::

በዳኛው ፍርድ ሁሉም ተደስተዋል:: ነጋዴው፣ ገገርው ሰውየ በሱ አጭር ክንድ የተለካ ጨርቅ በመግዛቱና በረጅሙ ክንዱ ባለመጠቀሙ፣ ገዢው ደግሞ ነጋዴው ባለቺው አጭር ክንድ እየለካ ከፍ ያለ ትርፍ ባለማግኘቱ፣ ወሬኞችም ሳምንቱን ሙሉ የሚያወሩት ወሬ በማግኘታቸው፣ ዳኛውም ከጨርቋ በተጨማሪ ጥቂት ቤሳ ሳንቲሞች በመስራቱ፣ ብቻ ሁሉም ተደስተው ዳኝነቱ ተበተነ:: የንጉሥ ሰሎሞንን ፍርድ የሚስተካከል ፍርድ ይልዎታል ይኼ ነው ::

ንጉሠ ነገሥቱ በአዲስ አበባ የተለያዩ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች አቋቁመዋል:: እድለኛ ከሆኑና በነዚህ የሚኒስትር መስሪያ ቤቶች በአውሮፓና አሜሪካ በተለያዩ ኮሌጆች የተማሩ ኢትዮጵያውያን የሚሰሩ ከሆነ እና እነሱን ካጋጠሞት የመጡበትን ጉዳይ ቶሎ ይጨርሳሉ:: ይሁንና ንጉሠ ነገሥቱ እነዚህን የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች በከፈቱ ጊዜ ለንጉሠ ነገሥቱ ታማኝና ቅርበት ካላቸው ከየጠቅላይ ግዛቱ የመጡ ጢማም ሹማምንቶች በአንድ ሌሊት ሚኒስትር ሲሆኑ ችግር መፈጠር ጀመረ::

እውነቱን ለመናገር እነዚህ ሹማምንቶች በሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ስራው እንዴት እንዲህ እንደሚሰራ ምንም የሚያውቁት ነገር አልነበራቸውም። እናም እኚህ ታታሪ ንጉሥ ለነዚህ አዲስ ለተሾሙ ሚኒስትሮች ከአውሮፓና ከአሜሪካ የተማሩ ሰዎች አስመጥቶ ስለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ አሰራር እንዲያማክሩ ማድረግ ተገደዱ።

እነዚህ የኢትዮጵያውያን ሚኒስትሮች አማካሪ ፈረንጆች ከአሜሪካና ከአውሮፓ አዲስ አበባ እንደገቡ በየተመደቡበት የሚኒስቴር መስሪያ ቤት ስራቸውን በታላቅ ጉጉትና ትጋት ቢጀምሩም፣ አንዳንድ ወግ አጥባቂና አዲስ ነገር ተቃዋሚ ሚኒስትሮች በስራቸው ላይ እንቅፋት ሆኑባቸው።

አንድ የገንዘብ ሚኒስትሩን እንዲያማክርና ገንዘብ ሚኒስቴርን በዘመናዊ መልኩ እንዲያደራጅ የተመደበ ፈረንጅ የገጠመውን ችግር ሲያወራ እንደሰማሁት የሚከተለውን ይመስላል።

ይኼ አማካሪ የገንዘብ ሚኒስቴርን በዘመናዊ መልኩ ለማደራጀት ቆርጦ ይነሳና አንዳንድ ወሳኝ መረጃዎች እንዲሰጡት ሚኒስትሩ ፊት ቀርቦ በዓመት በቀረጥና በግብር መልክ ምን ያህል ገንዘብ እንደሚሰበሰብ እንዲነግሩት ሚኒስትሩን ይጠይቃል። በዚህ የአማካሪ ተብየው ፈረንጅ ጥያቄ ግራ የተጋባው ሚኒስትር "እሺ ጌታ፣ ደህና፣ ሁሉንም አዘጋጅቼ እሰጥሃለሁ" ይልና ያሰናብተዋል። አማካሪው ፈረንጅ በነጋታውም ሲሄድ ተመሳሳይ መልስ እየገጠመው፣ ተስፋ ሳይቆርጥ ምኒስትሩ ፊት እየቀረበ ተመሳሳይ ጥያቄ እያቀረበ ተመሳሳይ መልስ እየገጠመው ወራት ያልፋሉ።

ሽማግሌው ሚኒስትር ይኼ ሞኛሞኝ ፈረንጅ አንድ ቀን ተስፋ ቆርጦ መጠየቁን ይተወዋል ብለው አምነዋል። የዋሁ ፈረንጅ ግን ተስፋ ሳይቆርጥ በየጊዜው እየተመላለሰ ሽማግሌውን ምኒስትር ያቺኑ ጥያቄ እያቀረበ ሲያስቸግር ሚኒስትሩ በጣም ተበሳጭተው ለጸሐፊያቸው፣ "ምን የሚገርም ቂል ፈረንጅ ነው። እኔ እስካሁን ለንጉሡም ገቢው ስንት እንደሆነ ነግሬ የማላውቀውን ለሱ እንድነግረው ይፈልጋል እንዴ?" አሉ ይባላል።

እኚህ ምኒስትር ወይ ስለ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት አወቃቀርና አደረጃጀት ምንም የሚያውቁት ነገር የለም፣ አልያም በደንብ ተደራጅቶና ተዋቅሮ ተቆጣጣሪ እንዲመጣባቸው አይፈልጉም።

አዎ የቼኮዝሎቫኪያ ልጆችም አዲስ አበባ በገቡና በቋሚነት በንግድ ሙያ ለመተዳደር ፈቃድ በጠየቁ ጊዜ ችግሮች ገጥመዋቸው ነበር። አንዱ የቼኮዝሎቫኪያ፣ የሀገሬ ልጅ እንዲህ ሲል ስለገጠመው ችግር አጫውቶኛል።

ይኼ ቼኮዝሎቫክ አዲስ አበባን እየተዘዋወረ ሲያጠና በአዲስ አበባ ከተማ በየቀኑ በርካታ ከብቶች፣ በጎችና ፍየሎች እንደሚታረዱና ኢትዮጵያውያንም ያለ

አግባብ ግማሹን ያህል አንጀት እንዲሁ ለውሾች ሲወረውሩት ያስተውልና፣ ቢያንስ የከብት፣ የበግና የፍየል አንጀት ገዝቶ ካዘጋጀ በኋላ ወደ አውሮፓ ለመላክ ያስብና የንግድ ፈቃድ ለማውጣት ወደ ጉምሩክ ይኼድና ማመልከቻ ያቀርባል።

የጉምሩክ ዳይሬክተር በደንብ የሚያውቀው ጓደኛው ስለነበር የመጣበትን ጉዳይ ለግማሽ ሰዓት ያህል በደንብ ያስረዳዋል። ዳይሬክተሩ በጥሞና ሲያዳምጥ ቆይቶ፣ "የከብት፣ የፍየል፣ የበግ አንጀት..? ምን ያደርግልሃል?" ሲል በመገረም ይጠይቀዋል።

ምንም እንኳን በድጋሚ ለዚሁ ዳይሬክተር ለግማሽ ሰዓት ያህል አንጀቱን ለምን ለምን እንደምንጠቀምበት ቢያስረዳውም አላመነውም። እንዲያውም ልክ ጓደኝነቱን ለሌላ መጥፎ ነገር መጠቀሚያ ሊያደርገው እንዳሰበ አይነት ነገር ቆጥሮት ምንም ክፉ ቃል ሳይናገር "ጉዳዩን መወሰን የሚችለው የንግድ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ነው" ብሎ ወደ ንግድ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት መርቶ አሰናበተው።

በሁለተኛው ቀን ከጠዋት ጀምሮ በንግድ ምኒስቴር መ/ቤት በጠባቧ እንግዳ ማረፊያ ወይም መጠበቂያ ክፍል እስከምሳ ሰዓት ድረስ ጠብቆ በመጨረሻ አንድ የንግድ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ሰራተኛ ወደ እሱ ይመጣና ምን እንደሚፈልግ ይጠይቀዋል። ጉዳዩን ከሰማ በኋላ ወደ ዳይሬክተሩ ቢሮ ይወስደዋል።

ለንግድ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ዳይሬክተርም ለጉምሩኩ ሰውዬ የነገረውን ደግሞ ይነግረዋል። ቀጥሎም አውሮፓውያን የተለያዩ የስጋ ምርቶችን በአንጀት ውስጥ ሞልተው እንደሚጠቀልሉና በጭስ ካደረቁ በኋላ የስጋዎቹ ምርቶች ለምግብነት በተለያዩ መልኮች ተዘጋጅተው እንደሚበሉ ሁሉ ጨምሮ ያስረዳዋል።

ዳይሬክተሩ በጥሞና ሲያዳምጠው ቆይቶ "እና ፈረንጆች አንጀት፣ ሸንፍላ፣ ምናምን ይበላሉ ልትለኝ ነው? በጣም ይሸታልኮ?" ብሎ እየሳቀ ይጠይቀዋል። ይገርማል፣ ይኼም ዳይሬክተር አንዱንም ቃል አላመነውም።

ብቻ ሳቁን እንደማፈን ብሎ፣ በዚህ ጉዳይ ላይ መወሰን የሚችሉት ብቸኛው የተከበሩት ምኒስትር እንደሆኑ ብቻ ነግሮ ለሁለተኛው ቀን ቀጥሮ ያሰናብተዋል። በሁለተኛው ቀን ዋናው ዳይሬክተር ተቀብለውት ብዙም ሳያዳምጠው ለሚኒስትሩ አቅርቦ ውሳኔያቸውን በጹሑፍ በአድራሻው እንደሚያሳውቀው ነግሮ አሰናበተው።

በዚያው ምሽት በየቄራው እየዞሩ አንጀት እንዲገዙለት የቀጠራቸው ላብአደሮች ገና ስራው ሳይጀመር ጥለውት ጠፉ። የአንጀት ንግዱም ጉዳይ አዲስ አበባ ውስጥ በተለያየ መልክ ተወራ።

አንድ ምሽት ይኼው ያገሬ ልጅ ከጎረቤቱ የግሪካዊው ሰውዬ ግሮሰሪ ጎራ ብሎ ሲጠጣ፣ ግሪካዊው የግሮሰሪ ባለቤት የአንጀቷን ወሬ ሰራተኞቼ ነገሩኝ ብሎ በአዲስ አበባ ስለሚወራው ወሬ በሰፊው ሲያጫውተው ቆይቶ በመጨረሻ "አንጀት እገዛለሁ

የሚሰው ፈረንጅ ሃብቶችን እያረደ ደማቸውን ወደ አውሮፓ ለመላክ የመጣ ጭራቅ ነው" ብለው ነጋዴች ብሉ ይነግረዋል። ይኼው ያገሬ ልጅ በዚያው ሰሞን ወደገበያ ሲወጣ በድንቅ አይኖች እየተተጉ፣ ሰዎች መንገድ ሁሉ እየለቀቁለት ይሄዱ ነበር።

ከተወሰኑ ቀናት በኋላ የንግድ ሚኒስትሩ ራሳቸው በሀገሪቱ አሉ የሚባሉ ባለሞያዎችን ሰብስበው ከእንጀራ ወረቀት ማውጣት ይቻል እንደሆነ መጠየቃቸውን ሰሙ ወሬ ሰማ። ከአንድ ወር በኋላ የሚልኳቸውን እንጀራቶች ከመላኩ በፊት እንዲያስመረምር ጥብቅ ትዕዛዝ ከተሰጠው በኋላ የንግድ ፈቃዱ ተሰጠው።

እነሆ አሁን ከአምስት አመታት በኋላ በአዲስ አበባ በነዚህ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች በመጠኑም ቢሆን ከፍተኛ ለውጦች ይታያሉ። ሚኒስትሮች አሁን እንደቢሮን ጊዜው ሲዘዋ በጣም ተጠራጣሪዎች አይደሉም።

እም አዲስ አበባ ለዘመናዊው ስልጣኔ በሯን ከፍታ ወደፊት ስትሮጥ፣ የቀረው የኢትዮጵያ ክፍል አሁንም እንደ ጥንቱ በአንድ ቦታ ቆሞ እያንቀላፋ ነው። ጦርነቱ ከመጀመሩ ጥቂት ቀደም ብሎ የአዲስ አበባ – ደሴ መንገድ ተሰርቶ አልቆ ስራውን ጀምሯል። በአዲስ አበባም ዙሪያ ወደተለያዩ ክፍለ ሀገራት የሚወስዱ የጥርጊያ መንገዶች እየተሰሩ ነው። ምንም እንኳን እነዚህ መንገዶች በጥሩ መልኩ እየተሰሩ ቢሆንም በነዚህ መንገዶች በክረምቱ ወራት በመኪና መሄድ በጣም አስቸጋሪ ነው። እስካሁን ፖርቱጋሎች በአባይ ወንዝ ላይ ከሰሩት የድንጋይ ድልድይ በስተቀር ሌሎች ምንም ዓይነት ድልድዮች አልተሰሩም።

ንጉሡ አዲስ አበባንና ጎጃምን በድልድይ ለማገናኘት አስበው ከአውሮፓ ድረስ ያስመጡት ብረታ ብረትና ሲሚንቶ አባይ ወንዝ ዳር ወርዶ ሲሚንቶውን የአካባቢው ገበሬዎች ጎጆዋቸውን ሲያስማምሩበት፣ ብረቶቹ አሁንም እዚያው እንደወደቁ በመዛግ ላይ ናቸው።

4

በአዲሱ ቤተ መንግሥት

ማታ በሀገሬ ልጅ በኢንጅነር ሉድቪክ ካልቮዳ መኖሪያ ቤት ድሎት ባላቸው ሶፋዎች ላይ ተቀምጠናል። ከአስር አመታት በላይ በኢትዮጵያ የኖረው ካልቮዳ በጣም ጠቃሚ የሆኑ ምክሮችን እየነገረን ስንጫወት፣ ጓደኛዬ አቶ ቪሌም ብርየር ስለ ቤት መከራየት ጉዳይ ወሬ አነሳና ካልቮዳ ኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ የመቆየቱ ሃሳብ ካለን ቤት መከራየቱ መልካም እንደሆነና ብዙ የማንቆይ ከሆነ ግን ብዙም ፋይዳ እንደሌለው መከረን።

በነጋታው ቪሌም ብርየር በኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ መቆየታችን ስለማይቀር ሉድቪክ ካልቮዳን ከምናስቸግር የራሳችንን ቤት መከራየቱ እንደሚሻል አሳመነኝና ከቃሉ ብዙም ሳይርቅ በዚያኑ እለት ቤት ተከራይቶ ጠበቀኝ።

እነሆ በዋናው አደባባይ ከግሪካዊው ዳቦ ጋጋሪ ባለ አንድ ፎቅ ህንጻ ውስጥ ፎቁን በሙሉ በወር 20 የማርትሬዛ ብር ልንከፍለው ቃል ገብተን ተከራየነው። ምድር ቤቱን የቼኮዝሎቫኪያው ተወላጅ አቶ ፔትራክ ተከራይቶ ስጋ ቤት ከፍቶበታል።

ይኼን የተከራየነውን ቤት የማደራጀቱን ሃላፊነት ሙሉ በሙሉ ብርየር ወሰደ። በአዲስ አበባ የቤት እቃ ገዝቶ ቤት ማደራጀት ቀላል አልነበረም። አንድም በአዲስ አበባ የአውሮፓውያን የቤት እቃዎች ማግኘት በጣም ሲበዛ ከባድ ነው። ሁለትም እቃዎቹ ሲገኙ ዋጋቸው የክርስቲያን ልጅ ከፍሎ የሚወጣው አይነት አልነበረም። ከተወሰኑ ቀናት በኋላ ብርየር ሁለት ታጣፊ አልጋዎች፣ አንድ ከተራ እንጨት እንደነገሩ የተሰራች ጠረጴዛ፣ አንድ ፋኖስና አንድ ከፍ ያለች የኢትዮጵያ ካርታ መግዛት ቻለ። ሌላው የልብስ ቁምሳጥኖች ማግኘት ስላልቻልን በግድግዳው ላይ ሚስማር እየተከልን እንደ ልብስ መስቀያ መጠቀም ቻልን። ከዚህ በላይ ቤታችንን ማደራጀቱ አስፈላጊ አይደለም። ሁኔታዎች ሲስተካከሉና ክረምቱ ሲወጣ አዲስ አበባን ለቀን እንሄዳለን።

ቀኑን ሙሉ ይዘንባል። ስራ የለንም። ቢሆንም ቀኑን ሙሉ ስንዞር ውለን ማምሻው ላይ አብዛኛው አውሮፓዊ ወደሚያዘወትራት መሸታ ቤት ለቢራ ጎራ እንላለን። አሁን አሁን ከመላው አለም እንደጉንዳን ሰራዊት ጋዜጠኞች፣ የጦር ሚዲያ ዘጋቢዎች፣ የታሪክ ሰዎች፣ ተጓዦች፣ የተለያዩ ኩባንያዎች ተወካዮች፣ የፈረንጅ ገበሬዎች፣ ነጋዴዎችና ሰላዮች፣ ምናልባትም ጦርነቱ ከተጀመረ በጦርነቱ ለመካበር አስበው የመጡ ሌቦች፣ ብቻ ምን አለፋችሁ አዲስ አበባ በውጪ ዜጎች ተጥለቅልቃለች።

ይኼ ሁሉ የውጪ ዜጋ የሚሰበሰበው በዋናው አደባባይ ባለች አንዲት ሲኒማ ቤት ነው። የተቆራረጠ፣ በየቀኑ የማይገም፣ ከመዘክር የወጣ የሚመስል አንድ የአሜሪካን ፊልም ከታየ በኋላ ሁሉም ለቢራ ወደ አዳራሹ ይገባል።

በዚች የመጠጥ አዳራሽ የውሸት ውስኪ፣ ቮድካ፣ ብራንዲ፣ ካርተር ውስኪና ሌሎችም ከሃምሳ አይነት በላይ የአልኮሆል መጠጦች ይሸጣሉ። ብልጣ ብልጡ ግሪካዊው የዚች መጠጥ ቤት ባለቤት በጠርሙሶቹ ላይ የሚለጠፉትን ባለቀለም ወረቀቶች ብቻ ገዝቶ በጠርሙሶቹ ላይ ይለጥፍና ራሱ የሚያወጣቸውንና የሚጠምቃቸውን መጠጦች በጠርሙሶቹ እየሞላ ይቸበችባል።

ይኼ ሌባ ግሪክ በዚህ የግርግር ወቅት በአጭር ጊዜ ለመክበር አስቧል መሰለኝ የመጠጦችን ዋጋ እጅግ በጣም አስወድዷቸዋል። ይኼም አልበቃ ብሎት እየመሸ በመጣ ቁጥር ዋጋውም እየጨመረ ይኼዳል። የጠፈፈው ጨኸት ከዚያ በየቀኑ የዚያችን ፈረንሳዊት እንደ ዘፈን እያጠነጠነ የሚያንጎራው ግራማፎን ሲጨመርበት አንጎል ያበጠብጣል። ይኼ ግራማፎን ላንቃው የሚዘጋው የመጨረሻው ጠጪ መጠጥ ቤቷን ለቆ ሲወጣ ብቻ ነው።

አቶ ሎሬንሶ ትዕዛዝ፣ በጣም ሲበዛ ዝነዝና የተማረ የንጉሡ የማስታወቂያ ሚኒስቴር ዳይሬክተር፣ ወደዚች የግሪኩ መጠጥ ቤት ጎራ ብሎ ከልብ የመነጨ

ሰላምታ አቀረበልኝ። ቀጥሎም ስለምፈልገው ነገር ሁሉ እንዲረዳኝ አንድ የምኒልክ ትምህርት ቤት አስተማሪ ሰጠኝ።

የምኒልክ ትምህርት ቤት በእውነት ዘመናዊ ትምህርት ቤት ነው። ይኼ መምህር በፍጹም ንጹህ ልብና ደግነት ወደ ብዙ ብዙ ቦታዎች ወሰደኝ። በወቅቱ ስላለው የኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታዎችና እውነታዎችም ብዙ ብዙ አጫወተኝ። አንድ ቀን ይኼው መምህር ከባርነት ነጻ የወጡ የጥንት ባሮች ልጆች ወደሚማሩበት "ፍል ውሃ ትምህርት ቤት" ወሰደኝ።

በ"ፍል ውሃ ትምህርት ቤት" ወደ 200 የሚሆኑ የተለያየ ቀለምና ከ 5 እስከ 14 ዓመት እድሜ ያላቸው ተማሪዎች ይማራሉ። ትምህርት ቤቱን በምጎበኝበት ወቅት እነዚህ ተማሪዎች በትምህርት ቤቱ ዳይሬክተር ትዕዛዝ ተሰልፈው የኢትዮጵያን ሕዝብ መዝሙር ዘመሩልኝ።

ቀጥለውም በቡድን ተከፋፍለው ጅምናስቲክ እየሰሩ አሳዩን። ከዚያ ወደየክፍላቸው በስነ ስርአት ተሰልፈው ሄዱ። እኔም በዳይሬክተሩ ታጅቤ ከምኒልክ ትምህርት ቤት መምህር ጋር መጎብኘት ጀመርኩ። ትንንሾቹ ወንዶችም ሴቶችም በአንድ አስተማሪ ረዳትነት ማንበብና መጻፍ ይማራሉ። ትልልቆቹ ወንዶቹ እንደዚሁ በሌላ ሙያተኛ መምህር እየተረዱ የእንጨት ስራ ትምህርት ሲማሩ፣ ትልልቆቹ ሴቶች ደግሞ በሁለት ክፍሎች ውስጥ ስለ ዘመናዊ ምግብ አሰራር ይማራሉ። ይኼ ትምህርት ቤት በወደፊት ሕይወት ውስጥ እጅጉን የሚጠቅም ተግባራዊ ትምህርት መቅሰሚያ ነው።

ከዚህ በጣም አስደሳች ጉብኝት ስንመለስ በመንገዳችን ላይ ይኼው መምህር በኢትዮጵያ ስላለው የባርነት ችግር ያስረዳኝ ጀመር። ምንም እንኳን ንጉሡ ነገሥቱ በልዩ አዋጅ ባርነትንና የባሪያ ንግድን ቢያግዱም እስከዛሬ ድረስ ችግሩ አለ። አለኝና ቀጥሎ፣ "አየህ ጌታው፣ የመጀመሪያዎቹ የዚህ ልዩ ህግ ተቃዋሚዎች ማንም ሳይሆኑ ራሳቸው ባሮቹ ነበሩ። ምናልባትም በኢትዮጵያ ውስጥ በእውነተኛ ስሙ ባርነት ብሎ ነገር አልነበረም ማለት ይቻላል። ማለትም የጎረቤት አገሮች ድንበር ጥሰው እየገቡ በግድ አስገድደው እየወሰዱ ከሚሸጧቸው ባሮች በስተቀር ማለቴ ነው።"

የኢትዮጵያ ባሪያ ሁሌም በድሎትና ያለምንም ሃሳብ ይኖራል። ጌታው ሃብታም እስከሆነ ድረስ ከአንድ ተራ ገበሬ፣ ድንጋይ የበዛበትን መሬቱን እንደዝንጀሮ እየቆፈረ፣ በአምባው እየኖረ፣ በመከራ ቤተሰቡን ከሚያስተዳድረው በላይ ያለ ሃሳብና ጭንቀት ሁሌም ሆዱን ሞልቶ በድሎት ይኖራል።

ጭሰኛው ወይም ገበሬው ዘመን በከፋ እና ምርቱ እዚህ ግባ በማይባልበት ወቅት ቤተሰቡን ለማስተዳደርና ከረሃብ ለመትረፍ ብድር በብድር ሆኖ ሲንገላታ፣ ባሪያው፣ ጌታው ምርት ካለበት ቦታ ገዝቶ በሚያስመጣው እህል ሆዱ እስኪቀዝር ይበላል።

የኢትዮጵያ ባሪያ ምንጊዜም ምንም አርነት ሃሳብ እና ጭንቀት አልነበረበትም። ሁሌም እስኪጠግብ ይበላል። ቀኑን ሙሉ ሲዝናና ሲተኛ ይውላል። አልፎ አልፎ ስራ ቢጤ ቢሰራም ቀስ እና ጠንቀቅ ብሎ ሰውነቱን ሳይጎዳ፣ ወዝን ሳይቆርጥ ነዉ የሚሰራው።

እነዚህ ባሮች ንጉሠ ነገሥቱ ባርነትን መሰረዙና ነጻ መሆናቸውን ከሁሉም በላይ ደግሞ ራሳቸውን በራሳቸው ማስተዳደር እንደሚኖርባቸው ሲሰሙ አብዮት ቀረሽ ግርግር ፈጠሩ። አብዛኛዎቹ ጌታቸውን ጥለው ነጻነታቸውን ተቀብለው መሄዱን አሻፈረኝ ብለው ከጌታቸው ጋር በግዛ ፈቃዳቸው በባርነት ስር ወድቀው በዚያው ያላ ሃሳብ ህይወታቸውን ቀጠሉ።

እዚሁ ስምንት ዓመት በፊት ማለት በመጀመሪያው የኢትዮጵያ ጉብኝቴ እዚህን ወደ ገዛ ባሮች በስራ ላይ እንዳሉ የማየቱ እድል ገጥሞኝ ነበር። እዎ እነዚህ ባሮች ለጌታቸው የድንጋይ ቤት ለመስራት ድንጋይ እየለቀሙ ነበረ። አስራ አራት ቀን ሙሉ ለቤት መስሪያ የሚሆን ድንጋይ ከአካባቢው እየፈለጉና እየመጡ ቤቱ ሊሰራበት ከታሰበው ቦታ ላይ ያስቀምጣሉ። የነዚህን ባሮች የአስራ አራት ቀን ስራ የአውሮፓ ሁለት ሰራተኞች በአንድ ቀን በሰሩት ነበር።

ብቻ እነዚህ 20 የሚሆኑት ባሮች አስራ አራት ቀን ሙሉ እያንዳንዱ ባሪያ አንድ ሰዓት ሙሉ ድንጋይ ሲፈልግ ይቆይና በጣም አነስ ያለች ድንጋይ ሲያገኝ እሷኑ ያንጠለጥልና አምጥቶ ከዚያች የድንጋይ ክምር ላይ ይወረውራትና ከጓደኞቹ ጋር ተቀምጦ ሁለት ሰዓት ያወራል።

ንጉሠ ነገሥቱ ባርነትን ካገዱ በኋላ ባሮች በነጻነት እንደሚኖር ሰው ነበር የሚኖሩት። ጌታቸው ተናደው ሊያስገርፏቸው ሲነሳ ወይ የነጻነት መብታቸውን ተጠቅመው ይጠፋሉ፣ አለበለዚያም እሜን ብለው ይገረፋሉ።

ልክ አዲስ አበባ እንደገባሁ በኢትዮጵያው የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር በብላቴን ጌታ ህሩይ በኩል በንጉሡ ፊት ቀርቤ እጅ እንድነሳ ማመልከቻ አስገብቼ ነበር። ይሁን እንጂ ንጉሠ ነገሥቱ በዚህ በከፋ ጊዜ ሌት ተቀን በጣም አንገብጋቢ ጉዳዮችን እየፈቱና እየመከሩ ስለሆነ ለኔ አይነቱ ተራ ሰው ጊዜ የላቸውም።

የኢትዮጵያው ንጉሠ ነገሥት ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ሌት ተቀን ከተለያዩ የሀገሪቱ ግዛቶች የሚመጡትን ሹማምንቶች እየተቀበሉ ያነጋግራሉ፣ ይመክራሉ። የውጪ ዲፕሎማቶችንም እየተቀበሉ ለረጅም ሰዓታት ያነጋግራሉ፣ ይመክራሉ፣ ይደራደራሉ።

ጣልያኖችንና ጠብ ጫሪነታቸውን በተመለከተ እያንዳንዷን ጥቃቅን ነገር ራሳቸው ንጉሠ ነገሥቱ ይወስናሉ። ሰላምን ለማስፈን ሌት ተቀን ይሰራሉ፣ ይለፋሉ። እናም ሌሎች ተራ ጉዳዮችን ስገዜው ወደ ጎን ቢተዉ የኢትዮጵያውን ንጉሠ ነገሥት አያሳማቸውም።

እንደዚህም ሆኖ የኔን ማመልከቻ ተቀብለው በአጭር ጊዜ ውስጥ እጅ እንድነሳ ተጠራሁ። አንድ ማንነቱን የማላውቀው ኢትዮጵያዊ በፈረንሳይኛ ቋንቋ በወርቅ ቀለም የተጻፈ የግብዣ ወረቀት አምጥቶ ሰጠኝ። በዛሬው ምሽት በአዲሱ ቤተ መንግሥት ንጉሠ ነገሥቱ በግል እንደሚያነጋግሩኝ የግብዣው ወረቀት ያስረዳል፣ ያሳስባል።

ከተጠርው ሰዓት ጥቂት ደቂቃዎች ቀደም ብዬ የአዲሱን ቤተ መንግሥት የመጀመሪያ በር በመኪና ሳልፍ ሁለቱ ዘቦች በተጠንቀቅ ቆመው ለንጉሠ ነገሥቱ እንግዳ የሚገባውን ሰላምታ ሰጡኝ።

ገና መኪናዋ በቤተ መንግስቱ ደጃፍ ከመቆሟ አንዱ የንጉሠ ነገሥቱ አሽከር የመኪናዋን በር ሲከፍትልኝ፣ ሁለተኛው ካፖርቴንና ኮፍያዬን ሲቀበለኝ፣ ሶስተኛው እንድከተለው ጠቁሞ ወደ ቤተ መንግስቱ ይዞኝ ገባ።

ምንም እንኳን በትክክል በተቀጠርኩበት ሰዓት ብደርስም ንጉሠ ነገሥቱ ካጠቃላይ ክፍለ ሀገራት ከመጡ ሹሞች ጋር ምክር ላይ ስለሆኑ ቢያንስ ለሩብ ሰዓት መጠበቅ አለብኝ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ድብልብል ብሎ የወፈረውና ምንጊዜም ፈገግታ የማይለየው ብላታ ኪዳነ ማሪያም፣ የንጉሠ ነገሥቱ ባለሟል፣ ጥቁር ዘመናዊ ሱፉን ግጥም አድርጎ እንደለበሰ ያ ፈገግታው ሳይለየው ወደ እኔ እየመጣ ንጉሠ ነገሥቱ ምክሩን ስለጨረሱ ሊያነጋግሩኝ እየጠበቁኝ እንደሆነ ነግሮ መንገድ እየመራኝ ስንሄድ አንድ የተከበረ ሰው ነጩን ባህላዊውን ልብስ እንደለበሰ ፈጠን ብሎ ተከተለንና ቀድሞ በር ከፈተልን።

ወለል ብሎ በተከፈተው በር ወደ ውስጥ ስገባ ንጉሠ ነገሥቱ ከትልቁ ጠረጴዛቸው ጀርባ በተለያዩ መዛግብትና ቴሌግራሞች ክምር ተሸፍነው እንደተቀመጡ አገኘኋቸው።

እንደ ኢትዮጵያውያን ባህል ሁሉ ግንባሬ መሬት እስኪነካ ሰጥ ብዬ ሰላምታዬን አቅርቤ ቀና ስል ራሳቸውን ብቻ በማነቃነቅ ለሰላምታዬ መልስ ሰጥተው ወዲያው ከፊት ለፊታቸው እንድቀመጥ በምልክት አዘውኝ ስቀመጥ፣ በኔና የንጉሠ ሰለሞንና የንግሥት ሳባ ቀጥተኛ ወራሽ በሆኑት የኢትዮጵያው ንጉሠ ነገሥት መካከል ብላታ ኪዳነ ማሪያም ተገትሮ ቆመ።

የንጉሠ ነገሥቱ የስራ ክፍል የተደራጀው በመጠኑ ነው። የግድግዳውን ጥግ ይዘው የተወሰኑ ቀያይ ሶፋዎች መደዳውን ተደርድረዋል። እንዳልኩት ክምርጥ

እንጨት የተሰራው የስራ ጠረጴዛቸው በፋይሎችና በቴሌግራሞች ተውጧል:: ልዩ ነገር ቢኖር የንጉሡ የጽሑፍ መሳሪያ ከወርቅ የተሰራች መሆኗ ብቻ ነው:: በዚቹው አነስ ያለች የንጉሠ ነገሥቱ የስራ ክፍል በርካታ ሹማምንቶች ሸማቸውን እንደለበሱ መደዳውን ቆመዋል ::

ምንም እንኳን ንጉሠ ነገሥቱ ከትልቁ ጠረጴዛቸው ኋላ እንደተቀመጡ ፈገግ ለማለት ቢሞክሩም ገጽታቸው በስራ በዛት እጅጉን እንደደከመ ያሳብቅባቸዋል:: መደዳውን እንደቆሙት ሹማምንቶች ሁሉ ንጉሡ ባህላዊውን የኢትዮጵያውያን ልብስ ለብሰው ጥቁር ተራ ካባ ደርበዋል:: እንዲህ ለስልጣኔ ሌት ተቀን የሚለፉት ንጉሠ ነገሥት በዚህ አስቸጋሪ ጊዜ እንኳን የጥንቱን የኢትዮጵያውያንን ባህልና ወግ አልረሱም::

እንዳልኩት ከፊት ለፊታቸው እንደተቀመጥኩ ብላታ ኪዳነ ማሪያም በመካከላችን ሲቆም አስተርጓሚ መሆኑ ገባኝ:: ምንም እንኳን ንጉሠ ነገሥቱ ፈረንሳይኛም እንግሊዘኛም አቀላጥፈው ቢናገሩም የኢትዮጵያውያን የነገሥታት ህግ ከውጭ ዜጎች ጋር በአማርኛ ብቻ እንዲናገሩ ስለሚያስገድድ የግድ አስተርጓሚ አስፈላጊ ነው::

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ፣ እድል ለዚህ አስቸጋሪ ጊዜ የመረጠቻቸው መሪ፣ በቁመናቸው አጠርና ከሳ ያሉ ናቸው:: ይኼ ረዘም ያለ ፊታቸው፣ በጥንቃቄ የተከረከመው ሙሉ ጥቁር ጢማቸው፣ ምናልባት ለሳይንቲስት፣ ለፈላስፋ ወይም ለደራሲ ይሆን እንደሆነ እንጂ አገሩን በደሙና በአጥንቱ ለመከላከል ቆርጦ ለተነሳ መሪ የሚሆን አይመስልም:: ግን ወደፊት እንደምናየው ንጉሠ ነገሥቱ እንደ ማንም ተራ ወታደር በጦር ሜዳ ውለው ታግለው አታግለዋል:: ተዋግተው አዋግተዋል::

አዎ በማይጨው የጦር ሜዳ ከእሳቸው በፊት እንደነበሩት ነገሥታት ሁሉ ትልቁን ሃላፊነት ወስደው፣ ጠቅላላውን የሀገሪቱን ጦር እየመሩ ህይወታቸውን አደጋ ላይ ጥለው ተዋግተዋል:: ይኼም ታላቅ ጅግና ሊያስብላቸው ይገባል::

በአዲስ ቤተ መንግሥት ንጉሠ ነገሥቱ ለውጪ ሀገር አምባሳደሮች፣ ዲፕሎማቶች፣ ጋዜጠኞች እና ታዋቂ ሰዎች፣ ኢትዮጵያውያንን ከፍተኛ ሹማምንቶችን ጨምሮ፣ በአንዳንድ ልዩ አጋጣሚዎች የራት ግብዣ ያደርጉ ነበር:: በዚህ የራት ግብዣ ላይ አሉ የሚባሉ የሀገሪቱ ምርጥ ምግቦች አንዳቸውም ሳይቀሩ ከውጪ ሀገር ምግቦች ጋር በአለም ላይ አሉ የሚባሉ የመጠጥ አይነቶች አንዳቸውም ሳይቀሩ እንደ ውሃ ይፈሳሉ::

በእንዲህ አይነቶቹ ግብዣዎች የሚያስተናግዱት ቀልጣፋዎቹ የንጉሠ ነገሥቱ አሽከሮች እንግዶች የያዙት ብርጭቆ ከማለቁ በፊት ከየት አቅጣጫ እንኳን እንደመጡ

ሳያስተውሉ መጥተው የጎደለውን ብርጭቆ ይሞላሉ:: ከነዚህ ቀልጣፋ አሽከሮች የሚሰወር አንድም ነገር የለም::

በእንዲህ አይነት የራት ግብዣ ላይ አንድ የንጉሠ ነገሥቱ እንግዳ የሆነ ፈረንጅ የቀረበለትን ምግብ በወርቅ ሹካና ማንኪያ ሲበላ ቆይቶ የወርቁን ማንኪያ ቀስ ብሎ ወደ ኪሱ ሲከት አሽከሮቹ ያዩና ለንጉሠ ነገሥቱ ይነግሯቸዋል:: ንጉሠ ነገሥቱ ይኼን ቅሌታም ፈረንጅ አዋርደው ከማባረር ይልቅ የወርቁን ማንኪያ ለማስታወሻ እንዳላየ ሰው ሆነው ተዉለት::

እኔም በንጉሠ ነገሥቱ የልደት በአል ላይ ራት ተጋብዤ ተገኝቼ ነበር:: ከራት ግብዣው በኋላ ያ ሰፊ አዳራሽ ወደዳንስ አዳራሽነት ተለወጠና ከሁሉም አይነት የሰው ልጆች ዘር፣ ቀለምና እድሜ – ከ20 እስከ 70 ዓመት እድሜ ታዳሚዎች – ብቻ ሁሉም በቫልስ፣ በሮክስ፣ በታንጎ ሙዚቃ እየታገዙ የሰዓት እላፊው እንኳን ሳያግዳቸው እስከ ንጋት ድረስ ደነሱ::

ይኼንን ዳንስ ንጉሠ ነገሥቱ ከእቴጌ መነንና ከትንሹ ልጃቸው ከሐረሩ መስፍን ጋር ከፍ ብሎ በተዘጋጀ መድረክ ላይ ተቀምጠው ይመለከቱ ነበር:: ቀጭኗ ልዕልት ፀሐይ በዳንሱ አዳራሽ መሀል ገብታ ስትውረገረግ እኩለ ሌሊት ሆነና ንጉሠ ነገሥቱ ከባለቤታቸው ከእቴጌ መነን፣ ከትንሹ የሐረሩ መስፍንና ከልዕልት ፀሐይ ጋር አዳራሹን ለቅቀው ቢሄዱም ዳንሱ እንደቀጠለ ነበር::

ንጉሠ ነገሥቱ ከሄዱ በኋላ እስካሁን ድረስ በይሉኝታ ጥግ ይዘው የተቀመጡት ከየጠቅላይ ግዛቱ የመጡት ጢማሞቹ ሽማግሌ ሹሞች በዳንሱ አዳራሽ ውስጥ በቆሙት መስታወቶች ራሳቸውን እያዩ ለመደነስ ይሞክራሉ:: ይኼን የሽማግሌዎቹን ዳንስ ያዩ የንጉሠ ነገሥቱን ወታደሮች ሊያስለጥኑ የመጡ የቤልጂግ ወጣት ወታደራዊ መኰንኖች ሽማግሌዎቹን ወደ አዳራሹ መሀል ወስደው ጥቂት እንቅስቃሴዎችን ያሳይዋቸው ጀመር:: እነዚህ ሽማግሌዎች ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ የዳንስ እውቀታቸውን አሻሽለው እስከጠዋት ድረስ ሲወላገዱ አንግተዋል::

በነዚህ አስቸጋሪ ቀኖች ውስጥ የኢትዮጵያ መኖርና አለመኖር የሚወሰንበት ጊዜ ነውና ንጉሠ ነገሥቱ በአዲሱም በአሮጌውም ግቢ (በምኒልክ ቤተ መንግሥት) ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ይመክራሉ:: በዚህ ጊዜ ከውጪ ወደ አዲስ አበባ የሚጎርፉ ዜናዎች በአብዛኛው ተስፋ አስቆራጮች ናቸው:: ምንም እንኳን አብዛኛዎቹ ኢትዮጵያውያን በኢትዮጵያውያንና በጣልያኖች መካከል ያለውን የኃይል ሚዛን አሳምረው ቢያውቁም አንዳቸውም እንሸነፋለን የሚል ሃሳብ በፊታቸው ላይ አይነበብባቸውም::

"አድዋ ላይ እንዳሸነፍናቸው ሁሉ አሁንም እናሸንፋቸዋለን" አለኝ የፖስታ ቤቱ ሠራተኛ ፖስታዬን እየሰጠኝ።

ፖስታ አዲስ አበባ ውስጥ በአድራሻ አይታደልም። ፖስታ የመጣለት ሰው ፖስታ ቤት ድረስ ወይ ራሱ አሊያም አሽከር ልኮ ነው የሚወስደው። በፊት ፖስታ ቤት በተወሰኑ ደቂቃዎች ውስጥ ትንሽ ፈጅም መሄድ ይችል ነበር። አሁን አሁን ፖስታ ትንሽ መዘግየት ጀምሯል። ጥሩው ነገር ከአውሮፓ ወደ አዲስ አበባ ፖስታ የሚመጣው በሳምንት አንድ ጊዜ በዛ ቢባል ሁለት ጊዜ ብቻ ነው።

በፖስታ ቤቱ አውሮፓውያን ከአበሻ የፖስታ ቤቱ መስኮቶች በአንዱ ብቻ ነው የሚስተናገዱት። የፖስታ ቤቱ ሰራተኞችም በተወሰኑ ሰዓታት ልዩነት ይቀያየራሉ። ስራ ገበታቸው ላይ የሌሉት የፖስታ ቤቱ ሰራተኞች ከፖስታ ቤቱ ጀርባ ባለች አንዲት ሰፋ ያለች ክፍል ውስጥ በንጉሠ ነገሥቱ የክብር ዘብ ወታደሮች እየተረዱ መትረየሶችን እየፈቱ ይገጥማሉ።

በሌሎች የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች የሚሰሩ ኢትዮጵያውያን፣ በየፈረንጆች ቤት ተቀጥረው የሚሰሩት ሳይቀሩ፣ ያሏቸውን የእረፍት ጊዜ ሁሉ ተጠቅመው ወደ ስልጠና ቦታ በመሄድ እስከ ምሽቱ ድረስ በአሰልጣኞቻቸው እየተረዱ፣.

...ቀኝ... ግራ... ቀኝ ..ግራ ...እያሉ ይረግጣሉ።

ጠቅላላው የኢትዮጵያ ህዝብ ለጦርነት እየተዘጋጀ ነው። የነሐሴ ወር መጨረሻ እየተቃረበ ነው። የቁርጥ ቀኑም እንደዚያው እየቀረበ ነው።

"ምረጥ ጌታ" አለኝ አንድ የፖስታ ቤት ተላላኪ። በእጁ የተወሰኑ ቴሌግራሞች ይዟል። ምስኪን ተላላኪ። በላቲን ፊደላት የተጻፉት አድራሻዎች ለሱ ምንም ትርጉም የላቸውም። በመንገዱ ላይ ያገኘውን ፈረንጅ ሁሉ እያቆመ ከያዘው ቴሌግራም የራሱን መርጦ እንዲወስድ ይጠይቃል። ይኼ ደግና ምስኪን ተላላኪ ልጅ አንዳንድ ፈረንጆች ተንኮለኞችና መሰሪዎች መሆናቸውን አልገመተም።

እነዚህ ተንኮለኞች የራሳቸው ያልሆነውን የጓደኞቻቸውን ወይም የንግድ ተቀናቃኞቻቸውን ቴሌግራም እንደሚወስዱ አያውቅም። አዎ ለዚህም ነበር በአዲስ አበባ የንግድ ምስጢር ብሎ ነገር ያልነበረው። አንዱ ታታሪ ነጋዴ ስንትና ስንት ወራት የደከመበትን የንግድ ምስጢር እነዚህ ብልጣ ብልጥ ተንኮለኛ ፈረንጆች ከዚህ ምስኪን ተላላኪ እጅ ላይ በሚመነትፏቸው ብጫቂ ቴሌግራሞች በአንድ ሌሊት የንግዷን ምስጢር ይደርሱባታል።

መጠጥ ቤቶች ለወትሮው ባዶ እንዳልነበሩ ሁሉ አሁን ከጠዋት እስከ ማታ እስከአፍጢማቸው ሞልተው ይውላሉ።

"ጣሊያኖች ጦርነቱን ሊያሸንፉ አይችሉም" ይላል አንዱ፣

"ከሳምንት በኋላ አዲስ አበባ ይገባሉ" ይላል ሁለተኛው፣

"ጦርነቱ መቶ ዓመት ይፈጃል" ይላል ሌላው፣

"ኢትዮጵያውያንን በሀገራቸው የሚያሸንፋቸው የለም" ይላል ሌላው ከፊት ለፊት፣ "ጣሊያንን ታንኮች በምናቸው ነው የሚከላከሉት?" ሲል ሌላው ይጠይቃል፤ "ጣሊያን አውሮፕላኖች አዲስ አበባን በመጀመሪያው ቀን ጦርነት ነው ከምድረ ገጽ የሚያጠፏት" ይላል ሌላው።

በሁሉም ጠረጴዛዎች ዙሪያ ወሬው ስለ ኢትዮጵያና ጣሊያን ጦርነት ነው። ብቻ እንዲህ በወሬ ተጠምጄ የቡና ቤቷ በር ሲከፈት እንኳን አላየሁም ነበር። ከጎኔ የተቀመጠው ሰው ጎሸም አድርጎ ወደ በሩ ሲያመለክተኝ ነበር እኔን ፈልጎ የመጣውን ሰው ያየሁት። ልጅ ዘውዴ በላይነህ ነበር። ልጅ ዘውዴ በላይነህ በፓሪስ ፖሊቴክኒክ ተቋም የተማረ ጎበዝ ጎልማሳ ነው። ይቸኩላል መሰለኝ ወደ ቡና ቤቷ ዘልቆ ሳይገባ ከሩቅ ጠራኝ።

"ወደ ጎንደር መብረር ትፈልጋለህ? አሁኑኑ ወደ ቤተ መንግሥት መመለስ አለብኝ። ንጉሠ ነገሥቱ መልሳችሁን አሁኑኑ ይጠብቃሉ" አለኝ።

"እንዴታ" አልኩት ወዲያውኑ ምንም ሳልጠራጠርና ሳላስብ።

"እሺ እንግዲያው ወደ ቤትዎ ሄደው ይዘጋጁ፤ ነገ ጠዋት መጥቼ አወስዳችኋለሁ። ንጉሠ ነገሥቱ ሁሉንም ነገር ራሳቸው ያብራሩላችኋል" አለኝና ተሰናብቶኝ ሄደ።

ልጅ ዘውዴ በላይነህ ቃሉን አክብሮ ጠዋት እመኖሪያ ቤታችን ድረስ መጥቶ ወደ ቤተ መንግሥት ወሰደኝ። ንጉሠ ነገሥቱ ያለ ምንም ፕሮቶኮል በቤተ መንግሥት ተቀብለው በጎንደር ስለሚጠብቀኝ ግዳጅ በአጭሩ አስረዱኝ። ጓደኛዬ አቶ ቪሌም ብረየርም አብሮኝ እንድሄድ በጠየቅሁት ጥያቄም ተስማምተው "በሉ ተዘጋጁ፤ በቅርብ ቀን ወደ ጎንደር ትበራላችሁ" ብለው ጨብጠው አሰናበቱኝ።

አንድ ሳምንት እንኳን አልሞላም። ልጅ ዘውዴ በላይነህ በሀገራችን ልጅ በሉድቪክ ካልቮዳ ቤት በጣም ከመሸ በኋላ፣ እኩለ ሌሊት ሊሆን ምንም አልቀረው፣ ቡና እየጠጣን ስንጫወት መጥቶ "ንጉሠ ነገሥቱ አሁኑኑ በቤተ መንግሥት ሊያነጋግሩን እንደሚፈልጉ" ሲነግረን ሉድቪክ ካልቮዳን ተሰናብተን ወደ ቤተ መንግሥት በልጅ ዘውዴ በላይነህ መኪና ሄድን። በመንገዳችን ላይ ንጉሠ ነገሥቱ እንደሚጠብቁንና ነገ ልክ ጎህ ሲቀድ በአንድ የኢትዮጵያ አውሮፕላን ወደ ጎንደር እንደምንበርም ጨምሮ አጫወተን።

ልክ ቤተ መንግሥት እንደገባን ንጉሠ ነገሥቱ አሁንም ያለ ምንም ፕሮቶኮል ተቀበሉን። አሁን ግን እንደኢትዮጵያ ጠቅላይ የጦር አዛዥ የመጨረሻዎቹን ትዕዛዞች ከሰጡን በኋላ በሁለቱም ለስላሳ እጆቻቸው ጨብጠውኝ፣

"ጀግኖችን ክቡር ሃላፊነት በመቀበላችሁ እናመሰግናችኋለን። ኢትዮጵያ ምንጊዜም ውለታችሁን አትረሳውም" አሉኝ። ከቤተ መንግሥት ተሰናብተን እንደወጣን በቀጥታ ወደ አውሮፕላን ጣቢያ ሄድን። አውሮፕላን ጣቢያ ስንደርስ፣ "ንጉሠ ነገሥቱ ትዕዛዝ ለነገ ከመንጋቱ በፊት አንድ አውሮፕላን ወደ ጎንደር የሚበር አዘጋጁ" ሲል ትዕዛዙን ልጅ ዘውዱ በላይነህ አስተላለፈ።

5

ከአዲስ አበባ ወደ ደብረ ታቦር

የመኝታ ቤቴ በር ሲንኳኳ ከእንቅልፌ ነቃሁ።

"ማነው?"

"ተነስ ጌታው" ሲል አንድ ደስ የሚል የሴት ልጅ ድምጽ ቀሰቀሰኝ። ይኼው ድምጽ ቀጥሎ "አሥር ሰዓት ሊል ነው። ሊነጋ ነው። ተነስ ጌታው!" አለኝ። ወርቅነሽ ነበረች። ገና የ17 ዓመት ወጣቷ ውብ ልጅ ወርቅነሽ፣ ቤታችንን እንድታስተዳድርልን የቀጠርናት፣ አዲስ አበባ በጨለማ ተውጣ እያንቀላፋች እኛን ቀሰቀሰችን።

ቀስ በቀስ እውነታው እየተገለጠልኝ መጣ። ዛሬ መስከረም 27 ቀን 1935 ዓ.ም. ነው። ከሁለት ሰዓት በኋላ አዲስ አበባን ለቀን ወደ ጎንደር መብረራችን ነው። ለምን ያህል ጊዜ? መቼ ይሆን የምንመለሰው? ይኼን እግዜሩ ብቻ ነው የሚያውቀው።

ከኔ የመኝታ ክፍል ቀጥሎ ባለው ክፍል ውስጥ ውሃ ሲንሿሿ ይሰማል። ቪሌም ብረየር ከኔ ቀድሞ ተነስቶ እየታጠበ ነው።

ወርቅነሽ ያዘጋጀችልንን የመጨረሻውን ምርጥ ቁርስ ከማይጠገበው ፊገሪታዋ ጋር በመብላት ላይ እንዳለን ትናንት ማታ የተከራየነው መኪና ሰዓቱን አክብሮ መጥቻለሁ፤ ደርሻለሁ፤ እንሂድ፤ አይነት ነገር ክላክሱን በተደጋጋሚ ነፋብን። አዎ

በእንዲህ አይነት መልክ ለመጓጓዣ ዝግ ወደቅነበት ተሰናብተን በመኪናችን ተሳፍረን ወደ አየር ማረፊያ ተፈተለክን።

አዲስ አበባ ገና ከእንቅልፏ አልነቃችም ነው። አብዛኛዎቹ ሱቆች ገና አልተከፈቱም። የተከፈተ ሱቅ ቢኖር የአንድ የአርመን ዳቦ ቤት ብቻ ነው። አርመኑ አዲሱን ሲጋግር ያፈራውን ለመግዛት ደንበኞች በወረፋ ተሰልፈው ትንሿን ሱቁን አጨናንቀዋል።

ፖሊሶችም በሊሮች ጉርድ የበርሜል ቤት አድረው ወደየስራ ቦታቸው ሲሄዱ ችግር አየር ማረፊያ ጨርሰዋል።

አየሩ ቁር እጅግ ፖሊሶችም በሊሮች ሲሄዱ ይታያሉ። በዚህ መልክ ያለ አንዳች ችግር ነበር። መካኒኮች ከጠዋቱ ወዲህ በተቻላቸው አየር ማረፊያው ደመቅመቅ ብሎ አውሮፕላኖችን ይጠጋግናሉ።

ከፊት ለፊታችን ካለች አንዲት አውሮፕላን ስር ሆኖ መካኒክ ለአብራሪው ... ምናምን ይለዋል። በዚህ መሀል ሁሉም ነገር ጥሩ ነው። ሞተሩ በትክክል ይሰራል። ምናምን ይለዋል። በዚህ መሀል አንድ የስፖርት መኪና በከባድ ፍጥነት ስትከንፍ መጣችና በአውሮፕላን ማቆሚያው በትልቁና ሰፊው አደባባይ (ሃንጋር) ደጃፍ ላይ ቆመች።

ከዚች ፉጣን የስፖርት መኪና ውስጥ አንድ ቀፍጣና መልከ መልካም ወጣት (የኢትዮጵያና የፈረንጅ ክልስ) ወጣ። ወጣቱ የኢትዮጵያን የአየር ኃይል ወታደራዊ የደንብ ልብሱን እንደለበሰ መለዮውን ደፍቶ እኛ ወደቆምንበት አቅጣጫ በፈጣን እርምጃ መራመድ ጀመረ። ወደኛ እየቀረበ ሲመጣ የዚህ ወጣት ወታደራዊ የደንብ ልብስ በብዙ የመርቅ ኒሻኖች ማጌጡን አስተዋልኩ።

እንግዲህ ይኼ ወጣት ነው በንጉሠ ነገሥቱ እኛን ወደ ጎንደር በአውሮፕላን ይዞን እንዲበር የተመረጠው የአውሮፕላን አብራሪ። ይኼ ወጣት አባቱ ፈረንጅ ሲሆን እናቱ ኢትዮጵያዊት እና የንጉሣዊ ቤተሰብ ልዕልት ናት።

በዚህ መሀል ከወጣቱ የስፖርት መኪና ጎን አንድ ሰማያዊ ሲምዚን መኪና ስትከንፍ መጣችና ገና ከመቆሟ፣ በፍጥነት በተከፈተው በር ልጅ ዘውዴ በላይነህ ዘመናዊውን የአውሮፓውያንን ሙሉ ልብስ ለብሶ ከረባቱን እንዳሰረ፣ ረጅም ካፖርቱን ደረብ አድርጎ ያ ሁሌም የማይለየው ፈገግታው ሳይለየው ወደኛ አቅጣጫ እንደመሮጥ እየቃጣው መጣ። እንደደረሰም፣ "እንደምን አደራችሁ? በቃ ዛሬ መብረራችሁ ነው አይደል?" እያለ የእጅ ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ ያንን ወጣት አውሮፕላን አብራሪ ሚካኤል ባቢቼቭ (ሚሻክ ጠራውና አስተዋወቀን። አዎ ወጣቱ አውሮፕላን አብራሪ ሚካኤል ባቢቼቭ (ሚሻክ ባቢች) ይባላል። እንግዲህ ለሚሻክ ባቢች ነው ህይወታችንን አሳልፈን በአደራ የምንሰጠው።

ሚሻክ ባቢችን ካስተዋወቀን በኋላና ስለ በረራችን በቀልድ መልክ ትንሽ ስንጫወት ቆይተን፣ ልጅ ዘውዴ በላይነህ እኔን ወደ ጎን ወሰድ አድርጎ በጣም ከለተር ብሎ አንድ የታሸገ ፖስታ እየሰጠኝ፤

"አደራ ጌታው፣ ይኼ ደብዳቤ ከሌላ ሰው እጅ እንዳይገባ ተጠንቀቅ። አደራ ጌታው፣ በጣም ትልቅ ምስጢር ያዘለ ነው። አደራ ጌታው፣ ለራስ ካሣ ከንጉሠ ነገሥቱ የተላለፉ ጥብቅ ትዕዛዞችን የያዘ ነው። አደራ፣ አደራ ጌታው እንደ ዓይን ብሌንህ ጠብቀው።"

እያለ ደጋግሞ አደራ እያለ አስጠንቀቀኝ። እንዲህ አደራ፣ አደራ ጌታው እያለ ካስጠነቀቀኝ በኋላ፣ "ይኼው ጌታው፣ ንጉሠ ነገሥቱ ቃል የገቡልዎት" ብሎ አንድ በወርቅ ቀለም ያጌጠ የመኳንንቶች የቆዳ ቀበቶ ሰጠኝ። ይህን ቀበቶ የሆነ ሰው ከዚህ በፊት ታጥቆት እንደነበረ የሚያሳይ ትንሽዬ ምልክት ይታይበታል። አዎ ንጉሠ ነገሥቱ ትናንት ታጥቀውት ከነበረው ቀበቶ ጋር የመንታ ያህል ይመሳሰላል። እርግጠኛ ነኝ ንጉሠ ነገሥቱ የራሳቸውን ቀበቶ ፈትተው ነው የላኩልኝ። አዎ በንጉሡ የንጉሠ ነገሥቱን ቀበቶ መታጠቅ ማለት እንደ ኢትዮጵያውያን ባህልና ወግ በንጉሠ ነገሥቱ የምታመን ሰው መሆኔን ማረጋገጫ ነው።

በርከት ያሉ ወታደሮች ከሰፊው አዳራሹ ውስጥ አንድ ባለ ድርብ ክንፍ አውሮፕላን "POTEZ" እየገፉ አወጡትና ሁለት መካኒኮች በታላቅ ቅልጥፍና መዘውሩን እያሽከረከሩ ሞተሩን ሲያስነሱ፣ ባቢች እኔንና ጓደኛዬን ብለየርን ወደ አንዲት ትንሽ የመልበሻ ክፍል ውስጥ ይዞን ገባ። ሚሻክ ባቢች በለበሰው ወታደራዊ የደንብ ልብሱ ላይ ቱታውን ደረበና አንድ በጣም ከባድ የቆዳ ካፖርት እየደረበ ለኛም የሱኑ አይነት ከባድ የቆዳ ካፖርት ደርበን እንድንለብስ አቀበለን። ካፖርቱን ስደርበው ከመክበዱም በላይ በጣም ስለሚሞቅ፤

"ይኼን ስንደርብ ሙቀቱን አንችለውምና ይቅርብን" ስል ለሚሻክ ባቢች ብነግረው፣ ሚሻክ ባቢች ሳቅ ብሎ "እዚያ ላይ" በሌባ ጣቱ ሰማዩን እያሳየ፣ "እዚያ ላይ በጣም ይበርዳል፤ ግዴለም ደርቡት!" እያለ ለራሱ ጭንብሉን እያጠለቀ ለኛም አቀበለን።

ያንን ከባድ ካፖርት ደርበንና ያቺን ጭንብል አጥልቀን ከዚያች ትንሽ የመልበሻ ክፍል ውስጥ ስንወጣ ለተመለከተን ሰው ያለማጋነን የማርስ ሰዎች እንመስል ነበር።

ሁለት ወታደሮች የኛን ሻንጣዎች አውሮፕላኗ ውስጥ መጫን ጀመሩ። እያንዳንዳችን ከአንድ ሻንጣ በላይ መጫን አንችልም፤ ወይም ደግሞ በአውሮፕላኗ እቃ መጫኛ ውስጥ ከኛ ሻንጣዎች ቀደም ብሎ ለራስ ካሣ የሚላኩ ዕቃዎች ስለተጫኑ ብዙ ቦታ የለም።

እኛ ወደ አውሮፕላኗ ሄደን ለመሳፈር ስንዘጋጅ ሶስት ሽማግሌ ሹሞች እኛ የለበስነውን አይነት ክቡር የቆዳ ካፖርት ለብሰውና በአናት የሚጠለቀውን ጭንብል በእጃቸው እንከርፍፈው እንደያዙ መጥተው ተቀላቀሉን።

“እነዚህም አብረውን በራሪዎች ናቸው” አለኝ የአውሮፕላኗ አብራሪ ሚሽክ ባቢች። ቀጥሎም “የጎንደር ጠቅላይ ግዛት ውስጥ ያሉ ወረዳዎች ሹሞች መሆናቸውን፤ ጦርነቱ በቅርብ ሊጀመር ስለሚችል በአስቸኳይ ወደ ግዛታቸው መሄድና ጦራቸውን አሰባስበው ለጦርነቱ እንዲዘጋጁ በንጉሠ ነገሥቱ ታዘው መሄዳቸው እንደሆነ” እና ሌላም ሌላም ነገር ጨማምሮ ሚሽክ ባቢች ለምን ዛሬ አብረውን መብረር እንዳለባቸው ሊያስረዳኝ ሞከረ።

“አውሮፕላኗ ለአብራሪውና ለታዛቢው ብቻ የሚሆን ሁለት ባዶ ቦታ ብቻ ነው ያላትና አብረውን ሊበሩ ፈጽሞ አይችሉም” ስል ቅዋሜዬን ጮክ ብዬ ከአውሮፕላኗ የሞተር ጩኸት ጋር እየተፎካከርኩ አሰማሁ።

“እንደነገሩ አድርገን እንበራለን፤ ለነገሩ በበረራችን አንዳች አደጋ ቢገጥመን አንዳችንም አንተርፍም” አለኝ ሚሽክ ባቢች።

ከአውሮፕላኗ አብራሪ ሚሽክ ባቢች አነጋገር እንደተረዳሁት ይኸ ባለ ብዙ ልምድ አውሮፕላን አብራሪ (የወርቅ ኒሻኖቹ እውነትም ምርጥ አብራሪ መሆኑን ይመሰክራሉ) እንኳን በአንድ አውሮፕላን ስድስት ሰው ጭኖ መብረሩ እንዳልተዋጠለት ያስታውቅ ነበር። ይሁን እንጂ የአዛዡን ትዕዛዝ እምቢ አሻፈረኝ ማለት ፈፅሞ አይችልም። መሞት ካለበት ይሞታል እንጂ ትዕዛዙን መቀበል ግዴታው ነው።

“ከነዚህ ሹሞች ጋር አብራችሁ መብረር የማትፈልጉ ከሆነ ለሹሞቹ ሌላ አውሮፕላን ይዘጋጅላቸዋል። እኛ ሶስታችን በአስተማማኝ ሁኔታ መብረር እንችላለን” አለኝ ሚሽክ ባቢች በተቃውሞዬ እንድገፋበት እየገፋፋኝ። ከሚሽክ ባቢች ጥቆማ በኋላ ዞር ብዬ ብረየርን ሳየው ብረየርም በዝምታ መስማማቱን ስለገለጸልኝ “እንግዲህ ወይ እኛ ብቻችንን እንበራለን። አለበለዚያ ፈጽሞ አንበርም” ስል ኮስተር ብየ ተናገርኩ።

እንዲህ እኛ ስንከራከር ስልኩ ጮኸና ባቢች ጥቂት በስልኩ በአማርኛ ሲያወራ ቆይቶ የመነጋገሪያውን እጀታ አሳልፎ ሰጠኝ። “አብራሪው እንደነገረኝ ከሶስቱ ሹሞች ጋር አብራችሁ መብረር አትፈልጉም አሉ?” አለ አንድ ድምጽ በስልኩ ገመድ።

“አዎ ጌቶች፣ በአውሮፕላኑ ውስጥ ያለው አንድ ክፍት ቦታ ብቻ ነው። እናም በሁለት መቀመጫ ላይ ለሶስት ሆኖ መብረር ራሱ ራስን አደጋ ላይ መጣል ነው። ጌቶች ስድስት ሆኖ መብረር ማለት ደግሞ ራስን በገዛ ፈቃድ መግደል ነው” ስል መለስኩ። “አብራሪው ያለኝ ሁላችሁንም በአንድ ላይ ይዞ መብረር እንደሚችል ነው” አለ አሁንም ደዋዩ ሰው።

“እኔ ደግሞ ፈጽሞ አይሆንም እላለሁ ጌታዬ። እናም በአንዲት አውሮፕላን ለስድስት ሆነን ተጨናንቀን ሁላችንንም አደጋ ላይ ጥለን መብረር አንፈልግም” አልኩ።

በዚህ መሀል የአውሮፕላኗ አብራሪ ባቢች ትከሻዬን መታ መታ አድርጎ በጣም ዝቅ ባለ ድምጽ “ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር ነው እያወሩ ያሉት” አለኝ። በጣም ደንግጬ ትንሽ ገዝም ካልኩ በኋላ፤

“C´est voter Majesté qui parle?” ለምናልባቱ ብዬ ጠየኩ።

“Oui, c´est moi!” ሲል የማውቀው የንጉሡ ድምጽ መለሰልኝ።

“በጣም ይቅርታ እጠይቃለሁ። ግን በውሳኔዬ እንድጸና እገደዳለሁ” አልኩና በመቀጠል፤ “የኛ አደጋ ላይ በከንቱ መውደቅ ለኢትዮጵያ ጦርም ጦርነቱ ከመጀመሩ በፊት ትልቅ ጉዳት ነውኮ” እያልኩ እየፈራሁ ደፍሬ ተናገርኩ።

“በአውሮፕላን ጣቢያ ቆዩ” ሲል በስልኩ ጆሮ ቀጭን ትዕዛዝ ተሰጠኝ። ወዲያው ቀጥሎ፣

“የራሳችንን ሰው እንልካለን” ካሉን በኋላ ስልኩ ዘጉት።

ከጥቂት ጊዜ ቆይታ በኋላ አንድ የቤተ መንግሥት መኪና ሲከንፍ መጥቶ እኛ የቆምንበት ቦታ ቆመና ከመኪናዋ ውስጥ አቶ ታደሰ፣ የንጉሠ ነገሥቱ ልዩ ጸሐፊ፣ ወጣና በፈጣን እርምጃ እየተራመደ “ምንድን ነው ችግሩ?” ሲል ቆጣ ብሎ ጠየቀኝ። ስለ ሁኔታው ሳስረዳው በታላቅ ትዕግስት ሲያዳምጠኝ ቆይቶ “ችግሩ ይገባኛል፤ እቀበለዋለሁም። ግን እኔ ምን ማድረግ እችላለሁ?” ሲል ለራሱም ግራ የገባው በሚመስል ሁኔታ ከተናገረ በኋላ አሁንም ጥቂት እንደማሰብ ብሎ “እነዚህ ሶስት ሹሞች ዛሬ የግድ ደብረ ታቦር መድረስ አለባቸው” አለና ወዲያው ፊቱን ወደ አብራሪው ባቢች መልሶ “ይቅርታ፣ ምንም ማድረግ አልችልም። ዛሬ ሁለት ጊዜ ወደ ደብረ ታቦር ትበራለህ” ሲል ለባቢች በትዕዛዝ መልክ ነገረው።

ከአቶ ታደሰ ንግግር እንደተረዳሁት እኛ የምንበረው ወደ ጎንደር ሳይሆን በቀጥታ በጣና ሃይቅ ዳርቻ አካባቢ ወዳለች ተራራማ ቀበሌ ደብረ ታቦር ነው። አብራሪያችን ሚሽክ ባቢች በአቶ ታደሰ ሃሳብ ተስማማ። አንድ ጊዜ በአደገኛ ሁኔታ አምስት ሰው ጭኖ ከመብረር ሁለት ጊዜ መብረሩን መርጧል። ለነገሩ ሌላ አማራጭ የለውም።

በዚህ መልኩ ለበረራ እንደተዘጋጀን ከመካኒኮቹ አንዱ አንድ ከፍ ያለች ከረጢት አምጥቶ ለባቢች ሲሰጠው ባቢች ከረጢቷን በጀርባው አዘላት። የአደጋ ጊዜ ከአውሮፕላን መዝለያ ዣንጥላ መሆኗ ነው። “ለኛስ?” ስል ባቢችን ዣንጥላዎቹን ለኛም እንዲሰጡን ጠየኩት። “ለናንተ አያስፈልጋችሁም። በታዛቢው መቀመጫ ቦታ ያለከረጢቱም ከገባችሁ ተአምር ነው” አለኝ።

ሚሽክ ባቢች እውነቱን ነበር፤ በተዛቢው መቀመጫ ቦታ እኔ እና ብረየር ጠንነት መስራ ገዘተን ከነር ተጨናንቀን የተቀመጥነው። ሚሽክ ባቢች እንደመሰለት ብሎ፣ "ለነገሩ ዣንጥላው ምንም ጥቅም የለውም። አደጋ ቢፈጠር ከቢች ውትፍ ቦታ መዝለል አትችሉም" አለን።

ሚሽክ ባቢች አውሮፕላኗን እሪ ሲያስብላት መላ ሰውነቷ መርገፍገፍ ጀመረ። እና ብዙም ሳትቆይ ይቺ አውሮፕላን በመሬት ላይ እንደሰንን መሮጥ ጀመረች። እንዲህ በከፍተኛ ፍጥነት በሚዱው ላይ ስትሮጥ ቆይታ ከፊት ለፊታችን ተገትረው ከተሙት የባህር ዛፎች ጋር ተላተመች እያልኩ አይኔን ስጨፍን አፍንጫዋን ወደ ሰማይ አንስታ መንሳፈፍ ጀመረች።

ወዲያው አዲስ አበባን አንድ ጊዜ ዞረን በቀጥታ ወደ ሰሜን መብረር ጀመርን። የስላሴ ሜዳ የተዘረጋ ባህር ይመስላል። አልፎ አልፎ የምናያቸው ጎጆዎች በእጅ የሚጨበጡ ይመስላሉ። አሁን ሚሽክ ባቢች ዝቅ ብሎ ስለሚበር መንደርተኞች ከጎጆቻቸው እየወጡ አንጋጠው አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ ቀለም የተቀባችውን የባቢችን ቆርቆሮ ይመለከታሉ።

እንዲህ ዝቅ ብለን ስንበር ከጀርባዬ የሆነ ነገር ሲጎረብጠኝና ሲነካካኝ ተሰማኝ። ምናልባት የሆነ እንስሳ ሊሆን ይችላል ብዬ ዞር ብዬ ለማየት ብሞክርም ከብረየር ጋር ተጣብቄ ስለተቀመጥኩ አንገቴን እንኳን ማዞር ሳይሆንልኝ ቀረ። ያ የሚጎረብጠኝ፣ የሚነካካኝ፣ የሚኮረኩረኝ ነገር፣ አሁንም አሁንም ህይወት እየዘራ ኩርኩራውም እየጠነከረ መጣ።

ኩርኩራው አላስቀምጥ ቢለኝ እንደምንም ብዬ ከተጣበኩበት ትንሽ ወጣ ብዬ አንገቴን ሳዞር በጣም ደነገጥኩ። በአይኔ የማየውን ነገር ማመን ሁሉ አቃተኝ። እንደዝንጀሮ ተኮማትሮ ከነዚያ ሶስቱ ጢማም ሽማግሌ ሹሞች አንዱ ተጠቅልሎ ተኝቷል። ገና ለመብረር ስናከበኩብ ሁለት ጊዜ በቂጣችን ዘጭ ያልንበት ምክንያት አሁን ገና ነው የገባኝ።

ሽማግሌው ሹም በድል አድራጊነት ተኮማትሮ በተኛበት ቦታ ሆኖ ይስቃል። እዎ እምቢ፣ አይሆንም፣ ከኛ ጋር አትብርም ብንለውም የኛን መደናገር ተጠቅሞ እኛ ሳናየው ከእቃዎች ጋር ተደባልቆ ራሱን ለአደጋ አሳልፎ ሰጥቶ እነሆ አብሮን ወደ ደብረ ታቦር እየበረረ ነው። ሽማግሌው ሹም ፍጹም ደስተኛ ይመስላል። በፊቱ ላይ ምንም አይነት ፍርሃት አይታይበትም። ለምንስ ይፈራል? አውሮፕላን እንደዚህ ሽማግሌ ሹም አስተሳሰብ ልዩ በሰማይ ላይ የሚበር ሁለት ክንፍ ያለው አውቶሞቢል፣ የፈረንጅ ስራ ነው። ፈረንጅ ደግሞ እንዳው ዝም ብሎ ወድቆ የሚሰባበር ነገር አይሰራም። እናም ይኼ ሽማግሌ ሹም እንወድቃለን፣ እንከስከሳለን፣ ብሎ ፈጽሞ አያስብም።

ከእንዲህ አይነት እምነት ውጪ ኢትዮጵያውያን የአውሮፕላን አብራሪዎችን በአለም ላይ ምርጥ፤ ደፋር እና ቆራጥ አብራሪዎች የሚያደርጋቸው አንድ ሌላ ነገር አለ። ያም ነገር አውሮፓውያን የአውሮፕላን አብራሪዎች ለበረራ ከመነሳታቸው በፊት ይምር በበረራም ላይ እያሉም ስለ አየር ጸባይ፣ ስለ ንፋሱ እና ስለ ሌላም ሌላም በበረራቸው ላይ ሊገጥማቸው ስለሚችለው ነገር ሁሉ ይነገራቸዋል።

ኢትዮጵያውያን አብራሪዎች ያለ ምንም የንፋስም ሆነ የአየር ጸባይ መረጃ በታላቅ ድፍረት በኢትዮጵያ አስፈሪ ተራራዎች መሀል እየተሹለከለኩ ወደሚያውቁት ሀገር ሁሉ ይበራሉ። እንዲህም ሆኖ እስካሁን ድረስ በኢትዮጵያ የአውሮፕላን አደጋ ደርሶ አያውቅም።

የአውሮፕላን ማረፊያ ጣቢያ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በአዲስ አበባ አንድ እነስ ያለች ዙሪያዋን በረጃጂም የባህር ዛፎች የተከበበች ሜዳ ነበረች። ሌላ ቦታ እንደ አክሮባቲስት፣ ዝበራዎች ጨርቅ እያወዛወዙ በሚያሳይዋቸው ቦታዎች ሁሉ ነበር የሚያርፉት።

በአንድ አጋጣሚ ስለ በረራና ስለሚያጋጥሙት ጓዝ በተነሳ ወሬ አንድ አብራሪ በባለ ሁለቱ መቀመጫ አውሮፕላኑ ቀኝና ግራ ባሉት ሁለቱ ጠንካራ የአውሮፕላኑ ብረቶች ላይ ሁለት ሳጥኖች በብረት ገመድ አስሮ ሌሎች ሁለት ሰዎች አሳፍሮ እንደሚበር እየማለና እየተገዘተ ነገረኝ። ላምነው አልቻልኩም ነበር። በኋላ ሁለት የአይን እማኝ ምስክሮች ይዞ መጥቶ አሳመነኝ።

እንዲህ በማያልቅ ትልቅ ባህር ላይ የምንሳፈፍ እየመሰለኝ ስንበር፣ በሃሳብ ከፈረንሳዊው አውሮፕላን አብራሪና ደራሲ ከዮሴፍ ከሰል ጋር የተገናኘንበትን አጋጣሚ አስታወስኩ።

እዎ ከዛሬ አምስት ዓመት በፊት ነበር ደቡብ የመን ውስጥ የተገናኘነው። ዮሴፍ ከሰል ያኔ ገና ከኢትዮጵያ መመለሱ ነበር። የተሰበረ እጁን ከመታሰሩም በላይ ፊቱ አላዋቂ የላጠው ድንች ይመስል ተገባብጦ ነበርና ምን አደጋ እንደገጠመው ጠይቄው ታሪኩን አጫወተኝ።

ከአዲስ አበባ ወደ ሐረር ለመሄድ በተነሱ ጊዜ የኢትዮጵያ መንግሥት ሁለት አውሮፕላኖች ለሱና ለጓደኛው ሰጣቸው። አንደኛውን ፈረንሳዊው ጓደኛው ሲያበር ሁለተኛውን ራሱ ዮሴፍ ከሰል ነበር ያበር የነበረው።

ዮሴፍ ከሰል ገና ከአዲስ አበባ ከመነሳቱ በፊት ወደ ሐረር ስልክ ደውሎ አውሮፕላን ማረፊያ ቦታ ተዘጋጅቶለት እንደሆነ ጠይቆ ነበር። ስልኩን የተቀበለው ሰው ለአውሮፕላኑ ማረፊያ ሜዳ አንዲት ጠጠር እንኳን ሳያስቀር አስለቅሞ እንዳዘጋጀለት ነግሮት ስለነበር ያለምንም መጨነቅ አውሮፕላኑን ከጓደኛው ጋር አስነስተው ወደ ሐረር ይበራሉ።

ዮሴፍ ከሰል በርካታ የድንጋይ ቤቶችን ሲያይ ሐረር መድረሱን ይረዳና የሐረርን ከተማ አየዞረ አውሮፕላን ማረፊያውን መፈለግ ይጀምራል። በተደጋጋሚ ሐረርን አየዞረ ቢፈልግም አውሮፕላን ማረፊያ የሚመስል ነገር እንኳን ማግኘት አልተቻለውም ነበር።

ጓደኛው ከሐረር ከተማ ወጣ ብሎ ሜዳ ነገር ሲፈልግ ሲበር አየውና እሱም እንደ ጓደኛው ሜዳ ብጤ ለመፈልግ አስቦ መስመሩን ሲለውጥ ሲል በድንገት ከከተማዋ ዳርቻ በስተሰሜን ጫፍ ላይ በርካታ ሰዎች አንዲት ትንሽ ሜዳ ከበው ያይና እነዚህ ሰዎች ወደ ተሰበሰቡበት ቦታ ዝቅ ብሎ ይበራል። በጣም ትንሽዬ አራት መአዘን ሜዳ ዙሪያዋን ችካል ቸክለውና በገመድ አስረው በጉጉት የአውሮፕላኗን ማረፍ ሲጠባበቁ ሲያይ፣ ምን አይነት ብልጥ ጭንቅላት ነች ይቺንን ያሰበቺው ብሎ ይገረምና ሰፊ ሜዳ ፍለጋ ከፍ ብሎ መብረር ከጀመረ በኋላ እነዚያን ያቺን 10 ሜትር በ10 ሜትር የሆነች ትንሽዬ ሜዳ ከበው በጉጉት የሚጠብቁትን ሰዎች ላለማስቀየም በዚያች ሜዳ ላይ ለማረፍ ይወስንና ይመለሳል።

እዎ ይቺን ትንሽ ሜዳ አንዲት ጠጠር እንኳን ሳያስቀሩ ልቅም አድርገው ለቅመው መሬቱን ተምትመው በደንብ አዘጋጅተዋታል። እዎ ዮሴፍ ከሰል በዚያች ትንሽዬ ሜዳ ላይ ሄዶ አረፈላቸው። በዚህ አደገኛ አስተራረፉ አውሮፕላኗ አንድ ጎማዋን መስዋዕትነት ስትከፍል ዮሴፍ ከሰል ደግሞ አንድ እጁን ከመሰበሩና ፊቱ ከመጋጋጡ በስተቀር የከፋ አደጋ ሳይደርስበት አረፈ። ዮሴፍ ከሰል ገጠመኙን ካጫወተኝ በኋላ በመጨረሻ፣

"ሐረሬዎች ያችን አውሮፕላን ማረፊያ በደንብ አድርገው ነበር ያዘጋጇት። ግን ያቺ ሜዳ ሃምሳ እጥፍ መሆን ነበረባት" ሲል አድናቆቱን ገልጾልኛል።

አሁን ሜዳውን ጨርሰን ለሁለት በተከፈለ መሬት ውስጥ ገባን። የአባይ ሸለቆ። በዚህ የአባይ ሸለቆ ውስጥ ብዙ ነጫጭ ቀጭን ገመድ የሚመስሉ ነገሮች ይታዩናል። እዎ ለኛ ነጭ ቀጭን ገመድ የሚመስሉን ነገሮች የአባይ ገባር ወንዞች ናቸው።

ወዲያው አንድ ብርማ ትልቅ ዘንዶ አየሁ። ሚሻከ ባቢቼብ ወደኔ ዞር ብሎ የሆነ ነገር ሊነግረኝ ሞከረ። ግን አንዲትም ቃል ልሰማው አልቻልኩም። እንዳልሰማሁት የተረዳ መሰለኝ በጣቱ ወደዚያ ብርማ ዘንዶ ቁልቁል እያሳየኝ "Nile....Bleu" ብሎ መስታወቱ ላይ ፃፈልኝ።

እዎ ለኔ ብርማ ዘንዶ መስሎ የታየኝ ነገር ትልቁ የአባይ ወንዝ "ጥቁር አባይ" ነበር። አባይ - የሸዋና የጎጃም ጠቅላይ ግዛት ድንበር። የአባይን ወንዝ ተከትለን በርካታ የጎጃም ተራሮችን እየታከክን ስንበር ቆይተን አሁንም ሚሻከ ባቢቼብ በአውሮፕላኗ የፊት መስታወት ላይ "Tana" ብሎ ፃፈ። እዎ የጣና ሐይቅ፣ የጥቁር

አባይ መነሻ ምንጭ። ጥቁር አባይ የወሎን፣ የጎጃምን፣ የሸዋንና የወለጋን ተራሮች እየናደ የሚወስድ ሌባ። የሱዳንና የግብፅ የዳቦ ቅርጫት፣ ጣና እና ጥቁር አባይ።

ከዚያም ለሚቀጥለው ሩብ ሰዓት ያህል ስንበር ቆይተን በርካታ ጥቋቁር ጠብታዎች የሚመስሉ ነገሮች ማየት ጀመርን። እነዚህ ከፍ ብለን ስንበር እናያቸው የነበሩት ጥቋቁር ነጠብጣቦች ዝቅ እያልን በበረርን ቁጥር የኢትዮጵያውያን መኖሪያ የጎጆ ቤቶች መሆናቸውን ለየናቸው። የጉዟችን መጨረሻ የደብረ ታቦር ከተማ ነበረች። ሚሻከ ባቢቼብ እንዲህ ዝቅ ብለን እየበረርን በምንዞራት ደብረ ታቦር ከተማ እንደምናርፍ በምልክት ነገረንና አሁንም ደብረ ታቦርን ዝቅ ብሎ ወርዶ እየበረረ የማረፊያ ቦታ ይፈልግ ጀመር።

በቤጌምድር (በወቅቱ አጠራር) ዋና ከተማ በደብረ ታቦር ራስ ካሣ ኃይሉ ዘዳርጌ የሰላሌው ይጠብቁናል። ሚሻከ ባቢቼብ ጥቂት ሲፈልግ ቆይቶ ለማረፊያ ቦታ የተመረጠውን ሜዳ ነጭ ነጠላ ለምልክት ተዘርግቶበት አገኘውና በቀጥታ ወደ ሜዳው በመብረር ፍጥነቱን ቀንሶ የማረፊያውን ቦታ ሁለት ጊዜ ከዞረ በኋላ ያለ ብዙ ችግር አረፈ።

ከአውሮፕላኗ ውስጥ እንደሰከረ ሰው እየተወላገድን ስንወርድ ራቅ ብለው የኛን ማረፍ በጉጉት ይጠብቁ ከነበሩ ሰዎች መካከል ሁለት ሹሞች በወታደሮቻቸው ታጅበው ፈጠን ባለ እርምጃ መጡ።

ረጅሙና ወጣቱ ጀነራል የራስ ካሣ የበኩር ልጅ ደጃዝማች ወንድወሰን ካሣ ሲሆን፣ ሁለተኛው አጠር እና ከሣ ያለው ደግሞ የንጉሡ ነገሥቱ ሰው ራስ ካሣን እንዲያማክር ከአዲስ አበባ የተላከው በጅሮንድ ለጥይበሉ ነው። እነዚህ ሁለት ከፍተኛ ሹሞች አውሮፕላኗ ያረፈችበት ቦታ ደርሰው ከልብ የመነጨ አቀባበል አደረጉልን።

ከእንዲህ አይነቱ ልብ ከሚነካ አስደሳች አቀባበል በኋላ ከጀነራል ወንድወሰን ጋር ጎን ለጎን በተዘጋጁልን ፈረሶች ላይ ተቀምጠን ወደ ደብረ ታቦር ከተማ ጉዞ ጀመርን። በመንገዳችን ሶስት ሙዚቀኞች ወይም ጡሩንባ ነፊዎች ያለ ማቋረጥ የሙዚቃ መሳሪያቸውን በኃይል እያስገደዱ ከፊት ለፊታችን ይሮጣሉ።

ከሙዚቀኞቹ ቀጥሎ ወታደሮች በሶስት ረድፍ ተሰልፈው እጅግ በሚያስደንቅ ሁኔታ ይረግጣሉ። ከወታደሮቹ ቀጥሎ ቁጥር ስፍር የሌላቸው የደብረ ታቦር ከተማ ነዋሪዎች ተከትለውናል። እኛ በዚህ መልኩ እጅብ በእጅብ ሆነን ደብረ ታቦር ቤተ መንግሥት ስንገባ ሚካኤል ባቢቼብ አውሮፕላኑን አስነስቶ ወደ አዲስ አበባ በረረ። በቤተ መንግስቱ ራስ ካሣ በታላቅ ትእግስትና ጉጉት ይጠብቁናል።

6

በራስ ካሣ ቤተ መንግሥት

ከጣና ሐይቅ በስተምስራቅ ከባህር ወለል 3.000 ሜትር በላይ ጉብ ካለችው የበጌምድር ጠቅላይ ግዛት ዋና ከተማ ደብረ ታቦር ስንደርስ የራስ ካሣ ሹማምንቶች ተቀበሉን:: ቀጥሎም ራስ ካሣም በቤተ መንግስታቸው እንደሚቀበሉን ተነገረንና ወደዚያው እየተጣደፍን ከደጃዝማች ወንድወሰንና ከበጅሮንድ ለጥይበሉ ጋር አመራን:: ደብረ ታቦር እስካሁን ካየኋቸው መንደሮች የምትለይበት ነገር ቢኖር ስፋቷ እና ከፍታዋ ብቻ ነበር። ሌላው እንደሌሎች መንደሮች ሁሉ በሳር ጎጆ የተሞላች ነበረች ::

የደብረ ታቦርን ከተማ አኩል ሰንጥቀን ሽቅብ ወደ ጉብታው ስንወጣ በከተማዋ በስተመጨረሻ ላይ የራስ ካሣ የእንጨት ቤተ መንግሥት ጉብ ብሎ በታላቅ ኩራት ተኮፍሶ ይታያል:: ቤተ መንግስቱ በሶስት ዙር የድንጋይ አጥሮች ዙሪያውን የታጠረ ነው:: ግንቡ ካልተጠረበ ድንጋይ የተገነባና ላይ በላይ የተደራረበ የነብ አጥር ሲሆን ይኼ የነብ አጥር ከወገቡ በላይ በሊጋም ሽምጥ ታጥሯል::

እያንዳንዱ ግንብ አንድ አንድ በር ሲኖረው በሮቹ በሁለት በሁለት ወታደሮች ይጠበቃሉ:: እነዚህን የግቢውን በሮች ባለፍን ቁጥር ወታደሮቹ መሳሪያቸውን እንዳነገቱ በተጠንቀቅ ቆመው ሰላምታ ይሰጡን ነበር:: ሶስተኛውን በር እንዳለፍን

ካሉት ሶስት ቤቶች ወደ መሃከለኛውና ትልቁ ቤተ መንግሥት አሽከርየው እየመራን ገባን::

ራስ ካሣ በቤተ መንግስታቸው የእልፍኝ አዳራሽ ውስጥ በፋርስ የአበባ ምንጣፍ ላይ በዙፋናቸው እንደተቀመጡ ተቀበሉን:: ራስ ካሣ እድሜያቸውን ለመገመት የሚያስቸግር ቢሆንም በሃምሳዎቹና በስልሳዎቹ እድሜ መካከል የሚመደቡ፣ ሰፋና ደንደን ያለ ሰውነት ያላቸው ሆኖ ክቡና በስሱ የተላጩት ጺማቸው በተፈጥሮ ብልህና አዋቂ መሆናቸውን ያጋልጣል::

የሚጎድል ነገር ቢኖር እንደ አብዛኛዎቹ የኢትዮጵያ ሹማምንቶችና የጦር መሪዎች በራስ ቅላቸው ላይ ያ ጎፈሬ አለመኖሩ ብቻ ነው:: አዎ ራስ ካሣ መላጣ ባይባሉም የራስ ፀጉራቸው መሳሳቱ ያስታውቃል::

ራስ ካሣ ልክ እንደ ልጃቸው እንደ ደጃዝማች ወንድወሰን ሁሉ እጅግ ልብ በሚነካ ሁኔታ ከልባቸው በደስታ ተቀበሉን:: ረጅሙን የኢትዮጵያውያን ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ ቀጥለው በአዲስ አበባ ስላሉ አዳዲስ ዜናዎች ሰረጅም ጊዜ በዝርዝር ሲጠይቁኝ እኔም ለጥያቄያቸው የምችለውን ያህል ከመለስኩ በኋላ ንጉሠ ነገሥቱ በእጃቸው ዕፊው የሰጡኝን የመሸኛ ደብዳቤ እየሰጠሁ ስለተላክንበት ግዳጅ በሰፊው አስረዳሁ::

በዚህ መልኩ ስለአዲስ አበባና በአዲስ አበባ ለጦርነቱ ስለሚደረገው ዝግጅት በማውራት ላይ እንዳለን ራስ ካሣ ድንገት የጨዋታ መስመራቸውን ለውጠው "ጣሊያኖች የመርዝ ጢስ ይጠቀሙ ይሆን?" አሉኝ:: ባልጠበኩት ሁኔታ ስለጠየቁኝ በጣም ተገረምኩ:: ግን ምን መመለስ ነበረብኝ? "ሊጠቀሙ ይችሉ ይሆናል:: ሞሶሎኒ አያደርግም አይባልም" አልኳቸው::

"ቢጠቀምም እኛ መፍራት የለብንም" አሉ ፍጹም በራስ መተማመን በሞላበትና ምስጢራዊ በሆነ ቃል:: ቀጥለውም፣

"ሌት ተቀን የጢስ መርዝ መከላከያ ጭንብል (ማስክ) እየሰራን ነው" አሉኝና አሽከራቸውን ከማየታቸው ፈጥኖ አመጣና አንድ ከተራ ጨርቅ የተሰራ በራስ የሚጠለቅ በሁለቱም አይኖች ትክክል መስታወት የተለጠፈበት ጭንብል መሳይ ቡቱቶ አሳዩኝ:: ቀጥለውም ያ ደግነት የተሞላበት ፈገግታቸው ሳይለያቸው "ታድያ ምን ትላለህ?" አሉኝ:: እኔ ግን በጭንብል መሳይ ነገሩ ላይ የተለጠፉትን መስታዎቶች እንዳየሁ ቤተ መንግሥት ስገባ ጀምሮ ግራ የገባኝ ነገር ተገልጾልኝ የቤቱን መስኮቶች ስቃኝ ባይናቸው ይከተሉኝ ኖሮ ሳቅ እያሉ "የልጄ የደጃዝማች ወንድወሰን ግኝት ነው" አሉኝ::

ቀጥለው አሁንም ሳቅ እያሉ "እና ምን ትላለህ? ማስኩ፣ ጭንብሉ ያው የቀረው ነገር ቢኖር ያ አፍ አካባቢ ተግጥሞ የሚንጠለጠለው ነገር ብቻ ነው" ሲሉኝ

ለዚያውም ቢታላት ኩራት፣ ምን ልበላቸው። እንኳን ይኼ ተራ ኋላ ቀር ለዚያውም ማጣሪያ /ፊሊተር/ የሚባል ነገር ያልፈጠረበት ነገር ቀርቶ የራስ ካሣ ጦር እስ የተባለ ዘመናዊ ማስክ ወይም ጭንብል እንኳ ቢኖረው ጣሊያኖች ያላቸውን ዘመናዊ የጦር ሜዳ ፐሊን ጋዝ ከተጠቀሙ እንደማያድናቸው ልቤ እያወቀ ምን ልበላቸው?

ወደፊት እንደምናየው ጣሊያኖች ይኼንን የጦር ሜዳ የጋዝ መርዝ ያለ ርህራሄ ተጠቅመውበታል። የኚህን ሰው ተስፋና ምኞት መቀማት ነበረብኝን? በኋላ ከማረፊያ ቤቴ ገብቼ አሰቀስኩ። አልቻልኩም ደጋግሜ አነባሁ።

መስቀል

ደብረ ታቦር የገባሁት በመጀመሪያው ቀን የመስቀል በዓል ላይ ነበር። መስቀል በኢትዮጵያውያን ባህልና እምነት የክረምቱ ወራት ማብቂያ የመጨረሻዎቹ ሶስት ቀናት ናቸው።

እስካሁን ሁሌም ከሰዓት በኋላ ይዘንባል። ምንም እንኳን ጠዋት ሰማዩ የጠራ እና የዳመና ዘር በሰማዩ ላይ ለምልክት እንኳን ባይታይም ከሰዓት በኋላ ከየት መጣ ሳይባል እንደጉድ ይዘንባል።

እንግዲህ እንደ ኢትዮጵያውያን እምነት እንዲህ ከሰዓት በኋላ ድንገት ደርሶ የሚንጎደጎደው ዝናብ ለሚቀጥሉት ሁለት ቀናት ይቀጥልና ጥሎን ይኼዳል ማለት ነው። ...ነገ ...ከነገ ወዲያ... በሶስተኛው ቀን የመስቀል በዓል ፀሐይ ደምቃ ትወጣና እስከሚቀጥለው ክረምት ድረስ በየቀኑ ታጅበናለች ማለት ነው። እምናም እንዲህ ነበር፤ ሃቻአምናም፤ ከዚያም በፊት እንዲሁ ነበር። አሁንም ወደፊትም እንዲሁ ይሆናል።

የክረምቱ ቀናት ሁሌም በተወሰኑ ቀናት ነው የሚያልቀው። ማንም ምንም ነገር ማድረግ አይችለውም። ይሁን እንጂ አንዳንድ ጊዜ ከነዚህ ቀናት ሊተላለፍ ይችል ይሆናል በማለት በደብረ ታቦር አሉ የሚባሉ አዛውንቶችን ሁሉ እየዞርኩ ብጠይቅም እንዳቸውም የክረምቱ ወራት ከመስቀል ሶስተኛ ቀን ማለፉን እንደማያስታውሱ አረጋገጡልኝ። ተፈጥሮ ድንቅና የሰው ልጆች ተመራምረው ገና ያልደረሰባት የራሷ የሆነ ምስጢራዊ መተዳደሪያ ደንብ ያላት ይመስላል።

ከደብረ ታቦር ከተማ ትንሽ ወጣ ብሎ ባለ አንድ ትልቅና ሰፊ ሜዳ ላይ የመስቀሉን በዓል ለማክበር ዝግጅቱ አልቋል። በሜዳው ዳር ላይ ቀይ የአበባ ምንጣፍ ተነጥፎ በአበባው ምንጣፍ ላይ የራስ ካሣ ተንቀሳቃሽ ዙፋን ተዘጋጅቶ ይጠብቃል። ራስ ካሣ በመኳንንቶቻቸው ታጅበው መጥተው በዙፋናቸው ላይ ሲቀመጡ ትልቁን ጥላ ከያዘው አሽከር በስተቀር መኳንንቱ ከራስ ካሣ አንድ እርምጃ ያህል ወደ ኋላ ራቅ ብለው ይቆማሉ። የራስ ካሣ የክብር ዘቦች ከራስ እና ከሹማምንቱ ኋላ ግራና ቀኝ በተጠንቀቅ ይቆማሉ። ሁለት ዘመናዊ የእውሮፕላን መቃወሚያ መትረየሶችም ተጠምደዋል። ራስ ካሣ፣ የሰሜን ጦር ጠቅላይ አዛዥ፣ ከንጉሠ ነገሥቱ ቀጥለው በኢትዮጵያ ሁለተኛ ሰው። በስተቀኝ በኩል ትንሽ ፈንጠር እና ከዙፋናቸው ዝቅ ብሎ በተዘጋጀ ቦታ ከብረየር ጋር ከመቀመጣችን የተለያየ ቀለማት ያላቸው ካባ የለበሱና ነጭ ሸሽ የጠመጠሙ በርካታ ቄሶች ወደ አደባባዩ እየቀረቡ መጡ።

እየቀረቡ ሲመጡ እንደማየው እያንዳንዱ ቄስ በግራ እጁ ጭራ ይዞ ግራ ቀኝ እያወዛወዘ ዝንቦችን ለማባረር ይሞክራል። በቀኝ እጁ ደግሞ በደማቅ ቀለማት ያሸበረቀ ጥላ ይዟል።

ቄሶቹ እንዲህ በቀለማት እንዳሸበረቁ በህብረት መጥተው በራስ ካሣ ዙፋን ፊት ቀርበው ትንሽ ከጸለዩ በኋላ የቄሶቹ አሰቃ ድንገት ፊቱን አዙሮ በጣም ዝግ ባለ እርምጃ ወደፊት ሲሄድ ራስ ካሣ ከዙፋናቸው ላይ ወርደው ጠመንጃቸውን ከጠመንጃ ያዣቸው ተቀብለው ካነገቱ በኋላ ቄሱን እየተከተሉ እኛም እንድንከተላቸው በምልክት አዘዙን። በዳከየ እርምጃ የሚያዘግመውን ቄስ እየተከተልን ያንን በእንጨት የተሰራ ፒራሚድ የሚመስለውን ዳመራ መዞር ጀመርን።

ከፊት ያ ቄስ፣ ከቄሱ ኋላ ራስ ካሣ፣ ከዚያ እኔ፣ ብረየር፣ ደጃዝማች ወንድወሰን ካሣ፣ በድሮንድ ለጥይበሉ ሆነን በህብረት ስንከተል፤ ከኛ ኋላ ሌሎች ሹማምንቶች፣ ከሹማምንቶች ቀጥሎ ተራው ወታደር፣ ከተራው ወታደር ቀጥሎ ከደብረ ታቦር ለመስቀል በአል የመጣው ህዝብ እያዘገመ ያንን የእንጨት ፒራሚድ ሶስት ጊዜ ከዞርን በኋላ ራስ ካሣ ያነገቱትን ጠመንጃ ለጠመንጃ ያዣቸው አቀብለው በዙፋናቸው ተቀመጡ። እኛም በተዘጋጀልን ወንበሮች ተቀምጠን መኳንንቱ እንደየ ማዕረጋቸው ቦታ ቦታቸውን እንደያዙ ከየት መጣ ያልተባለ ንፋስ አዘል ዝናብ መዝነብ ሲጀምር ያ ሁሉ ህዝብ ነፍሴ አውጪኝ ወደ ደብረ ታቦር ዝብርቅርቁ በወጣ ሁኔታ መሮጥ ጀመረ።

የኛ መኖሪያ

በደብረ ታቦር የምንኖረው በሲዊዲናዊው ሚሲዮናዊ ቤት ሲሆን መኖሪያችንም አንዲት ተራ ክፍል ነች። የክፍሏ ግድግዳዎች ከኤስኪሞዎች ቋንቋ በስተቀር በመላው አለም ቋንቋዎች የተጻፉ ጋዜጦችና መጽሔቶች ተለጥፈዋል። ጊዜ ላለው ሰው ጥሩ ቋንቋ መማሪያ ወይም ማዳበሪያ ስሌዳ ትሆን ነበር።

የኛ አስተናጋጆች ባልና ሚስቶቹ አቶ እና ወይዘሮ ፓልም ይባላሉ። ባለወርቃማ ፀጉሩ አቶ ፓልም ከጨብራራ ፀጉሯ ሚስቱ ጋር በደብረ ታቦር ሲኖሩ ሶስተኛ አመታቸውን ይዘዋል።

ባልና ሚስቶቹ ሚስዮናውያን ለኛ ባዘጋጁት ክፍል ውስጥ ሶስት ደረቅ የሳር አልጋዎች ያሉ ብርድልብስና አንሶላ ተዘርግተውበታል፡፡ ቀጥሎም ሶስት አነስ አነስ ያሉ ሳጥኖች እንደ ወንበር እንዲያገለግሉን ከአንዲት ከተራ እንጨት ከተሰራች ጠረጴዛ ጋር በቦታ ቦታቸውን ይዘዋል፡፡

ለስተኛዋ አልጋ ቀድማ ተይዛለች፡፡ ባለቤቷም በአርባዎቹ እድሜዎች ውስጥ ያለውና ኢትዮጵያ ውስጥ የተወለደው ግብጻዊው አቶ ያቆብ ነው፡፡ በአቶ ያቆብ ላይ ዘመናዊ መስሎ የሚታይ ነገር ቢኖር ገና ዱሮ በሃሩር ቀለሙን የለቀቀ ኮትና አንድ ጨምዳዳ ሱሪ መልበሱ ብቻ ነው፡፡ ሁሌም ማታ ማታ ደም በምትመስለው የዲናሞ መብራት እየተረዳ ለመብራቷም እየሰገደ አቶ ፓልምን ያመሰግናል ....merci, monsieur Palm፡፡

ብቻ ይቺ መብራት ብዙ ሳትቆይ ትጠፋለች፡፡ አቶ ፓልም ይችን በቤንዚን የምትሰራ ዲናሞ ከአውሮፓ ድረስ ቢያስመጣም ቤንዚን የሚያገኘው ወይ ከአዲስ አበባ አሊያም ከሱዳን ከመሆኑም በላይ ማግኘቱም ከባድና ረጅም ጊዜ የሚፈጅ በመሆኑ የዚቺን ዲናሞ ሞተር ለአጭር ጊዜም ቢሆን የሚያስነሳው እንዲህ አይነት ልዩ በሆኑ ቀናት ብቻ ነው፡፡ አቶ ፓልም ቤንዚን መቆጠብ አለበት፡፡

በሁለተኛው ቀንም የመስቀሉ በአል ቀጥሏል፡፡ እኩለ ቀን ላይ በራስ ካሣ ቤተ መንግሥት እንግዶች ሆነን ለምሳ ተቀመጥን፡፡ የምሳው ግብዣ የጤፍ እንጀራ በተለያዩ ወጦች ነበር። ራስ ካሣ ከፍ ባለ ቦታ ምንጣፍ ተነጥፎላቸው በዙፋናቸው ላይ ተቀምጠዋል፡፡ ለኔና ለባልደረባዬ ለቪሊም ብረየር ከጎናቸው በስተቀኝ የክብር ቦታ አዘጋጅተውልናል — አንድ ጠረጴዛና ሁለት ወንበሮች፡፡ ሌሎች እንግዶች እንደየማእረጋቸው አራትም አምስትም እየሆኑ ባንድ ማዕድ ዙሪያ በደረቁ መሬት ላይ ተቀምጠዋል፡፡

ከምሳ በኋላ በፈረስ ሆነን ከቤተ መንግሥት ወጥተን ህዝብ ተሰብስቦ ወደሚጠብቅበት ሜዳ አመራን፡፡ በብዙ ሺህ የሚቆጠር ሰው ይጠብቀን ነበር፡፡ በደጃዝማች፣ በፊታውራሪ፣ በቀኛዝማች እንዲሁም በጭቃ ሹም የሚመራው የገበሬ ወታደር ታማኝነቱን ለራስ ካሣ እየገለጸ እየፎከረና እየሸለለ አለፈ፡፡

አንድ ቆፍጣና በራስ ካሣ የሜዳ ላይ ተንቀሳቃሽ ዙፋን ፊት ቀርቦ ጎራዴውን እያወናጨፈ "በዚህ ጎራዴ አስራ አምስት አንበሶች ገድያለሁ፤ ሁለት እጥፍ ጣልያንም እገላለሁ" እያለ ይፎክራል፡፡ ከማልረሳው ለመጥቀስ ያህል አንድ አዛውንት ጎራዴያቸውን እያወናጨፉ "በዚህ ጎራዴ ከእምዬ ምኒልክ ጋር አስር ጣሊያን ገድያለሁ፤ አሁንም መቶ እጥፍ ጣሊያን እገድላለሁ" የሚለው ፉከራ አንዱ ነው፡፡

ሌላው አንድ በግምት ሀያ ዓመት የማይሞላው ጎረምሳ ሲናገር "እኔ ወጣት ነኝ፤ ከዚህ በፊት ጀግንነቴንና ታማኝነቴን ለማሳየት እድል አልነበረኝም፡፡ አሁን ግን ሀገሬን ሊወር የመጣን ጣሊያን እንደ ቆሎ እቆላዋለሁ፡፡ አንዱንም አልምርም" ሲል

በሰሜት ተናገረ፡፡ ያ ልጅ ከሁለት ወንድሞቹ ጋር አባቱን አጅቦ ከባሌ ራስ ካሣን ብሎ የመጣ የመሀል ሀገር ሰው ነበር፡፡

በእነዚያን ዕለት በዚያ ሰፊ ሜዳ አንዳንዶቹ ጦራቸውን ሹቀብ አንስተው ሲፎክሩና ሲሸልሉ ጦሩ ከጃቸው አምልጦ ራስ ካሣን ከዙፋናቸው እንዳያፈሩቸው ብሰጋም እሳቸው ግን ላፍታም ንቅንቅ አላሉም ነበር፡፡ በተለይ አንዳንዶቹ ወደሰማይ የሚተኩሱት ጥይት በጆሮዬ ስር ሽው ሲል መቶ ጊዜ ደንግጫለሁ፡፡ ራስ ካሣ እንደሁልጊዜው ሁሉ በተረጋጋ ሁኔታ በዙፋናቸው ተቀምጠው ጭራቸውን ቱቻ ያወዛውዙ ነበር፡፡

ፉከራ

ይኼንየመሰለውን የበዓል አከባበር ኢትዮጵያውያን "ፉከራ" ይሉታል፡፡ ኢትዮጵያውያን ለመስቀል በዓል ዓመቱን ሙሉ ሲዘጋጁና በታላቅ ጉጉት "ነገ ጣፋጭ ይገባልኛል" እንደተባለ ህፃን መስቀልን ዓመቱን ሙሉ ይጠብቃሉ፡፡

በፉከራ ወቅት ማንም ሰው በሚያውቀውም ሆነ በማያውቀው ሰው ፊት ቆሞ የፈጸማቸውን ወይም ወደፊት ሊፈጽማቸው ያሰባቸውን ጀብዱዎች በታላቅ ድፍረት እየፎከረ፣ እየሸለለ መናገር ቅዱስ መብቱ ነው፡፡

እነዚህ ፎካሪ ጀግኖች በተሰበሰበው ህዝብ ፊት ሹሞቻቸው የበደሏቸውን እያንዳንዷን ነገር እያነሱ ምንም አይነት በቀልና ቅጣት ሳይገጥማቸው መናገርም ይችላሉ፡፡ ይቺ ፉከራ ትልቁን ጌታ ራስ ካሣ ሳይቀር ትነካለች፡፡ ዛሬ ማንም ማንንም ቢወቅስ፣ ቢወነጅል፣ ቢሰድብ አይቀጣም፡፡ አዎ እነዚህ ጀግኖች ነገ ራስ ካሣን ተከትለው "ዘራፍ የካሣ አሽከር" ብለው ወደ ጦር ሜዳ ሊሄዱ፣ በራስ ካሣ ችሎት ተበድለውም ከሆነ የተበደሉበትን ነገር በአደባባይ መናገሪያው ብቸኛ ቀን ዛሬ ነውና ያለ ምንም ፍርሃት እየፎከሩ ይናገራሉ፡፡

እነሆ ዛሬም ከነዚህ ጀግኖች ጠረኞች መካከል የተወሰኑ በገዢዎቻቸው፣ በሹሞቻቸው ያልተደሰቱ፣ የተበደሉ፣ ተነስተው በደላቸውን በትልቁ የራስ ካሣ ዙፋን ፊት እንዲዳኙ እየፎከሩ ሹሞቻቸውን እየወቀሱ እና እየሰደቡ ሸለሉ፣ ፎከሩ፡፡

ከነዚህ ጀግኖች አንዱ በቀጥታ ከዚህ ቀደም በራስ ካሣ ችሎት ያለ ሃጥያቱ በግፍ ስለተፈረደበት ፍርድ አንስቶ ራስ ካሣን ሙልጭ አድርጎ ሰደባቸው። ራስ ካሣ በዚህ ጀግና ድፍረት ከመናደድ ይልቅ ስቀው ድፍረቱን እያደነቁለት እያለ የራስ ካሣ የክብር ዘብ ወታደሮች የመስቀል በዓል ጥንታዊው ወግና ባህል ከሚፈቅደው ውጪ ስለሆነ ይኼንን ጀግና ከፉከራው መሀል ጎትተው አወጡት፡፡ ከሰዓት በኋላ ባይሆንና ያ አደገኛ ዝናብ መጥቶ ህዝቡን ባይበትነው ኖሮ ፉከራው ሽለላው እስከ ምሽቱ ድረስ በቆየ ነበር፡፡

ሶስተኛ እና የመጨረሻው ቀን የመስቀል የመዝጊያ በዓል አከባበር ከሁሉም ቀናት እጅጉን በጣም የተለየና የደመቀ ነው። ራስ ካሣም ለበዓሉ መዝጊያ ግብር ያበላሉ። በዚህ ግብር ላይ ማንኛውም ተራ የራስ ካሣ ገባሬ ጭሰኛ እና አልባሌ ሰው ሳይቀር የመግባት መብት አለው።

ለግብሩም ጠቅላላው የራስ ካሣ ግቢ በነጭ ጨርቅ ተሸፍኖ ከሩቅ ላየው ሰው እጅግ በጣም፣ በጣም ትልቅ ድንኳን ይመስላል። ይኼ ግዙፍ የግቢ ድንኳን በተለያዩ ክፍሎች ተከፋፍሎ ለግብር ተዘጋጅቷል።

ራስ ካሣ እንደወትሮው ሁሉ ከፍ ብሎ በተሰራላቸው መድረክ ላይ የአበባ ምንጣፍ ተነጥፎና የኢትዮጵያ ባንዲራ ከጀርባቸው ተሰቅሎ በዙፋናቸው ላይ ተቀምጠዋል። እኛም ትንሽ ከሳቸው ዝቅ ብሎ የሽራ ወንበሮችና ጠረጴዛ ተዘጋጅቶልን ጎን ለጎን ተቀምጠናል። ዛሬ ያለወትሮው ግብሩ የቀረበው በመሶብ ፋንታ በብር ሰሃኖች ከብር ሹካና ቢላ ጋር ነው። ከየት እንዳመጡት ግን እግዜር ይወቀው።

ኢትዮጵያውያን ከፍተኛ የሚባሉት መኳንንቶች ሳይቀሩ የሚበሉት በእጃቸው ነው። እመኑኝ በእጅ መብላት ራሱን የቻለ ጥበብና ልምድ ይጠይቃል። ቀላል አይደለም።

ከፍተኛ የሚባሉት ሹማምንቶች በየመሶቡ ዙሪያ ነጭ ሸማቸውን እንደለበሱ በበርጩማዎች ላይ ተቀምጠዋል። አነስ ያሉ ሹማምንቶች ደግሞ ወረድ ብለው በመሶቡ ዙሪያ በደረቁ መሬት ላይ ተቀምጠዋል። ትልልቅ ድስቶች የያዙ አሽከሮች በግብርተኛው መሀል እየተዘዋወሩ አንድ-ሁለት-ሶስቱን እንጀራ ወጥ ውስጥ ይነክሩና በወጥ ለውሰው በመሶቡ ላይ ካደረጉ በኋላ በያዙት ትልቅ ጭልፋ ወጡን ደጋግመው እንዳወጡላቸው ግብሩ ይጀምራል።

ሌሎች ጠብደል አሽከሮች ሁለት ሁለት እየሆኑ በአጣና እንጨት ለሁለት የተሸከሙትን አንድ አራተኛ የበሬ ስጋ ይዘው በእያንዳንዱ መሶብ አጠገብ ሲቆሙ ሹማምንቱ በቀኝ እጁ ቢላውን ይይዝና በግራ እጁ ስጋውን አገላብጦ ካየ በኋላ ደህና መስሎ ከታየው ቦታ ላይ የሚበቃውን ያህል ላፍ አድርጎ በመቁረጥ ስጋውን በግራ እጁ እንደያዘ ለአንድ ጉርሻ ይበቃል የሚለውን በግምት ይመጥንና በጥርሱ ነክሶ ከታች ወደላይ ላፍ አድርጎ ይቆርጥና ይበላል። እንዲህ ከታች ወደ ላይ ስጋውን ላፍ አድርጎ ሲቆርጥ አፍንጫውንም ጨምሮ ያለመቁረጡ ተአምር ነው።

ግብር ላይ የተቀመጠው ሹማምንት ግብሩን እየበላ ያሻውን ያህል ጠጅ ደጋግሞ ያለ አንዳች ይሉኝታ ይጠጣል። እንዲህ አይነቱ መስተንግዶ አንድ ሰዓት ያህል ጊዜ ይፈጃል። በዚች አንድ ሰዓት በማትሞላ ጊዜ ውስጥ በነዚህ ታዳሚዎች መሶብ ዙሪያ ግማሽ ያህሉ የሙሉ በሬ ስጋ ድራሹ ይጠፋል።

ራስ ካሣና የተወሰኑ እጅግ ከፍተኛ መኳንንቶች እኛንም ጨምሮ በቦታቸው ሲቀሩ የቀረው የቤታች ሹም ጮማ በጮማ የሆነውን እጁን በራሰ ጸጉሩና በጢሙ ጠራርጎ ቦታውን ለሌሎች ይለቃል።

እነዚህ መጀመሪያ ግብር የገቡት ጠግበው ሲወጡ ሌሎች እየገቡ እየበሉና እየጠጡ፣ እነዚህም ለሌሎች ቦታቸውን እየለቀቁ ሲወጡ፣ ግብር ያልገቡት ሲገቡ፣ በሺዎች የሚቆጠሩ ግብርተኞች ግብር ገብተው ከወጡ በኋላ አዳዲስ የታጩ ሹሞች ራስ ካሣ ፊት ቀርበው ሹመታቸውን እግር ስመው ይቀበላሉ ። ከነዚህ ዛሬ አዲስ ከተሾሙት ሹማምንት መካከል ወጣቱ የራስ ካሣ ሶስተኛ ወንድ ልጅ አስፋ ወሰንም ይገኙበታል።

ወጣቱ አስፋ ወሰን ካሣ በአባቱ ፊት ቀርቦ ለክብራቸው እግራቸውን ስሞ ሲነሳ አባቱ ጥቁር ሆኖ በወርቅ የተሸቆጠቆጠውን የደጃዝማቾችን ካባ ለልጃቸው ሲያለብሱ ታላቅ የአባትነት ኩራት በፊታቸው ላይ ይነበብ ነበር።

ከእንዲህ አይነት የመስቀል በዓል አከባበርና ግብር በጥቅሉ “ትእይንት” ማግስት ስራዬን ለመጀመር ስነሳ ራስ ካሣ ክሩቤል የተባለ በመጠኑ ፈረንሳይኛ የሚችል ወጣት አስተማሪ ይርዳህ ብለው ላኩልኝ። በመቀጠልም ወታደሮቻቸው እንደንጉሡ ነገሥቱ የክብር ዘበኛ ወታደሮች እንዲሰለጥኑላቸው አዘዙኝ።

ይሁን እንጂ ራስ ካሣ ያልተገለጠላቸውና የዘነጉት ነገር ቢኖር እንደኛ የንጉሠ ነገሥቱ ወታደሮች ለአመታት ከሲዊዲንና ከቤልጂየም በመጡ መኰንኖች ወታደሮች ለረጅም ጊዜ መሰልጠናቸውንና፣ የእሳቸው ወታደሮች ለስልጠና ያላቸው ጊዜ ግፋ ቢል በቀኖች የሚቆጠር ብቻ መሆኑን ነበር።

በነጋታው በማለዳ ተነስቼ ልክ ፀሐይ እንደወጣች ወደ ማሰልጠኛው ቦታ፣ ከደብረ ታቦር ወጣ ብሎ ካለ ሜዳ፣ ከአስተርጓሚዬ ከክሩቤል ጋር ስደርስ በቦታው የነበሩት አምስቱን ኢትዮጵያውያን ማለትም በቤልጅየሞች ለወራት የማሰልጠን ትምህርት የወሰዱ እና በንጉሠ ነገሥቱ የራስ ካሣን ጦር እንዲያሰለጥኑ ከአዲስ አበባ የተላኩ መኰንኖችን ከጥቂት የራስ ካሣ ወታደሮች ጋር አገኘሁ። ስልጠናው መጀመር የነበረበት ከጠዋቱ አንድ ሰዓት ጀምሮ ነበር። ይሁን እንጂ ሌላ ሁለት ሰዓት አለፈ። ወደ ማሠልጠኛው ስፍራ ብቅ ያለ ግን ማንም ሰው አልነበረም።

ቢቸግረኝ ክሩቤልን ወታደሮቹ የት እንዳሉ? እንዲጠይቅ ላኩት። ወዲያው ከአምስቱ መኰንኖች አንዱ ጠጋ ብሎ “ጌታዬ የኛ ወታደሮች እንደ ፈረንጆቹ በካምፕ አይኖሩም። ግማሹ ከቤተሰቡ ጋር እቤቱ፣ ሌላው ደሞ ዘመድ አዝማድ ተጠግቶ፣ የቀረው ደግሞ እንዳቅሙ በየጥሻው በቀየሳት ጎጆ (ድንኳን) ነው የሚኖረው። እና እዚህ እስኪደርሱ ድረስ ትንሽ ጊዜ ይፈጃል" አለኝ።

በእንዲህ አይነት ሁኔታ የጀመርነው ስልጠና ፍጹም ተስፋ አስቆራጭ ነበር። ከአምስቱ መኩንኖች አንዱ ወደ 300 የሚሆኑ የባላገር ወታደሮች ወደጎን ወስዶ ከብዙ ልፋት በኋላ እንደነገሩ ማሰለፍ ቻለ። ሌላው ትልቁ ችግር አምስቱም ወታደሮች ማለት በቤልጂየሞች ሲሰለጥኑ ወታደራዊ ትእዛዞችን የሚያውቁት በፈረንሳይኛ ቋንቋ ስለነበር የገበሬው ወታደር ወታደራዊው ትእዛዙ ተተርጉሞ ምን ማድረግ እንዳለበት እስኪገባው ድረስ "ቀም" ለማለት እንኳ ጥቂት ጊዜ ይፈጅ ነበር። በኋላ ከሩቢል ወታደራዊ ትእዛዞችን ወደ አማርኛ ተርጉሞ ከብዙ ጊዜ ጥረት በኋላ፣ ወደፊት| ...ቀኝ ...ግራ ...ግራ... ቀኝ ...ማለትና ወታደሩ መርገጥ ጀመረ።

በእንዲህ አይነት ሁኔታ የተጀመረው ስልጠናችን ገና ብዙ ፈተናዎች ይጠብቁት ነበር። የራስ ካሣ ጦር እንደዘመናዊ ጦር አንድ ወጥ አመራር አልነበረውም። ራስ ካሣ ራሳቸው ደሞዝ የሚከፍሉት ጦር ማለትም ራሳቸው በቀጥታ የሚያዙት ጦር በሺዎች ቢቆጠርም እሳቸውን ብሎ ከመጣው ጦር ጋር ሲነጻጸር ግማሽ እንኳን አይሆንም ነበር።

ጦሩ ታማኝነቱና ታዛዥነቱ ላመጣው ደጃዝማች፣ ፊታውራሪ፣ ቀኛዝማች፣ ግራዝማችና አስከታች ወርዶም የበታች ሹም ብቻ ነው። እናም ይኼን የተበታተነ ጦር አዋቅሮ ማደራጀት አስፈላጊ በመሆኑ ጦሩን ከታች ከትንንሾቹ ሹማምንቶች ጀመርኩ። ይኼም ትልቅ ችግር ነበር።

ለምሳሌ፣ አንድ ሹም የራሱን ጦር ይዞ ከማሰልጠኛው ቦታ ጥሎ ሄደ። እንዲመለስና በስልጠናው እንዲቀጥል ስንሞክር እምቢ ስላለ ምክንያቱን ብጠይቅ "እንደምን ሆኖ እኔ ለካሣ 100 ሰው ይገኛ መጥቼ 50 ሰው ብቻ አዛለሁ። እንደምንስ ከእናቱ ጉያ ነጥቄ ያመጣሁትን ልጄን ለሌላ ሰው እንዲያዘው እሰጣለሁ። የመጣው ቢመጣ አንድም ሰው ከኔ አይለይም፤ ለእናታቸው ቃል ገብቻለሁ" ያለውና በኋላ በራስ ካሣ ልመና እና ተግሣጽ በማግባባት የተመለሰውን መርሳት ፈጽሞ አይቻለኝም።

ብቻ በዚህ መልኩ አልፎ አልፎ ራስ ካሣም እየሸመገሉልን መስመር መስመር ይዞ ሳለ፣ አንድ ዝናር በዝናር የሆነና ጠመንጃ ያነገተ ወጣት ከማሰልጠኛው ሜዳ መሀል ቆሞ ስራችንን እንዳንሰራ አገደን። ከስልጠናው ቦታ እንዲሄድና ስራችንን መስራት እንችል ዘንድ ቢጠየቅ አሻፈረኝ በማለቱ ምክንያቱን ባስጠይቅ፣ "ገና ትናንት ማታ ከሸዋ ሜጫ ደብረ ታቦር መድረሱንና ከ300 በላይ ወታደሮች ስላሉት ስልጠናችንንም በጣሙን ስላስደሰተው የኔም ጦር ይሰልጥንልኝ ብሎ ንትንቅ አልልም ማለቱን ተረዳሁ። የዚያን ተዋጊ ወጣት መሪ ተለማማጭ አይኖች ያየ ሰው እንደምን ቆይ፣ ተራ ጠብቅ ሊል ይችላል? እና ሌላ አንድ አዛዥ ጨምረን ስልጠናችንን ቀጠልን።

በእንዲህ አጭር ጊዜ ውስጥ ከየጎጆው የመጣውን የሰላሙ ጊዜ ገበሬ፣ የጠላት ወረራ ጊዜ ወታደሩን አስተምሮ፣ ስነስርአት አስይዞ፣ ወታደር ማድረግ ለሰው ልጅ የማይቻል ይመስል የነበረውን ስራ ጨርሰን ለራስ ካሣ ጦሩ ወታደራዊ ሰልፍ ለማሳየት ዝግጁ መሆኑን አሳወቅን።

ደብረ ታቦር በታሪኳ እንዲህ አይነት ትእይንት አይታ አታውቅም ነበር። ጦሩ በራስ ካሣ ፊት ሰላምታውን እያቀረበ በታላቅ ስነስርአት ሜዳውን ዞሮ በየመቶ ምድቡ ከራስ ካሣ ዙፋን ፊት ለፊት በተጠንቀቅ ሲቆም የራስ ካሣ ደስታ ወሰን አልነበረውም።

7

ጦርነቱ ተጀመረ

"ራስ ካሣ የምትናገረዋን ሳጥን ልኮልሃል ጌታዬ" አለ፣ እጅግ በሚያስደንቅ ሁኔታ በተጠንቀቅ ቆሞ ወታደራዊ ሰላምታ እየሰጠኝ:: ምንም እንኳን በባዶ እግሩ ቆሞ የተጨማደደች ኮፍያውን ቢደፋም ቆፍጣና ወታደር እንደሆነ አያጠራጥርም ነበር:: "ሳጥኗ መናገር ታቆመች ሰንብታለች አሉ" አለኝ አሁንም በተጠንቀቅ እንደቆመ::

በረንዳው ላይ አንድ ከፍና አርጀት ያለች ሳጥን ተቀምጣለች:: ሣጥኗ ገመዶቿ ተጎልጉለው ወደውጭ ወጥተዋል:: እንደ ራዲዮ ነገር መሆኗ ነው:: አዎ መጀመሪያ አካባቢ እንደሙከራ ከተሰሩት ባለ አራት መብራት ራድዮዎች አንዷ መሆኗ ነው:: በርከት ያሉ ምሽቶች ስፈታና ስገጥም ሰነባብቼ አንድ ቀን ያቺ ሳጥን መናገር ጀመረች:: ሳጥኗ ቀስ እያለችም ወዳጆች ታፈራልኝ ጀመር::

ሳጥኗ መናገር ከጀመረችበት ቀን ጀምሮ ሁልጊዜ ማምሻው ላይ ሁለት የማይነጣጠሉ ከአባይ ማዶ የመጡ የሸዋ ሹሞች መጠጫቸውን ይዘው በበረንዳዬ ይቀመጣሉ:: ብዙ ጊዜ ወደ ቤት እንዲገቡ ብጋብዛቸውም አሻፈረኝ ስላሉ ሁሌም በረንዳዋ ላይ ቁጭ ብለን መጠጫችንን እየማግን ሳጥኗን እንሰማ ነበር:: አሁን ትንሽ አማርኛዬ ተሻሽሎ መናገር ስለቻልኩ በጎደለው ክሩቤል እየሞላ ሳጥኗ የምትቀባጥረውን እየተረጎምኩላቸው ስንስቅ እናመሽ ነበር::

አንድ ቀን ጠንከር ያለ ሁካታ ያለበት ድምጽ ሰማን:: ሳጥኗን ቀስ ብዬ ላስተካክላት ሞከርኩ:: ሁካታው ግን እየበረታ መጣ:: አልፎ አልፎ ኢትዮጵያ ...ኢትዮጵያ ... የሚል የብዙ ሺ ህዝብ ድንፋታ ይሰማል:: ቀጥሎም የሞሶሎኒ ድንፋታ ጀመረ:: አርባ ዓመት ጠብቀናል በቃ አለቀ! ሞሶሎኒ የኢትዮጵያን ስም በጠራ ቁጥር በፓላዞ አደባባይ የተሰበሰበው ህዝብ ይጮሃል:: በዚያች ሳጥን የሚጮኸው ህዝብ ደስተኛ ይመስላል:: እኔና ወዳጆቼም የሆነ ነገር ይወረን ጀመር:: እየወረረን ያለው ስሜት ግን ደስተኛ አልነበረም:: ወዳጆቼ ዛሬ ትርጓሜ አላስፈለጋቸውም፤ ገብቷቸዋል:: "መጣሁ ማለቱ ነው ይኼ ሙሶሎኒ" አሉና ድንገት ብድግ ብለው ወደ ስራቸው ሄዱ::

እኔም ወደ ክፍሌ ስገባ ያቆብ የራስ ካሣን ሽልንጎች እየቆጠረ ወደ ሳጥኑ ይከታል:: ልረብሸው አልፈለኩምና ወደውጭ በመውጣት ከወትሮው በተለየ ሁኔታ ደብረ ታቦርን ቁልቁል አየኋት:: አሳዘነችኝ:: ወዲያው የቤኒቶ ሞሶሎኒን ድንፋታ እናቴ ስትሰማ ስጋቷ ታየኝና አዘንኩ:: ምን እየሰራሁ ነው ብዬ ራሴንም ደጋግሜ ጠየኩት::

ኢትዮጵያን ማንም አይረዳትም:: ብቻዋን ናት:: ሞሶሎኒን ሀሳቡን እንደገና እንዲያይ የሩስያ የማስፈራሪያ ቃል እንኳ አላቆመውም:: ምን ያድርግ? ፈረንሳዮችና እንግሊዞች አይዞህ፣ ከእግዚአብሔር የተሰጠህ ቅዱስ መብትህ ነው ብለውታል:: አሜሪካ እንኳ ሳትቀር በተዘዋዋሪ ደግፈዋለች:: አርፈሽ ተቀመጭ፤ ይኼ ነጻነት ነጻነት የምትይው ትግልና መፈራገጥ ለመላላጥ ነው ብላታለች:: አይ ኢትዮጵያ!

በደብረ ታቦር ያለሁ ብቸኛ አውሮፓዊ መሆኔ ሲታወቀኝ ሀዘን ተሰማኝ:: ወዲያው ለዚች ለተቀደሰች ሀገር ከነዚህ ምስኪን የገበሬ ወታደሮች ጎን በታላቅ ድፍረትና ጀግንነት መውደቅ በእግዚአብሔር የሚታደሉት ታላቅ ፀጋ መሆኑን ስረዳ ልቤ በደስታ ተሞላች:: ከዚች ቅጽበት ጀምሮ ኢትዮጵያዊ ሆኛለሁ:: አዎ ያ ወጣት እንዳለው የሀገሬን ድንበር ጥሶ የሚመጣን ወራሪ ጦር እንደቆሎ እቆላዋለሁ፤ እንደሙጃ እዘረጋዋለሁ፤ አጭደዋለሁ::

እንዲህ ብቻዬን ስፎክርና ስሽልል ራስ ካሣ የሰጡኝ "አንበሳ" አሽከር ቤተ መንግሥት እንደምፈለግ ነገረኝና በሩጫ መንገዴን በሸሎቆዎች እያቆራረጥኩ ስደርስ፣ ቤተ መንግሥት ከወትሮው በተለየ ሁኔታ በሰው ተሞልቷል::

በርካታ ሹማምንቶች በቡድን በቡድን እየሆኑ ይመክራሉ:: አንዳንድ ሹሞች ጥይት ለወታደሮቻቸው ማደል ጀምረዋል:: ራስ ካሣ ከልጃቸው ከደጃዝማች ወንድወሰን ጋር ቆመዋል:: ከፊት ለፊታቸው ሁለት አየር መቃወሚያ መድፎችም ተጠምደዋል::

ራስ የኔ ዜና ብዙም አላስገረማቸውም:: ይልቁን እሳቸው እኔ ያልሰማሁትን

ወሬ ነገሩኝ። ወድያን ወስደው "ራስ ስዩም ደውሎ እንደነበረና የጣልያን አውሮፕላኖች አድዋን በቦንብ መደብደባቸውን" ነገሩኝ። እንዲህ ስለሁኔታዎች ስንመክር አንድ ከመሮጡ ብዛት ሳንባው ባፉ ልትወጣ የደረሰች የሚመስል አሽከር እያለከለከ መጥቶ ለራስ ከንጉሠ ነገሥቱ የተላከ ቴሌግራም ሰጣቸው። ራስ ካሣ ቴሌግራሙን እንደነገሩ አየት አድርገው፤ ወደኔ መለስ ብለው ከፍ ባለ ድምጽ "ተዘጋጁ፤ ነገ እንንቀሳቀሳለን!" አሉ።

"ወዴት?"

"ወደጦር ግንባር!"

"ከንጉሠ ነገሥቱ ትዕዛዝ ደርሶኛል፤ ጦራችንን ይዘን በማለዳ ወደ ሰሜን እንድንሄድ" አሉና ድንገት ዞር ብለው ወደ ቤተ መንግሥት ገቡ።

በኋላ ላይ አሽከርዬው እንዳጫወተኝ ራስ ካሣ እልፍኝ ገብተው በር ዘግተው ለረጅም ሰዓት አለቀሱ። እንባቸውን አነቡ። የራስ ካሣ እንባ የፍርሀት አልነበረም። የራስ ካሣ እንባ ለብዙ ሺህ ያለ ሀጥያታቸው ለሚረግፉ የኢትዮጵያ ልጆች ነበር።

ራስ ካሣ ከልፍኛቸው ወጥተው ከጦሩ ጋር ወደሚንቀሳቀሰው ቤተ ክርስቲያን በመሄድ እግዚአብሔርን ሲማፀኑ ቆይተው ወደ ቤተ መንግሥት ሲመለሱ፣ በርካታ ሹሞች እና ታላላቅ የጦር አበጋዞች በዝምታና በትካዜ ራስ ካሣን ይጠብቁ ነበር።

በርካታው የጦር አበጋዝ አውሮፓም ስለነበር ዘመናዊ መሳርያ የታጠቀውን ወራሪ ጦር ለማቆም የያዙት ወታደር ከቶ እንደማይቻለው ጠንቅቀው ያውቃሉ። ግን ሌላ አማራጭ የላቸውም። እናም ለሀገር፣ ለወገን፣ ለታሪክ ለመሞት ቆርጠዋል።

የገበሬው ወታደር ጦር ሜዳ እስኪደርስ እንደ ህፃን ልጅ ጓጉቷል። አብዛኛው ከራስ ካሣ የተሰጠውን አዲስ ጠብመንጃ በፍቅር ያሻሻል። ይፈታል። ይገጥማል። እዎ በህይወት ለመቆየት የቀረችው ጓደኛው ነችና እፈቀራት፣ ወደዳት፣ አሻሻት፣ ተሸከማት። እዎ አርባ ዓመት ሙሉ ታሪክ ሲሰሙ፣ የጀግንነት ጀብዱ ሲያደምጡ ኖረዋል። አሁን እነሱም እነሆ ጀብዱ ለመፈጸም ቀናቸው ደርሷል። ታላቁን የአድዋ ድል ለመድገም። ባለ ታሪክ እና ባለ ገድል ጀግና ለመሆን።

እውነት ለመናገር ኢትዮጵያ ለጦርነቱ ዝግጁ አልነበረችም። ሞሶሎኒ ግን ለአመታት ሲዘጋጅበት ኖሯል። የሞሶሎኒ ሰላዮች በሃይማኖትና በተለያዩ የሳይንስ ምርምሮች ስም ያልዳሰሷት መንደር፣ ቀበሌ፣ አምባ አልነበረቿም። ከነዚህ ተመራማሪዎች መሀል አንዳንዶቹ በጦር ሜዳ ታላላቅ የጦር መኮንኖች ማዕረግ ይዘው ታይተዋል።

ከስድስት አመታት በፊት ከጓደኛዬ ከአሊዮስ ፖላክ ጋር ምስራቅ አፍሪካን በጉበኘሁበት ጊዜ በሰሜን ኢትዮጵያ በፈረስ ስንዘዋወር ጣልያኖች በኢትዮጵያ ድንበሮች ላይ ጠንካራ ምሽጎች ሲገነቡ ገርሞን ነበር። አዲቋላ ካሲኖ አንድ ከፍተኛ

የጣልያን መኩንን የመሳሪያ ግምጃ ቤት ሹም አሙኑን ሙሉ ወደ ኢትዮጵያ ድንበር የጦር መሳሪያ እንደሚያመላልሱና ይኼ የሚያግዙት መሳሪያ ኢትዮጵያን አይደለም ጠቅላላውን አፍሪካን ለመግዛት ይበቃል ሲል በታላቅ ጉራ ተናግሯል።

ጣልያኖች በትልልቆቹ የኢትዮጵያ ከተሞች ሁሉ የቆንስል ቢሮ ከፍተዋል። እነዚህ የቆንስል ቢሮዎች የሚመሩት ከፍተኛ ወታደራዊ ማእረግ ባላቸው ሰዎች ነበር። ቆንስል የከፈቱበት ዋናው ምክንያትም ግልጽ ነው፤ ለጦርነትና ለስለላ።

ለምሳሌ፤ ጣልያኖች በአድዋ ከሶስት ሚሊዮን ሊራ በላይ የፈጀ ህንጻ ሰርተዋል። በዚያን ጊዜ ኮሎኔል ቶኚ "ይኼ ህንፃ አንድ ቀን የአድዋው ገገር መቀመጫ ይሆናል" ሲል በድፍረት ተናግሯል። የጎንደሩና የመቀሌዎቹ ቆንስሎች በሙሉ ወታደራዊ መኮንኖች ናቸው። የደሴው ቆንስል ጀነራል እናራቶን በጣልያን የጦር ሰራዊት ውስጥ ከፍተኛ ቦታ የነበረው ሰው ሆኖ ደሴ መወዘፉ አላማ ቢኖረው ነው።

የሐረሩ ቆንስል ድፍረት ደግሞ በጣሙን የሚገርም ነበር። ያለምንም ይሉኝታና ፍራቻ በየጊዜው የሐረርንና የሱማሌን ድንበር ይጎበኝ ነበር። በቆንስሉ ቢሮ ተቀምጦ የሰራበት አንድም ቀን አልነበረም። ጦርነቱ ሲጀመር ግድም ከሐረር አነሱትና በኋላ የግራዚያኒ የደህንነት ጉዳይ ሃላፊ ሆኖ አዲስ አበባ ገባ።

ከዚህ በተጨማሪ ጣልያኖች በመላው ኢትዮጵያ በቁልፍ ቦታዎች ሁሉ የተሰገሰጉ ሰላዮች ነበሯቸው። በአዲስ አበባ በርካታ አውሮፓውያንና የሌሎች ሀገር ዜጎችም ለጣልያኖች ይሰልሉ ነበር።

አንድ የኢትዮጵያ ባንክ ሰራተኛ ፈረንጅ በአጭር ሞገድ የምታስተላልፍ የመገናኛ ራዲዮ እቤቱ ቀብሮ እስከ ጦርነቱ ፍጻሜ ድረስ ለጣልያኖች መረጃዎችን ያቀብል ነበር። ሌላው የሶሪያ ተወላጅ የሆነው ናስር የሚባል አረብ በወዶ ገባነት የኢትዮጵያ ሰራዊት አባል ሆኖ፣ በንጉሡ ትዕዛዝ በጂጂጋ የኢትዮጵያ ሰራዊት ንብረት የነበሩትን ተሽከርካሪዎች እንዲያስተዳድር የተሾመ ሰው፣ የጣልያኖች ሰላይ ነበር። የናስርን የመገናኛ ራዲዮ የደቡብ ግንባር የኢትዮጵያ ሰራዊት በጦርነቱ መጨረሻ ላይ አግኝቶታል።

ሞሶሎኒ በታላቅ ጥንቃቄ ለጦርነቱ ሲዘጋጅ ነበር። አዎ በአድዋ ጦርነት በአፄ ምኒልክ ድል ተመታ፣ የሃፍረት ካባ ተከናንባ ላለፉት 40 አመታት የኖረችውን ሀገሩን ስም ሊያድስና ከሁሉም በላይ ለመበቀልና በአፍሪካ ቁልፍ ቦታ ያላትን ታላቋንና ነጻዋን ኢትዮጵያን የራሱ ለማድረግ ቆርጦ ተነስቷል።

የወልወሉን ግጭትም የፈጠረው ለዚሁ አላማው ብቻ ነበር። ማርሻል ኢሚሊዮ ዴ ቦኖ ስለዚሁ ጦርነት የጻፈው ማስታወሻ ለዚህ ጥሩ ምስክር ነው። ማርሻል ዴ ቦኖ ከመጀመሪያው ጊዜ ጀምሮ ኢትዮጵያን የወረረው ጦር ዋና አዛዥ ከመሆኑም በላይ ወረራውን የነደፈው እሱ ነበር።

ይኼ ወሬኛ ማርሻል ባወጣው መጽሐፉ ላይ ያቀረባቸው መረጃዎች የጦርነቱን እውነተኛ ገጽታ ቁልጭ አድርገው ያሳያሉ። የካቲት 26 ቀን 1935 ዓ.ም. ሞሶሎኒ ለማርሻል ዴ ቦኖ የጻፈው ደብዳቤ ቃል በቃል ሲተረጎም "ምናልባት ንጉሡ እኛን የመውጋት ሃሳብ ከሌለው እኛ ማድረግ አለብን" ይላል። በሌላ ደብዳቤ ግንቦት 18 ቀን 1935 ዓ.ም. ሞሶሎኒ ሲጽፍ፣ "ምንአልባት ከአለም ህብረት መውጣት እንገደድ ይሆናል። ቢሆንም የጦርነቱ ጅማሬ ከአቀድነው ጊዜ ማለፍ የለበትም" ብሏል።

ከሁለት ወር በፊት መጋቢት 8 ቀን 1935 ዓ.ም. ማርሻል ዴ ቦኖ በራሱ በሞሶሎኒ እጅ የተጻፈ ምስጢራዊ ደብዳቤ ደርሶት ነበር። በዚህ ደብዳቤ ሞሶሎኒ ሲጽፍ፣ "እርግጠኛ ነኝ፣ በጥቅምት መጨረሻ ወይም እንዲያውም በመስከረም መጨረሻ ላይ አንተ ራስህ ቀዳሚ እርምጃ ወስደህ ጦርነት መጀመር ስላለብህ 300,000 ወታደሮች ከ330 እስከ 500 አውሮፕላኖችና 500 ታንኮች ጋር ተልኮልሃል" ይላል።

ገና የክረምቱ ጊዜ ከማለቁ በፊት በምጽዋ የጦር መሳሪያዎች ተከማችተዋል። እናም ዴ ቦኖ በማንንገር እጥረት ምሬቱን ለሞሶሎኒ ሲያቀርብ ሞሶሎኒ ያለምንም ቅዋሜ ዴ ቦኖ የጠየቀውን እያንዳንዷን ጥቃቅን ነገር ሳይቀር አሟልቶ ላከለት። ሁለት ዲቪዥን ሙሉ ጦር ምፅዋ ሲደርስ፣ ማርሻል ዴ ቦኖ ሌላ ኃይል ሲጠይቅ ሞሶሎኒ ያለምንም ማንገራገር የጠየቀውን ኃይል ላከለት።

በዚህ መልኩ ማርሻል ዴ ቦኖ የጠየቀው የኃይል ጭማሪ ጥያቄ አወንታዊ መልስ እያገኘ ምፅዋ ወደብ ነሐሴ 16 ቀን 1935 ዓ.ም. ሁለቱ የፋሺስት ዲቪዥኖች ማለትም 23 ማራትሶ እና 28 ኦቶብሬ ሲደርሱ፣ ቀጥሎ መስከረም 7 ቀን 1935 ዓ.ም. 21 አፕሪሌ፣ መስከረም 30 ቋሚው የጣልያን ጦር ግራን ሳሶ፣ በመቀጠልም ጥቅምት 12 ቀን የሲላ ዲቪዥን ጦር፣ ከስምንት ቀን በኋላ 3 ጂናዩ ጦር ታክሎበት በመጨረሻ ህዳር 1 ቀን 1935 ዓ.ም. የ1 ፌብራዩ ጦር ደረጃ በደረጃ ጓዛቸውን ምፅዋ ላይ አራገፉ።

ሞሶሎኒ እንዲህ ለጦርነት በምጽዋ ሲዘጋጅ በእንግሊዞች ሃሳብ እርግጠኛ ስላልነበረ ይኼንን ጦር በባህር እንዲከላከሉ ሁለቱን የጦር መርከቦች በአድሚራል ቫኑተሊሆ አዛዥነት በቀይ ባህር አቆማቸው።

ማርሻል ኢሚሊዮ ዴ ቦኖ በእጁ የገባውን ጦር በሶስት ክፍለ ጦሮች ከፍሎ ኢትዮጵያን ለመውረር እየተዘጋጀ ሲጠብቅ ከሞሶሎኒ ቴልግራም ደረሰው። በቴሌ ግራሙም ሞሶሎኒ ለ ዴ ቦኖ ሲፅፍ፣ "ኮንፈረንሱም ምንም አልወሰነም። ጄኔቫም ምንም አይወስንም። አንተ ወስን" ይላል።

ከተወሰኑ ቀናት በኋላ ጀነራል ዳላ ኦራ ወደ ኤርትራ ተመልሶ ጥብቅ ምስጢር ያዘለ ከሞሶሎኒ የተላከ ደብዳቤ ለማርሻል ኢሚሊዮ ዴ ቦኖ አመጣለት። በዚህ

ደብዳቤው ሞሶሎኒ ሲጽፍ፣ "ይኼ ጦርነቱን ከመጀመርህ በፊት የምጽፍልህ የመጨረሻ ደብዳቤ ነው። ከመስከረም 10 ቀን በፊት የመጨረሻውን ትዕዛዜን ጠብቅ። በዚያን ጊዜ ሌላ ሁለት ተጨማሪ ዲቪዥን ጦርና በርካታ አውሮፕላኖች እጅህ ይገባሉ ብዬ አስባለሁ። ይኼ ኃይልም ጦርነቱን ለመጀመርና ያቀድነውን ለመፈጸም የሚበቃ ይመስለኛል።" ቀጥሎም፣ "ልክ ከመስከረም 10 ቀን በኋላ ከኔ ቴሌግራም 'መልእክቱ ደርሶኛል' የሚል ቃል ሲደርስህ በሚቀጥለው 24 ሰዓት ውስጥ ወረራውን ትጀምራለህ። መስቀልንም በድል መሬት ታከብራለህ" ይላል የሞሶሎኒ ደብዳቤ።

ማርሻል ኢሚሊዮ ዴ ቦኖ እንዲህ ሲል "በአዲስ አበባ ያሉት የጣልያን ዲፕሎማቶች እስኪወጡ ጣልያን በኢትዮጵያ ላይ በይፋ ጦርነት እስክታውጅ መጠበቅ እንዳለበት" ለጠየቀው ጥያቄ ሞሶሎኒ፣ "ምንም ጦርነት ማወጅ ብሎ ነገር የለም። ጥቅምት 3 ቀን 1935 ዓ.ም. ከመንጋቱ በፊት ሌሊት ላይ ጦርነቱን እንድትጀምር አዝዤሃለሁ። ለዚህ ቴሌግራሜ አስቸኳይ መልስ እጠብቃለሁ" ሲል መለሰለት።

ማርሻል ዴ ቦኖ በመጽሐፉ ላይ አምኖ እንደጻፈው የኢትዮጵያ ጦር ሁኔታ ይኼን ያህል የሚያሰጋ ስላልነበረ ጦርነቱን ማወጅ ብዙም እንዳላስጨነቀው አምኖ ጽፏል።

ጥቅምት 2 ቀን 1935 ዓ.ም. ሞሶሎኒ የተለመደውን ኢትዮጵያን የማስፈራራት ድንፋታውን በሮማ አደባባይ ሲደነፉ ማርሻል ዴ ቦኖ ለሶስቱም ክፍለ ጦሮች አዛዥ ጀነራሎች ቀጭን ትዕዛዝ ሰጠ።

1ኛ፡ አንደኛው ክፍለ ጦር አዴግራትን እንዲይዝ፣

2ኛ፡ ሁለተኛው ክፍለ ጦር አድዋን እንዲይዝ፣

3ኛ፡ ሶስተኛው እና ኤርትራውያን የሚበዙበት ክፍለ ጦር በሁለቱ ክፍለ ጦሮች መካከል ግንኙነት ሳያቋርጥ ኢንጢቾን እንዲይዝ! አዞ ጦሩን ኢትዮጵያን እንዲወር ላከው።

ጥቅምት 3 ቀን 1935 ዓ.ም. ገና ከመንጋቱ በፊት በትክክል ልክ ሞሶሎኒ እንዳዘዘው የጣልያን ሰራዊት የኢትዮጵያን ድንበር ጥሶ መረብን ተሻገረ።

8

ራስ ሥዩም መንገሻ

በአድዋ ከተማ የመስቀል በዓል እየተከበረ ነበር። ራስ ሥዩም፣ የአፄ ዮሐንስ የልጅ ልጅና የምዕራብ ትግራይ ጠቅላይ ግዛት ገዢ፣ የመስቀል በዓልን ምክንያት በማድረግ በአድዋ የጣልያን ቆንስል ከነሙሉ ሰራተኞቻቸው በቤተ መንግስታቸው የራት ግብዣ አድርገውላቸው ነበር።

አይ ራስ ሥዩም! ጣልያኖቹ ግብዣው ሳያልቅ ይቅርታ ጠይቀው በጊዜ ሲወጡ እንኳን አልጠረጠሩዋቸውም ነበር። አንድ በአውሮፓ የተማረ ኢትዮጵያዊ በቆንስሉ ውስጥ አስተርጓሚ ሆኖ የሚሰራ ልጅ በኋላ በተንቤን ተገናኝተን እንዳጫወተኝ፣ ጣልያኖቹ ከራስ ስዩም ግብዣ በጥድፍያ ወደ ቆንስል ህንፃቸው ተመልሰው የተለያዩ መዝገቦችን ሲያቃጥሉ እንዳመሹና መሸከም ያልቻሉትን በርካታ ጠመንጃ ወደ ወንዝ ውስጥ ጨምረው በዚያው ምሽት በምስጢር አድዋን ለቀው ሸሹ።

ግን እነዚህ ችኩሎች አድለቢሶች ነበሩ። ምንም እንኳ በሽሽታቸው ዋናውን መንገድ ለቅቀው ጫካ ጫካውን ያለ ብዙ ችግር ሲጓዙ ቢያድሩም በመጨረሻ ድንበር ላይ ተያዙ። እነዚህ የቆንስሉ ሰራተኛ ጣልያኖች ድንበር ላይ ሁለት ስህተት ሰሩ። አንደኛ የመውጫ ደብዳቤ ከገዢው ከራስ ሥዩም አልያዙም ነበር። ሁለተኛ የዲፕሎማሲ መብታቸውን እንኳን ለመጠቀም ሳይሞክሩ ቀድመው ጉቦ ለመስጠት ተሽቀዳደሙ።

እውነትም አድለ ቢሶች ነበሩ። የእዚያን እለቱ የድንበር ጠባቂዎች አዛዥ ፍጹም ሀቀኛ ስለነበር ትናንት ራት በክብር ወደበሉባት ቤተ መንግሥት እንደሌባ ታስረው ተልከው፣ በምርኮኛ ደንብ እስር ቤት ወረዱት።

ጣልያኖች አድዋን በአውሮፕላን ሊደበድቡ ነው የሚለው ወሬ በመጠንከሩና ራስ ሥዩም የከተማውን ህዝብ ቅሌን ጨርቁን ሳይል አድዋን ለቆ እንዲወጣ በማዘዛቸው አድዋ ገና ሳትወረር የተወረረች ከተማ ይመስል ጭር አለች።

ራስ ሥዩም ከነጦራቸው ቤተ መንግስታቸውን ለቅቀው፣ ከአድዋ ወጣ ብለው፣ ከጫካ ገብተው፣ የንጉሠ ነገሥቱን ተጨማሪ ትዕዛዝ እየጠበቁ እንደተቀመጡ ምርኮኞቹ እስር ቤት እንደተተዉ አስታወሱ። ግን እነዚያን አድለቢስ ጣልያኖች ለአርባ ቀን እድላቸው ከመተው በስተቀር ሌላ አማራጭ አልነበረም።

በአድዋ አንድ አውሮፓዊ ነበር። ኮሎኔል ፌኦዶር የብገኖቪች ኮኖቫሎብ ይባላል። ኮሎኔል ኮኖቫሎብ ለብዙ አመታት በኢትዮጵያ የኖረና የኢትዮጵያም ዜግነት ያለው ከመሆኑም በላይ በንጉሠ ነገሥቱ ቤተ መንግሥት ሲያማክር ስለኖረ ስለ ኢትዮጵያና ስለ ኢትዮጵያውያን ብዙ ጠንቅቆ የሚያውቅ ሰው ነው። ለዚያም መሰለኝ ንጉሠ ነገሥቱ ራስ ሥዩምን ያማክር ዘንድ የላኩት። ከኮሎኔል ኮኖቫሎብ ጋር በኋላ በጦር ሜዳ ተገናኝተናል፤ የሁለቱ ራሶች ጦር ህብረት ከፈጠረ በኋላ። ወደፊት እንደምናየው ሙሉውን የተንቤን ጦርነትም በአንድ ዋሻ ውስጥ አሳልፈናል። ኮሎኔል ኮኖቫሎብ በአድዋ ስለገጠመው ነገር ሲያጫውተኝ እንዲህ ብሎኝ ነበር።

"ጥቅምት 3 ቀን ልክ ገና ጎህ እንደቀደደ አንድ የአድዋ ልጅ "አውሮፕላን... አውሮፕላን... አውሮፕላን..." እያለ የራስ ሥዩም ጦር የሰፈረበትን ሰፈር በጠበጠው። ኮሎኔል በፍጥነት ለባብሶ ከአንድ አነስ ካለች ቤት ጣራ ላይ ወቶ ሰማዩን ይቃኝ ገባ። አዎ ያ ልጅ እውነት ነበረው። ከአድዋ በስተሰሜን ሰባት የሚያብለጨልጩ ነጭ ነጠብጣቦች ይታዩ ነበር። ኮሎኔል ጣሪያው ላይ እንደቆመ አውሮፕላኖቹ እየቀረቡ ሲመጡ ኮሎኔል ምናልባት የኃይል ሚዛናቸውን ለማሳየት (ማኒፌስት ሊያደርጉ)፣ የአድዋን ህዝብ ለማስፈራራት የተላኩ ኤስካድሮች ይሆናሉ ብሎ ገመተ። ኮሎኔል ተሳስቷል። እነዚያ ሰባት የሰይጣን ቆርቆሮዎች የአድዋን ከተማ በማለዳ አጨሷት።

በመጀመሪያው ዙር በተነሳው አቧራ የራስ ስዩም ቤተ መንግሥት መትረፋን እንኳ ለማጣራት ኮሎኔል ኮኖቫሎብ ሳይቻለው ቀረ። እነዚያ ቆርቆሮዎች አድዋን ደጋግመው እየዞሩ የተሸከሙትን ቦምብ አራገፉባት።

በሞሶሎኒ አማች በካፒቴን ቻኖ (በኋላ የሞሶሎኒ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር) የሚመራው የአየር ኃይል አድዋን አደቀቃት። አዎ በዚያች ማለዳ በጊዜ ቤታቸውን ለቅቀው መውጣት ያልቻሉ 87 እናቶች፣ አሮጊቶች፣ አዛውንትና ልጆች ህይወታቸውን ከፈሉ። ራስ ሥዩም በጊዜ ጥሩንባ ባያስነፉ ኖሮ ሰለባው ሺ ጊዜ እጥፍ በሆነ ነበር።

የሚገርመው ነገር እነዚያ ለእጣ ፈንታቸው ተትተው የነበሩት ምርኮኞች የታሰሩባት ቤት እንዲት በምብ እንኳ ሳይነካት ቀረ። ጣልያኖች መረጃ ኖሯቸው ሳይሆን የእድልና የአጋጣሚ ጉዳይ ሆኖ ነው። ራስ ሥዩም በአስቸኳይ ሰው ልከው ምርኮኞቹን ወደ መሽጉባት የጫካ የጦር ሰፈር አስመጧቸው። ምናልባት በአድዋ ያሉ የተበተኑ ጦሮች ካገኟቸው እንዳይጨፈጭፏቸው በመፍራት ነበር ከአድዋ ወደ ጫካ ያስመጧቸው። ራስ ሥዩም ከጫካ ሳይወጡ የንጉሠ ነገሥቱን መመሪያ ሲጠብቁ፣ በመቶ ሺዎች የሚቆጠር በዘመናዊ መልኩ የሰለጠነና በታንኮች የሚደገፍ ጦር የኢትዮጵያን ድንበር ጣሰ። የመጀመሪያው የጣልያን ወታደር ወጣቱ መቶ አለቃ ሞርጋንቲኒ የኢትዮጵያን ድንበር መረብን ተሻግሮ የኢትዮጵያን መሬት ረገጠ። ከጥቂት ጊዜ ውሂያ በኋላ በአንድ ኢትዮጵያዊ የገበሬ ወታደር ግንባሩን በጥይት ተመቶ ወደቀ።

ጣልያኖች የአርባ ዓመት ቁጣቸውን አድዋን እንደ አዙሪት እየዞሩ እንደ ሐምሌ ዝናብ የቦምብ ናዳቸውን አወረዱባት። የራስ ሥዩም ጦር ፈጽሞ ለጦርነት ዝግጁ አልነበረም። እንዲህ ጣልያኖች አድዋን ከገፀምድር ለማጥፋት በቦንብ ሲያጋዩ የራስ ሥዩም ብቸኛ የጦር አበጋዝ በመቶዎች ከሚቆጠሩ ያልሰለጠኑ ወታደሮቹ ጋር ድንበር ላይ ቆሞ የኩቴ ቀረጥ ይቀበል ነበር። ያም በዛ ተብሎ በንጉሠ ነገሥቱ ትዕዛዝ ከድንበር 40 ኪሎሜትር ወደኋላ እንዲያፈገፍግ ተደረገ።

ጠዚህ ሰዓት የአለም የዜና ማሰራጪያዎች ስለ ታላቁ የአድዋ ደም መፋሰስ በሰፊው ለፈለፉ። በተለይ የፋሺስቶቹ የዜና ማሰራጪያዎች "አድዋን በቁጥጥር ስር ለማድረግ" የተከፈለውን መስዋትነት አጋነው፣ ብዙ ብዙ ከእውነት አርቀው አቀረቡ። እስቲ ምን አስዋሻቸው? ያለብዙ ደም መፋሰስ የያዙትን ይዘዋል።

ራስ ሥዩም እንደሆን ካላቸው የዘብ ጦር ጋር የጣልያንን ታንከኛና እግረኛ ለመግጠም ማለምም አይቻላቸው። ራስ ሥዩም ከነጦራቸው ከአድዋ ራቅ ብሎ በየጫካውና ጥሻው እንደ አደፈጡ የንጉሡን መመሪያና ከመሀል ሀገር በመንቀሳቀስ ላይ ያለውን ጦር ተስፋ እያደረጉ ሲጠብቁ፣ እነዚያን ከዱተኞች በቀል እንዳይደርስባቸው በመፍራት አስመጥተው የንጉሡን ተጨማሪ ትዕዛዝ ሲጠብቁ ከንጉሡ ቴሌግራም ደረሳቸው።

ከንጉሠ ነገሥቱ በደረሳቸው ቴሌግራም መሰረት ነጻ ለቀቋቸው። ራስ ሥዩም ትልቅ እፎይታ እየተሰማቸው በዚያው ምሽት አጃቢ ጨምረው የቆንስሉን ሰራተኞች ምርኮኛ ጣልያኖች እስከ አዲግራት ድንበር ድረስ ላኳቸው። ኢትዮጵያውያን እንዲህ አይነት ጨዋዎች ናቸው።

በዚህ መልኩ በተጀመረ ጦርነት የመጀመሪያው የጣልያን ብርጌድ ያለ ብዙ ችግር አዲግራት ገባ። አዎ እንደ መጀመሪያ የኢትዮጵያ ከተማ አዲግራት በወራሪው ጦር ስር ወደቀች። ከዛሬ አርባ ዓመት በፊት መቶ አለቃ ሳንቲኒ በሽንፈት የጣልያንን

ባንዲራ ከአዲግራት አደባባይ አውርዷል። ዛሬ ከአርባ ዓመት በኋላ በአዲግራት ያው ሳንቲኒ — ከአርባ ዓመት በፊት መቶ አለቃ ዛሬ ጀነራል ሳንቲኒ — የፋሽስቶችን ባንዲራ ባንድ በወላለቀ ጎጆ ጣርያ ላይ ጥቅምት 5 ቀን 1935 ዓ.ም. ሰቀለ።

ቀጥሎም አሁንም ከድንበር ጠባቂው የራስ ሥዩም ወታደሮች ጋር ለሁለት ሰዓት ያህል ተኩስ የገጠመው የሁለተኛው ክፍለ ጦር በጀነራል ማራቪን እየተመራ ያለብዙ ችግር አድዋን በእጃቸው ጥቅምት 6 1935 ረፋዱ ላይ አስገቡ። ጣሊያኖች አድዋን በቀላሉ እጃቸው ያስገቡበት ምክንያት በጣም ቀላል ነበር። ዋናው የኢትዮጵያ ጦር ያለው ገና መሀል ሀገር ነበር።

የመቀሌ ከተማም አወዳደቅ እጅጉን አስቂኝ እና አስለቃሽ ድራማ ነበር። የመቀሌው ገገር ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ከነጦሩ ወገኑን ከድቶ ለጣልያኖች በመገበሩ በመቀሌ ከተማ የነበረ ሰው ቢኖር የድሮው የአዲስ አበባ ከንቲባ ባላምበራስ ወዳጆና ታማኝ አማካሪያቸው ሻለቃ ካሣ ብቻ ነበሩ።

ሻለቃ ካሣ ኢትዮጵያ ካፈራቻቸው ጥቂት እውነተኛ ወታደራዊ መኰንኖች አንዱ ነው። ሻለቃ ካሣ በፈረንሳይ ሀገር በጦር አካዳሚ የተማረ ብልህ ሰው ሲሆን ንጉሠ ነገሥቱ ለአንድ ታላቅ ስራ ጦርነቱ ከመጀመሩ ጥቂት ቀደም ብሎ ባላምባራስ ወዳጆን እንዲያማክር በሚል ሽፋን ወደ መቀሌ ላኩት። ሻለቃ ካሣ በመቀሌ ወደ 300 ከሚጠጉ ወታደሮቹ ጋር ብቻ ነበር። ሶስት መቶ በወጉ እንኳን ካልታጠቁ ከገበሬ ወታደሮቹ ጋር መቀሌን በጠላት እጅ እንዳይወድቅ መከላከል ነበረበት።

የፋሽስቱ ጦር ከአዲግራት ተነስቶ በታላቅ ወኔ ያለብዙ ችግር ወደ መቀሌ ማምራቱን ሁሉም ሰምቷልና መጀመሪያ ባላምባራስ ወዳጆ የመቀሌን ከተማ ለቅቀው ከነጦራቸው ጫካ ገቡ። የባላምባራስ ወዳጆ ሰላዮች ባመጡት ወሬ ለጊዜው መቀሌ የገባው የደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ጦር ብቻ እንደሆነ ሲሰሙ ባላምበራስ ወዳጆ ከሻለቃ ካሣ ጋር በመምከር በተለያዩ ወረቀቶች የጹሑፍ ትዕዛዞች ያዘጋጃሉ። በጽሑፉም ውስጥ "ፊታውራሪ እንቶኔ መቀሌን ከቦ ወደ መቀሌ የሚያስገቡ ሁሉንም በሮች እንዲይዝ። ቀኛዝማች እንቶኔ ከ10,000 ወታደሮቹ ጋር መቀሌን ከወደ ምዕራብ በኩል ያለምህረት እንዲያጠቃ። ፊታውራሪ እንቶኔ ከ20,000 ጦሩ ጋር በደጀንነት እንዲጠብቅ" እና ሌላም ሌላም የውሸት ትዕዛዝና በእውነት የሌሉ ፊታውራሪዎችን ስም ጨማምረው ምርጥ ሰዎቻቸውን የወረቀቱን ትዕዛዝ አስይዘው በደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ሰዎች ይማረኩ ዘንድ ትዕዛዝ ሰጥተው ይልኳቸዋል።

የባላምባራስ ወዳጆ ሰዎች በትዕዛዙ መሰረት በደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ሰዎች እጅ በምርኮ ይወድቃሉ። ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ የባላምባራስ ወዳጆን ትዕዛዝ በቅጡ እንኳ ሳያነብ መቀሌን ለቅቆ ድንግርግሩ በወጣ ሁኔታ ሲሸሽ የሻለቃ ካሣ ከ300 የማይበልጡት ጀግና ወታደሮች ከባላምባራስ ወዳጆ ወታደሮች ጋር ህብረት ፈጥረው ጥቃት ይሰነዝራሉ። ምንም እንኳን የደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ሰዎች

የሚገርመው ነገር እነዚያ ለእጣ ፈንታቸው ተትተው የነበሩት ምርኮኞች የታሰሩባት ቤት አንዲት ቦምብ እንኳ ሳይነካት ቀረ። ጣልያኖች መረጃ ጥሬቸው ሳይሆን የእድልና የአጋጣሚ ጉዳይ ሆኖ ነው። ራስ ሥዩም በአስቸኳይ ሰው ልከው ምርኮኞቹን ወደ መሸንባት የጫካ የጦር ሰፈር አስመጧቸው። ምናልባት በአድዋ ያሉ የተበተኑ ጦሮች ነጋሪቸው እንዳይጨፈጭፏቸው በመፍራት ነበር ከአድዋ ወደ ጫካ ያስመጧቸው። ራስ ሥዩም ከጫካ ሳይወጡ የንጉሠ ነገሥቱን መመሪያ ሲጠብቁ፣ በመቶ ሺዎች የሚቆጠር በዘመናዊ መልኩ የሰለጠነና በታንኮች የሚደገፍ ጦር የኢትዮጵያን ድንበር ጣሰ። የመጀመሪያው የጣልያን ወታደር ወጣቱ መቶ አለቃ ሞርጋንቲኒ የኢትዮጵያን ድንበር መረብን ተሻግሮ የኢትዮጵያን መሬት ረገጠ። ከጥቂት ጊዜ ውጊያ በኋላ በአንድ ኢትዮጵያዊ የገበሬ ወታደር ግንባሩን በጥይት ተመቶ ወደቀ።

ጣልያኖች የአርባ ዓመት ቂማቸውን አድዋን እንደ አዙሪት እየዞሩ እንደ ሐምሌ ዝናብ የቦምብ ናዳቸውን አወረዱባት። የራስ ሥዩም ጦር ፈጽሞ ለጦርነት ዝግጁ አልነበረም። እንዲህ ጣልያኖች አድዋን ከገፀምድር ለማጥፋት በቦንብ ሲያጋዩ የራስ ሥዩም ብቸኛ የጦር አበጋዝ በመቶዎች ከሚቆጠሩ ያልሰለጠኑ ወታደሮቹ ጋር ድንበር ላይ ቆሞ የኑቄ ቀረጥ ይቀበል ነበር። ያም በዛ ተብሎ በንጉሠ ነገሥቱ ትዕዛዝ ከድንበር 40 ኪሎሜትር ወደኋላ እንዲያፈገፍግ ተደረገ።

በዚህ ሰዓት የአለም የዜና ማሰራጪያዎች ስለ ታላቁ የአድዋ ደም መፋሰስ በሰፊው ለፈለፉ። በተለይ የፋሺስቶቹ የዜና ማሰራጪያዎች "አድዋን በቁጥጥር ስር ለማድረግ የተከፈለውን መስዋትነት አጋነው፣ ብዙ ብዙ ከእውነት አርቀው አቀረቡ። እስቲ ምን አስዋሻቸው? ያለብዙ ደም መፋሰስ የያዙትን ይዘዋል።

ራስ ሥዩም እንደሆን ካላቸው የዘብ ጦር ጋር የጣልያንን ታንከኛና እግረኛ ለመግጠም ማለምም አይቻላቸው። ራስ ሥዩም ከነጦራቸው ከአድዋ ራቅ ብሎ በየጫካውና ጥሻው እንደ አደፈጡ የንጉሡን መመሪያና ከመሀል ሀገር በመንቀሳቀስ ላይ ያለውን ጦር ተስፋ እያደረጉ ሲጠብቁ፣ እነዚያን ከዳተኞች በቀል እንዳይደርስባቸው በመፍራት አስመጥተው የንጉሡን ተጨማሪ ትዕዛዝ ሲጠብቁ ከንጉሡ ቴሌግራም ደረሳቸው።

ከንጉሠ ነገሥቱ በደረሳቸው ቴሌግራም መሰረት ነጻ ለቀቋቸው። ራስ ሥዩም ትልቅ እፎይታ እየተሰማቸው በዚያው ምሽት አጃቢ ጨምረው የቆንስሉን ሰራተኞች ምርኮኛ ጣልያኖች እስከ አዲግራት ድንበር ድረስ ሳኳቸው። ኢትዮጵያውያን እንዲህ አይነት ጨዋዎች ናቸው።

በዚህ መልኩ በተጀመረ ጦርነት የመጀመሪያው የጣልያን ብርጌድ ያለ ብዙ ችግር አዲግራት ገባ። አዎ እንደ መጀመሪያ የኢትዮጵያ ከተማ አዲግራት በወራሪው ጦር ስር ወደቀች። ከዛሬ አርባ ዓመት በፊት መቶ አለቃ ሳንቲኒ በሽንፈት የጣልያንን

ባንዲራ ከአዲግራት አደባባይ አውርዷል። ዛሬ ከአርባ ዓመት በኋላ በአዲግራት ያው ሳንቲኒ — ከአርባ ዓመት በፊት መቶ አለቃ ዛሬ ጀነራል ሳንቲኒ — የፋሽስቶችን ባንዲራ ባንድ በወላለቀ ጎጆ ጣርያ ላይ ጥቅምት 5 ቀን 1935 ዓ.ም. ሰቀሉ።

ቀጥሎም አሁንም ከድንበር ጠባቂው የራስ ሥዩም ወታደሮች ጋር ለሁለት ሰዓት ያህል ተኩስ የገጠመው የሁለተኛው ክፍለ ጦር በጀነራል ማራቪኜ እየተመራ ያለብዙ ችግር አድዋን በእጃቸው ጥቅምት 6 1935 ረፋዱ ላይ አስገቡ። ጣሊያኖች አድዋን በቀላሉ እጃቸው ያስገቡበት ምክንያት በጣም ቀላል ነበር። ዋናው የኢትዮጵያ ጦር ያለው ገና መሀል ሀገር ነበር።

የመቀሌ ከተማም አወዳደቅ እጅጉን አስቂኝ እና አሰለቃሽ ድራማ ነበር። የመቀሌው ገዢ ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ከነጦሩ ወገኑን ከድቶ ለጣልያኖች በመግዛቱ በመቀሌ ከተማ የነበረ ሰው ቢኖር የድሮው የአዲስ አበባ ከንቲባ ባላምበራስ ወዳጆና ታማኝ አማካሪያቸው ሻለቃ ካሣ ብቻ ነበሩ።

ሻለቃ ካሣ ኢትዮጵያ ካፈራቻቸው ጥቂት እውነተኛ ወታደራዊ መኮንኖች አንዱ ነው። ሻለቃ ካሣ በፈረንሳይ ሀገር በጦር አካዳሚ የተማረ ብልህ ሰው ሲሆን ንጉሠ ነገሥቱ ለአንድ ታላቅ ስራ ጦርነቱ ከመጀመሩ ጥቂት ቀደም ብሎ ባላምባራስ ወዳጆን እንዲያማክር በሚል ሽፋን ወደ መቀሌ ላኩት። ሻለቃ ካሣ በመቀሌ ወደ 300 ከሚጠጉ ወታደሮቹ ጋር ብቻ ነበር። ሶስት መቶ በወጉ እንኳን ካልታጠቁ ከገበሬ ወታደሮቹ ጋር መቀሌን በጠላት እጅ እንዳይወድቅ መከላከል ነበረበት።

የፋሽስቱ ጦር ከአዲግራት ተነስቶ በታላቅ ወኔ ያለብዙ ችግር ወደ መቀሌ ማምራቱን ሁሉም ሰምቷልና መጀመሪያ ባላምባራስ ወዳጆ የመቀሌን ከተማ ለቅቀው ከነጦራቸው ጫካ ገቡ። የባላምባራስ ወዳጆ ሰላዮች ባመጡት ወሬ ለጊዜው መቀሌ የገባው የደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ጦር ብቻ እንደሆነ ሲሰሙ ባላምበራስ ወዳጆ ከሻለቃ ካሣ ጋር በመምከር በተለያዩ ወረቀቶች የጽሑፍ ትዕዛዞች ያዘጋጃሉ። በጽሑፉም ውስጥ "ፊታውራሪ እንቶኔ መቀሌን ከቦ ወደ መቀሌ የሚያስገቡ ሁሉንም በሮች እንዲይዝ። ቀኛዝማች እንቶኔ ከ10,000 ወታደሮቹ ጋር መቀሌን ከወደ ምዕራብ በኩል ያለምህረት እንዲያጠቃ። ፊታውራሪ እንቶኔ ከ20,000 ጦሩ ጋር በደጅንነት እንዲጠብቅ" እና ሌላም ሌላም የውሸት ትዕዛዝና በእውነት የሌሉ ፊታውራሪዎችን ስም ጨማምረው ምርጥ ሰዎቻቸውን የወረቀቱን ትዕዛዝ አስይዘው በደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ሰዎች ይማረኩ ዘንድ ትዕዛዝ ሰጥተው ይልኳቸዋል።

የባላምባራስ ወዳጆ ሰዎች በትዕዛዙ መሰረት በደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ሰዎች እጅ በምርኮ ይወድቃሉ። ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ የባላምባራስ ወዳጆን ትዕዛዝ በቅጡ እንኳ ሳያነብ መቀሌን ለቅቆ ድንግርግሩ በወጣ ሁኔታ ሲሸሽ የሻለቃ ካሣ ከ300 የማይበልጡት ጀግና ወታደሮች ከባላምባራስ ወዳጆ ወታደሮች ጋር ህብረት ፈጥረው ጥቃት ይሰነዝራሉ። ምንም እንኳን የደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ሰዎች

ብዛት ቢኖራቸውም ብዙ ራሳዎች ጥለው መቀሌን ለትቀው ሲወጡ ባላምባራስ ወዳጆና ሻለቃ ካሣ ወደ መቀሌ ሰተት ብለው ይገባሉ።

በዚች አነስተኛ መቀሌን የመያዝ ጦርነትም ሰባት የደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ወታደሮችና ሁለት ጣልያኖች ይማረካሉ። ምርኮኞቹ በዚያው ምሽት የሞት ፍርድ ተፈርዶባቸው ተገለዋል።

ብቻ ምን ያደርጋል፤ ባላምባራስ ወዳጆና ሻለቃ ካሣ ብዙም ሳይሞቃቸው የጣልያን ጦር በመድረሱ እንደገና መቀሌን ለቅቀው በህብረት ወደ ደቡብ ወርደው በአምባአላጌ ተራራ ወደ ሰሜን በመንዝ ላይ ካለው የኛ ጦር ጋር ተቀላቀሉ።

በዚህ መልኩ የጀነራል ሳንቲኒ ጦር ህዳር 8 ቀን 1935 ዓ.ም. ከጠዋቱ 3 ሰዓት ያለብዙ ችግር መቀሌን ተቆጣጠራት።

9

የደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ክህደት

ጣልያኖች ምንም አይነት ጦርነት ሳያውጁ የኢትዮጵያን ድንበር ጥሰው ከገቡ በኋላ በፕሮፓጋንዳቸው ለመላው የአለም ህዝብ እንዲህ ሲሉ ማደናገር ጀመሩ። ሆን ብለው ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሳን ከሞተው አባቱ ከራስ ጉግሳ፣ የአፄ ዮሐንስ የልጅ ልጅ፣ ጋር በማለዋወጥ ራስ ጉግሣ ከ12ሺ ጦሩ ጋር ንጉሡን ከድቶ በኢትዮጵያ ስልጣኔ ለማምጣት ከሚጥረው የጣልያን ጦር ጋር ተቀላቀለ ወዘተ. እያሉ ለፈፉ።

ራስ ጉግሣ ከሌሎች የኢትዮጵያ መኳንንት የሚለይበት ነገር ቢኖር ቀይ የራስ ፀጉሩና ጺሙ ብቻ ነው። ራስ ጉግሳ ይኼንን የብቸኛ ልጃቸውን ክህደት ቢሰሙ ኖሮ መቃብራቸውን ፈንቅለው እንደሚወጡ ጥርጥር የለውም።

ወጣቱ ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ቢበዛ 28 ዓመት ቢሆነው ነው። ይኼ ደጃዝማች ጦርነቱ ከመጀመሩ ጥቂት ወራት በፊት ጀምሮ ከጣልያኖች ጋር ሲደራደር ነበር። ልክ ጦርነቱ ሲጀመርና የጀነራል ሳንቲኒ ጦር አዲግራት ሲገባ ይኼ ወጣት ደጃዝማች መቀሌን ለትቆ ከጥቂት ወታደሮቹና አሽከሮቹ ጋር አዲግራት ሸሽቶ ገባ።

ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ለምን ሀገሩን ከዳ? ይኼ ደጃዝማች የምር የፖለቲካ ችግር ነበረበት? ወይስ የክህደቱ ምክንያት የኢኮኖሚ ችግር ነው? እንደኔ እንደኔ የዚህ ወጣት ደጃዝማች ክህደት ከፖለቲካ ይልቅ የኢኮኖሚ ችግር ይመስላል።

አዎ ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ከአባቱ ከራስ ጉግሳ ሞት በኋላ የተራቆተችውን የምስራቅ ትግራይን ግዛት ወርሶ በቅድመ አያቱ በአፄ ዮሐንስ ቤተ መንግሥት መቀሌ ገብቶ ተቀመጠ።

ለዚህ ወጣት ደጃዝማች እድል በሯን ለከፍተኛ ስልጣን ወለል አድርጋ የከፈተችለት መሰለ። ወጣት ነውና ከጊዜ ብዛት ትልቅ ቦታ እንደሚደርስ ምንም ጥርጥር አልነበረውም። ቢሆንም ንጉሠ ነገሥቱ ይኼንን ወጣት ደጃዝማች አያምኑትም ነበር።

ባለቀይ ጺሙ አባቱ ራስ ጉግሳ ከልክ ባለፈ ሁኔታ ከጣልያኖች ጋር ወዳጅ ነበር። ከጣልያኖችም በርካታ ትልልቅ ስጦታዎችን ያለምንም ይሉኝታ ይቀበል ነበር። እናም ወጣቱ ደጃዝማች የአባቱን ፈለግ ተከትሎ ሲጓዝ ከርሞ አሁን ከማይመለስበት ክህደት ውስጥ ገባ።

ቀድሞ ይኼን የተገነዘበው አስተዋዩ ንጉሥ ወጣቱን ከዚህ አጉል መንገድ ሊያወጣውና በተቻለ አቅሙ ወደ ራሱ ሊያቀርበው አስቦ ትንሿን ወጣቷን ልዕልት ልጁን ዳረለት። ይሁን እንጂ ይቺ ምስኪን እድለቢስ ልዕልት በድንገት ስትሞት ይኺ ወጣት ደጃዝማች ተመልሶ ነጻ ሆነና በተለያዩ የፖለቲካ ሻጥረኞች እጅ ወድቆ አሻንጉሊት ሆነ።

ወጣቱ ደጃዝማች የተጎናቀለችውን የምስራቅ ትግራይን ጠቅላይ ግዛት ወርሶ በመቀሌ ቤተ መንግሥት በተቀመጠ ጊዜ በመቀሌ ሶስት ግሪካውያን ነጋዴዎችም እየነገገዱ ይኖሩ ነበር። በኋላ ላይ እንደታየው ከነዚህ ግሪካውያን ነጋዴዎች አንዱ አቶ ፓናይ ቪአለቲ ለጣልያኖች ያደረ፣ በጣልያኖች የተገዛ ሰላይ ነበር።

ፓናይን በግሌ አውቀዋለሁ። ከዛሬ ስድስት ዓመት በፊት በሰሜን ኢትዮጵያ ስዘዋወር መቀሌ አግኝቸው ተዋውቄው ነበር። ይሁን እንጂ ያኔ የፓናይ ቪአለቲ ሁለተኛ ቆሻሻ ስራ ምን እንደነበረ ግምቱም አልነበረኝም።

አዎ ያኔ ፓናይ ቪአለቲ እቤቱ ጋብዞኝ ነበር። እናም በፓናይ ቤት አንዲት በጣም ሲበዛ ቆንጆዬ ልጅ (የፓናይ እህት መሆኗ ነው) አይቼ ነበር። ወጣቱ ደጃዝማች በዚች ወጣት ልጅ ውበት ተማርኮ በፍቅሯ ቢወድቅና የወንድሟ የፓናይ ቪአለቲ አሻንጉሊት ቢሆን ብዙም አይገርምም። ሲበዛ ቆንጆዬ ልጅ ናት።

ትግሩ ታዲያ ያቺ ውብ ግሪካዊት ቆንጆ የምር ይኼንን እድለቢስ ደጃዝማች አፍቅራው ነበር ወይስ እሷም እንደ ወንድሟ ቆሻሻ ጨዋታ እየተጫወተች ነበር? ይኼን ጥያቄ መመለሱ ከባድ ነው።

እውነታው ግን ይቺ ቆንጆ አብዛኛውን ጊዜዋን የምታሳልፈው ከወንድሟ ቤት ይልቅ በመቀሌ ቤተ መንግሥት ነበር። እድሜ ለዚች ቆንጆ እህቱ ፓናይ ቪአለቲ በምስራቅ ትግራይ ፈላጭ ቆራጭ የደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ብቸኛ አማካሪ ሆነ።

እንዲህም ሆኖ ወጣቱ ደጃዝማች ምንም እንኳን ከጣልያኖች ጋር ቢወዳጅም፣ ስጦታዎች ቢቀበልም ጦርነቱ ሲነሳ "ዞር በሉ! በሀገሬ አትምጡብኝ" ብሎ ጦሩን እንደሚያነሳ የጠረጠረ አንድም ሰው አልነበረም።

ሌሎች በርካታ ትልልቅ ሹማምንቶችም የጣልያኖች ወዳጆች ነበሩ። ስጦታዎችም ያለ አንዳች ይሉኝታ ይቀበሉ ነበር። ጦርነቱ ሲጀመር ግን በስጦታ በተቀበሏቸው ጠመንጃዎች በጦር ሜዳ ገጥመው ጥለው ወድቀዋል። እናም ወጣቱ ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሳም እንዲህ እንደሚያደርግ ሁሉም ያምን ነበር።

ይሁን እንጂ ያቺ ውብ ግሪካዊት ቆንጆ ወጣቱን ደጃዝማች በፍቅሯ ወጥመድ አስገብታ አሳመነችው። ወንድሟም አቶ ፓናይ ቪአለቲ አስፈላጊውን ነገር ሁሉ ከጣልያኖች ጋር ተደራደረለት። ከማርሻል ዴ ቦኖም እጅ የማረጋገጫ ደብዳቤ አመጣለት።

እንዳልኩት ልክ ጦርነቱ እንደተጀመረ ወጣቱ ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ከጥቂት ታማኝ ወታደሮቹና አሽከሮቹ ጋር መቀሌን ለቆ አዲግራት ሲገባ የጣልያን ፕሮፓጋንዳ የዚህን ወጣት ደጃዝማች ክህደት እንደ ታላቅ ድል ተጠቀመበት። ሞሶሎኒም ጊዜ ሳያጠፋ ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሳን ራስ ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ብሎ በጣልያኖች እጅ በወደቁ የኢትዮጵያ ግዛቶች ላይ በሙሉ ገገር አድርጎ ሾመው።

ሞሶሎኒ ሲቸኩል ስሌት ላይ ተሳስቷል። ማለት የዚህን የከዳ ደጃዝማች (አሁን ራስ) ፈለግ ተከትለው ሌሎችም ሹሞች ለጣልያን ይገብራሉ ብሎ ሲያስብ ተሳስቷል። ይኼ የሞሶሎኒ ዘዴ ስህተት እንደነበረ ዴ ቦኖ ሳይደብቅ በመጽሃፉ ላይ ሲጽፍ፣ "የደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ክህደት በሌሎቹ የኢትዮጵያ ጦሮችና አለቆቻቸው ላይ ምንም ተጽዕኖ አልነበረውም" ሲል መስክሯል።

ይሁን እንጂ በኋላ ከአምባ አርአዶሙ ጦርነት ሽንፈት በኋላ ጣልያኖች ምን ያህል የኃይል ብልጫ እንዳላቸው ያዩና ሽንፈት አይቀሬ መሆኑን የተረዱ፣ በቀልን የፈሩ፣ ያለቻቸውን ትንሽ ንብረት ለማዳን ያሰቡ በርከት ያሉ ሹማምንቶች ለጣልያኖች ባንዳነት ማደራቸው አይካድም።

እንዳልኩት ንጉሠ ነገሥቱ ስለ ደጃዝማቹ ፀባይ ጠንቅቀው ያውቁ ነበርና ጦርነቱ ከመጀመሩ ከመንፈቅ በፊት ሻለቃ ካሣ የተባለ በአውሮፓ በፈረንሳይ ሀገር የጦር አካዳሚ የተማረ ታላቅ ብቃት ያለው ወጣት መኰንን ወደ መቀሌ ልከው በደጃዝማቹ ላይ መረጃዎች እንዲሰበስብ አድርገው ነበር።

ይኼ ወጣት መኰንን በትክክል ደጃዝማቹ ለክህደት እየተዘጋጀ መሆኑን የሚጠቁሙ መረጃዎች አሰባስቦ ነበር። ይሁን እንጂ የታላቁ የአፄ ዮሐንስ 4ኛ ወራሽ አገሩን ይከዳል ብሎ የሚያምነው አንድም ሰው አጣ። በመጨረሻ ተጨባጭ ማስረጃዎችን እጁ ማስገባት ቢችልም ጊዜው ዘግይቶ ነበር። ደጃዝማቹ ከድቷል።

በኋላ በጦር ሜዳ ከሻለቃ ካሣ ጋር ተገናኘተናል። ከሻለቃ ካሣ ጋር በጦር ሜዳ በተገናኘን ጊዜ ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ የመቀሌን ቤተ መንግሥት ሊጣደፍ ለቅቆ ወደ አዲግራት በሸሸ ጊዜና ሻለቃ ካሣ ከነጋድራስ ወዳጆ ጋር በዘይ መቀሌን ለአጭር ጊዜም ቢሆን በተቆጣጠሩ ጊዜ በመቀሌው ቤተ መንግሥት ያገኘውን የተለያዩ ዶክመንቶች አሳይቶኛል። እነዚህ መረጃዎች (ዶክመንቶች) አብዛኛዎቹ በጥብቅ ምስጢር የተያዙና በወቅቱ የኤርትራ ገገር በነበረው በጀነራል በኋላ ማርሻል ኢሚሊዮ ዴ ቦኖ የተፈረሙ ነበሩ።

ከነዚህ ዶክመንቶች ውስጥ በአንዱ ደብዳቤ ማርሻል ኢሚሊዮ ዴ ቦኖ ለደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ሲጽፍ፣ "የጣልያን መንግሥት በጣልያን ባንክ ባለው የደጃዝማቹ የግል የባንክ ቁጥሩ 15,000 የምኒልክ ጠገራ የብር ሽልንጎች አስገብቷል" ሲል ጽፏል።

ጥቅምት መጨረሻ ላይ ጦራችን ኮረም ሲገባ በኮረም አንድ ፈረንጅ ታስሮ በወታደሮች እንደሚጠበቅ ሰማሁ። "ጥት አባቱን! የጣልያን ሰላይ ነው። ከመቀሌ ነው ይዘነው የመጣነው" አለኝ ይኼንን እስረኛ የሚጠብቅ አንድ የመቀሌ ልጅ የሆነ ወታደር።

ይኼንን እስረኛ ፈረንጅ የታሰረበት ቦታ ድረስ ሄጄ ጎበኘሁት። በአንዲት ትንሽ ቆሻሻ ጎጆ ውስጥ በብረት ሰንሰለት ከጎጇዋ ምሰሶ ጋር ታስሮ በተጎዘጎዘው የሚሽት ሳር ላይ ተኝቷል። ይኼንን እስረኛ ባየሁት ጊዜ እንደማውቀው ባውቅም፣ የትና መቼ ይኼንን ሰውዬ እንዳየሁት ሊመጣልኝ አልቻለም። በመጨረሻ ይኼ እስረኛ ማን እንደሆነ አስታወስኩ። አዎ፣ ፓናይ ቢአሲቲ የግሪክ ነጋዴና የጣልያኖቹ ሰላይ፣ የደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ አማካሪና ቤተኛ የነበረው ነው። አዎ ምንም እንኳን በጣም የተጎሳቆለና በፊቱ ላይ ድካምና ተስፋ መቁረጥ ቢነበብበትም እሱው ራሱ ፓናይ ቢአሲቲ ነው። ላነጋግረው ፈልጌ ነበር። ግን ዘቦቹ ከለከሉኝ።

ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ከግሪካዊቷ የፓናይ ቢአሲቲ እህት ጋር በክህደት ከመቀሌ ወደ አዲግራት በመሸሽ ህይወቱን ሲያተርፍ ፓናይ ቢአሲቲን ለአርባ ቀን እድሉ በመቀሌ ተወው። "ይኼን ሰው ምን ሊያደርጉት አስበዋል?" ብዬ ራስ ካሣን ጠየኳቸው። "ለንጉሡ ወደ ደሴ እልከዋለሁ። ንጉሡ የፈለጉትን ያድርጉት። በእርግጥ ሞት ይገባው ነበር። ግን በዚህ ከንቱ ከሃዲ ደም ማን እጁን ያጨማልቃል" አሉኝ ቆጣ ብለው።

10

ጦራችን በጉዞ ላይ

የአድዋ ከተማ በጣልያን ቦምብ ተወግራ በነደደች በነጋታው ራስ ካሣ ከልጃቸው ከደጃዝማች ወንድወሰን ጋር በደህና ፈጣን ፈረስ ወደ አንድ ሰዓት ገደማ የሚያስኬድ መንገድ ተጉዘው ከ20,000 በላይ የሆነው ጦራቸው ሰፍሮ ወደሚጠብቃቸው ቦታ ሄዱ።

ራስ ካሣ ደብረ ታቦርን ከመልቀቃቸው በፊት አስጠርተውኝ አንድ ጠንካራና ሸጋ ሰንጋ ፈረስ ከሁለት በቅሎዎች ጋር ለገሱኝ። የሚበቃኝን ያህል የጭነት አህዮች እወስድ ዘንድም ትዕዛዝ ሰጡ። ቀጥለውም የኔን ደህንነት ይጠብቁ ዘንድ አቶ ተሰማን ከሃያ የታጠቁ ወታደሮች ጋር መደቡልኝ።

ከሰዓት በኋላ ጦሩ ከሰፈረበት ሜዳ ደረስን። ከሩቅ በርካታ ድንኳኖች ይታያሉ ድንኳኖቹ ፈንጠር ፈንጠር ብለው አንድ ትልቅ ድንኳን ከሌሎች አነስ አነስ ካሉ ድንኳኖች ጋር መሀል ላይ ቆሟል። ሌሎች በመቶዎች የሚቆጠሩ የተለያየ መልክና ስፋት ያላቸው ድንኳኖች ዙሪያውን አጥረውታል።

እንግዲህ ከፍ ከፍ ያሉትና መሀል ላይ የቆሙት የትልልቆቹ ሹሞች ሆኖ ትንንሾቹ ደግሞ የትናንሽ ሹሞች ድንኳን መሆናቸው ነው። ሌላው ጦር ድንኳን ቀርቶ ለአግሩ ጫማ እንኳን አልነበረውም።

በዚያ የጦር ሰፈር ትንሽ ነጣና ደመቅ ያሉ ሁለት ድንኳኖች ጎላ ብለው ይታያሉ። በኋላ እንደተረዳሁት አንደኛው የራስ ካሣ እንግዳ መቀበያ ሲሆን ሁለተኛው ራስ ካሣ ሹማምንቱን ግብር የሚያበሉበት የግብር አዳራሽ መሆኑ ነበር።

ራስ ካሣ ለራሳቸው አነስ ያሉትና ድሉት ያልጎደላት ድንኳን ነበራቸው። ሳኒም እነስ ያሉትና ሁለት የጦር ሜዳ አልጋዎች፣ ለስለስ ያሉ ፍራሾች የተዘረጉባቸውን ከአንድ ታጣፊ ጠረጴዛና ከሁለት ወንበሮች ጋር አዘጋጅተውልኝ ነበር።

በዛች የጦር ሰፈር በሁለተኛው ቀን አንድ ዐጉሬ ልውጥ፣ ደራታ ፈረንጅ ብቅ አለ። በቀጥታ ወደኔ በመምጣት "ቄስ አቶ ሄንቲገ" እንደሚባል ነግሮኝ ተዋወቀኝ። ለምን እንደሆን ባላውቅም ይኼንን ሰው ውቃቤዬ አልወደደውም። እናም እዚህ ምን እንደሚሰራ ጠየኩት። ሳቅ ብሉ ለጥያቄዬ "በሰሜን ኢትዮጵያ ብዙ ዓመት እንደኖረና በጎንደር ዙሪያ ያለ ሚሽን አስተዳዳሪ እንደሆነ፣ ጨምሮም አሁን ራስ ካሣን ሊሰናበት መምጣቱን አጫወተኝ።" አሁን ከምንጊዜውም በላይ ጠረጠርኩት።

ራስ ካሣን ብቻ ለመሰናበት በቀላሉ ከአስር ቀን በላይ ተጉዞ እዚህ ደርሷል። ብቻ ቄሱ ከራስ ካሣ ጋር በእንግዳ መቀበያ ሳሎናቸው ለብዙ ሰዓታት ሲነጋገር ቆይቶ ተሰናበተ። ቄሱ አማርኛ አሳምሮ ይናገር ስለነበረ ከራስ ጋር ስለምን ጉዳዮች እንደተወያዩ ለጊዜው የሚያውቅ ሰው አልነበረም። ይሁን እንጂ ብዙ ሳይቆይ ወሬዎች ብቅ ማለት ጀመሩ።

እንደሰማሁት ቄሱ ለራስ ካሣ ከኤርትራው ገዢ ምስጢራዊ ደብዳቤ ይዞ መጥቶ እንደነበረና በዚሁ ደብዳቤ የኤርትራው ገዢ ራስ ካሣን "ከነጦራቸው እጅ እንዲሰጡና ከጣልያን ወገን ይገቡ ዘንድ የሚያግባባ" ነበር። ይሁን እንጂ ቄሱ ያለምንም ውጤት ተመልሷል።

ጦሩ በሶስተኛው ቀን ወደ ሰሜን ጉዞ ጀመረ። መጀመሪያ አካባቢ ጦራችን ለሶስትና ለአራት ሰዓት ያህል ተጉዞ ያርፍ ነበር። ይኼም በአብዛኛው ጦራችን እግረኛ ስለነበር ራስ ጦሩ እንዳይደክም በማሰባቸው ነበር።

እዎ አብዛኛው ሰራዊታችን ከየጥሻውና ከየአምባው የመጣና ጦርና ጎራዴ ብቻ የታጠቀ፣ በመጀመሪያው ቀን ውጊያ ጠላት ገሎ ጥሩ መሳርያ ለመታጠቅ በጽኑ እምነት የቆመ ጀግናና ጉጉ ጦር ነበር። በዚህ እንደሞላ ወንዝ እያጓራ በሚጓዝ ጦር ውስጥም እንደነገሩ ሸማ የተከናነቡና በጀርባቸው በቅርጫት ሙሉ የማብሰያ ቁሳቁሶች ያዘሉ ሴቶችም ነበሩ። የሚጠባ ልጅም የተሸከሙ ታይተዋል።

በዚህ መልኩ በመንገድ የገጠመውን ሁሉ እየጠራረገ የሚነጉደው ጦር ስርዓት አልባ ነበር። እያንዳንዱ አነስተኛ ሹም ጦሩን እየያዘ፣ የራሱን መንገድ እየወጣ፣ በጦር ሜዳ ከሌላው ዘግይቶ ላለመድረስ ፉክክር ገጥሞ ነበር። አንዳንድ ሹሞች ዋናውን መንገድ ትተው አቋራጭ ፍለጋ ተራራውን እየቧጠጡ ሲወጡ የጉንዳን

ሰራዊት ይመስሉ ነበር። ትንሽ ለየት የሚለውና ስርዓት ይዞ የሚጓዘው የራስ ካሣ ጦር ነበር።

ከፊት በርካታ ጡሩንባ ነፊዎች የነሀስም ድምጽ የሚተፉ ጡሩምባቸውን እየነፉ ይጓዛሉ። ከጡሩንባ ነፊዎች ቀጥሎ የራስ የክብር ዘበኛ ጦር አጓራው እስኪጨስ ይረግጣል ስል በጠጉ ተሰልፎ ሳይሆን ሁሉም ባሻው መንገድ እየጊያ ብቻ ይረግጣል። ይረግጣል ለማለት ያህል ነው። የራስ ካሣ የክብር ዘብ አዛዥ ቀኛዝማች አቧራውን ያጨሰዋል ለማለት ያህል ነው። (እኔ ብሆን ቀኛዝማች አንበሳ እለው ነበር) እንደ አንበሳ በፈረሱ ላይ ተጀግኖ አበበ እንደ ተቀመጠ ጦሩን ቀድሞ ይመራል። ከክብር ዘቡ ጦር በመቀጠል ራስ ባጌጠ ፈረሳቸው ላይ ሆነው ይኼዳሉ።

ከራስ በኋላ ሁለት አሽከሮች ይሮጣሉ። አንዱ አሽከር ተንቀሳቃሽ ዙፋናቸውን ተሸክሟል። ሁለተኛው ጥቁር ሆኖ መያገርው በብር ያጌጠ ከዘራቸውን ይዞ እሱም ይሮጣል። ከሁለቱ አሽከሮች ኋላ ሁለት ሌላ የራስ መሳሪያ ያገኙም ይሮጣሉ። ከነዚህ በኋላ የራስ ካሣ ልጅ ደጃዝማች ወንድወሰን ከሁለት ትላልቅ ሹማምንቶች (በጀርንድ ለጥይበሉና ቀኛዝማች ደህኔ) ጋር በፈረስ ይከተላሉ።

እኔም በፈረሴ እንደተቀመጥኩ ከራስ ካሣ ጎን እንድኼድ ተፈቅዶልኛል። ይኼም ታላቅ ክብር ነው፣ ከትልቁ ከራስ ጎን በፈረስ መጓዝ። ብቻ በዚህ መልኩ ፈረሰኛው ጦር እንደየማዕረጉ እየተሰለፈ ከኋላው እግረኛው ጦር፣ ከእግረኛው ኋላ እስከመጨረሻ ቁሳቁስ እና ስንቅ የተጫኑ ብዙ አህያዎች፣ አጋሰሶች፣ በጎች ፍየሎችና ለንጋዎች ጋር እነሱም በመንገዳቸው አቧራውን እያጨሱት ይኼዳሉ። በመጨረሻ ምግብ አብሳይ ሴቶችና አንዳንድ የሹማምንቱ የጭን ገረዶች ጠባቂ ተደርጎላቸው ይጓዛሉ።

ራስ ካሣ ተራራ ይወዳሉ መሰል በባሊበላና በሰቆጣ በኩል በቀላሉና በፍጥነት መገስገስ እየቻልን ራስ ተራራማና አስቸጋሪውን የደብረ ዘቢጥን መንገድ መረጡ። በመጀመሪያው ሳምንት ኋላ ቀር የሆነውን የስልክ ገመድ ባልተጠረቡ እንጨቶችና በዛፎች ላይ እየዘረጋጉ ከአዲስ አበባ ጋር ግንኙነት ለማድረግና ከንጉሠ ነገሥቱ ተጨማሪ ትዕዛዝ ለመቀበል ተሞከረ።

አልፎ አልፎ ግንኙነቱ እየሰመረልን ከቤተ መንግሥት ጋር መረጃዎች ተለዋውጠናል። በዚህ መልኩ አንድም ሁለትም ቀን እያረፍን አዲስ የሚመጣውን ጦር እየተቀበልን፣ ወታደሩ የጦርነት ልምምድ ያደርግ ዘንድ ሀሳብ አቀረብኩና የመጀመሪያውና የመጨረሻውም ልምምድ ተደረገ።

እንደ እባብ እየተሽሎኮሎኩ፣ ባገኙት ሁሉ እየተሸፈኑ ጠላትን እንዲያጠቁ የሚሰጣቸውን ትዕዛዝ ወታደሮቻችን ያለአንዳች ማመንታት እየፈጸሙ ከተራራው ጫፍ ደርሰው በፉከራና በሽለላ ጦራቸውን ለመወርወር፣ በጎራዴያቸው የጠላትን አንገት ለማረድ ቢዘጋጁም ነገሩ ልምምድ ነውና ሀዘንና ንዴት ፊታቸው ላይ

እየተከበበ፣ "ጣልያኖች የት ናቸው?" በማለት በሹሞቻቸው ላይ አፈጠጡ። ይኼ ልምምድ ብቻ እንደነበረ ሊገባቸው አልቻለም። እና በሁለተኛው ቀን ለልምምድ አንድም ወታደር ብቅ ሳይል ቀረ። ለዝበራ ወታደሮች እየተንፏቀቁና እየተሳቡ፣ እንደዘንዶ እየተወረወሩ ወደ ተራራ መውጣትና መውረድ፣ ጣልያኖች በዚያ ከሌሉ ከንቱ ድካም ነው። እንዲህ እነዚህን ምስኪን ባላገሮች ሳይ ሰውነቴን ወረረኝ። እንዴቱ ተንዘፈዘፈ። እም ቤት ንብረታቸውን፣ ልጆቻቸውን፣ ከብቶቻቸውን ለአዛውንቶችና ለሴቶች በትነው፣ ተራራ ወጥተው፣ ወንዝ ተሻግረው እዚህ ከማያውቁት ሀገር ደርሰዋል።

11

ዝቅ ካለ ሰማይ ስር

በየቀኑ የተለያዩ ሹማምንቶች ጦራቸውን እያያዙ መጥተው ከኛ ጦር ጋር ይቀላቀላሉ። ከፍ ከፍ ያሉት ሹማምንቶች ከራስና ከልጃቸው ከደጃዝማች ወንድወሰን ጋር ይሳሳማሉ። አነስ ያሉ ሹማምንቶች በራስ ካሣ ፊት ቀርበው ፊታቸው መሬት እስኪነካ እጅ ነስተው ይዘውት የመጡትን ጦር ብዛትና ጀግንነት እየተናገሩ፣ ይኼ ይዘውት የመጡት ጦራቸው ከራስ ካሣ ጦር ጋር በታማኝነት ለሀገሩና ለንጉሠ ነገሥቱ ተዋግቶ ይሞት ዘንድ ይለምናሉ።

የራስ ካሣ ጦር እጅግ በማደጉ በጉዟችን ላይ ጠባብ መንገድ ወይም ወንዝ ወይም ደግሞ አስቸጋሪ የሰርጥ መንገድ በገጠመን ቁጥር በሹማምንቱ መሀል ጭቅጭቅ ይፈጠራል። ይኸውም ጭቅጭቅ የኔ ጦር ይቅደም የኔ በማለት ነው። እኔ ለራስ ካሣ እንዲህ አይነት ችግሮች ዳግም እንዳይፈጠሩ ዘዴ እንዳለኝና ለዚያም የሰራዊታችንን ትክክለኛ ቁጥር ማወቅ እንዳለብኝ አስረዳኋቸው። ራስ ካሣም አሳቤን በደስታ ተቀብለው ስለሰራዊቱ ቁጥር ሁሉንም ቀኛዝማች አበበ እንደሚነግረኝ አስረድተው ወደ ቀኛዝማች አበበ ላኩኝ።

ቀኛዝማች አበበ ከሁለት አዛውንቶች ጋር በድንኳናቸው ተቀምጠው ጠጅ እየጠጡ ይጫወታሉ። ምን እንደሚያወሩ ባይሰማም አልፎ አልፎ ሳቃቸው ከሩቅ ይሰማ ነበር።በቀኛዝማች ድንኳን ገና ከመቀመጤ አሽከራቸው በቀንድ ዋንጫ ጠጅ

ሞልቶ ሰጠኝ። "ለጊዜው ጠጅ ነው። ያ እናንተ የምትወዱትን ቢራ የለኝም። እንደቢራ ባይሆንም ጥሩ ጠጅ ነው። ይጣሁ ጌቶች ይበሉ" እያሉ ቀኛዝማች እንደቢራ እንድጨልጥ ገፋፉኝ። እኔም ዋንጫዬን ከመጨለጤ አስከርዬው ከምኔው ዋንጫዬን እንደሞላት እንኳ ማስተዋል እየተሳነኝ የመጣሁበትን ጉዳይ አስረድቼ በትክክል የሰራዊቱን ቁጥር እንዲነግሩኝ ቀኛዝማች አበበን አጥብቄ ጠየኩ። ቀኛዝማች አበበ ጥያቄዬን ወደጎን በመተው ከወር በኋላ አስመራ ስንገባ ጥሩ እውነተኛ የጣልያን ቢራ እንደሚጋብዙኝ ደጋግመው ቃል ገቡልኝ።

ሶስተኛ ዋንጫዬን እንደያዝኩ በድጋሚ ጥያቄዬን አምርሬ አቀረብኩ። አሁን ቀኛዝማች አበበ በመገረም እያዩኝ "የወታደሮቹን ቁጥር ነው ያልከኝ ጌታው?" አሉኝ። "አዎ ቀኛዝማች፣ የወታደሮቹን ቁጥር ማወቅ አስፈላጊ ነው" አልኳቸው። "እሱንማ" አሉ ቀኛዝማች አበበ አሁን መሬት መሬት እያዩና በሁለቱም እጃቸው ጎፈሬያቸውን እያፍተለተሉ፣ "እሱንማ እግዜር ብቻ ነው የሚያውቀው። እኔማ እንዴት አውቄው? እዚህ ማንም አያውቅም" አሉኝ።

ቀኛዝማች አበበ እንኳን የጠቅላላ ጦሩን ቁጥር ሊያውቁ ቀርተው ራሳቸው ያመጡትን ጦር እንኳ በግምትም ቢሆን አያውቁም ነበር። እናም አላዋቂ መሆናቸውን ለመሸፈን ያህል "ጌታዬ፣ መድፉኛ ጠርምኮ አለን" አሉኝ።

በጣም ገረመኝ። ከጦሩ ጋር አንድ ሳምንት ሙሉ ስጓዝ እንኳን መድፍ ቀርቶ መድፍ የሚመስል ብረት እንኳ ሳላየሁምና እንደ መሳቅ ሲቃጣኝ፣ ቀኛዝማች አበበ እንደመቆጣትና ጮክ ብለው፣ "ተመልከት ጌታው!" ብሎ ከድንኳኗ ጀርባ ጨርቅ የተሸፈነች ነገር ገልጦ አሳየኝ። አዎ ብዙ ቁርጥራጭ ብረቶችና ኋላ ቀር የሆኑ የመድፍ አሮጌ ሳይቀሩ ተደርድረዋል። አሁን እንደምንም ሳቄን አፌን አደረኩ። ቀኛዝማችን ላስከፋቸው አልፈለኩም። ብረቶቹን ላያቸው ሰው ሙዚየም መቀመጥ የሚገባቸው፣ በታላቁ የአድዋ ድል በእምዬ ምኒልክ የጦር ሰራዊት ከጣልያኖች የተማረኩ እንደሆኑ ያስታውቃሉ። "እና ይኼው ነው?" አልኳቸው። ቀኛዝማች አበበ ጥያቄ ብዙም ሳይጨነቁ፣ "ምን ችግር አለው? ታያለህ፣ ለጊዜው ሁለት መድፎች ብቻ ናቸው ያሉን። ከጣልያኖች ጋር ስንገጥም ከእግዚአብሔር እርዳታ ጋር ብዙ መድፎች ይኖሩናል። ጣልያኖቹን በገዛ መድፋቸው ቀይ ባህር ውስጥ ነው የምንከታቸው" አሉኝ ፍፁም እርግጠኛና ሙሉ ወኔ በተሞላበት ቁራጥ ድምጽ።

በኋላ ከቀኛዝማች አበበ እንደተለየሁ እንደነገሩ በይሆናል በተሰራ የግምት ቁጥር እቅዱን አወጣሁኝ። ይሁን እንጂ ጥቅም ላይ ሊውል አይችልም ነበር። እንዳቸውም ትላልቅ ሹሞች ሊገባቸው ካለመቻሉ ሌላ አስፈላጊነቱ ሊገለጽላቸው አልቻለም። ራስ ካሣ ግን በጣም ተደስተውበት በጥንቃቄ መረጃ ከሚያስቀምጡባት ሳጥናቸው ውስጥ ጨመሯት።

የኛ ጦር እንዲህ ባለ ሁኔታ በዘመናዊ መልኩ ከሰለጠነና ዘመናዊ መሳርያ ከታጠቀው የጣልያን ጦር ጋር ሊገጥም "ወደፊት" ተጓዘ። የጣልያን አውሮፕላኖች አሁን አሁን እስከ መሀል ሀገር ድረስ ዘልቀው መብረር ጀምረዋል። የሰማይ ላይ ብቸኛ ንጉሦች ናቸውና ባሰኛቸው ሰዓት ሁሉ ዝቅ ብለው እየበረሩ የሀበሻውን ጦር ይቃኙታል።

አንድ ማለዳ በድንኳኔ ውስጥ ጋደም እንዳልኩ የሚንጣጣ የመትረየስ ድምጽ ሰማሁና ተስፈንጥሬ ወጣሁ። በርከት ያሉ የኢትዮጵያ ወታደሮች መትረየሶች ጠምደው ያለማቋረጥ ይተኩሳሉ።

በሁኔታው ተገርሜ መትረየስ አስተኳሹን አዛዥ ምን እንደተፈጠረ ብጠይቀው፣ "አይ ጌታው! እንዳው የጣልያን አውሮፕላኖች ሰሞኑን ድርሽም አላሉ። ያው መምጣታቸው አይቀርምና ባይሆን እስኪመጡ ወታደሮቼ በአሞራዎች እንዲለማመዱ ብዬ ነው" አለኝ። ቆም አልኩና ተኳሾቹን አስተዋልኩ።

ከፍ ብሎ በሰማዩ ላይ ተለቅ ተለቅ ያሉ አሞራዎች ይንሳፈፋሉ። ከታች ከመሬት የመትረየስ መአት ቢወርድባቸውም ደንታ ሳይሰጣቸው እነዚያ የሰማይ ላይ ጀቢራዎች መንሳፈፋቸውን ቀጥለዋል። ይኼ የአሞራዎቹ ንቀት ያናደደው አንድ ወታደር መትረየሱን ወርውሮ ምንሽሩን ከጣለበት አንስቶ አቀባበለና በመጀመሪያዋ ጥይት አንዱን አሞራ አወረደው። ወዲያው ሁሉም መትረየስ ተኳሾች መትረየሳቸውን ወደጎን ትተው በጠመንጃ የሰማይ ላይ አሞራዎችን ወደ መሬት ያወርዷቸውና ያረግፏቸው ጀመር።

ኢትዮጵያውያን በአለም እውቅና ተወዳዳሪ የሌላቸው አልሞ ተኳሾች ቢሆኑም በመትረየሱ ተኩስ ግን ገና ብዙ ይቀራቸው ነበር። ሰራዊታችን ገና ከዘመኑ መሳሪያዎች ጋር እንዳልተዋወቀ ይገባኝ ጀመር።

በሚቀጥለው ቀን ምሳ ሰዓት አካባቢ የራስ ካሣ ጸሐፊ እየተጣደፈ መጥቶ "ጌቶች ቶሎ ቶሎ ይበሉ፣ ይከተሉኝ ጌታዬ" እያለ እየተጣደፈ መንገድ እየመራኝ ሲሮጥ እኔም በሩጫ ተከተልኩት። እየሮጥን ምን እንደተፈጠረ ጠየኩት። "ጌቶች፣ አንድ ወታደር ቆስሎ አመጡት" አለኝ። ይኼን የራስ ካሣን ጸሐፊ ተከትዬ ወደ ድንኳን ስገባ አንድ ሆዱ ላይ በጥይት የተመታ የገበሬ ወታደር ልክ እንዳመጡት ከዝንጣፊ ቅርንጫፎች በተሰራ ቃሬዛ ላይ በጀርባው ተጋድሞ አየሁ። ቁስለኛው ከቃሬዛው እንዳይወድቅ እግሩን በጠፍር ታስሯል። ከፍ ብሎ ወደ ደረቱ አካባቢ በሌት መቀነት ሸብም አድርገውታል። ጎንበስ ብዬ ቁስሉን አየሁት። ከሞላ ጎደል የሆድ እቃዎቹ በሙሉ ወደ ውጭ ወጥተው ተዘርግፈዋል።

"ዶክተር ጥሩ!" ብል ሁሉም በአንድ ላይ አይናቸውን አፈጠጡብኝ። አዎ ለነዚያ ምስኪን ገበሬዎች ፈረንጅ ሁሉን አዋቂ ነበር። እና ዛሬም ያንን ምስኪን በፈረንጅ እጁ እንድረዳው በአይናቸው ተማጸኑኝ። ዋይ ዋይ፣ ማን በነገራቸው! እንኳን

ለማግኘት ዝግጁ ሆነው ቢጠብቁም፤ በፍጥነት እንዲገቡ ...

ቀስለኛ ማከም ቀርቶ የመድሃኒት ስሞች እንኳ ጠንቅቄ ስለማወቄን፡፡ "እምቢ አይሆንም፤ አልችልም፤ እኔ ዶክተር አይደለሁም፤ ቁስለኛ ማከም አልችልበትም እንዳልል የሚያምነኝ ማንም ሰው የለም፡፡ ብቻ ማንገራገሬን ያዩ አንድ ግራዝማች፣ "ጌታዬ ኦፕራሲው ባይሳካ ምንም አይደል፡፡ እንዲሁ ብንተወውም መሞቱ አይቀርምና አይዞዎት ሊረዱት ይሞክሩ" እያሉ አደፋፈሩኝ፡፡

በዚህ መሀል ኮቴን አውልቄ እጄን ታጥቤ ጎንበስ እንዳልኩ አንድ የሃበሻ መርፌ ወጊ መጥቶ ገላገለኝ፡፡ የሃበሻው መርፌ ወጊ ምንም አይነት የህክምና ትምህርት የለውም፡፡ ምንምም የህክምና መሳሪያዎች አልያዘም፡፡ ብቻ አንድ ጎጆ አረቄ ሲጠጣ ወሬውን ሰምቶ መጥቶ፣ እኔን ወደጎን ገፋ አደረገኝና ወደ በሽተኛው ተጠግቶ፣ እጁን እንኳ ሳይታጠብ ሆድ እቃዎቹን በነዚያ እጆቹ ወደ በሽተኛው ሆድ ጨምሮ በተራ መርፌ እንደ ድንች ኪሻ ሰፋው፡፡

ከዚያች ድንኳን ተመልሼ ቀኛዝማች አበበ ከለገሱኝ አረቄ አንድ ስኒ ቀዳሁና ጨለጥኳት፡፡ ልቤ ክፉኛ አዘነ፡፡ ጦራችን አንድ እንኳ ዶክተር አልነበረውም፡፡ የመድሃኒቱ ነገርማ አይነሳ ነው የሚባለው፡፡ በድጋሚ አረቄዋን በስኒ ሞልቼ ጠጣሁና አልጋዬ ላይ ዘፍ አልኩ፡፡ ሳላስበው አይኖቼ ያለቅሱ ጀመር፡፡ ልቤ ግን እንደ ጥቁር ድንጋይ እንደጠነከረ ይሰማኝ ነበር፡፡

እንዲህ በጦር ሜዳ አልጋዬ ላይ ተዘርግቼ አረቄ የያዘች ስኒዬን እንደጨበጥኩ ወደፊት ብቆስል፣ ልሞት ባጣጥር፣ ብሞት፣ እሞታታለሁ እንጂ በዚህ መርፌ ወጊ ዶክተራችን እንደማልታከም ለራሴ ቃል እየገባሁና ሌላም ሌላም ነገሮች እያሰላሰልኩ የቀኛዝማች አረቄ ስራዋን ሰርታ ኖሮ ተኛሁ፡፡ ጠዋት የተነሳሁት በአቶ ተሰማ ተቀስቅሼ ነው፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ከጦሩ ዘግይቼ ከመነሳቴም በላይ በአቶ ተሰማ በመቀስቀሴ ትንሽ እፍረት ተሰማኝ፡፡ ግን ለዚህ አሁን ጊዜ የለምና አቶ ተሰማም ፈረሴን ጭነውልኝ ስለነበር ቁርስም ሳላደርግ ጉዞ ጀምረን ወደፊት ሄድን፡፡

ደብረ ዘቢጥን እንዳለፍን የጦራችንና የስልኳ መንገድ ተለያየ፡፡ ካሁን በኋላ ከንጉሠ ነገሥቱ ዋና የጦር ድንኳን ጋር የምንገናኘው በራዲዮ ብቻ ሆነ፡፡ በእንዲህ አይነቱ ኋላ ቀር በሆነ ራዲዮ የምናደርገው ግንኙነት በቀላሉ ለጠላት አሳልፎ እንደሚሰጠንና እንደሚያጋልጠን ለራስ ካሣ አስረዳሁ፡፡

አማራጭ ባለመኖሩ አግዜር ይጠብቀን ብለን ግንኙነታችንን በተቆለፉ ቃላት መፍቻ አድርገን መረጃዎች ከአዲስ አበባ ጋር ብንለዋወጥም ብዙም አልረዳንም፡፡ ጣልያኖች ከኛ ቀድመው ይፈቱትና በሜትር ርቀት ስፈራችንን አካለው ያውቁ እንደነበር ኋላ ላይ ተረድቻለሁ፡፡

ምንም እንኳን ከደብረ ታቦር ከመነሳታችን በፊት ራስ ካሣ 400 አዲስ ጠመንጃዎች ቢያገኙም ለራሳቸው ወታደሮች እንኳን አልተዳረሰም ነበር፡፡ የቀረው ጦር እንግዲህ እንዲህ መላቅጡ በጠፋ ሁኔታ ከራሱ ጎጆ የሰቀላትን ጠብመንጃውን

አውርዶ፣ በራሱ ጥይት ዝናሩን ታጥቆ፣ ጎጆው ያፈራትን ስንቅ ቋጥሮ ወደፊት በታላቅ ቆራጥነት ይገሰግሳል፡፡

አንዳንድ የጦር ሹማምንቶች የራሳቸው አብሳዮች አሉዋቸው፡፡ ሳላው ሹም ለአቅመ አዳም እንኳ ያልደረሰ ወንድ ልጅን አስከትሏል፡፡ እነዚህ ልጆች በጉዞ ላይ የአባታቸውን ከባድ መሳርያ ተሸካሚዎች ሲሆኑ ማታ ማታ ጦሩ ሲያርፍ የማብሰያ እንጨትም ይሰበስባሉ፡፡ እነዚህ ልጆች ወደፊት እንደምናየው በጦር ሜዳ "በልጅ ጦር" ስር ተሰልፈው በታላቅ ጀግንነትና ቆራጥነት ከፍተኛ እና ታሪክ ሊጽፈው የሚገባ ጀብድ ሰርተዋል፤ ፈፅመዋል፡፡ እንግዲህ እንዲህ በጣም አሳዛኝ በሆነ መልኩ የታጠቀው ጦራችን የቀድሞ ደላንታን ተራሮች እየታከከ ወደ ሰሜን ገሰገሰ፡፡



12
ዋድላ

እነሆ ጦርነቱ ከተጀመረ ሁለት ሳምንት አለፈው። ጣልያኖች ከተከላካዩ የኢትዮጵያ ጦር ይኼን ያህል ብዙ ችግር ሳይገጥማቸው በቀላሉ አዲግራትንና አድዋን ይዘው ሌሎች ከተሞችን ለመያዝ በዝግጅት ላይ ናቸው።

ጣልያኖች እንዲህ ወደፊት ሲገፉ የራስ ካሣ ጦር ከጎጃም በጣም ቀስ እያለ ወደ ሰሜን ያዘግማል። በእያንዳንዷ ቀን በማለዳ ተነስተን እየገሰገስን እስከ ምሽቱ ድረስ በጉዞ ላይ ብንሆንም ይኼን እኛ ቀኑን ሙሉ የተጓዝነውን መንገድ ጥሩ ፈረሰኛ በሁለት፣ ቢበዛ በሶስት ሰዓት ውስጥ ያጠናቅቃል።

ለምን እንዲህ ሊሆን ቻለ? ብለን የጠየቅን እንደሆን መልሱ በጣም ቀላል ነው። ራስ ካሣ ተራራ ይወዳሉ። ከተራራዎችም በላይ ቤተ ክርስቲያናትን ያፈቅራሉ ብል ማጋነን አይሆንብኝም። እጅጉን በጣም ሲበዛ አማኝ ናቸው። በልጅነት ዘመናቸው ቄስ መሆን ይመኙ እንደነበር አንዳንድ ውስጥ አዋቂዎች ይናገራሉ። ይሁን እንጂ ግዛታቸውን ማስተዳደርና ሃይማኖተኛ መሆን አንድ ላይ ሊሄዱ ስላልቻሉ ራስ በመጨረሻ ወደ ሀገር ማስተዳደሩ መመለስ ተገደዱ። እናም ይኸው ደረጃ በደረጃ ከተራ ፊታውራሪነት እነሆ ዛሬ ራስነት ደረጃ ደርሰዋል።

በየቀኑ ማለት ይቻላል ቤተ ክርስቲያን ፍለጋ በርካታ ሰዓቶች በከንቱ እናጠፋለን። ምናልባት በመንገዳችን ላይ ቤተ ክርስቲያን ካላጋጠመን ራስ ካሣ ወደ አንድ ከፍ ወዳለ ጉሊት መሳይ ነገር ላይ ወጣ ብለው በጦር ሜዳ መነጽራቸው አካባቢውን፣ ተራራውን፣ ሸንተረሩን እየቃኙ እና እየዳሰሱ ናፍቆታቸውን ይወጣሉ። አዎ ራስ ካሣ ይኼንን ግዛት ከነበኙት በርካታ ዓመታት አልፈዋል። አዎ በዚህ አሁን

በለጋነት ግዛት ራስ ካሣ ጠቅላይ ገዢ ብቻ ሳይሆን ዋና ዳኛም ናቸው። ስለዚህም መሰለኝ ወደ እዚህ ግዛት ከገባን ቀን ጀምሮ የአካባቢው ነዋሪዎች በየጊዜው እየመጡ ጌታቸው በሰላም ስለመጣላቸው መደሰታቸውን ይገልጻሉ፣ አቤቱታዎች ያቀርባሉ፣ እውነቱን ለመናገር አቤቱታዎቹ ይበዛሉ።

ይኸው ዛሬም ራስ ካሣ ገና በዙፋናቸው ከመቀመጣቸው የአደባባይ ፍትህ ፈላጊዎች የአካባቢው ነዋሪ ሰዎች ያደፈና በላያቸው ላይ ያለቀ ነጠላቸውን እያደዘዙ፣ ግራና ቀኝ አደገታቸውን በማሰር በራስ ካሣ ችሎት ፊት ለመቅረብ እየተጋፉ ወደፊት ይላሉ። አዎ እንዲህ አይነት ፍትህ ፈላጊዎች በራስ ካሣ ችሎት ፊት ለመቅረብ ለአመታት ጠብቀዋል። እና ዛሬ ይቺ እድል እንዳታመልጣቸው ባለ በሌለ ኃይላቸው ከፊታቸው የቆመውን ህዝብ እየገፉ እና ዱላ ቀረሽ ግፊትግፊት ውስጥ እየገቡ ብቻ ሁሉም ወደፊት ይላሉ።

አዎ ይኼን አይነቱ የአደባባይ ችሎትና ፍትህ ምን ያህል የአዕምሮ ርካታ እንደሚያስገኝ የሚገባው ኢትዮጵያዊ ብቻ ነው። ኢትዮጵያውያን በተፈጥሮ ነገረኞች ሆነው ሳይሆን የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ትልቁ ምኞት በአደባባይ ችሎት ላይ ቆሞ ነገር አዋቂነቱን ማሳየት ነው። ይኼ አይነቱ አጋጣሚ ደግሞ ከፍ ላለ ሹመትም መንገድ ከፋች ብቻ ሳይሆን በአካባቢው ነዋሪዎች መካከል ከሳም ይሁን ተከስ በችሎቱ ስላደረገው ንግግር ለዓመታት ሲወራለት ይኖራል። አዎ እውነቱን ለመናገር እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ በተፈጥሮው አውቆ ተናጋሪ ነው።

“በታላቁ ንጉሥ በቴዎድሮስ አምላክ! በአምዬ ምኒልክ አምላክ! እኔ ገብረ ጊዮርጊስ የራስ ካሣ ታማኝ አሽከር” ብሎ ገብረ ጊዮርጊስ በጎረቤቱ ላይ ክሱን በራስ ካሣ ችሎት ፊት ይጀምራል። ከሳሽ ገብረ ጊዮርጊስ ጎረቤቱን ሲከስ “በመተት፣ በጥንቆላና በድግምት ላሜን ጡቷን አድርቆ ይኼው ለዓመታት አመሰናት” ሲል ክሱን ሰነዘረ።

ይኼን ክስ በራስ ካሣ ችሎት ሲያቀርብ ገብረ ጊዮርጊስ የችሎቱ ደንብ እንደሚያስገድደው ሁሉ የአሮጌ ነጠላውን ሁለት ጫፎች ብብቱ ስር ያስርና ወደታች እንደቀሚስ ለቅቆ፣ በመሬት ላይ የሚጎተተውን ሁለቱን የነጠላ ጫፎች ደግሞ ወደላይ ወስዶ በትከሻው ላይ ጣል ያደርጋቸውና፣ ከቆመበት ቦታ የቀኝ እጁን ጣቶች አፉ ላይ ይደገፍና፣ ወደ ራስ ካሣ ዙፋን ተንደርድሮ እየሮጠ አጠገባቸው ሲደርስ እንደምንም ይቆምና ልክ ከአፉ የሚወጡትን ጣፋጭ ቃላት ለራስ ካሣ እንደሚወረውር ሁሉ ጣቶቹን ወደ ራስ ካሣ ያወናጭፋቸዋል። በእንዲህ አይነት ሁኔታ እየተንደረደረ ይሮጥና ቃላቱን አሽጎድጉዶ ወደ ቦታው ይመለስና፣ ነጠላውን እንደገና አስተካክሎ እንደገና እየተንደረደረ ሮጦ ለዓመታት የተዘጋጀባቸውን ቃላቶችን ወደ ራስ ካሣ ዙፋን ይወረውራል።

ተከሳሹ ለጊዜው በቦታው ቆሞ ተራው እስኪደርስና በታላቁ የዘፋኝ ችሎት ፊት እሱም እንደ ከሳሽ ጎረቤቱ ንግግር አዋቂ መሆኑን ለጠቅላላው ሀገር ለማሳወቅና፣ ጎረቤቱ እንደወነጀለው መተተኛና ድግምተኛ እንዳልሆነ ለማሳወቅ ትእግስት አጥቶ በእልክ ይንቀጠቀጣል። ጥርሱን ያፋጫል።

ገና ከሳሽ ክሱን አቅርቦ ትንፋሹን እንኳን ሳይውጥ ተከሳሽም ልክ እንደ ከሳሽ ጎረቤቱ ሁሉ ያቺን ያደፈችውንና በመበጣጠስ ላይ ያለችውን ነጠላውን አስተካክሎ ከከሳሽ ጎረቤቱ ባላነሰ ፍጥነት ተንደርድሮ አየርጠ "ኃይለ ሥላሴ ይሙት፣ እግዚያብሔርም ምስክሬ ነው" እያለ እጁ ሌባ ጣቱን ቀስሮ ወደ ሰማይ ሲያሳይ ቆይቶ በአንገቱ ያሰራትን ማተቡን አውጥቶ፣ ለምናልባቱ ብሎ ደጋግሞ እየሳማት፣ ድግምተኛ እና መተተኛ አለመሆኑን እያስረዳ ራሱን ያለ ጠበቃ ተከላከለ።

ተከሳሽ ማተቧን ስሞ ወደ ውስጥ እንኳን ገና ሳይከታት ገብረ ጊዮርጊስ እንደገና ወደ ዘፋኙ ችሎት እየተንደረደረ በድጋሚ ክሱን በተመረጡ ቃላት አጣፍጦ አቅርቦ ወደ ቦታው ተመልሶ ነጠላውን ሲያስተካክል፣ ህዝቡም ፀጥ ብሎ የሚሆነውን በሚጠብቅበት በዚያች ቅጽበት አንድ የራስ ካሣ ወታደር፣ "ምን ያለው ክብት ነው" ሲል አስተያየቱን በገብረ ጊዮርጊስ ላይ ሲሰነዝር ወይም አናንቆ ሲሳደብ፣ በዚያችው ቅጽበት ገብረ ጊዮርጊስ ሰምቶት ኖሮ ገብረ ጊዮርጊስ ድምጹን ወደ ሰማበት አቅጣጫ ፊቱን አዙሮ፣ "የት አባቱንሳ! የውሻ ልጅ!" ብሎ ተሳደበ። የተሰደበው ወታደር ዓይኑን ጎልጉሎ፣ ጎራዴውን መዘዞ በዚያ በተሰበሰበው ህዝብ እንኳን እንዴት ዘሎ ገብረ ጊዮርጊስ አጠገብ እንደደረሰ ሳንገነዘብ የገብረ ጊዮርጊስ አንገት እስከ መጨረሻው ሊቀነጥሳት ሲል፣ የወታደሩ ጓደኞች ደርሰው ያቺን ቀጭን አንገት ከመቀንጠስ አዳኗት።

እዎ በኢትዮጵያ ከዚህ የከፉ ስድቦች ብዙ ቢሆኑም የኢትዮጵያን ወታደር "አባትህን የማታውቅ የውሻ ልጅ" ብሎ መስደብ ግን ና ግደለኝ እንደማለት ነው።

ራስ ካሣ ለጥቂት ጊዜ እንኳን መሳቃቸውን ያላቋረጡት አሁን ምልክት ሲሰጡ በዚያ ችሎት የተሰበሰበው ሰው ሁሉ ፀጥ አለ። ወዲያው ራስ ካሣ በተረጋጋ መንፈስና ድምጽ ፍርዳቸውን ሲሰጡ፣ ተከሳሹ ዝብሬ እውነት እንዳለው አስረግጠው ከተናገሩ በኋላ ገብረ ጊዮርጊስን ወደፊት ክብቶቹን በደንብ እያበላ እያጠጣ እንዲንከባከብ ጭምር አስጠነቀቁት። ይኼም የራስ ካሣ ውሳኔ ይግባኝ የሌለው የመጨረሻ ፍርድ መሆኑን ነግረው የዛሬው ችሎት በዚሁ ተፈታ፣ ተበተነ፣ አለቀ።

ሁለቱ ጎረቤታሞቹ ገበሬዎች ላለፉት ሁለት ሶስት አመታት ተጣልተው በባላገራነት ቢኖሩም በዛሬው ችሎት ሁለቱም ተደስተዋል። 1ኛ ተከሳሽ ለጎረቤቱ በክሱ መሰረት ለመሰነቺው ላም ተተኪ ወላድ ላም ባለመክፈሉ፣ 2ኛ ምንም እንኳን በክሱ ቢሸነፍም ከሳሽም ተደስቷል። በዚያ ሁሉ ህዝብ ፊት ንግግር አዋቂነቱን በታላቁ

የራስ ካሣ ችሎት ፊት አሳይቷልና ይኼው እንደገና እንደ ወንድማማች ተቃቅፈው፣ ተሳስመው፣ እንደ ጥሩ ጎረቤት ጎን ለጎን ተያይዘው ወደ ቀበሌያቸው በደስታ ሄዱ።

በእዚህ መሀል ዋናው ጦራችን ደረሰና አዳራችን በዚችው ቀበሌ ስለሚሆን ድንኳኖችን መትከል ጀመሩ። በአንድ ሰዓት በማይሞላ ጊዜ ውስጥ በዚች የተራራ ላይ ሜዳ ትልቅ ከተማ ተመሰረተ።

በዚች የድንኳን ከተማ እንብርት ላይ የራስ ካሣ ሁለት ትላልቅ ድንኳኖች ከልጃቸው ከደጃዝማች ወንድወሰን ካሣ ድንኳን ጋር አብረው ቆመዋል። የኛም ድንኳን ከደጃዝማች ወንድወሰን ድንኳን ትንሽ አለፍ ብላ ቆማለች። ከኛ ድንኳን ትንሽ አለፍ ብሎ ደግሞ ምንግዜም ከራስ ካሣ ጎን ተለይቶ የማይቀረው ተንቀሳቃሹ ቤተክርስቲያን በሁለት ወታደሮች እየተጠበቀ ቆሟል። ከነዚህ ትላልቅ ድንኳኖች ዙሪያ በጦር ሰፈራችን ያሉ ደጃዝማቾች፣ ፊታውራሪዎች፣ ቀኛዝማቾች፣ ግራዝማቾች፣ ባላባቶች፣ ባላንባራሶችና የቀሩት አነስተኛ ሹሞች ትናንሽ ድንኳኖች ትምትም ብለው ቆመዋል።

እነዚህ የሹማምንቱ ድንኳኖች በአመዛኙ ከውተት የነጡ ነጭ ድንኳኖች ስለሆኑ በአጋጣሚ የጣልያን አውሮፕላኖች ወደኛ አቅጣጫ ቢበሩ ያለ አንዳች ችግር ከብዙ ኪሎ ሜትር እርቀት ላይ ለይተው ሊያውቁን ይችላሉ። ከሰዓት በኋላ ራስ ካሣ በአደባባይ የዋለውን ችሎታቸውን ጨርሰው ለአንድ ሰዓት ያህል በፈረስ ሄደን ተዘጋጅቶ ከሚጠብቀን የጦር ሰፈራችን ደረስን። በድንኳን ገብተን ጥቂት እንዳረፍን የኛ አሽከር አገልጋይ ወደ ድንኳኗ አንገቱን ብቻ አሾልኮ፣ "ግብር ተዘጋጅቷል ጌታ" አለኝ። "ግብር" ኢትዮጵያውያን ከፍተኛ ሹማምንቶች ለበታች ሹሞቻቸው የሚያዘጋጁት ወይም የሚያበሉት የዕለት ድግስ ነው። ምንም እንኳን ዋናው ነገር ምግብና መጠጥ ቢሆንም፣ ግብር ዝም ብሎ ተራ ድግስ አይደለም። ግብር የራሱ የሆነ ልዩ ደንብና ስርአት አለው። ግብር እስካሁን ያለ ረጅም ታሪክ ያለው፣ የኢትዮጵያውያን ሲወርድ ሲዋረድ እዚህ የደረሰ ታሪካዊ መስተንግዶ ነው። እናም በኢትዮጵያ ያለ ግብር ህይወት የሚታሰብ ነገር አይደለም።

ለዚያም መሰለኝ ራስ ካሣ በየቀኑ ማለት ይቻላል ግብር የሚያበሉት። ራስ ካሣ ወደፊት እንደምናየው በጦር ሜዳም የጣልያን አውሮፕላኖች እንደዚያ እየዞሩ ክፉኛ በቦምብ በሚደበድቡን ጊዜ ሳይቀር ግብር ያበሉ ነበር።

ራስ ካሣ በጦርነት ወደ ጦር ሜዳ ስንሄድ በሰፈርንበት የጦር ሰፈር ግብር ማብላት ይችሉ ዘንድ ሁሌም በመሀል የጦር ሰፈር የሚቆም ትልቅ የግብር ድንኳን አላቸው። በዚህ የግብር ድንኳን ውስጥ በአንድ ጊዜ ከ100 ሰው በላይ መስተናገድ ይችላል። የየእለት ግብሩን የሚያዘጋጁ የራስ ካሣ የግል አሽከሮች ሲኖሩ ቁጥራቸውም ወደ 200 ገደማ ይሆናል።

እንግዲህ እነዚህ አሽከሮች ግብር በስነስርአቱ ማዘጋጀታቸውን ብቻ ሳይሆን ግብር የሚገባው ሹማምንት በደረጃውና በተመደበለት ቦታ ሁሉ በትክክል መቀመጡን

የሚቆጣጠር አንድ ሹም (ሊልፍኝ አስከልካይ) አለ። ይኼ ከሲታ አልፍኝ አስከልካይ ሹም ሁሌም ያቺን ወፐና ቅባት የጠገበች የደንብ ልብሱን ለብሶ የዘወትር ስራውን እስከ ጦርነቱ ፍጻሜ ድረስ በታላቅ ንቃት ያከናውን ነበር።

ይኼ ሹም ግብሩ በትክክል መዘጋጀቱን ካረጋገጠ በኋላ በዛች ወፐ በጠገበች ልብሱ ላይ ንጭ ነጠላውን አብብቱ ስር ያስርና የነጠላዋን ሁለት ጫፎች በሁለቱም ትከሻዎቹ ላይ ወደኋላ አጣፍቶ (አደግድጎ)፣ በራስ ካሣ ፊት ይቀርብና "ግብር መዘጋጀቱን ለራስ ካሣ ለክብራቸው የሚገባቸውን ሰላምታ አቅርቦ ይናገራል።

ራስ ካሣ በዚሁ አልፍኝ አስከልካይ ሹማቸው ታጅበው እንደ መጀመሪያ ሰው ለግብር ወደ ድንኳን ይገባሉ። ራስ ካሣ በግብሩ ድንኳን ውስጥ በተዘጋጀላቸው የክብር ቦታ እንደተቀመጡ አሽከሮች ቀርበው የተዘጋጀውን ግብር የተለያዩ ወጦች ያቀርባሉ። ሁለት ጎረምሶች ደግሞ ከራስ ካሣ ጀርባ ቆመው ራስ ካሣን ዝንቦች በምግብ ሰዓት እንዳያስቸግሯቸው በጭራ ዝንቦችን በጥንቃቄ ያባርራሉ። ምግቡ እንደቀረበ የራስ ካሣ የግል ጠባቂና ጠንካራው አገልጋይ ይቀርብና ከቀረቡት ምግቦች በትንሽ በትንሹ ይቀምሳል። አገልጋዩ ጠባቂያቸው ምግቡን ከቀመሰ በኋላ ራስ ካሣ ግብሩን ይጀምራሉ። ምናልባት ይኼ አጉል እምነት ይመስል ይሆናል። ግን በኢትዮጵያ ታሪክ በርካታ ነገሥታት ከምግብና ከመጠጥ ጋር ተቀላቅሎ በሚሰጥ መርዝ ዙፋናቸውን ያለፍላጎታቸው መልቀቅ ተገደዋል። በመርዝ ተገድለዋል።

ራስ ካሣ ያለምንም ጭቅጭቅ በኢትዮጵያ ውስጥ ካሉ ሃብታምና ከፍተኛ ስልጣን በጃቸው ካለ ጥቂት ከፍተኛ ሹማምንቶች አንዱ ናቸው። ቢሆንም ያለምንም ሹካና ማንኪያ እንደማንኛውም የርሳቸው ተራ ደሃ ጭሰኛ ገበሬ ሁሉ በእጃቸው ነው የሚበሉት። ራስ ካሣ ከበሉና እጃቸውን ታጥበው አፋቸውን ከተጉመጠመጡ በኋላ አሽከሮች ቀጣዮችን የእለቱን ግብርተኞች እንደየደረጃቸው ማስገባት ይጀምራሉ።

በራስ ካሣ ጦር ውስጥ ከራስ ካሣ ቀጥሎ ከፍተኛ የሚባለውን ስልጣን ያለው የበኩር ልጃቸው ደጃዝማች ወንድወሰን ነው። እናም ደጃዝማች ወንድወሰን እንደ ሁለተኛ ሰው ለግብር ይገባል። ለኔና ለጓደኛዬ ራስ ካሣ ከከፍተኛዎቹ ባለስልጣናት እኩል ቦታ ስለመደቡልን ከደጃዝማች ወንድወሰን ቀጥለን ከሁለቱ የንጉሡ ነገሥቱ እንደራሲዎች ከበጅሮንድ ለጥይበሉና ከቀኛዝማች ደህኒ ጋር እንደ ሶስተኛ ሰው ለግብር ገባን። ከኛ ቀጥሎ ሌሎች ከፍተኛ ሹማምንቶች ገብተው የግብሩ ድንኳን እስከሚፍንጠጥ ሞልቶ ግብር ተበላ። ግብርተኛው እንዲህ በአንድ መሶብ ዙሪያ አምስትም ስድስትም ሆኖ በባዶው መሬት ላይ በቂጡ ተቀምጦ እንጀራውም ወጡም እየተጨመረ የቻለውን ያህል ይበላል።

ወጥ የኢትዮጵያውያን ብሔራዊ ምግብ ማባያ ነው። ድሃ ሆነ ሃብታም ያለ ወጥ ምግብ የሚታሰብ ነገር አይደለም። ልክ እያንዳንዱ ህንድ በየቀኑ በእርድ

የተቀቀለ ሩዝ እንደሚበላው ሁሉ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊም በየቀኑ የራሱን እንጀራ በወጥ ይበላል።

በአንድ ወቅት በዐምቤይ የባቡር ጣቢያ ያገኘሁት የአንድ ማህራጂ ወጥ ቤት ሰራተኛ ህንድ ከሃምሳ አይነት በላይ የሩዝ ማባያ ወጦችን ከአልጫ እስከ ፈረንጅ ሊበላው የማይችል፣ በጣም የሚያቃጥል የበርበሬ ወጥ ማዘጋጀት እችላለሁ እያለ ጉራውን ነፍቶብኛል። ኢትዮጵያውያን ከዚህ ህንድ ጋር ሲወዳደሩ የሚችሉት አንድ አይነት ወጥ መስራት ሊመስል ይችላል። የኢትዮጵያውያንን የበርበሬ ወጥ ግን ከዚያ ጉረኛ ህንድ ጋር ፈጽሞ ማወዳደር አይቻልም። ያንን ህንድ ይኼንን የኢትዮጵያውያንን የበርበሬ ወጥ ቢያበሉት ተቃጥሎ እንደሚሞት ጥርጥር የለውም።

እንዲህ ግብር ገብተን ስንቀመጥ ብዙ ጊዜ በቅርብ የተቀመጠ ሹም ወደ እኔ ዞር ብሎ በወጥ የራሰ እንጀራ ጠቅልሎ ያጎርሰኛል። በርግጥ ይኼን ጉርሻ መቀበሉ ብዙም ደስ አይለኝም። ግን ምን ማድረግ አለብኝ። ኢትዮጵያውያን በጣም የሚወዱትንና የሚያከብሩትን ሰው በግብር ላይ ማጉረስ የወዳጅነታቸው መግለጫ ምልክት ነው። እና ወዳጅነቱን ሲገልጽልኝ እምቢ፣ አልቀበልም ማለት ነበረብኝ? ምንም እንኳን ግብርተኛው ወደ ግብር ከመግባቱ የእጅ መታጠቢያ ውሃ ቢቀርብለትም ለአመል ያህል እጆቹን ውሃ ያስነካቸው ይሆናል እንጂ እጁን ታጠበ ማለት ግን ፈጽሞ አይቻልም። ከግብር ሲወጣ ደግሞ እነዚያን በወጥና በጮማ የራሱ እጆቹን በጺሙና በራስ ፀጉሩ፣ በሸማው ሳይቀር ይጠራርጋታል እንጂ በውሃ አይታጠባትም።

የግብሩ ቀን የጾም ቀን ካልሆነ ሁሌም ሥጋ የጦረኞች ምግብ ነው። ለጦረኞች ኃይልና ድፍረት ይሰጣል የሚባለው ጥሬ ስጋ አይቀርም። ሰንጋዎቹ የሚጣሉት ግብር ከመጀመሩ ጥቂት ቀደም ብሎ ስለሆነ፣ ለሁለት በአጣና ሰክተው በትከሻቸው ተሸክመው በግብርተኛው ፊት ይዘውት የሚቀርቡት የበሬ ስጋ ነፍስ እንዳለው ሁሉ ይንቀጠቀጣል።

እንዲህ አሽከሮች ይዘውት ከሚቆሙት ስጋ ግብርተኛው ጥሩ ነው ብሎ ከሚገምተው ቦታ ላይ የሚበቃውን ያህል ይቆርጥና፣ አዋዜ ውስጥ ነክሮ ያወጣና፣ ለአንድ ጉርሻ የሚበቃውን ያህል ገምቶ በጥርሱ ይነክስና ከታች ወደ ላይ ላፍ አድርጎ ይቆርጠዋል። ሲያቀብጠኝ እንደነሱ ላፍ አደርጋለሁ ብዬ ለጥቂት አፍንጫዬን ከመሳቱም በላይ የጠቅላላው ግብርተኛ መሳቂያ ሆኜ አረፍኩት።

በዚህ መልኩ የመጀመሪያዎቹ ዙር ግብርተኞች እስኪበቃቸው እንጀራውንም ስጋውንም በልተው፣ ጠጁንም ጠጥተው ሲወጡ ጥቂት ከፍተኛ ሹማምንቶች ብቻ ቦታቸውን እንደያዙ ይቀራሉ ። የመጀመሪያዎቹ ሲወጡ ሌሎች በመቶዎች የሚቆጠሩ እየገቡ ይበሉና ይጠጣሉ። እነዚህም በልተውና ጠጥተው ሲወጡ ሌሎች ይገቡና

እነሱም በልተው፣ ጠጥተው፣ ጠግበው ሲወጡ ሌሎች እየገቡ ግብሩ እስከ መጨረሻው ይቀጥላል።

በእንዲህ አይነት ግብር ላይ በቂ ጠጅ ካለ ለሁሉም ይታደላል። አብዛኛው ሹማምንት ጠጁን የሚጠጣው በብርሌ ነው። ትልልቆቹ ሹማምንቶች ግን ከገሆን ወይም ከበሬ ቀንድ በተሰራ ዋንጫ፣ በግምጃ ጨርቅ ተሸፍኖ በሚሰጣቸው ዋንጫ ነው የሚጠጡት። ራስ ካሣ ለራሳቸው በልዩ ሙያተኛ አጊጦ የተሰራ የብር ዋንጫ አላቸው።

እንደ ኢትዮጵያውያን ጥንታዊው ወግና ባህል መሰረት ታላላቆቹ ሹማምንቶች እንደስልጣን ደረጃቸውና እንደ ግዛታቸው ወግ የጠጅ ዋንጫቸው የተለያዩ ቀለም ባላቸው የግምጃ ሽራፊ ጨርቆች ተሸፍነው ነው የሚሰጣቸው። ይኼ ወግ ደግሞ በምንም መልኩ በጦር ሜዳም ቢሆን ሊተላለፍ፣ ሊቀር አይችልም።

ይኼንንም ወግና ባህል በአይኔ ለማየት ታድዬ ነበር። አሽከሮች የአንዱን ፊታውራሪ ነጭ የግምጃ ጨርቅ ይጥሉና ለፊታውራሪው ዋንጫውን መሸፈኛ አጥተው፣ ተቸግረውና ደንግጠው ባለበት ቅጽበት እኔ ያደፊች መሃረቤን አውጥቼ ግንባሬን ስጠራርግ አንዱ አሽከር አይቶኝ ኖሮ፣ ሲሮጥ ወደኔ መጥቶ፣

«እባክህ ጌታ ላንድ አፍታ መሃረብህን አውሰኝ?» ሲል በተለማማጭ አይነ እየተማጸነ ለመነኝ።

«ለምንህ ነው? ምንስ ያደርግልሃል?» ስል ግራ ቢገባኝ ጠየኩት።

«የፊታውራሪ የግምጃ ጨርቅ ጠፋብኝ። እንዲህ ያለግምጃ ጨርቅ ዋንጫውን ለፊታውራሪ መስጠት አልችልምና እባክህ ላንድ አፍታ አውሰኝ?» እያለ በድጋሚ ተማጸነኝ። አልጨከንኩበትም፤ መሃረቤን ሰጠሁት።

ደስተኛው አሽከር ለጌታው ፊታውራሪ ጠጅ የሞላ ዋንጫውን በኔ መሃረብ ሸፍኖ ሲሰጥ ትልቅ እፎይታ ከፊቱ ላይ ይነበብ ነበር። አዎ በዚህ ዘመን ወግና ባህል፣ ደንብ ለማክበር ትንሽዬ ቁራጭ ጨርቅ ትበቃለች።

ግብርተኛው ሲጠግብ አሽከሮች የእጅ ውሃ ይዘው በግብርተኛው መሀል ይገባሉ። ግብርተኞችም ተራ በተራ እጃቸውን ይለቃለቃሉ። አብዛኛው ግብርተኛ በጥንቃቄ ጣቶቹን ብቻ ውሃ አስነክቶ ያቆማል። ለአንዳንዶቹ እጅን መታጠብ አላስፈላጊ ድሎት መስሎ ስለሚታያቸው በወጥና በቅቤ የራሰውን እጃቸውን በራሳቸው ፀጉርና በጺማቸው ጠራርገው ይነሳሉ።

አዎ ኢትዮጵያውያን ሴቶች ፀጉራቸውን ቅቤ ይቀባሉ። ዘመናዊውን የፀጉር ቅባት ሳይተካላቸው አይቀርም። የወንዶቹ ጦረኞች በቅቤ የተለወሰ እጃቸውን በፀጉራቸውና በጺማቸው መጠራረጋቸው ግን ሁሌም እንደገረመኝ ይኖራል።

ግብሩ እንዳለቀ ሁሉም ሹማምንቶች የግብሩን አዳራሽ ለቅቀው ሲወጡ፣ ራስ ካሣና ልጃቸው ደጃዝማች ወንድወሰን ብቻ ቦታቸውን እንደያዙ ሲቀሩ፣ በርካታ ትላልቅ ሹማምንቶች ሰብሰብና ፊ'ንጠር ብለው ይቆማሉ። በዚህ መሀል በርካታ የጠመጠመ ቄሶች ወደ ግብር አዳራሹ ይገቡና በራስ ካሣ የነፍስ አባት መሪነት የዕለቱ ጸሎት ይደረጋል። ከዚህ ጸሎት በኋላ የዕለቱ ግብር ይፈጸምና ራስ ካሣ እስካሁን በትግስት የሚጠብቁ ባለጉዳዮችንና መልክተኞችን መቀበል ይጀምራሉ።

እነሆ ላለፉት ሁለት ሳምንታት ቀስ እያልን ከ3,000 ሜትር በላይ ከፍታ ባለው ተራራማ ቦታ እየዘገምን ነው። አዎ ሁለት ሳምንት ሙሉ በውል በማይታወቅ ተራራማ ሀገር ማለት ከጣና ሐይቅ እስከ አሸንጌ ሐይቅ ድረስ በተሰቀለው የተራራ መሬት ላይ እየዘገምን ነው። እንዲህ ቀኑን ሙሉ ስንጓዝ አካባቢው ምንም አይለወጥም። አንድ ዓይነት ነው። በዚህ በተራራ ላይ በተዘረጋ ሜዳ ላይ አንድ ለምልክት እንኳን የሚሆን ከፍ ያለ ዛፍ አይታይበትም። ቀኑን ሙሉ መሬት ሲነካ የደረሰ ዳመና እንደዋጠን ነው።

አሁን ደረስን፣ ሜዳው አለቀ ስንል ያ ሜዳ እንደገና ሲዘረጋ፣ እንደገና ደረስን ስንል እንደገና ሲዘረጋ፣ ማለቂያ በሌለው በዚህ የተራራ ላይ ሜዳ ላይ ስንሄድ የደከመው ተጓዥ አይን የሚያየው ነገር ቢኖር እዚህም እዚያም ጉች ጉች ያሉ፣ የእዚህ የቀበሌ ነዋሪዎችን ጠቆር ጠቆር ያሉ ጎጆዎችን ጥላ ብቻ ነው።

ከዚህ አሰልቺና አድካሚ ጉዞ በኋላ እነሆ ዛሬ ጥቅምት 20 ቀን ከዚህ ረጅም የተራራ ጫፍ ወይም ሜዳ ላይ ደረስን። እንግዲህ በዚች ስፍር ለሚቀጥሉት ሁለት ቀናት እንሰፍራለን። ነጭ፣ ዳለቻና የሻኅቱ የሚመስሉ ድንኳኖች እንደ ባህር መዘርጋት ጀመሩ። በየሰዓቱ በርካታ ሹሞች ጦራቸውን እየያዙ ከምስራቅ በጌምድርና ከላስታ እየመጡ ከጦራችን ጋር ይቀላቀላሉ።

ሁለት ቀን ሙሉ ከጠዋት እስከማታ የራስ ካሣ አሽከሮች በሬዎች እያረዱ ለየሹሞች ያከፋፍላሉ። ሴቶችና ልጆች ደግሞ የደረሳቸውን ስጋ እየዘለዘሉ ተጠርታ በመጣች በምትመስለውና ደምቃ በወጣችው ፀሐይ በገመዶች ላይ እያንጠለጠሉ ያደርቃሉ። እንግዲህ ይኼ የደረቀ ስጋ (ቋንጣ) ለተዋጊው ወታደር ዋና የጦር ሜዳ ስንቁ ነው።

ራስ ካሣም ስራ አልፈቱም። ከጠዋት እስከማታ በተንቀሳቃሽ ዙፋናቸው ላይ ተቀምጠው፣ በትልልቆቹ ሹማምንቶቻቸው ተከበው፣ አዳዲስ ሹማምንቶችን ይቀበላሉ። የአካባቢው የሀገር ሽማግሌዎችም በራስ ካሣ ፊት እየቀረቡ በቀበሌያቸው ስለደረሰው ችግርና ጭቆና አቤቱታቸውን ያቀርባሉ። ራስ ካሣ ከዚህ በተጨማሪ ከየቀበሌው እህል፣ ጥራጥሬ፣ በግ፣ ፍየልና በሬ ለመሸጥ ከመጡ ገበሬዎች ጋር በዋጋ እየተከራከሩ ለወታደሮቻቸው ስንቅ ሲሸምቱ ይውላሉ። አዎ አንድ ጥሩ በሬ ቢያወጣ

ቢያወጣ ስምንት ብር ብቻ ነው። ከሁለት ቀን በኋላ ራስ ካሣ ለጦራቸው ወደፊት እንዲሄድ ቀጭን ትዕዛዝ ሰጡ።

ዛሬም ወደ ተከዜ ወንዝ ሳንወርድ አፋፍ ላፋፍ በተራራው ሜዳ ላይ ነው ስንሄድ የዋልነው። እንግዲህ አፋፍ ላፋፍ ስንሄድ ጠላት ባይገጥመንም አጥንት ድረስ ዘልቆ የሚገባ ቅዝቃዜ ግን እያንሰፈሰፈን ነው። ወፍራም ሹራብ ደርቤ በብርድ ልብስ ብጠቀለልም ምንም አልረዳኝም። አልፎ አልፎ ከፈረሴ ላይ እየወረድኩ ሰውነቴን ለማሟሟት ሶምሶማ ባልሮጥ ኖሮ በፈረሴ ላይ እንደተቀመጥኩ ደርቄ እንደምቀር ጥርጥር አልነበረውም።

ለነዚያ ምስኪን ኢትዮጵያውያን የገጠሬ ወታደሮች ከልቤ አዘንኩላቸው። በዚህ ውርጭ በላያቸው ላይ ያለ ነገር ቢኖር እያለቀች ያለች አሮጌ ሸማ ብቻ ናት። እንዲህ በራሴ ቆዳ ባላየው ኖሮ በኢትዮጵያ፣ ለዚያውም በምስራቅ አፍሪካ፣ እንዲህ ዓይነት ጨካኝ ብርድ አለ ቢሉኝ ኖሮ ምንጊዜም አላምንም ነበር። ምናልባትም በመላው ኢትዮጵያ በጣም ብርዳማው ቦታ ቢፈለግ አሁን እኛ የምንሄድበት የዋድላ ግዛት አንደኛ ሳይወጣ የሚቀር አይመስለኝም።

ማምሻው ላይ ተስማሚ ቦታ ስላገኘን ጦሩ እንዲሰፍር ትዕዛዝ ተሰጠውና ሁሉም በቆመበት ቦታ መስፈር ጀመረ። ይሁን እንጂ ጦሩ ድንኳን ለመጣል ከወትሮው በተለየ ሁኔታ ረዘም ያለ ጊዜ ወሰደበት። አይፈረድበትም፣ እንደ ድንጋይ በጠጠረ ውርጭ መሬቱ ተሸፍኗል።

በድንኳን ውስጥም የሰው ልጅ የማይችለው ከባድ ቅዝቃዜ አለ። ለዚያም መሰለኝ ከድንኳናችን በራፍ ላይ አሽከሮች ትንሽ ሞቅ እንዲለን አስበው ትልቅ እሳት ያነደዱልን።

ምንም እንኳን ካኒቴራ፣ ሁለት ሸሚዝ፣ አንድ ወፍራም ሹራብ፣ ኮትና ካፖርት ብደርብም፣ አልበቃ ብሎኝ ብርድ ልብሴን ተከናንቤም ብርዱ አሁንም እያንዘፈዘፈኝ ነው። ብቻ እንዲሁ በብርድ እየተንቀጠቀጥኩ እጄን ሳላስበው ወደኪሴ ስከት አንዲት እንደአንጨት የደረቀች ፖስታ አገኘሁ። ይቺን ፖስታ የተቀበልኩት አዲስ አበባ ወደ ደብረ ታቦር የበረርኩ እለት ነበር። ግን በዚያ ችኮላና ጥድፊያ ሳላነባት ተረሳችና እነሆ ዛሬ ሳገኛት ላነባት ጓጓሁ። ምንም እንኳን ፖስታዋ ብትደርቅም እንደምንም ከፈትኳትና ማንበብ ጀመርኩ። የደብዳቤዋ ፍሬ ነገር እንዲህ ይላል፤

«እኔ አሁን እረፍቴን ዩጎዝላቪያ ውስጥ እያሳለፍኩ ነው። እዚህ ጥሩ ያየር ፀባይ አለ። በየቀኑም ፀሐይ ስለሚወጣ ሙቀቱ ኃይለኛ ነው። ሁሌም አስብሃለሁ፤

እናም እኔ እንዲህ በዚች የባልካን ሙቀት ስቃጠል አንተ በአፍሪካ ሃሩር መጠበስህ ሲታወሰኝ ከልቤ አዝንልሃለሁ።» በጣም ተናደድኩና ደብዳቤዋን ጨምድጄ ከፊቴ በሚነደው እሳት ውስጥ ጨመርኳት። የአፍሪካ በረሃ ይቀልዳል? በሰሜን ዋልታ አካባቢ እንደሚኖር ኤስኪሞ ዲራቶ በድራቶ ሆኜ፣ እሳት ዳር ተቀምጬ ጥርሴ በብርድ እየተፋጨ «በአፍሪካ ሃሩር መጠበስህ» የምትለዋ አረፍተ ነገር አናደደችኝ። ዲንቂም የአፍሪካ ሃሩር።



13

ከአፄ ቴዎድሮስ የልጅ ልጅ ጋር

አሁን በላስታ ድንበር ላይ ነን። ባለፉት ቀናት በርካታ ሹማምንቶች ከየግዛቱ ከነጦራቸው እየመጡ ከጦራችን ጋር ስለተቀላቀሉ አሁን ጦራችን ወደ 50 ሺህ ገደማ ወይም ከዛ በላይ ሆኗል። እንግዲህ ይህ ግምት ብቻ ነው፤ ትክክለኛውን ቁጥር እግዜር ብቻ ነው የሚያውቀው።

እንግዲህ ወደ ሰሜን ለመሄድ ከዚች የተራራ ጫፍ ላይ ተነስተን፣ ወደታች ወርደን፣ በዚያች አስፈሪና አስቸጋሪ ጠባብ ስርጥ ማለፍ አለብን። ስፋቷ ግማሽ ሜትር የማትሞላዋንና ናዳ የበዛባትን ይቺን ስርጥ መውረዱ ምን ያህል አስቸጋሪና አደገኛ መሆኑን የተረዱት ራስ ካሣ ጦራቸውን ሁለት ቦታ ላይ ከፈሉት።

ወደ ተከዜ ወንዝ በዚች አስቸጋሪና አደገኛ የስርጥ መንገድ 1,200 ሜትር ቁልቁል ለመውረድ ከመሞከራችን በፊት ጦራችን ለማረፍ አፋፍ ላይ ቆመ። እንዲህ እዚች አፋፍ ላይ ቆሜ የተከዜን ሸለቆ ሳደንቅ ድንገት በጦራችን ግርግር ተፈጥሮ ፉከራውና ሽለላው ከሩቅ ይሰማ ጀመር። እስካሁን ያለ አንዳች ችግር በሰላም ሲጓዝ በነበረው ጦራችን መካከል ምናልባት አመጽ ተነስቶ ይሆናል በሚል ስጋት በፍጥነት ወደ ጦር ሰፈር ስመለስ ራስ ካሣን ወደ እነዚህ ወደሚፎክሩትና ወደሚሸልሉት ጦረኞች ሲሄዱ አየሁና በሩጫ ቀረሽ ርምጃ ተከተልኳቸው።

በቦታው ስንደርስ በነዚያ በሚፎክሩትና በሚሸልሉት መካከል የራስ ካሣ የበኩር ልጅ ደጃዝማች ወንድወሰን በበታች ሹማምንቶቹ ተከቦ የአባቱን መምጣት ሲጠባበቅ አገኘነው። ወዲያው ደጃዝማቹ አባቱን ሲያይ እየሮጠ መጥቶ ከእግራቸው ስር ወድቆ፣ እግራቸውን ለክብራቸው ስሞ ሲነሳ እንደ አባትና ልጅ ተቃቅፈው ተሳሳሙ። እንጀት በሚበላ ሁኔታም ተሰነባበቱ።

እዎ ጀነራል ደጃዝማች ወንድወሰን ግማሹን የራስ ካሣን ጦር እየመራ በምስራቅ በኩል ዞሮ ተከዜን ሊሻገር ሄደ። የቀረው የራስ ካሣ ጦር አሁን ከቆምንባት አፋፍ ላይ ቁልቁል ወርዶ የተከዜን ወንዝ ለመሻገር ይሞክራል። ከእንዲህ አይነቱ መሰነባበት በኋላ የራስ ካሣ ፈረሰኛ ጦር ለኛ ቅድሚያ ሰጥቶ መንገድ ስለለቀቀልን ቁልቁል ወደ ተከዜ ወንዝ ወረድን።

ይቺ የስርጥ መንገድ ታሪካዊ የሚያደርጋትና አንድ ምንጊዜም ማንም የማይረሳው ታሪክ አላት። በ1860ዎቹ ውስጥ ቴዎድሮስ የሚባል አንድ ጀግና ንጉሥ በኢትዮጵያ ነግሶ ነበር። ስለዚህ ጀግና፣ ደፋር እና የተማረ፣ አገሩን ከማንም በላይ ስለሚወድ ንጉሥ ብዙ ብዙ ታሪክ ተጽፏል።

አንዳንድ ክፉ ምላስ የታሪክ ፀሐፊዎች በስልጣኑ መጨረሻ ግድም ላይ አብደት ብጤ ነገር ጀምሮት ነበር እያሉ ይጽፋሉ ። ሌሎች ደግሞ ቴዎድሮስ ከጊዜው ቀድሞ የመጣ ንጉሥ ነው እያሉም ይፈላሰፋሉ። ሆነም ቀረ ቴዎድሮስ በህይወት በስልጣን ዘመኑ መጨረሻ ግድም ላይ ከእንግሊዞች ጋር በተፈጠረ አለመግባባት በሀገሩ ይኖሩና ይሰልሉ የነበሩ ፈረንጆችን -እንግሊዞችን- በሙሉ ሰብስቦ ያስራል።

ከነዚህ ከታሰሩ ፈረንጆችም መካከል በንጉሡ ቤተ መንግሥት ይኖር የነበረው ቆንስል ካሜሩንም ይገኝበት ነበር። ምንም እንኳን እንግሊዞች ችግሩን በዲፕሎማሲ ለመፍታት ቢሞክሩም፣ በእንግሊዞች ብልጣብልጥነትና ንቀት ክፉኛ የተናደደው ይኼ ንጉሥ አሻፈረኝ፣ አንድም እስረኛ አለቅም ብሎ እልህ ውስጥ ገባ። ይኼንን ታታሪ ንጉሥ ለመጣልና በምትኩ አሻንጉሊት ንጉሥ ለማንገስ፣ ነገር የሚሸርቡት እንግሊዞች በጀነራል ናፒየር የሚመራ የህንድ ጦር እስረኞቻቸውን ለማስፈታት ወደ ኢትዮጵያ ላኩ።

በ1867 ዓ.ም. በርከት ያሉ የህንድ ወታደሮች በእንግሊዛውያን መኰንኖች እየተመሩ ባህረ ነጋሽ (ኤርትራ) ገቡ። በዙላ ወደብ ጥቂት አርፈው ወደ መሀል ሀገር ዘልቀው ለመግባት ከየግዛቱ ገዢዎች ጋር እየተደራደሩና በጉቦ መልክ መሳሪያ እየሰጡ፣ በነዚሁ የየግዛቱ ገዢዎች መሪነት እስከዛሬ አንድም የወራሪ ጦር ረግጦት የማያውቀውን ሀገር ፍለጋ ወደ ማህል ሀገር ጉዞ ጀመሩ።

እንዳልኩት የቴዎድሮስ ተቃዋሚ የየግዛቱ ንጉሦች የጀነራል ናፒየርን ጦር መንገድ እየመሩ አሁን ልንወርዳት የምንቀጠቀጥላትን ስርጥ ሁሉ ወጥተው መቅደላ አፋፍ ላይ ደረሱ።

እም ጀነራል ናፒየር የጦር መሪ ብቻ አልነበረም። በጣም ጎበዝና ወደር የማይገኝለት ተደራዳሪ ዲፕሎማትም ነበር። አለዚያማ በነዚህ ትናንሽ ንጉሦች መሬት ላይ በሰላም ተጉዞ እዚህ መቅደላ አፋፍ ላይ ባልደረሰ ነበር።

ጀግናው ቴዎድሮስ ከታማኝ ወታደሮቹ ጋር የጀነራል ናፒየርን ጦር ገጥሞ ተዋግቶ በተሸነፈ ጊዜ ደኼ ጀግና ንጉሥ እጄን አልሰጥም ብሎ ራሱን ይገድላል። እንግሊዞችም እስረኞቻቸውን አስፈትተው በውላቸው መሰረት በመጡበት መንገድ ተመልሰው የኢትዮጵያን መሬት ለቅቀው ወደ ህንዳቸው ሄዱ።

የኔ ፈረስ እንዲህ በገደግታና በጥንቃቄ ቁልቁለቱን ሲወርድ በመንፈስ እነዚያን የደከሙ የጀነራል ናፒየር ወታደሮች በዚያ ጥንታዊና ደማቅ የወታደር የደንብ ልብሳቸው አየኋቸው፤ ሳልኳቸው።

የኔ ፈረስ ከራስ ካሣ በቅሎ ብዙም ወደ ኋላ ሳይርቅ በእርጋታ ስርጓን እየወረደ ነው። ከኔ ኋላ አንድ እስከዛሬ ያላየሁት ክስታራና ቆፍጣና፣ በሰላሳዎቹ እድሜ ውስጥ የሚገኝ ወጣት ሹም በፈረሱ ላይ ተቀምጦ ይኼዳል። በቅርቡ ከኛ ጦር ጋር የተቀላቀለ መሆን ይኖርበታል፤ እስከ ዛሬ በጦራችን መሀል አላየሁትም። በዚህ ወጣት ቆፍጣና መኰንን መገረሜን ያየ የኔ ፈረስ ልጓም ያዥ ወደኔ ጠጋ ብሎ፣ "የአፄ ቴዎድሮስ የልጅ ልጅ ነው" አለኝ።

ተከዜን ተሻግረን ጥቂት እንደሄድን ከፊት ለፊታችን ትልቅ ሜዳ ተዘረጋ። በዚህ ለጥ ባለ ሜዳ ስንሄድ ውለን የሙጃ ቀበሌ ተቀበለችን። በሙጃ ቀበሌ ባሉ ጎጆዎች መሀል ስንሄድ ቆይተን ከቀበሌዋ ትንሽ ወጣ ብሎ አንድ ጉብታ ላይ ሰፊ ግቢ አየን። ከዚህ ትልቅ ግቢ አጠገብ ስንደርስ ራስ ካሣ ከፈረሳቸው ላይ ወርደው በቀጥታ ወደ ግቢ ሲገቡ እልልታው እስከ ሩቅ ቦታ ድረስ ሳይቀር ይሰማ ነበር።

ቀልጣፋው አሽከራቸው መቼ እንኳን ወደ ግቢው ውስጥ እንደገባ ሳናስተውል በግቢው ውስጥ ተንቀሳቃሽ ዙፋናቸውን ስላቆመላቸው በዙፋናቸው ላይ ተቀምጠው የግቢውን ዙሪያ ገባ መቃኘት ጀመሩ። እንዲህ ግቢውን እየቃኙ በትዝታ በጣም በጣም ርቀው ሄዱ። አንድም ሰው ድፍረት ኖሮት ከዚህ የቀን ህልማቸው ሊቀሰቅሳቸው አልሞከረም።

የዛሬው ሽማግሌ ራስ ካሣ የወጣትነት ዘመኑን በሙጃ ነበር ያሳለፈው። ከዛሬ 30 አመታት በፊት ከሙጃ እንደ አንድ ተራ ፊታውራሪ ያለ ፍላጎቱ ነበር ወደ አዲስ አበባ የሄደው። እነሆ ዛሬ ከ30 አመታት በኋላ ወደሙጃ፣ እንደ ራስ ብቻ ሳይሆን የአምስት ሃብታም ትላልቅ ጠቅላይ ግዛቶች ገገርና ከንጉሠ ነገሥቱ ቀጥሎ በመላው ኢትዮጵያ እንደ ሁለተኛ ሰው የሚታየው ገገር ወደ ሙጃ ተመለሰ።

የዛሬው የጦራችን አዳር በሙጃ እንደሚሆን ሳይታለም የተፈታ ነው። በሁለተኛው ቀን ከሙጃና አካባቢው ቀበሌዎች፣ ራቅ ካሉ ቀበሌዎች ሳይቀር በርካታ

ሹማምንቶች እየመጡ ከራስ ካሣ ጋር እየተሳሳሙ ለ30 አመታት ያህል የቆየውን ናፍቆታቸው ተወጡ።

ከሰራዊታችን ምንጊዜም የማይለዩ አንድ ቄስ ከሙጃ ግቢ ፊት ለፊት ካለች አንዲት እነስ ያለች ዋርካ ስር ተቀምጠው፣ ዘወትር ከእጃቸው የማትለየውን መጽሐፋቸውን ሲያገላብጡ አገኘኋቸውና የእግዚአብሔር ሰላምታ አቀረብኩላቸው። ራስ ካሣ ከዛሬ ሰላሳ አመታት በፊት እንደ አንድ ተራ ፊታውራሪ ወደ አዲስ አበባ እንደሄዱ የነገሩኝ እኚህ ቄስ ናቸው። ቄሱ በትረካቸው ቀጥለው፣ "እየህ ፈረንጅ ጌታ፣ ራስ ካሣ የሸዋ መኳንንት ባያስቸግሯቸው ኖሮ ዛሬ የአንድ፣ ሁለት ደብር አለቃ በሆኑ ነበር" አሉና ቄሱ ስለ ራስ ካሣ ንጉሣዊ ቤተሰብነት ሲናገሩ፣ "ሳህለ ሥላሴ፣ ዳርጌን ወለደ፤ ዳርጌ ደግሞ ትሰማኙን ወለደ፤ ትሰሜ ደግሞ የኛን ራስ ካሣን ወለደች፤ ራስ ካሣ ደግሞ እነሆ እከታትሎ አራት ወራሾች ወልዶልናል፤ ወንድወሰን፣ አበራ፣ አስፋ ወሰንንና አስራት ካሣን።" እንዲህ እኚህ ቄስ ያጫወቱኝን የራስ ካሣን የዘር ግንድ እያብሰለሰልኩ ወደ ድንኳኔ ተመለስኩ።

ምንም እንኳን ከደብረ ታቦር ስንነሳ ጥቂት ሲጃራዎች የነበሩኝ ቢሆንም የመጨረሻዋን ሲጃራ ካጨስኩ ብዙ ስንብቻለሁ። እንግዲህ ምናልባት ሌላ ሲጃራ መግኘት የምችለው መቀሌ ስንገባ ነው። መቀሌ ለመድረስ ደሞ ቢያንስ የ14 ቀን መንገድ ይቀረናል። ለዚያውም መቀሌን ከኛ ቀድመው ጣልያኖች ካልያዟት ማለት ነው። እናም በጠዋት ተነስቼ ፈረሴን ጫንኩና ሙጃን ልጎበኝ ስነሳ ብልጣ ብልጡ አቶ ተሰማ ያ ሳቁና ፈገግታው ሳይለየው ትንባሆ የሚያበቅል ብቸኛ ቀበሌ ሙጃ ብቻ መሆኑን ነገረኝ።

ሙጃ ቀበሌ ስገባ ይቺ እግዜሩ የረሳት የምትመስል ቀበሌ በአንዲት ሲንጀር የልብስ ስፌት መኪና በመጠኑም ቢሆን የዘመኑ ስልጣኔ የዳሰሳት ትመስላለች። የሲንጀሯ ባለቤት የቀበሌዋ ልብስ ሰፊ ከጎጆው ደጃፍ ላይ ተቀምጦ የልጆች ጨዋታና ጩኸት ሳይረብሸው በእለት ተግባሩ ላይ ተሰማርቷል።

ልብስ ሰፊው ልዩ ችሎታና ጥበብ የግድ የሚያስፈልገው ሰው መሆን የለበትም። በአብዛኛው የተቀደዱ ልብሶችን መልሶ ሲሰፋ ይውላል። አልፎ አልፎ አዲስ ልብስ ሊያሰፋ የሚመጣ ደንበኛ ቢኖርም የሚያሰፋው ልብስ እጀ ጠባብ፣ ቀሚስ፣ ለልጆች ጥብቆ፣ ወዘተ. ስለሆነ ልብስ ሰፊው በዚህ ይቸገራል የሚል ግምት የለኝም። በእውነት ያንን እታች እግሩ ላይ የተጨማደደ ስራ ለመስፋት ልዩ የሆነ ጥበብ አያስፈልገውም።

አሰፊዎቹም ስልብስ ሰፊው ለዚህ ጥበባዊ ስራው የሚከፍሉት በጥራጥሬ፣ በበርበሬ ወይም በጨው ምናምን ስለሆነ ሰፋ ጠበበ፣ ረዘመ አጠረ ብሎ የሚከራከር ደንበኛ ይኖራል ብሎ መገመት ያስቸግራል። ሁሉም ኢትዮጵያዊ፣ ወንዱም ሴቱም፣ ከትከሻው የማትለየውን ነጠላም ሆነ ጋቢ ራሱ ለባሹ በቀላሉ በመርፌ በጁ ሊሰፋው

የሚችለው ነገር ስለሆነ የግድ ወደ ባለሲገጅሩ ልብስ ሰፊ የሚያስኬደው አይነት እርረሰም። እንደህ ወለሲገጅሩ ልብስ ሰፊ እየተፈላሰፍኩ በፈረሴ ስሄድ አንዲት በጭም ወብ ቀንጆ ልጅ በመንገዴ ገባች፤ "ኝ ጌታ፤ የፈለከውን ያህል ትንባሆ እንፖልሃለሁ" አለችኝ።

ግን ትንባሆ እንደምፈልግ በምን አወቀች? ገና ከግቢ ስነሳ ስለ ትንባሆ ነገር ያወራሁት ከአቶ ተሰማ ጋር ብቻ ነው። አቶ ተሰማን ደግሞ ከግማሽ ሰዓት በፊት በግቢ ነው ጥዬው የመጣሁት። በመንገዴ ላይ አንድም መንገደኛ ሰው ሳይገጥመኝ፣ ከፈረሴ ላይ አንድም ጊዜ ሳልወርድ ቀጭኗን መንገድ ተከትዬ ነው የሄድኩት። በመንገዴም ላይ ባህላዊውን የሃበሾች የትኩስ ዜና መለዋወጫ ማለት ከቀበሌ ቀበሌ የሚላክ ልውውጥ ሲጯጯሁ እንኳን አልሰማሁም። ሆነም ቀረ በዚች ከዘመኑ ስልጣኔ በጣም በጣም ወደኋላ ርቃ ባለች ትንሽ ቀበሌ ያለ ስልክ፣ ያለ ቴሌ ግራም፣ ያለ ምንም መገናኛ ዘዴ በቀላሉና እጅግ በሚያስደንቅ ፍጥነት መረጃ መለዋወጥ መቻላቸው እያስደነቀኝና ግራ እያጋባኝ የቀንጆዬዋን ጉብል ልጅ የትንባሆ ገበያ ተቀብልኩና አንድ ብር ሰጠኋት። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ያቺ ቆንጆ ጉብል በእቅፏ ሙሉ በወፍ እንኳን ያልደረቁ የትንባሆ ቅጠሎች እያስታቀፈችኝ፣ "ሚስት አለዎ ጌታዬ" አለችኝ።

ዋለኝም አልከፆት ሳቅ እያፈነኝ። "ሰሙ ጌታ እኔን ውሰዱኝ፤ ጥሩ ሚስት እሆንዎታለሁ" አለችኝና ከኔ ምንም አይነት መልስ ሳትጠብቅ፣ "ታማኝ ሚስት እሆንዎታለሁ። ሌት ተቀንም ጠንክሬ እሰራለሁ። በኔ የማያፍሩ ጌታ አደርግዎታለሁ" አለችኝ። ግራ ቢገባኝ፣ "ወደ ጦር ሜዳ ከራስ ካሣ ጋር እየሄድኩ እንደሆነ ታውቂ የለም እንዴ?" አልኳት። "እኮ ታዲያ ጌታ። ወደ ጦር ሜዳ እንደምን ብቻዎትን ይኼዳሉ ጌታዬ?" ቀጥላም ምንም መልስ ከኔ ሳትጠብቅ፣ "እዩ ጌታ ቢቆስሉ ማን ቁስሉን ያስርሉታል? ቢሞቱስ ማን ጉድጓድ ቆፍሮ ይቀብሮታል? ጌታ ግዴልም ይውሰዱኝ እያለች ተማጸነችኝ።

አሁን ነገሮች እየተገለጹልኝ መጡ። በኛ ሰራዊት ውስጥ አብዛኛው ሹም ከሚስቱ ወይም ከገረዱ ጋር ወደ ጦር ሜዳ የሚዘምትበት ምክንያት። አቶ ተሰማም አንዲት ቆንጆ ወጣት ሚስታቸው አብራቸው እዚህ አለች።

በሚቀጥለው ቀን በጉዟችን ቀጥለን ተራራውን በእግራችን ስንወጣ ሜዳ ብጤ ነገር ስናገኝ በፈረሶቻችን ላይ ሆነን ስንገሰግስ ውለን ከፊት ለፊታችን አንዲት ተራራ ጉብ ብላ ታየችን። ከዚች ተራራ ጫፍ ላይ ለመድረስ ቢያንስ ሶስት አራት ቀን ይፈጅብን ይሆናል። ከዚች ተራራ ጫፍ ላይ የኮረም ከተማ ትጠብቀናለች።

ከዚህ አይነቱ አድካሚ ጉዟችን ሁሌም የሚገላግለን ያቺ እረፋ የምትለዋ ጡሩንባ ተነፋችና ሌሊቱን የምናሳልፍበትን ቦታ መርጠን ድንኳናችንን እንደነገሩ ከጣልን በኋላ እኔ አካባቢያችንን ለመቃኘት ከሰፈር ወጣሁ።

የአምባላጌን ተራራ ለመውጣት ቢያንስ 3,000 ሜትር ከባህር ጠለል በላይ አሻቅበን መውጣት አለብን። በነዚህ ለሁለት በተከፈሉ በሚመስሉ ተራራዎች መካከል እንኳን ፈረንጅ፣ ኢትዮጵያዊውም ራሱ ለህይወቱ ምንም መተማመኛ የሌለው "የራያና አዘቦዎች" መሬት ተዘርግቷል።

በራያዎችና አዘቦዎች መሬት ላይ ገና ተከዜን ልንሻገር ስንወርድ ተሰናብቶን በስተምስራቅ በኩል ዞሮ የሄደው ደጃዝማች ወንድወሰን ትልቁን ድንኳኑን ጥሎ ሰፍሯል። አዎ ቢያንስ የአንድ ቀን መንገድ ያህል ቀድሞን ሄዷል።

ወደ ጦር ሰፈራችን ተመልሼ ስለ ጉዟችን ማስታወሻ ስጽፍ አንድ ፀጉረ ልውጥ ፈረንጅ ወደ ጦር ሰፈራችን መጣ። አጭር ቁምጣና ካኪ ሸሚዝ ለብሷል። የበረሃ ቆብም ደፍቷል። እድሜውም ከ35 ዓመት አይበልጥም። እኔን ባየኝ ጊዜ ብዙም አልተደነቀም። ብቻ የሆነ ነገር ሊነግረኝ ፈልጎ ወደ እኔ ሲመጣ ከኋላው የሚከተሉት ሁለቱ ቆፍጣና የራስ ካሣ ወታደሮች ከመንገዱ መልሰው ይዘውት ሄዱ።

ወዲያው ከሰፈር አንበሳን አስጠራሁና "ይኼንን አዲሱን ፈረንጅ አየኸው?" ስል ስለ አዲሱ ፈረንጅ የሚያውቀውን ቢነግረኝ ብዬ ጠየኩት። "የት አባቱ! የጣልያን ሰላይ ነው" አለኝ አንበሳ አስር ጊዜ በመጸየፍ ምራቁን ወደ መሬት እየተፋ።

በሰፈር ያሉትን ታማኝ ወዳጆቼን ሹሞችን ሳይቀር ስለዚህ ፀጉረ ልውጥ ፈረንጅ የሚያውቁትን ቢነግሩኝ ብዬ አጠያየቅሁ። ማንም ምንም ሊነግረኝ ሳይፈልግ ቀረ። ይኼንኑ አዲስ ፈረንጅ ራሴ ላናግረው ፈለኩና የት እንዳለ ሳፈላልግ ከሰፈራችን ወጣ ብላ ባለች አንዲት ጎጆ ውስጥ በወታደሮች እየተጠበቀ አገኘሁት።

የራስ ካሣ ፈረንጅ መሆኔን ደጋግሜ አስረድቼ እንዳናግረው ዘቦችን ብለምንም ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀርተው፣ ምንም ሳይቀናኝና ምንም ነገር ስለዚህ ፈረንጅ ሳላውቅ የዘወትር የግብር ሰዓት ደረሰና ወደ ግብር ገባን።

በግብር ላይ ከኔ ብዙም ሳይርቁ የሚቀመጡ አንድ የራስ ካሣ ቀኛዝማች "ፈረንጁ" በምርኮ መልክ ታስሮ እንደሚጠበቅ አይነት ነገር ጠቋቁመው ከነገሩኝ ወሬ ውጪ ምንም የረባ ነገር እጄ ሳላስገባ ወደ ድንኳኔ ተመለስኩ።

በሁለተኛው ቀን አዲሱ ፈረንጅ ከራስ ካሣ ከመጨረሻዎቹ የክብር ዘቦች ጋር በፈረስ ላይ ተቀምጦ ሲሄድ አየሁትና ወደ ኋላ ተመልሼ ላናግረው ሞከርኩ። ይሁን እንጂ ዛሬም አልቀናኝም። ጠባቂዎቹ ዘቦች ወደፊት ሄጄ በጉዞዬ እንድቀጥል ስላዘዙኝ ከፈረንጁ ጋር ሳልነጋገር ወደፊት ሄድኩ።

እንዲህ በጉዟችን ወደፊት ገፍተን የወንድሻን ቀበሌ እንደተሻገርን ከፊት ለፊታችን ትልቅ የበቆሎ አዝመራ ተዘርግቶ ጠበቀን። የበቆሎውን አዝመራ ያየው

አዝመራ ዘመተበትና ከጥቂት ጊዜ በኋላ ያ ሰራዊታችን ያለ አጋጅ ያንን የበቆሎ አዝመራ ለምልክት ሳይቀር ድራሹ ጠፋ።

ከዚህ ዘረፋ በኋላ ሰራዊታችን በጉዞው ቀጥሎ ዲልዲ የምትባል ቀበሌ ስንደርስ አዳራችን በዲልዲ እንዲሆን ተወስነና ድንኳኖቻችንን ጣልን። በዲልዲ የጦር ሰፈራችን እንደተለመደው የራስ ካሣ አብላዮች ግብር አዘጋጅና ግብር ገባን። ይገርማል ያንን አስረኛ ፈረንጅም ዘበኞች አምጥተው ከኛ ጋር አስቀመጡት። በግብር ላይ ድኼ አዲስ ፈረንጅ ኒድስትርም እንደሚባልና ዜግነቱ ስዊዲናዊ ሲሆን፣ የተወለደው አስመራ እንደሆነ ነገረን። ቀጥሎም አሁን የራስ ካሣ እስረኛም እንደሆነም አክሎ ነገረን። ግን በምን ምክንያት የራስ ካሣ እስረኛ ሊሆን እንደቻለ ኒድስትርም ምስጢሩን ሰራሲ ተወው።

የኔ ግምት ብቻ ሊሆን ይችላል። ኒድስትርም ለራስ ካሣ ሁለተኛውን የጣልያኖቹን መልእክት ይዞ የመጣ ሰው መሰለኝ። አሁንም ግምት ብቻ ነው። ኒድስትርም ለራስ ካሣ ይዞት የመጣው መልእክት "ደብዳቤ" ማስፈራራትና ኃይለ ቃል የበዛበት ነገር መሰለኝ። ለዚህም ሳይሆን አልቀረም ራስ ካሣ በጣም ተበሳጭተው ኒድስትርምን ያሰሩት። እንዳልኩት ይኼ የኔ ግምት ብቻ ነው።

ከሁኔታዎች መረዳት እንደምንችለው ራስ ካሣ አንቱ የሚባሉ ትልቅ ዲፕሎማት መሆናቸውን ነው። ጣልያኖች በተደጋጋሚ ላቀረቡላቸው የድርድር ሃሳቦች እና ሌላም ሌላም ነገሮች በሚያወላውልና በሚያደናግር መልሳቸው ጣልያኖችን ሲያደናግሩ፣ ማለት እሺም እምቢም ሳይሉ እነሆ አንድ ወር ሙሉ የጣልያን አውሮፕላኖች ሰላም ሰጥተውን አንድም ወታደር ሳናጣ ቀጥ ብለን ያለ ምንም ችግር ወደ ጦር ግንባር እየተቃረብን ነው።

አዎ ራስ ካሣ በዚህ ዲፕሎማሲያቸው ለሰራዊታቸው የሚበቃውን ያህል ጊዜ ገዝተዋል። ከግብር በኋላ ራስ ካሣ ከዙፋናቸው አስጠሩኝና ነገ ፀጉረ ልውጡን ፈረንጅ ስዊዲናዊውን ኒድስትርምን ከጠባቂዎች ጋር ወደ ደሴ ለንጉሠ ነገሥቱ እንደሚልኩት ነገሩኝ።

14
በአሽንጌ ሐይቅ

ከወጣቱ ሲዊዲናዊ ሚሲዮን ጉብኝት በኋላ ራስ ካሣ ከወትሮው ልምዳቸው ውጪ በፍጥነት ወደ ሰሜን ጦር ግንባር ጦራቸውን ይዘው መገስገስ ጀመሩ። እስከዛሬዋ ቀን ድረስ ወታደሮች ድንኳኖችን ነቃቅለው ወታደሩም ከያደረበት ጥሻ ተሰባስቦ ለጉዞ እስኪዘጋጅ ድረስ፣ ሁለትም ሶስትም ሰዓት በተንቀሳቃሽ ዙፋናቸው ላይ ተቀምጠው ወይ የአካባቢውን ነዋሪዎች ችግር ይፈታሉ፣ አሊያም ደግሞ ዝም ብለው ከበታች ሹማምንቶች ጋር እየቀለዱ ያወራሉ። አንድም ቀን ለጉዞ ተጣድፈው አያውቁም ነበር።

ብዙ ጊዜ በተደጋጋሚ ማለት ይቻላል ራስ ካሣን ወደ ሰሜኑ የጦር ግንባር በተቻለ ፍጥነት ቶሎ ቶሎ እንድንሄድ ብወተውትም ሁሌም ትከሻቸውን በግዴለሽነት ነቅነቅ አድርገው ያ ፈገግታቸው ሳይለያቸው "አይዞን፣ የምሰራውን ነገር አውቃለሁ" አይነት ነገር ይመልሱልኝ ነበር። አዎ ራስ ካሣ ፍጹም እርግጠኛ ነበሩ፣ የጣልያን አውሮፕላኖች ጦራቸውን እንደማይደበድቡ።

የዲልዲን የጦር ሰፈር ለቀን ከወጣንባት ቀን ማለዳ ጀምሮ ገና ከመንጋቱ በፊት ከጥቂት አጃቢ የክብር ዘብ ወታደሮቻቸው ጋር ብቻ የጦር ሰፈሮቻችንን ለቅቀው ወደፊት መሄድ ጀመሩ።

ከጦር ሰፈር ወተው ሄደዋል። ጠዋት ከእንቅልፌ ስነቃ ራስ ካሣ ገና ዱር ለመቆማቸው ምንም አይነት ምልክት ድንኳናቸም ትናንት በዚች የጦር ሰፈር ትእዛዝ ወታደሮች ነግቶ ዐለይ ሳይተዉ ድራሻቸው ጠፍቷል። አዎ በራስ ካሣ ጥብቅ ከመውጣቷ በፊት ኑትለው በመጋዣዎች ጭነው ወደፊት ሄደዋል።

አዎ አሁን ራስ ካሣ ጣልያኖች በጉዟችን ላይ በአውሮፕላኖቻቸው በቦንብ ይደበድቡናል የሚል ስጋት አድሮባቸዋል። ግን ይኼንን ድንገተኛ ስጋታቸውንና ፍርሃታቸውን እንዴት ብሎ መረዳት ይቻላል? ብቸኛው ማብራሪያ ሲዊዲናዊው ኢንስትሮም ይዞት የመጣው የጣልያኖች ደብዳቤ ብቻ ነው።

አሁን ጓዴ ብረየርም ከእንቅልፉ ስለተነሳ በፍጥነት ተጉዘን የራስ ካሣን ጦር ቢያንስ ጅራቱን መያዝ አለብን። ለኛ ፈረንጆች ደህንነት ጥበቃ ሃያ የሚያህሉ ወታደሮች ቢኖሩንም ዛሬ ከኔ፣ ከብረየርና ከአቶ ተሰማ በስተቀር አንዳቸውም የኛ ወታደሮች ባጠገባችን የሉም። እንዲህ በዚያ ሁሉ የባላገር ወታደሮች መሀል ጠባቂ ወታደሮች ባጠገባችን የሉም። እንዲህ በዚያ ሁሉ የባላገር ወታደሮች መሀል ከአቶ ተሰማ ጋር ብቻችንን እንደቆምን ራቅ ብሎ በኛ ላይ የሚፎክሩና የሚዝቱ ወታደሮችን መስማት ጀመርን። የኛ ጠባቂዎች በጦር ሰፈር ሲንቀዋለሉ በአጠገባችን ያሉና የኛ ጠባቂ አቶ ተሰማ ብቻ ናቸው። አቶ ተሰማ እነዚህን ባላገሮች እንዴምን ብቻቸውን ማቆም፣ ማገድና እኛ ጣልያኖች እንዳልሆንን ማስረዳት ይቻላቸዋል? ስድቦቹ እና ዛቻዎቹ እየቀረቡ እና እየጠነከሩ መጡ።

"እነዚህ ጣልያኖች እዚህ ምን ይሰራሉ?" ይላል ከፎካሪዎቹ አንዱ፤ "ወይ...ጉድ ወይ...ድፍረት ..." ይላል ሌላው፣ "ጉድ! ጉድ! አገራችንን መውረራቸው መድፈራቸው አንሶ እዚሁ መሃላችን ይንሸራሸራሉ? ጉድ! ጉድ!" ይላል ሌላው፤ "ጎበዝ ምን አታካራ ያስፈልጋል! እዚሁ በነዚሁ ላይ ጣልያኖችን መግደል እንጀምር" ሌላው ሃሳብ ያቀርባል። ታማኙና ደፋሩ የኛ ጠባቂ ወታደሮች አለቃ አቶ ተሰማ ጠብመንጃቸውን አቀባብለው ዘቅዝቀው እንደያዙ፣ "ተው! ተው! ተው! የራስ ካሣ ፈረንጆች ናቸው። ተው ብያለሁ ተው!" እያሉ በነዚህ በሚሳደቡና በሚዝቱ ወታደሮች መሀል እንደተቆጣ ነብር ሲያጉረጠርጡ፣ ያ ይሳደብ ይዝት የነበረው የባላገር ወታደር መንገዱን ከፈተልን። እና አቶ ተሰማም ፈረሶቻችንን ስላመጡልን ከነዚህ ወደፊት ከሚጠብቀን መከራ ከወዲሁ ሊገላግሉን ከተነሱት ኢትዮጵያውያን የገበሬ ወታደሮች ቁራ ወጥተን የራስ ካሣን ዋና ቀዳሚ ጦር ፍለጋ ወደፊት ሄድን።

በበኩሌ በነዚህ ኢትዮጵያውያን የገበሬ ወታደሮች አልፈርድባቸውም። ጣልያኖች ናቸው የሀገራቸውን ድንበር ጥሰው የገቡት። ጣልያኖችን ባገኙት ቦታ እና አጋጣሚ ሁሉ ቢገሉ የሚቃወምም ሆነ የሚቀየም ልብ የለኝም። ችግሩ ታዲያ እነዚህ የባላገር ወታደሮች በአውሮፓ ከጣልያኖች ሌላ ሌሎች የአውሮፓ አገሮች ውስጥ ሌሎች ፈረንጆች መኖራቸውን አለማወቃቸው ነው። የነገራቸው፣ ያስረዳቸው ሰው

የለምና ለነሱ ቆዳው ነጣ ያለ ፈረንጅ ሁሉ ጣልያን ነው። ጣልያን ደግሞ ጠላት ነው። ጠላት እስከሆነ ድረስ ለጠላት የተደገሰው ድግስ ሁሉ እስከ እንጥፍጣፊው ይገባዋል።

በጉዟችን ገፍተን በየሸለቆው፣ በየጅረቱ ታጉረው በፍጥነት ወደፊት እንዳንሄድ ከሚያግዱን ከብቶች እና የጭነት አጋሰሶች ጋር እየተጋፋን ስንጓዝ ቆይተን በመጨረሻ ከፊት ለፊታችን ወደፊት የሚሄዱ ፀጉራቸውን እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ ጦረኛ ሁሉ ያጎፈሩ ታጣቂ ፈረሰኛ ወታደሮችን ማየት ጀመርን። ምን ጊዜም ቢሆን ለምን እንደሆነ በማይገባኝ ምክንያት አብዛኛው የራስ ካሣ የክብር ዘብ ወታደሮች ካላቸው የኢትዮጵያ ወታደሮች የደንብ ልብስ ኮቱን ብቻ ለብሰው፣ በላዩ ላይ ነጠላቸውን ወገባቸው ላይ አስረው፣ ዝናራቸውን በላዩ ላይ ጠምጥመው በፈረሶቻቸው ላይ ተጀንነው እንደ ሁልጊዜው ሁሉ ሲሄዱ አየን። አዎ እነዚህ በትክክል የራስ ካሣ ወታደሮች ናቸው። ይኼ ማለት ደግሞ ወደ ራስ ካሣ እየተቃረብን መጥተናል ማለት ነው። እናም ከነዚህ የራስ ካሣ ወታደሮች ጋር ተቀላቅለን ወደፊት ሄድን።

አሁን ከነዚህ የራስ ካሣ ወታደሮች ጋር የያዝናትን የሸለቆ መንገድ ተከትለን ብንሄድ እርግጠኛ ነኝ ወደ ዋናው መንገድ እስክንወጣ ሁለት ሶስት ሰዓት ይፈጅብናል። እነዚህ ወታደሮች ግን እስከዛሬ ባልረገጡት ምንም በማያውቁት መሬት ላይ ሁሉ በታላቅ ፍጥነት አካባቢውን የማጥናትና ቶሎ የመወሰን ልዩ የተፈጥሮ ችሎታ አላቸው።

አንዱ መትረየስ በትከሻው የተሸከመ ቆፍጣና ጎረምሳ ጦረኛ የሸለቆዋን መንገድ ለቅቆ እጅግ በሚያስደንቅ ፍጥነት በትከሻው ምንም ነገር እንዳልተሸከመ ሁሉ ገደሉን እየቧጠጠ ወደ አፋፍ ወጣ። አለቃ ነገር ነው መሰለኝ፣ በርካታ ወታደሮቹ ተከትለውት ከሱ ፍጥነት በማይተናነስ ሁኔታ ገደሉን ወጥተው አፋፍ ላይ ያንን መትረየስ እስካሁን ከትከሻው ላይ ያላወረደውን የጦር አለቃቸውን ከበው ቆመው ቁልቁል የሰራዊቱን አካሄድ መቃኘት ጀመሩ። አዎ ከዚያች አፋፍ ላይ ሆኖ የራስ ካሣን ጦር አካሄድ በትትክክል ማየት ይቻላል። እናም ወጣቱ ሹም አካባቢውን በፍጥነት ካጠና በኋላ ለራስ ካሣ ማረፊያ የሚሆን ቦታ ፍለጋ ከነጦሩ ወደፊት ሄደ።

ብዙም ሳይቆይ ጩኸትና እልልታ ከርቀት መስማት ጀመርን። የራስ ካሣን ወደቀበሌያቸው፣ ወደ አምባቸው መምጣት የሚያበስሩ የቀበሌው ነዋሪዎች "የእንኳን ደህና መጡ" እልልታ ነበር።

እነዚህ የዚች አምባ ነዋሪዎች ጌታቸው ራስ ካሣ በቀበሌያቸው አረፍ ብለው አንዳንድ የቀበሌውን ችግሮች ይፈቱልናል፣ መልክ መልክ ያሲዙልናል ብለው ያምናሉ። የዕድልና የአጋጣሚ ነገር ሆኖ ጌታቸው ዛሬ በቀበሌያቸው አረፍ ብለው የማይቆዩ ከሆነ እነዚህ መንደርተኞች ለጎረቤት ቀበሌዎች አፋፍ ላይ ቆመው ጮክ ብለው በመጣራት ራስ ካሣ ወደ ጎረቤት ቀበሌ መዝለቃቸውን ያበስራሉ። እንዲህ

እየሙሁ ከገደል ማሚቶዎች ጋር ህብረት በመፍጠር ዜናውን ያሰራጩታል። ቀላልና ምንም ገንዘብ የማያስወጣ የመገናኛ ዘዴ - ጥኢትዮጵያውያን ጥንታዊ ቀላል ስልክ።"

ቀኛሚው የራስ ካሣ ታጣቂ ጦር በቀኛዝማች አበበ እየተመራ ከራስ ካሣ ቀድሞ ወደፊት ሲሄድ፤ ከዚህ ጦር ቀጥሎ ራስ ካሣ በክብር ዘብ ወታደሮቻቸው ታጅበው በወርቅ ገፕ በተሸለሙትና ባጌጠቿው በቅሏቸው ላይ ተቀምጠው ይኼዳሉ።

ከዚች ወርቃማ በቅሎ ኋላ አንድ ፈርጠምና ረዘም ያለ ጥቁር አሽከራቸው ጥቁር ቀለም ያለውን የዘር ሐረጋቸው ምልክት፣ በብር ተከትቦ ያጌጠውን በትረ መንግስታቸውን ይዞ ይሮጣል። ይቺ ለዚህ አሽከራቸው ብቸኛ ስራው ነች ።

ከዚህ በትረ መንግሥት ያዥ ኋላ ሁለተኛው አሽከራቸው ተንቀሳቃሽ ዙፋናቸውን ተሸክሞ ሱክ ሱክ ይላል። ለዚህኛውም አሽከራቸው ተንቀሳቃሽ ዙፋኗን ተሸክሞ የራስን ፈረስም ሆነ በቅሎ ዱካ ተከትሎ መሮጥ ብቸኛ ስራው ነች።

ዛሬ ደጃዝማች ወንድወሰን በተለመደው ቦታው የለም። ደጃዝማች ወንድወሰን የአባቱን ግማሹን ያህል ጦር እየመራ በበጅሮንድ ለጥይበሉ ታጅቦ የአንድ ቀን መንገድ ያህል ርቆን እና ቀድሞ ወደፊት ሄዷል።

ከራስ ካሣ እና ከአጀባቸው የክብር ዘባቸው ጦር ኋላ የንጉሠ ነገሥቱ እማካሪ ቀኛዝማች ደህኔ ይኼዳል። እኛም ከዚሁ ቀኛዝማች ጋር ተቀላቅለን ከጎኑ መሄድ ጀመርን። እንዲህ ከቀኛዝማች ደህኔ ጎን ስንሄድ ሶስተኛው የራስ ካሣ የግል አሽከር በጀርባው አንዲት ከፍ ያለች ተጣጣፊ ወንበር ተሸክሞ በሁለቱ አሽከር ጓደኞቹ ላይ ለመድረስ ሲሮጥ፣ ከታጣፊዋ ወንበር ላይ በወርቅ ቀለም በተቀባች አንዲት ብረት ላይ "Made in Czechoslovakia" ይላል። ይገርማል የቼኮዝሎቫኪያ ምርት በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ማየት ምን ያህል ያስገርማል።

ከኛ በኋላ አብዛኛው ሹማምንት አስቂኙን ጥቁር ሹሗን በርኖስ ደርበ ሲሄድ፣ ይኼ አለባበሳቸው በአውሮፓ በመካከለኛው ዘመን ጊዜ የነበሩትን ዘራፊ ሽፍቶችን አስመስሏቸዋል።

እንዲህ በዚህ መልክ ስንጓዝ ከአዲስ አበባ ጋር ረዘም ላለ ጊዜ ግንኙነት አልነበረንም። እና እነሆ ዛሬ የኛ ስልከኞች ገመዶቻቸውን ዘርግተው ግንኙነት ከአዲስ አበባ ጋር ለማድረግ እየሞከሩ ነው።

መላው አለም ስለዚህ ጦርነት ምን እያለ እንደሆነ ምንም የምናውቀው ነገር የለም። ጣልያኖች እንኳን የት ደርሰው እንደሆነ እስካሁን የሰማነውም የምናውቀውም ነገር የለም። ምናልባት መቀሌም በእጃቸው ወድቃ ሊሆን ይችላል። ምናልባትም ጣልያኖች ወደ አምባ አላጌ ዘልቀውም ሊሆን ይችላል። ብቻ ምንም አናውቅምና ጠቅላላ ተስፋችንን በዚችው ስልክ ላይ ጥለን በታላቅ ትግስት መጠበቅ ጀመርን።

የስልክ ግንኙነት ለማግኘት ሁለትም ሶስትም ሰዓት ምናልባትም ከዚያም ጊዜ በላይ ሊፈጅ ይችላል። አንዳንዴም ቀኑን ሙሉ ተሞክሮ ፈጽሞ ላይሳካ ይችላል።

ለጊዜው የምናውቀው ነገር ቢኖር የራስ ሥዩም መንገሻ ጦር በአድዋ ከሶስት ክፍለ ጦሮች ጋር ተዋግቶ የማይሆን መሆኑን ሲረዳ፣ ወደ ተንቤን ሄዶ የኛ ጦር እስኪደርስ ድረስ በጫካ መግባቱንና የጣልያኑ ጦር ያለ ብዙ ችግር በትግራይ መሬት ላይ እየተንሸራሸረ ወደፊት መሄዱን ብቻ ነው።



እየሮጡሁ ከገደል ማሚቶዎች ጋር ህብረት በመፍጠር ዜናውን ያሰራጩታል፡፡ ቀላልና ምንም ገንዘብ የማያስወጣ የመገናኛ ዘዴ - "የኢትዮጵያውያን ጥንታዊ ቀላል ስልክ፡፡"

ቀዳሚው የራስ ካሣ ታጣቂ ጦር በቀኛዝማች አበበ እየተመራ ከራስ ካሣ ቀድሞ ወደፊት ሲሄድ፣ ከዚህ ጦር ቀጥሎ ራስ ካሣ በክብር ዘብ ወታደሮቻቸው ታጅበው በወርቅ ጌጥ በተሸለመችና ባጌጠቺው በቅሏቸው ላይ ተቀምጠው ይኼዳሉ፡፡

ከዚች ወርቃማ በቅሎ ኋላ አንድ ፈርጠምና ረዘም ያለ ጥቁር አሽከራቸው ጥቁር ቀለም ያለውን የዘር ሐረጋቸው ምልክት፣ በብር ተከትቦ ያጌጠውን በትረ መንግስታቸውን ይዞ ይሮጣል፡፡ ይቺ ለዚህ አሽከራቸው ብቸኛ ስራው ነች ፡፡

ከዚህ በትረ መንግሥት ያዥ ኋላ ሁለተኛው አሽከራቸው ተንቀሳቃሽ ዙፋናቸውን ተሸክሞ ሱክ ሱክ ይላል፡፡ ለዚህኛውም አሽከራቸው ተንቀሳቃሽ ዙፋኗን ተሸክሞ የራስን ፈረስም ሆነ በቅሎ ዱካ ተከትሎ መሮጥ ብቸኛ ስራው ነች፡፡

ዛሬ ደጃዝማች ወንድወሰን በተለመደው ቦታው የለም፡፡ ደጃዝማች ወንድወሰን የአባቱን ግማሹን ያህል ጦር እየመራ በበጅሮንድ ለጥይበሉ ታጅቦ የአንድ ቀን መንገድ ያህል ርቆን እና ቀድሞ ወደፊት ሄዷል፡፡

ከራስ ካሣ እና ከአጀባቸው የክብር ዘባቸው ጦር ኋላ የንጉሠ ነገሥቱ አማካሪ ቀኛዝማች ደህኔ ይኼዳል፡፡ እኛም ከዚሁ ቀኛዝማች ጋር ተቀላቅለን ከጎኑ መሄድ ጀመርን፡፡ እንዲህ ከቀኛዝማች ደህኔ ጎን ስንሄድ ሶስተኛው የራስ ካሣ የግል አሽከር በጀርባው አንዲት ከፍ ያለች ተጣጣፊ ወንበር ተሸክሞ በሁለቱ አሽከር ጓደኞቹ ላይ ለመድረስ ሲሮጥ፣ ከታጣፊዋ ወንበር ላይ በወርቅ ቀለም በተቀባች አንዲት ብረት ላይ "Made in Czechoslovakia" ይላል፡፡ ይገርማል የቼኮዝሎቫኪያ ምርት በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ማየት ምን ያህል ያስገርማል፡፡

ከኛ በኋላ አብዛኛው ሹማምንት አስቂኙን ጥቁር ሹሟን በርኖስ ደርቦ ሲሄድ፣ ይኼ አለባበሳቸው በአውሮፓ በመካከለኛው ዘመን ጊዜ የነበሩትን ዘራፊ ሽፍቶችን አስመስሏቸዋል፡፡

እንዲህ በዚህ መልክ ስንጓዝ ከአዲስ አበባ ጋር ረዘም ላለ ጊዜ ግንኙነት አልነበረንም፡፡ እና እነሆ ዛሬ የኛ ስልከኞች ገመዶቻቸውን ዘርግተው ግንኙነት ከአዲስ አበባ ጋር ለማድረግ እየሞከሩ ነው፡፡

መላው አለም ስለዚህ ጦርነት ምን እያለ እንደሆነ ምንም የምናውቀው ነገር የለም፡፡ ጣልያኖች እንኳን የት ደርሰው እንደሆነ እስካሁን የሰማነውም የምናውቀውም ነገር የለም፡፡ ምናልባት መቀሌም በእጃቸው ወድቃ ሊሆን ይችላል፡፡ ምናልባትም ጣልያኖች ወደ አምባ አላጌ ዘልቀውም ሊሆን ይችላል፡፡ ብቻ ምንም አናውቅምና ጠቅላላ ተስፋችንን በዚችው ስልክ ላይ ጥለን በታላቅ ትግስት መጠበቅ ጀመርን፡፡

የስልክ ግንኙነት ለማግኘት ሁለትም ሶስትም ሰዓት ምናልባትም ከዚያም ጊዜ በላይ ሊፈጅ ይችላል፡፡ አንዳንዴም ቀኑን ሙሉ ተሞክሮ ፈጽሞ ላይሳካ ይችላል፡፡

ለጊዜው የምናውቀው ነገር ቢኖር የራስ ሥዩም መንገሻ ጦር በአድዋ ከሶስት ክፍለ ጦሮች ጋር ተዋግቶ የማይሆን መሆኑን ሲረዳ፣ ወደ ተንቤን ሄዶ የኛ ጦር እስኪደርስ ድረስ በጫካ መግባቱንና የጣልያኑ ጦር ያለ ብዙ ችግር በትግራይ መሬት ላይ እየተንሸራሸረ ወደፊት መሄዱን ብቻ ነው፡፡

15

የጠላት ጦር ከፊታችን

ቀን መቁጠሪያው ህዳር 3 ቀን 1935 ዓ.ም. እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ያሳያል።

ጣልያን የኢትዮጵያን ድንበር ጥሳ ከገባች ድፍን ወር መሆኑ ነው። የራስ ካሣ ጦር ወደ ሰሜን ገስግሶ ወራሪውን የጣልያን ጦር ወደ መሀል ሀገር ዘልቆ እንዳይገባ ተዋግቶ ማቆም አለበት።

ከመጀመሪያው ወደ መሀል ሀገር ከሚገሰግሰው የጣልያን ብርጌድ ወይም ክፍለ ጦር የሚለዩን የተወሰኑ ተራራዎችና ብዙ ስርጥ የሚበዛቸው አስቸጋሪዎቹ የቀላማው ቀበሌ መንገዶች ብቻ ናቸው።

ትናንት ማታ ራስ የሬድዮ ኦፕሬተሮችን አስጠርተው ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር ያገናኟቸው ዘንድ አዘዙ። የራዲዮ ግንኙነት ምን ያህል አደገኛ እንደሆነና በቀላሉ ሊያጋልጠን እንደሚችል ብወተውትም ራስ ካሣ ሳቅ ብለውና ትከሻዬን ቸብ ቸብ እያደረጉ፣ "አይዞህ፣ እኔና እሳቸው የምስጢር ቃል አለን፤ ተነጋግረንበታል። ከንጉሤና ተኔ በቀር ማንም አያውቀውም" አሉኝ።

በኋላ ላይ እንደታየው እውነት ነበረኝ። ራሱ ማርሻል ባዶሊዮ ብዙ ጊዜ ከንጉሠ ነገሥቱ የሚተላለፉ ወታደራዊ አመራሮች በሰሜን ካለው የኢትዮጵያ ከፍተኛ የጦር መሪዎች ሳይደርስ እጁ ይገባ እንደነበር አምኖ ተናግሯል።

የጣልያን የሬዲዮ ኦፕሬተሮች ከንጉሡ የሚተላለፉና ለኛ ቀልጣፋ ኦፕሬተሮች እንኳ ለፍቺ ጊዜ የሚወስዱ መመሪያዎችን ያለአንዳች ቁልፍ በቀላሉ ይፈቱ እንደነበር በኋላ ላይ አይተናል። ከዚህ ሁሉ ሌላ የኛ ኋላ ቀር እና ደካማ ራድዮ ልትሰበው

የማትችለውን የራዲዮ ትዕዛዝ በቀላሉ ሰበው እጃቸው ያስገቡ ነበር። አዎ ይቺ መከረኛ የማትረባ ራዲዮ አንድ ቀን የሰፈርንበትን ቦታ አጋልጣ ለጠላት እንደምትሰጠን የነበረኝ ፍራቻ ትክክል ነበር።

አንድ ቀን ማለዳ ራስ ካሣ ከጥቂት ወታደሮች ጋር በቅርብ ወዳለች አንዲት ጥንታዊ ቤተ ክርስቲያን እንደሄዱ፣ እኔም በድንኳኔ ተቀምጬ በቁራጭ መስታወት ፊቴን እያየሁ ጢሜን ለመላጨት ስታገል፣ አንድ አሽከር ከድንኳኔ በራፍ ተገትሮ፣ "ጣልያኖች! ጣልያኖች መጡ! ቶሎ ቶሎ ጌታዬ" እያለ ይዘላብድ ጀመር። አሽከሩ በጣም ተረብሿል ። ጣልያኖች ከኛ ቢያንስ 200 ኪሎ ሜትር ርቀው እንዳሉ በተሰባበረ አማርኛ ላስረዳው ስሞክር ለኔ መናገሩ አጉል ድካም መስሎ ስለተሰማው "ጣልያኖች መጡ! ጣልያኖች መጡ!" እያለ በየድንኳኖች በራፍ ጩኸቱን ለቀቀው።

ሁኔታው አስገርሞኝ ከድንኳኔ ስወጣ የሚያጉረመርም የአውሮፕላን ድምጽ ሰማሁና የጦር ሜዳ መነጽሬን አስተካክዬ ሰማዩን ቃኘሁ። አዎ ባለ ሶስቱ ሞተር ትልልቆቹ የጣልያን አውሮፕላኖች ነበሩ። በግምት 2,000 ሜትር ከፍታ ላይ ተንሳፈው ወደኛ ይበሩ ነበር። የኔ ተንቀሳቃሽ ድንኳን ሁሌም የምትቆመው ከራስ ትልልቅ ድንኳኖች ጎን ስለሆነ ለጀማሪ አውሮፕላን አብራሪም ቢሆን በቀላሉ ኢላማ ውስጥ የምትገባ ነበረች። እና እቃ ንብረት ለማሸሽ ቀርቶ የገዛ ነብስን ለማዳን መሸሸጊያ ብጤ እንኳ ለመፈለግ ዘግይቶ ነበር። በርካታ ወታደሮች ጠብመንጃቸውን እየፈላለጉ ድንጋይ ተንተርሰው ለተኩስ ተዘጋጅተዋል። በርከት ያሉ ሴቶችና ህጻናት በመረበሽ ከወዲያ ወዲህ ነፍስ አውጪኝ ይሮጣሉ። አውሮፕላኖቹ በሰፈራችን አናት ላይ ሲያንዣብቡ ሰፈራችን ቀውጢ ሆነች። ተራራውን ታቅፎ የመሸገው ጦራችን በነዚህ የሰይጣን ቀርቀሮዎች ላይ የጥይት ናዳውን በከንቱ አርከፈከፈው።

አብዛኛው ወታደር አውሮፕላን ሲያይ የመጀመሪያው ጊዜ በመሆኑ ጎበዝ ተኳሽነቱን ሀገር ምድሩ የመሰከረለት ጀግና እንደምን ይችን ቀርቀሮ ሊስት እንደቻለ እያሰበ ይገረማል። ብቻ ከአሮጌ ጠመንጃዎች አፍ ቡልቅ እያለች የምትወጣው የባሩድ ጭስ ለጣልያን ልምድ ያላቸው አብራሪዎች የጦራችንን አሰፋፈር አጋልጣ ሰጠች።

አውሮፕላኖቹ ሰፈራችንን ቃኝተው ሲያልፉን ያላዩን መስሎን ለጊዜው ተደሰትን። ግን ብዙም ሳይቆዩ የአሸንጌን ሐይቅ ዞረው በጦር ሰፈራችን አናት ላይ ዝቅ ብለው ሲበሩ እንዳገኙን ተረዳን። ከአሁን በኋላ ጥንቁቆችና ለጣልያን አውሮፕላኖች የቦንብ ውርጅብኝ ዝግጁ መሆን እንዳለብን ሁላችንም ተረዳን።

ራስ ካሣ ከቤተ ክርስቲያኗ እንደተመለሱ በአስቸኳይ ሹማምንቱን ለምክር ጠርተው ከመከሩ በኋላ በተቻለ ፍጥነት ከጣልያኖች የቦንብ ውርጅብኝ መከላከያ ምሽግ እንዲቆፈር ለሹማምንቱ ትዕዛዝ ሰጡ። ሃሳቡ በጣም ጥሩና ጠቃሚ ነበር። ግን በኢትዮጵያ ምድር ተግባራዊ ማድረግ አስቸጋሪና ፈጽሞ የማይቻል ነገር ነበር። እንኳን ተራው የገበሬ ወታደር ይቅርና አሉ ከሚባሉት ታላላቅ ሹማምንቶች እንኳን

ያ እንዲቆፈር የታዘዘው ኮማሊኖች የአውሮፕላን የቦንብ ውርጅብኝ መከላከያ ወይም መሸሸጊያ ምሽግ ምን እንደሚመስልና እንዴትስ መቆፈር እንዳለበት የሚያውቅ አንድም ሰው አልነበረም።

እንደዚህም ሆኖ አሁን ከ70ሺ ከሚበልጠው የራስ ካሣ ሰራዊት ውስጥ አንድ ክፍለ ጦር ብሬት በአዲስ አበባ በእንግሊዝ ኤምባሲ ግቢ ውስጥ ከአውሮፕላን ቦንብ መከላከያ ምሽግ ሲቆፈር ያየ ወታደር ተገኘ። ትልቁ እና ዋናው ችግር ግን ኢትዮጵያውያን የጉልበት ስራ ከበሽታ በላይ አጥብቀው የሚጠሉ መሆናቸው ነበር።

ራስ ካሣ በዚህ በእንግሊዞች ኤምባሲ ምሽግ ሲቆፈር ባየ ወታደር ተቆጣጣሪነት ምሽጉ እንዲቆፈር፣ ሁሉም ሹሞች የምሽጉን አቆፋፈር ቆመው እንዲያዩና እንዲያጠኑ ካዘዙ በኋላ ሙሉ ሃላፊነቱንም ለቀኛዝማች አበበ አሳልፈው ሰጡ።

ምስኪን ቀኛዝማች አበበ። ቀኑን ሙሉ ከድንኳን ወደ ድንኳን እየሮጡ ሹማምንቱን የምሽጉን አቆፋፈር እንዲመለከቱ ሲማጸን ዋለ። ቀኛዝማች አበበ እንዲህ ሲቀርብ ወደታሰበው ምሽግ ቦታ ብቅ ያሉት ጥቂት ሹሞች ብቻ ነበሩ። የቀሩት ሹሞች "ራስ ካሣ እኛን ለማዘዝ ምንም መብት የለውም!" ብለው እንዲሁ በየድንኳናቸው ወሬያቸውን ሲሰልቁ ዋሉ። ቀኑን ሙሉ ሲሮጥ የዋለበት ልመና ውጤት አሳዛኝ ነበር። ከ70ው ሺ ጦር ውስጥ

ብዙም ሳይቆይ ሌላ ሁለተኛ ችግር ተፈጠረ። ያም ችግር "ምሽጉን ማን ነው የሚቆፍረው? እንደገና ምሽጉን ቆፋሪ ሰው ሲፈልጉ ቆይተው በመጨረሻ ላይ አንድ ባሪያ አገኙና ይዘውት መጡ። እንግዲህ ከአውሮፕላን ቦንብ ውርጅብኝ መከላከያ ወይም መደበቂያ ምሽግ በአንድ ባሪያ ጉልበት መቆፈር አለበት ማለት ነው። አንድ ሰው ብቻውን ምሽጉን ሲቆፍር ሌሎቹ ቆመው እያዩ ይስቁ ነበር። ትልቁ ሃላፊነት የተሰጠው ቀኛዝማች አበበም ቢሆን ችግሩ ይኼን ያህል ያስጨነቀው አይመስልም። እሱም ከመሰል ጓደኞቹ ጋር ቆሞ እያወራ ይስቅ ነበር። እንደማየው ይኼ ምስኪን ባሪያ ይኼንን ምሽግ በሳምንትም ቆፍሮ አይጨርሰውም።

"ለምን ሌሎች ወታደሮች በቁፋሮው አይረዱትም? ይኼ ቁፋሮ ለአንድ ሰው አድካሚና ረጅም ጊዜ ይወስዳልኮ?" ስል ቀኛዝማች አበበን ጠየኩት። "ሌሎች?" ቀኛዝማች በመገረም እያየኝ "እዚህ ማን አለ ብለው ነው ጌታው?" አለኝ በግልጽነት። ወዲያው በአካባቢው ዝም ብለው ወሬ ወደሚሰልቁት ወታደሮች ጣቴን ቀስሬ ሳሳየው፣ ቀኛዝማች አበበ አሁን ኮስተር ብሎ፣ "ጌታው እነዚህኮ ወታደሮች ናቸው። እንዳቸውም ዶማና አካፋ እሺ ብለው አያነሱም" አለኝ። ቀኛዝማች አበበ እውነቱን ነበር። በኋላ ላይ እንደተረዳሁት የኢትዮጵያ ወታደር ምንም እንኳን ስራሱ ደህንነት ቢሆንም ራሱን ዝቅ አድርጎ ጉድጓድ ቆፍሮ አይደበቅም። መደበቅ ማለት ፈሪና ወራዳ ማለት ነው፣ ቢያንስ ለገበሬው ወታደር።

በጠቅላላው የጦርነት ጊዜ የራስ ካሣ ሰራዊት አንድም ከአውሮፕላን ቦምቦች መከላከያ ምሽግ ቆፍሮ አያውቅም። በስፊው የተወራለትና በአውሮፓ በሚታተሙ ጋዜጦች ተጋኖ የተነገረለት የመቅደላው ምሽግ ምናልባት ታላቁ የጦር መሪ ዳግማዊ ቴዎድሮስ ከእንግሊዞች ጦር ለመከላከል የገነባው ቅርስ ካልሆነ በስተቀር፣ የራስ ካሣ ጦር አንድም ምሽግ ለመገንባት አልሞከረም። ማምሻው ላይ ወደዚያች በአንድ ባሪያ ወደምትቆፈር ምሽግ ብሄድ የምሽጉ ብቸኛ ቆፋሪ ባሪያ በስራው ላይ አልነበረም። በሁለተኛው ቀን ያ ባሪያ ወደ ምሽግ ቁፈራ ስራው ብቅ ሳይል ቀረ። ምሽጉም እንደተጀመረች ሳታልቅ በዚያው ቀረች።

በሚቀጥለው ቀን ገና ጎህ ሳይቀድ አቶ ተሰማ ቀሰቀሱኝ። "ምነው አቶ ተሰማ እንዲህ በማለዳ?" ብላቸው፣ "የለም ጌታ ይነሱ! ቶሎ ይበሉ ጌታ ይነሱ!" አቶ ተሰማ መወትወታቸውን ቀጠሉ። እንደነገሩ ቀልጠፍ ብዬ ለባበስኩና ጠመንጃዬን አንግቼ አይኔን እያሻሸሁ ከድንኳኔ ወጣሁ። ሁለቱ የራስ ትልልቅ ድንኳኖች ያለወትሯቸው ያለዘብ ተገትረዋል።

ያ ብቻ ሳይሆን ስፈራ ጭር ማለቷ አስገርሞኝ ወደ አቶ ተሰማ ስዞር፣ አቶ ተሰማ ያንን ድንግርተኛ ሳቃቸውን እየሳቁ "አዩ ጌታ፣ የኛ ራስ በጣም ብልህ ናቸው" አሉና አሁን እየሳቁ በመቀጠል ራስ ትናንት ማታ ለወታደሮቻቸው በሌሊት ሰፈር ለቅቀው በተራራው ጫካ ውስጥ እንዲመሽጉና አንዳንድ የጦር ሹሞች ድንኳኖቻቸውንም እንዳለ እንዲተዉ ማዘዛቸውን አጫወቱኝ። በመቀጠልም "አየህ ጌታ! የኛ ራስ ብልጠት? እንግዲህ እነዚያ የጣልያኖች የሰይጣን ቆርቆሮዎች የራስን ትልልቅ ድንኳኖች ተሩቅ አይተው መጥተው አገኘን ብለው ለመደብደብ ዝቅ ሲሉ እኛ ተላይ ከተራራው ሆነን ቁልቁል እናት እናታቸውን እንላቸውና" ሳይጨርሱ አሁንም ሳቃቸውን ለቀቁት።

ትንሽ ሳቃቸውን ገታ አድርገው፣ "አየህ የራስን ብልህነት? ግዴለም ጌታ ዛሬማ አንድ ሶስቱን ባፍጢማቸው ነው የምንደፋቸው" አሉኝ አሁንም የደስታ ሳቅ እየሳቁ። አቶ ተሰማ ጣልያኖች ነገ እስኪመጡ ቁምጣ ይገዛልሀል እንደተባለ ህጻን ክፉኛ ጓጉተዋል።

እኔም የራስ የጦር ስልት ገብቶኝ ተራራውን ታቅፌ መትረየሴን ጠምጄ ጣልያኖችን እጠብቅ ገባሁ። ታድያ እንዲህ ገደል አቅፈን ድንጋይ ተንተርሰን ቀኑን ሙሉ ጣልያኖችን በሰማይ ብንጠብቅም፣ ወሬ የሰሙ ይመስል ብቅም ሳይሉ ቀሩ። የራስ ካሣም የጦር ስልት ሳይሞከርና በተግባር ሳይፈተን ቀረ።

በዚህ በጣም የተናደደ አንድ የገበሬ ወታደር፣ "ይኼ ፈሳም"! ወንድ ከሆነ ዛሬ አይመጣም ነበር? ቆይ እኔ ስውዬው! እንዲህ እንዳላገጡብን መቼስ አይቀሩ" እያለ በንዴት ሲፎክር ሰምቻለሁ።

በሁለተኛው ቀን የጦርተን ድጋፏናኛ ነቅተለን ጉዞ ጀመርን። ባብዛኛው የራስ ጦር የተራራውን ምሬብ ቦሬል ወገብ እየተከከ ሲሄድ ጥቂቶች የራስን ጀርባ እንዲጠብቁ ተብሎ የተራራውን ምስራቃዊ ወገብ ይዘው ይጓዛሉ። እኔም ይኼንኑ መንገድ መረጥኩ። ይሁን እንጂ የአቶ ተሰማ ወታደሮች በነተምህረቶ ያሉትን መንገድ እርሾ ነው ብለው ይሁን ብቻ እምቢ አሉ። ከብዙ ያቀ ተሰማ የመረጥኩትን መንገድ እርሾ ነው ብለው ይሁን ብቻ ወታደሮቹ ያለፍላጎታቸው ተከተሉን።

የተራራውን ወገብ እያሸን ተጉዘን ካንዲት ሜዳማ ቦታ ደረስን። ከሚዳቁ የተራራውን ወገብ እያሸን ተጉዘን ካንዲት ሜዳ ሜዳውን በነተምህረቶ ሙሉ ጥልቅ ያለ ገደል አለ። ገደሉን ወደቀኝ ትተን ሜዳ ሜዳውን ትንሽ እንደሄድን ከቁጥቋጦዎች ውስጥ፣ "ማነህ? ቁም! ቁም ብየሃለሁ!" የሚል ትንሽ እንደሄድን ከቁጥቋጦዎች ውስጥ ብዙ ብዙ አፈሙዞች እስኪንጋጥ ደርሶ ሰምተን ቆምን። ከቁጥቋጦዎች ውስጥ ብዙ ብዙ አፈሙዞች እየማተረሙጡን ነበር።

"እኛ ነን አትተኩሱ። እኛ ነን።" አቶ ተሰማ ብዙ ወተወቱ። ወታደሮቹ አቶ ተሰማን ሲያዩ አፈሙዞቻቸውን ወደ መሬት መልሰው አሳለፉን። ጥቂት እንደተጓዝን ከአንዲት እስከ ሃምሳ ቁጥሩ ስር በርከት ያሉ ሹሞች ዙሪያ ተቀምጠው ሲያወሩና ሲመክሩ አገኘናቸውና ወደ ሹሞቹ ስንጠጋ አንድ በጣም ሽምግል ያሉ፣ ፀጉራቸው የተንደረ ጥጥ የመሰለ፣ አንድ አይናማ ሰው ተነስተው፣ "እዚህ ምን ትሰራላችሁ? እሉን።" እዎ እኒህ አንድ አይናማ አዛውንት ደጃዝማች አስፋው ናቸው። ደጃዝማች አስፋው እዝሶ ዓለፋት አደጋ አመታት አለምን በአንድ አይናቸው ነው የሚያዩት። ሁለተኛውን አይናቸውን በታላቁና ገናናው የአድዋ ድል ከእምዬ ምኒልክ ጋር ሲዋጉ ጥለዋታል።

ደጃዝማች አስፋው ያኔ ከእምዬ ሚኒልክ ጋር በዘመቱ ጊዜ አንድ የጣልያን መትረየስ በፈረስ ሆኖ የተተኮሰት ጥይት አይናቸውን ብታፈስውም፣ ያ ሳይበግራቸው በሌላው በንራዬ የዚያን ጣልያን አንገት ቀልተዋታል። አዎ ደጃዝማች ከዚያች ቀን ጀምር አንድ አይናቸው ለዘላለሙ ብትጨልምም፣ ዛሬም ባንድ አይናቸው በዚያው ጎራዴ፣ በዚያችው መንገድ፣ ከተመሳሳይ ጠላት ጋር ለመግጠም እነሆ ጦራቸውን ይዘው ራስ ካሣን ተከትለው እዚች ደርሰዋል።

ዳግም የሩሹሱን ጦር ድል መተው የሀገራቸውን ድንበር ለማስከበር ሽምግልና የተጫጫነውን ወገባቸውን በዝናር ጥፍር አድርገው አስረው ቆመዋል። "እዚህ ምን ትሰራላችሁ? ተመልሳችሁ አሁኑኑ ከዋናው የራስ ካሣ ጦር ጋር ተቀላቀሉ! ባይሆን ጥቂት ወታደሮች እጨምርላችኋለሁ፤ በሉ ሂዱ።" አሉ ፍጹም አባትነት በተሞላበት ቃል።

"ምንም ችግር የለም ደጃዝማች፣ ከርስ ጋር እንቆያለን" አልኳቸው። "እግዚአብሔር ምስክሬ ነው። በፍጹም አይቻልም" አሉኝ፣ አሁን አምርረው። ቆጥለውም፣ "ስማኝ ልጅ" አሉና በቀኝ እጃቸው ማዶ ወደተራራው ጥግ እያሳዩኝ

"ታያለህ እነዚያን አረመኔ ራያዎች? ይኼው ሳምንታቸው ቂጥ ቂጣችንን ሲከተሉን። እነሀ አረመኔ ራያዎች ብዙ ናቸው። ጣልያኖችም መሳርያና ጥይቶች ስለላኩላቸው አንድ ሰዓት ጠብቀው ሊወጉን ነውና እባክህ ልጄ በጊዜ ተዋናው ጦር ተቀላቀል" አሉኝ።

ደጃዝማች አስፋው ለራሳቸው ሳይፈሩ ለኔ እንደ አባት በመጨነቃቸው ፍጹም ልቤን ነኩት። እንደ ወላጅ አባቴ ወደድኳቸው። ቢሆንም ወደኋላ የመመለሱን ሃሳብ ሳልቀበላቸው ቀርቼ እሳቸውም ማምረሬምን አይተው ዝም ስላሉኝ ለትንሽ ጊዜም ቢሆን አብሬአቸው ተቀመጥኩ። እንዲህ ከሹሞች ጋር ዙሪያ ገጥመን እየተጫወትንና ራያዎችን እየጠበቅን ብንቆይም፣ ራያዎችም ደፍረው ባለመምጣታቸው፣ ደጃዝማች ጦራቸውን ወደፊት በማለታቸው የራስ ካሣን ጦር ክንን ሽፋን እየሰጠን ጉዞ ቀጠልን።

በሁለት ትላልቅ ገደሎች መካከል ካለ አንድ ረባዳ ቦታ አዳራችንን ልናደርግ ወስነን ድንኳን ጥለን ለመተኛት ብሞክርም እንቅልፍ እምቢ አለኝ። ሌሊቱን ሙሉ ይዘንባል። ከፍ ከፍ ያሉ የገደል ጠብታዎች የድንኳኔን ጣሪያ እንደ ከበሮ ሲደልቁት አድረው ገና ጨለማው እንኳ ሳይለቅ ሽለብ ካልኩበት የሰመመን እንቅልፍ ቀሰቀሱኝ። ቁርስ እንኳ ሳናደርግ ፈረሶቻችን ተጭነው ስለነበር ጉዞ ጀመርን።

ከዋናው ጦራችን ጋር ገና ከመቀላቀሌ አንድ የራስ ካሣ አሽከር ራስ ካሣ እንዳስጠሩኝና ክፉኛ እንደተቆጡም መልክተኛው ነገረኝ። በራስ ካሣ ፊት እንደቀረብኩም፣ ራስ ሊገጥሙኝ ስለሚችሉ አደጋዎች ብዙ ብዙ ካሉኝ በኋላ ሁለተኛ ከዋናው ጦር ብዙ ርቀን እንዳንሄድና ያለነው በራያዎች መሬት ላይ በመሆኑ ሁኔታው ምን ያህል አደገኛ እንደሆነ አጥብቀው ነግረው አስናበቱኝ። እንግዲህ ከዚህ ከተጋለጠ መሬት ለመውጣትና በተቻለ ፍጥነት ርቆ ለመሄድ ፈረሶችን ቼ እንል ገባን።

ቀኑን ሙሉ ሜዳማ በሆነው በራያዎች ምድር ከላይ ከሰማይ የጣልያን የሰይጣን ቆርቆሮዎችን፣ ከኋላ አረመኔ የራያ ጦረኞችን አዝለን ስንነዝ ውለን ከሁለት ተራራ ከሚመስሉ ጉብታዎች ላይ ደረስን። በሁለቱ ትንንሽ ተራራዎች መካከል በቁልቋል የታጠሩ ብዙ ብዙ ክብ የሳር ጎጆ ቤቶች ይታያሉ። እዎ ያቺ የሳር ጎጆ የበዛባት ከተማ "ማይጨው" ናት። አሁንም ያስማቋረጥ ይዘንባል።

ወደ ማይጨው ስናመራ በርካታ ውትት የመሰለ ነጭ ሸማ የለበሱ ገበሬዎች በዕልልታ ተቀበሉን። አብዛኛው ገበሬ ታጥቋል። ሴቶችና ህጻናት ውሃ፣ ጠላ ብቻ በጃቸው ያለውን በመንገድ ላይ ላለው ጦር ያድላሉ። እኔም አንድ ከፍ ያለ ቅል ሙሉ ቀንጆ ቀዝቃዛ ጠላ ደርሶኛል።

እነዚህ የትግሬ የገበሬ ወታደሮች ጌታቸው ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ሜዳ ላይ በትናቸው፣ ሀገርና ህዝቡን ከድቶ ለጣልያን ገብሮ ኤርትራ ቢገባም በዚህ ሳይበገሩ አዲስ ሹም መርጠው፣ ሹማቸው በራስ ካሣ ተንቀሳቃሽ ዙፋን ፊት

... ከራስ ጦር ጋር የጠላትን ጦር ደዋጋ ዘንድ [illegible] እንደ[illegible] ራስ ካሣም ከወደቀበት እንዲነሳ አዘው እንዲልዷቸው አትሬጠ [illegible] የትግሬ ወታደር ውዲን ጥይቱን በደስታ ወደሰማይ [illegible]

[illegible] ነን፡ አገዜና በዳመናና በጉም የጣልያኖችን እይታ [illegible] እንደተራብ የቀበሮ መንጋ እያደፈጡ ቢከተሉንም [illegible]

[illegible] ተራራ [illegible] ለመድረስ ገና ሁለት የተራራውን ወገቦች [illegible] 2,910 ሜትር ከፍታ ያላትን አነስ ያለች ተራራ [illegible] የእያ ቀበሌ ነች።

[illegible] ራስ ካሣ ለአሽከሮቻቸው ምልክት ሲሰጡ ፈረሶችን [illegible] በአበባ ምንጣፍ ላይ ሲዘረጉ፣ ራስ ካሣ ከፈረሳቸው [illegible] ላይ ተቀምጠው አካባቢውን መቃኘት ጀመሩ። ሹማምንቱም [illegible] ሁሉ ዓዛቸውን እያወረዱ ማረፍ ጀመሩ። ዛሬ አዳራችን [illegible] ተራራ እንዲሁ ሲያዩት በእጅ የሚነኩት ቢመስልም [illegible] ትልቁ የአደባ ሸለቆ ተዘርግቷል።

[illegible] አካባቢውን እያየሁ ሳደንቅ በሃሳብ እና በትዝታ ወደ [illegible] ተመለስኩ። አሁን ከቆምኩበት ቦታ ትይዩ [illegible] አለባት። አዎ ትታየኛለች። ዛሬም እዛው ቦታ ላይ ነች፡ [illegible] አለ። ከዛሬ ስድስት ዓመት በፊት በዚሁ [illegible] አዎ ያቺ የቀጥቃጭ ጎጆ ዛሬም አለች።

[illegible] በትዝታ ባህር ውስጥ እንደተዘፈቅሁ ተደጋግመው [illegible] ከመንደሯ መሀል ጥቂት ወታደሮች ወደ ጦር [illegible] መንደርተኞቹ ወታደሮቹን እያባረሩ ይተኩሳሉ። ራስ ካሣ [illegible] የጦር ሜዳ መነጽራቸውን ተቀብለው ተኩስ ወደ [illegible] ቀኛዝማች አበበን አስጠሩ።

ቀኛዝማች አበበ [illegible] አፋቸውን ሸፍነው ወደ ራስ ካሣ ጎንበስ [illegible] ራስ ካሣ [illegible] ትዕዛዝ ተቀብለው ወደ ወታደሮቻቸው ከመመለሳቸው [illegible] ወታደሮች [illegible] እያቀባበሉ ቁልቁል ሮጡ።

ከሁለት ሰዓት በኋላ ቀኛዝማች አበበ ጥቂት የፊጥኝ የታሰሩ ወታደሮችና የቀበሌዋን ነዋሪዎች በሙሉ አስገዱ መጥተው ከራስ ካሣ ዙፋን ፊት ቆሙ። ችሎቱ [illegible] ጊዜ አልፈጀም። ቀበሌዋን ለመዝረፍ የወረዱት ወታደሮች የሰሩትንና [illegible] ነገር በሙሉ [illegible]

እንዲገረፍ፣ በወታደሮቹ ላይ የተኮሱት የቀበሌዋ ነዋሪዎች ደግሞ አስራ አምስት አስራ ምስት ጊዜ እንዲገረፉ ተፈረደባቸው።

መንደርተኛ ተኳሾቹን ለይቶ ማወቅ ከባድ አልነበረም። ቀኛዝማች አበበ የመንደርተኞቹን ጠመንጃ ከእያንዳንዳቸው እጅ እየተቀበለ አፈሙዙን ያሸታል። በባሩድ ሽታ ተኳሾቹን ያለ ብዙ ችግር ለይቶ ካበቃ በኋላ ለረጅሙና ጠብደሉ የራስ ካሣ ባለ ጉማሬ አሽከር አሳልፎ ሰጣቸው።

ወታደሮች ተቀጪውን ሰው ከፊት ሁለቱንም እጆቹን በረጅም ጠፍር ጥብቅ አድርገው አሰሩት። ከኋላም ተቀጪው ሁለት እግሩን ስለታሰረና ወታደሮች እንዳይንቀሳቀስ ወጥረው ስለያዙት፣ ተቀጪው በሆዱ እንደተኛ የተፈረደበትን ቅጣት እንዳንበሳ እያጓራና ከመሬት ወደሰማይ እየነጠረ ተቀበላት። ቀኛዝማች አበበ ከቆሙበት ቦታ ንቅንቅ ሳይሉ እየተወናጨፈ የተቀጪውን ጀርባ የሚገሸልጠውን የዚያን ግዙፍ ሰው የጉማሬ አለንጋ ምት ይቆጥራሉ።

ቅጣቱን የተቀበለውን ሰው ቤተሰቡ ወይም ጓደኞቹ ወስደው በደም የተጨማለቀውን ጀርባውን ጠርገው ያስታምሙታል። ቤተሰብም ሆነ ጓደኛ የሌለው ተቀጪ በተገረፈበት ቦታ እንደተኛ ይቀራል። ማንም ምንም አያደርግለትም። እንዲህ ተገራፊዎችን እዝን ብዬ ሳይ፣ "በጣም ጥቂቶች ናቸው 50 አለንጋ የሚችሉት" አሉኝ አቶ ተሰማ።



16

የብረት ዝናብ

ህዳር 7 ቀን ረፋዱ ላይ ዋናው የራስ ካሣ ጦር አምባላጌ ደረሰ። ሰራዊቱ 3,411 ሜትር ከፍታ ያለውን የአምባላጌን ተራራ እንደቀለበት እየዞረ፣ ከናዳው እየሸሸ፣ እንደምላጭ የሰላው ጥቁር ድንጋይ ባዶ እግሩን እየቆረጠው በሚያገኘው ዛፍ፣ ድንጋይና ቋጥኝ ስር ሁሉ ማረፍ ጀምሯል።

ወታደሩ በመንገድ ብዛት፣ በእንቅፋትና በሾሬ ድንጋይ የተጎዳ እግሮቹን ከነጠላው እራፊ ጨርቅ እየቆረጠ በእሳት ይተኩሳል። በጣም የደከመውም ድንገት ባረፈበት ቦታ ያገኘውን ነገር ደገፍ ብሎ ያርፋል። ከላይ ከተራራው ጫፍ አካባቢ በርከት ያሉ ሹሞች፣ ባብዛኛው የታጠቁና ጋሻቸውን በጎሽ ቆዳ ያሳመሩ ጦረኞች፣ አንድ ጠንከርና ደንደን ያለ ሰውነት ያለውን ሹማቸውን አጅበው ወደታች ይንደረደራሉ።

እኒህ ቆፍጣናና ልበሙሉ ሰው የላስታው ገገ ደጃዝማች ወርቅነህ ነበሩ። ደጃዝማች ወርቅነህ ራስ ካሣ ካረፉባት ዋርካ ስር እንደደረሱ ተንበርክከው የራስን የጃኖ ጫፍ ከሳሙ በኋላ ተነስተው አንድ ወር ሙሉ ወታደሮቻቸው የገነቡትን ከጠላት መከላከያ ምሽግ በታላቅ ኩራት አሳዩ።

እም አንድ ወር ሙሉ የገበሬው ወታደር በላስታው ገገ በደጃዝማች ወርቅነህ

ምሬት ከድንጋይና ከቋጥኝ በርከት ያሉ ካቦች ሰርተዋል። ግን ጥቅም ይኖረው ይሆን? እግዚአብሔር ያውቃል ልብል እንጂ እንደ ሃበሾቹ። ደጃዝማች ወርቅነህ በቀኝ ትከሻቸው ጠብመንጃቸውን አንግተው ለራስ ካሣ ስለጦራቸው ሲያወሩ ላያቸው ሰው የጦር ሰውነታቸውን የሚክድ ማንም ሰው አልነበረም። ብቻ ከወዲያ ወዲህ እየተጀነኑ ስለ ጦራቸው ብዙ ብዙ አወሩን።

በአምባላጌ ተራራ ወገብ ላይ ጉብ ካለችው ዋርካ ስር ራስ ካሣና በሰሜን የኢትዮጵያ ክፍል አሉ የሚባሉ ከፍተኛ ሹሞች ዙሪያውን ገጥመው ተቀምጠዋል። በዚቺው ዋርካ ስር ከዛሬ አርባ ዓመት በፊት ታላቁ የጦር ሰው እምዬ ምኒልክም ተቀምጠው ከሹማምንቱ ጋር እንዴት ወደ አድዋ መዝለቅ እንዳለባቸው ለድል ያበቃቸውን የጦር እቅድ መክረውና ነድፈው አውጥተዋል።

በዚችው ዋርካ ስር ከዘመናት በፊት በርካታ ገናና የኢትዮጵያ የጦር መሪዎች አርፈው፣ የጦርነት ስልታቸውን ነድፈው፣ ከውጪም ይሁን ከውስጥ ጠላት ጋር ተፋግተው አልፈዋል። ይኸው እነሆ ዛሬም የራስ ካሣ ጦር በዚችው ዋርካ ስር አርፎ የጦርነት ስልት ይነድፋል። የመከላከል ስልት። አንድ ከዛሬ አርባ ዓመት በፊት በዚችው ዋርካ ስር ያለፉ አዛውንት ዛሬም ይቺን ዋርካ ሲያዩ በትዝታ አርባ ዓመት ተመልሰው ሲተክዙ አየኋቸውና ሁኔታቸው አሳዝኖኝ እኔም ስተክዝ፣ "አየሀ ልበርግማ፣ ከዛሬ አርባ ዓመት በፊት ከእምዬ ምኒልክ ጋር" ብለው ረጅሙን ታሪካቸውን አጫወቱኝ።

እኒህ አዛውንት ከዛሬ አርባ ዓመት በፊት የእምዬ ሚኒልክ የጦር መሪ በነበሩት ራስ መኮንን (የንጉሠ ነገሥቱ አባት) ስር በአምባላጌ ውጊያ ተሳትፈው ነበር። አምባላጌ ከዛሬ አርባ ዓመት በፊት ይዟት የነበረውን የጣሊያን ሻለቃ ቶሰሊን ራስ መኮንን እንዲህ ብለውት ነበር።

"ውድ ወዳጄ ሻለቃ ቶሰሊ፣ ጀግንነትህንና ቀራጥነትህን አውቃለሁና አከብርሃለሁ። አደንቅሃለሁ። ይሁን እንጂ በዚህ ጦርነት ትሸነፋለህ። ስለዚህ አምባላጌን ለቅቀህ ወደመቀሌ ሽሽ። እንዲህ በሰላም ያለ ጦርነት አምባላጌን ለቅቀህ ከወጣህ ጦርህ እንደታጠቀ ወደ መቀሌ ሸሽቶ ያለችግር እንደሚገባ ቃሌን እሰጥሃለሁ። ወዳጄ ቶሰሊ ያለህን ጦር አውቃለሁ። እኔ አስር እጥፍ ጦር አለኝ። እና ኋላ በወታደሮቼ ብትገደል ልቤ ያዝናልና እባክህ አምባላጌን ለቅቀህ ውጣ።" ብለው መልእክት ቢልኩበትም፣ ሻለቃ ቶሰሊ "ከአለቆቼ ተጨማሪ ትዕዛዝ ካላገኘሁ አምባላጌን መልቀቅ አልችልም" ብሎ የራስ መኮንንን ልመና ባለመቀበሉ፣ ራስ መኮንን ለሁለተኛ ጊዜ ለሻለቃ ቶሰሊ መልክት ሲልኩ እንዲህ ብለው ነበር።

"ነገ ማለዳ ጦሬ ይዘምትብሀል። አሁንም ደግሜ ላሳውቅህ፤ ጦርህን ይዘህ ሂድ። ልቤን አታሳዝነው።" ሻለቃ ቶሰሊ በድጋሚ የራስ መኮንንን ደግነት ባለመቀበሉ የራስ መኮንን ጦር የሻለቃ ቶሰሊን ጦር ለወሬ ነጋሪ ሳያስቀር አጨደው።

በኋላ ራስ መኰንን የሻለቃ ቶሰሲን ሬሳ አስፈልገው ወታደሮቻቸውን ለአንድ ጀግና በሚገባው ክብር እንዲቀብሩት አዘው አይናቸው ያዘለውን እንባ ለመግታት ሲጣጣሩ ታይተዋል። እንግዲህ እንዲህ አይነት የጦር መሪ ያፈራችን ሀገር ነው ጣልያኖች ዛሬም ያልሰለጠነች አረመኔ ሀገር አድርገው በመላው አለም ጉራቸውን የሚነፉት።

ጦራችን የአምባላጌን ተራራ ታቅፎና ተንተርሶ መኖር ጀምሯል። አንዳንድ እንደነገሩ በችኮላ በየጥሻው ስር ከተወሸቁ ጎጆ ነገሮችም ይጫጭሳል። እኔም ረፋዱ ላይ ከሰፈር ወጣ ብዬ እንዲሁ ስዋልል የራስ መኰንን ጦር የሻለቃ ቶሱሲን ጦር የዛሬ አርባ ዓመት ካጨደበት ስፍራ ደረስኩ። አዎ አሁንም በርከት ያሉ ቀለሀዎች እዚህም እዚያም ወዳድቀው ይታያሉ። አንድ ሁለቱን አነሳሁና አገላብጬ አይቼ አፈሩን አራገፍኩና ወደኪሴ ከትቼ የሻለቃ ቶሱሲን የቀብር ቦታ ለመፈለግ አሰቢ መራመድ ስጀምር፣ እታች ሰፈራችን የሆነ ትርምስ አየሁና በፍጥነት እየተራመድኩ ወደ ሰፈር ተመለስኩ።

ሰፈር ስደርስ የደጃዝማች ወርቅነህ ወታደሮች እየተፋጠኑ ባገኙት ከፍ ባለ ድንጋይ ስር ሁሉ መሸጉ። ግራ ገብቶኝ ወደ ድንኳኔ ስገባ አቶ ተሰማ የመቀሌው ስልከኛ ደውሎ ስድስት የጣልያን አውሮፕላኖች እንዳየና ሁለቱ አሁን መቀሌን እየደበደቡ መሆኑንና አራቱ ደግሞ ወደኛ በመንገድ ላይ እንደሆኑ ነገሩኝ። እና እኔም ካዘጋጁት አለት ስር ገብቼ ለግማሽ ሰዓት ያህል አንጋጥጬ ሰማዩን ብቃኝም የጣልያን አውሮፕላኖች ብቅ ሳይሉ ቀሩ።

ከምሽጌ ስወጣ ራቅ ካለ ቦታ የቦምብ ፍንዳታ ይሰማል። እንግዲህ ጣልያኖች በመንገዳቸው ላይ የተቀረጠ የኢትዮጵያ ጦር አግኝተው እየደበደቡ ይሆናል። የአውሮፕላኖቹ መቅረት ሰፈራችንን እንደገና ሞቅ እንድትል አደረጋት።

የአውሮፕላኖቹ መቅረት ሰፈራችንን ስላረጋጋት ራስ ካሣም ከሹማምንቱ ጋር የጀመሩትን ምክር ቀጠሉ። እኔም እንዲሁ ከድንኳኔ ፊት ካሉ ወታደሮች ጋር ስጫወት ደጃዝማች ወርቅነህ ወደ ድንኳናቸው ስለጋበዙኝ፣ ደጃዝማች ወርቅነህን ተከትዬ ከፍ ብሎ ካንድ ድብቅ ቦታ ከቆመው ድንኳናቸው ገና ከመግባቴ አሽከራቸው የተለያዩ ምግቦች አቀረበልንና እጃችንን ታጥበን መጎራረስ ጀመርን። አሽከራቸው ለኔና ለደጃዝማች በብርሌ ጠጅ ቀዳልን። ሌሎች በሌላ አልባሌ እቃ ተቀድቶላቸው ጠጃችንን እየጠጣን ብዙ ብዙ ተጫወትን።

የደጃዝማች ወርቅነህ ጠጅ ከፍተኛ ዝናን በማትረፉ ለጠጃቸው ብቻ ሲሉ ብዙ ከፍተኛ ሹማምንቶች በሰበብ አስባቡ ድንኳናቸውን ይጎበኙ ነበር። በጣም ከመሸ በኋላ እየተደናበርኩ ወደ ሰፈር ተመለስኩ። ዛሬ ከመቸውም ግዜ በላይ በጣም ቀዝቃዛ ነፋስ ይነፍሳል። በርካታው ዘብ፣ የራስ ካሣ ሳይቀሩ፣ እዚህም እዚያም እሳት እያነደዱ ይሞቃሉ። ወደ ድንኳኔ ስቃረብ ከኔ ድንኳን ብዙም ሳይርቅ አንድ ከፍ ያለ አዲስ

ድንኳን ቆሟል። ዘቦቹም እስከዛሬ ያላየኋቸው ናቸው። እሳት አያነዱም፣ ዘብ ከቆሙበት ቦታ ንቅንቅም አይሉም። ሰላምታ ባቀርብላቸውም ምንም መልስ ሳላገኝ ወደ ድንኳኔ ገባሁ። በጣም ይበርዳል። ቢሆንም ገና ጋደም ከማለቴ እንቅልፍ ይዞኝ ጥርግ አለ።

ማልጄ ተነሳሁና ለሽንት ወጣ ብዬ ስመለስ ትናንት ከጎኔ ድንኳን ጥሎ የደረሰው የራስ ካሣ ሁለተኛ ልጅ ደጃዝማች አበራ መሆኑን ሰማሁ። የደጃዝማች አበራ ዘቦች በሙሉ ወጣቶች ናቸው። ከሁሉም በላይ ከትናንት ማታ ጀምሮ እስካሁን እንደታዘብኩት እነዚህ ከሌላው የኢትዮጵያ ሰራዊት የሚለዩበት ነገር ቢኖር ስነ ስርአታቸው ነበር።

አዎ ደጃዝማች አበራ ከ20,000 በላይ የሚሆነውን ጦሩን ይዞ ከሰላሌ ፊቼ ተነስቶ ትናንት ማታ አምባላጌ መድረሱ ነበር። አብዛኛው የራስ ካሣም ጦር የመጣው ከሰላሌ ነው። እነዚህ የራስ ካሣ ወታደሮች ከሰባት ወር በላይ በመንገድ ላይ ነበሩ። በዚህ ጊዜ ውስጥ አንዳቸውም ከሰላሌ ስለቤተሰቦቻቸው የደረሳቸው ምንም ዜና የለም። እናም በደጃዝማች አበራ ጦር መሀል እየተዘዋወሩ ስለ ቤተሰቦቻቸው፣ ስለጓደኞቻቸው ደህንነት ይጠይቃሉ። አንዳንድ የዱሮ ጓደኞቻቸውንም ተገናኝተዋል።

ደጃዝማች አበራ ገና በወጉ እንኳ ጺም ያላበቀለ ለግላጋ ወጣት ነው። ደጃዝማች አበራ ግማሽ ያህል ጊዜውን በትምህርት በአውሮፓ ትልልቅ ከተሞች ያሳለፈ በመሆኑ አሳምሮ እንግሊዘኛም፣ ፈረንሳይኛም ይናገራል። እንዳየሁት ብዙ መናገር የማይወድ ዝምተኛ ሰው ነው።

ቡና በጠዋት ጠጥቼ ሲጋራዎችንም አጫጭሼ የጦር ልብሴን ለበስኩና ወደ ራስ ካሣ እንግዳ መቀበያ ድንኳን አመራሁ። ከአንድ ሰዓት በኋላ ደጃዝማች አበራ ጦሩን በአባቱ ዙፋን ፊት ይዞ እንደሚቀርብ ተነገረንና ወደተዘጋጀው የሰልፉ ትእይንት ወደሚታይበት ቦታ አመራን።

ከፊቼ ከተማ የተነሳው የደጃዝማች አበራ ጦር በራስ ካሣ ዙፋን ፊት ለሁለት ሰዓት ያህል አለፈ። የደጃዝማች አበራ ጦር በአብዛኛው ፈረሰኛ ሲሆን የጦሩ ፈረሶችም በተለያዩ ደማቅ ቀለሞች ያጌጡና የተሸለሙ ነበሩ። ፈረሰኞችም ከለበሱት የጦር ልብስ በተጨማሪ የዝንጀሮ ጎፈሬ የደፉ ስለነበረ ግርማ ሞገስ ጨምሮላቸው ነበር። ይኼው በአመዛኙ በወጣቶች የተገነባው የደጃዝማች አበራ ጦር በአብዛኛው የዘመኑን መሳሪያ የታጠቀ ነበር።

የዚህ ጦር የበላይ መኰንኖች በራስ ካሣ ፊት ቀርበው ለእናት ሀገራቸው ለመሞት መዘጋጀታቸውን ግማሹ በአማርኛ ግማሹ በኦሮምኛ በእምዬ ምኒልክ ስም መሀላ እየገቡ ፎከሩ፣ ሸለሉ። በመጨረሻ በተኩስ ሰፈራችንን አደመቋት። ከዚህ ሁለት ሰዓት ከፈጀ ትእይንት በኋላ ወጣቱ ከናቤል በራስ ካሣ ፊት ቀርቦ፣ “ሞሶሎኒ ሁለት ወንድ ልጆቹን ለጦርነቱ ቢሰጥ የኛ ራስ ሶስት ልጆቹን ይዞ ቀርቧል፤ ደጃዝማች

ወንድወሰን፣ ደጃዝማች አበራንና ደጃዝማች አስፋ ወሰንን ብሎ በታላቅ ኩራ ተናገረ።

ከሩቤል ያልተረዳው ነገር ቢኖር ሞሶሎኒ በዚህ ሰዓት በሮማ በሞቀ ቤተ መንግስቱ መቀመጡንና ራስ ካሣ ግን ልክ እንደመጨረሻው ወታደራቸው ሁሉ መከራና ፍዳቸውን እያዩ እዚህ መድረሳቸውን ነበር።

እነሆ አምስተኛ ቀናችን ነው፣ የአምባላጌን ደቡባዊ ክፍል ተንተርሰን ከሰፈርን። የጣልያን አውሮፕላኖች ሰሞኑን ብቅም ስላላሉና ሰፈርም ለመቃኘት ሀሳብ 13 ቀን ረፋዱ ላይ ከሰፈር ወጣሁ።

ብዙ ሲጠበቅ የነበረው ነጋድራስ ወዳጆና ታማኝ ጓዳቸው ሻለቃ ካሣ ጋር ሰፈራችን ደረሱ። ሁለቱ የጦር መሪዎች በመቶዎች ከሚቆጠሩት ወታደሮች ጋ መቀሌን ለቀው ከሽፍቶች ጋር በታላቅ ተጋድሎ እየተዋጉ እዚህ መድረሳቸው ነው።

ደጃዝማች አበራም ጦሩን እንድጎበኝለት ጋብዞኝ ስለነበር እግረ መንገዴን ወደዚያው ከአቶ ተሰማና ከሻለቃ ካሣ ጋር ጥቂት ወታደሮች ጨምረን እመራት የደጃዝማች አበራ ጦር የሰፈረው እጅግ አስቸጋሪውን ምዕራባዊውን የአምባላጌን ተራራ ተንተርሶ ስለነበር ወደዚያው ተራራውን እየባጠጥን ወደ ጦሩ ሰፈር ልንደርስ ስንቃረብ እታች ጦራችን ከሰፈረበት ቦታ ጩኸትና ሁካታ፣ ግርግር በዛ። ብዙም ሳንቆይ ወዲያው የነዚያን መከረኛ የጣልያን አውሮፕላኖች ድምጽ ሰማሁ። ለጊዜው ግራ ገብቶኝ ሰማዩን ሳስስ አንድ የደጃዝማች አበራ ጦር ሻለቃ በጁ ወደታች ወደሰፈራችን ዝቅ ብለው የሚበሩ አራት አውሮፕላኖች አሳየኝ።

እንደሁልጊዜው ለስለላ የመጡ ስለመሰለኝ ችላ ብዬ ጉዞ እንደጀመርኩ በተደጋጋሚ ዝቅ ብለው በሚበሩ አውሮፕላኖች ላይ መትረየሶች በመንጣጣታቸው ከነበሩት በርከት ካሉ አውሮፕላኖች ሁለቱ ተመልሰው የካሣን ጦር የተሸከመተን የቦንብ ናዳ ያወርዱበት ጀመር።

ከታቀፍኩት ተራራ ትይዩ ከፍ ብለው በንቀት እንደነገሩ የሚጥሏቸው በንዝት እታች ሰፈር አቧራውን ያጨሱት ነበር። ምንም እንኳ ሰፈር የአውሮፕላን መቃወሚያ ቢኖርም አውሮፕላኖቹ በቂ ከፍታ ስለነበራቸው ያለአንዳች ፍርሀት እየዞሩ ሽክማቸውን አወረዱት።

ከዚች ቀን ጀምሮ እስከጦርነቱ ፍጻሜ ድረስ የጣልያን አውሮፕላኖች የራስ ካሣን ጦር እየተከታተሉ በቀን እስከ አስራ ሁለት ሰዓት በላይ ይደበድቡ ነበር፡ ከተከለልኩበት ቋጥኝ ስር ሆኜ ሰፈራችን ሲደበደብ በአቅመቢስነታችን ከፉኛ ተናደደ አንጀቴ እያረረ፣ ሰፈራችን በቦንብ አቧራ ጉም እስክትሸፈን ድረስ በፀጥታ ተመለከትኩ። ከሰፈር ብዙ ርቀን ስለነበር ወደ ደጃዝማች አበራ ሰፈር ቀጠልን። በዛ ላይ እያለን ከታች ከሰፈር ብዙ የቁስለኞች ዋይታ ይሰማ ነበር።

አውሮፕላኖቹ ያደረጉትን አድርገው ወደ ሰፈራቸው እየተመለሱ ሳለ አንዷ የተረገመች ቆርቆሮ ወደኋላ ተመልሳ ወደኛ መብረር ጀመረች። አብረውኝ ያሉትን ወታደሮቼን እንዳይተኩሱ ደጋግሜ ብጮህም ሰሚ አልነበረኝምና አውሮፕላኗ እኛንም መደብደብ ጀመረች። አንድ ከፍ ያለች ቦምብ እኔ ከተጠጋኋት ቋጥኝ ኀምሳ ሜትር ርቃ ከፍ ያለ አቧራ አስነሳች። የእድልና የሰከንዶች ጉዳይ ነው። አብራሪው አውቶማቲኳን ቦምብ ማውረጃ ቁልፍ የሚጫንበት ቅጽበት ሁሉ ከፍተኛ ሚና ይጫወት ነበር። ያቺን ኀምሳ ሜትር ርቃ የወደቀች ቦምብ ከሁለትና ሶስት ሰከንድ በፊት ቢጥላት ኖሮ አናቴ ላይ በወደቀች ነበር።

አውሮፕላኗ የቀራትን ሽክም አራግፋብን ከሄደችና ያስነሳችው አቧራ ከለቀቀ በኋላ ወደፊት ስል አምስት የራስ ካሣ ወታደሮች ጠሩኝና ወደታች ተመለስኩ። ብዙ ወታደሮች ከበው እንደጉድ አንድ ያልፈነዳች የጣልያን ቦምብን ይመለከታሉ። ጣልያኖች ኢትዮጵያን ለመውረር ሲዘጋጁ በገፍ ያስገቡትን ቦምብ በቀላሉና በፍጥነት ወደ መሀል ሀገር ማስገባት ባለመቻላቸው ወደብ ላይ ለፀሐይና ለሀሩር ተጋልጠው ለወራት በመቆየታቸው፣ በኢትዮጵያው ወታደር ላይ ከሚያዘንቡት የቦምብ ዝናብ ግማሹ ያህል ብቻ ነበር የሚፈነዳው። ምንም እንኳ ራስ ካሣ ያልፈነዱ ቦምቦችን እንዳይነኩ አዋጅ ቢያውጁም የሚሰማ ስላልነበረ እነዚህ ያልፈነዱ ቦምቦች ብዙ ሰው ጨርሰዋል።

በጉዟችን ቀጥለን ከደጃዝማች አበራ የጦር ሰፈር ደረስን። እስካሁን ካየኋቸው የጦር መሪዎች ደጃዝማች አበራ ለየት ያለ አቀራረብ አለው። ከሀያ ሺህ በላይ የሆነው ጦሩ ባብዛኛው በወጣቶች የተገነባና ደህና ስነምግባር ያለው ይመስላል። የመሪውን ትዕዛዞች ያላንዳች ማንገራገር ይፈጽማል።

ደጃዝማች ገና ከሩቅ ሲያየኝ ከድንኳኑ ወጥቶ እንደጥንት ጓደኛ አቅፎ ተቀበለኝ። ወደ እንግዳ መቀበያው ድንኳን ስናመራ የሆነ ወጣት ሹም ስላቆመን ከወጣቱ ሹም ድንኳን ገባን። ወጣቱ ግራዝማች ቤቱ ያፈራውን ጥሩ ነገር ሁሉ አቀረበልን። በኋላ ደጃዝማቹ አሽከሮቹን አዝዞ ከራሱ ድንኳን ብዙ ምግብና ጠጅ ስለመጣ ማምሻውን ከዚያ ወጣት ግራዝማች ትንሽዬ ድንኳን ውስጥ ስንጫወት አመሸን። በጫወታችን ብዙ ብዙ ስለፓሪስ ቡና ቤቶችና ስለ ሴቶቻቸው ስንጫወት ደጃዝማች አበራ በትዝታ ብዙ ርቆ እንደሚሄድ ያስታውቅበት ነበር።

አዎ ከብዙ ጊዜ በኋላ ይኼው እነሆ ትንሽ ስለ አውሮፓ በአውሮፓ ከኖሩ ሁለት ሰዎች ጋር (ደጃዝማች አበራ እና ሻለቃ ካሣ) ስጫወት ትንሽ ቀለል ብሎኝ ደጃዝማች አበራም ሌሎች ጠባቂ ወታደሮች ጨምሮልኝ ወደ ሰፈሬ ሲልከኝ፣ በጦር ሜዳ እንደ አለቃ እንደ አዛዥ በምግብ ሰዓት እንደጓደኛ የሆነ ወጣት መሪ መሆኑ ታወቀኝና እያደነቅኩት ቁልቁል ወደሰፈሬ ወረድኩ።

ሰፈር ስደርስ የመጀመሪያዎቹን የጦርነት ሰለባዎች እዚህም እዚያም ይቆጥር ነበር:: ቁስለኞችም ህመማቸውን ዋጥ አድርገው በየድንኳኑ ስር አረፍ ብለዋል:: በጣም ለተጎዱት ራስ ካሣ አንድ ሌላ ድንኳን አስጥለው በዚያው መርፌ ወጊ ዶክተራችን ህክምና እየተደረገላቸው ነበር::

ራስ ካሣ በዚሁ ምሽት በድጋሚ ያልፈነዱ ቦንቦችን ወታደሮች እንዳያነካኩ አዋጅ አስነገሩ:: በሁለተኛው ቀን ማለዳ ልጅ ከሩቤል ወደ ድንኳናችን ጎራ ብሎ ትናንት ሁለት ጓደኞቹ አንዲት ያልፈነዳች ቦንብ አግኝተው ሲመራመሩ የሆነውን ቃል በቃል አጫወተን::

"ወይ ጉድ! እንዳው ማን ይሆን የጣለው? እንዳው ግርም የሚል ብረትኮ ነው" ይላል ከጓደኛሞቹ አንዱ::

"ማን ይጥለዋል ብለህ ነው? የኛ ሰው እንዳልጣለው ግን ጥርጥር የለውም" ይመልሳል ሁለተኛው::

"ግዴለህም ወንድሜ ይኼን ብረት የጣለው ፈረንጅ ነው:: ግን ደግሞ እንደጥ ፈረንጅ በዚህ ሲያልፍ አላየንም:: የካሣም ፈረንጅ ቢሆን ይኼን አይነት ብረት ተሸክሞ ሲዞር አየሁ የሚል የለም" ይላል የመጀመሪያው::

ሁለተኛው ረዘም ላለ ጊዜ ብረቱን አገላብጦ ካየ በኋላ ሳቁን ለቀቀው:: "ምን ሆነሃል ጃል? እንዲያው እንዳበደ ሰው ብቻህን መሳቅህ?" ይጠይቃል የመጀመሪያው:: የሚስቀው ሳቁን እንደምንም አቁሞ፣ "አይ እንዲያው ይቺን ብረት ማን እንደጣላት ስለማውቅ ነገሩ ቢገርመኝ ነው መሳቄ" አለ አሁንም እንደመሳቅ እያለና ለጓደኛው በጣቶቹ ወደ ሰማይ እያሳየ::

"ከነዚያ የተረገሙ የጣልያን አውሮፕላኖች ነው የወደቀው:: የታባታቸውን እንኳን ወደቀባቸው:: መናጢዎች" አለ በድል አድራጊነት፣ ቢያንስ ይቺን ብረት ስለጣሉ እንደተጎዱ በመቁጠር::

"እውነት አለህ ወንድሜ:: ልክ ነህ ከነዚያ ከተረገሙ አውሮፕላኖች ውስጥ ከአንዷ መሆን አለበት የወደቀው:: ልክ ነህ፣ ልክ ነህ ወንድሜ::" አለ ደጋግሞ ሁለተኛው:: ወዲያው መለስ ብሎ፣ "ቦምብም ሊሆን'ኮ ይችላል?" አለ በጥርጣሬ ብረቷን እያያት::

"አንተ ደግሞ ወገኛ ብጤ ነህ መሰል:: አሁን ማ ይሙት ይቺ ቁራጭ ብረት ነች እንደዛ ጮኻ ሀገር ምድሩን የምትደበላልቀው? ጉድኮ ነው" እያለ ለራሱ አጉተመተመ::

"እም ወዳጅ እንዲች አይነት የማትረባ ቁራጭ ብረት ነች ድንገት እየፈነዳች ሰውን ከብቱን አጋሰሱን የምትፈጀው:: እንዲች አይነት ቁራጭ ብረት" አለ ትንሽ ዘጨጨት ብሎ::

"ብትክክል ከአውሮፕላኗ ውስጥ ነው የወደቀው:: እየህ ዞሬ እሄዳለሁ ብላ እንዲያው ዘንበል ስትል ይቺ ብረት ተንሸራትታ ወድቃባቸው ነው" እያለ በእጁ አውሮፕላኗ እንዴት ይቺን ብረት ልትጥላት እንደቻለች ሊያሳየው ሞከረ::

ይኼው ተመራማሪ ወጣት በምርምሩ ቀጥሎ በድል አድራጊነት ብረቷን ሲያስተውል ቆየና ፈገግ እያለ እስካሁን በነጠላው ጫፍ ላይ ቋጥሮ የያዛትን ብቸኛዋን ሃብቱን አንዷን ብር ፈታና ከቁራጯ ብረት ላይ ባለች ቀዳዳ መሳይ ነገር ላይ አስቀመጣት:: ብሯ በቁራጯ ብረት ጎድጓዳ ቦታ ላይ ተስፋፍታ ስትቀመጥ ተመራማሪው አሁንም በድል አድራጊነት ስሜት ፈገግ አለና ጓደኛውን እያየ ሌባ ጣቱን አፉ ላይ አድርጎ ጓደኛው ዝም እንዲል አዘዘው:: ጓደኛውም የዚህ ተመራማሪ የምርምር ውጤት ስለገባው እሱም ፈገግ ብሎ ድምጹን አጠፋ::

ሁለቱ ጓደኞች በቁራጯ ብረት ዙሪያ ተቀምጠው በቁራጯ ብረት ውስጥ ጣልያኖች ስለደበቁት ብር ብዛት ሲመራመሩ ቆዩ:: በመጨረሻ ከቁራጯ ብረት ውስጥ ብሮቹን እንዴት እንደሚያወጡ ብልሃት ሲፈጥሩ፣ ሲያወጡ፣ ሲያወርዱ፣አንዱም ብልሃታቸው ሳይሳካላቸው ቀረና በመጨረሻ ያቺን ቁራጭ ብረት በትልልቅ ድንጋይ ወቅረው ብሮቹን ሊያወጡ ወስነው ብረቷን በትልልቅ ድንጋይ ይወቅሯት ጀመር::

ተመራማሪው ልጅ ለስስተኛ ጊዜ ብረቷን በድንጋይ ሲወቅራት ብረቷ ለስቻት መለሰች ብው ብላ ፈነዳች:: ከነዚህ እድለ ቢሶች ተመራማሪው በቦንቧ ብትንትኑ ወጥቶ ሲሞት ሁለተኛው ጓደኛው በትንሹ ቆስሎ ምርምሩ አለቀ::

እነግዲህ ይኼው ልጅ ከሩቤልም የቆሰለውን ጓደኛውን ጠይቆ ሲመለስ ነው ይኼንን እውነተኛውን ታሪክ ያጫወተን::

17
በእሳት እና በጎራዴ

ሌሊቱን ሙሉ እንቅልፍ ባይኔ ሳይዞር ነው ያደረው። በጦር ሰፈራችን በጠዋት ግርግር ተፈጥሯል። ራስ ካሣ ህዳር 14 ቀን ቀኑን ሙሉ ከሹማምንቱ ጋር ሲመክሩ ውለው የአምባላጌን ተራራ ለቀው መቀሌ አጠገብ ለመስፈር ወስነዋል። መቀሌ ከሁለት ሳምንት በላይ በጣልያኖች እጅ ነች።

ከኛ ድንኳን ሃያ ሜትር እንኳን ሳትርቅ አንድ ቀጭን መንገድ አለች። ይቺ መንገድ የመሀል አገሩንና የሰሜኑን እስከ መቀሌ ብሎም እስከ አስመራ ድረስ የምትወስድ ብቸኛ መንገድ ነች።

ምሽቱን ሙሉ በርካታ ወታደሮች በዚችው መንገድ እየመጡ ከጦራችን ጋር ይቀላቀላሉ። እነዚህ ጦረኞች ራስ ካሣን ብለው ከሰላሌ የመጡ ናቸው። ራስ ካሣ ይኼ እሳቸውን ብሎ ከሰላሌ የመጣው ጦር ከ40 ሺህ ይበልጣል አሉኝ። እንደኔ እንደኔ ግምት ግን ለጦርነት ብቁ የሆነው ወታደር ብዛት ከ20 እስከ 30 ሺ ቢሆን ነው። እንደዚያም ሆኖ ጦሩ በአብዛኛው ሙሉ ትጥቅ የለውም። አንዳንዱ መሳሪያ ያለ

ጥይት ታጥቋል። ሌላው ሙሉ ዝናር ጥይት ታጥቆ መተኮሻው ጠብመንጃ የለውም። ሁለቱንም የታጠቀው ደሞ ከ20 ወይም ከ30 ጥይቶች በላይ የለውም።

ይኼ አዲሱ የሰላሌ ጦር በጨለማ የጦር ሰፈራችንን አጥለቀለቃት። ጨለማው ከአንድ ሜትር በላይ አያሳይም። እንዲህም ሆኖ አንዳንዶቹ የአዲሱ የሰላሌ ጦር አባሎች በጨለማው በራስ ካሣ ጦር መሀል እየተዘዋወሩ ዘመዶቻቸውን ጓደኞቻቸውን ይፈልጋሉ። እርስ በእርስ በኢትዮጵያውያን መገናኛ ዘዴ ራዲዮ ይጠራራሉ። ማለትም የሚፈለገውን ሰው ስም ከፍ ባለ ድምጽ በመጣራት የሚካሄድ ሲሆን በሺዎች የሚቆጠሩ የስም ጥሪዎች በአንድ ላይ ሲካሄዱ አካባቢው ወደ አንድ ትልቅ የገበያ ትርምስ ይለወጣል። እንደዚህም ሆኖ እያንዳንዱ ፈላጊ የተፈላጊውን ስም ጮክ ብሎ ሲጣራ እያንዳንዱ ወታደር ጥሪው ለሱ ይሁን ወይም ለሌላ ሰው ጠንቅቆ ያውቃል።

አቶ ተሰፋዬ...! አቶ ፈይሳ...! አቶ ኢብሳ..!. አቶ ተረፋ...! ምንጊዜም ከተፈላጊውና ከተጠሪው ሰውዬ ስም በፊት የክብር መጠሪያው "አቶ" መቅረት የለበትም። አቶ ቢቂላ..!. እርስ በርስ የማይተዋወቁትም ሰላምታ ይለዋወጣሉ። በታላቅ እና ከፍ ባለ ድምጽ "ወደ አስመራ!" ሲል ሌሎች በርካታ ድምጾች ተቀብለው "ወደ አስመራ!" ሲሉ የገደል ማሚቱዎች ተቀብለው ሩቅ ቦታ ድረስ "ወደ አስመራ!" የሚለው የነዚህ የገበሬ ወታደሮች መፈክር ይሰማል።

ማልደ ተነሳሁ። በጣም ይበርዳል። ምስኪን ሃበሾች! ድንኳን ቀርቶ ብርድ ልብስም የላቸውም። እንዴት ይሆን ይኼን የሚያንቀጠቅጥ ብርድ የሚችሉት? ከጠዋት ጀምሮ ከራስ ካሣ ድንኳን ጎን ሁሌም በምትቆመው የድንኳን ቤተ ክርስቲያን ዙሪያ ትላልቆቹ ሹሞች በፈረስ እየመጡ ድንኳኗ አጠገብ ሲደርሱ፣ ከፈረሳቸው ላይ ይወርዱና አሽከሮቻቸው የሚያቀብሏቸውን በግእዝ የተጻፈ የጸሎት መጽሐፍ ተቀብለው ከድንኳኗ ደጅ ቆመው ይጸልያሉ። እነዚህን ክርስቲያኖች ነበር የፋሽስቱ ፕሮፓጋንዳ ያልሰለጠኑ አውሬዎች የሚላቸው።

አቶ ተሰማን እየጠበቅን ነው። ከፊታችን አንድ በጣም ጠባብ የስርጥ መንገድ ትጠብቀናለች። እናም ያቺ መንገድ ትንሽ ለቀቅ እስክትል ድረስ መጠበቁ አይከፋም በማለት ነበር በትግስት አቶ ተሰማንና ጠባቂ ወታደሮቻችንን የምንጠብቀው።

ዛሬ እንዲህ የካሣ ጦር በዚች ጠባብ ሸለቆ ውስጥ ገብቶ ሲርመሰመስ እነዚያ ርኩሶች ቢያገኙት ኖሮ ክፉኛ በጎዱት ነበር።እድለኞች ነን ዛሬ ብቅም አላሉም። እኩለ ቀን ሆኗል። ጦራችን የመጨረሻዋን ድንኳን ነቅሎ ከሄደ ቆይቷል። እና ሰፈራችን ጭር ብላለች። በጦር ሰፈር ብቻችንን ቀርተናል። እንዲህ ብቻችንን ተቀምጠን አቶ ተሰማን ስንጠብቅ አንድ ወጣት ፊታውራሪ ወደኛ በፈረሱ እየጋለበ መጥቶ ከፈረሱ

ላይ ሳይወርድ፣ "ጌቶች እዚህ ምን ትሰራላችሁ?" ለሰና መልሳችንን እንኳን ሳይጠብቅ፣ "ጌቶች በሉ ቶሎ ቶሎ!" እያለ ሲወተውት ወታደሮቹ ፈረሶቻችንን ሳናዛቸው አመጡልንና ከዚህ የራስ ካሣ ወጣት ፊታውራሪ የኋላ ደጀን የፈረሰኛ ጦር መሪ ጋር ተቀላቅለን መጓዝ ጀመርን።

ይኼ የራስ ካሣ የኋላ ደጀን ፈረሰኛ ጦር አዛዥ ወጣት ፊታውራሪ ራስ ካሣ ስለሰጡት ትልቅና አስቸጋሪ ሃላፊነት ያጫውተን ጀመር። እዎ ራስ ካሣ ይኼንን ወጣት ፈረሰኛ ፊታውራሪ ጦራቸውን የኋላ ደጀን ሆኖ ከጠላት እንዲከላከል አዘውት ይኼው ገና ጦር ሜዳ ሳንደርስ ከትግራይ ሽፍቶች ጋር ጦርነት ውስጥ ገብቶ ሌት ተቀን ይዋጋል። በዚህ መልኩ ከዚህ ወጣት ፊታውራሪ ጋር ስንጓዝ ውስን፤ የአምባላጌን ተራራ ወጥተን በስተሰሜን በኩል ቁልቁል መውረድ ጀመርን። ቅድም እንዳልኩት እድለኞች ነን ዛሬ ቀኑን ሙሉ እነዚያ የተረገሙ የጣልያን አውሮፕላኖች ብቅም ሳይሉ ቀሩ። ዛሬ ቢመጡ ኖሮ ክፉኛ ጦራችንን በጎዱት ነበር።

ጀንበር ከጠለቀች የቆየች ቢሆንም አሁንም በጉዞ ላይ ነን። ገና ከራስ ካሣ የጦር ሰፈር አልደረስንምና በጣም ከመጨለሙ በፊት ጦር ሰፈር ለመድረስ እየገሰገስን ነው። ከመንገዳችን በስተምስራቅም በስተምዕራብም በኩል በተደጋጋሚ ተኩስ እንሰማለን። የኋላው እግረኛው ጦራችን ከሽፍቶች ጋር ጦርነት ውስጥ ነው። እኛ በዚህ መልኩ ወደፊት ስንገሰግስ የሆነ አንድ ፈረሰኛ ጦረኛ ወደኛ እየገሰገሰ ነው። ፈረሰኛው ጦር ወደኛ እየቀረበ ሲመጣ የፈረሰኞቹ ለሰቃ ሲሳደብና ሲራገም ከሩቅ ሰማሁት። በድምጹ ማንነቱን ለይቼ አወቅሁት። የራስ ካሣ የክብር ዘበኛ አለቃ ቀኛዝማች አበበ ነው። ራስ ካሣ እኛ ከዋናው ጦር ጋር አብረን እንዳልተጓዝን ሲረዱ ቀኛዝማች አበበን እኛን የገባበት ገብቶ ወደ ጦር ሰፈር እንዲያመጣን አዘውልከውታል።

አሁን ጨለማው እየጠነከረ መጣ። ከሁለት ሜትር በላይ ወደፊት ማየት አይቻልም። በእግሬ ብሄድ ኖሮ ሁለት እርምጃ እንኳን ወደፊት ሳልሄድ ገደል እገባ ነበር። ብቻ ብልጧ በቅሎ የቀኛዝማች አበበን በቅሎ ኮቴ ተከትላ ያለ አንዳች ችግር በጥንቃቄ እየወሰደችኝ ነው። ቀኛዝማች አበበ መንገዷን በትክክል ያውቃታል። ሃበሻ አንዴ የሄደባትን መንገድ ምንጊዜም ቢሆን አይረሳትም።

ከፊት ለፊታችን ትልቅ እሳት ተነስቶ በመንገዱ ያገኘውን ሁሉ በእሳት ላንቃው ይውጠዋል። "ሽፍታ! የት አባቱ!" ቀኛዝማች አበበ ያማርራል፤ ይራገማል፤ ይሳደባል። አሁን ገና በሰሜን ኢትዮጵያ ስላለው እውነታ መገንዘብና መረዳት ጀመርኩ። የምስራቅ ትግራይ ሰዎች ብዙዎቹ በገዛ ፈቃዳቸው ከራስ ካሣ ጦር ጋር ተቀላቅለዋል። የቀሩት ከቀበሌያቸው ሳይወጡ ወይ ቀማኛ ሽፍታ ሆኑ አሊያም

ሰበቃው ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ገብረው የዘገየውንና በጉዞ ላይ ደክሞ ወደ ኋላ የቀረውን የኢትዮጵያ ጦር ሰራዊት ይዘርፋሉ፤ ይገድላሉ።

አሁን ከትንሿ ጅረት ማዶ መሺክ ዳርቻ ደርሰናል። ከዚች የጅረት ዳርቻ ማዶ ላይ ብዙ ርቆ በየድንኳኖቹ በራፍ ላይ የሚነዱ እሳቶች ያደመቁት ቁጥር ስፍር የሌላቸው ድንኳኖችን ጥሎ የሰፈረው የደጃዝማች ወንድወሰን ጦር ሰፈር ይታያል። ከሁለት ሰዓት አድካሚ ጉዞ በኋላ በታላቅ ደስታ ደጃዝማች ወንድወሰን በጦር ሰፈሩ ተቀበለን።

ደጃዝማች ወንድወሰን የኛን የጦር ቁሳቁስ ጭኖ የሚጓዘው አቶ ተሰማ የት እንዳለ የሚያውቀው ምንም ነገር የለውም። ለምናልባቱ ብሎ አንድ ድንኳን ከሱ ጎን አስጣለልን። ሁለት የራሱ የሆኑ ብርድ ልብሶችም ሰጠን። በደጃዝማች ወንድወሰን ድንኳን ራት ከበላንና ጠጅም እስኪበቃን ከጠጣን በኋላ ትንሽም ብትሆን ድንኳን ውስጥ ገብተን ጤናማ እንቅልፍ ተኛን።

በሁለተኛው ቀን ከአቶ ክሩቤል ጋር ስንገናኝ አቶ ክሩቤል፣ "ዋይ ዋይ፣ ዋይ ዋይ ትናንትና ብዙ ሰው ገደሉ" አለኝ። "ማን ገደላቸው?" ስል ጠየኩት። "ዋይ ዋይ! የትግራይ ሽፍቶች ናቸው" አለኝ አስተማሪው አቶ ክሩቤል። "ለምን የገዛ ወንድሞቻቸውን ይገላሉ? ሊሆን አይችልም!" ስል ሁኔታው ሊገባኝ ባለመቻሉ ከአቶ ክሩቤል ጋር ሙግት ውስጥ ገባሁ። "ከመሀል ሀገር ስድስትና ሰባት ወር ሙሉ ፍዳውን እያየ ሲጓዝ ከርሞ እዚህ የደረሰው ወንድማቸው፣ የነዚህን ምስኪኖች ህይወትና ንብረት ከጠላት ለመከላከል የገዛ ህይወቱን አደጋ ላይ ጥሎ፣ ቤት ንብረቱን በትኖ መከራውን ባየ ለምን ይገድሉታል?" ስል በድጋሚ አቶ ክሩቤልን ጠየኩት።

"አብዛኞዎቹ የትግራይ ሰዎች ይኼንን የተቀደሰ ሃሳብ ይቃወሙታል" አለኝና ቀጥሎ፣ "አንዳንዶቹ ይኼ ከመሀል ሀገር የመጣው የአማራና የኦሮሞ ሰራዊት በትግራይ ከከረመ በትግራይ ያለውን አዝመራ፣ ከብትና ፍየል ይፈጀዋል ብለው ይፈራሉ። ሌሎች ደግሞ ጣልያኖች እስካሁን የወረሩት የትግራይን ግዛት ብቻ ነው፤ እናም ትግራይን ከጠላት ለመከላከል ብቸኛ መብት ያለው የትግራይ ሰው ብቻ ነው ብለው ያምናሉ።

እነዚህ ከጣልያኖች ጋር እኛ ብቻ ነን የመዋጋት መብት ያለን ብለው የሚያምኑት በጦርነቱ፣ ልክ እንደአድዋው ጊዜ ሁሉ እንደሚያሸንፉ እርግጠኞች ናቸው። ታዲያ ከጣልያኖች ጋር ብቻቸውን በጦር ሜዳ ገጥመው ጣልያኖችን ድራሻቸውን አጥፍተው ሲያሸንፏቸው፣ በጦር ሜዳ የሚያገኙትን ጠቅላላውን የጦር ሜዳ ምርኮ ለራሳቸው ሊያስቀሩ ያስቡ ናቸው። ስለዚህ በጦርነቱ የራስ ካሣ ጦር

ከገባበት የጦር ሜዳው ምርኮ ከራስ ካሣ ጦር ተርፎ ለኛ ምንም ነገር አይደርሰንም ብለውም ይፈራሉ" እያለ አቶ ክሩቤል ስለ ሁኔታው አስረዳኝ::

ቀጥሎም ጣልያኖች ይኼንን ችግር ጠንቅቀው ስለሚያውቁ በአማራውና በኦሮሞው ጦር ላይ ትግሬዎች መሳሪያ እንዲያነሱ በሰላዮቻቸው አማካኝነት ሲሰብኩና የነገር እሳት ሲቆሰቁሱ እንደከረሙም ጨምሮ ነገረኝ::

በሚቀጥለው ቀን ማለዳ አንድ ብልጣብልጥ ፊት ያለው መላጣ ሰውዬ በራስ ካሣ ድንኳን ፊት ለፊት በፍርሃት ተውጦ ወዲያ ወዲህ እያለ ሲንቆራጠጥ አየሁት:: በሰውዬው ሁኔታ መገረሜን ያየ አንድ የራስ ካሣ ፀሐፊ ወደኔ ጠጋ ብሎ፣ "ፈረንጅ ጌታ፣ ይህን መላጣ ትግሬ ታውቀዋለህ?"...ሲል ጠየቀኝና መልሴን ሳይጠብቅ፣ "ይኼ መላጣ ትግሬ ከአምባላጌ እስከ መቀሌ ድረስ ያለው ግዛት ዳኛ ነው" አለኝ:: ከዚያም ራስ ካሣ የዚህን መላጣ ዳኛ ልጅ አስረው ነገ ጠዋት በሚውለው ችሎታቸው የሞት ፍርድ እንደሚፈርዱበትም ጨምሮ ነገረኝ::

"ለምን?" ስል ግራ ቢገባኝ ፀሐፊውን ጠየኩት:: ፀሐፊው ምራቁን በጥላቻ ቱፍ ቱፍ ካለ በኋላ፣ "የት አባቱ ይገባዋል" አለኝና በመቀጠል ትናንትና የትግራይ ሽፍቶች በጦራችን ላይ ተኩስ ከፍተው ብዙ ወታደሮቻችንን ከመግደላቸውም በላይ አምስት ሳጥን ሙሉ ጥይት የጫኑ አጋሰሶችንም ዘረፉን:: እና ራስ ካሣ በጣም ተናደው ጦር ልከው ይኼንን መላጣ የትግሬ ዳኛ ከነልጁ አስመጥተው ካሰሯቸው በኋላ፣ ለዚህ መላጣ ዳኛ እስከ ጠዋት ድረስ የተዘረፉትን አምስት ሳጥን ሙሉ ጥይቶች ከነአጋሰሶቹ ካላመጣ ልጁን በሞት እንደሚቀጡት አስጠንቅቀው እስከ ነገ ጠዋት ድረስ የጊዜ ገደብ ሰጥተው ፈቱት አለኝ::

በነጋታው ጠዋት ላይ የዚህን የሚገርም ድራማ ፍጻሜ የማየት እድል ገጥሞኝ ነበር:: ወደ ራስ ካሣ ድንኳን ስሄድ መንገድ ላይ ያንን መላጣ የትግራይ ዳኛ አምስት አጋሰሶች አምስቱንም ሳጥኖች ሙሉ ጥይቶች እንደተጫኑ እየነዳ ሲሄድ አገኘሁት:: በእውነት እጅግ በጣም በጣም ተደነቅኩ::

"እንዴት የተዘረፈውን ጥይት ማግኘት ቻልክ" ስል ከመንገዱ አቆምኩና ጠየኩት:: መላጣው የትግሬ ዳኛ በዚህ የጦር ሰፈር ቢያንስ የሚያናግረው ሰው ፈረንጅም ቢሆን በማግኘቱ በጣም ተደስቶ ብሶቱን ያጫውተኝ ጀመር:: "ዋይ ዋይ ፈረንጅ ጌታ፣ ትናንት ቀኑን ሙሉ በየቀበሌው እየዞርኩ ስጠይቅ ዋልኩ:: ዋይ ዋይ ፈረንጅ ጌታ፣ በዘረፋው የገዛ ዘመዶቼ እጃቸው እንዳለበት አላወቅሁም ነበር:: እና ይኼውልህ ፈረንጅ ጌታ ወደ ዘመዶቼ ሄጄ እስከ ንጋት ድረስ ስሟገት አድሬ ይኼው

የዘረፉትን ጥይት ሰጡኝና የልጆን ነፍስ ሳተርፍ መጣሁ" አለኝ:: ቀጥሎም "ሁሉም ዘመዶቼ በኔ ተናደው ከኔ ጋር አያወሩም" እያለ አጫወተኝ::

ይገባኛል፤ ማንም ሰው ህይወቱን አደጋ ላይ ጥሎ የዘረፈውን ንብረት በገዛ ፈቃዱ ለዘረፈው ሰው አይመልስም:: በተለይ በአሁኑ ጊዜ ጥይት መገበያያ በሆነበት ዘመን 3 ጥይት አንድ ማርትሬዛ ብር እያወጣ የትኛው ዘራፊ ነው አምስት ትልልቅ ሳጥን ሙሉ ጥይቶች በገዛ ፈቃዱ የሚመልሰው?

ማምሻው ላይ እንደ ሁልጊዜው ሁሉ ሲጎበኘን ለመጣው አስተማሪው አቶ ክሩቤል ከመላጣው ዳኛ ጋር ያደረኩትን ንግግር አጫወትኩት:: "ውሸቱን፣ ውሸቱን ነው" እያለ በንዴት ተናገረና ቀጥሎ፣ "ርግጠኛ ነኝ ዋሽቷል:: ራስ ካሣም ውሸታም ዳኛ እንደሆነ ስላወቁ ነው ልጁን ያሰሩበት:: ይኼ መላጣ ዳኛ ራሱ ነው እነዚህን አምስት አጋሰሶች ከነጭነታቸው የዘረፈው:: አርባ መግረፍ ነበር!" እያለ ክሩቤል በጣሙን ተናደደ::

18
ተንቀሳቃሹ ከተማ

ህዳር አጋማሽ ላይ የራስ ካሣ ጦር የመጨረሻውን ድንኳን ከዓቢያቶ ነቅሎ የጣልያንን ወራሪ ጦር ሲገጥም ጉዞ ጀመረ።

የራስ ካሣ ጦር ርዝመቱ ከ15 ኪሎ ሜትር በላይ ነበር። ጦሩ የአምባ ሳጌን ተራራ ለቅቆ ወደ መቀሌ ሲገሰግስ ጣልያኖች በመቀሌና በዙሪያዋ በርከት ያሉ ጥራት ያላቸው ምሽጎች ሰርተው ነበር።

እንደ ኢትዮጵያውያን ሰላዮች (የገበሬ ሰላዮች እንደገበሬ ለብሰው፣ ምንም መሳርያ ሳይዙ በቀላሉ በጣልያን ጦር ስር ወደቀ ፍዳዋን ወደምታየው መቀሌ ይገቡና ይሰልሉ ነበር) አባባል ከመቀሌ ከተማ ውጪም በርከት ያሉ የጦር ካምፖች መመስረታቸውንና አንድ የጣልያን ጦር ወደ ተምቤን ግባት እየዘለቀ መሆኑን አስረድተዋል።

በመጀመሪያው ቀን ጉዟችን እያበቃ ከምትባል አንዲት ትንሽ መንደር ደረስን። ወዲያው ራስ ካሣ ከአንድ የተጠረበ ከሚመስል ገደል ወደ ወገቡ አካባቢ በጣም አስደናቂና ጥሩ ምሽግ ልትሆን

ምትችል የተፈጥሮ ዋሻ ሲያገኙ ነበር በዚች ቀበሌ እንደምንስነባብት የተረዳሁት። ዚያች ዋሻ በየቀኑ እንዳስፈላጊነቱ ከፍተኞቹ የጦር ሹሞች ለምክር ይሰበሰቡ ነበር።

እውነቱን ለመናገር እኔ ወደዚያች ዋሻ መሄድ ይቀፈኝ ነበር። ይታያችሁ ካሁን አሁን አንድ ድንጋይ ተፈንትሎ አለቀልኝ እያልኩ መስጋቱ፣ ከሁሉም በላይ ደግሞ ወደ ዋሻዋ የምትወስደዋ ጠባቧ መንገድ ምንም እንኳ ወታደሮች ጠራርበው ሊያስፋት ቢሞክሩም፤ እንኳን ለሰው ለዝንጀሮም ትኩብዳለች።

ከሁሉም በላይ የገረመኝ ሽማግሌው ራስ ካሣ በቀን አምስቴም ስድስቴም እንደ አስፈላጊነቱ ያቺን የዝንጀሮ መንገድ ያለ ችግር ይወጡ ይወርዱ ነበር። የራስ ካሣ ጦር ካለፈው የቦምብ ውርጂብኝ ተምሮ እዚያም እዚህም ከየአለቶቹና ከየድንጋዮች ስር ሁሉም ለራሱ ጉድጓድ ይቆፋፍር ነበር። የቦምቡ ድብደባ ሲጀምር የሚደበቅበት ጉድጓድ።

ጦራችን የሰፈረባት አዲሷ መንደር፣ ጦሩ እዚህም እዚያም እንደነገሩ የሚቀይላት ጎጆ በሁለት ቀን ውስጥ ወደ ትልቅና ግዙፍ ከተማ ተለወጠች። ተንቀሳቃሽ ዘላን ከተማ። በሶስተኛው ቀን ራስ ካሣ ትልቁ የእንግዳ መቀበያቸውን ድንኳን እንዲጥሉ ትዕዛዝ ሰጡ። ዛሬ ታላቅ እንግዳ ይጠብቃሉ፤ ራስ ሥዩም መንገሻን።

ራስ ሥዩም መንገሻ መተማ ላይ ከደርቡሾች ጋር ሲዋጉ የወደቁት የአፄ ዮሐንስ 4ኛ የልጅ ልጅ ናቸው። የምዕራብ ትግራይ ገዢ የሆኑት ራስ ሥዩም መንገሻ ጦርነቱ በተጀመረ ሳምንት የጣሊያኑ ጦር እየገፋ ሲመጣ አድዋን ለቀው መውጣት ተገደው ነበር።እነሆ ከጥቂት ታማኝ ወታደሮቻቸው ጋር ለስድስት ሳምንት በተንቤን ተራራማ ክፍል ተጠግተው የኢትዮጵያን ጦር ሲጠብቁ ከርመው ዛሬ ያ ቀን ደርሶ ወደ ጦር ሰፈራችን ብቅ አሉ።

ከጠዋት ጀምረው የራስ ካሣ የክብር ዘብ ከድንኳኑ ግራና ቀኝ እንደነገሩ ተሰልፈው ይጠብቃሉ። ቀትር ላይ መልክተኛው በፈጣን ፈረስ ቀድሞ መጥቶ የራስ ሥዩምን መቃረብ አበሰረን። ብዙ ሳይቆይ ጥቂት ፈረሰኞችና ነጭ ሸማ የለበሰው ጦራቸው ለአይን እይታ ገቡ። የራስ ካሣ የክብር ዘብ አዛዥ፣ ቀኛዝማች አበበ ወታደሮችን በተጠንቀቅ እንዲቆሙ አዘዛቸው። ወዲያው የጦር ነጋሪቶች ያን አስፈሪ ድምፃቸውን ከገደል ማሚቶው ጋር እየተቀባበሉ ያስተጋቡት ጀመር።

ራስ ሥዩም እንደደረሱ ከራስ ካሣ ጋር ተሳስመው ተያይዘው ወደ ድንኳን ገቡ። ራስ ሥዩምን ካጀቡት በርካታ መኳንቶች ጋር አንድ ረዘም ያለ እና የተጨማደደ ካኪ የለበሰና የጦር ሜዳ ቆብ የደፋ አውሮፓዊ አየሁ። ሰውዬው በፈጣን እርምጃ በቀጥታ ወደኔ በመምጣት፣ "ኮሎኔል ኮኖቫሎቭ እባላለሁ" አለና ለሰላምታ እጁን ዘረጋልኝ።

ቀጥሎም በፈረንሳይኛ "እርስዎ ርግጠኛ ነኝ የራስ ካሣ የጦር አማካሪ ፓርላሳ ነዎት አይደል?" አለኝ። መገረሜን ሳልደብቅ "እንዴት አወቁ?" ብዬ ሳልጨርስ ኮሎኔሉ ፋታ ሳይሰጥ "ሌሎች የታሉ?" ብሎ ጠየቀ። አሁን ይበልጥ ተገርሜ ጥቶችን ብዬ ጠየኩት "እስከማውቀው ድረስ ከአዲስ አበባ ለራስ ካሣ ጦር 14 አውሮፓውያን መኮንኖችና ሰባት እንግሊዛዊ ዶክተሮች ተመድበዋል" አለኝ ፈርጠም ብሎ። "ይቅርታ ኮሎኔል ከልቤ እንድስቅ ይፈቀድልኝ" አልኩትና እንዳበደ ሰው መሳቅ ጀመርኩ። እንደምንም ሳቄን አፍኜ አንድም ዶክተር በጦራችን እንደሌለና ባለው መርፌ ጣ የሀበሻ ዶክተር ሞቼ ብንፈራፈርም እንደማልታከም እና ያለነው ብቸኛ አውሮፓውያን እኔና ጓደኛዬ ብረየር ብቻ መሆናችንን ስነግረው፣ ትንሽ ራሱን አወዛውዞ አልፎ አልፎ ብቻውን እየሳቀ ወደ ድንኳን አመራ።

መጀመሪያ ብቻዬን ነበርኩ። ቀጥሎ ኮሎኔል ተጨመረና ሁለት ሆንን። ከዚሁ ሌላ ሶስተኛ ፈረንጅ መጥቶ ሶስት ሆንን። በስተመጨረሻ የኩባው ካፒቴን አሌሳንድሮ ዴል ቫል (የራስ ሙሉጌታ የጦር አማካሪ) መጣና አራት ሆነን ሳለ፣ ወደ ጦርነቱ ማለቂያ ግድም ላይ የመጀመሪያው አውሮፓዊ ዶክተር ሹፐለር ከአየርላንዳዊው ካፒቴን ሀይኪ ጋር ሲደርስ፣ ሁለት ሌላ የፖላንድ ተወላጆች በራስ ሙሉጌታ ሰፈር በጣልያኖች ምርኮ ስር ወደቁ።

ከጋዜጠኞችና የጦር ሜዳ ዘጋቢዎች ምንም እንኳ በአዲስ አበባ ቁጥራቸው ከ200 በላይ ቢሆንም በሰሜኑ የጦር ሜዳ አንድም አልነበሩም። እስከማውቀው ድረስ ወደ ደቡብም የዘለቀ ጋዜጠኛ አልነበረም።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ራስ ካሣ እንግዳ በመቀበያ ተንቀሳቃሽ ሳሎናቸው የክብር እንግዶችን ተቀብለው ከራስ ሥዩም ጋር ጎን ለጎን ተቀምጠዋል። እኔና ኮሎኔሉም ከራሶቻችን ጀርባ ቆመናል። ራስ ካሣም፣ ራስ ሥዩምም አጠር ያሉ ንግግሮች ካደረጉ በኋላ በንጉሠ ነገሥቱ ስም ዋንጫቸውን አነሱ፤ ለዳግማዊ ድል ወደፊት! ወደፊት! አዎ ራስ ካሣ በዚያች ምሽት የመጨረሻዋን የሻምፓኝ ሳጥናቸውን መስዋዕት አደረጉ።

በዚያች ምሽት ከኮሎኔሉ ጋር ሌሊቱን ሙሉ ስናወራ አደርን። አዎ ከዚያ ቅጽበት ጀምሮ እድላችን ተሳስራለች። ባንድ ድንኳን ውስጥ አብረን መኖር ጀምረናል። ወደፊት የሚገጥመንን ሁሉ ከጀግናው የኢትዮጵያ የገበሬ ሰራዊት ጋር ለመጋፈጥ ወደፊት!!! እያልን ሁለታችንም አሸለብን።

ጣልያኖች ስለሁለቱ ራሶች መገናኘት በሰላዮቻቸው አማካኝነት ሳይሰሙ አልቀረም መሰለኝ፣ በነጋታው ከጠዋቱ ሁለት ሰዓት ላይ ከላይ ከተራራው ጥግ ሶስት

የማስጠንቀቂያ ጥይቶች ተከታትለው ተተኮሱ። ወዲያው ከየገደሉ ስር ነጋሪቶች ድምፃቸውን አስተጋቡ።

ብዙም ሳይቆይ በሰማይ ላይ ድምፃቸውን አስቀድመው ሶስት ነጫጭና ትንንሽ አበባማቦች ታዩ! ቀጥለውም ሌሎች ሶስት ብቅ ብለው ሰፈራችንን አንድ ሁለቴ ከዞሩ በኋላ የቦምብ ዝናባቸውን ያወርዱብን ጀመር።

ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት ፀጥታ የሰፈነባትና ሰላማዊዋ መንደራችን በደቂቃዎች ውስጥ ወደ ገሀነም እሳትነት ተለወጠች። ይኼ የገሀነም እሳት እታች ከወንዙ ስር መደዳውን የሚግጡትን የቀንድና የጋማ ከብቶችን አስበርግጎ ነፍሴ አውጪኝ በያቅጣጫው ደንብረው ሲሮጡ ይታይ ነበር። አንድ ሰዓት የፈጀው ይኼ የቦምብ ዝናብ እንደ እድሜ ልክ ረዝሞብን ቆየ።

ከአንድ ሰዓት በኋላ እነዚያ የተረገሙ የቆርቆሮ አሞራዎች የሞት እሳት መትፋታቸውን ሲተዉ፣ ከተደበቅኩባት ዋሻ ወጥቼ ቁልቁል እየተንደረደርኩ ስወርድ ለላ የማስጠንቀቂያ ሶስት ጥይቶች ተከታትለው ተተኮሱ። ብዙም ጊዜ ስላልነበረኝ ሽቅብ መመለሱን ትቼ ካጠግቤ ካገኘኋት ትንሽ ቋጥኝ ስር ተወርውሬ ተኛሁ። ቋጥኟ ግማሽ አካሌን ስለሸፈነችልኝ እግሮቼን ወደ ቁጥቋጦ ውስጥ ወሽቄ ስጠብቅ አንዱ አውሮፕላን ከሌሎች ተለይቶ ወደኔ አቅጣጫ በመብረቅ ፍጥነት ይበር ጀመር። ነፍሴ ጉሮሮዬ ውስጥ ተወተፈች። በዚያ ቅጽበት አውሮፕላኑ በኔ ላይ የሚወድቅና ሞተሮቹ ፀትንትኔን የሚያወጡኝ እስኪመስለኝ ድረስ ፈራሁ። ይሁን እንጂ አብራሪው የሚጥላቸው በምቦች የሚወድቁት ከኔ ትንሽ ራቅ ብለው ስለነበር እንደምንም ራሴን አረጋግቼ አውሮፕላኑ እንዳለፈኝ ሽቅብ ወደ አስተማማኝ የራስ ካሣ ዋሻ ገሰገስኩ። ይዘግል ያችን ለዝንጀሮ እንኳን አስቸጋሪ የሆነች የስርጥ መንገድ እንዴት እንኳ እንዳለፍኳት ሳላውቅ እራሴን ከራስ ካሣ ዋሻ ውስጥ አገኘሁት።

ጣልያኖች የኢትዮጵያ ወታደሮች ተራራውን ተጠግተው መሽገዋል በሚል ግምት ሶስቱ የተራራውን አንድ ክፍል ሲደበድቡ ሌሎቹ ሶስቱቹ ደግሞ ከጀርባ ዞረው የቦንብ ዝናብ ያወርዱበት ነበር። አውሮፕላኖቹ ብዙ ጊዜ ዝቅ ብለው ሲበሩ ከከፍታ ቦታ ላይ በትክክል አብራሪውን ማየት ይቻል ነበር። እኔም ከራስ ካሣ የቋጥኝ ዋሻ ውስጥ ሆኜ አብራሪውን ጣልያናዊ ሳይ ደሜ ይፈላ ነበር። ብዙው ኢትዮጵያዊ ወታደር እንዲህ ዝቅ ብለው ሲበሩ ብዙም ሳያነጣጥሩ ደጋግመው ይተኩሱ ነበር።

ከእኛም ዋሻ ብዙ ጊዜ ይተኮስ ስለነበረ አብራሪው ሁኔታውን ተገንዝቦ ዋሻችንን እንደም በአውሮፕላኑ ላይ የተጠመደውን መትረየስ ያርከፈክፍብን ጀመር። በዚች ቅጽበት ሽማግሌው ራስ ካሣ ሳይቀሩ ይተኩሱ ነበር። ከጎኔ የመሸገ አንድ ወጣት

ወታደር ጣልያኖች ያወረዱብን የመትረየስ ጥይት ከዋሻዋ ጣርያ ላይ የሸረፈችው ድንጋይ እጄን ክፉኛ ስለጎዳው ከለበሰው ያደፈ ሸማ አራፊ ጨርቅ ቀርጦ እጄን ያሰር ነበር:: በዚህ መልኩ በተደጋጋሚ የቦንብና የጥይት ዝናብ ሲያወርዱብን ቆይተው በድንገት አንዷ ቅርቅር አሽቀልቁላ መውረድ ጀመረች። በዚህ ቅጽበት የመጀመሪያዋን የጣላት አውሮፕላን የኢትዮጵያ ወታደሮች እንደጣሉ ጥርጥር አልነበረውምና ሁሉም ከመሸገበት ዋሻ ወደሰማይ እየተኮሰና እየፎከረ በታላቅ ጩኸት አውሮፕላኗ ወደወደቀችበት አቅጣጫ መሮጥ ጀመረ:: ራስ ካሣም ጠመንጃቸውን እንዳነገቱ ቁልቁል ተንደረደሩ፤ እኔም ተከተልኳቸው::

ለአፍታ ያህል ቆም ብዬ እየፎከረና እንደ አንበሳ እያጓራ ውድ ጥይቱን እያንጣጣ በደስታ ቁልቁል እንደ ናዳ ወደ ሸለቆው የሚወርደውን ባለነጩን ሸማ የገበሬ ወታደር ሳይ እጅጉን በጣም ኮራሁ:: እኔም ደስታዬን መቆጣጠር አቅቶኝ ጥርሴን እያፏጨሁ ወደ ሰማይ እየተኮስኩ ቁልቁል ስንደረደር ሶስት ጥይቶች ተደጋግመው ተተኩሰ ለጥቆም ነጋሪቶች ከየቅጣጫው ጩኸታቸውን አሰሙ:: ይሁን እንጂ ያ እንደ ናዳ የሚነጉደው ወታደር አልሰማም፤ እየፎከረና እየጮኸ ወደ ታች ወረደ::

የኢትዮጵያው ጦር እንዲህ አጋጅ አጥቶ ሲወርድ ሁለቱ አውሮፕላኖች ማንገርበብ ጀመሩ ከቆምኩባት የገደል ጫፍ ላይ ሆኜ ቁልቁል ወደ ታች አያለሁ። አዎ እታች አረባዳው ቦታ ላይ አንድ አውሮፕላን ቆማለች ብዙ ወታደሮች ከተለያየ አቅጣጫ ወደ አውሮፕላኑ ይሮጣሉ አንደኛው አብራሪ የአውሮፕላኗን ሞተር ለማስነሳት ከመዘውሯ ጋር ሲታገል ሁለተኛው በአውሮፕላኗ ላይ የተጠመደውን መትረየስ በኢትዮጵያ ወታደሮች ላይ ሲያርከፈክፍ ወታደሮቻችን እንደቅጠል ይረግፉሉ:: እኛ ተከስክሳለች ብለን የገመትናት አውሮፕላን እንደምንም በግድ አርፋለች::

በዚህ መሀል ሁለቱ አውሮፕላኖች ደርሰው ገት ብለው በመብረር በኢትዮጵያው ወታደር ላይ የሞት ዝናብ ሲያወርዱ አብራሪው ሞተሩን ማስነሳቱ ቀናውና እንደምንም ተንፏቆ ማኮብኮብ በመቻሉ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ከተራራው ጀርባ ተሰወረ:: እስከ ምሽት ድረስ ወታደሮቻችን ሬሳና ቁስለኛ ሲሰበስቡ አመሹ። መርፌ ወጊው ሀኪማችን ፋታ አጥቶ ይዋከባል:: ያለ ምንም እረፍት ይሰራል:: በርካታ ሴቶች ሰብሰብ ሰብሰብ ብለው ተቀምጠው አሮጌ ሸማ ለቁስል ማሰሪያ ይቀዳሉ:: በየሃገሩ ስር እንደነገሩ ከተገነጠለ ቅርንጫፍ እንጨት በተሰሩ ቃሬዛዎች ላይ ቁስለኞች ተኝተዋል። የሞተው ወደ መቃብሩ ወርዶ ቦታ እስኪለቅ ድረስ ያለምንም ህክምና ተኝተው ህመማቸውን ውጠው ይጠብቃሉ::

በጦር ሰፈራችን በጣም የተጎዳንና ሲድን የማይችል እግር ወይም እጅ መቁረጥ ብሎ ነገር የለም። ለነገሩ ይኼን አይነት አስቸጋሪ ህክምና ሲያደርግ የሚችል ሐኪምም፤ የህክምና መሳሪያውም የለንም:: ሁለተኛ የአበሻው ወታደር እግሩን ወይም እጁን ከሚቆረጥ ሞትን ይመርጣል። እንደምን የእድሜ ልክ አካለ ጎዶሎ ሆኖ የዘመድ አዝማድ ሸክም ሆኖ መኖር ይቻለዋል? እና ሞትን ይመርጣል::

ማምሻው ላይ ቴሌግራፊስቶቻችን አንቴና ማቆሙ ስለቀናቸው ከአዲስ አበባ ጋር መገናኘት ችለናል። ቀጥለንም ከተለያዩ የአውሮፓ አገሮች የሚተላለፉ ድምፆችን ለናፍም ቆይተን ከሮማ የተላለፈ ዜና ሰማን::

አሥራ ስምንት የጣልያን ቦምባርደር አውሮፕላኖች ለሁለት ሰዓታት ያህል የራስ ካሣ ጦር የሰፈረበትን አይቦታ፣ የጦር ሰፈር መደብደባቸውን ገልጾ፣ ወደ ዝርዝር ዜናው በመግባት አንድ የጣልያን አውሮፕላን በኢትዮጵያ ወታደሮች ተመትቶ ጦሩ ከሰፈረበት የጦር ሰፈር ራቅ ብሎ ለማረፍ መገደዱንና አንድ የጣልያን ወታደራዊ ታዛቢ መኮንን መገደሉን አሳወቀ። አብራሪውም ከብዙ ድካም በኋላ የአውሮፕላን ሞተሮቹን ጠግኖ ሞተሩን አስነስቶ መብረር በመቻሉ ወደ ጣልያኖች የጦር ሰፈር መቀሌ በሰላም መመለሱንና ሌላም ነገር ጨማምሮ አወራ። አዎ የተገደለው ወታደራዊ ታዛቢ ካፒቴን ያኔ ከጦርነቱ በፊት በግድ ለራስ ካሣ የሰሜኑን የኢትዮጵያ ክፍል የሚያሳይ ካርታ የሰጣቸው መሆኑን በኋላ ዘግየት ብዬ ተረድቻለሁ።

የጣልያን ጦር ጀነራል ቀርቶ እያንዳንዱ የመቶ መሪ መኮንን ስለ እያንዳንዷ የኢትዮጵያ ተራራ፤ ወንዝ፣ ጅረትና ሸለቆ፣ ትንንሽ መንደሮችን እንኳ ሳይቀር የሚያሳይ ካርታ ይዞ ነበር። የኛ ጦር ግን የነበረችው ከትምህርት ቤት ለዚያውም ከጣልያን ትምህርት ቤት መማሪያ መጽሐፍ ላይ የተቀደደች የአየር ጸባይ ጠቋሚ ካርታ ብቻ ነበረች። ያቺ ወድቃለች፣ ተከስክሳለች ብለን የገመትናት አውሮፕላን ሰተቻከል ሁለት ካርታዎች ጥላልን ሄደች::

ካርታዎቹ ከአስመራ ከተማ እስከ መቀሌ፣ ከመቀሌ እስከ አምባላጌ ድረስ ያለውን ክፍል ግልጽ አድርገው የሚያሳዩ ነበሩ:: ይቺው ካርታ እስከ ጦርነቱ ፍጻሜ ድረስ የነበረችን ብቸኛ ካርታ ነበረች::

በጣም ከመሸ በኋላ ባጭር ሞገድ ከፓሪስ የሚተላለፍ ጣቢያ መሳብ ቻልኩ:: ከዛች ጣቢያ የታንጎ የሙዚቃ ሜሎዲ ይንቆሮቆራል:: ፍጹም ጣፋጭ የሆነ የዳንስ ሙዚቃ እዚህ በኢትዮጵያ ተራሮች ጫፍ ላይ እንደ ዝንጆሮ ድንጋይ ታቅፎ መስማት በጣም የሚገርም ነገር ነው:: እዚያ ፓሪስ ከዚህ ብዙ ርቆ የዘመኑ ወጣት ያለምንም

ሀሳብ ታንጎ እየደነሰ፣ ሴቱን እያጫወተ፣ ቪኖውን እየትጎነጨ፣ ሲስቅና ሲጫወት፣ በደስታ አለሙን ሲቀጭ፣ የእድሜ እኩዮቹ ወይም ታናናሾቹ የኢትዮጵያ ወጣቶች እዚህም እዚያም የሞት ጣር ያጥራሉ:: ቆስለው ህመማቸውን ውጠው ያለምንም ማስታገሻ መድሃኒት ያስታምማሉ::

ከሰፈርንባት የጦር ሰፈር ዙሪያ የተራቡ ጅቦች ያነፈንፋሉ:: አይ ደቺ ምድር፡ ብቻ የታንጎው ሙዚቃ ሲቆም አጠር ያለ ዜና ቀረበ:: "የተባበሩት መንግስታት ጦሮች መስጠታቸውንና በጣልያን ላይ ማዕቀብ መጣላቸውን አሳወቁ::" እንግዲህ በጣልያን እጅ እንድንወድቅ መቼም አይፈቅዱም፤ አያደርጉም፤ ይረዱናል:: ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ እኩለ ሌሊት ይሆናል:: ህዳር 18 ቀን 1935 ዓ .ም. አለፈች::



19

ሦስቱ ንጉሦች

ራስ ሥዩም መንገሻ ዛሬ ያደሩት እኛ ጦር ሰፈር ነው:: የራስ ሥዩም ጦር የሰፈረው ከኛ ጦር ሰፈር የተወሰኑ ሰዓቶች የሚፈጅ መንገድ እራቅ ብሎ፣ እታች እቆላው ውስጥ ነው:: ራስ ሥዩም መንገሻ ያላቸው የሚከተላቸው ወደ 5,000 የሚሆን ወታደር ብቻ ነው:: የቀረው ጦራቸው በትናንሽ ሹሞች እየተመራ ተበታትኖ ተንቤን ውስጥ ከጠላት ጋር ይዋጋል::

እንደሚመስለኝ ራስ ስዩም መንገሻ አድዋን ሲለቁ ብዙ ንብረት ያዳኑ አልመሰለኝም:: ወይም ደግሞ ለወታደሮቻቸው የወር ደሞዝ ለመክፈል ይችሉ ዘንድ ከራስ ካሣ 5,000 ጠገራ ብር [ማርትሬዛ ብር] ተበድረው ነው የሄዱት::

የኢትዮጵያ ወታደሮች የወር ደሞዝ አንድ ብር ነበር:: በዚች አንድ ብር ወር ከወር ቀለባቸውን ችለው መቆየት አለባቸው:: ይቺ አንድ ብር የገበሬውን ወዶ ገባ ወታደር አይመለከትም:: ለምሳሌ፣ የደጃዝማች አበራ 20,000 ጦር ከደጃዝማች አበራ አንዲት ብር እንኳ ሲወስድ አላየሁም::

የራስ ካሣ የጦርነት ካዝናቸው ወደ 300,000 የማርትሬዛ ብር ይጠጋ ነበር:: በዚህ በጦርነት ሰዓት ማንም የወረቀት ገንዘብ ስለማይቀበል፣ የነዚህን ከባድ የብር

ሳንቲሞች መሸከም ግድ ነበር። የራስ ካሣ ካዝና ክብደት ወደ ስምንት ቶን አካባቢ ሲሆን እነዚህን ብሮች በሳጥን ከተቶ ከጦሩ ጋር ለማጓጓዝ ወደ 200 የሚሆኑ አህዮች ያስፈልጉት ነበር። ባለፈው ከራያ ሽፍቶች ጋር ችግር በተፈጠረ ጊዜ ራያዎች የተወሰነ ሳጥኖች ዘርፈው ስለነበር፣ ራስ ካሣ ገንዘብ ቤታቸውን ብሮቹን እንዲቆጥር አዘዙት።

ከጠዋት ጀምረው አራት የገንዘብ ቤቱ ረዳቶችና ገንዘብ ቤቱ ተቀምጠው፤ ዋናው ገንዘብ ያዥ ሳጥኑን ይከፍትና ብሮቹን ሜዳ ላይ ዘርግፎ አንዷን ያነሳና ሲወረውር ሌሎቹ አራቶቹ "አንድ ይላሉ፤ ሁለተኛዋን ሲወረውር ሁለት ይላሉ፤ ሶስተኛዋን ሲወረውር ሶስት እያሉ ቆጠራ ውስጥ ገቡ። ከሰዓት በኋላ እንደ ገንዘብ ቤት ከተመረጠች አንዲት ዋሻ አጠገብ ሳልፍ ገንዘብ ቤቶቹ በትግስት እየቆጠሩ 12,375 መድረሳቸውን ሰማሁ። ማምሻው ላይ ስመለስ በዚያው በገንዘብ ቤት በኩል ሳልፍ ገንዘብ ቤቶች በዋሻዋ ውስጥ ሆነው ከፍ ባለ ድምጽ ይጨቃጨቁ ነበር።

ነገሩ በኋላ ስሰማ እንዲህ ነበር። አንድ የራስ ካሣ ዘብ ከራስ ካሣ ወደ ዋናው ገንዘብ ቤት ተልኮ ወደ ዋሻው ከገባ በኋላ መልክቱን ለዋናው ገንዘብ ያዥ እያስረዳ ከተቀለለው የማርትሬዛ ብር አንዷን በእግሮቹ ጣቶች ቀልፎ ሊወጣ ሲል ከአራቱ አንዱ ስላየው ዘቡም ብሯን ቢመልስም፣ ይኼ ግርግር ቆጣሪዎችን ቁጥር አሳሳታቸው። እና አንዱ 24,753 ነው ብሎ በሚኒልክ ሲምል፣ ሌላው ደሞ የለም 24,553 ነው ብሎ እሱም በሚኒልክ ይምላል።

በመጨረሻ ዋናው ገንዘብ ያዥ እንደ ንጉሥ ሰሎሞን ይፈርዳል። በሉ ከሁን መሸቷል። ነገ በጠዋት ተነስተን እንደገና እንቆጥራለን ይላቸውና ይለያያሉ። በሁለተኛው ቀንም መቁጠሩ ስላልሆነላቸው ጭቅጭቁን ትተው ለራስ ካሣ ምንም እንዳልጎደለ ተናግረው ብሮቹን ወደ ሳጥን መልሰው ቀለፏቸው።

በርከት ያሉ አስቸጋሪ ቀናቶች አለፉ። መላ አካላቴ ክፉኛ ደክሟል። ትኩሳት በትኩሳት ሆኛለሁ። በጦር ሰፈራችን እውነተኛ ዶክተር ቢኖረን ኖሮ ባለሁበት ሁኔታ በዘዘ ቢያንስ የተወሰኑ ቀናት ለጥ ብዬ በፀጥታ እንድተኛና ትኩሳቴን እንዳስታግም ባዘዘኝ ነበር። ግን መተኛቱ የማይታሰብ ጉዳይ ነው። እንዴትስ ታስቦ? ገና ሳይነጋ በወጋገኑ ድንኳናችንን ነቅለን ወደዋሻ መግባት አለብን። አለበለዚያ ልክ ነህ ሲቀድ እነዚያ የተረገሙ የቅርቅር አሞራዎች መጥተው ድራሻችንን ያጠፉናል።

አሁን የኢትዮጵያው ወታደር የጣልያንን አውሮፕላኖች ተላምዷቸዋል። ገና ሳይመጡ በፊት ድንኳኑን ነቅሎ ልክ የማስጠንቀቂያዎቹ ተኩሶች ሲተኮሱ ተረጋግቶ ወደ ቀፈራት ዋሻው ይገባል። በከንቱም ውድ ጥይቱን ማባከን አርግፍ አድርጎ ትቶታል። ምንም እንኳን በየቀኑ ለረጅም ሰዓታት በቦምብ ቢደበደቡንም እንደ

መጀመሪያው አካባቢ ብዙ ሰው አያልቅብንም ነበር። ያው ዋሻዋ የቦምብ ናዳ ሳትችል ቀርታ በቀፈራት ምሽጉ የሚቀበር እድለቢስ ግን አይጠፋም ነበር።

በዚህ መሀል ጣልያኖች ሽሬታ ከምትባል ቀበሌ ወደ መቀሌ አካባቢ የጀመሩትን የአውሮፕላን ማረፊያ ሰርተው ጨረሱ። እንደ ኢትዮፕያውያን ሰላዮች አገላለጽ ወደ ስላሳ አውሮፕላኖች፣ ወደ ሰላሳ ታንኮችና በርካታ የጭነት መኪናዎች ከብዙ ተንቀሳቃሽ ብረት ለበስ መኪና ነገሮች ጋርና በጣም ብዙ ወታደሮች ማስፈራቸውን ተናግረዋል። እዚህ ላይ የኢትዮጵያ ሰላዮች ወታደር ቁጥር ላይ ብዙ አይሆንላቸውም። እናም ብዙ የሚለውን ቃል ይጠቀሙ ነበር።

ኢትዮጵያውያን በአይነታቸው ተወዳዳሪ የማይገኝላቸው ድንቅ ሰላዮች ቢሆኑም በወታደር ቁጥር ላይ ችግር ነበረባቸው። አንድም በዘመናዊ መልኩ ያሸለቀው የተመደበውን ጦር ለይቶ ማወቅና ማስላቱ ላይ ችግር አለባቸው። ወይም ደግሞ እንዲያው ገዘም ብለው ብዙ ወይም በጣም ብዙ ማለት ይቀናቸዋል።

ራስ ካሣ ከራስ ሥዩም ጋር ከመከሩ በኋላ መቀሌ የሰፈረው ጦር ላይ ጥቃት ከመሰንዘራቸው በፊት ትክክለኛውን የጣልያን ወታደር ቁጥር ማወቅ በመፈለጋቸው፣ ብልጥና አሉ የሚሏቸውን ሹሞቻቸውን ለስለላ መላክ ጀመሩ። ሰላዮቻችን ወደ መቀሌ ሲገቡ በአብዛኛው እንደ ተራ ባላገር ገበያተኛ ለብሰውና ያለምንም መሳሪያ የፍየል ግልገል፣ ወይም ዶሮ፣ ወይም ደሞ የፍየል ቆዳ ይዘው ወደ መቀሌ ከተማ ገብተው ይመለሱ ነበር።

ይሁንም እንጂ አንዳንድ ገበሬዎች ለሁለቱም ወገን ይሰልሉ ስለነበረ ይኼንንም ጣልያኖች ደርሰውበት ለመቀጣጫ ብዙ ሰው በመቀሌ አደባባይ ሰቀሉ፤ ረሸኑ። ከነዚህ ምስኪኖች መሀል ብዙዎቹ በእውነትም የሆነ ነገር ሸጠው እቃ ለመግዛት የወጡ ገበሬተኞች ነበሩ። ጣልያኖቹ በዚህ መልኩ ብዙ ኢትዮጵያውያን ገበሬዎች ቢፈጁም የኛ ሰላዮች ሳይበገሩ በየቀኑ ወደ ገቦች ራስ ካሣ ፊት እየቀረቡ አድሉ እንዲሰጣቸው ይለምኑ ነበር።

አንድ ቀን ማምሻው ላይ አንድ ሽምግል ያለና ፀጉሩን ያንፈረ ረዘም ያለ ቢጫም ሽበቱ ሽማግሌ ራስ ካሣ ፊት ቀርቦ ወደ መቀሌ ይልኩት ዘንድ ለመኑ። ራስ ካሣ የሽማግሌውን ሁኔታ አይተው ደስ እንዲለው ብቻ ሲፈቅዱለት፣ እንዲጠነቀቅና ቤኤ እንደሚፈልገው ጭምር አስጠንቅቀውና ሞራል ሰጥተው ላኩት።

ይኸ ሽማግሌ ወደ መቀሌ ጉዞ ሲጀምር ዶሮም ይሁን የፍየል ግልገል፣ የፍየልም ቆዳ ምንም የሚሸጥ ነገር አልያዘም ነበር። በምትኩ ይኼ ብልህ ሽማግሌ

ሁለት እነስ ቢሉም ለሽክም የሚከብዱ ያልፈነዱ ቦምቦች ይዞ ጉዞውን ቀጥሎ በሁለተኛው ቀን በርካታና ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎች ይዞ ተመለሰ።

እኔም የወሬ ወሬ የሽሜውን ዝና ሰምቼ አይቅርብኝ አልኩና ያኔ ትኩሳት በነበረኝ ጊዜ ደጃዝማች አበራ ከለገሰኝ አረቂ ከሲጋራዎች ጋር ሽማግሌውን ጋበዝ አስደናቂውን ጉዞውን እንዴት እንደነበረ እንዲያጫውተኝ ለመንኩት። እውነት ለመናገር ሽሜው ሲያጫውቱኝ ሳቄን መቆጣጠር አልቻልኩም ነበር። ነገሩ እንዲህ ነው። ሽሜው ሁለቱን ቦንቦች በመያዝ ወደ አንድ የጦር ካምፕ ይኼዱና "አለቃችሁን አቅርቡልኝ" ይሏቸዋል። የጣልያን ወታደሮች የሚናገሩት ስላልገባቸው አስተርጓሚ ወዳለው አንድ መቶ አለቃ ይወስዷቸዋል። ሽማግሌው መቶ አለቃው ጋ ይቀርቡና "ጌታዬ ይኼውልዎት፣ ትናንት ወደ እርሻ ቦታዬ ስሄድ እነዚህን ሁለት ብረቶች ከማሳዬ ውስጥ አገኘኋቸው። እንደ ጎረቤቴ አባባል ከጣሊያን አውሮፕላኖች ቂጥ ስር ነው የወደቁት አሉ። እናም ይኼው እነሆ ይገባላችሁ መጥቻለሁና ይቀበሉኝ። ባክሺሽም (ጉሻ) ይስጡኝ" ብለው ይለምናሉ።

መቶ አለቃው በሽማግሌው ታሪክ እየሳቀና ቦምቦቹን ተቀብሎ ካሣውንም ሳይከፍለው ትክሻውን መታ መታ እያደረገ ከጣሪያ በላይ እየሳቀ ሽማግሌውን ያባርራቸዋል። ሽማግሌው በዚህ መልኩ ካንዱ የጦር ሰፈር ወደሌላው እየዞሩ "አንድ መቶ አለቃ ብረቶቼንም ወስዶ ብሬን ሳይሰጥ አባረረኝ። ከጣልያኑ ንጉሥ ዘንድ አቅርቡኝ" እያሉ ሲከሱ ሁሉም ቦታ እየሳቁባቸውና እያላገጡባቸው ሲያበሯቸው፣ ተመሳሳይ ታሪክ እያወሩ ተመሳሳይ መልስ እየገጠማቸው በመቀሌ ከተማና በአካባቢው ያለውን የጣልያን ጦር አንድም ሳይቀር ሰልለው ተመለሱ።

አዎ ድንቅና ብልህ ሽማግሌ መሆናቸው አስደስቶኝ እያደነቅኋቸው ምሽቱን ስንጫወት ቆይተን በኮዳዬ የነበረችው አረቂ ተንጠፍጥፋ ስታልቅ ተለያየን።

ለመጀመሪያ ጊዜ ራስ ካሣ ህዳር 25 ቀን የመጀመሪያ ልጃቸውን ደጃዝማች ወንድወሰንን እና ደጃዝማች ጨቡዴን ከ10,000 ወታደሮች ጋር የአምባራዶምን ተራራ ጫፍ እንዲይዙ አዘው ላኳቸው። የሚገርመው ነገር የጣልያን እውቅ ጀነራሎች ታሪክ የማይረሳው ታላቅ ስህተት የሰሩት አምባራዳምን የመሰለች ቁልፍ ቦታ የኢትዮጵያው ሰራዊት ሳይደርስ በፊት ቀድመው ያለመያዛቸው ነበር።

የሁለቱ ደጃዝማቾች ጦር የጣልያን ሰላይ አውሮፕላኖች እንዳያዩዋቸው ሌሊቱን ጨለማን ተገን አድርገው ሲጓዙ አድረው ሊነጋጋ ሲል አምባራዶም ደርሰው መሸጉ። የጣልያን አውሮፕላኖች ረፋዱ ላይ አምባራዶምን ሲዞሩ አረፋፍደው በስተመጨረሻ የተሸከሙትን የቦምብ ጭነት በትንሿ የእንጣሎ ከተማ ላይ አራግፈው ወደ መቀሌ ተመለሱ።

አምባራዶም ከባህር ወለል በላይ 2,756 ሜትር ከፍታ ያላት፣ ለሁለቱም ወደ ወሳኝ መንገዶች ማለት ወደ መሀል ሀገር ዘልቆ ለመግባት አምባላጌን አልፎ ወደ

ሰቆጣ ለማለፍ የሚያስችሉ መንገዶችን መቆጣጠሪያ ብቸኛ አማካይ ቦታ ነበረች። ሆኖም ቀረ ከሁለት ወር በኋላ አምባራዶምን ለመቆጣጠር ከራስ ሙሉጌታ ጦር ጋር ሁለት ሳምንት የፈጀ ከባድ ጦርነት ተደርጎበት የጣልያን ጦር ምንጊዜም የማይረሳው ከፍተኛ ጉዳትና ሽንፈት ገጥሞታል።

ዋናው የራስ ካሣ ጦር እስካሁን ከሰፈረንበት አይቦታ የጦር ሰፈር ሆኖ የራስ ሙሉጌታን መምጣት በትግስት ሲጠብቅ፣ የጣልያን ጦር ሌት ተቀን በመቀሌና አካባቢዋ ያለውን ጦር እያጠናከረ፣ ከመቀሌ ወደ መሀል ሀገር የሚወስድ ጥርጊያ መንገድ በመስራት ላይ ነው። በዚህ መንገድ ጠረጋ ስራ ላይ የተሰማሩት በአብዛኛው ኤርትራውያን ሲሆኑ የቀን ደሞዛቸውም አንድ ብር ተኩል ነበር።

እዚህ ላይ ከኢትዮጵያው ወታደር የወር ደሞዝ ማለት አንድ ብር ጋር ስናወዳድረው በርካታ የትግራይ ተወላጆች ከጦራቸው እየጠፉ ለጣልያኖች መንገድ ጠረጋ መግበራቸው፣ መግባታቸው ሊገርመን አይገባም።

እነዚህ የትግራይ ልጆች ጥቂት ብሮች ካጠራቀሙ በኋላ ወደ ሹሞቻቸው በመመለስ በጦርነቱ ሙሉ በሙሉ መሳተፍ ብቻ ሳይሆን ለራስ ካሣም በጣም ትልቅ ጠቀሜታ ያላቸው መረጃዎችን ይዘው ተመልሰዋል።

ጣልያኖች እንዲህ በቀላል ገንዘብ በርካታ የሰው ጉልበት ተጠቅመው መንገድ የመጥረጉን ስራ ገፍተውበት ከመቀሌ ብዙ ርቀው ሌት ተቀን እያሰሩ፣ አልፎ አልፎ ቀን ላይ በብዙ ብረት ለበስ ተሽከርካሪዎች ሲዘዋወሩ ታይተዋል። ይኼን የተገነዘቡት ሁለቱ ደጃዝማቾች (ወንድወሰንና ጨቡዴ) የመንገድ ስራውን ለማጨናገፍ ጥቃት ሲሰነዝሩም በቀላሉ ወደ ምሽጋቸው እንዲመለሱ በዘመናዊ መሳርያ የታጠቀው የጣልያን ልዩ ብርጌድ አስገድዷቸዋል።

ምንም እንኳ ጦርነቱ ከተጀመረ ሁለት ወር ቢያልፍም እስካሁን እዚህም እዚያም ከሚከፈቱ አነስተኛ ተኩሶች በስተቀር የኢትዮጵያው ጦር ፊት ለፊት ከጠላት ጦር ጋር ገና አልገጠመም። የራስ ካሣ ዋናው ጦር በትግእስት የራስ ሙሉጌታን ጦር እየጠበቀ ነው።

በንጉሠ ነገሥቱ አስተዳደር የኢትዮጵያ ጦር ሚኒስትር የሆኑት ራስ ሙሉጌታ ከአዲስ አበባ ከ100,000 ጦር በላይ ይዘው ከዛሬ ሁለት ወር በፊት ቢነሱም እንደምንሰማው ወሬ ከሳምንት በፊት ማይጨው ገብተዋል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሚናፈስ ወሬ ጦራቸው ማይጨው ከመድረሱ በፊት ወደ ቆቦ አካባቢ በራያዎች ጥቃት ደርሶበት እንደነበረና ከሁለት ቀን በላይ በፈጀው በዚሁ በሁለት ወንድማማቾች መካከል በተደረገ ጦርነት በርካታ ሰው ከሁለቱም ወገን ማለቁንና ራያዎች በስተመጨረሻ መሸሻቸውን ሰምተናል።

ለነገሩ የኛም ዘላኗ የጦር ሰፈራችን በየቀኑ ማለት ይቻላል በትግራይ ሽፍቶች

ሳትዘረፍ ያደረችበት ቀን የለም። ከማስታውሰውና ከባድ ደም ከፈሰሰበት ግጭት፣ ወ የጦር ሰፈር ማለት ነው፣ ታህሳስ 3 ቀን ሌሊት ነው። በዚሁ ወንድም የመግደል ጦርነት ከኛ ወገን 15 ወታደሮች ጦራችንንና ንብረታችንን ሲከላከሉ ሲወድቁ ከሽፍቶቹ ወገን ወደ 30 ገደማ በከንቱ ተገድለዋል። የቁስለኞችን ቁጥር መርፌ ወጊ ዶክተራችንም የሚያቀው አይመስለኝም። አሳዛኝ ታሪክ ነውና ይቅር። ቢያገለ አ ላስታውሰው አልፈልግም።

ታህሳስ 10 ቀን ረፋዱ ላይ ከወደ አምባላጌ በኩል አራት አውሮፕላኖች ወደመቀሌ እየተመለሱ ነው። በኋላ እንደሰማሁት እነዚህ አራት አውሮፕላኖች የንጉሠ ነገሥቱን ጦር ደሴ ላይ ደብድበው መመለሳቸው ነበር። ከሰዓት በኋላ ባለ ሶስት ሞተር አውሮፕላኖች አምባላጌን ዙሪያ መደብደብ ጀመሩ። ከወትሮው የተለየ ነገር ቢኖር አውሮፕላኖቹ አሁን ትላልቅ ቦንቦችን ስለሚጥሉ ፍንዳታው በሚያስነሳው አቧራ የሚንቀጠቀጠው መሬት እኛ ድረስ ይሰማ ነበር።

ማምሻው ላይ እታች አረባዳው ቦታ ላይ እንደ ጉንዳን ሰራዊት መስመር ይዞ የሚርመሰመስ የኢትዮጵያ ጦር ተራራውን እየወጣ ወደኛ ሲዘልቅ አየሁ። ቀዳሚውና በደጃዝማች አውራሪስ የሚመራው ከጅማ የተነሳው የራስ ሙሉጌታ ጦር ነበር። ሌሊቱን ሙሉ ሲጎርፍ ያደረው የራስ ሙሉጌታ ጦር ዝርክርኩ የወጣ በጉዞ የደከመ ነበር። በሚቀጥሉት ሁለት ቀናትም የባላገሩ ጦር ከያቅጣጫው እየመጣ ይቀላቀል ነበር። በመጨረሻ ታህሳስ 12 ቀን ለረጅም ጊዜ ሲጠበቅ የነበረው የራስ ሙሉጌታ ጦርና አሳቸው ራስ ሙሉጌታም ደረሱ።

የራስ ሙሉጌታ ወታደሮች ከኢትዮጵያ መንግሥት ደሞዝ የሚከፈላቸው እውነተኞቹ የኢትዮጵያ ወታደሮች ነበሩ። ራስ ሙሉጌታ ከጦሩ ጋር በርከት ያሉ በቤልጂየም መኮንንኖች የሰለጠኑ ወታደሮችም ነበሯቸው። ፈጣኖቹንም ባለ 20 ሚ.ሜ የሲዊዘርላንድ ካምፓኒ ኦርሊዮን (Oerlion) የሰራቸውን መካከለኛ መድፎች የታጠቀም ጦር ነበር።

ይሁን እንጂ በአብዛኛው የራስ ሙሉጌታ ጦር የታጠቀው ባህላዊውን መሳሪያ ነበር። በሺዎች የሚቆጠሩ እጅና እግራቸውን ብቻ ይዘው የመጡም ነበሩ። ራስ ሙሉጌታ የተራራውን ምስራቃዊ ክፍል ይዘው ሰፈሩ። በዚህ በኩል ብዙም ሰው የማይጠቀምበት ከመቀሌ ወደ ደቡብ እስከ ደሴ ድረስ የሚወስድ መንገድ ነበረው። ከወር በላይ የራስ ሙሉጌታ ጦር በመንገድ ላይ እያለ ብዙ የሚናፈሱ አስደሳች ወሬዎች ነበሩ።

እንደ ወሬው የራስ ሙሉጌታ ጦር በብዙ አውሮፓውያን መኮንኖች የሚመራና በርካታ የብሪታኒያ የቀይ መስቀል ዶክተሮችም እንዳሉትና ሌላም ሌሎች ጦራቸውን ... ወሬዎች ጣፍጠው ይወሩለት ነበር። አሁን ራስ ሙሉጌታንና ጦራቸውን

ላይ ያቺ ወሬ እውነትም ወሬ ብቻ ነበረች። አንድም ዶክተር አብሯቸው የለም። መኮንኖች? ከአንድ ኩባዊ ካፒቴን በስተቀር ማንም አልነበረም።

ኩባዊው ካፒቴን አሌሳንድሮ ዴል ቫል ሰላሳ ዓመት ቢሆነው ነው። የተወለደው አሜሪካን ሀገር ቴክሳስ አካባቢ ሲሆን እዚያ ቴክሳስ ወስጥ ሚሊተሪ አካዳሚ ገብቶ የተማረ ሲሆን፣ እዚያው አካዳሚ እያለ ከአንድ የሜክሲኮ ጀነራል ልጅ ጋር (የክፍል ጓደኛው) ይወዳጅና ሜክሲኮ ውስጥ አብዮት ሲፈነዳ ጀነራሉን ከአባቶቻቸው አጅቦ ወደ ሜክሲኮ ይኼዳል። የሜክሲኮው አብዮት ሳይሳካ ቀርቶ ጀነራሉ ከአባቶቻቸው ወደ ሌላ የላቲን አሜሪካ ሀገር ሲሰደዱ ወጣቱ አሌሳንድሮ አጅቧቸው ተሰደደ። ብዙም ሳይቆይ አሌሳንድሮ ኤክዋዶር ውስጥ በተካሄደ አብዮት ይካፈላል። በዚሁ አብዮት ኤክዋዶር ውስጥ በብዙ ጥይቶች ተመትቶ እንደቆሰለ ይማረካል።

አሌሳንድሮ ከኤኳዋዶር መንግሥት ምህረት ያገኝና ወደ ኩባ ይኼዳል። ይኼው ወጣት ካፒቴን ኩባ ውስጥ በተፈፀመ ወታደራዊ እንቅስቃሴ ይሳተፍና ተይዞ ሞት ይፈረድበታል። በእስር ላይ እያለ ዘበኞችን ጉቦ ከፍሎ አሳምኖ እንደ አንድ የእንግሊዝ መኮንን ልብስ ለብሶ፣ በአንድ ወደ እንግሊዝ ሀገር በሚያመራ መርከብ ተሳፍሮ እንግሊዝ ሀገር ይገባል። ከጥቂት ወራት በፊት ለንደን ኢትዮጵያ ኤምባሲ ቀርቦ ለንጉሠ ነገሥቱ ጦር ያገለግል ዘንድ ጠየቀ። ጥያቄው አወንታዊ መልስ አግኝቶ እነሆ ዛሬ የራስ ሙሉጌታ የጦር አማካሪ ሆኖ ካጠገቤ ቆሟል።

በነጋታው ረፋዱ ላይ ራስ ሥዩም መንገሻ ከትልልቆቹ ሹሞቻቸው ጋር ሰፈር ደረሱ። በራስ ካሣ የእንግዳ መቀበያ ድንኳን ለመጀመሪያ ጊዜ ሶስቱ ከፍተኛ ባለስልጣናት ለምክር ወደ ድንኳኗ ሳሎን ገቡ። ሶስቱ ያልነገሱ ንጉሦች ከፍ ብሎ በተዘጋጀ መድረክ ላይ ውዱ የፋርስ የአበባ ምንጣፍ ተነጥፎላቸው መሀል ላይ የሰሜን ጦር ጠቅላይ አዛዥ ራስ ካሣ ሲቀመጡ፣ ከቀኛቸው ወገን ራስ ሥዩም መንገሻ፣ የአፄ ዮሐንስ የልጅ ልጅ፤ በስተግራቸው ሸበቶው ሽማግሌ ራስ ሙሉጌታ፣ የኢትዮጵያ የጦር ሚኒስትር ተቀመጡ።

ለነዚህ ያልነገሱ ሶስት ንጉሦች እግራቸው ስር ያበባ ምንጣፍ ተነጥፎላቸው፣ እሉ የተባሉ ከፍተኛ መኳንንቶችና የጦር አበጋዞች እንደየ ደረጃቸው በስልጣን ተዋረድ ተቀምጠዋል። ምናልባትም በኢትዮጵያ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ይመስላል እንዲህ ዓይነት ከፍተኛ ባለስልጣኖች በአንዲት ድንኳን ውስጥ ሲሰበሰቡ።

አዎ በዚች ድንኳን ውስጥ ደጃዝማች ኃይሉ ከበደ የዋግ ሹም፣ የከበደ ልጅና ወራሽ፣ የአፄ ቴዎድሮስ የልጅ ልጅ ልጅ፣ ደጃዝማች አውራሪስ የጅማው፣ ደጃዝማች አበራ የሰላሌውና ታላቅ ወንድሙ ደጃዝማች ወንድወሰን እና ሌሎችም በርካታ ደጃዝማቾች፣ ፊታውራሪዎች፣ ቀኛዝማቾች፣ ግራዝማቾች እና ሌሎች ሹሞች ሁሉ ተሰብስበዋል።

የራስ ካሣ እልፍኝ አስከልካይ ለዛሬው ቀን ክብር የሚገባውን ልብሱን አውጥቶ እንደተጨማደደች ለብሶ፣ በዚያች ድንኳን ውስጥ ያሉት ሹማምንት በትክክል በደረጃቸው መቀመጣቸውንና እንደ ማዕረጋቸውና እንደ አካባቢያቸው ግ የተለያየ ቀለም ባላቸው አራፊ ጨርቅ እየተሸፈነ የሚታደላቸው ጠጅ መዳረሱን ይቆጣጠራል። ወታደራዊው ምክር ለረጅም ሰዓት ተካሂዶ በመጨረሻ አንድ ውሳኔ ላይ ተደረሰ። እያንዳንዱ ሹም ተራው ሲደርስ እየተነሳ የጣሊያንን ጦር እንዴት ገጥሞ ማሸነፍ እንዳሰበት የነደፈውን እቅድ አስረዳ። በመጨረሻ ደጃዝማች አበራ እና ደጃዝማች ኃይሉ ከበደ ያቀረቡት ሀሳብ ብዙ ካከራከረና ሌላ ብዙ ነገር ከተጨመሩበት በኋላ መቶ በመቶ ባንድ ድምጽ ጸደቀ። ይኼ ፕላን ከወታደራዊ ስትራቴጂክ አንጻር መጥፎ አደለም። ተግባራዊ ማድረግም ይቻላል።

በዚሁ እቅድ መሰረት ራስ ሙሉጌታ ከመቀሌ በስተምስራቅ ያለውን ቦታ እንዲይዝ፣ ራስ ካሣና ራስ ሥዩም በህብረት የአምባራደምን ተራራ ይዘው ወደ ተንቤን እንዲገፉና የመቀሌን ዙሪያ ከብቦ፣ በገራልታ ያሉ ሁሉንም መንገዶች በማቋረጥ ይዞ፣ የጣሊያን ሰራዊት ምንም አይነት ስንቅና ትጥቅ እንዳያገኝ ማድረግ ነበር።

በየቀኑ ወደ ጦር ሰፈራችን በቡድን በቡድን እየሆኑ የኤርትራ ተወላጅ የሆኑ ወታደሮች ይጎርፉሉ። እነዚህ ወታደሮች በሰላሙ ጊዜ ኤርትራ ውስጥ ውትድርና ገብተው ዛሬ ጦርነት ሲጀመር የጣሊያንን ጦር እየከዱ ከነትጥቃቸው በሚኒልክ ስም እየማሉ ከወንድሞቻቸው ጋር ይቀላቀላሉ። እነዚህ ውድ የኤርትራ ልጆች የኢትዮጵያው ጦር በሚቀጥሉት አምስት ወሮች ከጠላት ጋር ገጥሞ ድል በመታባቸው የጦር አውድማዎች ሁሉ ተሳትፈው ጀግንነታቸውን አስመስክረዋል።

የጣልያን ጥቁር ሸሚዝ ለባሽ የጦር መኮንኖች በውጊያ ላይ በመጀመሪያው እረድፍ ኤርትራውያንን አሰልፎ አስተማማኝ በሆነ ርቀት ይከተሉ ነበር። ኤርትራውያን ታዲያ ሁሌም ከኢትዮጵያው ጦር ጋር በገጠሙ ጊዜ ወይ ፈጽሞ አይተኩሱም፤ አልያም ሆን ብለው ወደ ሰማይ እየተኮሱ ከወንድሞቻቸው ጋ ይቀላቀሉ ነበር። ኢትዮጵያውያንም ኤርትራውያንን ትጥቅ ለማስፈታት ጊዜ ሳይፈጁ አልፈው የጣልያኑን ጦር ይገጥሙ ነበር። በእንዲህ ሁኔታ የሚደነግጠው የጣልያን ጦር ብዙም ሳይታኮስ ይሸሽ ነበር።

ኤርትራውያን በሚበዙበት የጣልያን ክፍለ ጦሮች ብዙ ጊዜ ብጥብጥ ይነሳ ነበር። በአብዛኛው ኤርትራውያን ጣልያናዊዎቹን አለቆቻቸውን ረሽነው ከነመሳ ትጥቃቸው ወደ ኢትዮጵያውያን ወንድሞቻቸው ወገን የሚዝቡበት ጊዜ ትንሽ አልነበረም።

በጦር ሰፈራችን እነዚህን ኤርትራውያን ለመቀበል በየቀኑ ድግስ ብቻ ነበር። ኤርትራውያን በእምየ ምኒልክ ስም እየማሉ በተለያዩ ደጃዝማቾችና ፊታውራሪዎች

ስር ይመደቡ ነበር። አልፎ አልፎም ራስ ካሣ ሹመት እየሰጡ የራሳቸውን ጦር እንዲመሩም ያደርጉ ነበር።

የጣልያን የቅኝ ግዛት አስተዳደሮች በነዚህ ኤርትራውያን ላይ ከፍተኛ የሚሉትን እርምጃ ሁሉ ይወስዱ ነበር። ወደ ኢትዮጵያ የከዳ ወጣት ቤተሰቦችን ንብረት ይወርሳሉ። ንብረትም ከሌላቸው ያስሯቸው ነበር። አልፎ አልፎም ለመቀጣጫ ወጣቶችን ሰብስበው ይረሽኑ ነበር። ይኼ የጣልያኖች ጭካኔ ውድ የኤርትራን ልጆች ግን ወደኋላ አላስበረገጋቸውም፤ በየጊዜው ይጎርፉ ነበር።

20

የጣልያኖች ብቀላ

የጣልያንና የኢትዮጵያ ጦርነት ጦርነት በኢትዮጵያ የአለም ጋዜጦች ለአንባቢዎቻቸው የሚያጎርሱት በመጀመሪያ ገጾቻቸው ላይ በትልቁ የሚጽፉ ቸው የለት ተለት ርእሰ ዜናዎች ነበሩ።

ግን በእውነት ይኼ ጦርነት ነበር? በፍጹም ይኼን ጦርነት ነው ብሎ ማመን አይቻልም። ሞሶሎኒ የጦርነት ትዕዛዝ ሳያውጅ የነጻን ሀገር ድንበር ጥሶ፣ በማን አለብኝነት በአውሮፕላን ቦምብ ህዝብን የሚጨርስ ወታደር ጦርነት ላይ ነኝ ሊል አይችልም። እንዲህ አይነት ወታደሮች "ቅጥር ነፍሰ ገዳዮች" እንጂ ወታደሮች ሊባሉ አይገባቸውም።

ጀግናው የኢትዮጵያ ልጅ ቤት ባፈራው መሳርያ፣ ጋሻ ጦሩን ታጥቆ፣ ጎራዴውን መዝዞ የቦምብ ናዳ እየወረደበት የሀገሩን ድንበር ለማስከበርና ውድ የሆነ ነጻነቱን ላለማጣት የሰለተ ወደ፣ ገደል ወርዶ፣ በዚህ ተግባሩን ለሽማግሌዎችና ለሴቶች ትቶ፣ ተራራ ወጥቶ፣ ገደል ወርዶ፣ በዙ ሸንተረሮች አልፎ፣ ብዙ ወንዞች ተሻግሮ ይኼው እዚህ ደርሷል።

ታህሳስ 9 ቀን ከረፋዱ ጀምሮ እስከማምሻው ድረስ ከሩቅ በየተወሰነ ደቂቃዎች ያለማቋረጥ ፍንዳታዎች ይሰማሉ። አሁን ኢትዮጵያውያን የጣልያን የሞርታር ቆርቆሮዎች የሚጥሉትን ቦምቦች ፍንዳታ ስለተላመዱት እንዲህ ከሩቁ የምንሰማው ፍንዳታ ከቁምነገር የሚቆጥር ሰው አልነበረም።

የደረሳቸው። ስለሁኔታው አስተማማኝ መረጃ የደረሳቸው።

ገና ትናንት ነበር ራስ ካሣ ስለሁኔታው አስተማማኝ መረጃ የደረሳቸው። የጣልያን መድፈኛ ጦር ከጦርነት ስልት አንጻር ምንም አይነት ጥቅም የሌላትን ከጊቫ ወንዝ አጠገብ ያለችውን የደብሪን ከተማ ይደበድባል። ከ150 በላይ የመድፍ ጥይት ያረፉባት ደብሪ ዱቄት ከመሆኗም በላይ ከከተማዋ በጊዜ መውጣት ያልቻሉ አዛውንቶች፣ ሴቶችና ህጻናትም መቀበሪያ ቦታ ሆነች።

ጣልያኖች ይኼንን ፍጹም ግፍ የተሞላበት አረመኒያዊ ድርጊት እንዲፈጽሙ ምን እንዳስገደዳቸው ማንም ሰው አያውቅም። ምናልባት የፋሽስቱ ጦር አለቃ ይኼን ሲያዝ ምን እንደሚሰራ ራሱም አያውቅ ይሆናል።

በሁለተኛው ቀን አንድ ቀጠን ያለ፣ ወጣት የትግራይ ልጅ ሰላሳ ከሚሆኑ ተከታዮቹ ጋር ወደ ጦር ሰፈራችን መጣ። የዚህ ወጣት ጎበዝ ተከታዮች አንድ አሮጌና አንድ የዘመኑን መሳርያ ከመታጠቃቸውም በላይ በርከት ያሉ መትረየሶችም ይዘው በ 80 አህዮች የተለያዩ መሳርያዎችና የጦር ቁሳቁሶች ጭነው ነበር።

ይኼንኑ ወጣት ሹም ወደ ድንኳኔ ጋብዤው ጠጅ ቀድቼለት ታሪኩን አጫወተኝ። ይኼ ወጣት ሹም ከተከታዮቹ ጋር ከወር በፊት የጣልያንን ጦር ሲከታተሉ፣ አልፎ አልፎም ኤርትራ ግዛት ውስጥም እየገቡ በጠላት ላይ ጉዳት ለማድረስ ቢሞክሩም ሳይሆንላቸው እየቀረ እንዲሁ ተራራውን ተገን እያደረጉ አመቺ ሁኔታዎችን ሲጠባበቁ፣ ከ10 ቀን በፊት ወደ ኤርትራ ድንበር አካባቢ ከዋናው የጣልያን ጦር 150 ኪሎሜትር ርቆ ወደ እንጢቾ በሚወስደው መንገድ አፋፍ ላይ መሽጎ ሳለ፣ እታች እቆላው ውስጥ በጠባቧ ሸለቆ የጣልያን ጦር ሲርመሰመስ ያስተውልና ጣልያኖቹ ተጠቃለው ወደ ሸለቆው መንገድ መግባታቸውን ካረጋገጠ በኋላ ለውጊያ ተከታዮቹን ያዛል።

ምንም እንኳን ጦራቸው ጥቃት ከሚሰነዝርባቸው የኢትዮጵያው ጦር በመቶ እጥፍ ቢበልጥምና ዘመናዊ መሳርያ የታጠቀ ቢሆንም፣ እንዲህ በድንገት ሳያስቡት ለዚያውም ከጦር ግንባር እንዲህ በዙ ርቀው መጠቃታቸው አስበርግጎቸው ነፍሴን አውጪኝ የታጠቁትን ጥለው ይሸሻሉ። እና እነሆ ይኼው ብልህ ወጣት የጣልያን ወታደሮች በዚያች ሸለቆ ጥለዋት የሸሹትን መሳርያ በሰማንያ አህያ ጭኖ መጥቶ በጀግና ወግ በራስ ካሣ ፊት ቀርቦ ተሾሟል።

እንዲሁም ታህሳስ 13 ቀን ከወደ መቀሌ አካባቢ ቀኑን ሙሉ የመድፍ ተኩሶች እንሰማለን። ማምሻው ላይ የኛ ወታደሮች በርከት ያሉ ኤርትራውያን የጣልያን ወታደሮች የጣልያኖችን ወታደራዊ ልብስ እንደለበሱ ይዘው ቀረቡ።

ከነዚህ የኤርትራ ልጆች አፍ እንደሰማሁት አንድ ኤርትራውያን የበዙበት ክፍለጦር ያምጻና አለቆቹን ገድሎ ከነሙሉ ትጥቁ ወደ ኢትዮጵያ ጦር ሊገባ ሲዘጋጅ፣ በመሀላቸው ከጂ ኖሮ ነገሩን መቀሌ ላሉ የጣልያን ከፍተኛ ሹማምንቶች

ያደርሳል። ጣልያኖች ጥቁር ሸሚዝ ለባሽ መድፈኛ ጦራቸውን ልከው አመጸኛውን ጦር ባስተማማኝ ርቀት ደበደቡት።

ያመጸው የኤርትራ ተወላጆች ጦር ቀኑን ሙሉ ለመከላከል ሲታኮስ ውሎ ማምሻው ላይ ተረታ። እጅ የሰጡትን የኤርትራ ልጆች ያለምንም ወታደራዊ ፍርድ ረሸኗቸው። እነዚህም ራስ ካሣ ፊት የቀረቡት ኤርትራውያን ነፍሳቸውን ያተረፉ ያመጸው ጦር አባል ሲሆኑ፣ እነሆ ራስ ካሣ ፊት ቀርበው ከኢትዮጵያውያን ወንድሞቻቸው ጎን ሆነው የጠላትን ጦር ገጥመው በግፍ የተረሸኑትን ወንድሞቻቸውን ደም ይከፍሉ ዘንድ በምኒልክ ስም የሚለምኑ ናቸው። እንዲህ አይነት ዜናዎችን ግን ጣልያኖች በሚለፍፉት የጦርነት ፕሮፓጋንዳዎች ውስጥ አያስገቧቸውም ነበር።

21
በነጋሪት ድምፅ

ጣልያኖች መቀሌን በያዙ ሰሞን ጥቂት ጦራቸውን ወደ ተንቤን ልከው ያለምንም ውጊያ ተንቤንን ሲይዙ ለአለም ህዝብ "የኢትዮጵያ ህዝብ ሰራዊታችንን በደስታና በእልልታ ተቀብሎታል" ብለው ለፍፈዋል።

ጣልያኖች በተንቤን ላሉ ሹሞች ሙሉ ስልጣናቸውን ትተው፣ እንደ ወትሮው እንደ ሰላሙ ጊዜ ሀገር እንዲያስተዳድሩ ስለተዋቸው በተንቤን ምንም እንዳልተፈጠረ ህይወት ቀጥሎ ነበር።

ማርሻል ባዶሊዮ፣ ማለት ደካማውን ማርሻል ዴ ቦኖን የተካው የፋሺት ጦር ጠቅላይ አዛዥ፣ ተንቤን በጣልያን እጅ እንደወደቀች ፍጹም ርግጠኛ ነበር። ስለዚያም በጀነራል ጃቪያኖ የሚመራውን ጦር ከእንዳ ሚካኤል አንስቶ ወደ ተንቤን የላከው። ይህ በእንዲህ እንዳለ 3ኛው የኢትዮጵያ ሰራዊት ለሜኑ ጦር ግንባር ደረሰ።

የራስ እምሩ ጦር ተከዜን ተሻግሮ ከደጃዝማች አያሌው ብሩ [የሰሜን ገገር] ጦር ጋር ተቀላቅሎ፣ ከአክሱም እስከ አድዋ ባለው ግዛት ውስጥ ያለውን የጣልያን ጦር አስጨንቀው ያርበደብዱት ጀመር።

በዚህ የተነሳ ማርሻል ባዶሊዮ የጀነራል ጃቨያኖን ጦር ከተንቤን እንስቶ ለሁለተኛው የጣልያን ክፍለ ጦር ደጀን እንዲሆንለት አስቦ ወደ እንዳ ሚካኤል መለሰው። በዚህ መልኩ ማርሻል ባዶሊዮ በተንቤን 4 ሻለቃ ጦር ከጥቂት ታንክች ጋር ብቻ ነበር የተወው።

ማርሻል ባዶሊዮ የተንቤኑን ትክክለኛና እውነተኛ ሁኔታ የተገነዘበው አይመስልም። የተንቤን ሹሞች ያለምንም ውጊያ ሰራዊቱን የተቀበሉት አቅማቸውን ገምተው የኢትዮጵያ ሰራዊት ተንቤን እስኪደርስ ድረስ ብቻ ነበር።

ታህሳስ 10 ቀን ራስ ካሣ ከራስ ሥዩም ጋር ተማክረው ደጃዝማች ኃይሉ ከበደን ወደ ተንቤን በመላክ ከተንቤኑ ገገር ከደጃዝማች አማረ ጋር ከአቢ አዲ በስተጀርባ ያለውን አለታማ ተራራ እንዲይዝ አዘዙት።

በዚህ መሀል ታህሳስ 15 ቀን ዳጃዝማች ወንድወሰን ከአቢዪቶ ተነስቶ ወደ አምባራዶም ጨለማን ተገን አድርጎ በመጓዝ፣ ከደጃዝማች ጨቡድ የጭልጋው ገገር እና ከደጃዝማች አድማሱ ጦር ጋር ሊነጋጋ ሲል ተቀላቅሎ ገና በወጉ እንኳን ሳይመሽግ የጣልያን አውሮፕላኖች መጥተው በቦንብ ደበደቡት።

የጣልያን ጦር ወረድ ብሎ ከአቢ አዲ ከተማ አጠገብ ሰፍሮ ነበር። የኛም ጦር በየጊዜው በአምባራዶም ጦሩን አጠናከሯል። እንዲሁ በየቀኑ ጨለማን ተገን እያደረገ ወደ ተንቤን የሚዘልቀውን የኢትዮጵያን ሰራዊት የጣልያን ሰላይ አውሮፕላኖች አይተውት ኖሮ ለአንድ ሰዓት ያህል 7 ባለ 3 ሞተር ትልልቅ አውሮፕላኖች በትላልቅ ቦንቦች ደበደቡት።

በዚሁ ምክንያት ማርሻል ባዶሊዮ ወደ አቢ አዲ 7 ሻለቃ ጦር ከብዙ ታንኮችና ብረት ለበስ ተሽከርካሪዎች ጋር ላከ። ማርሻል ባዶሊዮ የላከው 7 ሻለቃ ጦር አቢ አዲ ከመድረሱ በፊት ታህሳስ 18 ቀን ከ10 ሰዓት በላይ በፈጀ ውጊያ ጣልያኖች መሸነፍ ብቻ ሳይሆን እስካሁን ይዘዋት የነበረችውን አምባ ጸለሪን ለቅቀው ወደ አቢ አዲ መሸሽ ተገደዋል። ጣልያን ጸለሪን ለማስመለስ ከፍተኛ ውጊያ ቢያደርግም እስካሁን በእጁ የነበረችውንም አቢ አዲን በሽንፈት ለቆ ወደ ወረዩ ማፈግፈግ ተገዷል። በዚያ የነበረው ሰራዊታችን ዋናው የራስ ካሣ ጦር እስከደረሰበት ቀን ድረስ አቢ አዲን በታላቅ ወኔ እየተዋጋ በደሙ በእጁ አቆይቷታል።

በዚሁ ጦርነት የተካፈለ አንድ ኢትዮጵያዊ ወታደር ኋላ ላይ እንዳጫወተኝ ጣልያኖች አምባ ጸለሪን መልሶ ለመያዝ በከባድ መትረየሶች እየታገዙ ከሰማይ

የአውሮፕላን ቦምቦች እንደ ነሐሴ ዝናብ ቢያወርዱባቸውም፣ ኢትዮጵያውያን ወታደሮች እንዲትም ስንዝር ወደኋላ አላፈገፈጉም ነበር።

ምንም እንኳ በርከት ያሉ ኮማንዶዎች ወደ ላይ መዝለቅ ቢችሉም በየቋጥኙ ስር የመሸገው የኢትዮጵያ ወታደር ፋታ አልሰጣቸውም ነበር። አንድ የኢትዮጵያ ወታደር የሚተኩሳት ጥይት የአንድ ጣልያን ወታደር ሞት ማለት ነበረች። ኢትዮጵያውያን ፍጹም እርግጠኛ ሆነው ኢላማቸውን መምታት ካልቻሉ አይተኩሱም። ለምንስ ዝም ብለው ይተኩሱ? የሶስት ጥይት ዋጋ አንድ ማርትሬዛ ብር በሆነበት ጊዜ፣ አንድ ብር የአንድ ወታደር የወር ደሞዝ በሆነበት ሁኔታ።

ኢትዮጵያውያን ተኩስ አቁመውና ጦራቸውን እየወረወሩ በጋሻቸው እየመከቱ በጣልያኖች መሀል በመግባት የጠላትን ጦር አንገት በጎራዴያቸው ይቀሉት ጀመር። በጁ በእንዲህ አይነት የኢትዮጵያውያን የጀግንነት ውጊያ የተደናገጠው የጣልያን ጦር ያለውን ከባድ መሳሪያ ጥሎ ቢያንስ አንገቱን ለማዳን ይሸሽ ነበር። ኢትዮጵያውያን የሚሸሸውን የጣልያን ጦር እያሳደዱ ከአቢ አዲ ሲያበሩት 8 ሻለቃ ጦር ወደ ወረዩ በመሸሽ ህይወቱን አትርፏል።

በታህሳስ ወር ሁለተኛ አጋማሽ ላይ ጣልያኖች የራስ ካሣንና የራስ ሙሉጌታን ጦር በአውሮፕላን መደብደባቸውን ቀጥለዋል። ከኢትዮጵያም ወገን በአብዛኛው በዚያው ኋላቀር አውሮፕላን መቃወሚያ ሲንጣጡ ቢውሉም፣ የጣልያን አውሮፕላኖች እንደ ሁልጊዜው ባስተማማኝ ከፍታ ላይ ስለሚበሩ ምንም የሚፈጠር ነገር አልነበረም። ጦራችን እስካሁን አንድ እንኳ የጠላት አውሮፕላን የመጣል በለስ አልቀናውም።

አልፎ አልፎ ወታደሮች መጠናቸው የተለያየ ከጣልያን አውሮፕላኖች ላይ የወደቁ ቆርቆሮዎች ይዘው ይመጡ ነበር። ይኼ የሚያሳየው ጦራችን የሚተኩሳቸው የአውሮፕላን መቃወሚያ ጥይቶች ከፍተኛ ጉዳት ባያደርሱም ኢላማቸውን ይመቱ እንደነበር ነው። በተጨማሪ የፋሽቱ ጦር ጠቅላይ መምሪያ አልፎ አልፎ በምንጠልፈው ራዲዮ እንደምንሰማው አውሮፕላኖቻቸው ከፍተኛ ጉዳት ደርሶባቸው በመከራ ወደ ጦር ሰፈራቸው ይመለሱ እንደነበር አምነው ይናገሩም ነበር።

ታህሳስ 19 ቀን ምሽት በጦር ሰፈራችን የተለመደው የክተትና የተነስ ነጋሪቶች ይጎሰሙ ጀመር። ከያቅጣጫው ጡሩንባዎች ይነፋሉ፤ ከበሮዎች ይደለቃሉ። ይኼ ደግሞ ለሰራዊታችን ድንኳንህን ነቅለህ ተነስ፤ ወደፊት መጓዛችን ነው ማለት ነው።

ወዴት? ማንም አያውቅም። ማንም ምንም አይጠይቅም።

ራስ ካሣ ነጋሪት ጎሳሚያቸውን አስጠርተው ነጋሪቶች እንዲጎሰሙ አዘዙ። ቀጥለውም አንዱን ሹማቸውን ጠርተው ጦሩን ይዞ ቀድሞ እንደ ቀዳሚ ጦር እንዲሄድ አዘዙት። በቃ ራስ ከዚህ በላይ ስለጦራቸው መጨነቅ የለባቸውም። ይኼ

በሙቶ ሺዎች የሚቆጠረው ጦራቸው የሚንቀሳቀሰው በየግሉ ከራሱ ሹማምንቶች፣ መኳንንቶችና የጦር አበጋዞች ጋር ራሱን ችሎ ነው።

የአንዱ ደጃዝማች ጦር የሌላውን ደጃዝማች ጦር ተከትሎ፣ የአንዱ ፊታውራሪ ጦር የሌላውን ፊታውራሪ ጦር ጭራ ይዞ እየተከተለ፣ ሌላውን የፊታውራሪ ጦር በጀርባው ደርቦ፣ እንዲህ እንዲህ እያለ፣ ያንዱ ሹም ጦር የሌላውን ሹም ጦር እየተከተለ፣ መጨረሻ በሌለው አኳኋን እንደአባይ ወንዝ እየተጠማዘዘ የሚጎርፈው ጦር ተያይዞ ያለምንም ቅንብር እና ስነስርአት ይነጉዳል።

ወታደሮቻችን ድንኳኖቻቸውን እየነቃቀሉ እቃዎቻቸውን ይቋጥራሉ። እድለኞች ያሉቻቸውን ቋጠሮ በከሱት አህዮቻቸው ላይ ይጭናሉ። እድለቢሶች የጭነት ከብቶቻቸው ባለፉት ቀኖች በወረዱት የቦምብ ዝናብ የሞቱባቸው የቀረች ንብረታቸውን በጀርባቸው አዝለው፣ በጭንቅላታቸው ተሸክመው፣ ጦራቸውን ተከትለው ይጓዛሉ።

ትናንት ማታ ከአዲሱ የጦር ሰፈራችን ብንደርስም፣ ጦራችን ማለቲያ በሌለው የጉዞ ሰንሰለት ተያይዞ ቢንቀሳቀስም፣ ከሁለት ቀን በኋላም አሁንም አይቦታ ጦር ሰፈር ገና ድንኳኖቻቸውን ያልነቀሉ ወታደሮቻችን ከትግራይ ሽፍቶች ጋር የሞት ሽረት ትግል ያካሂዱ ነበር።

ራስ ካሣ ከራስ ሥዩም ጋር በጋራ አንድ ድንኳን ሙዲኘ ከተባለች ቦታ ላይ አስተክለው አረፉ። ይቺ የተራራ ጫፍ ከአምባላጌ እስከ መቀሌ ከተማ ድረስ አይታ ነበራት። ወታደሮቻችን የኛንም ድንኳን ከራሶቹ አጠገብ አቆሟት። የኛ ድንኳኖች ከቆሙበት ቦታ ስር የቡየ ወንዝ ተዘርግታ ትታያለች። ከዚች ወንዝ ባሻገር በጥሩ የጦር ሜዳ መነጽር በሺዎች የሚቆጠሩ የጠላት አመዳም ድንኳኖችን ማየት ይቻል ነበር። ሁለቱ ኢትዮጵያውያን ቴሌግራፊስቶች ኂላቀሯን አንቴና ከኛ ድንኳን አለፍ ብላ ካለች አንድ ጉብታ ላይ አቆሟት።

በሁለተኛው ቀን ታህሳስ 20 ቀን ከሩቅ የሚነጉድ የአውሮፕላን ድምጽ መስማት ጀመርን። ድምጹ እየቀረበ በመጣ ቁጥር ወደ ሰማይ ብናንጋጥጥም፣ ምንም ማየት አልቻልንም ነበር። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ አንድ በግምት 14 ዓመት የሚሆነው የአባቱን ጠመንጃ ያዥ ህጻን፣ ከፍ ብለው የሚበሩትን የጣልያን አውሮፕላኖች አሳየኝ። አዎ በጣም ከፍ ብለው በሰማዩ ላይ የሚበሩት የጠላት አውሮፕላኖች እንደ ትንንሽ ነጠብጣቦች ሲያንጸባርቁ ቆይተው በግልጽ እይታ ውስጥ መግባት ጀመሩ።

በውጊያ አሰላለፍ ከመቀሌ ተነስተው ወደ ደቡብ የሚበሩት እነዚህ አውሮፕላኖች አሰላለፍ አንድ አውሮፕላን ከፊት ሆኖ ከጀርባው እንደ ክንፍ በተዘረጋ መልኩ አስራ ሁለት፣ ቀጥሎ ስድስት፣ ቀጥሎ ሶስት፣ በመጨረሻ አምስት ሆነው ነው የሚበሩት። ወዴት ነው የሚበሩት? ወደ ደሴ? ንጉሠ ነገሥቱ ከደሴ ድንኳናቸውን ነቅለው ወደ

ኮረም ጉዞ መጀመራቸውን ሰምተናል። ወደ አዲስ አበባ? ወደ አዲስ አበባ ከሆነ አዲስ አበባ ለአውሮፕላን የቦንብ ድብደባ ፍጹም ዝግጁ አልነበረችም።

ሃያ ሰባት የውጊያ አውሮፕላኖች ለግዳጅ ተሰማርተዋል። ጣልያኖች፣ ለመጀመሪያ ጊዜ እንዲህ በአንድ ጊዜ ይኼን ያህል የውጊያ አውሮፕላኖች ለአንድ ድርጊት ሲያሰልፉ መቼም ለከፍተኛ ድርጊት መሆን አለበት። ብቻ ሁላችንንም የሆነ ነገር ወረረን። በዚህ ላይ እነዚህ 27 አውሮፕላኖች በረራቸው ወደ አዲስ አበባ ከሆነ፣ አዲስ አበባ ለአውሮፕላን የቦምብ ድብደባ ፍጹም ዝግጁ አይደለችም።

በኔ ትዕዛዝ አንዱ ቴሌግራፊስት ቴሌግራፍ ከማስተላለፊያው መሳርያ አጠገብ ቁጢጥ ብሎ የቴሌግራፉን ቁልፍ ተጫነው። ወዲያው ቲ... ቲ... ቲ... ዳቲ...ቲ ዳቲ...ቲ ትብ... ትብ... ትብ... የኤሌክትሮ ማግኔቱ ሞገድ በአየር ላይ መንጎድ ጀመረ። የውጊያ አውሮፕላኖችን ቀድሞ አዲስ አበባ መድረስ አለበት። ...ቲ ....ቢ አዲስ አበባን መጥሪያ ምልክታችን ነበረች። ወዲያው ቴሌግራፊስቱ መልዕክት መቀበያው ቦታ ላይ ተቀምጦ አዲስ አበባ ይመልስ እንደሆነ መጠባበቅ ጀመረ። የኛ መቀበያ ማዳመጫችን ደንቁሯል፤ የመቀበያው መሳርያ ድንጋይ አልቋል፤ ሞቷል። አዲስ አበባ ያለው ቴሌግራፊስት በቦታው ተቀምጦ እንደሚሰማን ተስፋ ከማድረግ በስተቀር ሌላ አማራጭ የለንም። መላክ እንችላለን። የመላኪያው መሳርያ ዲናሞ በቤንዚን የሚሰራ ሞተር አለው።

ያለማቋረጥ እየደጋገምን "ተጠንቀቁ! ተጠንቀቁ! 27 አውሮፕላኖች ወደ አዲስ አበባ እየበረሩ ነው። ተጠንቀቁ! ተጠንቀቁ! 27 አውሮፕላኖች ወደ አዲስ አበባ እየበረሩ ነው። ተጠንቀቁ! ተጠንቀቁ!" ብቻ ያለማቋረጥ ለግማሽ ሰዓት ያህል አስተላለፍን። እኛ ይኼን ስናስተላልፍ የጠላት አውሮፕላኖች ኮረምን አልፈው ነበር።

ብዙ ቆይቶ እንደሰማሁት አዲስ አበባዎች የኛን ማስጠንቀቂያዎች በትክክል ሰምተው አውሮፕላኖችን ቢጠብቁም አውሮፕላኖቹ ድርሽ ሳይሉ ቀሩ። ከሁለት ሰዓት በኋላ አውሮፕላኖቹ እንዳሰላለፋቸው ወደ መቀሌ ተመለሱ። ሁለት አውሮፕላኖች ግን ይጎድሉ ነበር። ተመትተው ወድቀው ይሆን? ትናንት የጣልያን ራዲዮ ጣቢያ እንዳወራው በርካታ የጣልያን ተዋጊ አውሮፕላኖች በአሸንጌ ሐይቅ አካባቢ በጉዞ ላይ የነበረውን የኢትዮጵያን ሰራዊት ክፉኛ እንደደበደቡት በጉራ አወራ።

ማምሻው ላይ ከአዲሱ የደሴ ራዲዮ ጣቢያ ጋር ግንኙነት አደረግን ።ይቺ ራዲዮ ጣቢያ የንጉሠ ነገሥቱ ራዲዮ ጣቢያ መሆኗ ነው። ይቺው የራዲዮ ጣቢያ ጦርነት ከተጀመረበት ቀን ጀምሮ ለመጀመሪያ ጊዜ የተቀበለፈ መልዕክት ለራስ ካሣ አስተላለፈች። በተቀበለፈው መልዕክቷም፣ "ንጉሠ ነገሥቱ በትርቡ ወደ ሰሜን ጦር ግንባር ዘመናዊ መሳሪያ ከታጠቀው ጦራቸው ጋር በቤልጂየሞች የሰለጠነውን የክብር ዘበኛቸውን ይዘው እንደሚዘልቁ አሳወቁን። ቀጥለውም 1,500 የሚሆኑ የጉራጌ

ተጠሳጆች ከደሴ ጀምረው ወደ ኮረም፣ ከዚያም አልፎ ወደ አሸንጌ ሐይቅ የሚወስደውን መንገድ ሌት ተቀን በመስራት ላይ መሆናቸውን ጨምረው አስረዱኝ።

ሌሊቱን ሙሉ ጠንካራና ኃይለኛ መብራት ከታች ከጣልያኖች የጦር ሰፈር በተወሰኑ ጊዜዎች ልዩነት ይበራብናል። ይኼው አይን የሚወጋ መብራት አልፎ አልፎ ወደ ድንኳኔም ዘልቆ ስለሚገባ መተኛት አልቻልኩም። በብዙ ትግልና ራስ ማባበል ሸለብ አደረገኝ። ወዲያው በህልሜ ወደ ትውልድ ሀገሬ "ቼኮስሎቫኪያ" የገባሁ ወይም እዚያው ያለሁ ይመስለኛል። እንዲሁ በህልሜ፣ በጣፋጩ ህልሜ፣ ብዙ ሳልገፋበት አስደንጋጭ የነጋሪት ድምጽ ቀሰቀሰኝ። ቀስ በቀስ አካባቢዬን ስቃኝ ገና በመንጋት ላይ መሆኑን ተረዳሁ። የነጋሪቱም ድምጽ "ተነሱ! ድንኳኖቻችሁን ንቀሉ" ነበር።

እኛ እንዲህ ሳይነጋ በፊት ተነስተን፣ ድንኳኖቻችንን ነቅለን፣ ወደ መሸሸጊያችን ዋሻ መግባት አለብን። አለበለዚያ ፀሐይን ተከትለው እንደሞራ የሰማይ ጌታ የሚሆኑት የጣልያን አውሮፕላኖች ሲሳይ መሆናችን ነው። ይኼው ሰሞኑን መቀሌ ያሉት የጣልያን ጀነራሎች የራስ ምታት የሆነው በመቶ ሺዎች የሚቆጠረው የራስ ካሣ ጦር የገባበት መጥፋት ጉዳይ ነው።

ከድንኳኔ ስወጣ ከድንኳኗ በራፍ ሁለት ድንቅ ነገሮች ገጠሙኝ። አንደኛው ከብዙ ቀናት በኋላ በትልቅ ገበቴ አንበሳ ውሃ ሞልቶ አቀረበልኝ። ሰውነቴን ውሃ ሲነካው ነው። መቼም አንበሳው ከእኩለ ሌሊት በፊት መነሳት አለበት፤ እታች ወንዝ ወርዶ ይኼን ውሃ እንድታጠብ ሲያመጣልኝ። አይ ያንበሳው ነገር!

ሁለተኛው ደግሞ ምንጊዜም ልረሳው የማልችለው የኢትዮጵያ ተራሮች እይታ ነበር። ተራሮች በነጭ ጉም ተሸፍነው አሳይ ሰማዩ ጥርት ብሎ ሳየው፣ ያለሁበት ተራራ ጭልጥ ባለ ውቅያኖስ ውስጥ ያለች ትንሽ ደሴት ትመስል ነበር። ነጩ ጉም ሁሉንም ሸለቆዎች ስለሸፈናቸው የአምባራዶም የተራራ ጫፍ ከውቅያኖስ ውስጥ የበቀለ ትንሽ ቋጥኝ ወይም ትንሽ ድንጋያማ ደሴት ይመስል ነበር። ያለወትሮው ፍጹም ፀጥ ያለ ሰላም ሰፍኖ ነበር።

ገና አሁን ነው ዛሬ ታህሳስ 24 መሆኑ የታወቀኝ። አዎ ዛሬ በመላው አለም ከዛሬ ሁለት ሺ ዓመት በፊት የሰውን ልጅ ለማዳን የተወለደውን፣ የእግዚአብሔርን የፈጣሪን ልጅ የእየሱስ ክርስቶስን የልደት በዓል ይከበራል። ያስታውሳል። አዎ ዛሬ በአለም ባሉ ቤተ ክርስቲያናት ሁሉ "ሰላም ለሰው ልጆች ሁሉ" እየተባለ ይጸለያል።

አዎ ሰላም ለሰው ልጆች ሁሉ? ታዲያ በነዚህ በመቶ ሺህ በሚቆጠሩ ባላገሮች መካከል እንደሰው ልጅ የሚቆጠር ጠፍቶ ነው ሰላም የተነሱት? አዎ ጥቂት ፋሽስቶች በሞሶሎኒ እየተመሩ ታሪክ ለመፃፍ ስለተመኙ ብቻ ይኼ ሁሉ ሰው ማለቅ አለበት?

አዎ ሞሶሎኒና ተከታዮቹ ታሪክ ይፅፋሉ። ግን እንደሚመኙት ሳይሆን፣ የሚፅፉት ታሪክ በደም የተጨማለቀ፣ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ የራሳቸውን ሰው ጭምር

ጨፈጨፈ! ምንጊዜም ቢሆን ማንም ይቅር የማይለውና አለም የማይረሳው ጥቁር ታሪክ ነው፤ አሳፋሪ ታሪክ።

ማታ በደጃዝማች አበራ ትንሽ ዋሻ ውስጥ እኔና ሁለቱን አውሮፓውያን ጓደኞቼን አቶ ብረየር እና ኮሎኔል ኮኖቫሎቭን ጨምሮ ተቀምጠናል። በዋሻዋ ውስጥ አንድ ትንሽ ሳጥን ላይ ነጭ ፎጣ ተነጥፎበት፣ አንድ ቅጠል የሌላት ጭራሮ ላይ ጥጥ በታትኖባት፣ በመጠኑም ቢሆን የገናን ዛፍ የምታስታውስ ጭራሮ ተቀምጣለች። ጓደኛችን አቶ ብረየር በእውነት አስደንቆናል። ቀኑን ሙሉ ሲደክምባት የዋለው። ሻማ በጦር ሰፈራችን ሲፈልግ ውሎ በመጨረሻ አንድ ቁስ ሁለት ጫፍ አለጉት አነሱት አበራችው።

ደጃዝማች አበራ፣ የራስ ካሣ ሁለተኛው ልጅ፣ ለኛ የፈረንጆች ገና አንድ በግ አረደልን አሽከሮች አበሳስለው እስኪያመጡት ድረስ ጠጃችንን ይዘን እየተጫወትን ነው። ደጃዝማች አበራ ከዚህ ግብዣ በተጨማሪ በኮባ ቅጠል ጠቅልሎ ስጦታዎች ሰጠን። በእውነቱ የአውሮፓውያንን ባህል አልረሳም።

እኔ ልክ እንደ ህፃን ልጅ እየቦረቅሁ ስጦታየን በመጣደፍ ከፈትኩት። አንድ ፓኮ ሲጋራ ነበረች። በዚህ ጦር ሜዳ አንድ ፓኮ ሲጋራ ከሚሊዮን ብር ይበልጣል። ማጨስ ስላባብቼ ነበርና እየተጣደፍኩ የመጀመሪያዋን ሲጋራ ለኮስኩ። ከዚህ ሁሉ ጊዜ በኋላ ነበር ሌሎች የደረሳቸውን ስጦታ ለመቃኘት ቀና ያልኩት። ሁላችንም ተመሳሳይ ስጦታ ነበር የደረሰን። ሁላችንም ከመጠን በላይ ተደስተን ነበር። ሁለቷን ፍሬ አከታትዬ ካጨስኩ በኋላ ነበር ለደጃዝማች አበራ ታላቁን ምስጋናዬን ያቀረብኩለት።

እንዲህ በደጃዝማች አበራ ዋሻ ተቀምጠን ጠጃችንን እየጠጣን፣ ሲጋራችንን እያጨስን ስንጫወት ሁላችንም በትዝታ በጣም ሩቅ ወዳለው አገራችን ነጉደን፣ ዘመዶቻችንን እያስታወስን በትዝታ ባህር ተዘፍቀን ነበር በስሜኑ የጦር ግንባር የገናን፣ የፈረንጆችን ገና ያከበርነው።

እኛ እንዲህ በትዝታ ርቀን ከጦር ሰፈራችን ራቅ ብሎ አልፎ አልፎ ድው! ድው! ድው! የሚሉ የተኩስ ድምጾች እንሰማለን። እነዚህም የትግራይ ሽፍቶች ለዘረፋ ይመጣሉ። ምን ያድርጉ! ጣልያኖች በመሳሪያና በገንዘብ ይረዷቸዋል። ለዚያም መሰለኝ በደጃዝማች አበራ ዋሻ ደጃፍ ላይ ሁለት አነስ አነስ ያሉ መትረየሶች የተጠመዱት።

የትግራይ ሽፍቶች ብዙ ጊዜ በድፍረት እስከ ጦር ሰፈራችን እምብርት ድረስ ዘልቀው ለመዝረፍ ሞክረዋል። ሽፍቶችን ከሌላው የባላገር ወታደር መለየት አስቸጋሪ ነው። ሽፍቶቹም ልክ እንደ ባላገሮቹ ወታደሮች ሁሉ የሚለብሱት ያደፈ ሸማ ነው። እና በመጀመሪያ እይታ ማንም ሰው ሽፍቶች መሆናቸውን መገመትም፣ መለየትም አይቻለውም።

በገና ዕለት፣ በጌታ የልደት ቀን እንኳ በሰሜኑ የጦር ግንባር ሰላም የለም። አበራ ቀሻ አንድ አሽከር እየለከለከ መጥቶ በነጠላው ጫፍ አፉን ሸፍኖ ለደጃዝማች አበራ በጆሮው የሆነ ነገር ሹክ አለው። አፍን በነጠላ፣ በለበሰው ሽማ ጫፍ ሸፍኖ ማውራት የኢትዮጵያ ፕሮቶኮል ያስገድዳል። ምን ተፈጠረ? ብዬ ጠየቅሁ።

ደጃዝማች አበራ እንዳስረዳን የማለዳውን ጥቅጥቅ ያለ ጉም ተጠቅመው የጣልያን ወታደሮች ወደ አፍንላ መጠጋታቸውንና በአምባራደም ተራራ ላይ ያለው የደጃዝማች ወንድወሰን ጦር ድጋፍ ይፈልጋል። ቀጥሎም ሳቅ እንደማለት […] ወንድወሰን ምናልባት ጣልያኖች ጥቃት ይሰነዝሩ ይሆናል ብሎ ስጋት ይዞታል። ይሁን እንጂ በሚቀጥሉት ሁለት ቀናትም ጣልያኖች ጥቃት ሳይሰነዝሩ ቀሩ።

ከሰዓት በኋላ ደጃዝማች ወንድወሰን አባቱን ጥየቃ ወደ ሰፈር መጣ። ይኼን የሰማነው ራስ ካሣ የላኩት አሽከር ወደ ቀሻው፣ ማለት ከፍተኛ መኳንንቶች ወደሚሰበሰቡበት ቀሻ፣ ባስቸኳይ ደርሰን ከደጃዝማች ወንድወሰን ፊት እንድንቀርብ ትዕዛዝ ሲያደርሰን ነበር።

ለምን እንደተፈለግን ለማወቅ እየጓጓን በችኮላ ወደ ቀሻዋ አመራን። ከራሶቹ ቀሻ እንደደረስን ወጣቱ ደጃዝማች በጉጉት ያለ ትግስት እንደሚጠብቀን ተነገረን። ደጃዝማች ወንድወሰን ወደተቀመጠበት ቦታ፣ ከቀሻው በራፍ አልፍ ብሎ ዝቅ ወዳለው ቦታ ወረድን። ደጃዝማች ወንድወሰን እንደተቀመጠ በጉልበቶቹ መሀል መሬት ላይ የተደገፈ የሆነ ሞላላ ነገር ይዟል።

“የኔ ወታደሮች ይችን ነገር አምጥተው ሰጡኝ” አለ፤ የኢትዮጵያውያንን ባህል ማለት ሁለት ሰዎች ሲገናኙ ረዘም ላለ ጊዜ የሚለዋወጡትን ሰላምታ በመጣስ፣ በጉልበቶቹ መሀል ደግፎ የያዘውን ሞላላ ነገር እያሳየን።

“ቦምብ ነው” አለ ኮሎኔል ኮኖቫሎቭ። ወዲያው ቦምቧን ባይኑ እየቃኘ በመቀጠል፣ የት አደረጋችሁት ጭንቅላቷ ላይ ያለውን ድቡልቡል ነገር? ማፈንጃውን ሲል ጠየቀ። ጉማጅ ግንድ የምትመስለው ነገር ሙሉ በሙሉ በቦምብ መርዝ የተሞላች ነች። ይሁን እንጂ የብረት ልብሷ በፈነዳች ጊዜ ወፍራሙ ብረት ወደ ብዙ ቁርጥራጭ ብረትነት በመለወጥ ነው ያገኘውን ሁሉ የሚገነጣጥለው የሚሰነጣጥቀው። የቦንቧ ወፍራም የብረት ካፖርት ይቀራል።

ወጣቱ ደጃዝማች በብልጠት ይስቃል። ደጃዝማች ወንድወሰን በጉልበቱ መሀል የያዛት ሞላላ ነገር ጣልያኖች በአውሮፕላኖቻቸው የሚወረውሯት ቦምብ እንደሆነች አሳምሮ ያውቃል።

ወዲያው ፊቱን ወደ አሽከሮቹ ሲያዞር ሁለቱ አሽከሮቹ የቦምቧን የብረት ልብስ አመጡለት። በሁለቱ አሽከሮቹ እየተረዳ ቦምቧን ወደ ልብሷ ሲከታት ሞከረና የሆነ ነገር ትዝ ብሎት ወደ ኪሱ ገብቶ ቡጢ የሚያህለውን የቦንቧን ማፈንጃ ከኪሱ አወጣ።

ወንድወሰን በቀጥታ ማፈንጃዋን በቦምቧ አናት ላይ እየሸረበ ካስገባ በኋላ ቦንቧን […] ለመመለስ ትግሉን ሲቀጥል፣ ትንሹ ደጃዝማች አበራ እንደቆመ “ወንድወሰን ሊፈነዳ ይችላል'ኮ?” አለው። ትልቁ ደጃዝማች ታናሽ ወንድሙን በፌዝ […] ሳቅ አለና “ሊፈነዳ ይችላል?” የአበራን ቃል ደገመና በመቀጠል “ለምን […] ትፈነዳለች? ሲወረውሯት ያልፈነዳች?” አለና መግጠሙን ቀጠለ። ቀጥሎም “እውነቱን ንገረኝ ካልከኝ ልንገርህና የኔ ሰዎች ያገኟት ከሳምንት በፊት ነበር። […] ቀን ጀምሮ ሁሌም ይዣት ነው የምዞረው። ደግሞም ሁለት ቀንና ሌሊት […] አይቼ ነው እንዲህ የፈታታኋት” አለ በታላቅ ኩራት።

ደጃዝማች አበራ ወደሰፈር ስንመለስ አንድ ምንጊዜም የማልረሳውን የታላቅ ወንድሙን ግዴለሽነት አሳሰበኝ። “ወንድወሰን የማይገነዘበው ነገር ቢኖር እዚች ቀሻ ውስጥ ይቺ ቦምብ ብትፈነዳ፣ በሰሜኑ ጦር ግንባር ሉሉ የተባሉትን ራሶች፣ ደጃዝማቾች፣ ፊታውራሪዎች ወዘተ. ልታጠፋ መቻሏን ነው፤ ብቻ ምን አለፋህ ሰራዊታችንን ያለ መሪ ሊያስቀረው እንደሚችል አይገነዘብም” አለኝ።

እውነቱን ነበር። ያቺ ቦምብ በዚያች ቀሻ ብትፈነዳ ኖሮ ያንን ሁሉ የጦር አበጋዝ በአንድ ጉድጓድ ትቀብረው ነበር። ጦራችንም ያለ መሪ የውጊያ ብቃቱና ሞራሉ ይወድቅ እንደነበር ጥርጥር የለውም።

በኋላ ላይ እንደ ሰማሁት በደቡቡ የጦር ግንባር አንድ አሜሪካዊ ዶክተር፣ “የራስ ነሲቡ ጦር ዶክተር”፣ እንዲህ ከአንዲት ካልፈነዳች ቦምብ ጋር ሲጫወት ፈንድታበት ሞቷል።

22

የአውሮፕላን ቀብር

በሙጂ ተራራ ላይ እስከመሸግን ድረስ ጣልያኖች ሰላም የሰጡን ይመስላል። የጠላት ሰላይ አውሮፕላኖች በየቀኑ የተራራውን ጫፍ እየዞሩ የኢትዮጵያን ሰራዊት ቢፈልጉም የራስ ካሣን ጦር ሊያገኙት አልቻሉም። ይሁን እንጂ የደጃዝማች ወንድወሰንን እና የደጃዝማች ጨቡዴን ጦር፣ በደቡብ ምስራቅ አምባራዶም የመሸገውን፣ በየቀኑ ይደበድቡት ነበር።

ጦርነቱ እንደተጀመረ የጣልያን አብራሪዎች ይበሩ የነበሩት ከፍ ባለና አስተማማኝ በሆነ ርቀት ነበር። ቀስ እያሉ የኢትዮጵያው ሰራዊት የያዘው አሮጌና ኋላ ቀር አውሮፕላን መቃወሚያ ምንም ጉዳት እንደማያደርስባቸው ሲያዩ ዝቅ እያሉ መብረር ጀመሩ።

በመጨረሻዎቹ የታህሳስ ወር ቀኖች የጣልያን አብራሪዎች ዝቅ ብለው በመብረር ትናንሽ ቦንቦችን እየጣሉ በጫካ ውስጥ የሚሽሎከለከውን የገበሬ ሰራዊት አውሮፕላኗ ላይ በተጠመደ መትረየስ ይለቅሙት ጀመር።

የጣልያን አውሮፕላኖች መቶ ሜትር በማይሞላ ከፍታ ላይ ዝቅ ብለው በሸለቆዎች ውስጥ ሳይቀር ይበሩ ነበር። ብዙ ጊዜ እንዲህ ዝቅ ብለው እያበረሩ እታች

ቆው ውስጥ ሲደበድቡ ይቆዩና ከፊታቸው ካለው ተራራ ጋር ከመጋጨታቸው ፊት አውሮፕላኗን ሽቅብ ያስነሷታል።

አንድ ቀን ታዲያ ስድስት አውሮፕላኖች በዚሁ መልኩ ዝቅ ብለው በመብረር ኢትዮ አቶላው ውስጥ ያለውን ሰራዊታችንን ሲደበድቡ ቆይተው፣ አምስቱ አውሮፕላኖቻቸውን አፍንጫ ቀና አድርገው ሲበሩ፣ ስድስተኛው አፍንጫውን አንስቶ መብረር ሲሞክር በቂጡ እንዘጭ ብሎ ቀረ። ለሁለተኛ ጊዜ ለመነሳት ሲሞክር የቀኝ ክንፉን ሰበረ። በዚህ ጊዜ የኛ ሰራዊት ጠመንጃውን እየተኮሰ ቁልቁል ሲንደረደር ምንጊዜም የማልረሳውና እስከሞት ሊገባኝ የማይችል ነገር ተፈጠረ።

አምስቱ አውሮፕላኖች ከመንገዳቸው ተመልሰው የወደቀውን ጓደኛቸውን ቁልቁል ሲያዩ ቆይተው፣ አንደኛው በጣም ዝቅ ብሎ በመብረር በወደቀው አውሮፕላን ላይ ከመቶ ኪሎ ግራም ቦምብ በላይ ጣለበት። ሌሎቹም አራቱ አውሮፕላኖችም ልክ እንደ ጓደኛቸው ዝቅ ብለው በየተራ በመብረር በዚያ በወደቀ ጓደኛቸው ላይ የቦምብ ሸክማቸውን አራገፉበት።

ማምሻው ላይ ያ አውሮፕላን ወደ ወደቀበት ቦታ ወረድኩ። ከዚያ ባለ ሶስት ሞተር አውሮፕላን የቀረ ነገር ቢኖር ጥቂት ቁርጥራጭ ብረቶችና እንደ ጎርፍ የወረደ ደም ብቻ ነበር ። በኋላ ብዙ ተመሳሳይ ታሪኮችን ሰምቻለሁ።

ታህሳስ 26 ቀን የጦር ሜዳ ከበሮዎች ይጎሰሙ ጀመር። ወደፊት መጓዛችን ነው። የተወሰኑ ግዴለሾችና ደፋሮች ገና ማምሻው ላይ ጉዞ ጀምረዋል። በትካሻቸው ላይ ነጭ ሸማቸውን ለብሰው ሲርመሰመሱ የጣልያን አውሮፕላኖች ሰላዩዋቸው። እዚህ የተረገሙ አውሮፕላኖች እየተመላለሱ የቦንቡን ዝናብ አወረዱባቸው። ከዚች ቅጽበት ጀምሮ አውሮፕላኖቹ እየተመላለሱ በሙጃ እና በደብረ አይሊ መካከል ያለውን መሬት በተደጋጋሚ በትናንሽ ተሰፈንጣሪ ቦንቦች ደበደቡት።

ዋናው የራሶች ጦር ሁሌም ከመሸ በኋላ ነበር የሚጓዘው። ለጉዞው ይረዳው ዘንድ ከጠዋት ጀምረው ወታደሮች ብዙ ችቦዎችን፣ ክትክታዎችን እየቀጠቀጡ ያስሩ ነበር። ይኼን ለረጅም ሰዓት የሚበራ ችቦ ለኩሶ ሌሊት የሚጓዘውን የኢትዮጵያን ሰራዊት ላየው ሰው፣ ፍጹም ለአይን ማራኪ ነበልባል የሚተፋ ዘንዶ ይመስል ነበር።

እኛም የጦር ሰፈራችንን ለቀን የመጨረሻውን የራሶችን ጦር ተከትለን መጓዝ ጀምረናል። ምንም እንኳን ጀንበር መጥለቅ ብትጀምርም ከኋላችን የቦምብ ፍንዳታዎች ድምጽ ሰማን። አምስት የጣልያን አውሮፕላኖች በአናታችን ላይ በረው ሲያልፉ አብራሪዎቹ እንዴት እንዳላዩን ባላውቅም ለቀን የወጣነውን ሰፈር ነበር የሚደበድቡት።

ከሁለት ሰዓት ጉዞ በኋላ ጨረቃም ከተራራው ጀርባ ገብታ ስለተደበቀች

በጨለማ መጓዝ ጀመረናል። ወይ ደግሞ የተከተልነውን የደጃዝማች አበራን ጦር ልንደርስበት አልቻልንም። እኛንም ያጀቡን ወታደሮች ችቦ አልነበራቸውም።

አሁን ከተራራው ወርደን ወደ ሰፊው ሸለቆ እየገባን ነው። ከፊታችን በርካታ ያሉ ወታደሮች ትንሽ እረፍ ብለውና በጉዞው ለመቀጠል ሰብሰብ ብለው እየጎደዱ ተቀምጠዋል። ዋናው ጦር ከፊታቸው መጨረሻ እንደሌለው ዘንዶ እየተፋ ሲምዘገዘግ ከሩቅ ይታያል። ከፊት ለፊታችን ፈረሰኛ ጦር እየሄደ ነው። ከፈረሰኞቹ መሀል የወጣቱን ደጃዝማች አበራን ድምፅ ሰይቼ አወቅሁት። እሱ ደጃዝማች አበራ ነው። እኔ መሆኔን ከሩቅ ሲለይ "አይ... ፈረንጆች" እያለ ፈረሱን አዙሮ መጥቶ ተቀበለንና ከፈረሰኛው ጦሩ ጋር ተቀላቅለን መጓዝ ጀመርን።

ከፈረሰኛው የደጃዝማች አበራ ጦር ጋር ለሁለት ሰዓት ከተጓዝን በኋላ በዛሬው የጦር ሰፈራችን ደረስን። ልክ እኛ በጦር ሰፈር ስንደርስ ወታደሮች ጉዟቸውን አቋመው መተኛት ጀምረዋል። በደረቅ መሬት ላይ፣ ሜዳው መሀል ላይ የደጃዝማች አበራ ድንኳን ቆማለች። የኛ ድንኳን ገና ኋላ ነው። ምንም አይደለም። ሁላችንም በፈረሶቻችን ላይ ሁለት ሁለት ብርድ ልብሶች ጭነናል እና እኛም በደረቁ መሬት ላይ ተኛን።

ገና ሸለብ እንዳደረገን እነዚያ መከረኛ ከበሮዎች ይጎስሙ ጀመር። ተሎ ተነስተን መጓዝ አለብን። አሁን መንገዷ እየጠበበችና አስቸጋሪ እየሆነች መጥታለች። ሸቀብ ወጥቶ እንደገና ቁልቁል መውረድ፣ ሰሞኑን የምንሄድበት መሬት ተመሳሳይ ነው። ደጃዝማች አበራ አሁን ፈረሱን በበቅሎ ለውጦ ጦሩን እየመራ ወደፊት ገስግሷል። እንዲህ በፍጥነት የሚገሰግሰው የደጃዝማች አበራ ፈረሰኛ ጦር ብዙም ሳይቆይ ከአይታችን ተሰወረ። የደጃዝማች አበራን ጦር ፍጥነት መያዝ አቅቶን እንዲህ በብዙ ሺህ አህዮችና የጭነት ከብቶች፣ እግረኛ ወታደሮች፣ ፈረሰኞች ብቻ በሺዎች በሚቆጠሩ ተዋጊዎች መሀል ብቻችንን ቀረን። ሁሉም ይቸኩላል። በጊዜ ለመድረስና ጥሩ ምሽግ ለመያዝ እና ነግቶ እነዚያ የብረት አሞራዎች መጥተው ሳይደበድቡን ለመደበቅ።

እንዲህ ስንጓዝ ገና ወደ ጦር ሜዳ ሰሞኑን ከደረሱ ወታደሮች መሀል ገጠሙ እንደገመተከት አላወቁንም። አንዱ ወደኋላ ተመልሶ ልክ እንደሚሸጥ ከብት አገላብጦ ከአየን በኋላ ወደ ሰራዊቱ ወደ ጓደኞቹ ተመለሰ። ሌላው ጠመንጃውን እያቀባበለ ባለንበት እንድንቆም አዘዘን።

"ጉት አባቴ ደግሞ ፈረንጅ! ጣልያን የት አባቱን!" እያለ መቀባጠር ጀመረ። በዚህ መሀል አንድ ጥይት ተተኮሰች። ከወታደሮቹ አንዱ መሳሪያው ባርቆበት ይሁን አውቆ ተኩሶብን እንደሆነ አላውቅም ብቻ ጥይቷ ማናችንንም ሳትመታ አልፋ ሄደች። አሁን ሁኔታዎች ለኛ አደገኛ እየሆኑ ነው።

ልክ እንደገመትኩት እነዚህ አዲስ ወታደሮች ሦስት ፈረንጆች አብረዋቸው ነጋዴዎች እየውቁም። እናም ጣልያኖች መስለናቸዋል። የእድል ነገር ሆኖ አንድ የሚያውቀን ሹማግሌ ሹም በፈረስ ሆነው ደረሱልን። "የካማ ፈረንጆች ናቸው። ተው! ተው! የካማ ፈረንጆች ናቸው" እያሉ ያንን አዲሱን ጦር አረጋግተው፣ ነፍሳችንን አድነው፣ እሳቸውን ተከትለን እንድንጓዝ አደረጉ። የደጃዝማች አበራን ጦር እስክንደርስበት ሽማግሌውን ሹም ተከትለን ተጓዝን፤ እስከ ጠዋት።

ጠዋት ደብረ አይላ በስተምዕራብ የአምባላጌ ወንዝ ላይ ደረስን። ራስ ካሣ በስተሰሜን በኩል ያሉትን የተፈጥሮ ዋሻዎች ሁሉ ይዘው ሰፍረዋል። አሁን ባለንባት ቦታ ብዙ የተፈጥሮ ዋሻዎች ባለመኖራቸው የደጃዝማች አበራ ጦር ምንም ዋሻ ባለው ጫካ ውስጥ ምንም ድንኳን ሳይጥሉ፣ በጋርዮሽ ስርአተ ማህበር ጊዜ እንደሚኖሩት ሰዎች ሁሉ፣ ዝም ብለው ጫካ ውስጥ ገብተው ሰፍረዋል።

የጣልያን አውሮፕላኖች በተደጋጋሚ እየዞሩ የኢትዮጵያን ሰራዊት ቢፈልጉም የኛን የጦር ሰፈር ማግኘት አቅቷቸው እንዲሁ ሲዞሩ ውለው ወደ መቀሌ ተመለሱ። ምሽት ላይ የጦር ሰፈራችን በሰዎች ግርግር ተበጠበጠች። ቢቸግረኝ ከተኛሁበት ተነስቼ በሰፈር ያገኘኋቸውን አንድ ሹም፣ ሽማግሌውን ባላምባራስን "ምን ተፈጠረ ባላምባራስ?" ስል ጠየቅኋቸው።

"ጣልያኖች እንጣሎን ያዟት" እያሉ ኀራዴዎቻቸውን ከወዲህ ወዲያ ያወናጭፋሉ። ተናደዋል፤ በጣም ተበሳጭተዋል። ወዲያው ባላምባራስ ወታደሮቻቸውን ሰብስበው በጨለማ ወደ ራስ ካሣ የጦር ሰፈር ገሰገሱ።

የእንጣሎ ትንሽዬ ከተማ ከአምባራዶም በደቡብ ምስራቅ በኩል የምትገኝ ስትሆን አሁን እኛ ከሰፈርንባት የጦር ሰፈር 5 ኪሎ ሜትር በማይሞላ ርቀት ላይ ነች። ጠዋት በማለዳ ወደ እንጣሎ ገስግሶ ሄዶ የነበረው ሰራዊት ወደ ጦር ሰፈር መመለስ ጀመረ። ማታ ጣልያኖች እንጣሎን ያዟት የሚለው ወሬ ውሸት ሆኖ ተገኘ። ወይም ይኼን ወሬ ያመጣው ሰው ጣልያኖች አፍንላን ለመያዝ ሲገሰግሱ ያየ መሆን አለበት።

ገና ከመንጋቱ በፊት ከጣልያን አብራሪዎች አይን እጅግ በሚደንቅ ሁኔታ ተሰወርን። ከ14 ቀን በፊት ራስ ካሣ እያንዳንዱ ወታደር ከመንጋቱ በፊት ድንኳኑን ነቅሎ ወደ ጥሻውና ተራራው እንዲገባ ጥብቅ ትዕዛዝ ሰጥተው ስለነበር የራስ ወታደሮች፣ ማለትም በድንኳን ውስጥ የሚተኙት፣ ከመንጋቱ በፊት ድንኳኖቻቸውን ነቅለው ከደበቁ በኋላ ወይ ወደ ተገኘው ዋሻ ይገባሉ አልያም በየጥሻው ውስጥ ተበትነው በመደበቅ ቀኑን ያሳልፋሉ። ለዚህም ነበር የራስን ጦር የጣልያን አብራሪዎች ማግኘት ያልቻሉት። የጣልያን ጠቅላይ ጦር አዛዥ ጦራችን እንዲህ በቀኑ ወደ ሰሜን ተራሮች ወደ ተንቤን እየገሰገሰ መሆኑን ፈጽሞ አልገመተም።

ከተንቤን ሆኖ መቀሌ ያለውን የጠላት ጦር ድባት ለመምታት መዘጋጀቱ ፈጽሞ አልመጣላቸውም፤ አልተገለጠላቸውም።

አብዛኛው ተራው ወታደርና ብዙዎቹ ሹማምንቶች ሳይቀሩ ለምን ገና ከመንጋቱ በፊት ድንኳኖቻቸውን ነቅለው በዋሻዎችና በጫካዎች ውስጥ ገብተው መደበቅ እንዳለባቸው አልገባቸውም። አብዛኛዎቹ የመሰላቸው የጣሊያን አውሮፕላኖች በሚጥሉት ቦንብ ድንኳኖቻቸውን እንዳይበጫጨቁባቸው ታስቦ የተሰጠ ትዕዛዝ አድርገው ነው የቆጠሩት።

ለዚህም ማስረጃ የሚሆን አንድ አጋጣሚ ገጥሞኝ ነበር። ራስ ካሣ ለከሊነጋጋ ግድም ከድንኳን ወጥተው ከተወሰኑ ወታደሮቻቸው ጋር ወደ አንዲት ዋሻ ይኼዳሉ። በጦር ሜዳ የቀሩ ወታደሮቻቸው የራስ ካሣን ድንኳኖች፣ የግብሩን ድንኳን ሳይቀር ይነቅሉና በጫካዎች ውስጥ ይደብቃሉ። ጦራችን በሰፈረበት የጦር ሰፈር ሁሉ ሁሌም የማትጠፋው የራስ ካሣ የድንኳን ቤተ ክርስቲያን ግን እንደቆመች ነው።

ድርጊታቸው ቢገርመኝ የወታደሮቹን አለቃ ጠርቼ "ለምን የድንኳኗን ቤተ ክርስቲያን ነቅለው እንዲደብቁ ወታደሮቹን እንደማያዝዙ" ጠየኩት። "የድንኳኗን ቤተ ክርስቲያን?" በመገረም ጠየቀኝና በመቀጠል፣ "ይኼ የኛ ጉዳይ አይደለም ጌታው። አዩ ጌታ ቤተ ክርስቲያኗ የእግዚያብሄር ንብረት ናት። እግዜሩ የራሱን ንብረት ይጠብቃል። እና እግዜሩ የራሱን ንብረት መጠበቅ ካልቻለ እኛ ተራ ሟቾች ምን ማድረግ ይቻለናል?" አለኝ። ብቻ ለረጅም ጊዜ እስኪገባው ድረስ ካስረዳሁት በኋላ ያችን የድንኳን ቤተ ክርስቲያን ነቅለው እንዲደብቁ ለወታደሮቹ ትዕዛዛ ሰጠ።

እያንዳንዱ የኢትዮጵያ ጦር እርስ በርሱ የሚገናኝበት ራዲዮ አልነበረውም። ራስ ካሣ ብቻ ናቸው አንድ ራዲዮ ያለቻቸው። በዚች ራዲዮ ራስ አዲስ አበባና ደሴ ካለው የንጉሡ ነገሥቱ ጦር ጋር ይገናኛሉ።

ይኼም የራስ ግንኙነት የሚካሄደው ቤንዚን እስካለን ድረስ በመሆኑ ሰሞኑን ራዴዮኗ ዝም ብላለች። የነበረንን ስድስት ቆርቆሮ ቤንዚን ተጠቅመን ጨርሰናል። ራስ ካሣ ደግሞ በአስቸኳይ ወደ ደሴ ለንጉሡ ነገሥቱ መልዕክት መላክ ይፈልጋሉ።

እንዲህ መላው ጠፍቶን እያለን ባጋጣሚ ራስ ሥዩም መጡና ችግሩን ጠየቁን። ሁሌም መላ አያጡምና ያለውን የቤንዚን ችግር ስንነግራቸው ረዳታቸውን ጠርተው ጣልያኖች መቀሌ ቤንዚን እንዳላቸው ጠየቁት። "እንዴታ ራስ" ብሎ መለሰላቸው ረዳታቸው ልጅ ተድላ። ልጅ ተድላ እስከቅርብ ጊዜ ድረስ አስመራ ቆንስል ሆኖ ሲሰራ ቆይቶ ጦርነቱ ሊጀመር አካባቢ ወደ መቀሌ ተመልሶ የራስ ሥዩም አማካሪ ሆነ።

ራስ ሥዩም ቤንዚን ጣልያኖች መቀሌ እንዳላቸው ሲያውቁ ፊታቸው በደስታ እየበራ ሳቅ ብለው ሁለት የመቀሌ ልጆችን አስጠርተው ቤንዚን ይዘው እንዲመለሱ

ላሏቸው። ሁለቱ ወጣት ወታደሮች መቀሌ ተወልደው ያደጉ የመቀሌ አራዶች ለዘሩ! የጣሊያንን ዘቦች በቀላሉ ሸዋውደው መቀሌ መግባት እንደሚችሉ ብዙ ጓደኞቻቸው እያሞጋገሱ አጽናኑን።

በሁለተኛው ቀን አንዱ የመቀሌ ልጅ አንድ ጀርካን ቤንዚን ይዞ ሲመለስ፣ ሁለተኛውን ልጅ ጓደኛውን ግን ጣልያኖች ይዘውት በጥይት ደብድበው እንደገደሉት ሰማን። አሁን መልዕክት መላክ እንችላለን።

ከራስ እምሩ ጋር፣ ማለትም በሰሜን ምዕራብ በኩል በአድዋና አክሱም መካከል የጣሊያንን ጦር ከሚወጋው ከሶስተኛው የኢትዮጵያ ሰራዊት ዋና አዛዥ ጋር፣ ራስ ካሣ የሚገናኙት በጣም ኋላ ቀር በሆነው በጥንቱ የፖስታ መልክተኛ በኩል ነበር።

በኢትዮጵያ የዘመናት ታሪክ ፖስተኛ እንደ ቅዱስ የሚቆጠርና በእንጨት ባላ ላይ ሰክቶ በጉዞ ላይ ከፍ አድርጎ የሚይዛትን መልዕክት ከያዘ በጠላት መሬት ላይ ቢሄድ እንኳ ፖስተኛውን የሚነካው ሰው አልነበረም። አሁን እንዲህ ዘመን ተለውጦ ጅ የጦር ሰፈር በሩጫ ከአራት ቀን በኋላ ከራስ እምሩ ዘንድ የሚደርሰውን መልዕክተኛ ሯጭ የትግራይ ሽፍቶች እየገደሉ መልዕክቷን በይሁዳ ሽልንጎች ለጣልያኖች መሸጥ ጀምረዋል።

ሌሎችም የኢትዮጵያ ክፍሎች አስተማማኝ አይደሉም፤ ጣልያኖች የሚያጎርሷቸው ጉርሻ ልባቸው ያበጠ ሽፍቶች ለወታደሮቻችን የሚመጣውን ማናቸውንም ነገር መንገድ እየጠበቁ ይዘርፋሉ። እኛም ለግል ጉዳይ የምንጠቀምባቸውን ቁሳቁሶች ከጨረስን ቆይተናል። እነዚህን ቁሳቁሶች ከአዲስ አበባ ጭኖ ለማስላክ ለራስ ካሣ አሁን ከአቅማቸው በላይ አስቸጋሪ ነው። እንዳንጨነቅና እንዳንቸገር የምንፈልገውን ነገር ሁሉ በገዛ ፍላጎታቸው ራስ ሥዩም መንገሻ ያሟሉልናል፤ እርሳስ፣ ወረቀት፣ ሲጃራ፣ እና ሌሎች ነገሮች። ለራስ ሥዩም የመቀሌ ልጆችን ጠርተው ማዘዝ ብቻ ይበቃል። እንዴትና ከየት ነው የሚያመጡት? ከጣልያን የጦር ሰፈር ከመቀሌ። በዚህ መልኩ ሳያውቁት የጣልያን የጦር ሰፈሮች የኢትዮጵያው ሰራዊት ቀላቢዎች ሆነው ነበር።

23

ጠላት አፋፍ ላይ



ዛሬ የፈረንጆች አዲስ ዓመት ነው፤ 1936 ዓ.ም.። ጣልያኖች ዛሬ ሰላም የሰጡን ይመስላል። ጠዋት ላይ እንዲት የሰለላ አውሮፕላን ብቅ ብላ ትንሽ ዞር ዞር ካለች በኋላ ተመልሳ ወደመቀሌ ተመልሳለች።

ሰፈራችንም ይቺን ፋታ ተጥቅሞ ሴቱ እንስራውን ተሸክሞ ቀረብ ወደ አለ ወንዝ ውሃ ፍለጋ ወርዷል። ወንዶቹ ከሰፈር ወጣ ብሎ ከየማሳው የሰባሰቧትን ነዶ አስረው በራሳቸው ተሸክመው ወደሰፈር በመመለስ ላይ ናቸው። አንዳንዶችም በየቀበሌው ሲዘዋወሩ ቆይተው ከየቤቱ የሸማመቱትን ጥራጥሬ በሸማቸው ቋጥረው ሲመለሱ ይታያሉ።

እኔም ጠዋት ለልጅ ወልደ ገብርኤል በቅሎዬን አውሼው ወደ አንባሎ መንደር ወርዶ አምባሻና ጠጅ ይገዛልን ዘንድ ከሄደ ቆይቷል። ልጅ ወልደ ገብርኤል እንደ ማንኛም የገጠሬ ወታደር ሁሉ ባረደች ኮቱ ላይ ያደፈች ሸማውን ደርቦ ነው የሚሄደው። ምናልባት ከሌሎች የሚለይበት ነገር ቢኖር ከፊት የግር ጣቶቹ ብቅ ጥልቅ የሚሉበትና ጨርሶ ተገንጥሎ ወድቆ እንዳይጠፋበት በልጥ ጥርቅም አድርጎ ያሰረውን ጫማውን ማድረጉ ብቻ ነው።

ልጅ ወልደ ገብርኤል ከዛሬ ዓመት በፊት ፈረንሳይ ሀገር ፖለቲካል ሳይንስ ሊማር የሄደ ልብሱን ለብሶ የፓሪስ ቡና ቤቶችን ያስስ የነበረ የአራዳ ልጅ እንደነበረ አሁን ላየው ሰው ማመን ያስቸግራል። በኋላም ትምህርቱን ጨርሶ ከፈረንሳይ ተመልሶ የራስ ሥዩም ሁለተኛ ጸሐፊ ሆኖ ለማገልገል ደጅ ሲጠና፣ ጦርነት ተጀመረና እነሆ እሱም እንደ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ወታደር ሁሉ ሸማውን ለብሶ፣ ጠመንጃውን አንግቶ፣ የእናት ሀገሩን ዳር ድንበር ጥሶ የመጣውን የፋሽስት ጣልያንን ጦር ሊገጥም፣ አገሩን ከጠላት ጦር ሊከላከል፣ እነሆ እዚህ ደርሷል።

ዛሬ በዚች አዲሷ የጦር ሰፈራችን ቢያንስ አርፈን እንውላለን የሚል ግምት ነበረኝ። ግምቴ ግን ስህተት ነበር። እንዚያ የጦር ሜዳ ከበሮዎች መደለቅ፣ ጡሩንባዎች መነፋት፣ ነጋሪቶች መጎሰም ጀመሩ። መሄዳችን ነው፣ ወደፊት!

አቶ ተሰማ እየተጣደፉ መጥተው እቃችንን ከአሳሰሩና በጭነት ከብቶች ከጫኑ በኋላ፣ ጊዜ ሳንፈጅ ከሰራዊቱ ጋር ወደፊት እንድንገዝ አሳሰቡ። ሰራዊታችን ለጉዞ እየተጣደፈ ያለችውን ንብረት እየቆጣጠረ ሲነሳ እኛ ልጅ ወልደ ገብርኤል ከአንባሎ ሳይተመለስ ልንጠብቀው ወስነን ቀረን። አቶ ተሰማም ብዙ ጠብቀው ስለሰለቻቸው ያለውን ሰጥበቃችን ሁለት ወታደሮች ብቻ ትተውልን ከሄዱ ቆዩ። ልጅ ወልደ ገብርኤል እስካሁን ብቅ አላለም። እኛም ብቻችንን ቀረን። እንዲህ ሰፈሩ ጭር ብሎ ሳለ ከሩቅ የትግራይ ሽፍቶች ሲጮሁ ሰማን፤ አሁን ብዙ መቆየት አንችልም። ሊደጋ እየቀረበ ነው። እንዲህ ጦራችን ሰፈሩን ለቆ ሲጓዝ ሽፍቶች መጥተው እየተጯጯሁ በጉውን ተነጥሎ የቀረውን እድለቢስ የኢትዮጵያ ወታደር ይዘርፋሉ።

እኛም አደገኛ ሁኔታ ውስጥ እየገባን መሆኑን ተገንዝበን ልጅ ወልደ ገብርኤልን ለአርባ ቀን እድሉ ትተነው ለጉዞ ስንነሳ ከታች መጀመሪያ የበቅሎ ራስ ብቅ አለች። ቀጥሎም ተንገፎ ልጅ ወልደ ገብርኤል እየተንማለለ ብቅ ሲል ሁላችንም ተደሰትን። ወዲያው በፈረሶቻችን ላይ ሆነን ቱ በለው አልን፤ ወደፊት!

ደም የመሰለችው ጀንበር ቀስ እያለች ቡታዋን ለጨረቃ ለቅቃ ዞራ በስሜን ተራሮች ጀርባ ገብታ ተሰወረች። ምንም እንኳን ሙሉ ጨረቃ ብትሆንም አልፎ አልፎ በዳመና ስለምትሸፈን ለዛሬው የምሽት ጉዟችን ብዙም ሳትረዳን፣ እድሜ ለፈረሶቻችንና በቅሎዎቻችን ተፈጥሮ በዳረገቻቸው ጸጋ እየተረዱ ጥቅጥቅ ባለው ጨለማ አስቸጋሪውን መንገድ ልክ በሰፊ አስፓልት ላይ እንደሚበር መኪና ይዘውን ይሄዳሉ። ብዙም ሳንቆይ ተራራውን እየወጣ ጥቅጥቅ ካለው ጫካ ውስጥ ገብቶ ከእይታ ከሚሰወረው የኋላው ደጀን ሰራዊታችን ላይ ደረስንበት።

እንዲህ በችቦ መብራት እየተረዳ በሌሊት የሚጓዘውን ሰራዊት ከሩቅ ላየው ሰው እሳት ጎርፍ እሳት የሚተፋ፣ አስገራሚና ርዝመቱ መጨረሻ የሌለው እጅግ በጣም ረጅምና ግዙፍ ዘንዶ ይመስላል።

በጣም ከመሸ በኋላ እንዲት ትንሽዬ መንደርን አልፈን ከአንዲት አስቸጋሪ የሰርጥ መንገድ አጠገብ ደረስን። በእንዲህ አይነቷ አስቸጋሪ የሰርጥ መንገድ አካባቢ ብዙ ጊዜ እኔ እቀድም እኔ አምባገርዎች ይነሳሉ። እንዲህ አይነት ስግብግብ እና ችኩሎች በሞሉበት ቦታ እንኳን ቢሆን፣ ቁስለኛ ኋላ ቀር በሆነው ቃሬዛ የተሸከሙ ወታደሮች ሁሌም ቅድሚያ ነበራቸው።

ሰሞኑን በጦራችን መሀል አንድ ሌላ ከጣልያን ወታደሮችና ከጣልያን የአውሮፕላን ቦምቦች የከፋ ጠላት መጥቶብናል። አደገኛው ተስቦ ገብቷል። ከ200 በላይ በሽተኞች ደብረ አይላ ላይ ትተን መምጣት ተገደናል።

ከተራራው ጫፍ ላይ ስንደርስ ራስ ካሣ የት እንዳሉ ጠየቅን። ሁሉም የጠየቅናቸው ወታደሮች ራስ ወደፊት ቀድመው እንደሄዱና የሰላሌው ደጃዝማች አበራ ግን ብዙም ሳይርቅ መስፈሩን ሲያስረዱን፣ ደጃዝማች አበራ ወዳጃችን እንደሆነ ማወቃቸውን እንድናውቅላቸው ጭምር ነበር።

እንዲህ ጥቅጥቅ ባለ ጨለማ ውስጥ ደጃዝማች አበራን ማፈላልግ ዋጋ የለውም። እኛም በጣም ደክሞናል። እቃዎቻችንን የጫኑት አህዮች ገና በጉዞ ላይ እያለን ነው ከብዙ ሺህ የጭነት ከብቶች ጋር ተቀላቅለው የጠፉብን። ምንም አደለም። ዛሬም ሁለት ብርድ ልብሶች አሉንና መሬት ላይ አንጥፈን ተኛን። ዛሬ ግን አጥንት የሚሰብር ብርድ ይበርዳል። ይበርዳል? ይቆረጥማል ነው የሚባለው። እኔ ከተኛሁበት ሁለት ሶስት ርምጃ እራቅ ብሎ አንድ በሬ ተኝቶ ያመነዥካል።

በሌሊቱ ብርድ እየተንቀጠቀጥን ገና ሳይነጋ ተነስተን ፈረሶቻችንን ራሳችን ጭነን እየተጣደፍን ያችን አስቸጋሪ ሰርጥ የጣልያን አውሮፕላኖች ሰማዩን ሳይወሩ በፊት ለመውረድ ገሰገስን። ከነጋ በኋላ ስርጧን ለመውረድ መሞከር እራስን ለሞት እንደመዳረግ ነው። ይኼንን አደጋ የኢትዮጵያ ወታደሮች አሳምረው ስለሚያውቁት ከዚሁ አደጋ ለመሸሽና በጊዜ ስርጧን ለመውረድ ያለውን ንብረት ተሸክሞና የጭነት ከብቶቹን ነድቶ መሄድ ግድ ነውና እንደ ጎርፍ ከሞላው የህዝብ መአት መሀል ገብተን ተቀላቀልን።

ፀሐይ ከወጣች ትንሽ ብትቆይም እስካሁን የጣልያን አውሮፕላኖች ብቅ አላሉም። በትግስት ተራችንን ጠብቀን ከጠዋቱ ወደ 3 ሰዓት ገደማ ላይ ደረስንና ያችን አስቸጋሪ ሰርጥ ወርደን እታች እሜዳው ላይ ደረስን። ሜዳው ይመች ስለነበረ የተሰበሰበውን ፍጥነታችንን ጨምረን ያቺን የሰው ጎርፍ መፈናፈኛ በሌለው ቦታ ላይ ስርጥ ርቀን ሄድን።

ብዙም ሳይቆይ ከሩቅ የባለ ሶስት ሞተር አውሮፕላን ድምጽ ሰማሁና ፈረስን ገትቼ በጦር ሜዳ መነጽሬ ሰማዩን መቃኘት ጀመርኩ።አብራሪው ዶጋግሞ እየዞረ በለለው ከቃኘን በኋላ አልፎን ወደዛች ሰርጥ በረረ። በዚያች ሰርጥ ማምለጫ በሌለው ስራዊታችን ላይ ያቺ ባለሶስት ሞተር አውሮፕላን ለግማሽ ሰዓት ያህል እየዞረች 18

ከባድ ትላልቅ ቦምቦች ከመጣሏም በላይ አውሮፕላኗ ውስጥ በተጠመደ መትረየስ የጥይት ዝናቧን አውርዳ፣ በግድያ ስራዋ ረካች መሰለኝ ዞራ ወደ መቀሌ ተመለሰች።

አሁን መቀሌ ሩቅ አደለችም። ምንም እንኳ ምንም ካርታ ባይኖረኝም ከርቀት የሚያነበኩቡ አውሮፕላኖችን ማስተዋል ስለሚቻል ወደ መቀሌ መቃረባችንን መረዳት ቀላል ነበር። ሁለት አውሮፕላኖች ማምለጫ ያጣውን የኢትዮጵያ ስራዊት ሜዳ ላይ አግኝተውት እያሯሯጡ ደበደቡት።

አሁን ከቆምኩባት የተራራ ጫፍ አብራሪው በጣም ዝቅ ብሎ ስለሚበር ያለ የጦር ሜዳ መነጽር በባዶ አይን ቁልጭ ብሎ ይታይ ነበር። እናም ሀሳቤን ጥዬ ስመለከት አብራሪው ቀጥ ብሎ ወደኛ መብረር ጀመረ። ይኼን ስናይ ሁላችንም በፍጥነት ባገኘነው ቋጥኝ ስር ተጠግተን ተደበቅን። አብራሪው ሁለት ጊዜ ያህል ከዞረን በኋላ አራት ትልልቅ ቦንቦች ጥሎብን ሄደ። የመጨረሻዋ አራተኛዋ ቦምብ እኛ ከመሸግንባት በግምት አርባ ሜትር ርቀት ላይ ስትፈነዳ ባስነሳችው የአቧራ ጉም ለተወሰነ ደቂቃ ታፈንን።

የአቧራው ጉም ሲጠራ ሁላችንም ከመሸግንበት ወጣን፤ ዛሬም ፍጹም እድለኞች ነን፤ ማናችንም ምንም አልሆንንም። እታች ገላጣው ሜዳ ላይ ግን በርካታ እድለቢሶች ቆስለው፣ የጣር ጩኸታቸውና ዋይታቸው ዘልቆ እኛ ያለንበት ቦታ ድረስ ይሰማ ነበር። በዚህ መሀል ግንባር ቀደሙን የራስ ካሣን ጦር ሌሎች አውሮፕላኖች የገባ ወንዝን ሲሻገር አግኝተውት ደበደቡት።

ከመሸግንበት ወጥተን ተሰባስበን ስንጓዝ ቆይተን ካንዲት ትንሽ የትግራይ መንደር ደረስንና የሚበላ ነገር፣ ቢያንስ እንባሻ (የትግሬዎች ዳቦ)፣ ብንገዛ ብለን ወደ መንደሯ አመራን። ብዙም ወደ መንደሯ ሳንዘልቅ መንደርተኞቹ ከቤታቸው ጣሪያ ላይ ሆነው የመሳሪያቸውን አፈሙዝ በኛ ላይ ደቅነው እያስፈራሩ ጮሁብን። ሁሌም ከኛ የማይለየው ጓደኛችን ልጅ ወልደ ገብርኤል እንደተረጎመልን መንደርተኞቹ ወደ መንደሯ ከዘለቅን እንደሚተኩሱብንና ወደ መንደሯ ዘልቀን እንዳንገባ እንደሚያስፈራሩን ነገሩን።

ልጅ ወልደ ገብርኤል መንደርተኞቹን ቢያንስ እንባሻ እንኳን እንዲሸጡልን ሊያግባባቸው ቢሞክርም አሻፈረኝ ስላሉ፣ እንደራበን በጉዟችን ቀጥለን ማምሻው ላይ ገባ ወንዝ ደረስን። የጊባን ወንዝ ተሻግረን በቀይ አፈር ነጭ ምስጦች በሰሩት ቤት (ምስጦቹ ቤት ቁመት ካንድ ፈረሰኛ ጦረኛ በላይ ስለነበር እንደከለላ እየተጠቀምን) እየተሹለከለክን አልፈን ራስ ካሣ ከሰፈሩበት ዋሻ ደረስን።

በዚሁ የራስ ካሣ ምሽግ አቶ ተሰማም የኛን ድንኳን አስቁመውልን ነበር። የሚገርማል አቶ ተሰማ ከወታደሮቻቸው ጋር የጭነት ከብቶችን እየነዱ ሲሮጡ ውለው ከኛ በፈረስና በበቅሎ ከምንጓዘው በብዙ ሰዓት ቀድመው ደርሰው ነበር። ጦር ሰፈራችን

እንደደረስን ትንሽ እህል ቀማምሰን ሰሞኑን በእንቅልፍ እጦትና በጉዞ በጣም ተዳክመን ስለነበር ልክ እንደራሳ ተኛን።

ሰሞኑን ለጣልያኖች በሰላይነት የሚያገለግሉት የትግራይ ተወላጆች ለማርሻል ባዶሊዮ የራስ ካሣ ጦር ወደ ተንቤን ዘልቆ እየገባ ስለመሆኑ ዘገባ ቢያቀርቡም፣ ማርሻል ባዶሊዮ እውነት ሊሆን ይችላል ብሎ ስላላመናቸው ሳይቀበላቸው ቀረ።

ማርሻል ባዶሊዮ ከ100,000 በላይ የሚቆጠረው የራስ ካሣ ጦር እንዴት እንዲህ በአጭር ጊዜ ውስጥ በዚህ አስቸጋሪ መንገድ በእግሩ ተጉዞ ተንቤን ሊገባ መቻሉ ሊዋጥለት ስላልቻለ የሰላዮቹን ዘገባ ውድቅ አደረገው። አዎ ማርሻል ባዶሊዮ የካሣን ጦር በ20 ሰዓት ውስጥ 120 ኪሎ ሜትር መጓዝ ሊያምነው ያልቻለ ተአምር ሆነበት። ማርሻል ባዶሊዮ ያልተረዳው ነገር ቢኖር ዋናው የኢትዮጵያ ሰራዊት ትልቁ መሳሪያ ተንቀሳቃሽነቱ መሆኑን ነበር።

ማርሻል ባዶሊዮ ከጣሊያን አዲስ 3 ብርጌድ ሙሉ ጦርና በርካታ የጦር ቁሳቁሶች፣ ብረት ለበስ ተሽከርካሪዎች ጭምር ስላገኘ የኮሴሪያ (Cosseria) ብርጌድና የፌብራዮ (1Febberaio) ብርጌድ ጨፍልቆ፣ 4ኛውን ክፍለ ጦር መሰረተ። 4ኛውን ክፍለ ጦር ባዶሊዮ የመሰረተው በአድዋና አክሱም መካከል በነራስ እምሩ ተወጥሮ የሚጨነቀውን 2ኛውን ክፍለ ጦር እየረዳ በስተምዕራብ በኩል ወደ መሀል ሀገር ዘልቆ እንዲገባ ነበር።

እስካሁን ድረስ በምዕራብ ኤርትራ እና በብሪቲሽ ሱዳን መካከል ያለው ድንበር ክፍትና በማንም የማይጠበቅ መሆኑን ራሱ ማርሻል ባዶሊዮ በጻፈው "La Guerra d' Ethiopia" መጽሐፉ ላይ፣ በዚህ በስተምዕራብ በኩል እንቅልፍ የነሳውን ሀሳቡን መገላገሉንና በአንድ ፊቱ አሁን የሚያስጨንቀውን የተንቤን ጉዳይ እንደሚፈታ አምኖ ጽፏል።

የጣልያን የስለላ አውሮፕላኖችና የትግራይ ሰላዮች ለማርሻል ባዶሊዮ ደጋግመው የኢትዮጵያ ሰራዊት ወደ ተንቤን በመጉረፍ ላይ መሆኑን ባቀረቡት ዘገባ መሰረት፣ ማርሻል ባዶሊዮ ሁለት ብርጌድ ጦር፣ አንደኛውን ኤርትራውያን የሀዘብበትን ከእንጢቾ አንስቶ፣ ሁለተኛውን ብርጌድ 28 ኦቶብሬን (28.ottoberን) ከመቀሌ አንስቶ ጥር ሁለት ቀን ወደ ተንቤን ላከው። ሁለት ተጨማሪ ሻለቃ ጦሮች የወረዩን ምሽግ ሲያጠናክሩ፣ የቀረው ጦር በሃውዜን በርባ ዶሮና በአዲ ዘብሃ እንደሰፈረ ተቀምጧል።

የጣልያን ብርጌዶች ጥር ሶስት ቀን ቢደርሱም ራስ ካሣ ከዋናው ጦራቸው ጋር ወደ ኪዳነ ምህረቱ ወርደው ድፍን አራት ቀን ተቀመጡ። ጥር 8 ቀን በተንቤን ዋና ከተማ አቢ አዲ ገባንና ጣልያኖች ጥለውት ከሸሹት የጦር ሰፈር አጠገብ ተራራውን ተገን አድርገን ሰፈርን። በሁለተኛው ቀን ራስ ካሣ እኔንና ኮሎኔል ኮኖቫሎቭን አስጠርተው ምናልባት ጣልያኖች ጥቃት ቢሰነዝሩ ጥሩ የመከላከያ ቦታ እንመርጥ ዘንድ አካባቢውን እንድናጠና አዘዘው ላኩን።

በማለዳ ተከትተን የጦር ሰፈራችንን ለማጥናት ወጣን። በመጀመሪያ ወደ ለተማሙ ተራራ ጉዟችንን አቀናን። ጣልያኖች ይኼን አካባቢ ይዘውት በነበረበት ዘመን አጭር ጊዜ ውስጥ ደኑን መንጥረው፣ አለቱን ፈልጠው፣ አስቸጋሪውን መንገድ ጥሩ አድርገው አስተካክለውታል።

በዚችው መንገድ እየሄድን አካባቢያችንን መቃኘት ጀመርን። በዚችው መንገድ ላይ ጣሊያኖች በሁለቱ ጀግና ደጃዝማቾች፣ ደጃዝማች ኃይሉ ከበደ እና ደጃዝማች ... ጦር ሲሸነፉ ሸሽተው ወደ ወረዩ የወረዱት።

በዚችው መንገድ እየሄድን ግራ ቀኙን ስናስተውል በየቦታው ባዶ የምግብ ... የቻኮሌትና የሲጋራ ፓኮዎች እዚያም እዚህም ወድቀው አየን። በተለይ ... የሲጋራ ፓኮዎች በከፋ አይን አየሁዋቸው። ካጨስን ሰንበትናል። ... ምንም የሚጨስ ነገር የለም።

ከተራራው ጫፍ አካባቢ አንድ በሰው ልጆች እጅ የተጠረበችና በጊዜዋ እንደ ... ክርስቲያን ታገለግል የነበረች በመጠኑም ቢሆን ሰፋ ያለች ዋሻ አገኘን። ... ዋሻ ማግኘታችን ወሳኝ ነበር። ምክንያቱም ይቺ ዋሻ በኋላ ላይ ለጠቅላላው ... ጦር የበላይ ሹማምንቶች ከጣሊያን አውሮፕላኖች መሸሸጊያ ዋና ምሽግ ሆና አገለግላለች።

ከዋሻዋ እንደ ወጣን ከዋሻዋ አግድም ሜዳ ሜዳውን ከአራት ሰዓት በላይ ... መንገድ በሚፈጅ ቦታ ላይ የተወሰኑ ወታደሮች አገኘን። እነዚህ ወታደሮች ... በፍጥነት ይሰራሉ። ስራውም ተቀላጥፎ እጅ በጅ እየሄደላቸው ነው። አዎ ... ኢትዮጵያውያን መስራት ከፈለጉ በጉልበት ስራም ጎበዞች ናቸው። ቆም አልንና ምን ... እንደሆነ ጠየቅናቸው።

ሸምገል ያለ ጢማም ሹማቸው ወደኛ ጠጋ ብሎ ሳቅ እያለ፣ አንድ አሮጌ ... ጣቱን ቀስር እያሳየን፣ ለመድፉ መንገድ እያሰራ መሆኑንና ከሰሞኑ (አሁንም ... ጣልያኖች ሰፈር ጣቱን ቀስሮ እያሳየን) በዚህ መድፍ ድራሻቸውን እንደሚያጠፋቸው በኩራት ነገረን።

ኮሎኔል ኮኖቫሎቭ ቆም ብሎ መድፉ ሊቆምበት የታሰበውን ቦታና ጣልያኖቹን ሰፈር አስተያይቶ ወደ ሹሙ ዞር ብሎ ጣልያኖች ቢያንስ ከ6 ኪሎ ሜትር በላይ ርቀው እያሉ እንደምን በዚህ አሮጌ መድፍ ሊደበድባቸው እንዳሰበ ... ሹሙ ትንሽ አሰብ አድርጎ "አዬ አዬ አዬ ግዴለም እሰና ወታደሮቹን ... አቁመው ከፍ ካለ ቦታ ላይ ጥሩ ቦታ ይፈልጉ ዘንድ አዘዛቸው።

ከቀናት በኋላ ይኼንኑ ሹም መድፍ ሲያስተኩስ የማየቱ እድል ገጥሞኝ ነበር። ... ሲያስተኩስ በአየሁት ጊዜ መሳቅ ወይስ ማልቀስ እንዳለብኝ ሳይገባኝ ... ብዬ ቆሜ አየሁት።

ሹሙ መድፍ በህይወቱ ሲያስተኩስ የመጀመሪያው ጊዜ ሳይሆን አይቀርም፡ መድፍ እንደ ጠብመንጃ የሚተኮስ ሳይመስለው አልቀረም መሰል፣ ለረጅም ሰዓት የመድፉን ማጉጫበሪያ ሲፈልግ ቆይቶ ስላጣው፣ ቀለህ ማስገቢያውን ከፍቶ ወይ የመድፉ ስሬ እፍ የጣልያኖቹን መንደር እያሻሻረ ሲፈልግ ቆይቶ ያገኝ ሲመስለው አስተካክሉ አቆመውና ተኳሾችን እንዲተኩሱ አዘዛቸው። ከአስር ጊዜ በላይ አስተኩሶ እስኪሞት ድረስ በማይገባው ሁኔታ በመገረም፣ እንዴት ይኼ መድፍ ጣልያኖቹ መንደር ሳይደርስ መሀል መንገድ ላይ እየሄደ መፈንዳቱን እያየ፣ ራሱን እየነቀነቀ መድፈኞቹን ወደፊት ቀረብ እንዲሉ አዘዛቸው።

ከመድፈኞቹ አልፈን አካባቢያችንን ማጥናቱ ላይ ቀጥለን የጣልያኖች የጦር ሰፈር ግልጽ ሆኖ እስከሚታይበት አፋፍ ድረስ ተንዝን። አፋፉ ላይ እንደቆምን አታች አሜዳው ላይ በሰፊው የተዘረጉ ዳሶች የጣልያን ድንኳኖች ልክ እንደ ነጠብጣብ ሆነው ታዩን።

የጣልያኖቹን ዳሶች ድንኳኖች እንዳየን ገደሉን ወርደን፣ እሾሀማውን ጫካ አልፈን፣ ሜዳው ላይ ደርሰን፣ ወደፊት ስንሄድ በርከት ያሉ ኢትዮጵያውያን ወታደሮች ጥቅጥቅ ያለውን ጫካ ተገን አድርገው እንደሰፈሩ አገኘናቸው።

እነሱን አልፈን ወደፊት ስንሄድ የጣልያኖቹ ቀዳሚ ጠባቂ ወታደሮች አዩን መሰለኝ መትረየሶቻቸውን አንጣጡብን። ግን በጣም እሩቅ ነበሩ። ቢያንስ ከ2 ኪሎ ሜትር በላይ ርቀው ነበር የተኳኩሱብን። እንዲህ በከፍተኛ ጥንቃቄ እያንዳንዷን ቦታ ካጠናን በኋላ ወደ ሰፈር ተመልሰን ለራሶቹ ዘገባ አቀረብን።

ከላይ ከተራራው ላይ ባሉ ቋጥኞች ስር ሆነን ለረጅም ሰዓት የጣልያን ወታደሮችን እንቅስቃሴ አጠናን። ጣልያኖች በተወሰኑ ጊዜ ልዩነቶች ምግብ፣ መሳሪያና በርካታ የጦር ቁሳቁሶች የጫኑ የጭነት መኪናዎች ወደ ጦር ሰፈራቸው ይገቡላቸው ነበር።

እዚያው እቋጥኞቹ ስር እንደተቀመጥን ባለ ሶስት ሞተሮቹ የጣልያን አውሮፕላኖች እያጓሩ መጣንላችሁ ሲሉን ሰማናቸው። ኢትዮጵያውያን ወታደሮች አውሮፕላኖቹን ነጭ ሸማቸውን እንደለበሱ ወዲያ ወዲህ ሲሉ እንዳልነበረ ሁሉ የአውሮፕላኖቹን ድምጽ ሲሰሙ በሚያስደንቅ ሁኔታ ወደ ጫካው ውስጥ ገብተው ከጣልያን አብራሪዎች አይን ተሰወሩ።

ግንባር ቀደሙ የኢትዮጵያ ጠባቂ ጦር አሁን በጣም በሚገርም ሁኔታ ባጭር ጊዜ ውስጥ ከጣልያን አብራሪዎች አይን ስር እንደ ተአምር መሰውርን ለምዷል። ጣልያኖች ምንም እንኳ አንድም ኢትዮጵያዊ ወታደር ማየት ባይችሉም ተደብቀውበታል ብለው የገመቱበትን ቦታ ሁሉ የቦምብ ሸክማቸውን አውርደውበት ይመለሳሉ። አንዳንድ ጊዜም በጣም ዝቅ ብለው በመብረር ኢትዮጵያውያንን አለ

ለማስተኮስና ከኢትዮጵያውያን አርጌ መሳሪያዎች አፈሙዝ ቡልቅ እያሉ ... ጭሶች እየተረዱ ለመደብደብ ቢሞክሩም፣ ሰራዊቱ በከንቱ ጥይቱን ማባከን ... ጣልያኖች በከንቱ በባዶ ሜዳ ቦምባቸውን እያራገፉ ወደ መቀሌ ይመለሳሉ።

አንድ ቀን የጣልያኖች ግንባር ቀደም ጠባቂ ጦር አንድ ኢትዮጵያዊ ወታደር ... ሰፈሩ በጣም ርቆ እንዲሁ ሲንቀዋለል ይይዙታል። ይኼው ቀውላላ ወታደር ... ጠብመንጃ አልያዘም ነበርና የጣልያኑ አዛዥ ላቀረበለት ጥያቄ "ሰላማዊ ... ነዋሪ ገበሬ መሆኑን" ሲያስረዳው፣ የጣልያኑ አዛዥ የማያምንበት ... ስላልነበረው በነጻ እንዲለቁት ያዝዛቸውና ይለቁታል። ሲወጣ በጣልያኖች ... ሰፈር ራት ይታደል ነበረና ለዚሁ ቀውላላ ሚስኪንም ራት ሰጥተውት ራቱን ... ቡና ጠጥቶ፣ የተረፈውን ነጭ ዳቦ "ፉርኖ" በሸማው ቋጥሮ ወደሰፈር ... ለጓደኞቹ ስለገጠመው ሁኔታ አጣፍጦ ይነግራቸዋል።

በሰፈራችን አሁን መጨረሻ ግድም ላይ ቡና የሚጠጡት ራሶችና ሌሎች ... ከፍተኛ ሹማምንቶች ብቻ ስለነበሩ፣ በተጨማሪም በጦር ሰፈራችን የምግብ ... እየመጣ ስለነበር የዚያ ቀውላላ ወታደር ጓደኞች ይኼን ተራ የባላገር ወታደር ... ልክ እንደ ራስና ከፍተኛ ሹም ማስተናገዳቸው ገርሟቸው ምራቃቸውን ... ከመሀላቸው አንዱ ተነስቶ፣ "ጎበዝ፣ እንሂድና ጣልያኖችን እንጎብኝ" ብሎ ... ሲያቀርብ በዚያች የጦር ሰፈር ያለው የገበሬ ወታደር ሁሉ በአንድ ድምጽ ... ጠብመንጃቸውን በየጥሻው ጥለው ቡና ሊጠጡ ሳይጠሩ ወደ ጣልያኖች ... ሄዱ።

ጎምላ የሚሆኑት እነዚህ ባላገር ገበሬዎች ሰብሰብ ብለው ቡና ሊጠጡ ወደ ... ሰፈር መገስገሳቸውን ያየው የጣልያን ቀዳሚው ጦር ገና ከሩቁ በመትረየስ ... ይቀበላቸዋል። ቡና ሊጠጡ ቋምጠው የሄዱት ባላገር ወታደሮች ጣልያኖች ... በቡና ቁርስ ምትክ በጥይት ሲቀበሏቸው እግሬን አውጪኝ ሽሽት ይገባሉ። ... ግዴለሽነት በተሞላው አድራጎታቸው ሁለቱ ባላገሮች በትንሹ ሲቆሰሉ ሌሎች ... ወደ ሰፈር ይመለሳሉ።

ከነዚህ የዋህ የባላገር ወታደሮች አንዱ ወደኔ ጠጋ ብሎ ስለ ገ...ው ... "እየህ ፈረንጅ ጌታ፣ እኛ ሰው ናቸው ብለን ቡና ልንጠጣ ብንሄድ ... ተቀበሉን። ቆይ ግዴለም! እነዚህ የማይረቡ ጣልያኖች። እንዳው እምዬ ... ምስክሬ ናት፣ ዋጋቸውን ያላሳየኋቸው እንደሆነ። ግዴለም!" እያለ ቡጢውን ... በጣልያኖች ላይ ፎከረ። ኢትዮጵያውያን ባላገር ወታደሮች እስከዚህ ድረስ ... የእግዜር ሰዎች ነበሩ።

አማራዎች ምንም እንኳ ሙስሊሞችም ቢኖሩባቸውም፣ በአመዛኙ ... እና በጣሙኑ ሲበዛ በእግዚያብሔር አማኞች ናቸው። በጦር ሜዳም ... መጸለይ ይቻላቸው ዘንድ እያንዳንዱ ከፍ ከፍ ያለ ሹም ሳይቀር የራሱን ቄስ፣

የራሱን የንፍስ አባት ይዞ ነው ወደ ጦር ሜዳ የመጣው። ቄሶችም ሆኑ ካህ የራሳቸው የሆኑ ወታደሮች ያላቸው ከመሆኑም በላይ በጦር ግንባር ሜዳም ጠመን ይዘው ይሳተፋሉ፣ ይዋጋሉ።

ራሶችና ደጃዝማቾች የራሳቸው ተንቀሳቃሽ ታቦትም አላቸው። ራስ ካሣ በነፍ አባታቸው የሚመራ ተንቀሳቃሽ ቤተ ክርስቲያን (ታቦት) አላቸው። ከራስ ሥዩም ጋር ራሳቸው ዋናው አቡነም አብረው አሉ። እያንዳንዱ ወታደር በእጅ የተጻፈ ትንሽ የጸሎት መጽሐፍ አለችው። ታዲያ ጣልያኖች ይኼን የመሰለ ለፈጣሪው ያደ ህዝብ "እምነት የለሽ አውሬ ህዝብ ነው" ብለው ለአለም ህዝብ ይለፍፋሉ።

በየምሽቱ ሁለቱ ራሶች በትንሽ ድንኳን ውስጥ ባለች ተንቀሳቃ ቤተ ክርስቲያን ጀንበር በጠለቀች ቁጥር ለፈጣሪያቸው ሁሌም ለሰዓታት ጸሎት ያደርሳሉ። ድንኳኗ በጣም ጠባብ ስለሆነች በርካታው ከፍተኛ ሹማምንት ከድንኳኗ ውጪ በግማሽ ክበ ጸሎቱን ያደርሳል። ዋናው ቄስም በያንዳንዱ ምሽት ከፍ ባለ ተራራ መሳይ ነገር ላይ ወጥተው ከፍ ባለ መረዋ ድምጽ ጸሎታቸውን ለእግዚአብሔር ያደርሳሉ።

በጸሎታቸውም ያገራቸውን ድንበር በማን አለብኝነት ደፍሮ የመጣን የጠላ ሰራዊት ከሀገራቸው ጠራርገው ያወጡ ዘንድ፣ እግዚአብሔር ብርታቱን ሰጥ ይረዳቸው ዘንድ ሳይታክቱ በየምሽቱ ይለምናሉ፣ ይማጸናሉ። በያንዳንዷ ምሽ በፍጹም ለስላሳና ለጆሮ በሚስብ ድምጽ የሚጀመረውን መዝሙር ወይም ቅዳ በየዋሻውና በየቋጥኙ ስር፣ በየጥሻው ውስጥ ያለው በመቶ ሺ የሚቆጠረው ሠራ የወንዶች ድምጽ ይቀበልና ሲደግመው፣ ከነሱ የገደል ማሚቱው ተቀብሎ በጣም ሩ ላሉት ሲያስተጋባው፣ ይህ ነው ተብሎ መግለጽ የማይቻል ፍጹም ልብ የሚነ ሰውነት የሚያንቀጠቅጥ ስሜት ይሰማል። እኔ እንዲህ አይነቱን የዘወትር ጸሎ ስሰማ ሰውነቴን ይወረኛል። ይህ ነው ብዬ የማልገልጸው ስሜት ይሰማኛል።

በየቀኑ ልክ ጀንበር በሰሜን ተራራ ጀርባ ስትዞርና ወደቤቷ ስትገባ፣ ይጸል ከጠለቀችበት የሰሜን ተራራ አካባቢ የሚመጣ የሚመስል የራስ ካሣ የነፍስ አባት ቄ ድምጽ ተዓምራዊ በሆነ መልኩ ተራራዎችን አልፎ ምናልባትም እታች ጣልያኖ ሰፈር ድረስ ይሰማ ይሆናል።

“ሀቅን ይዘን ነው የምንዋጋ። እግዚአብሔርም ይኼን ያውቃል” ሲል የቄ ድምፅ፣ ወዲያው ከታች በመቶ ሺ የሚቆጠረው ሠራ የወንዶች ድምጽ “እግዚአብሔር ያውቃል” ሲል ያስተጋባል። “ጣልያኖች መሬታችንን ሊቀሙ ነው የመጡት። ይኼንንም እግዚአብሔር ያውቃል” ሲሉ ቄሱ፣ “እግዚያብሄር ያውቃል” ሲል የድምጽ ናዳ ይወርዳል።

“ጦራችንን ሰብቀን፣ ጎራዴያችንን መዝዘን፣ ጠመንጃችንን አንስተ እናባርራቸዋለን። እግዚአብሔርም ይረዳናል።”

“እግዚያብሄር ይረዳናል” ሲል ያ ሸካራ የገበሬ ወታደሮች ድምጽ ያስተጋባል። “እግዚያብሄር ሀቃችንን አይተህ፣ እውነታችንን ተረድተህ እርዳን” ሲል ያ ሁሉ ሰራዊት ወደፈጣሪው አንጋጦ ይለምናል።

ወዲያው ለተወሰኑ ደቂቃዎች ሁሉም ነገር ሰጥ ረጭ ይላል። በዚያ ጥቅጥቅ ጨለማ ፍጹም የሚያስፈራ ፀጥታ ይሰፍናል። ወዲያው ብዙም ሳይቆይ ከሁሉም አቅጣጫ ጭብጨባ ይሰማል። ፍጹም ልብ የሚነካ ጭብጨባ። መቶ ሺ እጆች በአንድ ላይ በአንድ ጊዜ ሲያጨበጭቡ፣ ጣሊያኖች ሲሰሙ ምን አይነት ስሜት እንደሚሰማቸው ባላውቅም፣ እኔን ግን ምንም አይነት የሰው ልጅ ጭብጨባ እንዲህ ልቤን ነክቶት አያውቅም።

ኢትዮጵያውያን በእንዲህ አይነቱ ጭብጨባ ሰራዊታችንን በመፍጀት ላይ ያለውን የተስቦ በሽታ ያባርራል ብለው ያምናሉ። ታዲያ እኛስ የማናምንበት ምን ምክንያት አለ? እናም ማጨብጨብ እንጀምራለን፣ አንዴ፣ ሁለቴ፣ ሶስቴ፣ እስከመጨረሻው።

24
የፋሽስቱ ጦር ሽንፈት

በኢትዮጵያ የፋሽት ኢጣሊያ ዋና ጦር አዛዥ ማርሻል ባዶሊዮ፣ በታህሳስ ወር መጨረሻ ግድም ላይ እንደ ዋና የጦር መምሪያው ወይም ጣቢያው መቀሌን መርጦ ከዋናው ጦሩ ጋር መቀሌ ከተማ ገብቶ ከተመ::

ማርሻል ባዶሊዮ መቀሌ ሲገባ በመቀሌና በመቀሌ ዙሪያ 62 ሻለቃ ጦር ማለት ወደ 62,000 ጦር ገደማና 350 መድፎች የያዘ ጦር ሰፍሮ ይጠብቀው ነበር:: በላይ እንግዲህ ባዶሊዮ መቀሌ ሆኖ ከመቀሌ በስተደቡብ ምዕራብ ከ100,000 በላይ የራስ የሚቆጠረውና የተወሰኑ አሮጌ መድፎችና ብዙ የአየር መቃወሚያ የታጠቀው የራስ ሙሉጌታ (የኢትዮጵያው የጦር ሚኒስትር) ጦር ከአምባላጌ እስከ ዛል ካባ ድረስ ተከለው ተዘርግቶ፣ ሽማግሌው የጦር ሚኒስትርም ድንኳናቸውን በአምባ አርአዳም ተክለው ይጠብቃሉ::

ሁለተኛው የጣልያን ክፍለ ጦር 30 ሻለቃ ጦርና 193 መድፎች ይዞ በአድዋና ገዢ በአክሱም መካከል ሰፍሮ በራስ እምሩ የጎጃሙ ገገርና በአያሌው ብሩ የሰሜን ጦር ተወጥሮ ፍዳውን ያያል::

ከአድዋ እስከ መቀሌ 140 ኪሎ ሜትር ገደማ የሚሆነውን ርቀት ጣልያኖቹ ሁለተኛውይ ጥርጊያ መንገድ ሰርተው አድዋን ከመቀሌ ጋር አገናኝተዋታል:: የኤርትራ ተወላጆች ክፍለ ጦር ሁለት ቦታ ተከፍሎ አንዱ እንጢቾ ሲሰፍር፣ ሁለተኛው ሀውዜን፣ በአድዋና በመቀሌ መካከል ግማሽ መንገድ ላይ ሰፍሯል::

የጣልያኖቹ ትልቁና ዋናው ደካማ ጎናቸው ከመቀሌ በስተቀኝ በኩል በተንቤን ያለው ጦራቸው ነው:: ይኼም በተንቤን ያለው የጣልያኖች ጦር በሁለቱ ራሶች ጦር ተከቦ በፍርሃት እየተንቀጠቀጠ ተቀምጧል::

ምንም እንኳ ጣልያኖች ከታህሳስ ወር መጀመሪያ ጀምሮ ጠቅላላውን የተንቤን ግዛት በቁጥጥራቸው ስር ቢያደርጉም፣ ተንቤን ባለው የኢትዮጵያ ጦር እየተወገሩ የተዝቤንን ዋና ከተማ አቢ አዲን ሳይቀር እየገፋ ለመጣው የኢትዮጵያ ሰራዊት አስረክበው መውጣት ተገደዋል::

ማርሻል ባዶሊዮ በተከታታይ በተንቤን ያለውን ጦሩን ለማጠናከር አዲስ ኃይል ቢልክም በተንቤን ያለውን የኢትዮጵያ ሰራዊት ሊቋቋመው ባለመቻሉ፣ በድጋሚ መጀመሪያ 10 ሻለቃ ጦር ልኮ በመጨረሻ የፋሽስቱን 28 ኦዮበሬ ብርጌድ ጦር ልኮ ይኼው ብርጌድ ጥር 8 ቀን ተንቤን ገባ::

ማርሻል ባዶሊዮ በተንቤን ያለውን የኢትዮጵያ ሰራዊት ብዛትና ብቃት በትክክል የተረዳ አይመስልም:: ይኼው አላዋቂነቱ ለሽንፈቱ አይነተኛ ምክንያት ነበር:: በአዲስ አበባ ያሉ የውጭ ሀገር ጋዜጠኞች ጣልያኖች መቀሌን በቀላሉ መያዛቸውን ሰምተው ብዙ ሳይቆይ ከመቀሌ 100 ኪሎ ሜትር ርቆ ኤርትራ ድንበር አካባቢ ከፍተኛ ጦርነት መካሄዱን ሲሰሙ በጣም ተገረሙ:: ይኼ ሊሆንስ ይችላል? ብለው ጠየቁ:: አዎ ይችላል:: የጣልያንና የኢትዮጵያ ጦርነት በሌላው አለም ከሚካሄዱ የአለም ጦርነቶች በብዙ መልኩ ይለያል::

ይኼ ጦርነት አንድ የተወሰነ የጦር ሜዳ ግንባር አልነበረውም፤ ወይም ደሞ ሁለቱ ጦሮች በአንድ መስመር ገብተው አይዋጉም:: ሁሉም ተንቀሳቃሽ ጦርነት ነበር:: የጣልያኖቹ ጦር ወደ ኢትዮጵያ እየገባ፣ ከጦርነት ስልት አንጻር ወሳኝ ናቸው የሚላቸውን ከተሞች በቀላሉ እየያዘ፣ በነዚህ ከተሞች ኃይሉን እያጠናከረ፣ ምሽጎች እየሰራ፣ ከተሞችን ከከተሞች ጋር በጥርጊያ መንገድ እያገናኘ ይቀመጣል:: አድዋ፣ አክሱም፣ መቀሌ፣ አዲግራት፣ እንጢቾ፣ ሀውዜንና ሌሎችንም ከተሞች እየያዘ እና በጥርጊያ መንገዶች እርስ በእርስ እያገናኘና ኃይሉን በነዚህ ከተሞች እያጠናከረ ሰፍሯል::

እንዲህ ጣልያኖች ዘለው ከተማ እየገቡ ቢቀመጡም በከተሞች መካከል ያለው ቦታ ግን ፈጽሞ ያልተጠበቀ ስለነበር በነዚህ ባዶ መሬቶች ላይ የኢትዮጵያ ሰራዊት እየገባ እንደልቡ ሲንሸራሸር ይውላል:: በተንቀሳቃሽ ጦርነት፣ በማያውቁት ሀገር፣

በጣም አስቸጋሪ በሆነ ተራራማ ቦታ ላይ ጦር መምራት ራሱን የቻለ ልዩ ጥበ[...] የተሞላበት የጦርነት ስልት ያስፈልገዋል።

ማርሻል ባዶሊዮ ኢትዮጵያውያን በጣልያኖች የተያዙባቸውን አገ[...] ለማስለቀቅ ጥቃት ያስነዝራሉ ብሎ በጣሙን ያምንና ተስፋ ያደርግ [...] ኢትዮጵያውያን ከተሞቻቸውን ለማስለቀቅ ጥቃት ሲሰነዝሩ ጥሩ አድርጎ ከ[...] ምሽግ ውስጥ ሆኖ የኢትዮጵያን ሰራዊት ወገብ ሰብሮ፣ በታትኖ ሊያጠፋው አ[...] እየከጠረት በተስፋ ይጠብቃል።

የኢትዮጵያው ሰራዊት መሪዎች ማርሻል ባዶሊዮ ባቀረበላቸው ቁና እንቁላ[...] ላይ ሄደው እንደማይቀመጡ ሲረዳ ትግስቱ አልቆ፣ ራሱ ጥቃት ሊሰነዝርና እ[...] የነሳውን የተንቤን ጉዳይ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ሊፈታ ወሰነ ልዩ ወታደራዊ ስል[...] ይነድፋል።

ዋናው የማርሻል ባዶሊዮ እቅድ በሰሜን የኢትዮጵያ ጦሮች (የራስ ካሣ፣ የራ[...] እምሩ እና የራስ ሙሉጌታ ጦሮች) እርስ በእርስ እንዳይደጋገፉ እንዲ ማቆም ነ[...] በዚህም ስልቱ መሰረትም የተወሰነ ጦሩን ወደ ጊባ ወንዝ በመላክ ጥቃ[...] በሚሰነዝርበት ጊዜ ራስ ሙሉጌታ አጋዥ ጦር ወደ ተንቤን እንዳይልክ ቀረው ጦ[...] እንዲያግድ ያደርጋል። በመቀጠልም፣ በአክሱምና በአድዋ ያለውን ጦሩን በሻግ[...] ተንቀሳቅሶ ራስ እምሩን ፊታ እንዲገጥ አዘዘ፣ በተንቤን ያለውን ጦሩን ጥቃ[...] እንዲሰነዝር ያዛል።

የጣልያን ሰራዊት በተንቤን አካባቢ በምትገባል መንደር ከአድዋ ወደ መቀ[...] በሚወስደው መንገድ ላይ ተጠናክሮና ተሰብስቦ ሰፍሯል። እነስ ያለ ሌላ የጣልያ[...] ሰራዊት ድግሞ አዲይ በባዛ ላይ 10 ኪሎ ሜትር በስተምዕራብ በሁል ርቀ ሲሰፍ[...] ሌላ ደግሞ ያለ 3 ሻለቃ ጦር ከ28 ኦክቶበሬ ብርጌድና ሌሎች በርካት ያሉ የኤርት[...] ተወላጆች ሻለቃ ጦር ጋር ከራስ ካሣ ዋና ጦር 7 ኪሎ ሜትር ገደማ ርቀ በወሰ[...] እንደሰፈረ ጥቃት እንዲሰነዝር ይታዘዛል።

በተንቤን በራስ ካሣ ጦር ላይ ጥቃት እንዲሰነዝር የታዘዘው የዚህ ጦር ዋ[...] አዛዥ ጀኔራል ዲያመንቲ ይባላል። በኋላ ላይ ባገኘነው መረጃ ጀኔራል ዲያመን[...] በጣልያን ሰራዊት ውስጥ ሲያገለግል ተራ መቶ አለቃ የነበረ እና ደካማ የጦር መ[...] ነበር። ስለዚህም ከጥር 20 እስከ ጥር 24 ቀን 1936 ድረስ በተደረጉ ጦርነ[...] የመራው ጦር ውጤት ጥሩ ማስረጃ ነው። ጀኔራል ዲያሜንቲ በጥቅሉ ነገ[...] እንጋጠ በሚያየው ተራራ ውስጥ ሙሉው የራስ ካሣ እና የራስ ሥዩም ጦ[...] መሰፈሩንና ይኼ ጦር በዘምንነቱ ለቁርስም እንደማይበቃ የተረዳ አይመስልም።

ጀኔራል ዲያሜንቲ ስለሁለቱ ራሶች ጦር አሰፋፈርና ኃይል ምንም መረጃ [...] በኋላ ወታደሮች አግኝተው በአመጡት የብርጌዱ ማስታወሻ ደብተር [...] ማንበብ ችለናል። የብርጌዱ ጸሐፊ ሁሉንም ነገር በጥንቃቄ ጽፎታል። በብርጌዱ [...] መመዝገቢያ ደብተር ላይ እንደምናነበው "28 ኦክቶበሬ ብርጌድ ከጣልያን [...] እኔ አዲስ አበባ የገባሁ ዕለት ነው። እኔ ደብረ ታቦር ስደርስ ይኼ [...] ኤርትራ ገብቷል። 28 ኦክቶበሬ ብርጌድ ከመቀሌ ተነስቶ ተንቤን የገባው የኛ [...] ጦር ሰፈሩን ከደብረ አባይ ነቅሎ አቢይ አዲ በገባ ማግስት ጥር 2 ቀን ነበር።

ጥር 15 ቀን ይኼው የብርጌዱ ጸሐፊ ሲጽፍ፣ "አልፎ አልፎ በጦር ሰፈራችን [...] ወደ ወራዩ አካባቢ የተወሰኑ የኢትዮጵያ ወታደሮች በቡድን በቡድን እየሆኑ [...] ይታያሉ። ታዲያ በነዚህ ባላገሮች ላይ መትረየሶቻችን መጮኽ ሲጀምሩ [...] ባላገሮች ከአይናችን ይሰወራሉ" ይልና፣ ይኼው የብርጌዱ ጸሐፊ በመቀጠል፣ [...] ተራራው ላይ አቢ አዲ አካባቢ የኛ ሰላዮች በአመጡት ወሬ በጣም ብዙ [...] ሀገር የባላገር ወታደሮች ሰፍረዋል። የኛ አውሮፕላኖች በየቀኑ በቦንብ [...]ደበድቧቸውና፣ በመጨረሻም የኛ አብራሪዎች በአመጡት ዘገባ እንደምንረዳው [...] ምንም የባላገር ወታደሮች ብትንትናቸው መውጣቱንና በተራራው ውስጥ [...] ሃይል የሚያሰጋ ነገር እንደሌለ" ጠቁሞ ጽፏል።

ከብርጌዱ ማስታወሻ ደብተር እንደምንረዳው፣ ጀኔራል ዲያሜንቲ የጣልያን [...]ፕላኖች በየቀኑ በሚያዘንቡት የቦንብ ዝናብ የራስ ካሣን ጦር በታትኖ ማጥፋት [...] ንቅንቅ እንኳን እንዳላደረገው አልተረዳም።

ቀኑን ሙሉ ከራሶቹና ከሌሎች ከፍተኛ ሹማምንቶች ጋር በደብረ አምባ አፋፍ [...] ተቀምጠን ለረጅም ሰዓት በጦር ሜዳ አትሊ መነጽር የጣልያኖችን ሰፈር ወራዩ [...] እንመለከታለን።

ወደ ወራዩ የጣልያኖች የጦር ሰፈር ከመቀሌ በርካታ ታንኮች፣ ብረት ለበስ [...]ርካሪዎችና ምግብና ሌላ የጦር ቁሳቁሶችን የጫኑ የጭነት መኪናዎች ቀኑን [...] ይጎርፋሉ። ራስ ካሣ በጦር ሜዳ መነጽራቸው የጣልያኖችን የጦር ሰፈር ሲቃኙ [...] "እይይ... የፈረንጅ ነገር" አሉና፣ በመቀጠል እነዚህ ጣልያኖች ፈረንጅም [...] መሰል፣ አሁን ማያመት ፈረንጅ እንዲህ አይነት ነገር እንደምን ይሰራል? [...] አልፈጠረባቸው ልበል?" አሉ። ቀጥለውም "እየህ ጌታው ልብ አድርግማ" [...] ወደ ወራዩ እያሳዩን "አሁን ወታደሮቼን ትዕዛዝ ብሰጣቸው ጀንበር [...] ሳይ ለወሬ ነጋሪ ሳያስተርፉ ይጨፈጭፏቸው ነበር" አሉኝ።

ይሁን እንጂ ራስ ካሣ ለወታደሮቻቸው ትዕዛዝ አልሰጡም። ይኼን ያደረጉበት [...] የንጉሠ ነገሥቱን ጥብቅ ትዕዛዝ ላለመጣስ ነበር። ንጉሠ ነገሥቱ ኃይለ [...]ላሴም የጦር አበጋዞቻቸው በሰጡት ጥብቅ ትዕዛዝ "ምን ጊዜም ቢሆን

የኢትዮጵያ ሰራዊት ከመከላከል አልፎ ቀድሞ ጥቃት እንዳይሰነዝር" ደጋግመው አስጠንቅቀዋል።

ንጉሠ ነገሥት ኃይለ ሥላሴ አሁንም የመንግስታት ህብረቱ "የጣልያን ወራሪን ሰራዊት ያቆምልናል" ብለው ያምናሉ። ንጉሠ ነገሥቱ ኃይለ ሥላሴ በዚህ ስህተት በተሞላበት እምነታቸው ከባድ ጥፋት ሰርተዋል። የኢትዮጵያ ሰራዊት ልክ እንደ ገናናው ምኒልክ ጊዜ የጣልያንን ሰራዊት ልክ ሊያስገባው የሚችልበትን ብዙ እድል አሳጥተውታል ።

ማርሻል ባዶሊዮ የኢትዮጵያን ጦር ቆስቁሶ ጥቃት እንዲሰነዝር መገፋፋቱ እንዳልተሳካለት ሲረዳ ጥር 15 ቀን የሚከተለውን ትዕዛዝ ለጀነራሎቹ አስተላለፈ።

1ኛ ወራዩ ያለው ጦር የማስመሰል ጥቃት ሰንዝሮ የኢትዮጵያን ሰራዊት ከመሸገበት እንዲወጣ ገፋፍቶ ወደ ጦር ሰፈሩ በመመለስ፣ ሌላ ኃይል እስኪደርስለት ድረስ እንዲከላከል፤

2ኛ በተመሳሳይ ሁኔታ አዲ ዙሀባ ያለውም ጦር ይንቀሳቀስና ከምስራቅ በመንቀሳቀስ ላይ ያለውን ጦር እንዲጠብቅ ያዝዝና፤ ዋናውን የማጥቃት ዘመቻ አባሪ ያለው ጦር እንዲያደርግ ወስኖ ለጀነራሎቹ ትዕዛዙን ያስተላልፋል። በወፍራሙ የ28 ኦቶበሬ የጦር ሜዳ ማስታወሻ መዝገብ ጥር 20 ቀን ላይ እንደተጻፈው "ትናንትና ማታ አዛዦችን ለበታች ሹሞች የማጥቃት ዘመቻውን እቅድ እንዳስረዳው፣ የዚህ ጦር ዋናው አላማ አቢ አዲን መያዝና እስከ ገባ ወንዝ ድረስ ያለውን ቦታ መያዝ ሆኖ፣ ወታደራዊ እቅጣጠር በ4:00 ሰዓት በኮሎኔል ቼቼዮኒ (Ceccioni) የሚመራው መድፈኛ ጦር ወደፊት ቀድሞ ሄዶ መድፎቹን አቁሞ በመትረየሶች እየተረዳ ከጀርባው፣ ከጦር ሰፈር ተነስቶ ወደ አቢ አዲ የሚዘልቀውን ጥቁር ሸሚዝ ለባሽ የፋሽስት እግረኛ ጦር ሽፋን እንዲሰጥ" ይላል።

ይኼም የመጨረሻው የብርጌዱ ጸሐፊ የመጨረሻ ቃል ነበር። የመጨረሻው ገጽ የማስታወሻው ደብተር በደም ተጨማልቋል። የብርጌዱ ጸሐፊ በጽህፈት ስራው ላይ እንዳለ ከኢትዮጵያ ወታደር በተተኮሰች ጥይት ግንባሩን ተመቶ ተደፍቷል።

በዚያች ቀን በማለዳ ስንነሳ ጣልያኖች በኛ ላይ ሊዘምቱ ከሰፈራቸው መንቀሳቀሳቸውን እንኳ አናውቅም ነበር። ልክ ፀሐይ እንደወጣች እነዚያ የሰማይ ላይ የቀርቀሮ አሞራዎች መጥተው አቢ አዲን ወደ ጎን ትተው ደብረ አምባንና ጀኘ አካባቢ ያለውን የደጃዝማች አበራንና ግንባር ቀደም ጦራችንን የቦንብ ናዳቸውን ያወርዱበት ጀመር።

እንደ ሁልጊዜው ሁሉ ድንኳናችንን ነቅለን በደጃዝማች አበራ ጠባብ ዋሻ ሁና ቀማምሰን እየተቻኮልን ወደ ራስ ካሣ ድንኳን አመራን። የራስ ካሣ ድንኳን

ከደጃዝማች አበራ ሰፈር ግማሽ ኪሎ ሜትር ያህል ይርቃል። የሁለቱ ራሶች ዋሻ ዛሬ ባይ ነች። አንድ የራሶች አሸክር የሆነ ገመድ ነገር እየተበተበ ራሶቹ ከአንድ ሰዓት በፊት በማለዳ ተነስተው ወደ ቤተ ክርስቲያን መሄዳቸውን ነገረንና እኛም ወደዚያው አመራን።

በተራራው መሀል በሰው ልጅ እጅ የተፈለፈለችና የተጠረበችው ይቺ የዋሻ ቤተ ክርስቲያን፣ እንዲህ ዛሬ ወና ሳትሆን በፊት በጊዜዋ የተደነቀችና የተወደደች ሳትሆን እንደማትቀር ጥርጥር የለውም። ከዋሻዋ ቤተ ክርስቲያን ስንደርስ በሩ አካባቢ ሆከት ያሉ ዘቦች ቆመዋል። ከዘቦቹ አንዱ የጣልያን የመቶ አለቃ ማዕረግ ያለው ወታደራዊ ልብስ ለብሶ የብረት ቆብ ደፍቷል። ይኼ ወታደር ከወር በፊት በደጃዝማች ማሩ በተመራ ጦር ተንቤን ውስጥ በተካሄደ ጦርነት የቆሰለ ነው። ከጦርነቱ በኋላ ራሱ የገደለውን መቶ አለቃ የጦር ሜዳ ልብስ አውልቆ ለብሷል። በወርቅ ቀለም የተነደፈችውን የጣልያን መንግሥት መለያ ምልክት እንኳ በጣጥሶ ለመጣል አልሞከረም። እንዳው ዝም ብሎ ለብሶታል።

በጣም እየተቻኮልን ገብተን ጨለማ በተላበሰችው ዋሻ ውስጥ በምንጣፍ ላይ ከራሶቹ ጎን ከመቀመጣችን አንድ አሽከር እያለከለከ መጥቶ፣ አፉን በሸማው ጫፍ ሸፍኖ፣ ለራስ ካሣ በጆሯቸው የሆነ ነገር ነገራቸው። ራስ ካሣ ፍጹም በተረጋጋ ድምጽ ወደ ራስ ሥዩም ዞር ብለው "ጦር መጣ" አሉ። ከራስ ካሣ ጀርባ ቆሞ የነበረ የራስ ካሣ የክብር ዘብ አለቃው ቀኛዝማች አበበ፣ ከራስ ካሣ ምንም አይነት ትዕዛዝ፣ ሳይጠብቅ ከዋሻዋ ቤተ ክርስቲያን ከመውጣቱ እነዚያ አስደንጋጭ ጡሩንባዎች ጩኸታቸውን ለቀቁት።

የጡሩንባዎችን የማስጠንቀቂያ ጩኸት የገደል ማሚቶዎች እየተቀበሉ ሲያስተጋቡት በጣም ርቆ ለሰፈረውም የኢትዮጵያ ሰራዊት ሁሉ ይሰማ ነበር። በየቦታው ተቀምጠው እስካሁን ፀሐይ ይሞቁ የነበሩ ወታደሮች በፍጥነት መሳሪያቸውን ከየጣሉበት ስርቻ እያወጡ ማቀባበል ጀመሩ። በተወሰኑ ደቂቃዎች ልዩነት ከቤተ ክርስቲያኗ ፊት ለፊት ያለቺውን ትንሽ ዳገታማ ሜዳ በብዙ ሺ የሚቆጠሩ የሚሸልሉ፣ የሚፎክሩና በወኔ የሚንቀለቀሉ ወታደሮች አጥለቀለቋት።

"ጦር መጣ! ጦር መጣ! ጦር መጣ!" እያለ አንዱ ከአንዱ እየተቀበለ ያስተጋባል። የሚፎክሩት ወታደሮች በዛሬው ውሏቸው ስንት የጣልያን ወታደር አንገት እንደሚቀነጥሱ ጮክ ብለው እየፎከሩና እየሸለሉ፣ እየጮሁ ቁልቁል ወደ ጦር ሜዳ ተንደረደሩ።

አንድ ከታች ከጦር ሰፈር የመጣ መልክተኛ እንደተናገረው ጣልያኖች ገፍተው ወደ ደብረ አምባ ተቃርበዋል። በደብረ አምባ ያለው የአበራ ጦር ብቻ ነው። በጦር ሜዳ መነጽሬ እንደቃኘሁት እስከ ወራዩ ድረስ ያለውን የጦር ሜዳ መቃኘት ጀመርኩ።

በትክክል ባለ ነጩን ሸማ የኢትዮጵያ ወታደር ከፋሽቱ ወታደር ለይቼ ማየት ይቻለኛል። ወታደሮቻችን በድፍረት እና በታላቅ ወኔ ወደፊት ይገፋሉ፤ ይሮጣሉ።

የመጀመሪያው ረድፍ ገና ሳይተኩስ ይረግፋል። በመድፍና በመትረየስ እየታገዙ ጣልያኖች የኢትዮጵያውን ሰራዊት ክርቀት እየመቱት እነሱም ወደፊት ይገፋሉ። ይኼም አልበቃ ብሎ እነዚያ አውሮፕላኖች ከመቼውም ጊዜ በላይ በጣም ዝቅ ብለው፣ ምናልባትም የአውሮፕላኖቻቸው ጎማ የኢትዮጵያን ወታደር እናት እስኪነካ ድረስ ዝቅ በማለት በመትረየሶቻቸው የኛን ጦር ያረግፉታል።

ነጩ ጎርፍ የወደቀውን የጦር ሜዳ ጓዱን እየዘለለ ወደፊት ይነጉዳል። አንዱ ሲወድቅ ሌሎች አስሮች እየተተኩ፣ አስሮች ሲወድቁ ሌሎች ኀምሳዎች እየተተኩ የጣልያንን ጦር እንደ ደራሽ ውሃ አጥለቀለቁት።

የኢትዮጵያው ሰራዊት ከጎኑ እና ከፊቱ የሚወድቀውን የጦር ሜዳ ወንድሙን እየዘለለ ሲጓዝ ከላይ ከተራራው ጫፍ ሌሎች በሺ የሚቆጠሩ ተዋጊዎች ድንጋዩን እየዘለሉ፣ እየፎከሩና እየሸለሉ ወርደው ተቀላቀሉ። የማያልቅ የሰራዊት ጎርፍ ራስ ካሣ ተዋጊ ወታደሮቻቸውን ሲያዩ ፊታቸው በደስታ ፈካ።

ራስ ካሣ ወደኔ ዞር ብለው፣ "አየህ ጌታው፣ ኢትዮጵያዊ እንዲህ ነው የሚዋጋው" አሉኝ እና ቀጥለውም "እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ሲወለድ ጀምሮ ጀግና ተዋጊ ነው። እንዴ ውጊያ ውስጥ ከገባ በዚህ ምድር ላይ ምንም የሚያቆመው ኃይል የለም" አሉኝ፤ የኢትዮጵያው ወታደር እታች አጦር ሜዳ በጦሩ የጠላቱን ደረት እየሰነጠቀ በጎራዴው አንገት ሲቀላ እያሳዩኝ።

ትንሽ እንደ መተከዝ ብለው፣ "አየህ ጌታው፣ ደግሞ ኢትዮጵያዊም አንዴ ሸሽት ከጀመረ የሚያቆመው ምንም ኃይል የለም" አሉኝ፤ እኛ ከቆምንባት አፋፍ ጀምሮ እንደ ጎርፍ ቁልቁል እያጓራ የሚወርደውን የኢትዮጵያ ሰራዊት መንገድ እየለቀቁለት። የተወሰኑ ወታደሮች በቡድን በቡድን እየሆኑ ከጾኚ ወንዝ ዳርቻ የቆሰሉ የጦር ሜዳ ወንድሞቻቸውን በእንጨት ቃሬዛ እየተሸከሙ ሸቅብ ወደ ጦር ሰፈራችን ይወጣሉ።

እነዚሁ በቃሬዛ ቁስለኛ ተሸክመው ወደ ጦር ሰፈራችን በመቃረብ ላይ ያሉ ወታደሮች ከርቀት "ጣልያኖች ሸሹ! ጣልያኖች ሸሹ!" እያሉ በታላቅ ደስታ ወደኛ ይጮሃሉ። ይኼን አስደሳች ዜና አንዱ ከአንዱ አፍ እየተቀበለ ሲያስተጋባ፣ በጣም ርቀው የሰፈሩት ሴቶች ከልጆቻቸው ጋር ሆነው ባሎቻቸው ከጦር ሜዳ እስኪመለሱ ድረስ እንጀራ እየጋገሩ፣ ወጥ እየሰሩ በታላቅ ትግስት የሚጠብቁት እናቶች ሳይቀር ሰምተው እልልታቸውን አቀለጡት።

ከሰዓት በኋላ ላይ የደጃዝማች ኃይሉ ከበደ መልክተኛ ከራስ ካሣ ፊት ቀርቦ፣ መልፋ ላይ ከ3ኛው የጣልያን ክፍለ ጦር ጋር የሞት ሽረት ትግል የሚያካሂደው

የደጃዝማች ኃይሉ ከበደ፣ የደጃዝማች ወርቅነህ እና የበጅሮንድ ለጥይበሉ ጦር ለድል በቃ፤ ጣልያኖች በአዲ ዘሀባና በአባሬ ያላቸውን ጦር አስነስተው እየመጡባቸው ስለሆነ ሳይከበቡ በፊት ራስ ካሣ ጦር እንዲልኩላቸው ርዳታ እንደሚጠይቁ አስረዳ።

ወደ ደብረ አምባ ገፍቶ የመጣውን የጠላት ጦር የአባትና ልጆቹ ጦር (የካሣ እና የልጆቻቸው ወንድወሰንና አበራ) ወታደሮች ብትንትናቸውን አውጥተው አባረሩት፤ ራስ ካሣ ከጦራቸው ቀንሰው በደጃዝማች ወንድወሰን መሪነት ለሁለቱ ደጃዝማቾች ተጨማሪ ኃይል ላኩላቸው።

የማርሻል ባዶሊዮ የውጊያ ስልት፣ ማለት የራስ ካሣን ጦር ቆስቁሶ ከመሽገበት አውጥቶ፣ ወገቡን ሰብሮ ለመበታተንና ዋናው ጦሩ የአባሬን ገደል በተሳሉ እንዲያልፍለት ያቀደው፣ ሳይሳካለት መቅረት ብቻ ሳይሆን ጦሩ እጅግ በጣም ከፍተኛ የሚባል ጉዳት ደረሰበት። አሁን ጦራችን በሶስት የጦር ሜዳዎች ተከፋፍሎ ስለሚዋጋ የጦር ሰፈራችን አቢ አዲ ወታደር አልባ ሆናለች።

ይሁን እንጂ የጣልያን አውሮፕላኖች እንዲህ ባዶ የሆነችውንና በአብዛኛው ሴቶችና ህጻናት የመሸጉባትን አቢ አዲን ፍጹም አረመኔያዊነት በተሞላበት መልኩ በቦምብ ደበደቧት። እነዚህ የቀርቀሮ ቁራዎች አቢ አዲን እየዞሩ በትላልቅና በትናንሽ ቦምቦች ደብድበው ይኼዳሉ። በቦምቡ ፍንዳታ የተነሳው አቧራ ገና በአየር ላይ ተበትኖ ሳይጠፋ ደግሞ ሌሎች ይመጡና ይደበድቧታል። በዚህ መልኩ ስድስት አውሮፕላኖች መጥተው አቢ አዲን ደብድበው ሲመለሱ፣ ሌሎች ሰባት አውሮፕላኖች መጥተው ሲደበድቡ ውለው ሲሄዱ፣ ሌሎች እየመጡ እየደበደቡ በዚሁ አረመኔ ተግባራቸው እስከ ጀንበር መግቢያ ድረስ ቀጠሉበት።

በደጃዝማች ወንድወሰን የሚመራው የራስ ካሣ ጦር መልፋ ከመሸ በኋላ ስደርስ የደጃዝማች ኃይሉ ከበደና የደጃዝማች ወርቅነህ ጦር በጣልያኖች ዘመናዊ ጦር መሣሪያ እጥር ተከቦ ይደበደብ ነበር። የነዚህ ሁለት ደጃዝማቾች ጦር በጣልያኖች የጦር እጥር ተከቦ፣ ማምለጫ በሌለው ወጥመድ ውስጥ ገብቶ እየተደበደበ እያለ ኃይለኛ ወጥሮ ሲከላከል አመሸ። በዚህም የመከላከል ውጊያ ደጃዝማች ወርቅነህ ክፉኛ ቆሰሉ።

በሁለተኛውም ቀን የጣልያን ጦር እንደገና ኃይሉን አሰባስቦ ከወራዩ ተነስቶ ለሁለተኛ ጊዜ ወደ ደብረ አምባ በመዝለቅ ጥቃት ሰነዘረ። ዛሬም በጾኚ ወንዝ ዳርቻ በግራ ለወንድ የእጅ በእጅ ቅልጥ ያለ ውጊያ አደረጉ። ኢትዮጵያውያን ጀግኖች በታላቅ ጀግንነት የጣልያን መትረየሶች ሳያግዷቸው ጦራቸውን እየሰበቁ፣ እየጮሁ፣ እየፎከሩና እየሸለሉ፣ በታላቅ የጀግንነት ወኔ እየጮሁና እያጓሩ ጣልያኖች መሀከል በመግባት የፋሽቱን ጦር ወታደሮች በጦራቸው እየሰነጠቁ፣ በጎራዴያቸው አንገቱን እየቀሉ መድረሻ አሳጡት።

ሬፈድሬድ እንዳለ ኢትዮጵያውያን ጀግኖች የጣልያኑን ጦር ከደጁ ... ገደል ስር አስጠግተው በመክበብ ማምለጫ አሳጥተው ጠዘጠዙት። እንዲህ ... አጥቶ በያንዳንዷ ደቂቃ ሞቱን እየጠበቀ ተስፋ ቆርጦ የቆዘነውን የፋሺስት ... ከታች ከወራዩ 3 ታንኮች መትረየሶቻቸውን ከርቀት እያንጣጡ ሲረዱት ... ገሰገሱ።

እነዚህ ሶስት ታንኮች፣ የኢትዮጵያውያን አርጌ ጠመንጃዎች ... ሳያበሳቸው ፊታቸው ያለውን ሁሉ እየጨፈጨፉ የሚሄዱት ብረቶች፣ የሚያገኙ ... ጠፍቶ ወደፊት ገሰገሱ። ድል በእጃቸው ገብቶ የነበሩት ብቸኞቹ የኢትዮጵያ ... ከነዚህ ታንኮች በሚተኮሱ የመትረየስ ጥይቶች መውደቅ ጀመሩ። በዚች ... እድል ፊቷን አዙራ ድል ለጣልያኖች የገባች መሰለች።

እንዲህ አንጎል በሚያደርግ ጦርነት ኢትዮጵያውያን በአርጌ ጠመንጃ... በጦርና በጎራዴያቸው ባንድ ወገን፤ ደግሞ ፋሽስቶች የዘመኑን ዘመናዊ የጦር መ... ታጥቀውና ይኼም አነሰ ተብሎ በታንክ በመታገዝ በሚጠዛጠዙበት ... የሚረግፉትን የኛን ጦር አባሎች ሳይ፣ ራስ ካሣ "ኢትዮጵያውያን እንደ ማፈግ... ከጀመሩ ወደፊት የሚገፋቸው ምንም ኃይል የለም" ያሉኝ ድንገት ትዝ አለኝና ... ሀዘን ተሰማኝ። ድል በጃቸው ገብቶ የነበሩት ጀግና ኢትዮጵያውያን በነስቱ ታንክ ኃይል የሚረቱ መሰለ፤እንዲህ ድል ለጣልያኖች የሆነ በመሰለበት ሰዓት እነ... ሽማግሌ ሹም ፊቱን አዙሮ ወደ ታንኮቹ ሲሮጥ አየሁ።

ሽማግሌውን ሹም ያዩ በርካታ ኢትዮጵያውያን ጀግኖች ተከተሉት። ሽማግሌውን ሹም መጀመሪያ ላይ መቶ የሚሆኑ ሲከተሉት፣ መቶዎቹን በሺ... የሚቆጠሩ ይከተሉ ጀመር። እንዲህ ወደ ታንኮቹ የሚሮጠውን የመጀመሪያ ረድ... ጀግኖች የጣልያን ታንኮች ከሩቁ ወደ መሬት ያስተኟቸው ጀመር። በጣልያን ታንክ ጥይት ተመትቶ በወደቀ አንድ ወታደር አስር ሌላ ጀግኖች እየተተኩ፣ የወደቀ የጦ... ሜዳ ወንድማቸውን እየዘለሉ ወደፊት ገሰገሱ። የጣልያን ታንኮች ያለማቋረጥ በጥይ... ተግባራቸው ቢቀጥሉም፣ በታንኮቹ ዙሪያ የወደቁ ኢትዮጵያውያን ጀግኖች ... ቢከመርም፣ ይኼ ጀግኖቹን ወደኋላ ሳይስብ ጀግኖቹ አሁንም የወደቁ የጦር ጓ... ጓዶቻቸውን እየዘለሉ ወደፊት ገፉ።

አሁን አንዳንዶቹ በጣም ወደ ታንኮቹ ተጠግተው ቀዳዳ እየፈለጉ እየሞከሩ ... ለመተኮስ ሲሞክሩ ብረት ለበሶቹ ታንኮች በጀግኖቹ ላይ ያለምንም ... እየወጡባቸው ወደፊት ገሰገሱ።

የተንቤን ሙቀት ታንከኞቹን የላይኛውን መግቢያ በር እንዲከፍቱ ... አስገደዳቸው። ይኼንንም ሰፊ ቀዳዳ ያዩት ጀግኖች ጦራቸውን ሰብቀው በመሄድ ... ባለው ታንክ እየሷጠጡ ወጥተው ወደ ውስጥ ወደ ታንኩ ጓዳ መውረወር ጀመሩ። ... ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ የመጀመሪያዋ ታንክ ድምጿን አጥፍታ ...

...ቆመች፣ ... ፀጥ እርጭ አለ። የመጀመሪያዋን ታንክ እድል እጣ ፈንታ ያዩት ...ለሶቹም ... ታንኮች ፊታቸውን አዙረው ወደ ጦር ሰፈራቸው ወደ ወረዩ መፈርጠጥ ጀመሩ።

በሸሽት ላይ ካሉት ሁለቱ ታንኮች አንዷ የተንዛዜን አሸዋማ መሬት ከዳትና ... አሸዋ ታስራ ስታንገራ፣ አሁንም በርካታ ነጭ ሸማ ለባሽ ጀግኖች ከታንኳ ... ላይ ወጥተው ጦራቸውን ሰብቀው ሲወረውሩ ታንኳ እየዞረ እርምጃ ጸጥ ... ሆኖ ሁለተኛዋ ታንክ ሮጣ አመለጠች።

ኢትዮጵያውያን ጀግኖች አንድ ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ በባዶ እጅ፣ በጦርና ... ሁለት በዘመኑ አሉ የተባሉ ዘመናዊ ታንኮች ማረኩ። ምንም እንኳ ለሁለቱ ... ከሁለት መቶ በላይ ውድ የኢትዮጵያ ጀግና ልጆች ውድ ህይወታቸውን ... ሁለም፣ ታንኮቹን በእጃቸው አስገቡ።

በዚህ መሀል ጥገኛው መንገድ ሁሉ እግሬ እውጪኝ የሚሸሸውን የጣልያን ... ኢትዮጵያውያን ጀግኖች እያባረሩ፣ በገባበት ጉድጓድ እየገቡ እንገቱን ይቀሉት ... እንዲህ የጣልያኑ ፋሺስት ጥቁር ሸሚዝ ለባሽ ጦር እየሸሸ በጥሩ ሁኔታ ... የጦር ምሽጉ ወረዩ እየገባ ሲሸሽግ፣ ኢትዮጵያውያን ጀግኖች የወረዩን ... ሰብረው በመግባት ጦራቸውን እየሰበቁ፣ ጎራዴያቸውን እየወናጨፉ መሀሉ ... መሽጎ የከበረው የጣልያን ጦር የደገነው መትረየስ ፋይዳም ስላልከለረው ... ጥሶ በጠመንጃው አፈሙዝ ላይ በሰካው ሳንጃና ከሽጉጦቹ ... ጥይቶች መከላከል ጀመረ። በእጅ ለእጅ ውጊያ ወደር የማይገኝላቸው ... የኢትዮጵያ ልጆች የጣልያኑን ሰራዊት መድረሻ አሳጡት።

የወረዩው ውጊያ በኢትዮጵያውያን ድል አድራጊነት እንደተፈጸመ ከብዙው ሺህ ... ሰራዊት ውስጥ ወደ ሶስት መቶ የሚሆኑ ብቻ ቀርተው፣ እነሱም ... ሁለት ቀናት ሲከላከሉ ቆይተው በመጨረሻ በሺዎች የሚቆጠሩት ... እጣ ደረሳቸው።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ደጃዝማች ኃይሉ ከበደን፣ ደጃዝማች ወንድወሰንና ... ለጎያበሉን ሲረዳ ወደ መልፋ የወረደው ደጃዝማች ወንድወሰን፣ ... የብረት አጥር ሰብሮ በመግባት የደጃዝማች ኃይሉ ከበደንና የደጃዝማች ... ጋር እየረዳ ከአዲ ዙሀባ የመጣውን የጣልያን ጦር እንዳልከበረ አድርጎ ... በእድል የተረፈው የጣልያን ጦር ከአባ ስርጥ ስር ከሚሸሸው ጦር ጋር ...

ከነዚህ ድሎች በኋላ ኢትዮጵያውያንን የሚያማኛቸው ኃይል ጠፍቶ ... የጣልያን ክፍለ ጦር ላይ ዘመቱበት። ምንም እንኳን በሁለቱም ወገን ... የወታደር ቁጥር ተመጣጣኝ ቢሆንም ጣልያኖች ከታጠቁት ዘመናዊ

መሳሪያ ጋር በባዶ እግሩ እየሮጠ እሮጌ ጠመንጃ፣ ጋሻና ጦር ከታጠቀው የኢትዮጵያ ጦር ጋር ማወዳደር ግን ፈጽሞ አይቻልም።

ውጊያው እስከ ምሽቱ ድረስ ቆየ። አንዳንድ የውጊያ አውድማዎች ባለቤቶቻቸውን ከአስር ጊዜ በላይ ለዋውጠዋል። ኢትዮጵያውያን መሀኖ የምትባለውን የጦርነት አውድማ መንደር ስድስት ጊዜ በጃቸው አስገብተው ስድስት ጊዜ ተነጥቀዋል።

በዚህ ጦርነት ከሁለቱም ወገን በሺዎች የሚቆጠሩ ወታደሮች ወድቀዋል። በመጨረሻ ላይ ኢትዮጵያውያን ጀግኖች የመሀኖን የጦር አውድማ መንደር ለሰባተኛ ጊዜ ተቆጣጥረው እጃቸው በማስገባት፣ የቀረውንና በመሸሽ ላይ ያለውን የጣልያን ጦር ጀግኖቹ እያሳደዱ ለወሬ ነጋሪ ሳይቀር ድራሹን አጠፉት። ማርሻል ባዶሊዮ በእንዲህ አይነት ሁኔታ የመጀመሪያውን የሽንፈት ካባ ተከናነበ።

25

ከድል በኋላ

ማርሻል ባዶሊዮ ልክ የጦሩን ድባቅ መመታት እንደሰማ በተለያየ ቦታ ላይ ላሉ ጀነራሎች በፖስታ የታሸገ ትዕዛዝ አስተላልፎ ይኼን ፖስታ ጀነራሎቹ ከራሱ የቃል ትዕዛዝ እስኪደርሳቸው ድረስ እንዳይከፍቱ አዘዛቸው።

እንዲህ አሸጎ ለጀነራሎቹ በላከው ደብዳቤ ውስጥ በትክክል የጣልያን ጦር ከተንቤንና ከመቀሌ ወታደሮቹን የሚያስወጣበት መስመሮች የተነደፈበት ነበር። ማርሻል ባዶሊዮ በአስቸኳይ ወደ ተንቤን አዲስ ጦር ከላከ በኋላ በመቀሌ ድንኳኑ ውስጥ በፍርሀት ተቀምጦ የኢትዮጵያን ሰራዊት እንቅስቃሴ ማጥናት ጀመረ።

ማርሻል ባዶሊዮ በተንቤን በደረሰበት ሽንፈት ሙሉ ሀላፊነት ለመውሰድ ዝግጁ ነበር። እንዲያውም ጠቅላላ ጦሩን እስከ ኤርትራ ድንበር ድረስ ለማሸሽ ወስኗል። በሌላ አነጋገር በስተምስራቅ የነበረው ጦሩ መድቀቁን አውቋል። ኢትዮጵያውያን የተቀዳጁትን ድል ተጠቅመው ወደ ሰሜን ይዘልቁ እንደሆን በስጋት ቢጠብቅም ኢትዮጵያውያን ንቅንቅ ሳይሉ ያገኙትን ድል ሳይጠቀሙበት ቀሩ። አዎ አሁንም "መከላከል ብቻ" ለሚለው የንጉሠ ነገሥቱ ትዕዛዝ ከሁሉም በላይ ፍጹም ታማኝ የሆኑ የጦሩ መሪዎች ይህን ሰራዊት የማሸነፍ እድል ነሱት።

ኢትዮጵያውያን ከዚህ ድል ያገኙት ነገር ቢኖር በርካታ የጦር ቁሳቁስ ም
ብቻ ነበር። በኢትዮጵያውያን የዘመናት ታሪክ በጦር ሜዳ የተገኘ ማናቸውም በ
የአሸናፊው ጦር ነውና፣ አሸናፊዎቹ የኢትዮጵያ ጀግኖች ከጦር ሜዳ ውጊያ
ከጠላታቸው የፋሽስት ወታደር ላይ የማረኩትን ምርኮ በትከሻቸው እየተሸከሙ
ጦር ሰፈራችን መመለስ ጀምረዋል።

በኢትዮጵያውያን የዘመናት ባህል መሰረት በጦር ሰፈር በታላቅ ትግ
ይጠብቁ የነበሩት የጀግኖቹ እናቶችና ሚስቶች ጀግኖቹን እልልታቸውን እየቀሉ
ይቀበሏቸው ጀመር። እያንዳንዱ ከጦር ሜዳ የሚመለስ ወታደር ምንም እንኳ የ
ልጅ ከሚችለው በላይና በእግሩ መቆም እስኪሳነው ድረስ ቢደክምም፣ ጦር ሰ
ሲደርስ በጦር ሰፈሯ መሀል ይቆምና፣ እየፎከረ በዋለባቸው የጦር ሜዳ አውድማ
የፈጸማቸውን ጀብዱዎች ሎክ ብሎ ሲናገር፣ ከቦ ያለው ሰው በጭብጨባና በእልል
ይቀበለዋል።

በእንዲህ አይነት ሁኔታ ጀግኖቹ በጦር ሜዳ ውሏቸው የፈጸሙትን ጀብ
ዘርዝረው ከጨረሱ በኋላ፣ አሁንም ያለ የሌለ ኃይላቸውን አሰባስበው ሎክ በማለ
በጦር ሜዳ የወደቁ የጦር ሜዳ ወንድሞቻቸውን ስም እየጠሩ ለያንዳንዳቸው ክብር
ለጀግንነታቸው አንድ አንድ ጥይት ወደሰማይ ይተኩሳሉ።

በዚህ መልኩ በጦር ሜዳ የወደቁ ልጆቻቸውን፣ ባሎቻቸውን
ወንድሞቻቸውን የተረዱ ሴቶች ኡኡታቸውንና እዬዬያቸውን ይጀምራሉ። በራስ ካ
ጦር ሰፈር ቀኑን ሙሉ ወደ ሰማይ ያለማቋረጥ ይተኮሳል። ከሚተኮሱት ጥይቶ
እንደምንረዳው ጦራችን ያጣው የወታደር ብዛት ቀላል አይሆንም። ምሽቱን ሙ
ከየጥጋው አሳዛኝ ለቅሶና ዋይታ ያለማቋረጥ ይሰማል።

ሁለቱ ራሶች በድንኳናቸው ሆነው በርካታ ሹማምንቶችን እየተቀበሉ ስ
ጦርነቱ ሁኔታ ዘገባ ይቀበላሉ። እኔም ከደጃዝማች አበራ ድንኳን በራፍ ላ
ከደጃዝማች አበራና ከኮሎኔል ኮኖቫሎቭ ጋር አረፍ ብዬ ስለ ደጃዝማች አበራ የጦ
ሜዳ ውሎ ስናወጋ፣ ያንን እነዚያ ሶስት ታንኮች ሰራዊታችንን ሲያጭዱ እያ
መጀመሪያ ሰው ወደ ታንኮቹ ዞረው ሲሮጡ የነበሩትን ሽማግሌ ሽም በራሶች ድን
ደጃፍ ላይ ቆመው አየኋቸው። እሳቸውም እንደሌሎች ሹሞች ሁሉ ዘገባ ሊያቀ
ተራቸውን እየጠበቁ ነው። ይገርማል እኚህ ሽማግሌ ሹም ከነዚያ ታንኮች ጥይ
የተረፉት በተዓምር መሆን አለበት።

ተራቸው ደርሶ ስለ ጦር ሜዳ ውሏቸው፣ ስለፈጸሙት ጀብድ፣ ስለአሟቸ
ወታደሮቻቸው ቁጥር ዘገባ ለራሶች አቅርበው ሲወጡ ጠብቄ ሰላምታ አቀረብኩላቸ
ስለ ጦር ሜዳ ውሏቸው ጠየኳቸው።

እኚህም ሽማግሌ ሹም ስለ ጦርሜዳ ውሏቸው ሲያጫውቱኝ፣ "ስሙ ጌታ
አሉና ታሪካቸውን ጀመሩ። "ስሙ ጌታ፣ እነዚህ የጣልያን ታንኮች በጣሙን ጠንካ

ሃ ነው ያላቸው" አሉና በመቀጠል፣ "ስሙ ጌታ፣ እንዳው በሽማግሌ ጉልበቴ ሮጬ
ከባልያኑ ታንክ ተጠጋሁና ወደፊት እንዳይኼድ ላቆመው ፈልጌ፣ ጎማውን ልቁረጠው
አልችና ጎራዴዬን መዝዤ ብሰነዝር ጎራዴዬን ጎምዶት አረፈው" አሉና ሁለት ቦታ
የተሰበረች ስለታም ጎራዴያቸውን አሳዩኝ። "ስሙ ጌታ" በማለት ቀጥለው ሽማግሌው
ሹም በዚህ ስለታም ጎራዴ አዲስ አበባ በርካታ የመኪና ጎማ መቁራረጣቸውን
ምኒልክ ስም እየተገዘቱ ማሉልኝ። የዋህነታቸው ቢያሳዝነኝም ጀግንነታቸውን ግን
አድንቄ ለዘላለሙ በልቤ ጻፍኩት።

ከሰንት በኋላ የኔም አንበሳ ወደ ሰፈር ተመለሰና ሶስታችንም ማለት እኔ፣
ደጃዝማች አበራ እና ኮሎኔል ኮኖቫሎቭ በደጃዝማች አበራ ድንኳን ፊት ለፊት
እንደተቀመጥን አንበሳ ለደጃዝማቹ ክብር የሚገባውን ሰላምታ ሰጥቶ፣ በሽማው ጫፍ
አቱን ሸፍኖ ይቅርታ ከጠየቀ በኋላ፣ በሽማው የቋጠረውን ከእግሬ ስር ዘረገፈው።

"ምንድነው አንበሳዬ?" ስለው፣ አንበሳ ሳቅ አለና "አዬ... ረሳህ ማለት ነው
ቃል የገባሁልህን" ብሎ ትንሽ አዘነና "የመጣው ቢመጣ፣ የፈነዳው ቢፈነዳ ጦርነት
ስንገጥም ሲጃራ አመጣልሃለሁ አላልኩህም?" አለኝ በኩራት ሳቅ እያለ። በዚህ ጊዜ
ደጃዝማች አበራም ሳቅ ስላለለት አንበሳ ልክ እንደ ህጻን ልጅ ፈነደቀ። አዎ አሁን
አስታወስኩ፣ ከወር በላይ ሲጋራ አጭሰን አናውቅም ነበር። እናም የሲጋራ ወሬ
ተነስቶ ሁላችንም ማማረር ስንጀምር፣ ታዲያ አንበሳው በየቀኑ ይገባልን የነበረውን
ቃል "አይሏችሁ፣ ትግስት ይኑራችሁ። በመጀመሪያው ቀን ከጣልያኖች ጋር
ስንገጥምና ልክ አስገብተን ድራሻቸውን ስናጠፋ፣ የምትፈልጉትን ያህል ሲጃራ
አመጣላችኋለሁ" የሚል ነበር።

እነሆ ቃሉን ጠብቆ በዋለበት የመጀመሪያ ቀን የጦር ሜዳ የገባውን ቃል
አልፈጸም ምናልባትም ከማንም ጀግና በላይ ህይወቱን አደጋ ላይ ጥሎ፣ በጣሊያኖቹ
የጅን ሲዘዋወር ውሎ፣ እነሆ ብዙ ባኮዎች የጣሊያን ሲጋራዎች አምጥቶ ከእግሬ ስር
አፈሰሰልኝ።

በአብዛኛው ከጦር ሜዳ የሚመለስ ወታደር ከጦር ምርኮው ውጪ የጣልያን
ወታደሮችን የጦር ሜዳ ልብስ ደርቧል። ከነዚህ ወታደሮች መካከል የመኰንኖችን
ልብስ የለበሱት ጀነን ይላሉ። አሁን በአጠገባችን አንድ የደጃዝማች አበራ ወታደር
ከአንድ መቶ አለቃ ወታደር የጦር ልብስ ለብሶ እየተጀነነ አለፈ። ቀጥሎም አንዱ
የጣልያኖች የጀነራል ማዕረግ የተከተፈበት የብረት ቆብ ደፍቶ "ከገደልኩት የጣልያን
ወታደር ላይ ነው የወሰድኩት" እያለ ከባልደረቦቹ ጋር እየተከራከረ አልፎ ሄደ።

ኢትዮጵያውያን ከድል በኋላ ከጣልያኖች እጅ ባስለቀቋቸውና አሁን
በሚቆጣጠሯቸው የጦር ሰፈሮች የብርጌዱን የጦር ሜዳ መዝገብ ብቻ ሳይሆን ሌሎች
የጦር በርካታ የጣልያን ወታደሮች የግል ደብዳቤዎች፣ የተለያዩ ወታደራዊ ምስጢር
የያዙ መዝገቦች አግኝተው ወደ ጦር ሰፈራችን ይዘው ተመልሰዋል።

የፋሽስቱ ጦር ወታደሮች ቤተሰቦች፣ እናቶች፣ ሚስቶች፣ እጮኞች፣ እህቶች በጻፏቸው ደብዳቤዎች ስለተላከላቸው ገንዘብ እጅጉን በጣም ያመሰግናሉ። ከነዚህ ወታደሮች መካከል አንዱም እንኳ ወደ ሀገሩ አይመለስም። ለሞሶሎኒ የቀን ቅዠትና አብደት አድረው፣ የፋሽስቱ መንግሥት በሚከፍላቸው ገንዘብ ቤተሰባቸውን ለመርዳት አስበው፣ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ በመነሳታቸው እድል ፊቷን አዙራ ከፋኛ ቀጣቻቸው። እነሆ ሬሳቸው በተንቤን አሸዋማ መሬት ከደብረ አምባ ጀርባ እንደብቅል ተሰጥቶ ያሞራ ሲሳይ ሆኗል።

ከድል በኋላ አቢ አዲ ወደ ትልቅ ገበያነት ተለወጠች። በትልቁም በትንሹም አንዱ ይሸጣል፣ ሌላው ይገዛል። በርካታ ወታደሮች እርስ በርሳቸው የተለያዩ ጥቃቅን ነገሮችን ይለዋወጣሉ። ሹሞች ከወታደሮቻቸው ላይ መትረየሶች፣ ጠመንጃዎች፣ ጥይቶች፣ የጦር ሜዳ መነጽሮችንና የገበሬው ወታደር የማይፈልጋቸውን የጦር ቁሳቁሶች ሁሉ ይገዛሉ። ወታደሮቹ የሸጡትን ሸጠው፣ የለወጡትን ለውጠው፣ ለራሳቸውም የተወሰኑ ጥቃቅን ነገሮች ያስቀራሉ። በዚህ መልኩ አቢ አዲ ቅልጥ ያለች ገበያ ሆና ትውላለች።

በሶስተኛው ቀን አንድ አይናማው ሽበቱው ሽማግሌ ደጃዝማች አስፋው (የአፄ ምኒልክ ማህተም ጠባቂ የነበሩት) ከድል በኋላ ወደ ጦር ሰፈራችን ተመልሰው፣ በሁለቱ ራሶች ድንኳን ገብተው ወጡ። በኋላም ማምሻው ላይ እኛ በደጃዝማች አበራ ሰፈር እሳት እየሞቅን ስናወጋ ደጃዝማች አስፋውም መጥተው አብረውን ተቀመጡ። ከዚያም ከሶስት ቀን በፊት እንዴት ከጥቂት ወታደሮቻቸው ጋር 18 መድፎችና በርካታ መትረየሶችን እንደማረኩ ሲያወጉን፣ “እየሀ ጌታ” አሉ ንግግራቸውን ሲጀመሩ። “እየሀ ጌታ፣ አንድ ወታደሬ ከጸጊ ወንዝ ማዶ ላይ ጣልያኖች ብዙ መድፍ ጠምደው መሰፈራቸውንና ቁጥራቸውም ብዙ እንዳልሆነ ነገረኝ። እኔም የቀሩኝን ጥቂት ወታደሮቼን ይዤ እንደ አባብ መሬት ለመሬት ስንሳብ ውለን አጠገባቸው ደረስን። እናም እያንዳንዳችን ጥሩ አድርገን አልመን ግንባር ግንባራቸውን ስንላቸው ተደናግጠው መበርገግ ሲጀምሩ ወታደሮቼ የኔን ትዕዛዝ እንኳን ሳይጠብቁ እያባረሩ የገቡበት ገብተው ለወሬ ነጋሪ እንኳን ሳያስቀሩ ጨፈጨፏቸው። እኔማ አርጅቻለሁ አቅም ኖሮኝ ከነሱ እኩል አልሮጥ” አሉ።

ቀጥለውም “እየሀ ጌታ፣ እኔህ ወታደሮቼን ልዘዝ ብልም አይሰሙኝም። የጣልያን ወታደር ሲያዩ ደማቸው ይፈላና አንገቱን ቆርጠው የወደቁ ወንድሞቻቸውን ደም ሳይከፍሉ እሺ ብለው አይመለሱም” አሉ። አሁንም እዝን ብለው ሲያስቡ ቆዩና “እየሀ ጌታ፣ በዚህ ጦርነት አንድም የጣልያን ወታደር አልተረፈም” ብለው ለትረካቸው ማሳመኛ ይሆን ዘንድ ኪሳቸውን ዳበስ አድርገው የመድፈኛውን በርጌድ አዛዥ የኮሎኔል ሴቼዮኒን (Ceccioni) የግል መታወቂያ አሳዩኝ።

በዚህ መልኩ የደጃዝማች አስፋው ወታደሮች 18 ዘመናዊ መድፎች በርካታ መትረየሶች፣ ለቁጥር አስቸጋሪ በጣም ብዙ ሳጥን ጥይቶች፣ በርካታ ፈንጂዎችና የተለያዩ የጦር ሜዳ ቁሳቁሶችን ማረኩ። ሶስት ቀንና ሶስት ሌሊት የፈጀው የመጀመሪያው የተንቤን ጦርነት በራስ ካሣ ጦር ሙሉ በሙሉ ድል አድራጊነት ተፈጸመ። ቀኑን ሙሉ ሁለቱ ራሶች ከሹሞቻቸው ስለ ጦርነቱ ሁኔታ ዘገባዎች ሲቀበሉና ለድል አድራጊው ጦራቸው ሹመት ሲሰጡ ዋሉ።

ማምሻው ላይም ደጃዝማች አበራ ከራሶቹ ፊት ቀርቦ ስለ ሰላሌው ሰራዊቱ የጦር ሜዳ ውሎ ሰፋ ያለ ዘገባ ካቀረበና ሌሎች ተጨማሪ መመሪያዎች ከተቀበለ በኋላ፣ ከራሶቹ ድንኳን ወጥቶ በቀጥታ ወደኛ በመምጣት አብሮን ተቀመጠ። ይገርማል፣ ለወትሮው ወታደሮች የደጃዝማች አበራን የጦር ሰፈር እዚህም እዚያም ሰብሰብ ብለው በማሲንቋቸው እየተጫወቱ ደመቅመቅ እንዳላደረጓት ሁሉ ዛሬ ፀጥ እርጭ ብላለች። የማሲንቆ ጨዋታም ሆነ ለቅሶና ዋይታ አይሰማም። በነጋታው ረፋዱ ላይ በደጃዝማች አበራ ድንኳን ውስጥ ቁርስ ላይ እንደተቀመጥን በርካታ የበታች ሹሞች መጥተው ከደጃዝማቹ ፊት ይቀርቡ ዘንድ ጠየቁ።

“ደጃዝማች፣ ምን ተፈጠረ?” ብዬ ጠየኩት። “ትናንት በጦርነቱ ሁለት ፊታውራሪዎች አጣሁ” አለ፣ በማዘን ሳይሆን ፍጹም ቆጣ ብሎ። “ብዙ ወታደሮች አጣህ እንዴ?” ሲል ኮሎኔል ኮኖቫሎብ ላቀረበለት ጥያቄ፣ “አሁንም ከ20 ሺ በላይ ጦር አለኝ። ችግሩ ግን የወረጃርሰው ቀዳሚ ጦር ሁለቱን ፊታውራሪዎች ማለት መሪዎቹን አጣብኝ” አለና አሰብ አድርጎ፣ “አሁን የነዚህ ሹሞች ጥያቄ” ብሎ ሊነግረን የፈለገውን የሹሞቹን ነገር መልሶ ትቶ አሽከርዬው ሹሞቹን እንዲያስገባ አዘዘው። በዚህ ጊዜ ደጃዝማች ከሹሞቹ ጋር ብቻውን ያወራ ዘንድ ልንወጣ ብድግ ስንል “ቁጭ በሉ” አለ፣ አሁን ቃሉ ትዕዛዝ የተሞላበት ነበር።

ወዲያው ሳት ብሎ በይቅርታ አይን እያየን፣ “ምክራችሁን እፈልጋለሁ” አለን። ሹሞቹ ወደ ድንኳኗ ገብተው በአንድ ላይ ለደጃዝማቹ የሚገባውን የክብር ሰላምታ ካቀረቡ በኋላ ለጥቂት ጊዜ እርስ በርስ ተያዩና አንድ በእድሜያቸው ጠና ያሉ ሹም በኦሮምኛ አጠር ያለ ንግግር አደረጉ። ቀጥለውም ሌሎች ሹሞች አንዱ በአማርኛ ሌላው በኦሮምኛ ለደጃዝማቹ ችግራቸውን አስረዱ። ሁሉም ሹሞች ያወሩት ስለ ተመሳሳይ ችግር ነበር።

ሹሞቹ ችግራቸውን አስረድተው ንግግራቸውን ጨርሰው እንደቆሙ፣ ደጃዝማች አበራ ወደኛ ዞር ብሎ የሹሞቹን አቤቱታ በጥቂቱ ካስረዳን በኋላ የኛን መልስ ሳይጠብቅ ቆመው ወደሚጠብቁት ሹሞቹ ፊቱን መልሶ ውሳኔውን ማምሻው ላይ እንደሚያሳውቃቸው ነግሮ ሹሞቹን አሰናበታቸው።

ሹሞቹ ተሰናብተው እንደወጡ ደጃዝማች ትንሽ ሲያስብ ቆይቶ ድንገት ብድግ ብሎ ከድንኳኗ ወጣ። እኛም በደመነፍስ ተከተልነው። እንደምንከተለው የገመተ

መሰለኝ ፊቱን ሳይመልስ እርምጃችንን ጨምረን እንድንከተለው ነገረን። ከደጃዝማች ፈጣን እርምጃ እኩል መሄድ ባለመቻላችን እሱ ጋ ለመድረስ እንደ መሮጥ እየቃጣን ትንሽ እንደተጓዝን፤ ደጃዝማቹ አንድ የተጠረበች የምትመስል ጥቁር ድንጋይ አጠገብ ሲደርስ ፈጣኑን እርምጃውን ገትቶ ቆም ብሎ ጠበቀን። ከድንጋይ ላይም እንድንቀመጥ ጋበዘንና እሱም ከመሀላችን ተቀመጠ።

ድንጋይዋ ላይ እንደተቀመጥን፤ "ያቺን ዋርካ ታይዋታላችሁ?" አለን። ሁላታችንም በአንድ ጊዜ "አዎ" ብለን መለስን። ደጃዝማች አበራ አሁንም ወደ ዋርካዋ ፍዝዝ ብሎ እየተመለከተ፤ "ሌላስ ምን ይታያችኋል?" ሲል ጠየቀን። እኔ ይታየኝ የነበረውን ስናገር ኮሎኔል "ከዋርካዋ አጠገብ አነስ ያለች ቋጥኝ አለች። በቋጥኟ ላይ አንድ ሰው የተቀመጠ ይመስላል" ሲል ግልጽ አድርጎ አስረዳው። "በትክክል" አለና ደጃዝማች በመቀጠል "የኔም ችግር በዚያች ቋጥኝ ላይ የተቀመጠው ሰው ነው" አለን። "እንዴት ማለት? አልገባኝም?" አለ ኮሎኔል ኮኖቫሎቭ። ለነገሩ የደጃዝማቹ ችግር እኔንም ሊገባኝ አልቻለም።

ደጃዝማች አበራ ጥቂት ተክዝ ብሎ እንደማሰብ ካለ በኋላ፤ "ትናንት ሁለት የጦር መሪ ፊታውራሪዎች እንዳጣሁ ነግሬያችኋለሁ አይደል?" ብሎ ጠይቆ መልስ ሳይጠብቅ በመቀጠል፤ "እነዚያ ፊታውራሪዎች የወረጃርሶው ቀዳሚ ጦር መሪዎች ብቻ ሳይሆኑ ወንድማማቾች ነበሩ" አለና አሁንም ፍዝዝ ብሎ በዚያች ቋጥኝ ላይ ተኮማትሮ የተቀመጠውን ሰው እያየ "ታዲያ የሹሞቹ አቤቱታ ሁነኛ ሰው መርጬ እንድሾምላቸውና አሁንም ግንባር ቀደም ሆነው በመዋጋት የመሪዎቻቸውን ደም ይከፍሉ ዘንድ ነው" አለ፤ አሁንም አይኑን ከዚያች ቋጥኝ ላይ ሳይነቅል።

"ታዲያ ችግሩ ምንድነው? ማለቱ አንዱን ጎበዝ ተዋጊ መርጠህ አትሾምላቸውም እንዴ?" ሲል ኮሎኔል አከታትሎ ጠየቀው። አሁንም አይኑን ከቋጥኟ ላይ ሳይነቅል፤ "ኮሎኔል፤ ነገሩ እንደምትገምተው ቀላል አደለም" አለና በመቀጠል "ለነገሩ ጃርሶዎች አሁንም አንድ ፊታውራሪ አላቸው" አለ ሳቅ እንደማለት ብሎ።

"ታዲያ ወረጃርሶዎች ፊታውራሪ መሪ ካላቸው ለምን ሌላ መሪ እንድትሾምላቸው ይጠይቁሀል?" ስል እንዲያብራራልኝ አበቤ ጠየኩት። አሁን ፊቱን ወደኛ መልሶ ሳቅ አለና እንደገና ፊቱን ወደ ቋጥኟ መልሶ፤ "ይታያችኋል ያ ሰው? ቋጥኟ ላይ የተቀመጠው?" አለን በድጋሚ። አሁንም በአንድነት "አዎን" አልነው። "ቋጥኟ ላይ የተቀመጠው ሰው ነው የመጨረሻው የወረጃርሶ ፊታውራሪ" አለን። "እውነቱን ለመናገር የችግሩ መሰረት አልገባኝም? ጃርሶዎች ፊታውራሪ ካላቸው ለምን አዲስ ፊታውራሪ ይጠይቁሀል?" አልኩት።

አሁንም በመጠኑ ፈገግ ብሎ፤ "አንደኛ ይኼ ፊታውራሪ ቢበዛ 16 ወይም 17 ዓመት ቢሆነው ነው። ሁለተኛ ትናንት አንዱን ወንድሙን ከጦር ሜዳ አስመጥቶ ዋርካዋ ስር ቀብሮ እነሆ ከቋጥኟ ላይ ሳይነሳ ሁለተኛ ቀኑን ይዟል። ሶስተኛ ሹምቱ

በዚህ መልኩ ከቀጠለ እንደ ወንድሞቹ ጥሩ መሪ አይደለምና ጥሩ ተዋጊ አዋጊ ይሾምልን ብሎኝ ናቸው። አሁንስ ገባህ?" ሲል በፈገግ አይነት ነገር ጠየቀኝ። በመቀጠልም "የኔ ችግር ግን እሱ አይደለም" አለን፤ አሁን እዝን እና ጭንቅ ብሎ። "እህህ ጌታው፤ እውነቱን ለመናገር እኔ በጃርሶው ጦር ላይ ምንም ኃይል የለኝም። ጦሩ ታማኝነቱ ለሁለቱ ፊታውራሪዎች ብቻ ነበር። ይኼን እስከ አራት ሺ ድረስ የሚቆጠረውን ሰራዊት አንዱን ቀኛዝማች ወይም ፊታውራሪ አድርጌ ብሾምለት ለምሾመው ፊታውራሪ ላይታዘዝ ይችላል። እና ያለኝ አማራጭ የመጨረሻውን ፊታውራሪ ሀዘኑን ጨርሶ እንደ ወንድሞቹ ሁሉ ጦሩን እንዲመራ ማሳመን ወይም አንዱን ሾሜ ቀዳሚው የጃርሶ ጦር ፍርክስክሱ ሲወጣ ማየት ብቻ ነው" አለን።

"አይ ሌላ ዘዴ ይፈለግለታል፤ ለማንኛውም ለውሳኔ አትቸኩል" አለው ኮሎኔል ኮኖቫሎቭ።

"አይ ኮሎኔል አየስማህ! ዛሬ ማምሻው ላይ ቁርጬ ውሳኔዬን ለሹሞቹ መንገር አለብኝ" አለው አሁን ሳቅ ብሎ፤ "አለበለዚያማ ጥራ ስጋዬን በቁሜ ይበሉታል" አለና ሳቅ ተንፈራፈረ።

"አየችሁ ገና ከሰላሌ ሳንነሳ የጃርሶው ጦር መሪ ፊታውራሪ በድንገት ታመው ሞቱ። ከዚያ ሁለቱ ወንድማማቾች ጦራቸውን በጥንድ በህብረት እየመሩ የመጨረሻውን ወንድማቸውን አቢን አስከትለው መጡ። ትናንት አንዱ በጦር ሜዳ ለግንባር ጦሩን እየመራ ግንባር ቀድሞ ሲዋጋ እንደጀግና በደብረ አምባ ወደቀ። ሁለተኛው ፊታውራሪ ይማረክ፤ በመድፍ ጥይት ብትንትኑ ወጥቶ ይውደቅ አይታወቅም። አሁን የቀረኝ ገና የ16 ዓመት ልጅ፤ ገና አባይን ሳንሻገር እናታቸው ለማጥተው አደራ ያሉኝን ልጅ ምን ላድርገው? ጦር ስጥቼው ወደ ሰላሌ ብልከው እንኳ ከትግራይ ሽፍቶች ቢያመልጥ ከራያዎች ወጥመድ አያልፍም። ጦሩን እንዲመራ ገፋፍቼ እንደ ወንድሞቹ ቢወድቅና የፈጣሪ ስራ ሆኖ ሰላሌ ብመለስ እንዴት አድርጌ የእሮጊቷን አይን ማየት እችላለሁ? በዚህ ፈጣሪ ብቻ ይርዳኝ" አለ ደጃዝማች አበራ።

በኋላ ላይ ስለ አቢ እንደሰማሁት አባትዬው ሁሌም ትንሹ ልጃቸው ዘመናዊ ትምህርት ተምሮ ዘመናዊ ሰው ሆኖ ከጊዜው ጋር እንዲራመድላቸውና እንደሳቸው ከመሬት ጋር ተጣብቆ እንዳይቀር በማለት፤ ከልጅነቱ ጀምረው አዲስ አበባ በመላክ አስተምረውት እነሆ በሚቀጥለው ዓመት ወደ ፈረንሳይ ሀገር ለከፍተኛ ትምህርት ተዘጋጅቶ ነበር። ምን ያደርጋል! ሀገር ተወረረችና ትምህርቱም ቀርቶ ሁሉም ወደ ጦር ግንባር ተባለና አቢቹም አባቱን በጃርሶ ቀብሮ፤ እናቱን ብቻቸውን ጥሎ፤ ሁለት ወንድሞቹን ተከትሎ፤ በደጃዝማች አበራ ጦር ስር ተሰልፎ፤ ትንቤን ደርሶ በመጨረሻው ቀን ውጊያ ሁለት ወንድሞቹንና የጦር አለቆቹን አጥቶ፤ የአንዱን ወንድሙን ሬሳ በዋርካዋ ስር ቀብሮ፤ ሁለተኛውን በመንፈሱ እየፈለገና እየተሰናበተ እነሆ እዚች ቋጥኝ ላይ ሲቀመጥ ሁለተኛ ቀኑ ነው።

አቢቹ እንደባላገሮች ሹሞች የሚያስብ ሰው አይደለም:: የተማረና ያለ እድሜው የበሰለ የልጅ አዋቂ ቢሆንም ገና ከጅምሩ እግዚያብሔሩ መከራውንና ሀዘኑን ጭኖበት፣ በልጅ አዕምሮው ሌት ተቀን እያሰበ መወሰን ተቸግሮ ተቀምጧል። እንዲህ ሁላችንም ስለ አቢቹ እየተጨነቅንና ለደጃዝማቹ ጭንቀት መፍትሄ እየፈለግን ዝም እንዳልን ኮሎኔል ኮናቫሎብ፣ "እድልና ጊዜ ስጠው:: ምንም ወጣት ቢሆን ዞሮ ዞሮ መወሰኑ አይቀርም:: ምናልባትም እንዲህ የማሲንቆ ጨዋታ፣ ለቅሶና ዋይታ በሰፈሩ ከልክሎ፣ ብቻውን በቋጥኟ ስር ተቀምጦ በራሱ መንገድ ወንድሞቹን እየተሰናበተና የራሱንም የወደፊት እጣ እየወሰነ ይሆናል" ብሎ አጽናናን::

እኔም የኮሎኔልን ንግግር እያዳመጥኩ አቢቹን የማናገር ስሜቱ እየገፋ መጥቶ ምክንያት ፈልጌ ከደጃዝማች አበራና ከኮሎኔል ጋር ተሰናብቼ የምሄድበትን ጊዜ ስጠብቅ፣ ከሩቅ የኛን እንበሳ የሆነ ነገር ይዞ ወደ አቢቹ ሲያመራ አየሁ:: እንበሳ ከያዘው ነገር በዋንጫ ለአቢቹ ከቀዳና ከሰጠው በኋላ ወረድ ብሎ ከአቢቹ እግር ስር ተቀመጠ:: እኔም እንበሳ ሲመለስ ወሬ ለመቃረም ወሰንኩና ሀሳቤን ቀይሬ ከደጃዝማችና ከኮሎኔል ጋር ወደ ሰፈር ተመለስኩ::

እንበሳ ወደ ሰፈር ተመልሶ ገና ወደ ድንኳኗ ከመግባቱ በጥያቄ አጣደፍኩት። እንበሳ በተረጋጋ መንፈስ ብዙ በጣም ብዙ ነገር ስለአቢቹ ካወራኝ በኋላ፣ በመቀጠል የአቢቹ አባት ከመሞታቸው በፊት ለአቢቹ የመረጡለትን እጮኛ ውበትና ቀንጅና እያሞጋገሰ አወራኝ:: በመጨረሻም እኔ በጉጉት እጠብቀው የነበረውን ወሬ እነሳና እንደአቢቹ እምነት ትልቁ ወንድሙ ያልሞተና በጣልያኖች ምርኮ ወድቆ እንደሚሰቃይ፣ ወንድሙን ነጻ ለማውጣት መወሰኑንና ሌሎችም ሌሎችም ብዙ ብዙ ነገሮችን አጫወተኝ:: እኔም እንበሳዬን አመስግኜ የቋጠርኳትን ወሬ ይዤ ወደ ደጃዝማች አበራ ድንኳን ተፈተለኩ::

ይሁን እንጂ እኔ ይዤው የመጣሁትን ወሬ ሳልተነፍስ የደጃዝማቹ አሽከር መጥቶ አፉን በሸማ ሸፍኖ፣ አቢቹ ከደጃዝማቹ ፊት ይቀርብ ዘንድ እንደሚጠይቅ ሲነግረን፣ ደጃዝማች አበራ በስሜት ከተቀመጠበት ተነስቶ ግባ በለው አለ። አቢቹ ገና ከደጃዝማቹ ድንኳን በራፍ አለፍ እንዳለ ከደጃዝማቹ እግር ስር ወድቆ ለደጃዝማቹ የሚገባውን የክብር ሰላምታ ለማቅረብ ወረድ ሲል ደጃዝማች አበራ አፈፍ አድርጎ አንስቶ አቀፈው:: ሁለቱ ወጣቶች ለረጅም ጊዜ ተቃቅፈው ከቆዩና ደጃዝማች የአቢቹን ትከሻ መታ መታ እያደረገ ካረጋጋው በኋላ፣ "እሺ አቢቹ፣ ታዲያ ምን አሰብክ?" አለው::

አቢቹ ብዙም ሳይጨነቅ አጠር አድርጎ ወንድሙን ነጻ ለማውጣት የጦር ሰፈሩን ንጋት ላይ ለቅቆ ከጥቂት ወታደሮቹ ጋር እንደሚሄድና፤ የጃርሶውን ጦር ዘንድ እነሱ ይመሩት ዘንድ አጎቱ ቀኛዝማች ገለታና ቀኛዝማች ሼክ ሁሴን አባወርቁ በህብረት ይመሩት ዘንድ

ደጃዝማቹን ተማጽኖ ተሰናብቶ ከመውጣቱ በፊት ሁላችንንም ወደ ሰፈሩ ጋብዞን ወደ ጦር ሰፈሩ ወረደ::

አቢቹ ጦር ሰፈሩ እንደደረሰ የራሱ የሆኑትን የመጨረሻ ንብረቱን ሶስት በሬዎች አረዳቸው። ይኼን ያዩ ሌሎች የበታች ሹሞችም ቤት፣ የጦር ሜዳ ቤት፣ ያፈራውን ይዘው እየመጡ፣ የተከለከለው የማሲንቆ ጨዋታ ተፈቅዶ ሞቅ ሞቅ ሲል እኛም ግብዣውን አክብረን ተገኘን::

እንዲህ እኔ፣ ደጃዝማች አበራ፣ ኮሎኔል ኮናቫሎብና አቢቹ መደዳውን በበግ ቆዳ (ድብዳብ) ላይ ተቀምጠን እየበላንና አረቂና ጠጅ እየጠጣን ስንጫወት ቆይተን፣ አቢቹ ከተቀመጠበት ተነስቶ ቆመና ሁሉም ፀጥ ሲል ጠብቆ አጠር ያለች ምስጋና የበዛበት ንግግር አደረገ። ከዚያም ለአጭር ጊዜ ጥቂት ወታደሮች ይዞ ከጦር ሰፈር በመውጣት ወንድሙን ፍለጋ እንደሚሄድ፣ በህይወት ካገኘው አገኘው፤ ሞቶም ከሆነ ከወንድሙ ጎን እንደሚቀብረው ተናገረ። ለጊዜው የጃርሶውን ጦር ቀኛዝማች ገለታና ቀኛዝማች ሼክ ሁሴን አባወርቁ እንዲመሩት ደጃዝማችን መማጸኑን፤ ሹሞቹ ለደጃዝማች አበራ ያላቸውን ታማኝነት በምኒልክ ስም እንዲምሉ ለምኖ ተቀመጠ። ጦሩም በሹሞቹ አማካኝነት እየተነሳ ለደጃዝማች አበራ ያለውን ታማኝነት በምኒልክ እየተገዘተ፣ እየፎከረና እየሸለለ ተቀመጠ።

ሌላው ከአቢቹ ጋር የአቢቹን ወንድም ነጻ ለማውጣት የሚሄዱት ወታደሮች የምርጫ ትእይንት ነበር። በመጀመሪያ ታላላቅ ሹማምንቶች እየተነሱ እየፎከሩና እየሸለሉ ከአቢቹ ጋር ለመሄድ ቆርጠው መነሳታቸውን ገለጡ። በዚህ መሀል አቢቹ ተነስቶ ካመሰገነ በኋላ በመቀጠል አቢቹ የሚፈልገው ወደ 200 ገደማ ወዶ ገባ ጥሩ ተኳሽና ተዋጊ ጦር ብቻ እንደሆነ ገልጾ፤ እነዚህ 200 ተዋጊዎች ሚስቱን ጨርቁን ሳይሉ ፈጥነው መንቀሳቀስ የሚችሉ ወጣቶች ብቻ መሆን እንዳለባቸው ሲገልጽ በዚህ ንግግሩ በርካታ ሽማግሌ ሹማምንቶችን አስኮረፈ።

የሽማግሌ ሹሞችን ማኩረፍ ያዩት ብልሁ ቀኛዝማች ሼክ ሁሴን አባወርቁ ተነስተው፤ "ልባድርጉማ ጎበዝ! መቼም እኔም ለጌታችን ከመሞትና ከመሰዋት በላይ ምንም ዕድቅ ነገር እንደሌለ አውቃለሁ። ከዚህም ውጪ አልመኝም። ከዚህስ በላይ የክብር ሞት ምን ይገኛል? ይሁን እንጂ እንደጉርምስና ጊዜዬ ከድንጋይ ድንጋይ እየዘለልኩ፣ እንደ ዝንጀሮ ገደል እየቧጠጥኩ ወጥቼና ወርጄ ፈጥኜ መዋጋት አይሆንልኝም፤ አርጅቻለሁ። እናም ለጌታችን እኔ ባይሆንልኝ የበኩር ልጄን ሰጥቻለሁ" ብለው ሲቀመጡ፣ ሌሎች ሹሞችም እየተነሱ ወጣት ልጆቻቸውን ለአቢቹ ሰጡ። እነዚህ የሹሞች ልጆች ራሳቸው ከጦራቸው ወጣት፣ ደፋርና ጎበዞችን እየመረጡ፤ ደጃዝማች አበራም አንድ ዘመዱን በታማኝነት አቢቹን ያገለግል ዘንድ ከጥቂት ወታደሮች ጨምሮ ሰጠው። ሊነጋጋ ሲል አቢቹ ወደ 200 ገደማ የሚሆኑ ወታደሮቹን እየመራ ከጦር ሰፈር ወጣ።

አቢቹ 200 ገደማ የሚሆኑትን ቀልጣፋ ወጣት ተዋጊዎቹን ይዞ በደጃዝማች አበራ ፊት ቀርቦ ተመረቀና በዚያው ሌሊት የጦር ሰፈሩን ለቅቆ ከሄደበት ሰአት ጀምሮ አቢቹን አየሁ የሚል ሰው ጠፋ። ምንም እንኳ እኔም እንደሰዉ ሁሉ አቢቹን ከዚያን ምሽት ጀምሮ ባላየውም፣ ስለ አቢቹ ተጋነው የሚወሩ ጀብዱዎቹን በታላቅ ጉጉት እሰማ ነበር።

ይኼም ተጋኖ የሚወራው የአቢቹ ጀብድ በራስ ካሣ የጦር ሰፈር በሌሊት ተሰራጭቶ በርካታ ወጣት ተዋጊዎች ዋናውን ጦራቸውን ትተው፣ ወርደው በየግል የጦር ሜዳ የአርበኝነት ትግል ከጀመረው የአቢቹ ጦር ጋር መቀላቀል፣ ማግለል ጀመሩ።

ምንም እንኳ ተማርኳል፣ የመድፍ ጥይት በጣጥሶ ጥሎታል፣ እና ሌላም ሌላም ወሬ ሲወራበት የነበረው የኛርሶው ፊታውራሪ ከደጃዝማች ወንድወሰን ጦር ጋር ወደ መልፋ ወርዶ ሲዋጋ ቆስሎ ሲያገግም ሰንብቶ፣ ከሳምንት በኋላ ወደ ዋናው የጦር ሰፈር ተመልሶ ጦሩን መምራት ጀመረ። ይሁንና አቢቹን መልሶ ከጦሩ ጋር እንዲቀላቀል ማድረግ ግን አልተቻለም ነበር።

ወንድምዬው ብዙ መልክተኞች ቢልክም ግማሹ በዚያው ቀረ። የሚመለሱትም የአቢቹን ጦር ሲፈልጉ፣ ከሳምንት በላይ ሲንከራተቱ ሰንብተው ባዶ እጃቸውን ይመለሳሉ። በየቀኑ ዋናውን ጦራቸውን እየከዱ ወደ አቢቹ የሚኮበልሉት ወጣት ተዋጊዎች ቁጥር ከቀን ወደ ቀን በመጨመሩና ይኼም ወሬ ከራሶች ድንኳን በመድረሱ እኔ፣ ኮሎኔልና ደጃዝማች አበራ ተጠርተን ከራሶቹ ፊት ቀረብን። ልጄንም ወደ እናት ጦሩ ይመልስ ዘንድ እንድናባብል ትዕዛዝ ተሰጠን።

አቢቹ መጀመሪያ ላይ ከሰፈር እንደወጣ አነስተኛ የጣልያን የተበተኑ ጦሮችን እየፈለገ፣ በደረቅ ሌሊት አደጋ እየጣለ፣ ስንቅና ትጥቅ እየዘረፈ፣ ጦሩን ዘመናዊ መሳሪያ እያስታጠቀ፣ ማደራጀት ጀመረ። ከዚያ ጦሩን ይዞ የጠላት ጦር ባልጠበቀው ቦታና ሰዓት ድንገት እየደረሰ ያልተጠበቀና ያልታሰበ አደጋ እየጣለ፣ አልፎ አልፎ ሌሊት የጣልያኖቹን የጦር ሰፈር ሰብሮ እየገባ አደጋ እየጣለ፣ ንብረት እየዘረፈ ከጦሩ የተረፈውን እና ጦሩ የማይፈልጋቸውን ነገሮች ወደ ዋናው ጦር መላክ ማከፋፈል ጀመረ።

እንዲህ ሳይታሰብ የሚጥለው አደጋ ጣልያኖቹን ክፉኛ ከመጉዳቱም በላይ የፋሽስቱን ጦር የበላይ አዛዦችን ክፉኛ ስላስቆጣ፣ የጣልያን ወታደራዊ መኮንኖች ለትግራይ ሽፍቶች ከፍተኛ ገንዘብና ዘመናዊ መሳሪያ በመለገስ የትግራይ ሽፍቶች የአቢቹን ጦር አሳደው እንዲመቱ አደረጉ።

የትግራይ ሽፍቶች አቢቹን በመፈለግ ላይ እንዳሉ ጥር ወር መጨረሻ ቀን ላይ ማርሻል ባዶሊዮ በቅርቡ ከሮማ ከተላከለት ትኩስ ጦር ላይ ሁለት ሻለቃ ጦር መንዝሮ ቀንሶ፣ ዘመናዊ የሚባሉ መሳሪያዎች አስታጥቆ፣ ወደ ተንቤን የላከው ጦር መንገድ

ላይ ሲያዘግም አቢቹ ያያል። ከዚያም የጣልያኑን ሁለት ሻለቃ ጦር እንቅስቃሴ ከሩቅ ሆኖ ለረጅም ሰዓታት ሲከታተል ቆይቶ፣ ወታደሮቹን ይጠራና ጣልያኖቹ ምሽቱን ያሳልፉበታል ብሎ የገመተው ቦታ ቀድሞ በመሄድ፣ ስምንቱን ከጣልያኖች ከዘረፉቸው በርካታ ቤንዚን የሞሉ ትላልቅ ቆርቆሮዎች አንድ አስሩን ያህል በየቁጥቋጦው ውስጥ ያፈሱ ዘንድ ያዝና፣ ከዚያ በጣም ራቅ ብሎ ይመሽጋል።

የአጋጣሚ ነገር ሊሆን ይችል ይሆናል። ጣልያኖቹ አቢቹ ሌሊቱን ያሳልፉበታል ብሎ በገመተው ቦታ ላይ ድንኳኖቻቸውን ተክለው ይሰፍራሉ። የአቢቹ ጦር እኩለ ሌሊት ላይ ያንን ቤንዚን የጠገበ ቁጥቋጦ እሳት ይለቅበትና በድንገት የእሳቱ ወላፈን የቀሰቀሳቸው አዲሶቹ የጣልያን ወታደሮች መላው ጠፍቷቸው ሲደናበሩ፣ የአቢቹ ወታደሮች በእሳቱ ወገንን እየተረዱ አዲሶቹን የጣልያን ወታደሮች ግንባር ግንባራቸውን እያሉ ያስተኟቸው ጀመር። እንዲህ ከየት አቅጣጫ እንኳን እንደሚተኮስባቸው ያላወቁት ጣልያኖች መላ ቅጡ በጠፋ ሁኔታ ሲርመሰመሱ አልመው ተኳሾቹ የአቢቹ ተዋጊዎች አንድ በአንድ ለቀሟቸው።

አደጋ የደረሰበት ይኼ ሁለት ሻለቃ ጦር ስለሁኔታው በራዲዮ ለአለቆቹ ቢያሳውቅም፣ የጣልያኖቹ አጋዥ ጦር ከሰፍራው ከመድረሱ በፊት እነአቢቹ ከዚያ ሁለት ሻለቃ ጦር ለወሬ ነጋሪ ሳያስቀሩ ሲነጋጋ ሲል የቻሉትን ያህል ንብረት ዘርፈው፣ የተረፈውን ለትግራይ ሽፍቶች ትተው እንደ አመጣጣቸው ማንም ሳያያቸው ተሰወሩ።

ይኼ ማርሻል ባዶሊዮን ያስለቀሰ፣ ለሰሚው ማመን የሚያስቸግር ጀብዱ የአቢቹ ጦር እንደሰራው ጥርጥር የለውም። ለዚህም ጠዋት ከድንኳኔ ስወጣ ከደጃፍ ያገኘኋቸው በርካታ የሲጋራ ፓኮዎችና ሁለት ሳጥን ሙሉ የጣልያን ቪኖ ምስክሮች ናቸው። ሁሌም እነአቢቹ በለስ ሲቀናቸው የሚዘርፏትን የጠላት ንብረት፣ የጦርና የምግብ ቁሳቁስ ሁሉ ሌሊት አምጥተው ለዋናው ጦራቸው ያከፋፍሉ ነበር።

ታዲያ እነ አቢቹ በዚህ መልኩ ትግላቸውን አፋፍመው ሳለ አንድ ሌሊት ከትግራይ ሽፍቶች ጋር ችግር ገጠማቸው። የአቢቹ ጦር እንደ ወትሮው ሌሊት ሌሊት ሁለቴና ሶስቴ ሰፈሩን እየቀያየረ ሲንቀሳቀስ፣ የትግራይ ሽፍቶች አንድ ሰላሳ መንገድ ላይ አግኝተውት አናሳልፍም በማለት በከፈቱበት ተኩስ ሽፍቶቹ የአቢቹን ሁለት ተዋጊዎች ይገድላሉ።

አቢቹ መጀመሪያ ልክ ችግሩ እንደተፈጠረ ከሽፍቶቹ ጋር ተደራድሮ ለማለፍ ቢሞክርም ሽፍቶቹ አንዲት መንደር ውስጥ መሽገው አናሳልፍም ብለው በከፈቱት ተኩስ ሁለት ተዋጊዎቹን ሲገሉበት፣ አቢቹ ትግስቱ አልቆ መጀመሪያ ሽማግሌዎች፣ ሴቶችና ህፃናት መንደሯን ለቀው እንዲወጡ ለሽፍቶች ያቀረበው ጥያቄ አወንታዊ መልስ አግኝቶ አዛውንቶች፣ ሴቶችና ህጻናት መንደሯን ልክ ለቀው እንደወጡ ያቺን

የሳር ጎጆ የሞላባትን መንደር በሳት አጋየው። ከዚያ ከየመሸገበት እየወጣ ሽሽት የጀመረውን ሽፍታ እያሳደደ ቀጠቀጠው።

ምንም እንኳ እነዚህ መንደራቸውን ለቀው እንዲወጡና ነፍሳቸውን እንዲያድኑ የተፈቀደላቸው አባውንቶች፣ ሴቶችና ልጆች ንጋት ላይ ጦር ሰፈራችን ደርሰው ስለሁኔታው ለሹሞች አስረድተው ደጃዝማች አበራ በፊታውራሪ ሙሉ የሚመራ ጦር ወደ መንደሯ ቢልክም፣ የፊታውራሪ ሙሉ ጦር በቦታው ያገኘው ነገር ቢኖር የመንደሯን አመድና እዚህም እዚያም የወደቁ የትግራይ ሽፍቶችን ሬሳ ብቻ ነበር።

ከዚች ቀን ጀምሮ እስካሁን በታላቅ ኩራት ሸንጣቸውን ገትረው ከራስ ካሣ ጋር ይከራከሩለት የነበሩትን ራስ ሥዩም መንገሻን አጣ። መንደር ማቃጠል ከጀመረ ከጣልያኖችና ከትግራይ ሽፍቶች በምን ይሻላል? እያሉ ክፉኛ አማረሩ።

በኛም መንደር ስለ አቢቹ ሁላችንም የተለያየ አስተሳሰብ መያዝ ጀመርን። ከአንደኛው የአለም ጦርነት ጊዜ ጀምሮ በተለያዩ የጦር ሜዳዎች የዋለው ኮሎኔል ኮኖቫሎቭ መቶ በመቶ የአቢቹ ደጋፊ ሲሆን፣ ደጃዝማች አበራም ውስጥ ውስጡን በሆዱ አቢቹን ቢደግፍም እንደ ጦር አዛዥነቱ አቢቹን በአደባባይ ሳይደግፍም ሌላም አስተያየቶች ሳይሰጥ ዝም አለ። እኔም የራስ ካሣ የጦር አማካሪ እንደመሆኔ መጠን፣ ምንም እንኳን የአቢቹ ጀግንነት ፍጹም ቢያኮራኝም፣ መንደር ማቃጠል ብቻ ሳይሆን እንዲህ በታላቅ ወኔና ድፍረት የጣልያኖቹን የጦር ሰፈር ሰብሮ እየገባ የሚጥለው ትልቅ አደጋ ጣልያኖችን እጅግ በጣም አስቆጥቶ፣ ሌሊት በተደፈሩ ቁጥር ቀን በነዚያ የሰማይ ላይ አሞራዎች የሚያዘንቡት የሞት እሳት በየቀኑ ፍጹም አረመኔያዊነት የተሞላበት እየሆነ እንዲመጣ ትልቁ መንስኤ አቢቹ እንደሆነ ስረዳ መላው ጠፍቶኝ እኔም ዝም ማለትን መረጥኩ።

ኮሎኔል ኮኖቫሎቭ አቢቹ በፈለገው የጦር ሜዳ፣ በመረጠው ሰዓትና ቦታ የጠላትን ጦር መጨፍጨፍ የተቀደሰ፣ በእግዚአብሔር የተሰጠው ቅዱስ መብቱ ነው ብሎ ያምናል።

26
የጣልያኖች ጭካኔ

ድቅድቅ ያለ ጨረቃ የሌለው ጨለማ በተንቤን ተራሮች ላይ ተኝቷል። ጥቂት ወታደሮች ሰብሰብ ብለው በሳጥኖች ላይ ተቀምጠው እሳት እያነደዱ ይጫወታሉ፣ ያወጋሉ።

ከነዚህ ወታደሮች አለፍ ብሎ እኛም በሳጥኖች ላይ ተቀምጠን እሳት እየሞቅን ብቸኛዋን የራስ ካሣን ራዲዮ ከፍተን አንድ የአውሮፓ ሀገር የራዲዮ ጣቢያ ስናዳምጥ፣ ራድዮ ቴሌግራፊስቱ ቁልፉን ጠምዘዝ ሲያደርገው አንድ የጣልያን ሬዲዮ ጣቢያ ውስጥ ገባን። ወዲያው የአንድ ሴት ድምጽ ይሰማን ጀመር። የምታወራውም ጣልያኒኛ ነበር።

"Radio-Roma! Comunicato del Ministero per la stampa e la propaganda numero 105! Il maresciallo badoglio telegrafa"

እጅግ በጣም ታማኝ በሆኑ የመረጃ ምንጮች መሰረት ጠንካራ የሚባለው የራስ ካሣ ጦር በተንቤን ተራሮች ላይ ለፍሮ በጦራችን ላይ ጥቃት ለመሰንዘር በዝግጅት ላይ መሆኑን ስረጋግጥ፣ የካሣን ጦር በነን ዞሮ የጠላት ጦር ሳያስበው ጥቃት ለመሰንዘር ወሰኜ

ጥር 20፣ 21 እና 22 ቀን 1936 ዓ.ም. በተደረጉ ከፍተኛ ውጊያዎች ጥር 22 ቀን 1936 ዓ.ም. ማምሻው ላይ በኛ ጦር ፍጹም ድል አድራጊነት ጦርነቱ ተፈጸሟል።

የሮማ ራዲዮ ጣቢያ ለመላው አለም ታላቅ አይን ያወጣ ውሸቱን ያሰማ ጀመር። በተንቤን የጦር ሜዳ የጣልያን ሰራዊት ድል አድራጊነት? ታላቅ ወሸት በመጠኑ ጣልያኒኛ የሚሰማው ራዲዮ ቴሌግራፊስታችን ከንፈሮቹ በንዴት እየተንቀጠቀጡ የንዴት ሳቅ እየሳቀ ባጋንዳ "BAGANDA" ብሎ ቡጢውን ጨበጠ።

ጣልያኖች ፕሮፓጋንዳቸውን በሰፊው ተያይዘውታል። በተቻላቸው አቅም በተንቤን የደረሰባቸውን ታላቅ ሽንፈት ለመደባበቅና ለመሸፋፈን እየሞከሩ ናቸው. ጣልያኖች እንዲህ ለመላው አለም ህዝብ የውሸት ዜና ሲያስተላልፉ፣ በሺዎች የሚቆጠሩ ታልመው የተተኮሱ የኢትዮጵያ ወታደሮች ጥይቶች ግንባራቸውን የፈለጣቸው፣ የጀግናው የገበሬ ወታደሮቻችን ጎራዴዎች አንገታቸው ላይ ያፏጩባቸው፣ በገበሬዎች ክንድ በተወረወሩ ጦሮች ደረታቸው የተበሳ፣ በሺዎች የሚቆጠሩ የፋሽስቱ ጥቁር ሸሚዝ ለባሽ ወታደሮች፣ ለገገርዎቻቸው የተሰለፉ የኤርትራ ተወላጆች ሬሳ ከደብረ አምባ እስከ ወራዩና አልሮም እስከ መልፋ ደጋ በየጥሻውና በየሜዳው ወድቀው፣ የሌሊት የተራቡ ጅቦችና የቀን አሞራዎች መጫወቻ ሆነዋል።

የፋሽስቱ ጥቁር ሸሚዝ ለባሽ ወታደሮች 28ኛው ኦቶብሬ ብርጌድ እንዳይሆን ሆኖ ደቆ ሁለት ሶስተኛው እጅ የሰራዊቱ አባላት ምንግዜም ወደሀገራቸው አይመለሱም። ሬሳቸውም ቀባሪ የለውም። በዚህ ጦርነት በኢትዮጵያ ወታደሮች ከተገደሉት በጣም ብዙ የጦር መኮንኖች በተጨማሪ ሶስት ጀነራሎችና አንዲት ጦር ያለች ሴት ወታደራዊ ልብስ እንደለበሰች ተገድላ ማየታቸውን የኢትዮጵያ ወታደሮች የአይን ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል።

ከተንቤን ድል በኋላ የራስ ካሣ የጦር ሰፈር ከምን ጊዜውም በላይ ደመቅመቅ ማለት ጀምራለች። ከጣልያኖች የተወረሱት በርካታ ድንኳኖች ሲተከሉባት ከወትሮው ደመቅ ብላ መታየት ጀምራለች። ለሰፈራችን ድምቀት የታሰበ ይመስል የጦር ሰፈራችን ከወትሮው ነዋሪዎቿ ለየት ያሉ ልዩ ሶስት ነዋሪዎች ጨምራለች፤ ሶስት በተንቤኑ የጦር ሜዳ የተማረኩ የጣልያን ወታደሮች፣ ሶስት የጦር ሜዳ ምርኮኞች፣ ሁለት ተራ ወታደሮችና አንድ ምክትል መቶ አለቃ።

ኢትዮጵያውያን እነዚህን ምርኮኞቻቸውን ልክ እንደታላቅ የንጉሥ እንግዳ ይንከባከቧቸዋል። በተለይ ለነዚህ ምርኮኞች ደህንነት በራስ ካሣ ትልቅ ሀላፊነት የተሰጠው ደጃዝማች አበራ በእውነቱ እንደምርኮኛ ሳይሆን ልክ እንደታላቅ የመሳፍንት ልጆች ታላቅ እንክብካቤ ያደርግላቸው ነበር። ደጃዝማች አበራ እነስ ያለት ድንኳን ለግሏቸው ምንም እንኳን ሌት ተቀን በድንኳኖቹ በራፍ ዘብ ቢቆምባቸውም በጦር ሰፈራችን በጠባቂዎቻቸው ታጅበው እንደልባቸው ይዘዋወሩ ነበር።

እነዚህ አዲስ የጦር ሰፈራችን ነዋሪዎች ከሁሉም በላይ እስካሁን በአይናቸው ጣልያኖችን ለአላዩት ሴቶችና ህፃናት እንደ ታላቅ ተዓምር ነበሩ። "ወይ ጉድ ጣልያኖች" እያሉ ሴቶቹ በህይወት ቆሞ የሚሄድ የጣልያን ወታደር በአይናቸው በማየታቸው አድናቆታቸውን ሲገልጹ፣ ህፃናት ልክ ምርኮኞቹ በጠባቂዎቻቸው ታጅበው ከድንኳናቸው ሲወጡ፣ ግር ብለው እየተከተሉ "ጣልያኖች፣ ጣልያኖች፣ ጣልያኖች" እያሉ እየተጯጯሁ በመከተል አንዳንድ ደፋር የሚሉ ህፃናት ጠጋ ብለው ነካ ነካ ሲያደርጓቸው ይታይ ነበር።

ደጃዝማች አበራ ለምርኮኛው ምክትል መቶ አለቃ የራስ ካሣን ልብስ ሰፊ ከዘቸኛዋ የሲንጀር የልብስ ስፌት መኪናው ጋር አስጠርቶ፣ በተቀዳደደው ወታደራዊ ልብሱ ምትክ በልኩ በተመሳሳይ ሁኔታ አዲስ ወታደራዊ ልብስ ሲያሰፋለት፣ የራስ ካሣ ልብስ ሰፊ ከአሮጌው ወታደራዊ ልብስ ላይ ማዕረጉን ገንጥሎ በአዲሱ ወታደራዊ ልብሱ ላይ ለጠፈለት።

ይኼው የዋሁና እሩህሩሁ ደጃዝማች ለነዚሁ ምርኮኞች ሲጋራ ልመና አሽከሮቹን ወደኛ ይልክ ነበር። እነዚህ ሲጋራ ለማኝ አሽከሮች የሆኑ ሲጋራዎች እስከንሰጣቸው ድረስ ለረጅም ሰዓት ሳይታክቱ አይናቸውን ሲያቁለጨልጩብን እኛም ብዙ ባይኖረንም ካለችን እናካፍላቸው ነበር።

ሲጋራ በጠፋ ሰሞን እንኳ ይኼው ወጣት ደጃዝማች አሽከሮቹን ከጦር ሰፈራችን ብዙ ርቆ ወደ መሸገው የልጁ ጦር ድረስ ሳይቀር እየላከ፣ የሀገራቸውን ሲጋራ ያስጨሳቸው ነበር። ለዚህ ውለታው ግን ደጃዝማች አበራ ከጦርነቱ በኋላ የራሴን ህይወት ለማትረፍ ስል ሰራዊቴን አላስፈጅም" ብሎ እጁን ሰጥቶ በእጃቸው ለወደቀ ጊዜ ያለ አንዳች ፍርድ በጥይት ደብድበው ገደሉት።

ከተንቤኑ ድል በኋላ የኢትዮጵያ ሰራዊት ያለ ችግር ወደፊት ገፍቶ መቀሌን ሳይቀር ማስለቀቅ ይችል ነበር። ይሁን እንጂ ሰራዊታችን ያገኘውን ድል ሳይጠቀምበት ቀርቶ በዋለበት የጦር ሜዳ የማረከውን ንብረት እየተሸከመ ወደ ዋናው የጦር ሰፈር አቢ አዲ ተመለሰ።

በዚህ መልኩ ጣልያኖች ከባድ መስዋትነት ከፍለው ያጡትን የጦር ሰፈራቸውን ምንም እንኳ የልጁ ጦር ድንገት እየደረሰ አደጋ እየጣለ በመሰወር ከፍተኛ ጉዳት ቢያደርስባቸውም፣ ከዋናው የራስ ካሣ ጦር ጋር ግን አንዲት ጥይት እንኳ ሳይታኮሱ መልሰው መያዝ ጀመሩ።

ራሶች በድል አድራጊነት የያዟቸውን ከጦር ሜዳ ስልት አንጻር ወሳኝ ከተሞች፣ መንደሮችና ቀበሌዎች ሁሉ የንጉሠ ነገሥቱን "መከላከል ብቻ" ፖለቲካ ወይም የጦር ሜዳ ስልት ላለመዳፈር እና ለማክበር ሲሉ፣ የራሶች የበታች ሹማምንትና መኳንንቶች ደግሞ ምንም እንኳ የጦር ሜዳ ልምድ ቢጎድላቸውም፣

እነሱም ራሳቸን ተከትለው ከፍተኛ መስዋእት ከፍሎ ድል የተጎናጸፈውን ጦራቸው ከድል ሜዳ እያነሱ ወደ ዋናው የጦር ሰፈር ሲመልሱት፣ ጣልያኖች የለፀን ዋ ድንገተኛ አደጋዎች ከመከላከል ውጪ ያለምንም ችግር በጦር ሜዳ ያሟቸው ከተሞች መልሰው እንዲት ጥይት ሳይተኩሱ ያዙ።

እነዚህን የጦር ሰፈሮች እንደገና ያለ ምንም ጦርነት የያዘው የጣልያ ጦር ምሽጉን እንደገና ገንብቶ፣ በጥር ወር መጨረሻ ላይ ሁለት የጣልያን ሁለት የኤርትራውያን ተወላጆች ብርጌድ 29 ሻለቃ ጦር ይዞ፣ በ76 መድፍ እየታገዘ በርካታ መትረየሶችን ጠምዶ እንደገና ከፊታችን ቆመ።

ይኼን የጣልያኖችን መመለስ ያዩ ተራ የባላገር ወታደሮች መገረማቸውን መደንቃቸውን ሳይሸሽጉ "ወይ ጉድ …! እንዲያው እንደዚያ እንዳልጨፈጨፍናቸው ሁሉ፣ እነዚህ ጣልያኖች አሁንም እዚያው አሉ" በማለት ትናንት ከትናት ወዲያ በመቱበት የጦር አውድማ የጣልያን ወታደሮችን በማየታቸው እንደተገረ እየታያቸው ተደንቀው ተናግረዋል።

ቀን ቀንን እየተካ ጊዜው ይኼዳል። ኢትዮጵያውያን ሴቶች ከማለዳ እስከምሽ ድረስ በባህላዊው መንገድ ጤፍ ያለው ጤፉን፣ ማሽላ ያለው ማሽላውን፣ በቆሎ ያለው በቆሎውን፣ ብቻ ቤት ያፈራውን እህል በወፍጮ ወይም በእጃቸው እየፈጩ እንጀራ ይጋገራሉ፣ ወጥ ይሰራሉ።

ሴቶች ልጆቻቸውን እያጫወቱ ቀኑን በዚህ መልኩ ሲገፉት ወንዶቹ ያለም ስራ የመከላከያ ምሽጎቻቸውን እንዲጎን ለመገንባት ሳይሞክሩ እንዲሁ በየቡድኑ በየጥላው ስር ተቀምጠው ልክ ጦርነት እንደሌለ ሁሉ ይጫወታሉ፣ ያወጋሉ።

የኢትዮጵያው ሰራዊት ያገኘውን ድል በዚህ መልኩ እያጣጣመ ሲቀመጥ፣ ጣልያኖች እንደገና ምሽጎቻቸውን አድሰው፣ ጦራቸውን አጠናክረው ቦታ ካስያዙ በኋላ ሰሞኑን ሰላም ስጥተውን የሰነበቱት ነፍሰ ገዳይ አውሮፕ ከምንጊዜውም በላይ ያለ እንዳች ርህራሄ ከጠዋት እስከማታ እየተመላለሱ በየምግብ መደብደቡን ቀጠሉበት።

የጣልያን አውሮፕላኖች የቦንብ ሸክማቸውን አራግፈው፣ የተኩስ ተልዕኮ ጨርሰው፣ ጀንበር ከመጥለቋ በፊት ወደ መቀሌ ሲመለሱ፣ በስፈራችን ይወርድና፣ በህይወት ያሉ የጣልያን ቦንቦች ያልሳሟቸው ወታደሮች ከየምሽ ከየዋሻቸውና ጉድጓዳቸው እየወጡ የሌሊቱ ህይወት ይጀምራል።

አሁን የኢትዮጵያ ወታደሮች እንደ ዱሮው ሲጨላልም ድንኳናቸው ተክለው ከመንጋቱ በፊት መነቃቀሉ አጉል ድካም መስሎ ስለታያቸው ድንኳናቸው ሳይተክሉ በባዶ ሜዳ ላይ መተኛት ጀምረዋል።

ጣልያኖች በቦንቦች ምትክ ስማዩን በበራሪ ወረቀቶች መሙላት ሰሞኑን ጀምሯል። በእነዚህ በአማርኛ (በግእዝ) ፊደል በአማርኛና በትግረኛ ቋንቋ ተጽፈው የተበተኑ ወረቀቶች ማርሻል ባዶሊዮ በደቡቡ የጦር ግንባር የጣልያን ጦርን ድል ማድረጋቸውን በሰፊው ያትታል።

የካቲት 4 ቀን 1936 ዓ.ም. አረፋዱ ላይ ስስት አውሮፕላኖች አቢ አዲን ላይ ቆይተው፣ አለቀልን እያልን ስንሰጋ አውሮፕላኖቹ ስማዩን በነጭ ወረቀት ሞልተውት ወደ መቀሌ ተመለሱ።

በዚህ በሰፊው በሚበተኑ የፋሺስቶች የፕሮፓጋንዳ ወረቀቶች ማርሻል ባዶሊዮ የኢትዮጵያ ወታደሮች ያለምንም ማንገራገር እጃቸውን እንዲሰጡና ወደ መንደሮቻቸው እንዲመለሱ እየጠየቀ፣ በመቀጠል በደቡቡ የጦር ግንባር ማርሻል ግራዚያኒ የራስ ደስታን ጦር ድባቅ መምታቱን፣ በዚህ ደም በተራጨበት ጦርነት 1,000 በላይ የራስ ደስታ ወታደሮች መሞታቸውንና ከ10,000 በላይ የሚሆኑት ደግሞ ከባድ መቁሰላቸውን እንዲሁም ድል አድራጊው የማርሻል ግራዚያኒ ጦር ወደ አዲስ አበባ በመገስገስ ላይ መሆኑን ያትታል።

ይሁን እንጂ ይኼ የማርሻል ባዶሊዮ ፕሮፓጋንዳ በራስ ካሣና በራስ ሥዩም ጦር ላይ ምንም ተጽእኖ አልነበረውም። እንዲያውም የራስ ካሣ ሰራዊት በደቡብ የራስ ደስታን ጦር መሸነፍ ሲሰማ፣ ተሸነፉ በተባሉት የጦር ሜዳ ወንድሞቹ የራስ ደስታ ሰራዊት ላይ እየሳቀ በራሱ ይበልጡን እንዲኮራና እንዲተማመን አደረገው።

ማርሻል ባዶሊዮ ወረቀት በትኖ የካማን ጦር ማፈራረሱ እንዳልሆነለት ሲያይ ከምንጊዜውም በላይ የአውሮፕላን ድብደባውንና አረመኔያዊ ተግባሩን አጠናከሮ፣ ልክ ጀምበር ፀሐይ እንደወጣች አስጀምሮ ጀንበር እስክትጠልቅ ድረስ ስላስማራቸው፣ የኢትዮጵያ ሰራዊት ከመሸሸጊት ዋሻ እንኳ ብቅ አድርጎ ማየት አይችልም ነበር።

ጣልያኖች ከትግራይ ሽፍቶችና በጉርሻ ካደሩ የአካባቢው ሰዎች ባገኙት ወሬ ጣልያኖች የቦንብ ዝናባቸውን በየቀኑ ሲያዘንቡ የራሶቹ ጦር በየገደሉ ስር ተደብቆ ... የጣልያኖቹ በምግብ ምናልባት ርቦት ሳር ሲግጥ የውሃ እህል ቢገድል ... እንዳልቡት ጦሩን እንዳልበታተኑት" ሲረዱ እጅግ በጣም በሸቀው ስልታቸውን ... በምግብ በገደሎች አናት ላይ ማውረድ ጀመሩ።

ከአንድ ገደል ስር ባለች ዋሻ እኛ ስስታችንና ሀያ የሚሆኑ የደጃዝማች አበራ ... አባቶች በደጃዝማች አበራ ዋሻ ከደጃዝማች አበራ ጋር ተጨናንቀን ... ጣልያኖች በአዲስ የድብደባ ስልታቸው መሰረት ከእኛ ማዶ ላይ ... ገደል፣ የማይበዛውን የዋሻዎቹን ጣራ፣ ያንን የሰማይ ስባሪ የሚያክል ... ድንጋይ፣ በቦምብ እየቦኩ ደጋግመው ይወግሩት ጀመር።

እነዚህ ስድስት ባለ ሶስት ሞተር አውሮፕላኖች ያንን ገደል እየዞሩ ሲደበድቡት ቆይተው በድብደባው የተነሳው አቧራ በሰማይ ላይ ተበትኖ ገና ሳይጠራ ሌሎች ስድስት አውሮፕላኖች መጥተው ይደበድቡታል። በእንዲህ ዓይነት ቢጓ ጠዋት ፀሐይ ስትወጣ የጀመሩ ቀኑን ሙሉ ሲደበድቡት ውለው ጀንበር ልትጠልቅ ትንሽ ሲቀራት ያ እድለቢስ ገደል ዱላው ቢበዛበት አልችል ብሎ እየተገነደሰ ይወርድ ጀመር። ይኼ እድለቢስ ምስኪን ገደል እንዲህ ወገቡ ላይ እየተቀጨ ሲወርድ ከእኔ የመሸጉትን፣ እንደ አምላክ ያመኑትን፣ እነዚያን ምስኪን ነዋሪዎቹን ከነነፍሳቸው በውስጡ ይቀብራቸው ጀመር።

እንዲህ አምነውት በከለላው ስር የገቡትን ምስኪን ባላገር ወታደሮች ከነህይወታቸው በር ዘግቶ፣ ማምለጫ አሳጥቶ ሲቀብራቸው፣ በብዙ ጦር ሜዳዎች የቀለውን ኮሎኔል ኮናቫሎቭን እንኳ ዘግንኖት የወንድ ልጅ ልቡን ቢወጋው ለእዚህ ምስኪን ባላገር እድለቢሶች እንባውን አወረደው። ኮሎኔል ኮናቫሎቭ በዚህ ፍጹም አረመኔነት በተሞላበት ዘግናኝ ተግባራቸው ጣልያኖችን እንዲህ አቅመቢስ ሆኖ በተወሸተባት ዋሻ ውስጥ ሆኖ እየረገመ ለነዚያ ምስኪን ባላገሮች ስትስት ብሎ አለቀሰ።

ኢትዮጵያውያን በጣልያን አውሮፕላኖች ላይ በአርጌ ጠብመንጃቸው መተኮስ ዋጋ እንደሌለው ካወቁ ስለቆዩ፣ እንዲህ ጣልያኖች በማን አለብኝነት ሰማዩን የግል ግዛታቸው አድርገው እንዳሻቸው ዝቅ ብለው እየበረሩ ሽክማቸውን ሲያወርዱበት ነፍሱን ለፈጣሪው ሰጥቶ ዝም አላቸው። እንዲህ በደጃዝማች አበራ ዋሻ አቅመቢስ ሆነን ስንቀመጥ ቀኑ እንደ ዓመት እየረዘመብን ጀንበር የምትጠልቅበትን ሰዓት በታላቅ ጉጉት እየጠበቅን፣ ነግቶስ ነገ ዳግም ፀሐይን ማየት እንችል ይሆን? እያልን ስንጨነቅ ጀንበር ጠለቀች።

እዎ ዛሬም እድለኞች ነን፣ ሁላችንም ፈረንጆች ሰላም ነን። ኢትዮጵያውያን ካልሞቱ ወይም ካልቆሰሉ ከየተደበቁበት ዋሻ፣ ገደል ወይም ጉድጓድ መውጣት ይጀምራሉ። አንዳንዶቹ አሁንም ምስጋናቸውን ለፈጣሪያቸው ለማድረስ ሲጸልዩ ይሰማሉ።

ልክ ጀንበር እንደጠለቀች ራቅ ካለ የተራራ ጫፍ ላይ ያ ቄስ ለእግዚአብሔር ምስጋናውን እያቀረበ ሲጮህ፣ ወዲያው በሺዎች የሚቆጠሩ ድምጾች ተቀብለው "አሜን" ሲሉ፣ ገደሎቹ ይቀበሉትና በማሚቶዎቻቸው ሲያስተጋቡት ያ ድምጽ በጣም ርቆ ይሰማ ነበር።

ጣልያኖች እስከ ጥር 20 ቀን 1936 ዓ.ም. ድረስ ምንም እንኳን ለ የሚባለውን የዘመኑን መሳሪያ ታጥቀው በምድር በታንክና በመድፍ እየታገዙ፣ በሰማይ ላይ ያለምንም ተቀናቃኝ የቦምብ ዝናባቸውን እያወረዱ፣ የኢትዮጵያ ሰራዊት ሊመክተው በማይችለው ሁኔታ በጦርነቱ ቢገፉም እስካሁን ያለው ጦርነት ወደፊት ከሚመጣው ጋር ሲተያይ ሰብአዊነት የተላበሰ ነው ማለት ይቻላል።

ከጥር 23 ቀን 1936 ዓ.ም. በተንቤን ከደረሰባቸው ታላቅ ሽንፈት በኋላ ግን ከዚህ መልኩ በጦርነቱ ከገፉ ዳግማዊ አድዋ እንደሚመጣ የተገነዘበው ማርሻል ባዶሊዮ የጦርነቱን ስልት ቀይሮ፣ ወይም በሌላ አነጋገር የአየር ላይ ጥቃቱን እንደቀጠለም ጊዜ በላይ አጠናክሮ፣ ያለምንም እረፍት ልክ ፀሐይ እንደ ወጣች ጀምሮ ጀንበር እስክ ጠለቀችበት ሰዓት ድረስ የኢትዮጵያ ሰራዊት መሽጎበታል የተባለውን ቦታ ሁሉ እንዲደበድቡ አደረገ።

ይህ አልበቃ ያለው ማርሻል ባዶሊዮ ተራ እና ሰላማዊ መንደሮች ላይ ሁሉ ሳይቀር በመርዝ ጭስ የተሞሉ በርካታ የመስታወት ቱቦዎችን ያለ ርህራሄ መጣሉን ቀጠለ። ጥር 23 ቀን ጣልያኖች ተሸንፈው ከለቀቁት የጦር ሰፈራቸው ወረዱ የኢትዮጵያ ወታደሮች እንደምርኮ ዘርፈው ካመጧቸው ንብረቶች አንዷ አንድ ቀጠን ያለች ቡናማ ቀለም ያላት ፈሳሽ ነገር የተሞላባት የመስታወት ቱቦ ነበረች። በዚች የመስታወት ቱቦ ላይ የተለጠፈ ወረቀት "ተጠንቀቁ"፣ ይኼ በመርዝ ጭስ የተቃጠለ ሰውነት ማከሚያ ነው" ይላል።

እዎ ይህ ጣልያኖች ኢትዮጵያን ሲወሩ ጀምሮ የኢትዮጵያን ሰራዊት በመርዝ ጭስ አፍነው ድራሹን ለማጥፋት መወሰናቸውን ያሳያል። አሊያማ ደካማው የባላገሩ ሰራዊት እንኳን የመርዝ ጪስ ሊጠቀም ቀርቶ ከዚህ መርዘኛ ጪስ መከላከያ የጋዝ ጭንብል ከረጢት እንኳን የሌለው ከመሆኑም በላይ፣ መርዙ እንኳን ቢኖረው እንዴት አድርጎ እንደሚጠቀም እንኳን የማያውቅ መሆኑን የሚያውቁ ያውቁታል።

ጥር ወር መጨረሻ ላይ ጣልያኖች በደጃዝማች አበራ የጦር ሰፈር ላይ አንድ ትልቅ የመርዝ ጭስ የተሞላ የመስታወት ሙቀጫ የመሰለ ነገር ጣሉ። ይኼ የመስታወት ሙቀጫ በደጃዝማች አበራ ሰፈር ከመሬት ወድቆ ሲከሰከስ ወደቢጫነት የሚወስደው በጣም የሚገማ ጉም ሲነሳ በጊዜ ያየው ኮሎኔል ኮናቫሎቭ እጅግ የሚገርም ፍጥነትና ሁኔታ ከተቀመጠበት ቦታ ተነስቶ እንደ እብድ ሰው ወዲህና ወዲያ እየሮጠ በጣም ከፍ ባለ ድምፅ "ተጠንቀቁ! ቶሎ ቶሎ በሉ! የመርዝ ጪስ! ቶሎ በሉ! የመርዝ ጪስ፣ ቶሎ ወደላይ ወደ ገደሉ ውጡ!" ብሎ ረዘም ላሉ ደቂቃዎች ያለማቋረጥ በሰባራ አማርኛ፣ ትግርኛ፣ ኦሮምኛ ለፈለፈ።

እዎ የኮሎኔልንና በኋላ የኛንም ድምጽ የሰሙ እስካሁን በየዋሻው የተደበቁ የደጃዝማች ወንድወሰን ሰዎች ከየመሸጉበት ቦታ እየወጡ፣ ከጣልያኖች አውሮፕላን ዘወትር መትረየስ ጥይት እየወረደባቸው፣ ልክ እንደ ዝንጀሮ ከየምሽጋቸው ዘለው እየወጡ ገደሉን እየቧጠጡ ሽቅብ መውጣት ጀመሩ። እዎ በወንድማማቾቹ ደጃዝማቾች በአበራና በወንድወሰን የጦር ሰፈር በርካታ ወታደሮች ልክ እንደሰከረ ሰው ጥቂት ደቂቃዎች ተንገዳግደው ሸብረክ እያሉ እስከመጨረሻው ማንቀላፋት ጀመሩ። በዚህ አደገኛ የመርዝ ጭስ የተቃጠሉ፣ ምንም አይነት ዶክተርና መድሃኒት በሌለበት የጦር አውድማ እየተቃጠሉ ወደ እማይቀርበት አለም አዘገሙ።

ምስኪን ኢትዮጵያውያን ከአዲሱ የጣልያን አደገኛ መሳሪያ ጋር እንዴት መከላከል እንኳ እንደሚችሉ መላው ጠፍቷቸው፣ ጸሎታቸውን ወደ እግዚአብሔር እያደረሱ ሁሉን ለሱ ሰጥተው ተቀምጠዋል፡፡ በየካቲት ወር መጨረሻ ላይ ለረጅም ጊዜ ያላየናቸውና ደረጃ በደረጃ የረሳናቸው፣ ገና ደብረ ታቦር በገባሁ ጊዜ ቶሎ የቅርብና ጥሩ ወዳጄ የነበሩት ባላምበራስ ወልደ ማርያም ወደ ጦር ሰፈራችን መጡ፡፡

ባላምበራስ ወልደ ማሪያም በመጀመሪያው ቀን የጣልያኖች የአውሮፕላን የቦንብ ድብደባ ክፉኛ ቆስለው አይቦታ የጦር ሰፈር ለአርባ ቀን እድላቸው ጥለናቸው ባንመጣ ኖሮ፣ ዛሬ እንዲህ ፍጹም ጤነኛ ሆነው ወደ ጦር ሰፈራችን ብቅ ማለት መቻላቸው ብዙም ባላስደነቀን ነበረ፡፡

ባላምበራስ ወልደ ማርያም ለሁለተኛ ጊዜ የጣልያንን ወራሪ ጦር ለመግጠም ሲጓዙ፣ ዘመኑ ባፈራው ከሰማይ ላይ በሚወርድ ቦንብ እግራቸውን ክፉኛ ቆስለው፣ ዶክተር ቀርቶ ህመም ማስታገሻ በሌለው ሰራዊታችን ውስጥ በድንኳናቸው ውስጥ ተኝተው፣ የጣዝማ ማር በቁስላቸው ላይ እየተቀባላቸውና በቆሻሻ ሸማ እየታሰረላቸው ስንባብተው፣ ጦራችን ወደፊት ሲጓዝ በዚያው ጥለናቸው ሄድን፡፡

ብዙው ሰው ወደ ትውልድ አገራቸው፣ "ወደ ዳሞት (ጎጃም ውስጥ መሰለኝ) ተመልሰዋል" ሲል አነስ ያለው ክፍል ደግሞ "ያው ህመማቸው ጠንቶባቸው እንደማንኛውም ቁስለኛ ወታደር ሁሉ፣ ሌላም ሌላም በሽታ ተቀላቅሎባቸው እዚያው አይቦታ የጦር ሰፈር ሳይሞቱ አይቀሩም" ብሎ እርሙን አውጥቶ፣ በየቀኑ የሚገጥመውን መከራ እየታገለና ነገን ዳግም ለማየት እየጸለየ፣ ባላምበራስ ወልደ ማርያምን እስከመፈጠራቸውም ረስቷቸው ነበር፡፡

ወደ ዳሞት ተመልሰዋል ወይም በመንገድ ላይ ሞተዋል ተብለው የተረሱት ሽማግሌው ባላምበራስ ወልደ ማርያም ፍጹም ጤነኛ ሆነው፣ በበቅሏቸው ላይ ጉብ ብለው፣ ወደ ጦር ሰፈራችን አቢ አዲ በድንገት ብቅ ሲሉ ሁላችንም መደነቃችንን መገረማችን ገደብ አልነበረውም፡፡

ማምሻው ላይ በደጃዝማች አበራ ሰፈር በኩራዝ ዋሻ ውስጥ ዙሪያ ገጥመን ስናወጋ ባላምበራስም መጥተው ስለተቀላቀሉ የወትሮ ጨዋታችንን ትተን የባላምበራስ ወልደ ማሪያምን አስደናቂ ታሪክ መስማት ጀመርን፡፡

ባላምበራስ ወልደ ማርያም ትንሽ ሳት ብለው ልክ ጦራችን አይቦታን መልቀቅ ሲጀምር አንድ ጣልያኖቹን ከድቶ ከወንድሞቹ ጋር የተቀላቀለ የሀማሴን ተወላጅ ጣልያኖቹ በአድዋ የጦር ሰፈራቸው ትልቅ ሃኪም ቤትና በርካታ ሀኪሞች ከፈቶ መድሀኒቶች ጋር እንዳላቸው ያጫውታቸዋል፡፡ ባላምበራስም ጨለምለም ሲል በቅሏቸውን ያስጭኑና በሰፈር ያሉ ሰዎች አግዘዋቸው በቅሏቸው ላይ ጉብ ይላሉ፡፡

ከጦር ሰፈር ሲወጡ ለጠየቃቸው ሁሉ ወደ ዳሞት እንደሚሄዱ ነግረው ጉዞ ይጀምራሉ፡፡

የዳሞቱን መስመራቸውን ወደጎን ትተው መስመራቸውን ወደ አድዋ ያቀናሉ፡፡ ወደ አድዋ ሲጓዙ ለአቀማቸው የጣልያን ወታደር ሁሉ፣ የተንቤን ክልል ሰላማዊ ነዋሪ ከመሆናቸውም በላይ የታላቁ ጌታ የሞሶሎኒ ወዳጅ መሆናቸውንና አንድ ቀን በማሳቸው ውስጥ በእርሻ ላይ እንዳሉ ከጣልያን አውሮፕላን ቲፕ ስር የሆነ ነገር ወድቆ በማሳቸው መሀል ሲፈነዳ የተፈናጠረ ብረት በእግራቸው አጥንት ውስጥ ገብቶ ማውጫው መንገድ ጠፍቷቸው፣ ይኼንኑ ጉዳይ ወደ አድዋ ለማሳወቅ የሚሄዱ መሆናቸውን ያስረዳሉ፡፡

ባላምበራስ ወልደ ማሪያም በመንገዳቸው ለአጋጠማቸውና ለአስቆማቸው ሰው ሁሉ ይኼንኑ የፈጠራ ወሬያቸውን ደጋግመው እያወሩ አድዋ ይደርሱና ይኼንኑ ውሸታቸውን አድዋ ላለው ዶክተር ይገልጣሉ፡፡ ጣልያኑ ዶክተርም ቁስላቸውን ከአየ በኋላ በአስቸኳይ የቀዶ ጥገና ክፍል አዘጋጅቶ፣ በዘመናዊ ህክምና አጥንታቸው ላይ ተሰክቶ የነበረውን የቦንብ ብረት አውጥቶ፣ እስኪያገግሙ ድረስ በሆስፒታሉ እንዲተኙ ፈቀደላቸው፡፡ እስታማሚዎቹም ጥሩ አድርገው እንደቀለቧቸው ሰውነታቸው ይመሰክራል፡፡ በመጨረሻ በትክክል መዳናቸው ታውቆ ወደ መንደራቸው ሊያሰናብቷቸው፣ በበቅሏቸው ላይ ተፈናጠው፣ በአቋራጭ መንገድ ሲገሰግሱ ውለው፣ ከእናት ሀገር ጦራቸው ጋር እነሆ ተቀላቅለው፣ የጣልያንን ጦር ለመግጠም እንደመጡ ሳቅ እያፈናቸው አጫወቱን፡፡ እኛም በአዛውንቱ ድፍረትና ዘዴ ተደንቀን አሳቸው ሲስቁ እኛም ሳቃችንን ለቀቅነው፡፡

በዚህ ጊዜ አስደሳቹ የተንቤኑ ድል በመላው የትግራይ ጠቅላይ ግዛት ብቻ ሳይሆን በመላው ኢትዮጵያ እስከ ደቡብ ጦር ግንባር ድረስ ዘልቆ ተጋኖ መወራት ጀመረ፡፡ የዚህን የካሣን ጦር አስደናቂ ድል የሰሙ በዚህ ጦርነት ያልተካፈሉት ብዙዎች እጅጉን በጣም አዘኑ፡፡ ቆጫቸው፡፡ ያሳዘናቸውና ያስቆጫቸው የካሣ ጦር የጣልያኑን ጦር ማሸነፉ ሳይሆን፣ እነሱ በስንፍናቸው ከዚህ ጦር ጋር ተሰልፈው ተዋግተው ጦሩ ድል ከተጎናጸፈ በኋላ በዘረፈው ንብረት ሃብታም ሲሆን እነሱ ባዶ እጃቸውን በመቅረታቸው ብቻ ነበር፡፡

ይኼ የራስ ካሣ ጦር ድል አድራጊነት ክፉኛ ያሳዘናቸው ግን የተንቤን ተዋሳኝ የሆኑቱ የሰሆላ ሰዎችን ነበር (በካርታው ላይ SELOA ይላቸዋል)፡፡ የሰሆላ ሰዎች በደህናውና በሰላሙ ጊዜ ያቺኑ የተራራ ቀበሌያቸውን እንደነገሩ አራርሰው፣ ከአመረቱት ምርት ላይ የተራራማ ቀበሌያቸውን እየታከከ የሚያልፍ ሲራራ ነጋዴ በመዝረፍ ጎደሎዋቸውን ሞላልተው የሚኖሩ፣ ከህግ ውጪ የሚተዳደሩ ከመሆናቸውም በላይ፣ ለራስ ሥዩምም ሆነ ለደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ግብር ሳይከፍሉ በሆኑት የተራራ ላይ ቀበሌያቸው ላይ ተሰቅለው በነጻነት የሚኖሩ ሰዎች ነበሩ፡፡

ታዲያ ሀገር ስትወረር አንድም ራስ ሥዩምን ለዘመናት በፈጸሙት ወንጀል እንዳይቀጧቸው በመፍራት፤ ሁለትም በዚህ በክፉ ጊዜ ያቺ ሁለተኛ የመተዳደሪያ ሙያቸው ይበልጡን እንደምታብብ ተስፋ በማድረግ ወደ ጦር ሜዳ ሳይወርዱ እንዲሁ በመንደሮቻቸው ተቀምጠው ቀሩ።

ታዲያ እንዲያ ተስፋ ያደረጉበት በዘረፋ የመበልጸግ ጉዳይ ሳይሆንላቸው ቀርቶ፤ ከሁሉም በላይ በተንቤኑ የመጀመሪያው ቀን ጦርነት የተሳተፉ ጓደኞቻቸው፣ ዘመዶቻቸው በአገኙት ድል ከጦር ሜዳ በማረኩት ምርኮና ሃብት ሲሸለሉና ሲፎክሩ እነሱ ባዶ እጃቸውን በቀበሌያቸው በመቀመጣቸው ክፉኛ አዘኑ፤ ተቆጩ።

የሰሆላን ሰዎች እንዲህ እነሱ ባዶ እጃቸውን ተቀምጠው፣ የካሣ እና የሥዩም ጦር ባለሃብትና ባለስም ሲሆን ማየቱ ጥቅም የለውምና እንዲያው ለወደፊቱ ምን ማድረግ እንዳለባቸው በአንዲት መንደር ተሰብስበው መምከር ጀመሩ። ከተሰበሰቡት የሰሆላ ሰዎች ገሚሶቹ "ተሰብስበን ወደ ተንቤን ወርደን፣ ለሥዩም ገብረን፣ አብረነው ጣልያንን እየወጋን እኛም እንደሌላው የሥዩምና የካሣ ጦር ሁሉ ሃብት እናከማች" ሲሉ ሃሳብ አቀረቡ።

ይኼ ሃሳብ የጸደቀ ከመሰለ በኋላ አንዱ ተነስቶ፣ "ጎበዝ ሞኝ አትሁኑ። አሁን ማ ይሙት ለዘመናት የሥዩምን ሲራራ ነጋዴ ስንዘርፍ ኖረን፣ አሁን ስተት ብለን ሄደን አብረንህ ጣልያንን ልንወጋ ልንገብርልህ መጣን ብንለው እሺ ብሎ አቅፎ የሚቀበለን መሰላችሁ? ሞኝ አትሁኑ። ከምንመኘው ሃብትና ስም ይልቅ ቅጣት ነው የሚጠብቀን። አይሆንም፣ ሄደን አብረነው አንዋጋም" ሲል ተቃወመ። ሌላው ሲራራ ነጋዴ ዘራፊ ተነስቶ፣ "ራስ ሥዩም አብረነው እንድንዋጋ ቢፈቅድ እንኳን፣ ወደፊት እንዳሻን እየዘረፍን በነጻነት መኖር አንችልም። ይኼ ለሥዩም ባርነት መግባት ነው፤ ሌላ መላ መምታት አለብን" ሲል ተጨማሪ ተቃውሞ አቀረበ።

በዚህ መልኩ ቀኑን ሙሉ ሲመክሩ ውለው ማምሻው ላይ በአንድ ሃሳብ ተስማሙና ይኼንን ሃሳብ ለራስ ሥዩም የሚያደርሱ መልክተኞችን መርጠው፣ ወደ ራስ ሥዩም መንገሻ ወደ ተንቤን፣ ወደ አቢ አዲ ላኳቸው። እነዚህ የነጋዴ ዘራፊዎች "እንደራሴዎች" ወደ ራስ ሥዩም የጦር ሰፈር አቢ አዲ ብቅ ያሉት እኛ በአጋጣሚ የጦር ሜዳ ምክር ላይ እንደተቀመጥን ነበር። የሰሆላ ሰዎች መልክተኞች "እንደራሴዎች" በራስ ሥዩም መንገሻ አጋፋሪ በኩል፣ "ለጥብቅ ጉዳይ እንደመጡና በራስ ሰዩም መንገሻ ዙፋን ፊት ቀርበው እጅ መንሳት እንዲፈቀድላቸው" ጠየቁ።

እኔ ከተወሰኑ ቃላት ውጪ ትግሪኛ አልችልም። እና እነዚህ መልክተኞች ደግነቱ ለራስ ሥዩም የሚያቀርቡትን አቤቱታ ፍሬ ነገር መረዳት አልቻልኩም። ደግነቱ ለራስ ሥዩም የሚያቀርቡትን አቤቱታ ፍሬ ነገር መረዳት አልቻልኩም። ደግነቱ

"ለ2,000 እና ለ3,000 የጣልያን ጦር የሚበቃ ኃይል እንዳላቸው አሳስበው፣ የተከበሩት ጌታ ራስ ሥዩም መንገሻ የጣልያኑን ጦር በጦራቸው አግደው ይዘው አሳልፍም በማለታቸው የሰሆላ ሰዎች ባለፈው የምርት ዘመን እምብዛም አልቀናቸውም። ስለዚህ ቢያንስ የጣልያንን ወታደሮች ገድለው እንዳይዘርፉና ትሯቸውን እንዳይደጋግፉ የተከበረው ጌታ የራስ ሥዩም ጦር አግዶ አሳልፍም በማለቱ፤ ክፉኛ የተቸገሩ መሆናቸውንና ከዚህ ጦርነት ምንም ጥቅም ሳያገኙ ባዶ እጃቸውን መቅረታቸውን ጨምረው ገለጹ። ራስ ሥዩም መንገሻ ፈቃዳቸው ሆኖ አንድ 3,000 የጣልያን ጦር ቆርሰው ወደ ግዛታቸው ቢያሳልፉላቸው ውለታውን እግዚአብሔር ሁሉ እንደሚያገኙት ጨማምረው ገልጸው አቤቱታቸውን አሰሙ" ብሎ እየሳቀ ልጅ ወልደ ገብርኤል ሲተረጉምንልኝ፣ የእነዚህ ምስኪን፣ የዋህ ሰዎች ሃሳብ እኔንም እያሳቀ አስለቀሰኝ።

በየካቲት ወር 1936 የመጀመሪያ ሳምንት ላይ የኢትዮጵያ ወታደሮች ኦርሊኮን (Oerlikon) በተባለው የሲዊዘርላንድ አየር መቃወሚያ መሳሪያ አንድ የጠላት አውሮፕላን መትተው ጣሉ። የኢትዮጵያ ወታደሮች ባለሶስት ሞተር ትልቅ አውሮፕላን መትተው ሲጥሉ የመጀመሪያቸው ነው። አውሮፕላኑ እንደተመታ ጭሱን ሽቅብ እያበነነ ቁልቁል ባፍንጫው ሲደፋ ሲያሽቆለቁል አብራሪው ዣንጥላውን ዘርግቶ ሽቅብ ወደ ላይ ተስፈነጠረ። እንዲህ በፍጥነት ቁልቁል የሚወርደው አውሮፕላን አሁን በጪሱ ምትክ እሳት እየተፋ ከደብረ አንባ በስተጀርባ ወርዶ ባፍንጫው ተከሰከሰ። ወታደሮቻችን ወደ ተከሰከሰው አውሮፕላን እየሮጡ በቦታው ሲደርሱ፣ አውሮፕላኑ እየነደደ ባጠገቡ የነበሩትንም ቁጥቋጦዎች ሁሉ ውጦ ይማግዳቸው ነበር።

የዚህ አውሮፕላን አብራሪ አውሮፕላኑ እንዳይተርፍ ሆኖ መመታቱን ሲያይ በጊዜ ጥላውን ዘርግቶ ቢዘልም፣ በዚያ ረፋድ ጠንከር ያለ ንፋስ ይነፍስ ስለነበር ተንሳፋፊውን አብራሪ ንፋሱ ከሰፈሩ ብዙ አርቆ ወሰደው። ወታደሮቻችን እንዲህ በሰማይ ላይ ትልቅ ጥላ ዘርግቶ የሚንሳፈፈውን የጣልያን አውሮፕላን አብራሪ እንደተዓምር እያዩ እየተከተሉት ያርፍበታል ብለው የገመቱት ቦታ ቢደርሱም፣ አብራሪው ጥላውን በጊዜ ሰብስቦ ከአይናቸው ተሰወረባቸው።

ምንም እንኳ አብራሪው በሰላም መሬት ላይ ማረፉ የማያጠራጥር ቢሆንም፣ ይኼ አብራሪ ወደ ጦር ሰፈሩ ተመልሷል ብሎ መገመት ግን ያስቸግራል። ወይ የኢትዮጵያ ወታደሮች የሚተኩሷቸው ጥይት ሰለባ ሆኗል። አልያም አሁን እጅጉን በጣም የሰው ስጋ የለመዱትና የተራቡት የሌሊት ጅቦች ራት ሆኗል።

በሁለተኛው ቀን ወታደሮቻችን ዳግም በለስ ቀንቷቸው ሁለተኛውን ባለ ሶስት ሞተር አውሮፕላን ጣሉት። ይኼኛው አውሮፕላን እንደ ትናንቱ አልነደደም። አብራሪውና ታዛቢው ግን ሞተዋል። ወታደሮቻችን አውሮፕላኑን ለመጣላቸው መረጃ

ይሆናቸው ዘንድ ከአውሮፕላኑ ውስጥ የተለያዩ ጠቃሚ ናቸው ብለው የገመቷቸውን ነገሮች ገነጣጥለውና ሁለቱን ሟች የጠላት ወታደሮች ሬሳ ተሸክመው ከሁለቱ ራሶች ፊት ቀረቡ።

ሁለቱ ራሶች ሌሎች ወታደሮች የጠላት ወታደሮችን ሬሳ እንዲቀብሩ አዘዙው፣ ግዳይ ለጣሉት ወታደሮች የሚገባቸውን ሽልማትና ሹመት ለመስጠት ለምክር ወደ ድንኳናቸው ገቡ። በዚህ መልኩ ቀን ቀንን እየወለደ፣ ቀናት አልፈው ሳምንቶች ተተኩ። ጣልያኖችም የአውሮፕላን ድብደባቸውን ረገብ ስላደረጉት ሰላም የሰፈነ መሰለ።

እነሆ የራስ ካሣ ጦር በአቢ አዲ እንደሰፈረ ሳይንቀሳቀስ ሁለተኛ ወሩን ይዟል። ሁለት ወር በአልሞላ ጊዜ ውስጥ የተንቤን አካባቢ ነዋሪዎች ጦርነትና ጦርነት የሚያስከትለውን አደጋ ሁሉ ለመዱት። የተንቤን አካባቢ እናቶች ደረጃ በደረጃ፣ ቀስ በቀስ ከየተደበቁበት ተራራ ስርና ዋሻ ውስጥ እየወጡ ልጆቻቸውን እያዘሉ ወደ አቢ አዲ መመለስ ጀምረዋል።

ብዙም ሳይቆይ የአቢ አዲ ከተማ ነዋሪዎች ወደ ጎጇቸው ተመልሰው ከጦርነቱ በፊት እንዳለው አይነት ባይሆንም እንደነገሩ የተለመደ ህይወታቸውን መኖር ጀመሩ። አልፎ አልፎ፣ ይኼ የጣልያኖቹ የአውሮፕላን ድብደባ ረገብ በማለቱ፣ በአቢ አዲ ከተማ ላይ ነዋሪዎቿ ከጦርነቱ በፊት ገበያ ይውልባት በነበረች አነስተኛ ሜዳ ላይ ይሰበሰቡና ነጠላቸውን መሬት ላይ ዘርግተው እቃዎቻቸውን እየዘረጉ መገበያየት ይጀምራሉ።

በእንዲህ አይነት ገበያዎች ላይ ብዙ የኛ ወታደሮችም ለሸመታ ይወጣሉ። በእንዲህ አይነት የጦር ሜዳ ገበያ ላይ በርበሬ፣ ጨው፣ አምባሻ፣ ማር፣ ጠጅ፣ አረቄ፣ ጠላ፣ ብዙ አይነት የጥራጥሬ እህሎች፣ ዶሮዎች፣ የፍየል ጠቦቶች፣ የጫንት ከብቶችና ብቻ ሌላም ሌላም ነገሮች ገበያ ላይ ይውላሉ። በዚህ የጦር ሜዳ ገበያ ከማርትሬዛ ብር ሌላ በጥይትም መገበያየት ይቻላል። አዎ ጥይት እንደ ገንዘብ ሆና ያገለግላል። ለዚህም መሰለኝ ኢትዮጵያዊ ወታደር አልሞ ኢላማውን በትክክል መምታቱን ርግጠኛ ካልሆነ የማይተኩሰው። አዎ ወታደሮቻችን በከንቱ ጥይት ከማባከን ጦራቸውን እየሰበቁ ጎራዴያቸውን እያፋጩ የእጅ በእጅ ውጊያ ነው የሚወዱት። እና እኔም እንዲህ ገበያ ሲውል ሁሌም አንበሳን ጥሩ ጠጅ መርጦ እንዲገዛልን አልከው ነበርና ዛሬም ወደ ገበያ ላኩት።

ይሁን እንጂ አንበሳ ገና ከመውጣቱ የአውሮፕላን ድምጽ ስለሰማሁ፣ ቆይና ከድብደባው በኋላ ትሄዳለህ ብለው፣ "ግዴለም ጌታ፣ ግዴለም ጌታ" እያለ፣ ገንቦዋን ትከሻው ላይ አሸራሽሮ እያስቀመጠ፣ ከሰፈር ወጥቶ ወደ ገበያ ሄደ።

በሰዓት ላይ አንበሳ በድንጋጤ እየተንቀጠቀጠ ወደ ሰፈር ተመለሰና፣ ትንሽ ጎደል ያለችውን ጠጅ የያዘች ገንቦ እያሳየኝ "ታያለህ ጌታ፣ ቦምቡ አጠገቤ ሲወድቅ

ዞሶ አሽቀንጥሮ ቢጥለኝ፣ ጉድ ነው! ሁሉንም ያለመድፋቴ" እያለ ስለ ጠጁ መድፋት አሜወተ። እኔ አንበሳዬ በቦምቧ ትልቅ ድንጋጤ ብትጥልበትም፣ ለጠጁ የፈራውን ያህል ለራሱ ነፍስ አልፈራም ነበር።

በሚቀጥለው ወር ሁለተኛ አጋማሽ ላይ ጣልያኖች የኢትዮጵያ ወታደሮች ተደብቀውባቸዋል ብለው የገመቷቸውን ገደሎች ሁሉ በትላልቅ ቦንቦች መደብደብ ቀጠሉበት። አንዳንድ ገደሎች የቦንቡ ድብደባ ሲበዛባቸው እንደጉመን ... መቃብራቸውን ቆፍረዋል። በገደል ስር ያሉ ዋሻዎች አሁን ... ጥገኞቻቸውን ለራሳቸውም መከታ የሚፈልጉ መሆናቸውን የተረዱት ... የበዛና በየገደሉ ስር ባሉ ዋሻዎች ውስጥ መደበቁን ትተውታል። እና ወታደሮቻችን አሁን ... የሚል አይነት ሁሉን ለፈጣሪያቸው ትተው፣ የቦምብ ድብደባ ... የመጣው ይምጣ በሚል አይነት ... ቁጥር አነስተኛ ድጋፎችን መከታ አድርገው በትዝብት መመልከት ጀምረዋል።

አንባቸውን በሁለት ረድፍ ዘለላ ዘለላውን እያወረዱት አቶ ተሰማ ከደጃዝማች ... ድንኳን ገቡ። አቶ ተሰማ ከጣና ሐይቅ ጀምረው ጉዛችንን በአህያ እየጫኑና ... መሰልቶች ከሌቦችና ከዘራፊዎች እየጠበቁ እዚህ አቢ አዲ እስከንደርስ ድረስ ... ያልተለዩ የቅርብ ወዳጃችን ናቸው።

ከአምስት ቀን በፊት እንደ ማንኛውም ሹሞችና ወታደሮች ሁሉ ባሏን አጅባ ... ጦር ሜዳ የመጣችው የአቶ ተሰማ ወጣት ባለቤት (ሚስት)፣ ቀኗ ደርሶ ምጥ ... ከአቢ አዲ ከተማ ሜፍ ላይ በአንዲት ጎጆ እኖሯትና፣ በሁለተኛው ቀን ... አዋላጅ አሮጊቶች ርዳታ ወንድ ልጅ ተገላገለች።

አቶ ተሰማ በጦር ሜዳ ወንድ ልጅ በማግኘታቸው ደስታቸውን ተካፍለው ... ሳይጠግቡት፣ ዛሬ አንድ የተረገመች የጣልያን አውሮፕላን በጦር ሰፈራችን ... የአሳታማ ቦንቦቿ አንዷ የአቶ ተሰማ ወጣት እራስ ሚስት ባረፈችበት ... ጎጆ ቤት ላይ ወርዳ ፈነዳች። ምንም እንኳ በቅርብ የነበሩ ሰዎች እራሷን የአቶ ተሰማ ባለቤትንና አንበሳውን ልጃቸውን ለማዳን ቢሞክሩም፣ እሳቱ በፍጥነት ተዛምቶ ... ያሉትን የሳር ጎጆዎች ሁሉ በትጋበት ከነነዋሪዎቻቸው አመድ አደረጋቸው። ... ምስኪን እናት ከነ ልጇ (አንበሳዋ) ምንም ኃይል ሊረዳት ሳይችል ቀርቶ ... ራት ሆነች። በዚህ ታላቅ ጭካኔ፣ የሰው ልጅ ህይወት ዋጋ ቢስ ሆነ። ራሴን ... ተሰማ ቦታ ተክቼ ሰጥቂት ደቂቃዎች አሰብኩትና ምርር ብዬ አለቀስኩ። አሁን ... ሆድ እየባሰኝ መጥቷል። ይኼ አልበቃ ብሎ አሁን በጦር ሰፈራችን አንድ ... ማንም ሊያግደው የማይችል አደገኛና መሰሪ ጠላት ገጭቶ ወደ ሰፈራችን ...

ይኼ የምስኪን ኢትዮጵያውያን ጠላት፣ ከጣልያን መናጢ የአውሮፕላን ቦንብ፣ ከትግራይ ሽፍቶች አደጋ ሁሉ የከፋ ሊገፋትና ሊታገሉት የማይቻል ጠላት ነው። ተላላፊ በሽታ፣ ተቅማጥ፣ ተስቦ፣ ወረርሺኝ።

ወጣቱ ጎልማሳ ልጅ ተድላ ከጦርነቱ በፊት በኤርትራ የኢትዮጵያ ቆንስል ጦርነቱ ሲጀመር ግድም ጀምሮ የራስ ሙሉጌታ መንገሻ የጦር አማካሪ ከጥቂት ቀናት በፊት እንደተጫጫነውና ብዙም ጤንነት እንደማይሰማው አጫውቶኝ ነበር። ከዚያን ቀን ጀምሮ በራሶች ድንኳን ስለማላየው ግራ ገብቶኝ ስነሳ ብቼ ዛሬ ከልጅ ተድላ የተባለ አሽከር ከኔ ድንኳን ደጃፍ ላይ ቆሞ፣ ልጅ ተድላ እንደተጫጫናቸውና ጤናቸው እስከዚህም እንዳልሆነና ሊያዩን እንደሚፈልጉ ሲነግረን ወደ ልጅ ተድላ ዋሻ እየተጣደፍን አመራን።

ከትንሺ ዋሻ ገባ ብሎ ካንዲት ግርግይ ላይ አርጌ ሸማ ለብሶ ልጅ ተድላ ተኝቶ አገኘነው። ልጅ ተድላ ገና ወደ ዋሻዋ መግባታችንን ሲያስተውል፣ ያለ የሌለ ኃይሉን አሰባስቦ ፈገግ ለማለት እየጣረና የሆነ ነገር ለመናገር እየሞከረ ለሰላምታ እጁን ዘረጋልን።

የልጅ ተድላ ክብና ሞላ ሞላ ያለች ሳቂታ ፊት ዛሬ ከመቼውም ጊዜ በላይ ጠውልጋ ወደ አጽምነት ተለውጣለች። ያ ወዘና የሞላው ፊቱ ጣረሞት መስሏል። ገና ወደ ዋሻዋ ከመግባታችን ልጅ ተድላ በሌለው ኃይል ፈገግ ለማለት እየሞከረ እጁን ሲዘረጋ እንዳስተዋልኩት፣ ከንፈሮቹ ብቻ ሳይሆኑ ምላሱ ጭምር ጭላሽት መስሏል። ልጅ ተድላ አሁንም በአለ በሌለ ኃይሉ አጥንትና ቆዳ ብቻ የቀሩትን እጁን ለሰላምታ እንደዘረጋልን ነው። ግን ልንጨብጠው እንችላለን? በምንስ አይነት አደገኛ በሽታ እንደተለከፈ እናውቃለን?

አዎ ምናልባት በሳሙና መታጠብ ይበቃን ይሆናል። ግን አቢቹ ከጣልያን ዘርፎ ከአመጣቸውና ከደረሱን ሳሙናዎች የመጨረሻውን ቁራጭ ከታጠብንበት ሶስተኛ ቀናችን ነው። እንግዲህ ከጨበጥነው በምን ይሆን የምንታጠበው? በሰፈር ያለው ውሃ እንኳን ጤና መሆኑን አናውቅም። ግን የወዳጅ፣ የጓደኛ እጅ ነው። ለአለፉት አምስት ወራት አብሮን ፍዳውን ሲያይ የቆየ ጓደኛ፣ ወዳጅና የጦር ሜዳ ወንድማችን እጅ ነው። እና ሁላችንም አንድ በአንድ፣ ተራ በተራ ጨበጥነውና እግዚአብሔር ምህረቱን ያወርድለት ዘንድ ተመኘንለት። ልጅ ተድላ በደስታ ሳቀ አለ ለመጨረሻ ጊዜ።

እንዳችንም አናውቅም፣ ልጅ ተድላ ያንን ጠንካራ ሰውነቱን በልቶ እንዲህ አጽሙን ብቻ ያስቀረውን በሽታ። ለመጀመሪያ ጊዜ የቅርብ ወዳጃችን ሲለየን ሆዳችን እየተንቦጫቦጨ ወደ ደጃዝማች አበራ ድንኳን ተመለስን። ከዚያች ቀን ጀምሮ በየቀኑ አንድ የምናውቀው ወዳጃችን ወይም በሰፈር የተግባባነው ሰው ቀኑን አብሮን ሲጫወት

ውሎ፣ ማምሻው ላይ ተጫጫነኝ እያለ ደካክሞ ካረፈባት መደቡ ሳይነሳ ወደማይቀርበት ሀገር ማዘንግም ጀመረ።

የናስ የሶስታችን አውሮፓውያን ተራ መቼ ይሆን? ወደ 8,000 ያህል የገበሬ ወታደሮች በመጀመሪያው ቀን ጦርነት ወድቀዋል። በየቀኑ የጣልያን አውሮፕላኖች ሚያርከፈክፏቸው ቦንቦች ከ10 እስከ 100 የሚደርሱ አድስ ቢስ ወታደሮች ያሽንፏቸው ይቀበራሉ። አሁን ደግሞ ወታደሮቻችን በማይታይና መምጫው የማይታወቅ፣ መድሃኒት በሌለው ጠላት፣ ተቅማጥ፣ ተስቦ እና ወረርሺኝ በየቀኑ ወደማይቀርበት ያዘግሙ ጀመር።

በየቀኑ በአቢ አዲ የጦር ሰፈር ከጠዋት እስከማታ እየዬና ዋይታዎች ይሰማሉ። ማምሻው ላይ ከጦር ሰፈር ትንሽ ወጣ ብሎ፣ ለሟች የመጨረሻ ስንብትና የነፍ መንፈስ ማባረሪያ በተደጋጋሚ ወደ ሰማይ የሚተኮሱ የጥይት እሩምታዎች ይሰማሉ።

ማምሻው ላይ ሁሉም የሟች ቤተሰቦችና ጓደኞች ሟችን በተንቤን ደም በጠገበ አፈር ቀይ መሬት ውስጥ ለመቅበር ከሰፈር ይወጣሉ። በልጅ ተድላ ተመሳሳይ የቀብር ስነስርአት ላይ እኔ ከኮሮኔል ኮኖቫልቭ፣ ከብረየር እና ከደጃዝማች አበራ ጋር ተገኘሁ፣ እንደማንኛውም የኢትዮጵያ ገበሬ ወታደር ሁሉ ለሟቹ ክብርና መጥፎ መንፈስ ማባረሪያ አከታትዬ ተኮስኩ።

27

ያልሞቱ ሬሳዎች ቀሻ

በየካቲት ወር አጋማሽ ላይ 135 ትልልቅ ሳጥኖች ሙሉ ጥይት የተጫኑ 80 መጋዣዎች በ50 ታጣቂ የራስ ሙሉጌታ ወታደሮች ታጅበው አቢ አዲ ደረሱ። በድምሩ 243,000 ጥይቶች ለ80,000 ታጣቂ የራስ ካሣ ወታደሮች ከኢትዮጵያ መንግሥት የተላከ የመጀመሪያው የትጥቅ ድጋፍ ነበር። ይኼም እስከ ጦርነቱ መጨረሻ ጊዜ ድረስ የመጀመሪያውም የመጨረሻውም ድጋፍ ነበር።

እነዚህን ጥይቶች ከትግራይ ቀማኞች ሽፍቶች እየተከላከሉ የመጡት የራስ ሙሉጌታ ወታደሮች ወደ ጦር ሰፈራቸው ሰሞኑን እንደሚመለሱ ስሰማ፣ ከዚህ የሰው ልጅ ሊሸከመው ከማይችለው ፍዳን የሚያበላ ጭንቀት የበዛበት ህይወት ትንሽ ማረፍ ፈለኩና፣ ከሆነልኝም እስከ ደሴ ዘልቄ ለመሄድ አብዬ ራስ ካሣን ያሰናብቱኝ ዘንድ ፍቃዳቸውን ጠየኳቸው።

እንዲህ ከአምስት ወር ቆይታ በኋላ ቢያንስ ለጥቂት ቀናት ወደ አምባራያ ወርጄ ማረፍ እንደምፈልግ አስረድቼ ፈቃዳቸውን ስጠይቃቸው፣ ሽማግሌው ራስ ካሣ ጉዳዩ ምን ያህል አስቸጋሪና አደገኛ እንደሆነ አስረድተው፣ ተቆጥተው፣ እዚሁ

አጠገባቸው እንደሁልጊዜው ሁሉ ከልጃቸው ከደጃዝማች አበራ የጦር ሰፈር አርፌ እንድቀመጥ በአባትነት መከሩኝ።

"እመነኝ ጌታው፣ እስከ ደሴ አትደርስም። ከአምባላጌ እስከ ወልዲያ ድረስ ባለው መሬት ላይ ጠላቶቻችን ጣልያኖች በኛ በወንድሞቻቸው ላይ ያስታጠቋቸው የራያና የአዘቦ አረመኔ ሽፍቶች ይገድሉሃል። ገና እንግዲህ ከአቢ አዲ ሲወጣ የትግራይ ሽፍቶች ተከታትለው መንገድ ዘግተው ይዘርፉሃል፣ ይገሉሃል። እስከ ደሴ ዘልቀህ ለመሄድ ሀሳቡ ካለህ ቢያንስ ሺህ የታጠቀ ወታደር ያስፈልግሃል። ስለዚያውም እድለኛ ከሆንክ ነው" እያሉ መከሩኝ።

ይሁን እንጂ እኔ ለመሄድ ወስኜ ነበር። የትግራይ ሽፍቶች በሞኝ እንደማይለቁኝ አውቃለሁ። ቢሆንም ኀምሳ የታጠቁ የራስ ሙሉጌታ ወታደሮች አሉኝ። ምንም ቢሆን ከአቢ አዲ የጦር ግንባር የከፋ ነገር በጉዞዬ ላይ ሊገጥመኝ እንደማይችል አሰብኩና፣ "ሄለም እሄዳለሁ" አልኳቸው።

ከሁለት ቀናት በፊት የጣልያን አውሮፕላኖች አቢ አዲ አሚጋዳው ላይ ይገኙ የነበሩትን ከብቶች፣ ፈረሶች፣ አህዮችና በቅሎዎች በቦንብ እያሳደዱ ሲደበድቧቸው የኔንም ፈረስና ሁለቱን በቅሎዎቼን ገድለዋቸው ስለነበር፣ ራስ ካሣ ከራሳቸው የገዛ በቅሎዎች አንዷን መርጠው ሰጡኝ። ጓዜን ጠቅልዬ ለጉዞ ስነሳ ራስ ካሣ እስከ ልጃቸው ደጃዝማች አበራ የጦር ሰፈር ድረስ መጥተው ተሰናበቱኝ።

ለመጨረሻም ጊዜ ይኼን አጉል ሀሳቤን ለውጬ እዚሁ አብሬአቸው እንድቆይ ለመኑኝ። "አምስት ወር ሙሉ እንደ ጥሩ ጓደኛሞች አብረን ኖረናል። አምስት ወር ሙሉ ክፉ ደጉን አብረን አሳልፈናል። አምስት ወር ሙሉ የገጠሙንን ችግሮች አብረን በጋራ ተወጥተናል። እባክህ ልጄ አትሂድ፣ ይቅርብህ። እንዲህ የምለምንህና የምመክርህ ልክ እንደ ልጄ ነውና እባክህ ልጄ አትሂድ። የትግራይ ሽፍቶች ይገድሉህና የሽማግሌ ልቤን ታሳዝነዋለህ። እባክህ አትሂድ" አሉኝ። አልሰማኋቸውም።

የካቲት 15 ለየካቲት 16 አጥቢያ ሌሊት ገና ጨረቃ ብርሃኗን በጥርሳሙ የደብረ አምባ ተራራ ላይ ከመፈንጠቋ ከድንኳኔ አጠገብ የሰዎች ድምጽ ሰምቼ ከእንቅልፌ ባንኜ ተነሳሁ። ወዲያው አንድ ሰው አንገቱን ወደ ድንኳኔ አስገብቶ፣ "ተነስ ጌታ፣ ጌታ ጌታ ተነስ!" አለኝ። ገና በትክክል እንቅልፌን ባልጨረስም ያለ የሌለ ኃይሌን አሰባስቤ ለመነሳት ስጣጣር ያው ድምጽ በድጋሚ፣ "ጌታ ጌታ፣ ተነስ ጨረቃ ወጥታለች እንሂድ" አለኝ።

አዎ ይኼን ድምጽ አሳምሬ አውቀዋለሁ። የባሻምበራስ ኪዳን ማሪያም ድምጽ ነበር። ባሻምበራስ ኪዳን ማሪያም ለራስ ካሣ ጦር በሰማኒያ አጋሰስ ጥይት ጭኖ የመጣው የ60ዎቹ ታጣቂ የራስ ሙሉጌታ ወታደሮች መሪና ሹም ናቸው።

አንበሳ ቀደም ብሎ ተነስቶ በአትራቢያው ካለችው ጅረት ውሃ ይዞልኝ መጥቶ ስለነበር በፍጥነት ከመገቤ በላይ ታጠብኩ። ቁርስ ለማድረግ ጊዜ አልነበረም ወይም ባላምባራስ ኪዳነ ማርያም በአፋጣኝ አቢ አዲን ለቅቀን እንድንወጣ ይወተውቱ ስለነበር ያለ ቁርስ ለጉዞ ተዘጋጀሁ።

በዚህ መሀል ሁለት ወታደሮች ያለችኝን ቋጠሮ (ሁለት ትናንሽ የጉዞ ሻንጣዎች) ባንድ መጋገ ላይ ጫኗት። ወዲያው ዙሪያዬን ቃኝሁና በቅሎዬን እንዲያመጡልኝ ጠየኩ። መልስ ሳጣ ወደ አንዱ ወታደር ዞር አልኩና "በቅሎዬ የታለች?" አልኩት። "ይቺው ጌታ" አለኝ። ወዲያው ንግግሩን ቀጥሎ "ጌታዬ ይቀመጡና እንሂድ" አለኝ።

ምንም እንኳ ጨለማ ቢሆንም ያቺ ጠንካራ፣ በጣም የምታምርና ከምርጥ ዘር ተመርጣ ለጉዞ የሰለጠነች፣ ራስ ካሣ ለመሰናበቻ የሸለሙኝ በቅሎ አልበረችም። ያቺ ፍጹም ኮሳሳ፣ በጣም አጭርና ደካማ በቅሎ ነች። "ይቺማ የኔ በቅሎ አደለችም" አልኩት። "መቼስ ምን ይደረጋል ጌታው" አለኝ እዝን ብሎ። በጣም ውዷንና ምርጥ ዘሯን በቅሎ፣ ከራስ ካሣ ለጉዞዬ በስጦታ ያገኘኋትን፣ ሌሊት አንዱ ብልጥ በደካማና በሽተኛ በምትመስል በጣም ትንሽ በቅሎ ለውጧታል።

ታዲያ በዚህ ምክንያት ጉዞውን ማሰናከል አልነበረብኝምና በዚያቺው ለራሷ እንኳን ዘመከራ የምትራመድ በምትመስለው በቅሎ ላይ ተቀምጬ ጉዞ ጀመርን። እዛ ከመንጋቱ በፊት በፍጥነት ተጉዘን እነዚያ ፀሐይን ተከትለው ብቅ የሚሉት የሰማይ ላይ የቆርቆር አሞራዎች በአቢአዲ ላይ ማንገርበብ ሳይጀምሩ በፊት ከአቢ አዲ በጣም ርቀን መሄድ ነበረብን። በጭጋግ ተሸፍና በወጉ ብራህናን ባልለገሰቺው ጨለፉ እየተረዳንና በቋጥኞች መሀል እየተሽለኮለክን ወደ ታች ወደ ከተማዋ ወረድን። ከከተማዋ ጫፍ ላይ 50 ታጣቂ ወታደሮችና 80 መጋገዎች ለጉዞ ተዘጋጅተው ይጠብቁን ነበር።

ራስ ካሣ እኔን እንዲያገለግለኝ የሰጡኝና በጦር ሰፈር ሁሌም ከአጠገቤ የማይለየው አንበሳና ታማኙ ኀደኛዬ ልጅ ወልደ ገብርኤል አብረውኝ ለጉዞ ተነስተው ስለ ነበር፣ ጊዜ ሳናጠፋ ገስግሰን ወርደን ዋናው መንገድ ውስጥ ስንገባ ይጠብቁን የነበሩት የራስ ሙሉጌታ 50 ታጣቂ ወታደሮች ከኛ ጋር ተቀላቀሉና የተራራውን ምዕራባዊ ወገብ እየታከክን ቁልቁል ወደ ደቡብ ወረድን። እንዲህ በጠባቧ መንገድ ቁልቁል ስንጓዝ የፈረሶች፣ የበቅሎዎችና የአጋሰሶች የሚተረማመስ ኮቴ የሚያስነሳው አቧራ እያፈነን ቁልቁል መንገዱን ሽክሽክነው።

እንዲህ እኛ እርስ በርሳችን እየተጋፋን እንደናዳ ስንወርድ፣ እኛ ላይ ለመድረስና ወደ ኋላ ላለመቅረት ያለምንም እረፍት ትንፋሻቸውን ውጠው በእግራቸው ለሚሮጡት ወታደሮች አዘንኩላቸው። እናም ፍጥነቱን ትንሽ ገታ አድርጌ ለነዚህ ያለ ምንም እረፍት ለሚሮጡት ወታደሮች ትንሽ ትንፋሽ የመዋጫ ጊዜ

ልሰጣቸው ሰሞከርኩ፣ "ጌታዬ፣ አይዞህ ወደፊት ሂድ። ለኛ አታስብ" የሚሉኝ በሙሉ በተለይ አንዱ ቀደም ብሎ ወደፊት በመምጣት ልክ ከዚያው ከሊታ በትሎዬ ጋር ቁልቁል እየነገደ፣ "ጌታዬ፣ ጌታ አይዞህ በርታ! አሁን ፀሐይ ሳትወጣ በፊት ቦሆዜ ከዚህ ገላጣ መሬት ርቀን መሄድ አለብን። አሰበለዚያ እነዚያ የተረገሙ አውሮፕላኖች ያገኙንና ጉዳችን ነው የሚፈላው። አይዞህ ወደፊት!" እያለ አብሮኝ ያለማቋረጥ ይሮጥ ነበር።

ገና ጎህ ከመቅደዱና ፀሐይ ብርሀናን መፈንጠቅ ከመጀመሯ የነዚያን የተረገሙ የሰማይ ላይ አውሮፕላኖች ድምጽ ከርቀት መስማት ጀመርን። ብዙም ሳይቆዩ በመጥራት ላይ ባለው ሰማይ ላይ ከርቀት የሚታዩ ሶስት ነጠብጣቦች እየቀረቡና ድምጻቸው እየጠነከረ ሲመጣ ያው የተለመዱት ባለሶስት ሞተር ቦምብ ጣዮቹ አውሮፕላኖች መሆናቸውን ተረዳሁ። የነዚህ ርጉም አውሮፕላኖች ኢላማ ዛሬም እንደ ወትሮው ሁሉ የፈረደባት አቢ አዲ ናት።

ብዙም ሳይቆይ ራቅ ብሎ የሚሰማ የቦምብ ፍንዳታ እሩምታ ሰማን። ዚህ ቅጽበት ይህ ነው ብዬ የማልገልጸው ስሜት መላ ሰውነቴን ወረረኝ። ምን ይሆን ልዩነቱ? ማለት የትናንቱ እና የዛሬው? ለጥቂት ጊዜ በቅሎዬን ገታ አድርጌ ለላይ፦ አሁን በአለንበት ኪዳነ ምህረቱ ዛፎች አንዴ ወደኋላ አንዴ ወደፊት፣ ወደ ግራና ወደ ቀኝ ብቻ ንፋሱ እንደነፈሰላቸውና እንዳሻቸው ዘንበል ቀና እያሉ የዕለት ተግባራቸውን ያለመረበሽ ሲያከናውኑ ይታያሉ።

በኪዳነ ምህረቱ ወፎች እንደሁልጊዜው ሁሉ ዝማሬያቸውን እያሰሙ፣ ወዲያ ወዲህ ውር ውር ሲሉ ይታያሉ። ትልልቆቹ ነጭ ምስጦች ሳይቀሩ ለምንም ነገር ደንታ ሳይሰጣቸው በማለዳ ተነስተው በቤት ግንባታ ስራቸው ላይ ተሰማርተዋል። ከዚች ከኪዳነ ምህረቱ በስተሰሜን ትንሽ ራቅ ብሉ ግን ዛፎች፣ ገደሎች፣ ቁጥቋጦዎች፣ ችፍርጎች ሳይቀሩ በየቀኑ በቦምብ ውርጅብኝ ስራቸው አለኪነቀል፣ ዘራቸው እስኪጠፋ ድረስ ፍዳቸውን እያዩ ነው። እዚች ኪዳነ ምህረቱ ሰላም ወርዶ ከዚች ራቅ ብሎ ያለች ምድር ግን በቦምብ እሳት እየነደደች ነው።

የኪዳነ ምህረቱን ቀላማ ቀበሌ አሳምሬ አውቀዋለሁ። ማንንን ባይሆን፣ በኝ እያንዳንዷን ድንጋይ አውቃታለሁ ማለት እችላለሁ። ፀጥር ወር መጀመሪያ ላይ ጦራችን ከአይቦታ ተነስቶ ወደ አቢ አዲ ሲያመራ በኪዳነ ምህረቱ ለተወሰኑ ቀናት ሰፍሮ ነበር። በኪዳነ ምህረቱ በጥንት ጊዜ ከአለት ድንጋይ የተፈለፈለች ወይም የተጠረበች፣ በማማሽ የተፈጥሮ ዋሻ ሃሆነች የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አለች። ቤተ ክርስቲያኗ ሰፋ ሰፋ ያሉ በርካታ ክፍሎች በሳሏት ቀጉን ዘቤተ ክርስቲያኗ ዋሻ አሳልፈን ድንገዘገዝ ሲል ጉዞ ለመጀመር ከባላምባራስ ኪዳነ ማርያም ጋር ተስማማን እኔ መንገድ እየመራኋቸው ወደ ዋሻዋ የሚጠስደውን መንገድ ያዝን ሄድን። ወደ በራፉ ዋሻዋ ከሚያስገባው ትንሽ ቀዳዳ ለመድረስ እስትንፋሳችን ሰጥ ወጥተን ወደ በራፉ

ስንጠጋ! ሊኛር የሚሰማኝን ድምጽ አቆመን። "ቁ...ም ጌ...ታ! ጌ...ታ ጌ...ታ ቁም በሽታ! በ ...ሽ... ታ! በ... ሽ... ታ" እያለ የሚያቃስት ድምጽ ከውስጥ አቁመን። እንነቴን እንዳስገባሁ ለመቃኘት ሞከርኩ። በአብዛኛው በዚያች ቀሻ የተኛው ወታደር ስጋው አልቆ አጽሙ ብቻ የቀረ በግማሽ የሞተ ነው።

በዚያ ቀዝቃዛ ድንጋይ ላይ ያለቻቸውን አሮጌ ሸማ ብቻ ተከናንበው የተኙትን ወታደሮች (አጽሞች) ላይ መላ ሰውነቴን እንቀጠቀጠኝ። እነዚህ ወታደሮች የተለከፉበት በሽታ ተራና በቀላሉ የሚፈወሱት አይነት አይደለም። እነዚህ በሽተኛ ወታደሮች ይፍጠንም ይዘግይም እንጂ ሞት የተፈረደባቸው ምስኪኖች ናቸው። እናም እነዚህ ምስኪኖች በታላቅ ወኔና ትግስት ሞታቸውን የሚጠብቁ በህይወት ያሉ ሬሳዎች ናቸው።

በዚች ቀሻ ከ60 በላይ በሽተኞች ሸማቸውን ተከናንበው ተኝተዋል። አዎ ያለ ሆጥያታቸው ሞት የተፈረደባቸው ምስኪን ወታደሮች ናቸው። አብዛኛዎቹ በሽተኛ ወታደሮች የመጨረሻዋን ቀን በታላቅ ተስፋ የሚጠብቁ ናቸው። እዚህ እነዚህ በሽተኞች ከዚህ ስቃያቸው የሚገላግላቸው ወይም የሚያስታምማቸው ምንም ሰው የላቸውም። ምንም አይነት የህመም ማስታገሻ መድሃኒትም የላቸውም። ብቻቸውን ናቸው። እናም እነዚህ ምስኪን አድለቢሶች በታላቅ ተስፋ የማይቀረውን ሞት ይጠብቁሉ። አዎ ከዚህ አይነቱስ ስቃይ ሞት ታላቅ ነጻነት ነው። ሁሉም በዚች ቀሻ ተኝቶ የአርባ ቀን እድሉን አሜን ብሎ ተቀብሎ፣ ፈጣሪውን ወደቤቱ እንዲጠራው እየለመነና እየጸለየ ህመምና ስቃዩን ችሎ ፀጥ ብሎ ተኝቷል።

ማንም ሰው ወኔ ኖሮት እነዚህን ምስኪኖች ከዚህ ስቃያቸው ሊገላግላቸው አልሞከረም። ወኔ ያለው ሰው ቢገኝ እንኳን እነዚህን ምስኪኖች ምንም ሊረዳቸው አይቻለውም ነበር። ያለ ምህረት ሞት ተፈርዶባቸዋል። እኔም እዚያችው በር ላይ እንደቆምኩ ከያዝኳት አነስተኛ መድሀኒት ቢያንስ ለአንድ ቀን እንኳ ቢሆን ህመማቸውን ሊያስታግስላቸው ቢችል በማለት ቀንሼ ሰጠኋቸውና እግዚአብሔር ምህረቱን እንዲያወርድላቸው ተመኝቼ፣ ያቺን ያልሞቱ ሬሳዎች የታጎሩባትን ቀሻ ለቅቀን ሌላ ቀሻ ፍለጋ ኪዳነ ምህረቱን ማሰስ ጀመርን። ያገኘናቸው ሁሉም ቀሻዎች በበሽተኞች ተሞልተዋል። እናም ሀሳባችንን ቀይረን ያልሞቱ ሬሳዎች የሞሉባትን ኪዳነ ምህረቱን ለቅቀን በጉዟችን ቀጠልን።

ምንም እንኳን የጣልያን ሰላይና ደብዳቢ አውሮፕላኖች ሲበሩ አልፎ አልፎ ቢታዩም በፍጥነት እየተንገዘን በቋጥኞችና ቁጥቋጦዎች መሀል ስንሽሎኮሎክ ውለን ከቀትር በኋላ ቋጥኝ ከበዛበትና በግማሽ ከደረቀ የወንዝ ዳርቻ ደርሰን ጉዟችንን ገታን።

ከአቢ አዲ ለጉዞ ስንነሳ በርካታ እንባሻዎች ገዝቼ ነበርና እንበሳን ጠርቼ "እንበሳዬ እስቲ አንድ እምባሻ አቀብለኝ፣ ለሌሎችም አድላቸው" አልኩት። "እሺ ጌታ" ብሎ እንበሳ እየፈነደቀ ከተቀመጠበት ተወርውሮ ተነስቶ እንባሻ የከተተበትን ከረጢት

ይዞ ወደኛ ሲመጣ ገና ከሩቅ ሳየው ሆዴ የሆነ ነገር ጠረጠረና "እንበሳዬ፣ እንዴው በምንድነው የከተትከው?" ስል ጠየኩት። እንበሳዬ አሁንም ያ ማራኪ ፈገግታው ሳይለየው "በአሮጌ ሱሪዬ ነው ጌታ" አለኝ። "የታባክ፣ አንተ የማትረባ ውሾ ቆሻሻ ሌላም ሌላም የኢትዮጵያውያንን ስድብ አወረድኩበት። የእንበሳን አድራጎት ሳስበው ልጊታው! ላቆመው የማልችለው ሳቅ ይዞኝ ሆዴ እስኪቆስል ድረስ በሳቅ ተንተከተኩ።

እስቲ አሁን ባሳጣው ነገር ስድስት ወር ሙሉ ያሳንዳቸ ቅያሬ ሌት ተቀን ሲንከባለልበት በኖረው፣ የቅማሎች መዓት ሲተረማመሱበትና ሲጨፍሩበት በኖረው እንበሳ አድራጎት ወታደሮቻችንን ደንታ አልሰጣቸውም። እንበሳ አሮጌው ሱሪው ውስጥ እያወጣ የሚያድላቸውን እንባሻ ያለምንም መረበሽ በጥታ ያበሉ። ተመልከት ጌታ፣ እንባሻው እኮ ሽጋ ነው። ቅማሎችም ቢሆኑ እስከዚህ ጋዴ ኖሯቸው ዘልቀው ወደ እንባሻው አይገቡም" እያለ ባላምበራስ እንዱን እንጀራ እየጎረሱ በጣቶቹ መታ መታ ካደረገና እንደማራገፍም ሞክሮ ከነ ላይ ሽረፍ አድርጎ እየበላ እኔም እንድበላ ጋበዘኝ።

ለነገሩ እኔ እንዲህ በቀላሉ የምጸየፍና የማንገራግር ሰው አይደለሁም። ከዚህ በፊት የአረብ አገሮችን ስጎበኝ በአንዲት አነስተኛ መንደር ተጠራሁ የቀረቡልኝን እንግዳ በልቻለሁ። በተለይ ቻይናና ጃፓን በነበርኩበት ጊዜ ከባህር የሚወጡ ምናምንቴዎችን ሳይቀር፣ እስከ መርዛማ እባብ ድረስ፣ ጠባብሰው ያቀረቡልኝን ሁሉ በልቻለሁ። የእንበሳዬ እንባሻ ግን ከሚቻለኝ በላይ ሆነብኝ።

ይህቺን አጋጣሚ በመጠቀም በዚችው በግማሽ በደረቀች ወንዝ ውሃ ትንሽ ጠለቅ የሚል ቦታ ፈልጌ በጣም ንጹህ ውሃ የቋጠረ ቦታ ስላገኘሁ ከብዙ ወራት በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ መላ ሰውነቴን በደንብ ታጠብኩ። የዚች ወንዝ ንጹህና የቋጠረ ውሃ የማይጠገብ ሆኖብኝ ደጋግሜ እየጠለቅሁ ታጠብኩ። ለመጨረሻ ጊዜ እንደነገሩ በችኮላ የታጠብኩት ከዛሬ ሁለት ወር በፊት ጊባ ወንዝ ውስጥ ጠራችን ወር ተቀምጦ ሲገሰግስ ነበር። ከዚያች ቀን ጀምሮ ከሁለት ወር በላይ በለቢ እና እንደም ጫማዎች ቀኑን ሙሉ ያለማቋረጥ በቦምብ ስለሚደበድቡን፣ እንደም ምሽቱን ተገን አድርገው የትግራይ ሽፍቶች ከጠር ሰፈራችን ትንሽ እስክንርቅላቸው እንደተራብ ድብ ስለሚጠብቁን በወጉ ፊታችንን እንኳ ለመታጠብ እድሉ አልነበረንም።

ፀሐይ ከመጥለቋ በፊት እንደገና ለጉዞ ተዘጋጀን። አሁን ጉዟችን በመጠኑም ቢሆን ረጋ ያለ ነበር። ልጅ ወልደ ገብርኤል በፓራስ አደባባይ እንደሚዘዋወር ሁሉ ሄ ልክ እንደ ማንኛውም የባላገር ወታደር ያደፈ ሸማውን ለብሶ በዚያ እኛ ከሄድንበት በቅሎዬ ጎን ይኬዳል።

በመድረቅ ላይ ያለችውን ወንዝ ዳርቻ ይዘን ተጉዘን እንዚያችንን ጨለማው መውረስ ሲጀምር ከሩቅ የውሾች ጩኸት ሰማን። የውሾች ጩኸት ገና ምልክት ነው።

ሁሉም ሰዎች እሱና እኛም ርሀቡም እየጠነከረብን መጥቶ ስለነበር ውሾች በአሉበት ቦታ ሁሉ ሰዎች ለቡና እኛም ርሀቡም እየጠነከረብን መጥቶ ስለነበር ቢሆንስ የሆነ የሚበላ ነገር መግዛት እንኳ ብንችል ብለን አትጣቻችንን የውሾችን ጩኸት ወደ አምንለማዛት አደረግን። ብዙም ሳንጓዝ ከአንዲት መንደር ደረስን። የደሀዘ መንደር ነበረች።

ወደ ደሀክ ቀበሌ ብዙም ሳንጠጋ አንዱን ወታደር ወደ ቀበሌዋ ሄዶ ቢቻል እንጀራና የሚበጣ ነገር፣ አለበለዚያም ዶሮና ጥራጥሬ ገዝቶ እንዲመጣ ላክነው። ወታደሩ ወደ ጨለማው ውስጥ ገብቶ ከመሰወሩ የውሾቹ ጩኸት እየጠነከረ መጣ። ወዲያው አንድ ሻካራ የወንድ ድምጽ "ማነው?" ሲል በትግርኛ ጠየቀ። የኛ ወታደር ትግርኛ አይችልም። የመጣው ከአዲስ አበባ አካባቢ ካለች አንዲት ወረዳ ነው፤ እናም ለሰውዬው በአማርኛ "እንባሻ ወይም ዶሮ መግዛት" እንደሚፈልግ በማስረዳት ላይ እንዳለ ትግሬው አከታትሎ ሁለት ጊዜ ተኮሰበት። ወዲያው የደቡክ መንደር ነዋሪዎች የወታደሩን ድምጽ ወደ ሰሙበት አካባቢ ደጋግመው ይተኩሱ ጀመር።

በምስኪኑ ወታደር ላይ እንዲህ የጥይት ዶፍ ሲወርድበት ወታደሮቻችን ያለምንም ትዕዛዝ መሳሪያቸውን ከትከሻቸው ላይ እያወረዱ ማቀባበል ጀመሩ። በነዚህ መንደርተኞች አሳፋሪ ድርጊት እጅጉን በጣም ተናደው ጨሰዋል። እኔም አልፈርድባቸውም። እነዚህ ምስኪን ወታደሮች ቤት ንብረታቸውን በትነው፣ የነዚህን ምስኪን መንደርተኞችና መሰሎቻቸውን ንብረትና ደህንነት ከጠላት ለመከላከል እዚህ ድረስ መጥተው፣ እነዚህ ውለታ ቢስ መንደርተኞች ግን ተቀብለው በማስተናገድ ፈንታ የጥይት ሰላምታ ያቀርቡላቸዋል? ያለምንም ማስጠንቀቂያ ይተኩሱባቸዋል? በዚህ ሁኔታ በንዴት ራሳቸውን የሳቱት ባላምበራስ ኪዳነ ማሪያም መንደሯን ከበው ለማቃጠል ተነሱ።

ባላምበራስ ለወታደሮቻቸው ትዕዛዝ ከመስጠታቸው በፊት ልጅ ወልደ ገብርኤል ንዴታቸውን አበራርደ፣ እስቲ እኔ ልሞክራቸው፣ አለና መሳሪያውን ጥሎ ባዶ እጁን ወደ መንደሯ አመራ። ብዙም ሳይቆይ የወልዴን ድምጽ ሰማሁ። "አትተኩሱ ወዳጅ ነኝ፤ ወንድማችሁ ነኝ።" አላቸው በትግርኛ። መንደርተኞቹ አንዲት ጥይት ሳይተኩሱ ወልዴን ወደ መንደራቸው ገፍተው እንዲጠጋ ፈቀዱለት። ወልዴ መንደርተኞችን ምን እንዳላቸው ባላውቅም፣ ብዙም ሳይቆይ ተመልሶ መጥቶ ወደ መንደሯ እንድንሄድ ጋበዘን። እኔ በልጅ ወልደ ገብርኤል ሙሉ በሙሉ ስለምተማመን ምንም ሳላንገራገር ተከተልኩት። ብዙው ወታደር ግን ተንኮል ሳይሆን አይቀርም ብሎ በመጠርጠር ጠመንጃቸውን እንዳቀባበሉ ከኋላዬ ተከተሉኝ።

በመንደሯ የመንደሯ ሹምና ሌሎች አዛውንቶች ቆመው ይጠብቁን ነበር። ካጠገባቸው ስንደርስ ልክ እንደ ጥንት ወዳጃቸው አቅፈው ስመው ተቀበሉን። "ዋይ ዋይ ፈረንጅ ጌታ፣ አሁን ይኼ እግዚአብሔር ምን በድለነው ነው እንዲህ አይነቱን ጊዜ ጥሎብን የሚቀጣን? ፈረንጅ ጌታ፣ የተበላሸ ጊዜ፣ የተረገመ ጊዜ፣ ለኛም፣

ለጠላታችሁም ሀገር የማይበጅ ጊዜኮ ነው ጌታ ፈረንጅ፣ ወዳጅ ከጠላት ተለይቶ የማይታወቅበት ጊዜ፣ ርጉም ጊዜ፣ ክፉ ጊዜ" የመንደሯ ሹም ብዙ ብዙ አማርረው ተናገሩ።

"ለምን በኛ ወታደር ላይ ተኮሳችሁ?" ብዬ ሹሙን ስጠይቃቸው፣ ልጅ ወልደ ተረጎመላቸውና ሽማግሌው ሹም "ዋይ ዋይ፣ ዋይ ዋይ ፈረንጅ ጌታ፣ ልጅ ወልዴ ለለብን። ታዘናል ፈረንጅ ጌታ" አሉ። "ማነው ያዘዛችሁ?" ብዬ የሽማግሌውን ምሬት የተሞላ ንግግር አቋረጥኩት። "ጣልያኖች ጌታ፣ ጣልያኖች ናቸው ያዘዙን ፈረንጅ ጌታ" አሉ ሽማግሌው አሁንም በምሬት።

ሽማግሌው ሹም የምሬት ንግግራቸውን በመቀጠል ጣልያኖች እንዳዟቸውና በመንደራቸው አጠገብ የኢትዮጵያ ወታደር ሲያልፍ መተኮስና ወደ መንደር ዘልቆ ገብቶ እህል ውሃ እንዳይቀምስ ማድረግ እንዳለባቸው መታዘዛቸውን፣ ይህን ሳያደርጉ ቢቀሩና ከመንደሯ አንዱ ሰው እንኳን አንዲት እንክላ ውሃ ለኢትዮጵያ ወታደር ሰጥቶ ቢገኝ የጣልያን አውሮፕላኖች በማለዳ መጥተው መንደራቸውን አፈር ድሜ እንደሚያበሏት እንዳስጠነቀቋቸውና፣ ሌላም ሌላም በምሬት ተናገሩ። ቀጥለውም "እንግዲህ ፈረንጅ ጌታ፣ ምን እናድርግ? ጣልያኖች እንደሆን ያለምንም ርህራሄ በአውሮፕላናቸው መጥተው ሴቶቻችንና ልጆቻችንን ይገድላሉ" አሉ። ሽማግሌው ሹም እንዲህ እያማረሩ፣ መላው ጠፍቷቸው እንደተቸገሩ እየገለጹ፣ ተጉዘን ከመንደሯ መሀል ደረስንና ሹሙ ከአንዲት አነስተኛ ጣሪያዋ ሳር የለበሰ ጎጆ ደጃፍ ላይ ቆመው ወደ ውስጥ እንድንገባ ጋበዙን።

የመንደሯ ሹም ጎጆ ሰፋ ብላ ከእንጨትና ከጭቃ ከመሰራቷና ጣሪያዋ በየፍ ሁኔታ በሳር ከመሸፈኑ ውጪ፣ መስታወት የሌላቸው መስኮት ቢጤ አነስተኛ ቀዳዳዎች አሏት። ደብረ ታቦርን ለቅቄ ከወጣሁ በኋላ ጣሪያና ግድግዳ ባለው ቤት ውስጥ ገብቼ ስቀመጥ የመጀመሪያ ጊዜ ነው። ወደ ውስጥ እንደገባን ከፍ ብሎ ከተሰራ መደብ ላይ ሳር ተጎዝጉዞ ከአጠገባቸው እንድቀመጥ ጋበዙኝ። ሹሙ አሁን ለኔ የማይገባኝ ነገር ለራሳቸው የሚያወሩ በሚመስል ድምጽ እያልጎምጎሙ ሸማቸውን ሲፈታትሹ ቆይተው ፊታቸው በሀዘን እንደጠቆረ፣ አንዲት የተጨማደደች ወረቀት አውጥተው ሰጡኝ።

"ተመልከት ፈረንጅ ጌታ! ጣልያኖች እንግዲህ እንዲህ አይነት ወረቀት ነው በጣሪያችን ላይ የሚበትኑት" አሉኝ። ወረቀቷን ዘረጋጋሁና አየኋት። በትግርኛ ቋንቋ የተጻፈች ስለነበረች ለልጅ ወልደ ገብርኤል እንዲተረጉምልኝ ሰጠሁት። ጣልያኖች በትግራይ መንደሮች ከበተኗቸው ወረቀቶች የአንዷ ወረቀት ሙሉ ይዘት ይኼን ይመስል ነበር።

ለትግራይ ህዝብ!

በሀገራችሁ ሰላም አስፍነን ስልጣኔና ብልጽግናን እንድናሰፍን እግዚአብሔር ልኮናል። ይሁን እንጂ የአማራና የኦሮሞ ጨቋኞች፣ ቀማኛና ሰው በላ ወታደሮቻቸውን አስልፈውብን ይኼንን የተቀደሰና ከእግዚአብሔር የተሰጠንን ተልኮ እንዳንፈጽም እያወኩን ነው።

የተከበርክ የትግራይ ህዝብ ሆይ፣ እነዚህን የአማራና የኦሮሞ ቀማኛ ሽፍቶች በመንደርህ ሲዘዋወሩ ብታገኝ እህል ውሃ ሳታቀምስ፣ ጥይትህን እየተኮስክ እንደውሻ ከመንደርህ እንድታባርራቸው እናሳስብሀለን።

እነዚህ የአማራ ሽፍቶች ወደ መንደራችሁ ተጠግተው የሚበላም ሆነ የሚጠጣ ነገር ሲገዙ ቢቀርቡ አብርሯቸው። አዝናችሁ ምንም ነገር፣ ምንም አይነት ርዳታ እንዳታደርጉላቸው አጥብቀን እናሳስባለን። ከማሃላችሁ ይኼን ትዕዛዛችንን ተላልፎ አንድ ሰው እንኳ ለአማራ የሽፍታ ወታደር አንዲት እንባሻ ሲልግስ ወይም ሲሸጥ ቢገኝ፣ ምህረት የሌለው ቅጣታችን በሁላችሁም ላይ ይደርሳል።

በማሃላችሁ የራሳችን ሰዎች ስላሉን ጨለማን ተገን አድርጋችሁ ትዕዛዛችንን ተላልፋችሁ ብትገኙ፣ ጎህ ሲቀድ አውሮፕላኖቻችን መጥተው መንደራችሁን ዶጋ አመድ ያደርጓታል ወዘተርፈ።

አሁን ገባኝ፣ ለምን የትግራይ ሰዎች አነስተኛ የኢትዮጵያ ወታደሮች በመንደሮቻቸው አካባቢ ሲያገኙ ተኩስ እንደሚከፍቱባቸው። አሁን ገባኝ፣ ለምን የአዲ ዳሮ መንደር ሰዎች ምንም ነገር ሊሸጡልን ፍቃደኛ እንዳልነበሩና በቶሎ መንደራቸውን ለቀቀን ካልሄድን ተኩስ እንደሚከፍቱብን የዛቱብን። አሁን ገባኝ አቢቹ፣ የትግራይ ሽፍቶች የትግራይ መንደሮችን ከለላ አድርገው በጠሩ ላይ አደጋ ሲጥሉና ወታደሮቹን ሲገሉበት፣ ያለ ምንም ምህረት መንደር የምታቃጥልበት ምክንያት። አሁን ገባኝ ባላምበራስ ኪዳነ ማሪያም ይቺን መንደር ከብበው ለማቃጠል የተነሱበት ምክንያት።

ፋሺስቶች በጣም አደገኛ የፕሮፓጋንዳ መሳሪያ ፈጥረዋል። ፋሺስቶች የትግራይ ቀበሌ ባላገሮችን እያስፈራሩና በዛቻ እያስገደዱ የገዛ ወንድሞቻቸውን እንዲገድሉ እያደረጓቸው ነው። ምስኪን የትግራይ ገበሬዎች! መላው በጠፋ ሁኔታ ላይ ናቸው።

የጣልያኖችን ዛቻ ፈርተው ትዕዛዛቸውን ቢፈጽሙ፣ የኢትዮጵያ ወታደሮች በታላቅ ንዴት መሳሪያቸውን አዙረው ጠቅላላ መንደሯን አመድ ያደርጓታል። የጣልያኖችን ዛቻ ወደ ጎን ትተው፣ ትዕዛዛቸውን ጥሰው የሀገራቸውን ድንበር ለመከላከል ከመሀል ሀገር ድረስ የመጡትን የገዛ ወንድሞቻቸውን ረድተው ቢገኙ፣

እንዚያ የተረገሙ የሰማይ ላይ የቆርቆሮ አሞራዎች መጥተው መንደራቸውን በቦምብ ያንዷታል።

ኋላ ላይ ራሴ በዓይኔ በብረቱ እንዳየሁት፣ ጣልያኖች ከወታደራዊ ስልት አንፃር ምንም አይነት አደጋም ይሁን ጥቅም የሌላቸውን ተራ መንደሮች ያለ አንዳች ምክንያት በአውሮፕላኖቻቸው ከማለዳ ጀምረው ጀንበር እስከመጥለቂያ ጊዜ ያለ ምንም እረፍት እየዞሩ፣ የመጨረሻዋ ድንጋይ በቦምብ ተወቅራ አመድ እስክትሆን ድረስ ለሌሎች መቀጣጫ እንዲሆን ደብድበዋል።

በተመሳሳይ የፕሮፓጋንዳ ወረቀቶች በኋላ ላይ በመላው ኢትዮጵያ በአውሮፕላኖቻቸው በትነዋል። ጣልያኖች እንዲህ ሌት ተቀን በፕሮፓጋንዳቸው ገፍተውበት ከሚበትኗቸው ወረቀቶች ጋር አብረው የፋሺስቱ የሞሶሎኒ መንግሥት አርማ ያለበትን የጣልያን ባንዲራ ጨምረው ይበትኑ ስለነበር፣ በትግራይ ቀበሌዎች ብቻ ሳይሆን በሌሎችም የኢትዮጵያ ግዛቶች ገበሬው በጎጆው ጣሪያ ጫፍ ላይ ሰቅሎ ሲውለበለብ አይቻለሁ።

ለዚህም መሰለኝ ብዙ ጊዜ በመንደሮች መሀል ስናልፍ የፋሺስቱ አርማ ያለበት የጣልያን ባንዲራ በጎጇቸው ጣሪያ ላይ እየተውለበለበ፣ የመንደሩ ሰዎች ግን እኛን በታላቅ ደስታና ወንድማዊነት በተሞላበት ሁኔታ ተቀብለው ሲያስተናግዱን የነበረው።



28

ከሽፍቶች ጋር ግብ ግብ

ከአምስት ወር አስቸጋሪ ህይወት በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ጣሪያና ግድግዳ ባለው የሹሙ ጎጆ ቤት ውስጥ መደብ ላይ ሳር ተጎዝጉዞልኝ ለ4 ሰዓት ያህል ወገቤን አሳረፍኩ። አራት ሰዓት ገደማ እንደሬሳ ከተጋደምኩበት መደብ ላይ ልጅ ወልደ ገብርኤል ቀሰቀሰኝና ለቀጣዩ ጉዟችን ተነሳን። ሁላችንም ጊዜ ሳናባክን ባፋጣኝ ተነስተን በተቻለ ፍጥነት እየተጓዝን አምባ አርአዶም ከራስ ሙሉጌታ የጦር ሰፈር መድረስ አለብን። እንግዲህ ከራስ ሙሉጌታ የጦር ሰፈር ለመድረስ ቢቀረን የሁለት ቀን መንገድ ብቻ ነው።

በዛሬው የሌሊት መንገዳችን በአፋጣኝ ከፊታችን የተዘረጋውን ገላጣውንና ሜዳማውን መንገድ ተጉዘን ጊባ ወንዝ መድረስ አለብን። ጊባ ወንዝ ከደረስን፣ የጊባ ወንዝ ዳርቻ ጥቅጥቅ ባለ ጫካ የተሸፈነች ስለሆነች ከነዚያ መዘዘኛ አውሮፕላኖች አይን በቀላሉ መሰወር እንችላለን።

ሲነጋጋ አካባቢ ከወንዟ ዳርቻ ደረስን። ከዚያ ወደ ወንዟ ዘልቀን በመግባት

የወንዟ ውሃ ጉልበታችንን እየነካ ያንኑ ዳርቻ ይዘን በጉዟችን ገፋን። በዚህ ሁኔታ ስንጓዝ ውለን እነዚያ መከረኛ አውሮፕላኖች ድምጻቸው ከሩቅ ሲሰማን፣ ከወንዟ ወጥተን ጫካ ውስጥ እየተደበቅን፣ እነሱ ሲሄዱ መልሰን ወደ ወንዟ እየገባን ስንበጣረቅ ውለን፣ ከቀትር በኋላ መስመራችንን ለውጠን ከወንዟ ወጥተን በቋጥኞች መሀል መንገዳችንን ሽቅብ ወደኮረብታው አድርገን ስንጓዝ ጀንበር ጠለቀች።

በነጋታው ማለዳ በመንገዳችን ላይ ተበታትነው ወደአቢ አዲ የሚሄዱ፣ በሁኔታቸው እጅጉን በጣም መሰላቸታቸውና መድከማቸው የሚታወቅባቸው የኢትዮጵያ ወታደሮች አገኘን። እነዚህ ወታደሮች በአብዛኛው የሸዋ ኦሮሞዎች ናቸው። ባላምበራስ ኪዳነ ማሪያም ከነዚህ የሸዋ ኦሮሞዎች ጋር ረዘም ላለ ጊዜ ሲወያዩ ቆዩ። ምንም እንኳን ስለምን እንደሚያወጉ ባላውቅም ከሁኔታቸው እነዚህ ወታደሮች እጅጉን በጣም የተበሳጩና ያዘኑ ይመስላሉ።

"ምን ተፈጠረ ባላምበራስ?" ስል ስለሁኔታው ጠየኳቸው። "ምን አልክ ጌታ? ምንም ጌታ" አሉኝ ባላምበራስ ያለወትሯቸው ቃላቶቻቸውን ቆጥበው። አሁን የሆነ ነገር እንደተፈጠረ ስለጠረጠርኩ ባላምበራስን ወጥሬ ያዝኳቸው። ባላምበራስም ሲያንገራግሩ ቆይተው "እነዚህ ወታደሮች የሚሉት" አሉና ንግግራቸውን ገታ አድርገው ትንሽ አሰብ ካደረጉ በኋላ እንደገና ወደኔ መለስ ብለው "እየህ ጌታ፣ እነዚህ ወታደሮች የሚሉት የራስ ሙሉጌታ ጦር በአምባራዶም በጣልያኖች ተከቧል ነው። እንዲያውም ጣልያኖች ገፍተው መጥተው ገረገራን ይዘዋል። በዛልቃባም ሜዳ ላይ ከፍተኛ ውጊያ እየተካሄደ ነው። ደጃዝማች ወልደ ማሪያምና ደጃዝማች አውራሪስም የጣልያኖችን ኃይል ስላልቻሉት ከምሽግ ወጥተው ወደኋላ ተመልሰዋል። ወደ ራስ ሙሉጌታ የጦር ሰፈር የሚወስዱት ሁሉም መንገዶች በጣልያኖች ታጥረው ተይዘዋል። እናም ዘልቀን ወደ ደሴ መሄድ የምንፈልግ ከሆነ ትንሽ ወደቀኝ ታጥፈን ጣልያኖችን ወደግራ ትተን በአፋጣኝ ማለፍ አለባችሁ ነው። ወደ ራስ ሙሉጌታ መሄዱ ራስን በራስ እንደ መግደል ነው፣ ነው የሚሉት ጌታ" አሉኝ ባላምበራስ።

ከነዚህ የሸዋ ኦሮሞ የኢትዮጵያ ወታደሮች ተሰነባብተን ከተለያየን ጥቂት ጊዜ በኋላ ሌሎች ወታደሮች ልክ እንደፊተኞቹ ተበታትነው ሲጓዙ አገኘናቸው። እነዚህ ግን ሸዌዎች አልነበሩም። እኒህኞቹ ደግሞ የራስ ሙሉጌታ ጦር ጣልያኖችን ገጥሞ ከገረገራ አባሮ አሁን መቀሌን ለመያዝ ከፍተኛ ውጊያ ላይ መሆኑን አስረዱን። ማንን እንመን?

ልጅ ወልደ ገብርኤል የትግራይ ልጅ እንደመሆኑ መጠን የአካባቢውን ወግና ባህል፣ የህዝቡንም አስተሳሰብ ጠንቅቆ ከሁላችንም በላይ ያውቀዋል። አሁን ከሁለቱም ወገን እንደሰማነው እውነት ነገር ቢኖር በዚህ ሰዓት በአምባራዶም ከፍተኛ የሞት ሽረት ውጊያ እየተካሄደ ነው። እኛ አሁን በአለንበት ሁኔታ የኢትዮጵያ ወታደሮች የተ እንዳሉና ጣልያኖች በየትኛው አቅጣጫ እንኳ እንደመሸጉ ምንም የምናውቀው ነገር

ከጣልያኖች እጅ ሊጥለን ይችላል:: እናም የለም:: ይኼም አላዋቂነታችን በቀላሉ ከጣልያኖች እጅ ሊጥለን ይችላል:: እናም ልጅ ወልደ ገብርኤል ጊዜ ሳናጠፋ ወደ አቢ አዲ ተመልሰን ከራስ ካሣ ጦር ጋር እንቀላቀል ሲል፣ ራስ ካሣ መንገድ እንዲመሩን የሰጡን ሽማግሌው ሹም ባህሩ ደግሞ የራስ ሙሉጌታ ጦር ተከቦ እንኳን ቢሆን ማንም የማያውቃት ምስጢራዊ መንገድ ስለማውቅ ወደ ራስ ሙሉጌታ ያለ ችግር አደርሳችኋለሁ ብለው ይምሉ ይገዘቱ ጀመር::

"አይዞህ ጌታ አታስብ! ሹም ባህሩ ያለ ምንም ችግር ከራስ ሙሉጌታ ዘንድ ያደርሰናል:: ጌታ ሙት! እንዲያው በጣልያኖች መሀል እንኳ መሄድ ቢኖርብን ይኼ ሹም ባህሩ ሽማግሌ መሆኑን አትይ፤ ብልህና ትልቅ ሽማግሌ ነው፤ አይዞህ እንዲህ ብለህ እንዳታስብ፣ ከራስ ሙሉጌታ ዘንድ ያደርሰናል" እያሉ ባላምበራስ ወትውቱ:: የባላምበራስ ያሁኑ ውትወታ መማጸንም የተላበሰ ይመስል ነበር::

ባላምበራስ ኪዳነ ማሪያም ወደ ራስ ካሣ የጦር ሰፈር አቢ አዲ ላለመመለስ አጥብቀው የሚከራከሩበት አንድ የግላቸው ምክንያት ነበራቸው:: ምናልባት እንዲህ በጊዜ ወደ ራስ ካሣ ጦር ሰፈር ብንመለስ የራስ ካሣ የጦር ሹማምንቶች "ጣልያንን ፈርቶ ተመለሰ" ብለው እንዲያላግጡባቸው ፈጽሞ አልፈለጉም::

ከባላምበራስ ኪዳነ ማሪያም ውትወታ በኋላ ትልቁ፣ ታላቁ ሽማግሌ በንግግራቸው በመቀጠል፣ "አንዴ ቃል ገብቻለሁ፤ ለራስ ካሣ ጎምላዎቹን ወታደሮችና አንተንም ፈረንጅ ጌታ፣ ከራስ ሙሉጌታ ዘንድ መንገድ መርቼ ላደርስ ቃሌን ሰጥቻለሁ:: የገባሁትን፣ የሰጠሁትን ቃሌንም እጠብቃለሁ::" ትልቁ ሽማግሌ ምንም እንኳ ብዙም ጉዳዩ ብለን ባንሰማቸውም አንድ አንጀቴን የበላችኝ ቃል ተናገሩ:: "እንዲያው ብቻዬን እንኳ ከመላው የጣልያን ሰራዊት ጋር መዋጋት ቢኖርብኝ እዋጋለሁ፤ እሞታለሁ እንጂ ለካሣ የገባኋትን ቃሌን አልሽርም:: ካሣ ይሙት!" እያሉ ለብቻቸው ይምላሉ፤ ይገዘታሉ::

የኚህ ሽማግሌ (ሹም ባህሩ ሲባሉ የሰላዋ መንደር ሹም ናቸው) ምንም እንኳን የታጠቁት መሳሪያ ነገር ቢኖር አንዲት መጥረቢያ ብቻ ብትሆንም፣ እንዲህ ፍጹም በራስ መተማመንና የገቡትን ቃል ለመፈጸም ያላቸው ጽኑ እምነትና አቋም አንጀቴን በላው:: በዚህ መልኩ እያለን አልፎ አልፎ የምናገኛቸው የደከሙና ተበትነው ወደ አቢ አዲ የሚጓዙ ወታደሮች ልክ እንደሸዋዎቹ የሜጫ ኦሮሞዎች ሁሉ የራስ ሙሉጌታ ጦር በጣልያኖች መከበቡንና ወደዚያ ማምራቱ አደገኛ መሆኑን ደጋግመው ቢያስጠነቅቁንም፣ በመጨረሻ ወደፊት ለመሄድ ወሰንንና ለቀጣዩ መንገድ ተነሳን::

በትልቁ ሽማግሌ ሹም ባህሩ ምክር ዋናውን መንገድ ለቅቀን ወደ ተጎራባቹ ኮረብታማና ቁጥቋጦ የበዛበት መንገድ ገባን:: ከኮረብታዋ አናት ላይ እንደወጣን እታች በዳለቻ ድንኳኖች የተጥለቀለቀችውን የጣልያኖችን የጦር ሰፈር በትክክል ማየት ቻልን:: ከዚቺው ኮረብታ ላይ ሆነን የአምባራዶም መንገድ በትክክል መቋረጧን

ተረዳን:: ከርቀት የመድፎች ጥይት ድምጽ ሲያጓራ ይሰማል:: በአምባራዶም ትልቅ የጦርነት እሳት እየነደደ ነው:: አሁን በቆምንባት ኮረብታ ዙሪያ ተዓምራዊ ሰላም ሰፍኗል::

ይኼ ተዓምራዊ ሰላም ለጥቂት ጊዜም ቢሆን በጦር ሜዳ መሆናችንን አዘናጋን:: ለጊዜው በዚች ኮረብታ ላይ ምንም የሚያሰጋ ነገር እንደሌለ አድርገን ቆጠርን:: ከኮረብተዋ ተነስተን ወደ ተራራው ስንወጣ፣ አሁንም ዋናውን መንገድ ለቅቀን በስተቀኛችን መጓዝ ጀመርን:: ልጅ ወልደ ገብርኤል እስካሁን ወደ አቢ አዲ እንመለስ ባይና የዚህ መንገዳችን አጥብቆ ተቃዋሚ ቢሆንም አሁንም ከጎኔ አብሮኝ እየሄደ ነው::

ከአንድ ሰዓት ጉዞ በኋላ አሁን በትክክል የመድፎችና አልፎ አልፎ የሚንጣጡ መትረየሶች ድምጽ ይሰማን ጀመር:: አውሮፕላኖች አሁንም አሁንም እየመጡ ዞረውን ተመልሰው ወደ መጡበት አቅጣጫ ይበራሉ:: የአውሮፕላኖቹ አብራሪዎች ሊያዩን አይችሉም:: ገና የአውሮፕላኖቹን የርቀት ድምጽ ስንሰማ በጊዜ ዋናውን መንገድ ለቅቀን በየቁጥቋጦውና ቋጥኙ ስር እንደበቃለን:: ከዚያ አውሮፕላኖቹ ጎብኝተውን ሲመለሱ ከየመሸግንበት ወጥተን ስንጓዝ፣ ሲመጡብን ስንደበቅ፣ ሲሄዱልን ወጥተን በጉዟችን ስንገፋ ከተራራው ወገብ ላይ ደረስን::

አሁን በጠባቧና በገላጣዋ መንገድ የግድ መሄድ አለብን:: በዚህ መልኩ በጠባቧና በገላጣማዋ መንገድ ስንጓዝ፣ ከመንገዷ በስተቀኝና በስተግራ በኩል ካሉ አጫጭርና ጥቅጥቅ ካሉ ቁጥቋጦዎች ውስጥ ነጭ ሽማ የለበሱ ታጣቂ ባላገሮች ብቅ ብቅ ማለት ጀመሩ:: እነዚህ ታጣቂ ባላገሮች ትግሬዎች ናቸው:: ሁሉም ታጥቀዋል:: እነዚህ ታጣቂዎች ደረጃ በደረጃ ከየቁጥቋጦው ውስጥ እየወጡ ወደኛ መቅረብ ጀመሩ:: ወደፊት እንዳንሄድም መንገድ ዘጉብን ማለት ይቻላል:: ይሁን እንጂ በአንዳቸውም ላይ የጠላትነት አይነት ስሜት አይነበብም::

"በሥዩም አምላክ! ወዴት እየሄዳችሁ ነው?" አለ የአንድ ወጣት የነዚህ ባላገሮች ሹም ድምጽ:: "በካሣ አምላክ! ወደ ራስ ሙሉጌታ እየሄድን ነው" ሲል ልጅ ወልደ ገብርኤል መለሰለት:: አሁን ልጅ ወልደ ገብርኤል ወደ ወጣቱ ሹም ገፃ ባለ እርምጃ እየተራመደ ሄዶ በራስ ካሣና በራስ ሥዩም የተፈረመ የይለፍ ደብዳቤ ወረቀታችንን አሳየው::

ይኼ ወጣትና የተማረ ሹም ኮስተር ለማለት ሞከረ፤ ግን ከመካከላችን ይኼ ወጣት የተማረ ሹም ከጀርባው ስውርና አደገኛ ጨዋታ እየተጫወተ እንደነበረ የገመተም፣ የጠረጠረም አልነበረም:: ይኼ ወጣት ሹምና ተከታዮቹ የከዳተኛው፣ የባንዳው የደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ተከታዮችና አገራቸውን ከድተው ከጣልያኖች ጋር አብረው የገዛ ወንድሞቻቸውን እየወጉ በገዛ አገራቸው ላይ የዘመቱ ሆዳሞች፣ ወራዶች ናቸው የሚል ጥርጣሬ የነበረው አንድም ሰው አልነበረም::

የደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ወታደሮች እንደ ጣልያን ወታደሮች መለዮ አይለብሱም። ሁሉም እንደ ማንኛውም የኢትዮጵያ የባላገር ወታደር ሁሉ የሚለብሱት ያደፈ ሸማ ነው። እናም ያለ ችግር ቢያሻቸው የትግራይ መንደር ሰላማዊ ነዋሪዎች እንደሆኑ፣ ቢያሻቸው ደግሞ የራስ ሥዩም ወታደሮች መሆናቸውን ገልጸው መዋሸት፣ ማታለልና ያለ ችግር መንቀሳቀስ ይቻላቸዋል።

ወጣቱ ሹም የመሸኛውን ደብዳቤ ወረቀት በቅጡ እንኳ ሳያይ መልሶ ለልጅ ወልደ ገብርኤል እየሰጠ የመሸኛው ደብዳቤ ትክክል እንዳልሆነና ከራስ ሥዩም በደረሰው ጥብቅ ትዕዛዝ መሰረት ያለ ፈቃድ ማንም ወታደር ከጦር ግንባር ተመልሶ በዚች መንገድ ማለፍ እንደማይችል ካስረዳው በኋላ፣ አሁን በቀጥታ ወደኔ እያየ፤ "አንተና ፈረንጁ መሄድ ትችላላችሁ፤ የቀሩት ነምሳዎቹ ታጣቂ ወታደሮች ግን ትጥቃቸውን ፈትተው ከኔ ጋር መሄድ አለባቸው" አለው።

ልጅ ወልደ ገብርኤል ያለማቋረጥ ከወጣቱ ሹም ጋር ይከራከራል። ሊያግባባውም ይሞክራል። በዚህ መሀል እኔና ነምሳዎቹ ወታደሮቻችን በዝግታ በመንገዳችን ቀጠልን። እንዲህ በዝግታ እየሄድን ወደ አዲዳሮ ቀበሌ ተቃረብን።

የኛ ታጣቂዎች ነምሳ ብቻ ናቸው። በዙሪያችን ግን ከሶስት እጥፍ በላይ በሚሆኑ ሽፍቶች ተከበናል። የኛም ወታደሮች የራሳቸው የሆነ መለዮ የሌላቸው፣ እንደ ሽፍቶቹ ሁሉ ያደፈ ሸማ የለበሱ ስለነበር በቀላሉ ተቀላቀሉ። አሁን ማን ወታደር ይሁን ማን ሽፍታ፣ እርስ በርሳቸው አይተዋወቁም።

ይገርማል ከየት ይሆን ይኼ ሁሉ ታጣቂ የመጣው እያልኩ ስገረም፣ አሁንም አሁንም ከየቁጥቋጦው ታጣቂዎች እየወጡ ጠባቧን መንገድሞሏት። ማንም ሊያቆመን ስላልሞከረ አሁንም በዝግተኛው መንገዳችን ቀጥለናል። እንዲህ በዝግታ ወደፊት እየሄድን አሁን በመድረቅ ላይ ካለች አንዲት ትንሽ ወንዝ ዳር ደረስን። ሁሉም ወታደር ተጠምቶ ስለነበር በደረቀችው ወንዝ ውስጥ እየሄደ ትንሽ ውሃ የቋጠረች ጉድጓድ ፍለጋ በያቅጣጫው ተበተነ። እኔም ትንሽ እንደሄድኩ አንዲት ትንሽ ውሃ የቋጠረች ቦታ ስላገኘሁ በኮዳዬ ልሞላ ጎንበስ ስል አንድ የታፈነ፤ እንደመጮህ የሚያደርገው ድምጽ የሰማሁ መሰለኝ። ለቅጽበት የሰማሁት ድምጽ የልጅ ወልደ ገብርኤል መሰለኝ። ቀና ብዬ ሳይ ልጅ ወልደ ገብርኤል አሁንም ከዚያ ወጣት ሹም ጋር እየተሟገተ ነው። ኋላ ላይ ልጅ ወልደ ገብርኤል እንዳጫወተኝ ያን የታፈነ ጩኸት ያሰማው ራሱ ነበር። ልጅ ወልደ ገብርኤል ድምጹን ከፍ አድርጎ ማውራት ሲጀምር ወጣቱ ሹም አፉን በእጁ እንዳፈነው ነገረኝ።

ይኼ ወጣት ሹም ሆን ብሎ ወልዴን ከኛ ለይቶ አስቀርቶ የኛ ወታደሮች በደረቀችው ወንዝ ዳርቻ እንደተበተኑ አንድ በአንድ በጥይት ሊለቅሙን አስበዋል። ልጅ ወልደ ገብርኤል የትግራይ ልጅ በመሆኑ ብቻ ከዚህ ጭፍጨፋ ሊያድኑትም ወስነዋል።

የደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሳን ሰዎች መሰሪ አላማ በትክክል የተረዳው ልጅ ወልደ ገብርኤል ከወጣቱ ሹም ጋር የተያያዘውን ሙግት በተቻለው አቅም ሁሉ እያራዘመ፣ ለኛ ትንሽ ጊዜ ለመግዛት፣ እድል ለመስጠት እየሞከረ ነው። ያንን የታፈነ ጩኸት መሳይ ድምጽ እንደሰማሁ ቀና ብዬ ልጅ ወልዴን ምን እንደተፈጠረ ድምጼን ከፍ አድርጌ ጠየኩት።

ልጅ ወልደ ገብርኤል "በጉዟችን መቀጠል አለብን" ሲል ልክ ምንም ነገር እንዳልተፈጠረ ሁሉ ፍጹም ተረጋግቶ መሰለኝ። ልጅ ወልደ ገብርኤል የሆነ ነገር ሊጠቁመን ቢሞክር ኖሮ ሽፍቶቹ ያለ ምንም ምህረት በጥይት እንደሚቆሉን አውቋል፤ እናም ፍጹም ራሱን አረጋግቶ ልክ ለኛ ደንታ እንደሌለው ሰው ለመሆን እየሞከረ በሙግቱ ገፋበት።

ሽፍቶቹ ከአምስት እጥፍ በላይ ሆነዋል። ከሁሉም በላይ ደግሞ ባጭር ርቀት ከበውን በእርጋታ ውሃ እንደሚጠጣ ከብት ይጠብቁናል፤ ሲያርዱን። በድንገት ትንሽ ነገር ቢፈጠር ከኛ መሀከል ለወሬ ነጋሪ የሚቀር አንድም ሰው አይኖርም።

ኋላ ላይ እንደ ሰማሁት ልጅ ወልደ ገብርኤል ልክ ከትግሬዎች ጋር እንደተሻረከና እኛን አሳልፎ እንደሸጠን መስሎ ወጣቱን ሹም አግባብቶ፤ ወታደሮቹ ወጣቱም ሹም የኛ ታጣቂዎች የትም የማይደርሱ ለእርድ የቀረቡ፣ የታሰሩ ወይም በበረት የገቡ ከብቶች አይነት አድርጎ ቆጥሮን በልጅ ወልደ ገብርኤል ሽምግልና ይስማማል።

ልጅ ወልደ ገብርኤል ወጣቱን ሹም እንዲህ መሰሪ ተግባራቸውን በሌላ ቦታ እንዲፈጽሙ ሲያስማማው፣ እንደምንም ብሎ እኔን የሚያስጠነቅቅበት ጊዜና አጋጣሚ ሊያገኝ እንደሚችል አምኗል። ይሁን እንጂ ልጅ ወልደ ገብርኤል እንዲህ ፍጹም ተረጋግቶ "በመንገዳችን መቀጠል አለብን" ብሎ ሲለኝ ከመጀመሪያው ጊዜ ጀምሮ ስጠረጥረው የነበረውን ነገር የበለጠ እንዳምንበት አደረገኝ። ሽፍቶቹ ቀስ እያሉ በዑድን በቡድን እየሆኑ ከኛ ፈንጠር እያሉ ለመሄድና ጥሩ መከታ ቦታዎችን ለመያዝ ሲሞክሩ ከአየሁበት ጊዜ ጀምሮ ጥርጣሬ ገብቶኝ ነበር። አሁን ልጅ ወልደ ገብርኤል አረጋገጠልኝ።

"ወደፊት!" ብዬ ለወታደሮቻችን ትዕዛዝ ሰጠሁ። በዚህ ጊዜ ባላምበራስ ኪዳነ ማሪያም ፈጠን ብለው ወደኔ ተጠግተው፣ ለራሳቸው እንኳ በቅጡ በማይሰማ ድምጽ ኮስተር ብለው "ተጠንቀቅ ጌታ፣ እነዚህን ትግሬዎች። እኔ የነሱ ሸር መች ጠፍቶኝ ጌታ። የሆነ መሰሪ ነገር አስበዋል" አሉኝ። ባላምበራስ ኪዳነ ማሪያም ምናልባት ተኩስ ቢከፈት እንኳ በገዛ ሰውነታቸው ከጠላት ጥይቶች ሊከላከሉልኝ የቀረጡ ይመስል፣ ልክ እንደ ተቆራኙ ፍየሎች ወይም ልክ እንደ ተጣበቁ ሰዎች ነበር በጣም ተጠጋግተን የምንራመደው።

ልጅ ወልደ ገብርኤል አሁን ክርክሩን አቁሞ ፊጠን እያለ ወደኔ ገሰገሰ። ያ ወጣት ሹምም በሴንቲሜትር ልዩነት ኮቱውን ተከትሎ ከኋላው በፍጥነት ይራመዳል። ልጅ ወልዴን ቀና ብዬ ሳየው በፊቱ ላይ የሆነ ነገር፣ የሆነ ታላቅ ነገር ሲነግረኝ እንደሚፈልግ በግልጽ ይነበባል። ይሁን እንጂ ወጣቱ ሹም ፋታ ሳይሰጥ እንደ ጥላ ስለሚከተለው አንዲት ቃል መተንፈስ አልተቻለውም። ልጅ ወልዴ አይናገራት፤ አይተንፍሳት እንጂ ስለታሰበልን ድግስ መጀመሪያውኑ ገምቼ ነበርና አሁን በደንብ ገባኝ።

እንዲህ ወደመታረጃችን ቁራ ስናዘግም ከሩቅ የአውሮፕላኖች ድምጽ ሰማን አውሮፕላኖቹ እየቀረቡ ሲመጡ የበረራ አቅጣጫቸውን በኛ አናት ላይ አደረጉት። አውሮፕላኖቹ በአናታችን ላይ እንዲህ መብረር ሲጀምሩ አንዳንድ ወታደሮቻችን ፈጥነው ወደ ቁጥቋጦዎች ውስጥ ሲገቡ ልጅ ወልደ ገብርኤል ፍጹም ተቆጥቶ በኃይለኛ ድምጽ፣ "ወደፊት!" አለና ወታደሮቹ ሳይበታተኑ መንገዱን ይዘው ወደፊት እንዲሄዱ እየጮኸ አዘዘ።

አዎ የአውሮፕላኖቹ አብራሪዎች በቀላሉ አይተውን ዝቅ ብለው በመብረር፣ በመትረየሶቻቸው ሊለቅሙን ይችላሉ ወይም በቀላሉ በሁለትና በሶስት በምቦች ሊያጋዩን ይችላሉ። "ጌታ፣ አይዞህ በርታ፤ ልንደናበር ፈጽሞ አይገባም!" ሲለኝ ልጅ ወልደ ገብርኤል አሁን ከአውሮፕላኖቹ የከፋ ነገር እየተደገሰልን እንደሆነ ገባኝ።

እድለኞች ነን የጣልያን አውሮፕላን አብራሪዎች አላዩንም። አንዴ ዞረውን ተመልሰው ወደመቀሌ ሄዱ። እነዚህ አብራሪዎች ሳይፈልጉና ሳይመኙ እነሱ ሊያደርሱብን ከሚችሉት አደጋ እጅጉን በጣም ከከፋ አደጋ አዳኑን። ልክ አውሮፕላኖቹ እየቀረቡ ሲመጡ የደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ሰዎች በያቅጣጫው ተበትነው ነጻ መንገድ ለቀቁልን። ወጣቱ ሹምም መቼና ወዴት አቅጣጫ እንደሆነ ባላውቅም ተሰውሯል። ይቺን አጋጣሚ ልጅ ወልደ ገብርኤል በመጠቀም፣ ጠጋ ብሎ ባጭሩ ስለሚጠብቀንና ስለተደገሰልን አደጋ አስረዳኝ።

በወታደሮቻችን ላይ "ቶሎ ቶሎ በሉ!" እያለ ጮኸባቸው። እንዲህ ጮክ ብሎ "ቶሎ ቶሎ ገበዝ! ቶሎ ቶሎ!" እያለ ከፍተኛ ግፊት አድርጎ ወደፊት እንድንሮጥ አደረገን። በዚህ ሩጫችን ገፍተን ትንሽ እንደራቅን ከፊታችን አንድ ጥቅጥቅ ያለ ጫካ ስላገኘን ወዲያው ወደጫካ ውስጥ ገብተን ትንፋሻችንን ለመዋጥ ሞከርን። እንዲህ ከዚህ መንቀሳቀሻ ከሌለው ጫካ ውስጥ ስንገባ እነዚያ መሰሪ ሽፍቶች ያሰቡትን ትተው ወደ ሰፈራቸው እንደሚመለሱ ገመትኩ። እናም የልጅ ወልደ ገብርኤልን ጉትጎታ ችላ ለማለትና ጥቂት ጊዜ ለማረፍ ሳቅማማ፣ "ሽፍታ! ሽፍታ! የት አባቱ! ግሞ ሽፍታ!" እያለ የሚጮኽ ድምጽ ሰማሁ። ወዲያው አንዲት ጥይት ጭኸች። የጥይቷን ብቸኛ ጬኸት ተከትለው ሌሎች ጠመንጃዎችም ተናገሩ።

በዚች ቅጽበት ከጥቂት ጊዜ በፊት ሰላም የሰፈነባት፣ ወፎች ይዘምሩባት የነበረች ድንግል ጫካ ወደየጦርነት አውድማነት ተለወጠች። ከየአቅጣጫው የጥይት አሩምታ ያንባርቃል። እስካሁን ከፊቴ በሰላም ይኼዱ የነበሩ ወታደሮች ለጥቂት ጊዜ ራስ ቅላቸውን ያዝ ያደርጉና ወደ መሬት ዝልፍልፍ ብለው ይወርዳሉ፤ ይወድቃሉ። ከየአቅጣጫው ከየቁጥቋጦው ስር ትንሽ ጉም መሳይ ጭስ ብን እያለች ስትወጣ ጠላት የመሸገበትን ቦታ ስለምታጋልጥ ወታደሮቻችን ጭሷን ተከትለው የሽፍታውን ወታደር በመሸገበት ያስተኙትና፣ እንደሁልጊዜው ሁሉ "የት አባቱ! ደግሞ ሽፍታ!" ይላሉ። ልክ ስጋው እንደማይበላ አውሬ እየቆጠሩት።

እንዲህ ተኩሱ ተፋፍሞ መሬት ቁና በሆነችበት ሰዓት ባላምበራስ ከመሸጉበት ተነስተው "ጌታ ተነስ! አሁን ነው ጊዜው!" አሉና ጣታቸውን ቀስረው አንዲት ገደል ሲሪዱኝ ሞከሩ። አሁንም በመሸግሁባት ቁጥቋጦ ውስጥ ሆኜ ሽጉጤን ጥይት እየሞላሁ እተኩስ ስለነበር የሰማኋቸው ወይም መሄድ የማልፈልግ መስሎ ስለተሰማቸው፣ ይጎትቱኝ ጀመር።

"ቶሎ በል ጌታ! ከዚች መሄድ አለብን፤ ቶሎ በል ጌታ ተነስ!" አሉኝ አሁንም ክንዴን ጨምድደው እንደያዙ። አዎ ባላምበራስ ኪዳነ ማሪያም እውነታቸውን ነው፤ ሽፍቶች በብዙ እጥፍ ወታደሮች ይበልጡናል፤ አስፈላጊ ሆኖ ካገኙትም ተጨማሪ ኃይል መጥራትም ይችላሉ። እና እዚች ጫካ ውስጥ መሽጎ እስከ መጨረሻው ሰዓት መጠዛጠዙ ዋጋ የለውም። እናም ወደ ገደሏ ከባላምበራስ ኪዳነ ማሪያምና ከወታደሮቻችን ጋር መሮጥ ጀመርን።

በዚህ ተኩስ መሀል ፈረሶቻችንና በቅሎዎቻችን ተደናብረው ወዲህና ወዲያ ይሮጣሉ፤ በተባራሪ ጥይት የተመቱ እንሰሳት እዚህም እዚያም ወድቀው የሞት ጣር ያጥራሉ፤ የኔም ከሲታ በቅሎ ክፉኛ ቆስላ ስለነበር ከስቃይዋ በሽጉጤ ገላገልኋትና ሮጬ ገደሉን እንደ ዝንጀሮ መቧጠጥ ጀመርኩ።

ግንባር ቀደሞቹ ወታደሮቻችን ከገደሉ ጫፍ ላይ ሌላ ውሂያ ውስጥ ገብተዋል። ከታች ገደሉን ገና በመውጣት ላይ ያሉት ደግሞ በታላቅ ጀግንነት እየተከላከሉ አንዱ ለሌላው የሽፋን ተኩስ እየሰጠ ገደሉን ወጣን። ገደሉን ከወጣን በኋላ ከፊት ለፊታችን ካለች ቁጥቋጦ ውስጥ መሽገው ወደፊት እንዳንገፋ አደረጉን። ከታች ከገደሉም ስር እየተከተሉን ነው። እንዲህ ከላይ ታች ተከበን ባለንባት ቅጽበት ወታደሮቻችን በቁጥቋጦው ውስጥ ባለነጭ ሸማ ሽፍታ ውልብ ሲል አነጣጥረው ከመሬት ይደባልቁትና፣ "የት አባቱ! ደም ሽፍታ!" ይላሉ እያንዳንዷ ታልማ የተተኮሰች ጥይት ኢላማዋን ስትመታ።

በእንዲህ አይነት ጥቂት ስንጠዛጠዝ ቆይተን ሽፍቶቹ በሹማቸው ትዕዛዝ ማፈግፈግ ጀመሩ። እኛ ሽፍቶቹን እያባረርን የመደብደቡ አላማ አልነበረንም። የኛ

ብቸኛው አላማ ያለ ምንም ግጭትና ደም መፋሰስ በተቻለ ፍጥነት ከራስ ሙሉጌታ የጦር ሰፈር መድረስ ነበርና የሚሸሹትን ሽፍቶች ትተን በጉዟችን ቀጠልን።

እነዚህን ሽፍቶች በዚህ መልኩ አባርረን፣ ተገላግለን፣ ወደፊት ስንገሰግስ ከፊት ለፊታችን ሌላ የቅድሞቹን የሚመስሉ ያደፈ ሽማ የለበሱ የታጠቁ ብዙ ትግሬዎች ገጠሙን። እነዚህ ሽፍቶች ለሁለት ተከፍለው ግማሾቹ በአቋራጭ ቀድሞ መንገድ መዝጋታቸው ይሆን? ግን ሌላ ምንም አማራጭ የለንም፣ ወደፊት ከመግፋት በስተቀር። እና አሁንም ወደፊት እንሮጣለን፣ ከፊት ለፊታችን የችፍርግ ያህል ከፍታ ያላት ከለላ ነገር ስናገኝ እንወድቅና ተኝተን እንታኮሳለን፣ ግንባር ቀደሞ ጦር ሲተኩስ ከኋላ ያለነው እንቀድምና እንደገና ወድቀን እንመሽግና ተኩስ ስንከፍት ከኋላ ያሉት ወደፊት ቀድመው ይመሽጋሉ። እንዲህ ሁለት ሶስት ቦታ ተከፍለን አንዱ ቡድን ለሁለተኛው፣ ሁለተኛው ለሶስተኛው የሽፋን ተኩስ እየሰጠ ወደፊት ገሰገስን።

በዚህ መልኩ ስንሮጥ፣ ስንወድቅ፣ ስንነሳ እንደገና ስንሮጥ፣ ልባችን እንደከበሮ እየደለቀና ሳንባችን ጉሮሯችን ስር ሊወተፍ ደርሶ ከተራራው ጫፍ ደረስን። አሁን ከፊታችን በመበተን ላይ ያሉትን እያባረርን ወደፊት ስንገፋ ከፊት ለፊታችን አንዲት መንደር ተደነቀረች። ከዚች መንደር ጎጆዎች ውስጥ ወንዶቻቸው መሳሪያቸውን እያቀባበሉ ወደኛ መተኮስ ጀመሩ። አንዳንዴ የሚተኩሷቸው ጥይቶች በአናታችን ላይ ሽው ብለው ያልፉ ነበር። ጠላቶች ወይስ ወዳጆች?

ለቅጽበት ያህል ቆም ብዬ አሰብኩ፣ ብዙ ለማሰብና ለመፈላሰፍ ግን ጊዜ የለም። ከቀኝም ከግራም፣ ከጀርባችንም ከፊታችንም ጠላቶች እያራወጡን ነው። ያለን አማራጭ አንድ ብቻ ነው። ወደፊት መግፋት ብቻ። ያለ ምንም ትዕዛዝ ወታደሮቻችን ወደፊት ገፉ። የወታደሮቻችን ሹም ባላምበራስ ኪዳነ ማሪያም አሁንም ከጎኔ እየሮጡ ናቸው። ልጅ ወልደ ገብርኤል ከኋላዬ እየሮጠ አንዳንዴ ዞር እያለ ወደ ኋላ ይተኩሳል። ወደ ፊት ገፍተን ወደመንደሯ ስንሮጥ፣ መንደርተኞቹ በጥይት ተቀበሉን። ቢሆንም ከመንደርተኞቹ ተኩስ ምንም አደጋ ሳይደርስብን ወደ መንደሯ ተቃረብን።

በሩጫችን ገፍተን ወደ መንደሯ መሀል ስናመራ ከመጀመሪያዋ ጎጆ በራፍ ላይ አንድ ጎልማሳ መሳሪያውን ወድሮ በኔ ላይ ሲያነጣጥር አየሁት፣ ግን ዋጋ አልነበረውም። ሽጉጤን ወደ ጎልማሳው እስካዞር ይቀድመኛል። እንዲህ በአለቀች ሰዓት ጎልማሳው የጨበጠውን ምላጭ ሳይስብ ጠመንጃውን ወደፊት ጥሎ እሱ ወደ አንበሳ ተኳሽ ነበር። በአንድ ምት ግንባሩን ነድሎ ፀጥ አድርጎታል።

ብዙም ጊዜ ሳላጠፋ ከሌላ አላሚ አይን ለመሰወር ተወርውሬ ከጎጆዋ ግርግይ ስር ተኛሁ። እንዲህ ጎጆዋን ተከልዬ ሽጉጤን እንደወደርኩ ከጎጆዋ አንዲት ሴት ልጇን እንዳዘለች እጆቿን ወደላይ አንስታ መጥታ ከፊቴ ተደፋች፣ እናትዬዋ

ትጮሀለች፣ ያዘለችው ልጅ ምርር ብሎ ያለቅሳል። ወዲያው ጠቅላላው መንደር ጩኸት በጩኸት ተደበላለቀ። ብዙዎቹ "ፈረንጆች፣ ፈረንጆች" እያሉ ይጮሀሉ። ምናልባት ጣልያኖች መስለናቸዋል። ይኼን ስህተት ማስተባበያም ሆነ ማስረጃ ጊዜ የለንም። የራስ ካሣ ወታደሮች መሆናችንን መናገር በቂ ነበር። ግን ሰሚ የለም።

እንዲህ መላው በጠፋ ሁኔታ ላይ እንዳለን የመንደሯ ሹም ከልጃቸው ጋር ወደኔ ቀረብ ብለው ሰላምታ ካቀረቡልኝ በኋላ የሆነ ነገር ሲናገሩ፣ ልጃቸው ተቀብሎ በተሰባበረ ጣልያንኛ "ሹም ከጥንት ጀምሮ የጣልያኖች ወዳጅ በመሆኑ፣ አሁንም ወዳጅ ነውና መንደሯን ያለምንም ማንገራገር ለጣልያኖች ያስረክባል!" አይነት ነገር ነገረኝ። ለሹሙ ልጅ ይኼ ታላቅ ስህተትና ያለመግባባት መሆኑን ላስረዳው አስቤ ሀሳቤን ቀየርኩና ወደፊት አልኩ። ጊዜ ማጥፋት ነው። ከነዚህ መንደርተኞች ሺህ ጊዜ ይበልጥ የከፋ ጠላት በጀርባችን አዝለናልና መንደሯን ለቀን ወደፊት ሮጥን።

በዚህ መልኩ ይቺን መንደር ለቀን ቁልቁል ሮጥን። መንደሯን አልፈን ጥቂት እንደሄድን ከአንዲት አነስተኛ አፋፍ ላይ ደረስን። ከአፋፏ ስር እታች ጥቅጥቅ ያለ ጫካ አለ። ወደታች ለመውረድም ብዙም የማያስቸግር የስርጥ መንገድ አለቺውና ጊዜ ሳናጠፋ በዚያችው ስርጥ ወርደን ከሚከተሉን ሽፍቶች አይን ለመሰወር ገና ስርጧን ከመውረዳችን፣ ከፊት ለፊታችን ሌላ ባለ ነጭ ሽማ የታጠቀ ሰራዊት መሽጎ ጠበቀን።

አሁን ከራስ ካሣ የጦር ሰፈር የወጣሁባትን ቀን መርገም ጀመርኩ። ለደቂቃ እንኳን ያለ ጠላት የምንተነፍስበት ቦታ በመጥፋቱ ከአቢ አዲ እግሬን የነቀልኩበትን ቀን በሆዴ እየረገምኩ ከፊታችን መሽገው ከሚጠብቁን ታጣቂዎች ጋር ተፋጠን እንደቆምን፣ አንድ ከሳና ረዘም ያለ ገብስማ ፀጉር ሰው፣ "ብኃይለ ሥላሴ አምላክ!" አለ። ወዲያው ልጅ ወልደ ገብርኤል ሲመልስ "በንጉሥ አምላክ! አትተኩሱ ወገኖች ነን!"

ከዚህ የልጅ ወልደ ገብርኤል መልስ በኋላ ያው ገብስማ ጸጉር ከሲታ ሰውዬ ወጣ ብሎ መሳሪያውን አቀባብሎ እንደደገነ፣ "ማን ናችሁ? የማን ናችሁ?" ሲል ጠየቀ። ልጅ ወልደ ገብርኤልም፣ "የራስ ካሣ ወታደሮች ነን። የንጉሠ ነገሥቱን ፈረንጅ አጅበን ወደ ራስ ሙሉጌታ የጦር ሰፈር እየሄድን ነው" አለውና ቀጥሎ በዚህ መንገዳችን በሽፍቶች መጠቃታችንንና ያለ እረፍት እንደምንጓዝ አስረዳው።

ይሁን እንጂ ይኼ ገብስማ ፀጉር ከሲታ ሹም ወልዴን ሊያምነው አልቻለም። እናም ከያዝነው ከለላ ወጥተን ወደፊት እንድንጠጋ አዘዘው። እኛም አንድም አማራጭ የለንም። አንድም እነዚህኞቹ ቢያንስ እስካሁን ምንም ኃይለ ቃል ሲናገሩ አልሰማንባቸውምና ብቻ ከሲታው ሹም እንዳዘዘው ሁላችንም ወደፊት አመራን።

እኛ በዚህ መልኩ ወደፊት ስንገፋ የሹሙ ወታደሮችም የተቀባበለ ጠመንጃቸውን እንደወደሩ እነሱም በዝግታ ወደፊት ገፉ። በመካከላችን ሁለት ሜትር የማይሞላ ርቀት ሲቀር ሁላችንም ቆምን። በነዚህ የሹሙ ሰዎች ፊት ምንም አይነት

የመትትት ሰዓት አይነዘብም። ወዲያው ከሲታውና ገብስማ ፀጉሩ ሹም ወደፊት መጥና እኛን ለቀም አድርጎ አጥብቆ ጨበጠኝ። ሹማቸውን ተከትለው የሹሙ ወታደሮችም በሹማቸው ጣፍ መዳፋቸውን እንደመሸፈን እያሉ የኛን ወታደሮች መጨበጥ ጀመሩ። ተራ ያልደረሳቸው የሹሙ ወታደሮች ዙሪያውን ከበቡን።

ሹሙና ልጅ ወልደ ገብርኤል በእናታቸው ቋንቋ በትግርኛ ረዘም ላለ ጊዜ ሲያወሩ ቆይተው፣ ልጅ ወልደ ገብርኤል ወደኔ ተመልሶ፣ ከሲታውና ገብስማ ፀጉሩ ሹም ያጫወተውን ይነግረኝ ጀመር።

ይኼ ከሲታና ገብስማ ፀጉር ሹም ቀኛዝማች ወልደ ጊዮርጊስ ሲባል ከ300 በላይ ወታደሮቹን ዛሬ በማለዳ አሰባስቦ ራስ ሙሉጌታን ሊረዳ ሲገሰግስ በመንገድ ላይ ተኩስ በመስማቱ፣ "እዚህ እግዜሩ ረሳት ቀበሌ" ድረስ ጣልያኖች የመጡ መስሎት በመገረም መሽጎ ሲጠባበቅ፣ እኛን በማግኘቱ መደነቅ ብቻ ሳይሆን እጅጉን በጣም መደሰቱንና መንደሩም ሩቅ ስላልሆነ ወደዚያው እንድንሄድ መጋበዙን አጫወተኝ።

ፍጹም ወንድምነት በተሞላበት ሁኔታ ቀኛዝማች ወልደ ጊዮርጊስ ብዙም ወደማትርቀው መንደሩ ይዞን ሄደ። የቀኛዝማች ወልደ ጊዮርጊስ መንደር በበርካታ የሳር ጎጆዎች የተሞላች ሆና እያንዳንዷ ጎጆ ከሌሎች ጎጆዎች በመጠነኛ ርቀት በራሷ የግቢ አጥር የተከለለች ነች።

29

ለሁለት ቀን የአርበኞች መሪ

ከቀኛዝማች ወልደ ጊዮርጊስ ጋር በመንደሮቹ መሀል ጥቂት ስንሄድ ቆይተን ከመንደሩ በስተመጨረሻ ላይ፣ አንድ ከሌሎቹ ጎጆዎች ብዙም የማትለይ ሆና ጊቢዋ ሰፋ ካለች ጎጆ ስንደርስ ቆም አሉና፣ "በል ግባ ጌታ" አሉኝ።

እኔ የአጥሩን በር ሳልፍ ከኔ በኋላ ባላምበራስ ሊጋ ማሪያምና ልጅ ወልደ ገብርኤል ተከተሉኝና በቀኛዝማች መሪነት ወደጎጆዋ ውስጥ ገባን። የቀኛዝማች ጎጆ ጨለምለም ከማለቷ ውጪ ውስጧ በጣም ማራኪና ቀዝቀዝ ያለ አየር የተሞላች ነበረች።

በጎጆዋ ውስጥ ሁላችንም ገብተን መስተናገድ ስለማንችል አብዛኛው ወታደር በጎጆዋ ታዛ ተቀመጠ። በጎጆዋ ውስጥ እንዛ እየተነበፈልን ከተቀመጥን በኋላ፣ የቀኛዝማች ሁለት አሽከሮች በብዙ መሶቦች እንጀራና በጣም የሚያቃጥል የበረዘ ወጥ አቀረቡልን። ተርበን ስለነበር ምንም እንኳን እኔን ወጡ ከቶኛ ቢያቃጥለኝም ያለምንም ይሉኝታ የቀረበልንን ጥርግ አድርገን በላን። እነዚሁ አሽከሮች ማለፊያ ጠጅ አቅርበውልን ስለነበር ደጋግሜም ጠጣሁ።

ማዕድ ተነስቶ ጥማታችንንም ቆርጠን ዋንጫችንን እንደጨለጥን የመንደሯ ሽማግሌዎች ወደ ቀኛዝማች ጎጆ ጎራ ማለት ጀመሩ። የመንደሯ አባወራዎች ከጎጆዋ ደጃፍ አካባቢ ግማሾቹ ደረቁ መሬት ላይ ተቀምጠው ሌሎቹ ደግሞ ወደፊት ገፋ

ብለው የጎጆዋን ምሰሶ እና ወጋግራዎች ተደግፈው እንደቆሙ፣ በኢትዮጵያና በህዝቧ ላይ ስለወረደው መከራ ያወሩኝ ጀመር:: “ዋይ ዋይ ፈረንጅ!” “ፈጣሪን በደልነው መሰል

“ዋይ ዋይ ፈረንጅ ጌታ! ዋይ ዋይ ፈረንጅ ጌታ! ትናንት ከትናንት ወዲያ አጥብቀው ባገራችን ላይ መከራ አወረደብን:: ፈረንጅ ጌታ! ትናንት ከትናንት ወዲያ ይከባበሩ የነበሩ፣ ትናንት ከትናንት ሰላም ይባባሉ የነበሩ፣ ትናንት ከትናንት ወዲያ ይከባበሩ የነበሩ፣ ዛሬ ጊዜው ቢከፋ ገና ከሩቅ ሲተያዩ ያለምንም ወዲያ ልጄን ለልጅህ ይባባሉ የነበሩ፣ ዛሬ ጊዜው ቢከፋ ገና ከሩቅ ሲተያዩ ያለምንም የረባ ምክንያት እርስ በርስ ይታኮሳሉ፤ ይገዳደላሉ::”

“ዋይ ዋይ ፈረንጅ ጌታ! ይኼው እኛስ ራሳችን እንዲሁ ድኼንነት መከራ ፈርተን ወደ ጓሮም ስንዞር መሳሪያችንን ታጥቀን አደል? ለምን? ለምን? ለምን ፈረንጅ ጌታ?” እኔ እመልስላቸው ይመስል፣መንደርተኞቹ ያለማቋረጥ ጥያቄያቸውን ደረደሩት:: ግን መንደርተኞቹ የኔንም መልስ ሳይጠብቁ ራሳቸው ይመልሳሉ:: “ፈረንጅ ጌታ! ምን ይደረግ ብለው ነው፣ ጊዜው ከፋ:: መንግሥት የለ፤ ንጉሥ የለ፤ ንጉሡን አጤውንም ገደሏቸው፤ ጌታችንንም ራስ ሥዩምን ገደሏቸው:: እንግዲህ ንጉሥ የለም:: መንግሥት የለም:: ህግ የለም:: እንዲህ በከፋ ጊዜ፣ አይ አምላካችን ምን በድለንህ ይሆን?”

ሌላም ሌላም ብዙ እሮሮዎች መንደርተኞቹ አሰሙ:: ሁሉም በአብዛኛው ደጋግመው የሚያወሩት መንግሥት ስለአለመኖሩ፣ ህግ ስለመጥፋቱ፣ ስለ አጼውና ስለ ራስ ሥዩም መገደል ነው:: ይኼ የቀኛዝማች መንደርተኞች ያልተጨበጠ ወሬ ደግሞ ልጅ ወልደ ገብርኤልን ክፉኛ አስቆጣው መሰለኝ፣ በጣም ከፍ ባለ ድምጽ በመንደርተኞቹ ላይ አንባረቀባቸው:: “ራስ ሥዩም አልተገደሉም:: ፍጹም ጤና ናቸው:: ከጥቂት ቀናት በፊት አናግሪያችኋለሁ” ብሎ ሊያስረዳቸው ሞከረ:: ግን ያመነው አንድም ሰው አልነበረም::

“አይ ጌታው፣ ይኼው በነጩ ወረቀት ተጥፎ:: የለም ራስ ሥዩም ሞተዋል” አለ ምሰሶውን ተደግፎ ብዙ ጊዜ ወደኔ አይኖቹን እያቁለጨለጨ የሚያወራው የመንደሪቱ አንድ አባወራ:: ቀጥሎም ከጥብቆው ውስጥ አንዲት ብጣሽ ወረቀት አውጥቶ ለኔ ሰጠኝ:: በእውነቱ በጣም በጥሩ ሁኔታ በሺጋ ትግሪኛ አምራ አስመራ ውስጥ የታተመች ወረቀት ነች:: ጣልያኖች እንዲህ በየጊዜው በሚበትኗቸው ወረቀቶች አብዛኛውን ህዝብ ወደማሳመኑ እየተቃረቡ ነው::

አሁን የቀኛዝማች ወልደ ጊዮርጊስ መንደር ገባር ከሆኑት አንዱ አባወራ ያቀበለኝ ወረቀት ጠቅላላ ይዘቷ መንደርተኞቹ ያሉትን ያጠቃልላል:: ጣልያኖች ለትግራይ ህዝብ በሚበትኑት ወረቀት ላይ ህዝቡ ወደፊት በመግፋት ላይ ባለው የጣልያን ጦር ላይ እጁን እንዳያነሳ እያሳሰበ፣ እያስፈራራ፣ በኢትዮጵያ ምድር መንግሥት እንደሌለና አጼው በጣልያን አውሮፕላኖች በምብ ተደብድቦ መገደሉን

አትቶ፣ ጣልያኖች ሰላምና መረጋጋት በመላው ኢትዮጵያ ለማስፈን በእግዚአብሔር ተልከው መምጣታቸውን ይገልጻል::

“ትልቅ ውሸት ነው:: ሁላችሁም እንደምታውቁት ይኼን ወረቀት የሚበትኑት የጣልያን አውሮፕላኖች እንጂ የኛ አይደሉም:: ለነገሩ እኛስ አውሮፕላኖችን ከየት አምጥተናቸው? ንጉሠ ነገሥቱም ፍጹም ጤና ናቸው:: ከነጦራቸው ከደሴ ተነስተው ወደ ኮረም ጉዞ ተጀመሩ ሰንብተዋል:: በቅርብ ቀን ሰሎይ ይደርሳሉ” አለ ልጅ ወልደ ገብርኤል::

ይሁን እንጂ አንድ የመንደሩ ሽማግሌ ሹም በልጅ ወልደ ገብርኤል ንግግር አለመስማማቱን ራሱን እየነቀነቀ እስካሁን ተኮማትሮ ከተቀመጠበት ተነስቶ ነገሩ ምንም ፋይዳ የሌለው ጉዳይ መሆኑን ማተት ጀመረ:: ሽማግሌው ሹም ምርር ብሎ፣ “አታይም እንዴ ልጅ ወልዴ? የተጻፈው እኮ በኛው ቋንቋ በትግሪኛ ነው:: የጣፈውም የኛው ሰው ትግሬ ነው” አለ::

በየካቲት ወር የጣልያን አውሮፕላኖች በተለያዩ የኢትዮጵያውያን ቋንቋዎች በተጻፉ ወረቀቶች መላውን የኢትዮጵያን መሬት አጥለቅልቀውታል:: የነዚህ በራሪ ወረቀቶች ጠቅላላ ይዘት በውሸት የተሞላ ቢሆንም ከሞላ ጎደል ብዙ ኢትዮጵያውያንን ማሳመን ችለው ነበር:: “ንጉሠ ነገሥቱ ሞተዋል መንግሥት የለም” የሚለው ደረቅ ውሸት በመላው ኢትዮጵያ ተዳርሷል:: ኢትዮጵያውያን ይኼን ውሸት የሚያስተባብሉበት ምንም መንገድ የላቸውም:: እንግዲህ መንግሥት ከሌለ ህግም የለም:: ህግ ከሌለ ደግሞ የኃይለኞችና የጠንካሮች ህግ ይመጣል::

ኢትዮጵያውያን በፍርድ ቤት ጉዳዮቻቸውን መፍታትና መዳኘት ትተዋል:: እርስ በርሳቸው በተገናኙበት ቦታና ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ችግራቸውን በኃይል መፍታት ጀምረዋል:: ወንድ ልጅ ጎጆውን መሳሪያውን ሳይታጠቅ መልቀቅ የማይታሰብ ነገር እየሆነ መጥቷል:: እዚህ ግባ በማይባል ትንሽ ጭቅጭቅ በተነሳ አምባጎር የሰው ህይወት ይጠፋል:: የሟች ቤተሰቦች ህግን ሳይጠቀሙ ተከታትለው ደም ይበቀላሉ:: ሰዎች በተገናኙ ቁጥር መገዳደል ጀምረዋል:: በዚህ ክፉ ጊዜ ማንም ሰው የትኛው ቀማኛና ሽፍታ፣ የትኛው ደግሞ ሰላማዊ ሰው መሆኑን ለይቶ ማወቅ ተቸግሯል፤ ወይም ደግሞ መለየቱ ፈጽሞ አይቻለውም::

በየካቲት ወር 1936 ዓ.ም. የኢትዮጵያ እና የህዝቦቿ መከራ ይኼን ይመስል ነበር:: ይኼን እያሰብኩ ቀኛዝማች ወልደ ጊዮርጊስ ከጎጆዋ ከወጣ በኋላ እንቅልፍ ወሰደኝ:: ብዙም ሳልተኛ ከጎጆዋ በራፍ አካባቢ የሚጨቃጨቁ ሰዎች ድምጽ ቀሰቀሰኝ:: ወዲያው ገብስማው ፀጉር ቀኛዝማች ወልደ ጊዮርጊስ በጣም እያዘኑ መጥተው “ጌታ፣ ተነስ አደጋ መጥቷል! ቶሎ ከዚች መንደር መጥፋት አለብን” አሉኝ::

... ትናንት ቀኑን ሙሉ መከራችንን፣ አንድ የቀኛዝማች ታማኝ ወታደር፣ ወደ መንደሩ ተጠግተው መመሽጋቸውንና ጉህ ፍዳችንን ሲያበሉን የዋሉት ሽፍቶች ሊያጠፉብን መዘጋጀታቸውን ዘርዝሮ እንደነገራቸው ቀኛዝማች ወልደ ሲቆር አደጋ ሊጥሉብን መዘጋጀታቸውን ጌታ፣ እነዚህን ሽፍቶች ምንም ኃይል አያግዳቸውም። ጊዮርጊስ አስረዱኝ። ቀጥለውም "ጌታ፣ እነዚህን ሽፍቶች ምንም ኃይል አያግዳቸውም። ትናንት በተካሄደ ተኩስ ሹማቸውንና ሌሎች አምስት ወታደሮቻቸውን አጥተዋልና፣ ትናንት በተካሄደ ተኩስ ሹማቸውንና ቀድመን ተዚች ገላጣ መንደር እርቀን ወደ ተራራው በቶሎ እንዲህ በጨለማ ሳይነጋ ቀድመን ተዚች ገላጣ መንደር እርቀን ወደ ተራራው ጫፍ ወተን መመሸግ አለብን" አሉኝ አሁን አምርረው።

"አይሆንም፣ የትም አንሄድም፣ እዚሁ ሆነን እንገጥማቸዋለን" አልኩ። ቀጥዬም ቀኛዝማችን "አንቱ 300 ወታደሮች አለዎት፣ እኔም 50 አሉኝና" ብዬ ንግግሬን ሳልጨርስ ቀኛዝማች ወልደ ጊዮርጊስ "ዋይ ዋይ ፈረንጅ ጌታ! እኔ አሁን 300 ወታደር የለኝም። የቀሩኝ ሀያ ቢበዛ ሰላሳ ቢሆኑ ነው ፈረንጅ ጌታ። የቀሩት ወታደሮቼ ከሽፍቶች ጋር ተቀላቅለዋል። ትናንት ባንተ ወታደሮች ከተገደሉት መካከል ዘመዳቸውን አግኝተው ከቶኛ ተቆጥተዋል። አንተንም ሊበቀሉህ ምለው ተገዝተዋል፣ ፈረንጅ ጌታ።" አሁን ቀኛዝማች እውነቱን እንደሆነ ጭንቅ ያለው ፊቱ ይናገር ነበር።

ምንም ማድረግ አንችልም፣ እንደደከመን እንቅልፍ ሳንጠግብ በዚህ ድቅድቅ ጨለማ ተራራ መቧጠጥ አለብን። ደግነቱ ቀኛዝማች ወልደ ጊዮርጊስ እያንዳንዷን ድንጋይ ጠንቅቆ ያውቃታል። ቢሆን ቢሆን እኩለ ሌሊት ቢሆን ነው፣ ጨረቃዋም ጨክና ከተራራው ጀርባ ተደብቃለች፣ ከአንድ ሜትር በላይ አርቆ በማይታይ ጨለማ በዳክዬ እርምጃ ቀኛዝማች ወልደ ጊዮርጊስን ተከትለን አንዲት ኮሽታ ሳናሰማ ወደ ተራራው ወጣን።

ከሁለት ሰዓት የዳክዬ ጉዞ በኋላ ከተራራው ጫፍ ደረስን። አዎ ተራራው በአናቱ ላይ እጅግ በጣም የሚያስገርሙ የተፈጥሮ የመከላከያ ምሽጎች አሉት። አዎ እዚህ ከመሸግን የፈለገውን ያህል ጦር ቢሰለፍብን ጥይቶቻችን እስካላለቁና ውሃ ና ምግብ ጨርሰን በረሃብና በውሃ ጥም እስካልሞትን ድረስ ብዙ ጊዜ መከላከል እንችላለን። እንዲህ ሳስብ፣ በድንገትና በችኮላ ከመንደሩ ተጣድፈን ስንወጣ በቂ ስንቅ ያለመያዛችን ትዝ አለኝ። "እህሳ ምን ትላለህ?" ብለው ቀኛዝማች ላቀረቡልኝ ጥያቄ፣ "አዎ ጥሩ ቦታ ነው። አጋዥ ኃይል እስኪመጣልን ድረስ እዚህ መሽገን መከላከል እንችላለን" አልኳቸው። "ኃይል ከየት ይመጣል ብለህ ነው ጌታ?" አሉኝ ቀኛዝማች፣ አሁን በመገረም ጢማቸውን እንደመፈተግ እያሉ።

ከዚህ ራቅ ብሎ አምባራዶም የራስ ሙሉጌታ ጦር አለ፣ አሁን ካለንበት ተራራ ጫፍ ትይዩ የግማሽ ቀን መንገድ ርቀት ላይ ሳምሪ ከምትባል ቦታ የራስ ሥዩም ሚስት ከ5,000 ጦራቸው ጋር ሰፍረዋል፣ አሁን ካለንበት የተራራ ጫፍና በአቢ አዲ እኩሌታ ቦታ ላይ አቢቹ ከ2,000 በላይ ከሚሆነው ጦሩ ጋር ከሽፍቶች ጋር እየተዋጋ ሰፍሯል። ቀኛዝማች ወልደ ጊዮርጊስን ጠራሁና፣ "ሁለት ታማኝ

ወታደሮችዎን ወደ ራስ ሙሉጌታ የጦር ሰፈር ልከው፣ ያለንበትን ሁኔታ አስረድተው 300 ወታደሮችና የተወሰኑ መትረየሶች ይዘውልን እንዲመጡ ላኩ። ሌላ ሁለት ታማኝ ወታደሮችን ከራስ ሥዩም ሚስት ዘንድ ሳምሪ ልከው እርዳታዋን እንደምትፈልግ እንዲያስረዱ ላኩ። ሌሎች ሁለት ታማኝና ደፋር ወታደሮችዎን ወደ አቢቹ ልከው ችግር ውስጥ እንዳለን እንዲነግሩት አድርገው ላኩ" አልኩና ቀኛዝማች ወልደ ጊዮርጊስን ለመንኳቸው።

የጦር እርዳታ ልመና ወደ ራስ ካሣ መላኩ ዋጋ የለውም። ከራስ ካሣ የሚመጣ የጦር ኃይል እንኳን ቢኖር እዚህ ቢደርስልን ግፋ ቢል ከአራት ቀናት በኋላ ነው። አራት ቀን ሙሉ ግን በዚች ተራራ ጫፍ ላይ ያለምንም ስንቅና ውሃ መቆየት አንችልም። ቀኛዝማች ወልደ ጊዮርጊስ በዚችው ምሽት ልመናዬን ተቀብለው፣ ታማኝ ሰዎቹን መርጦ መልክቱን ሲልክ ወደ መንደሩ ቁልቁል ገሰገሰ።

ከተራራው ጫፍ ገደል ላይ እንደ ውሃ ልክ ተጠርባ ከተዘረጋች ግርግይ ላይ ሰፍረን በታላቅ ትግስት ቀኛዝማች ወልደ ጊዮርጊስ ኃይል አስተባብረው እስኪደርሱልን መጠበቅ ጀመርን።

ቃኚ ወታደሮቻችን ቀኑን ሙሉ በተወሰነ ጊዜ እየተቀያየሩ አካባቢያችንን ቢቃኙም ምንም ዝር የሚል ነገር አልነበረም። ማምሻው ላይ ቀኛዝማች ወልደ ጊዮርጊስ ብቻቸውን ወደምሽጋችን ብቅ አሉ። ቀኛዝማችን ገና ከሩቅ ሳያቸው ድምጼን ከፍ አድርጌ ተጣራሁ። ቀኛዝማች ወደኛ እየቀረቡ ሲመጡ እጅጉን በጣም እንዳዘኑ ያስታውቅ ነበር። ቀኛዝማች ካጠገቤ አረፍ ብለው፣ የመንደሩ ሰዎች እኛን ለማዳን የሚያደርጉትን ጥረት በክፉ አይን እንደሚያዩትና፣ በጎ ፈቃደኞች አግኝተው መልእክቱን ለመላክ ተቸግረው እንደነበርና በመከራ አሳምነው የላኳቸው መልክተኞቹ ምንም ፋይዳ ሳይፈይዱ እንደተመለሱ እዝን ብለው ነገሩኝ።

ወደ ራስ ሙሉጌታ የጦር ሰፈር መልክተኞቹ ፈጽሞ መጠጋት እንዳልተቻላቸውና፣ የራስ ሙሉጌታ ጦር በጣልያን ሰራዊት ተከቦ ሲዋጋ ሰንብቶ ትናንት የአምባራዶምን ተራራ ጫፍ ለጣልያኖቹ መልቀቁንና፣ የራስ ሙሉጌታ ወታደሮች ዝብርቅርቁ በወጣ ሁኔታ ወደ አምባላጌ ማፈግፈግና መሸሽ መጀመራቸውን፣ የራስ ሥዩም ባለቤት ከሳምሪ 5,000 ጦሯን ይዛ ከሶስት ቀን በፊት ወደ ስሜን ተራራ መውጣቷንና፣ ለቃው የሄደችውን ሳምሪን ጣልያኖች እንደተቆጣጠሩት ካስረዱኝ በኋላ፣ በእኛና በራስ ካሣ ጦር መካከል ሰፍሮ ያለውና ከ2,000 በላይ ፈጣንና ተወርዋሪ ጦር ያለው አቢቹም፣ በአንድ ወገን የደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ሰዎች፣ በሌላ ወገን በትግራይ ሽፍቶች፣ ከታች ደግሞ በጣልያን ወታደሮች ተከቦ በከባድ ውጊያ ላይ መሆኑና የመልክተኞቹ ወደዚያ ደፍረው ለመሄድ እንኳን ፍቃደኛ ሳይሆኑ እንደቀሩ በአዘነ ልባቸው ቀኛዝማች ወልደ ጊዮርጊስ አስረዱኝ።

እንግዲህ ያለን የመጨረሻ እድል በራሳችን መተማመን ብቻ ነው:: እንዲህ እጅጉን በጣም ተስፋ አስቆራጭ ሁኔታ ላይ እያለን ጣልያኖች ወደ ቀኛዝማች ወልደ ጊዮርጊስ መንደር መጠጋት ጀመሩ:: ትንሽ ከአሰብኩ በኋላ ልክ እንደመጨረሻ እድል ቀኛዝማችን አሮፍጠው ወደሚጠብቁን ሽፍቶች ሄደው በምን መልኩ ነጻ መንገድ ሊከፍቱልን እንደሚችሉ እንዲደራደሩ ላኳቸው:: በድርድሩም በርካታ የጭነት ከብቶችና ጠመንጃዎችን ልንሰጣቸው መዘጋጀታችንን ማስረዳት እንዳይረሱም ደጋግሜ አስታወስኳቸው::

አሁን ትግስት አጥቼ የሽፍቶቹን መልስ እየጠበቅሁ ነው:: ትግስቴ ወደማለቁ ሲቃረብ ቀኛዝማች ተመለሱ:: "እሺ ቀኛዝማች? ምን አሉ? ተቀበሉን?" እያልኩ ገና ብቅ ከማለታቸው ድምጼን ከፍ አድርጌ እየጮኽኩ ጠየኳቸው:: ቀኛዝማች በታላቅ ሀዘን ራሳቸውን አውዛወዙ:: በአረማመዳቸው እጅጉን መድከማቸው ያስታውቃል:: ግን ከትናንት ጀምሮ ሳይታክቱ፣ ለአንዲት ደቂቃ እንኳን ሳያርፉ ሲንከራተቱ ውለዋል:: አሁን የግዳቸውን ከጎኔ ተቀምጠው፣ "እምቢ አሉኝ! አልተቀበሉኝም" አሉኝ::

ቀኛዝማች ከጥቂት ጊዜ ዝምታ በኋላ ቀጥለው "ሽፍቶቹ አሁን ያለንበትን ሁኔታ አሳምረው ያውቃሉ:: ምንም ስንቅና ውሃ እንደሌለን አውቀዋልና መጀመሪያ በረሃብና በውሃ ጥም ሊቀጡን ወስነዋል:: አዲሱ ሹማቸውማ፣ ያለ ውሃ ግፋ ቢል ሶስት ቀን ብትችሉ ነው:: ከሶስት ቀን በኋላ የማጥቃት እርምጃ እንወስዳለን፤ እንዘምትባችኋለን:: ከዚያም ሁላችሁንም ከፈጀናችሁ በኋላ ያሻንን ያለ ከልካይ እንወስዳልን፤ እያለ ፎከረብኝ አሉኝ::

ምንም የሚጠጣ ውሃ የለንም:: ለሰማዩ ቀረብን መሰለኝ ገደሉን ተንተርሰን ቆጭ ባልንባት ግርግይ ላይ ፀሐይዋ ያለ ገላጋይ እየወቃችን ነው:: ብቻዬን ተቀምጬ እንዲህ መላው ከጠፋ ፍጹም ተስፋ አስቆራጭ ሁኔታ እንዴት እንደምንወጣ ያለማቋረጥ አስባለሁ፤ አወጣለሁ፤ አወርዳለሁ:: እያንዳንዷን እድል እንደፀጉር እየሰነጠቅሁ አብሰለሰላለሁ:: ግን ሀሳቤን አሰባስቤ ይኼ ነው የምለው ቁርጥ ያለ ሀሳብ ሳይኖረኝ በግማሽ እንደ እንቅልፍ፣ በግማሽ ደግሞ እንደ ቀን ቅዠት ነገር ያዘኝና ከኔ ትንሽ ፊንጠር ብለው የሚመክሩትን ባላምበራስ ኪዳነ ማሪያም፣ ልጅ ወልደ ገብርኤልንና ቀኛዝማች ወልደ ጊዮርጊስን በውይይታቸው ትቼ በሀሳብ ሄልም ብዬ ጠፋሁ::

አዎ ነገሩ የሆነው ያኔ ልጅ ተድላ በተስቦ በሽታ በድንገት የሞተ ሰሞን ነው:: በዚያን ሰሞን ከሁለቱ ራሶች ዘንድ በተደጋጋሚ እኔ፣ ኮሎኔል ኮናቫሎቭና ደጃዝማች አበራ ተጠርተን በተደጋጋሚ ልጁን እንድናቆመው ትዕዛዝ ተሰጠን:: ግን አቢቹን ማቆምና ወደ ጦሩ እንዲመለስ ማድረግ ማናችንንም አልተቻለንም ነበር:: ታዲያ አንድ ቀን ቀኛዝማች ሼክ ሁሴን አባወርቄ በጣም ተቆጥተው ወደኔ መጡና፣ የሆነ ምስጢር ነገሩኝ:: እኔም እሳቸውን ይዤ ኮሎኔልን አስጠራሁና ከደጃዝማች አበራ ዋሻ

የሰባበሁን መምከር ያገዘን:: ቀኛዝማች ሼክ ሁሴን አባወርቄ የሰሙትን ምስጢር ለደጃዝማች አበራ ሲነግሩት ያለወትሮው በጣም ተበሳጭቶ በከፍተኛ ድምጽ "ሊሆን አይችልም! ሊሆን አይችልም!" እያለ ጮኸ::

ነገሩ እንዲህ ነበር:: ልጁ (አቢቹ) ዝናዉ እየሰፋ፣ ቀን በቀን የጦሩ ቁጥር እየጨመረ ሄደ፣ እንዳውም በመጨረሻ ሰዓት ላይ አንድ ሀብቶም በሚባል የሀማሴን ልጅ የሚመራ ወደ 300 የሚሆኑ የኤርትራ ተወላጅ ወታደሮቹን ይዞ ከልጁ ጦር ጋር ተቀላቀለ በተባለበት ሰሞን የትግራይ መንደሮች ከመቼውም ጊዜ በላይ መጨስ ጀመሩ:: እናም ይኼ ወሬ ከሁለቱ ራሶች አልፎ ከአፄው ጆሮ ይደርስና አፄ ኃይለ ሥላሴ በራዲዮ ለሁለቱ ራሶች ቀጭን ትዕዛዝ ይሰጣሉ፤ ያም "ልጁን አቁሙት" የሚል::

አዎ አፄው፣ ንጉሠ ነገሥቱ፣ አሁንም ጦርነቱን በሰላም እፈታለሁ ብለው ተስፋ ያደርጉ ስለነበር፣ እንዲህ እንደ አቢቹ አይነት አርበኞች የጠላትን ጦር ድንገት እየደረሱና አደጋ እየጣሉ፣ የገደሉትን ገድለው፣ የዘረፉትን ዘርፈው እንዳመጣጣቸው ድንገት ውልቅ የሚሉት ነገር፣ አፄው አሁንም ተስፋ በሚያደርጉት ሰላም እንቅፋት እንዳይሆንባቸው በመስጋት በቀጭኑ ትዕዛዛቸው "ልጁን አቁሙት" ብለው ሁለቱን ራሶች አዘዟቸው::

በአርበኛው የልጁ ጦር ላይ የሁለቱ ራሶች ጦር ሊዘምትበት እንደተዘጋጀ ነበር ቀኛዝማች የሰሙት ምስጢር የሚያስረዳው:: እና ከብዙ ውይይት በኋላ አቢቹን በዘዴ ወደ ደጃዝማች አበራ የጦር ሰፈር አምጥተን አስረንም ቢሆን ልናስቀረው አሰብንና ምክንያት ተፈጥሮ መልክተኛ ልንልክበት፣ መልክተኛውም አቢቹ የሚያምነው ሰው የቅርብ ጓደኛው አንበሳ እንዲሆን ተወሰነ::

መጀመሪያ አንበሳ ዋሽቶ አቢቹን በማስያዙ ለመተባበር ፍቃደኛ አልነበረም:: በኋላ ላይ ደጃዝማች አበራ ለብቻ ወስዶ "አንበሳዬ እይማ! እኔ ጤነኛ አደለሁ? አሁን አቢቹ ጠላቱ ስለበዛ ከበው ሳይገድሉት በፊት ሄደህ፣ አበራ በሞት አፋፍ ላይ ነውና ቶሎ ድረስ ብትለው በኔ አይጨክንምና ቶሎ ይመጣል:: ከዚያ መከሬም ለምኜም ቢሆን እዚሁ አስቀረዋለሁ" ብሎ ደጃዝማች አንበሳን ካሣመነው በኋላ ወደአቢቹ፣ ወደማይታወቀው "የልጁ የጦር ሰፈር" ላከነው::

አዎ አንበሳ ለአቢቹ መልክቱን በትክክል እንደሚያደርስና አቢቹም የጦር አለቃው በሞት አፋፍ ላይ ሆኖ ሲጠራው ሳይውል ሳያድር እንደሚመጣ እርግጠኛ ሆን:: አቢቹ ጨለማን ተገን አድርጎ ማታ ሲመጣ እያንዳንዳችን ምን ምን ማድረግ እንዳለብን ስንወያይ በጠራራው ፀሐይ አቢቹ ድንገት ከች አለ:: ሽበጥ ጫማ የተጫማ፣ አጭር ቁምጣ ታጥቆ በጣም ሰፋ ያለ እጂጌ ጉርድ ኮቱን በወታደር ቀበቶ ጥፍር አድርጎ ያሰረ ጨበሪያም ልጅ ድንገት ከዋሻዋ ዘው ብሎ ገብቶ ከእንዱ ጥግ ሲቆም፣ በዚያች ዋሻ ውስጥ ያለን ሰዎች ሁሉ አፋችንን ከፍተን ቀረን:: አቢቹ ነበር::

መሳሪያ አልታጠቀም፤ ግን በዚያ ሰፋ ባለና በወታደር ቀበቶ ጥብቅ አድርጎ ባሰረውና ቡፍ ባለው ኮቱ ውስጥ ሽጉጡን እንደወሸቀ ጥርጥር የለውም። እንዲህ ሁላችንም ተደናግጠን ዝም እንዳልን ደጃዝማች አበራ አሽከሩን በአይኑ ጠቀስ ሲያደርገው አሽከሮው ሹልክ ብሎ ወጣ። የአሽከርዬው አወጣጥ ከዋሻዋ ደጃፍ ላይ ዘብ የቆሙትን ወታደሮች ለመጥራት እንደሆነ ሁላችንም ገብቶናል። እርግጠኛ ነኝ ከአሳሳቁ አቢቹም በደንብ ገብቶታል። ብዙም ሳይቆይ አሽከርዬው እጆቹን ወደላይ አንስቶ ከጀርባው መሳሪያ ተደግኖበት ወደ ዋሻው ተመለሰ። አሁን አቢቹ ከዋሻዋ ውጪ ኃይል እንዳለውና በደንብ አስቦበት እንደመጣ ሁላችንም በዚያች ዋሻ ውስጥ ያለን ሰዎች ገባን።

"ምርኮኛ መሆናችን ነው እንዴ አቢቹ?" ሲል ኮሎኔል ኮኖቫሎቭ እንደተቀመጠ አረቄውን በትንፋሽ ጨልጦ ጠየቀው። "በፍጹም! ኮሎኔል በፍጹም! ማን የማን ምርኮኛ ይሆናል ጌታው?" ሲል መለሰና ወዲያው ቀጥሎ "ለምን ግን ደጃዝማች? ለምን?" ሲል ደጃዝማችን ጠየቀ። አሁን ደጃዝማች ትንሽ አሰብ አድርጎ፣ ሁለቱ ራሶች ያሰቡለትን ድግስ ፍርጥርጥ አድርጎ አስረዳው። እንዲህ ደጃዝማች አቢቹን ሲያስረዳው አቢቹ በዝምታ ያዳምጥ እና "ግን ለምን? ግን ለምን?" እያለ በተደጋጋሚ ይጠይቃል።

የአዌውን ፍላጎት ኮሎኔልም፣ እኔም በወግ በወጉ ልናስረዳው ሞከርን። ይሁን እንጂ የአቢቹን "ግን ለምን?" ጥያቄ መመለስ የቻለ ሰው አልነበረም። አቢቹ ተሰናብቶን ከመሄዱ በፊት ግን አንድ እስከ ህይወቴ መጨረሻ ድረስ የማልረሳው አጭር ንግግር አድርጎ ነበር።

"ደጃዝማች፣ ገና ከሰላሌ ስንነሳ ታማኝነቱን በምኒልክ ስም ቃል የገባሁት ላንተ እንጂ ለሽማግሌዎች ወይም ለንጉሡ አደለም። እኔ ንጉሥ አደለሁም፤ ተራ ወታደር እንጂ። እና እኔ ሁለት ሶስት ወር ደሴ ተጎልቼ ጣልያኖች እጄን እስኪይዙኝ አልጠብቅም። ላንተ ግን አሁንም በምኒልክ ስም፣ በምኒልክ አምላክ በድጋሚ ቃሌን እሰጣለሁ። ለአንተ እሞታለሁ። ተመለስ ላልከው ግን፣ የት ነው የምመለሰው? ምንስ መመለሻ ቤት አለኝና? እዚህም እዚያም እሳት እየነደደ እንዴት ቁጭ ልበል? ሽማግሌዎቹ ጦር ሊሰዱብኝ አስበው ከሆነ ደግ፤ ምንም ችግር የለም። ግን እኔ ከነሱ ጠብ እንደሌለኝና የሀገሬ ታማኝ ወታደር እንደሆንኩ አስረዳልኝ። ደጃዝማች፣ ስማኝማ! ምናልባት ካልተገናኘን እማማን ደስተኛ እንደነበርኩ ንገራት። በእሳተ ጎሞራ መሀል ማለፍ ቢኖርብኝም ወደ ሰላሌ እመለሳለሁ" ነበር ያለው።

አዎ "በእሳተ ጎሞራም መሀል ቢሆን።" ይቺ የአቢቹ ቃል ትልቅ ወኔ ሰጠችኝና ከገባሁበት የቀን ቅዠት እንደመባንን ብዬ፣ ላቤን በሽማዬ ጠራርጌ ወደነ ልጅ ወልደ ገብርኤል ለመሄድ ስነሳ፣ እነሱም ምክራቸውን ጨርሰው ኖሮ ከተቀመጡበት ተነስተው ወደኔ መጡ። ወዲያው ባላምበራስ ኪዳነ ማሪያም ወደፊት ጠጋ ብለው አጠር ያለች ንግግር አደረጉ። "ግዴለም ፈረንጅ ጌታ፣ አይዞህ! ሁላችንም

መሞት አለብን! አዎ ፈረንጅ ጌታ፣ አሁን መክረን ጨረስን። ግን አንተን ከመግደላቸው በፊት እኛን በሙሉ መግደል አለባቸው። አንድ ሰው እስኪቀር ድረስ እንሞትልሀለን" አሉኝ።

ከኔ በፊት ለኔ ለመሞት መወሰናቸው እንጀቴን በላው። በነሱም ኩራሁ። ይሁን እንጂ ምንም ጥቅም አልነበረውም። በምንም መልኩም ቢሆን ቆራጥነት ገደል፤ ከዚች የተራራ ጫፍ ገደል ስር ተቀምጠን ሞትን መጠበቅ የለብንም። በተገኘ አጋጣሚ ከዚች ተራራ ጫፍ ተነስተን በጠላት ጦር መካከል እየተዋጋን ለማምለጥ መሞከር አለብን። አዎ "በእሳተ ጎመራ መሀልም ማለፍ ቢኖርብን" እያልኩ ላስረዳቸው ሞከርኩ።

እያንዳንዷን የማምለጫ መንገድና ዘዴ በዝርዝር ተወያየንበት። ልክ ጨለምለም ከማለቱ በአንድነት ተነስተን፣ ሽፍቶች ሳይዘጋጁና ሳይጠብቁን ድንገት አደጋ ጥለን ሲበታተኑ እንደምንም ብለን ወደ አምባላጌ ለመዝለቅ እንሞክር። ከተሳካልን እስከ ደሴ ድረስ ገፍተን ከአፄው ጦር ጋር እንቀላቀላለን፤ ካልሆነልንም እንደምንም ብለን ከራስ ሙሉጌታ ጦር ሰፈር ለመድረስ መጣር አለብን አልኳቸው።

"አዬ አዬ ፈረንጅ ጌታ! ይኼማ የማይሆን ነገር ነው፤ አይሆንልንም፤ አይሳካልንም። ወደደቡብ የሚወስዱት መንገዶች በሙሉ በጣልያን ጦር ተይዘዋል። በደንብም ይጠበቃሉ። ተራሮች በሽፍቶች ተሞልተዋል። አሁን እንደ ተራበ ጅብ አፋቸውን ከፍተው የሚጠብቁንን ጅቦች ዛሬ ብናልፋቸው፣ ነገ ሌሎች ጅቦች ቁርስ ያደርጉናል። በተለይ አንተን ፈረንጅ ጌታ፣ አንዲት ስንዝር መሬት አያስኬዱህም። በአሁን ጊዜ እንኳን ፈረንጅ የኛም ሰው አንዲት መንደር መሻገር አይቻለውም።" ብቻ ሁሉም በአንድ ድምጽና በተመሳሳይ ሁኔታ ሀሳቤን ያስተባብሉብኛል።

"እሺ በቃ፣ በሌላ መንገድ እንሄዳለን እንጂ መጥተው እስኪጨፈጭፉን ተቀምጠን አንጠብቃቸውም" አልና እንደገና በሌላ ዘዴ ላሳምናቸው እሞክራለሁ፤ ግን ከሁሉም ጓዶቼ አይን የሚነበበው አንድ ነገር ብቻ ነበር። ሁሉም ይቺን የተራራ ጫፍ ይዘው እስከ መጨረሻው ድረስ ተዋግተው ለመሞት ቆርጠዋል። አዎ የጊዜ ጉዳይ ብቻ እንደሆነና ሞት አይቀሬ መሆኑን ሁሉም በደንብ አሳምረው ያውቃሉና፣ መሞታቸው ላይቀር ለምን በከንቱ ይድከሙ፤ ላይሆን ነገር። በዚህ ፍጹም ተስፋ አስቆራጭ በሆነ ሁኔታ ላይ እያለን አሁን አብረውኝ ያሉትን ሹሞች እንደገና ከብዙ ድርድር በኋላ ከዚች የተራራ ጫፍ ላይ ወርደን ለማምለጥ መሞከር እንዳለብን ማሳመን ተቻለኝና የማምለጥ እቅዴን ተግባራዊ ለማድረግ ዝግጅቱን ጀመርኩ።

"ዛሬ ማታ ወደሰሜን ጥቃት እንሰነዝራለንና ጨለማን ተገን አድርገን ሁላችንም ባንድ ላይ ተሰባስበን ለመጓዝ ያዳግተን ይሆናል፤ ግን ትልቅ የሚባለውን መስዋዕትነት ከፍለንም ቢሆን እንደምንም ለማምለጥ ሞክረን፣ የሞተው ሞቶ፣ በህይወት የቀረ ወታደር ሁሉ ጊባ ወንዝ ዳር እንድንገናኝ" አልኳቸው።

እኔ እንዲህ በድፍረት ስናገር እስካሁን ተቀምጠው ያዳምጡ የነበሩት ባላምበራስ ኪዳነ ማሪያም ከተቀመጡበት ተነስተው ፊቴ ቆሙና "እውነትክን ነው ጌታ! እንዲህ እነሀ ሽፍቶች ሳይጠብቁን ድንገት ተነስተን እየተታኮስን ወደራስ ካሣ የጦር ሰፈር ለመድረስ እንሞክራለን" ካሉ በኋላ ንግግራቸውን በመቀጠል ወደ ጦራችን ጭር ብለው ከተናኙ በኋላ፣ ምናልባት ራስ ካሣም ተንቤን ላይኖሩ ይችላሉ፣ ምናልባት አቢ አዲም በጣሊያኖች እጅ ወድቆ ይሆናል፣ ግን ምንም አይደለም፣ እኛ ግን እጅ አንሰጥም። ከጠላቶቻችን ጋር እንደ አርበኛ እንዋጋቸዋለን:: እኛንም አንተ ትመራናለህ!" አሉ።

እኔም ከባላምበራስ ኪዳነ ማሪያም ቀጥዬ "በእቅዳችን መሰረት ቀን ቀን ተደብቀን እየዋልን፣ ሌሊት ሌሊት በአነስተኛ የጣልያን ጦሮች ላይ ሳይታሰብ አደጋ እየጣልንና መንገድ እየስለቀቅን ቀስ በቀስ ወደ ሰሜን እናመራለን:: በእያንዳንዱ ሌሊት በጠላቶቻችን ላይ አደጋ እየጣልን፣ በዚያው ልክ በፍጥነት እየተንዘን ወደ ሰሜን እንገስግስና የራስ ካሣን ጦር እንይዛለን:: ከእዚያ ባይሆን ከጦሩ ጋር እስከመጨረሻው ድረስ እንዋጋለን" አልኳቸው::

ባላምበራስ አሁን ፈገግ እያሉ "እንዲህማ ከገፋን ምናልባት እስከደሴም መዝለቅ እንችል ይሆናል:: የእግዜር ፈቃዱ ከሆነ ደግሞ እስከ አዲሳባም እንገፋለን፣ ብቻ እሱ ያውቃል፣ እግዚአብሔር ያውቃል" አሉ:: ከዚህ የባላምበራስ ኪዳነ ማሪያም ንግግር በኋላ በሁሉም ወታደሮች ውስጥ ልክ አዲስ ህይወት እንደተዘራበት ሁሉ፣ ሁሉም ያላንዳች ማቅማማት የባላምበራስን ሀሳብ ተቀበሉት:: ወታደሮቻችን አሁን አንድ በአንድ እየተነሱ፣ ወደኔ በመምጣት በቀኝ እጃቸው ጠመንጃቸውን እንደጨበጡ በተጠንቀቅ በመቆም መሃላ መግባት ጀመሩ::

"በምኒልክ አምላክ፣ እስከ የመጨረሻዋ የደም ጠብታዬ ድረስ ላንተ ለፈረንጅ ጌታ እዋጋለሁ! ምንጊዜም ለጣልያኖች እጄን አልሰጥም! ጌታ ካንተ ጋር ለሀገሬ እየተዋጋሁና አንተን ከጠላቶች እየጠበቅሁ ከኢትዮጵያው ጦር ጋር እቀላቀላለሁ ወይም እወድቃለሁ::" ሁሉም በተመሳሳይ ሁኔታ ከፊቴ በተጠንቀቅ እየቆሙ፣ በምኒልክ አምላክ ስም እየማሉ፣ ታማኝነታቸውንና ቆራጥነታቸውን አረጋገጡልኝ::

አዎ ኢትዮጵያዊ በምኒልክ ስም የገባው ቃል ቅዱስ ነው:: ምንጊዜም አይሽረውም:: እና ለሁለት ቀንም ቢሆን በዚህ ሁኔታ የአርበኞች መሪ ሆንኩ:: ወዲያው ሁላችንም ላንድ አፍታ ቆም ብለን የምኒልክ አምላክ ይረዳን ዘንድ ለመንን፣ ጸለይን::

ገና አዲስ አበባ እያለሁ በርካታ አውሮፓውያን "ኢትዮጵያውያን አደጋ ላይ በሆኑ ጊዜ ብቻህን ጥለውህ ይጠፋሉ ወይም ለጠላት አሳልፈው ይሰጡሀል፣ አልያም ይገድሉሀል ወዘተ." ብለው አስጠንቅቀውኝ ነበር:: ታዲያ እነሆ ዛሬ እነዚያ

አውሮፓውያን እውነት እንደሌላቸውና ኢትዮጵያውያን በምኒልክ ስም የገቡት ቃል መሀላቸው ቅዱስ እንደሆነና በምንም ኃይል እንደማይሻር አየሁ::

አሁን የነዚህ ወታደሮች (አርበኞች) መሪ ነኝና ተፈጥሮ የጨለማ ጥላዋን ዘርግታ ከጠላት ስትሸፍነን ወታደሮቼን የተራራውን ጫፍ ለቀን በተራራው በስተጀርባ ቁልቁል እንድንወርድ "ወደፊት!" ብዬ አዘዝኩ:: ከነበርንባት የተራራ ጫፍ ላይ ሆነን እንደቃኘነው አሁን የመረጥነውን የተራራውን ጀርባ የጣልያኖች ጦር ወርሮ እታች ረባዳው ቦታ ላይ ድንኳኖቹን እንደባህር ዘርግቶ፣ እዚህም እዚያም እሳት እያነደደና በጄኔሬተር የሚሰራውን ኃይለኛውን መብራት በተራራው ወገብ ላይ አሁንም አሁንም እያበራ ተራራውን ይቆጣጠር ነበር::

ከተራራዋ ጫፍ ገና ከቀፎው እንደወጣ ንብ ግር ብለን ቁልቁል ስንወርድ፣ ከጠመንጃ የሚተኮሱ ጥይቶች መንጣጣት ጀመሩ:: እንዲህ እኛን ዙሪያ ገባውን አጥረው የምንሆነውን ይጠብቁ የነበሩት የትግራይ ሽፍቶች እላይ ከተራራው ጫፍ ላይ የሆነ ነገር እንደተፈጠረ ስለገመቱ ተኩስ ከፈቱብን:: ለዚህ ተኩስ እኛም አጸፋውን እየመለስን አቀርቅረን ቁልቁል ወረድን:: በዚህ ሁኔታ ከየአቅጣጫው ተኩስ በተኩስ ሆነ:: ጥቅጥቅ ያለ ጨለማ ስለነበር ከየትና ማን በማን ላይ እንደሚተኩስ እንኳን አይታወቅም ነበር::

በዚህ አጋጣሚ የጣልያን ጦር ቃኚና ተረኛ ዘቦች ይኼ ተኩስ የኢትዮጵያ ወታደሮች በእነሱ ላይ የከፈቱት የጥቃት ዘመቻ ስለመሰላቸው፣ እነሱም በዚሁ ጥቅጥቅ ባለ ጨለማ መትረየሶቻቸውን አናገሯቸው:: ጣልያኖች እንዲህ ጥቅጥቅ ባለ ጨለማ ምንም የሚያዩት ጠላት ባይኖራቸውም እንዲያው ዝም ብለው በይሆናል በመትረየሶቻቸው የተራራውን ወገብ ይወግሩት ጀመር::

እኛ ሁላችንም ወደ መሬት አጎንብሰን መሮጣችንን ቀጥለናል:: የጥይት እሩምታ ሲበዛ በአገኘነው ቦታ እንወድቅና በሆዳችን እንደእባብ እየተሳብን፣ ተኩሱ ረገብ ያለ ሲመስል ደግሞ አሁንም ከመሬት ላይ በግማሽ ብቻ ተነስተን እንዳጎነበስን ስንሮጥ፣ እንደገና የተኩሱ ዶፍ ጠንከር ሲል ከመሬት ወድቀን በደረታችን ስንሳብ፣ በየጥሻው ስንሽሎኮሎክ ጠንካራ ቀንጥሮች ልብሶቻችንን ቀዳደው ቡቱቱ ሲያደርጉት፣ ጠንካራ የአጋምና የተለያዩ እሾኮች መላ ሰውነታችንን ሰነጣጥቀው ደም በደም ቢያደርጉንም፣ ምንም ሳይሰማን አሁንም ወደፊት እየገፋን ነው::

በአንዲት አጋጣሚ አካባቢዬን ቃኘት ሳደርግ ከተራራው ጫፍ ስንነሳ ጀምሮ አብረውኝ የተነሱት አምስት ወታደሮች አሁንም ሁለቱ ከኔ ፊት፣ አንዱ ከግራ፣ ሌላው ከቀኝ፣ የመጨረሻው ከጀርባዬ ሆነው እኔን መሀል አስገብተው ከሁሉም አቅጣጫ አጥረውኝ አብረውኝ ስወድቅ ይወድቃሉ፣ ስነሳ ይነሳሉ፣ ስሮጥ ይሮጣሉ፣ በሆዴ ስሳብ አብረውኝ በሆዳቸው ይሳባሉ:: እስከ መጨረሻው በገዛ ገላቸው

ሊከላከሉልን ቆርጠው የተነሱ ምርጥ የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጆች፣ ስለኪንዱ እንኳን ካጠገቤ ሳይርቁ ይከተሉኛል፤ ይጠብቁኛል::

እድለኞች ነን:: የትግራይ ሽፍቶች እንዲህ ጠንካራ የጣልያን ጦር በሰፈረበት የተራራው አቅጣጫ ለማምለጥ ይሞክራሉ ብለው ስላሳሰቡ፣ ይኼንን የተራራውን ጀርባ የሚጠብቁት ሽፍቶች ኃይል በጣም ደካማ ነበር:: እንዲህ ስንወድቅ ስንነሳ፤ በሆዳችን ስንሳብ ስንንተት፤ እንደገና ተነስተን እንገብሰን ስንሮጥ ምን ያህል ጊዜ እንዳለፈ እንኳ ልብ አላልንም:: አንድ ሰዓት፤ ሁለት ሰዓት? ሶስት ሰዓት? አላውቅም:: ስለ ጊዜ ማሰብ አቆሜአለሁ:: ቢሆንም ብዙ ርቀን እንደሄድን እገምታለሁ:: ወይም ደግሞ አሁን ከጀርባችን የምንሰማው የተኩስ ድምጽ ራቅ እያለ ሄዷል::

ብዙም ሳይቆይ ይኼ የተኩስ ድምጽ ጠንከር ብሎ መሰማት ጀመረ:: ኣዎ ጣልያኖች በዚህ ሌሊት የጥቃት ዘመቻ ከፈቱብን ብለው በአሰቡት የኢትዮጵያ ጦር ላይ መልሶ የማጥቃት ዘመቻ ከፈቱበት:: በእንዲህ አይነት ሁኔታ ጣልያኖች ባለማወቅ የራሳቸውን አጋሮች በነበሩት የትግራይ ሽፍቶችን በመድፍና በመትረየስ ደበደቧቸው::

ሌሊቱን ሙሉ በየጥሻው በዚያ ድቅድቅ ጨለማ እንጨቱ፣ እሾሁ፣ ቆንጥሩ፣ ስለታማው ሾፌ ድንጋይ ሳይቀር ሰውነታችንን እየቀረደደ፣ ስጋችንን እየቦጨቀው ብዙ ወጥመድ የበዛባቸው ስርጦችን ወርደንና ወጥተን፣ ገደል እየቧጠጥን መገስገሳችንን ቀጠልን:: በዚህ መልኩ የተራራውን ጫፍ ለቅቀን ወርደን ከዚያ ተራራ ተጎራባች ከሆነ ሌላ ተራራ ወገብ ላይ ወጥተን አሁንም ተራራውን ለመውጣት እየቧጠጥን ነው:: አሁንም ከርቀት የጣልያን መድፍና መትረየሶች ሲያጓሩ ይሰሙ ነበር:: አልፎ አልፎም ከእኛው ወገን ከቀዳሚው ጦራችን አንድ ወይም ሁለት ጥይቶች ሲጮሁ ይሰማል:: ይኼም የኛ ወታደሮች የሚጠረጠር ነገር ከፊት ለፊታቸው ሲደነቀር የሚተኩሱት ተኩስ ነበር::

በዚህ መልኩ ሌሊቱን ስንፈረጥጥ አድረን አሁን መንጋት ጀመረ:: በዚህ ጊዜ ከፊት ለፊታችን ሰው የማይኖርባቸው ወና ጎጆዎች አገኘን:: ጎጆዎቹን እንዳለፍን የጊባ ወንዝ ስትንሿሿ ሰማንና ድምጹን ወደምንሰማበት አቅጣጫ ገሰገስን:: ከጊባ ወንዝ ዳርቻ ስንደርስ ቀዳሚው ጦራችን ቀድሞ ደርሶ ኖሮ በታላቅ ደስታ ተቀበለን:: ብዙም ሳይቆይ ሌሎች በቡድን በቡድን እየሆኑ ደረሱ:: ሁለት ወታደሮች ብቻ በቀጠሮው ቦታ መድረስ ሳይቻላቸው ቀረ:: በዚህ የሌሊት ፍርጠጣችን ሁለት ምርጥ ወታደሮችን አጣን፤ ምንም እንኳ ሁለት ወታደሮቻችን ከተከበብንበት የተራራ ጫፍና ከከበበን አስር እጥፍ ጦር ስር ለማምለጥ ባደረግነው ጀግንነት የተሞላበት ጀብድ መስዋትነት ቢከፍሉም፣ መስዋዕቱ ከባድ አልነበረም ማለት ይቻላል::

ወዲያው ጊዜ ሳናጠፋ አጭር ምክር አደረግን:: "የደከመው ሰው አለ?" ስል ወታደሮቼ መሀል ቆሜ ጠየኩ:: እኔ ራሴ ከዚህ አስቸጋሪና ረጅም፣ እረፍት የለሽ ሩጫ በኋላ ከሚቻለኝ በላይ እጅጉን በጣም በጣም ደክሞኛል:: ቢሆንም አሁን ምንም ጊዜ ማጥፋት እንደሌለብን ተረድቼ ነበር:: ቢያንስ ለተወሰነች ጊዜ፣ ለአንዲት ወይም ለግማሽ ሰዓት ጋደም ብል ምንኛ ደስ ባለኝ:: ግን ፈጥነን ወደፊት መግፋት አለብን፤ ወደ ራስ ካሣ:: አዎ በፍጥነት ተጉዘን ከራስ ካሣ የጦር ሰፈር በመድረስ ለራስ ካሣ ምን አይነት ትልቅ አደጋ ወደ አቢ አዲ እያመራ እንደሆነ ማሳወቅ አለብን:: ከፍተኛና በጣም አደገኛ የጣልያን ጦር ወደ አቢ አዲ ጓሮ በመግባት ላይ መሆኑን ለራስ ካሣ መናገርና ማስጠንቀቅ አለብን::

"ከኛ መካከል የደከመው ማነው?" በድጋሚ ጠየኩ:: "ማንም" ሲሉ ወታደሮቻችን በአንድነት መለሱ:: ሳይደክማቸው ቀርቶ ሳይሆን ያለንበትን ሁኔታ ጠንቅቀው ተረድተውታል:: "በቃ በጉዟችን ቀጥለን ያለምንም እረፍት አቢ አዲ ለመድረስ እንሞክራለን:: በዚህ መልኩ ከገሰገስን ነገ ጠዋት ረፋዱ ላይ ከራስ ካሣ ጦር ሰፈር መድረስ ይቻለናል" አልኩ:: ሁሉም ያለ አንዳች ቅዋሜና ማንገራገር ተስማሙ:: እና ወዲያው በጉዟችን ቀጠልን:: የጉዟችንን መስመር ትንሽ ቀልበስ አድርገን፣ እንዲህ እሾክና ቆንጥር ከበዛበት ጫካ ውስጥ ወጥተን፣ የጊባን ወንዝ ዳርቻ ተከትለን መጓዝ ስንጀምር፣ "ጠንቃቆች መሆን አለብን ጎበዝ!" ከማለቴ ካፌ ቀበል አድርገው "ልክ ነህ ጌታ:: መጠንቀቅ አለብን!" አሉና፣ ባላምባራስ ኪዳነ ማሪያም ጠንከር ጠንከር ያሉ ወታደሮችን መርጠው እንደቀዳሚና ቃኚ ጦር ወደፊት ላኳቸው:: በዚህ መልኩ ገና 20 ደቂቃ እንኳን ሳንጓዝ ቀዳሚው ጦራችን አከታትሎ ሁለት ጥይት ተኮሰ::

ወዲያው ባላምባራስ "ደግሞ ሽፍታ፣ የታባቱንስና!" እያሉ ሲራገሙ ሰማናቸው:: ሽፍቶቹ በጣም ጥቂት ስለነበሩና የኛንም ብዛት ሲገነዘቡ በፍጥነት መንገድ ለቀውልን ሸሹ:: የጊባን ወንዝ ዳርቻ እንደገና ለቅቀን፣ ከፊታችን የሚሄደው ቀዳሚው ጦር በሚቀድልን መንገድ እየተሽሎከለክን ስንጓዝ ውለን፣ ከቀትር በኋላ ተመልሰን ከጊባ ወንዝ ዳርቻ ደረስን:: አሁን ከወንዟ ዳርቻ ወደታች ወርደን በጊባ ወንዝ ውስጥ ገባን:: ቀዝቃዛው ውሃ እስከ ጉልበታችን ድረስ ውጦን በውሃው እየተንቦራጨቅን በጉዟችን ቀጠልን::

እንደገና ከውሃው ወጥተን የወንዟን ዳርቻ ይዘን ስንጓዝ ሶስት የጣልያን አውሮፕላኖች መጥተው ጥቂት ሲዞሩን ከቆዩ በኋላ ተመልሰው ሄዱ:: ግን ብዙም ሳይቆዩ ተመልሰው መጡ:: አብራሪዎቹ በትክክል አይተውናል:: እናም አውሮፕላኖቻቸውን በጣም ዝቅ አድርገው በማብረር እየዞሩን በአውሮፕላኖቹ ውስጥ በተጠመዱ መትረየሶች ይደበድቡን ጀመር:: ይኼ የመትረየስ ድብደባም አልበቃ ብሏቸው በትናንሽ

ቦንቦች ሳይቀር ወገሩን፤ ደበደቡን:: እነዚህ ከሰማይ ላይ የሚወረወሩ ቦንቦች መሬት ደርሰው ሲፈነዱ የሚያስነሱት አቧራ አፍኖ ሊገድለን ከመድረሱም በላይ ከአንዱ እርምጃ በላይ ማየት አላስቻለንም ነበር:: እናም ሁላችንም ምንም መከላከያ ከሌለው ሜዳ ላይ ተኝተን የሚሆነውን እንጠብቃለን:: እንዲሁ ሳስበው እኔም እንደ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ፋታሊስት ሆኛለሁ:: አሁን የጠላት የቁርቁር አሞራዎች ስራቸውን ጨረሱ መሰለኝ፣ ሜዳው ላይ ተኝተን አቧራ እንደለበስን ጥለውን ወደ ሰፈራቸው ወደ መቀሌ በረሩ::

በእውነቱ የአውሮፕላኖቹ አብራሪዎቹም ሆኑ መትረየስ ተኳሾቹ መጥፎና የማይረቡ ተኳሾች መሆን አለባቸው:: ምክንያቱም በዚህ ተኩሳቸውና የቦንብ ውርጅብኛቸው ሁለት ወታደሮቻችን ብቻ ነበሩ ቀለል ባለ ሁኔታ የቆሰሉት:: የቆሰሉት ወታደሮች፣ ቁስላቸው ይኼን ያህል ከባድ ሆኖ መንገድ የሚከለክላቸው ስላልነበር፣ ቁስሎቻቸውን በሸማ እራፊ እንደ ነገሩ አሳስረንላቸው በጉዟችን ቀጠልን:: በዚህ ሁኔታ ነብሳችን ልትወጣ እስክትቃረብ ድረስ ድክም ብለን የገዛ ሬሳችንን እየጎተትን ኪዳን ምህረቱ ደረስን:: ኪዳን ምህረቱ ካልሞቱት ሬሳዎች ዋሻ (ቀበሌ):: እዚህ ሽፍቶች ደፍረው ድርሽ አይሉም:: በሽታ ይፈራሉ::

ጥቅጥቅ ካለው የኪዳን ምህረቱ ጫቃ ወጥተን ወደረግረጉ ሳንጠጋ በደረቁ መሬት ላይ ተኛን:: ምንም የምንለብሰው ብርድ ልብስም ሆነ ሸማ የለንም:: ልብሶቻችንንም አጋምና ቀጋው እየቦጨቀ አስቀርቶት በላያችን ላይ የቀረው ጨርቅ ምንተእፍረታችንን ይሸፍን እንደሆነ ነው እንጂ እርቃናችንን ነን ማለት ይቻላል::

ደክሞናልና ሜዳው ላይ ዝም ብለን እንደከብቶች ተኛን:: ከረግረጉ መሬት ላይ ቀዝቀዝ ያለ አየር ይነፍሳል። ይኼ ነው የሚባል ቢንቢም ሆነ የወባ ትንኞች መከላከያ መረብ ቀርቶ ፊታችንን የምንሸፍንበት ጨርቅ ሳይኖረን እንዲሁ እርቃናችንን በሜዳው ላይ ተዘረጋን:: በአጭር ጊዜ ውስጥ በወባ ትንኞች መላ ሰውነታችንን ብንነደፍም ህመሙ ሳይሰማን እንቅልፍ ጭልጥ አድርጎ ወሰደን:: እኛ እንዲህ ድክም ብሎን ስንተኛ በአየሩ ላይ በመቶ ሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ትንኞች ክንፍ ይርገበገባል:: ከኛ ትንሽ ራቅ ብሎ የሚያስካኩ ደስተኛ ጅቦች ጩኸት እንኳን ሳይቀሰቅሰን ለረጅም ሰዓት ተኛን:: እኔንማ እንኳን የነዚህ ጅቦች ጩኸት ቀርቶ ለአጭር ጊዜ ከሽፍቶች ጋር ተደርጎ የነበረው የተኩስ ልውውጥ እንኳን አልቀሰቀሰኝም ነበር:: ከሀያ ሰዓት በላይ ያለምንም እረፍት ተጉዘን ስለ ነበር፣ እንዲያውም ሮጠን ማለቱ ይሻላል፣ እንዲህ እንደሬሳ መተኛታችን አይፈረድብንም! አያሳማንም::

ከአቢ አዲ ከወጣሁ ከ5 ቀን በኋላ የካቲት 21 ቀን ማለዳ ወደ ራስ ካሣ የጦር ሰፈር አቢ አዲ ተመልሼ ገባሁ:: ራስ ካሣ እጅጉን በጣሙን ተገርመው፣ በታላቅ

ደስታ ተቀበሉኝ:: የአስገረማቸው መመለሴ ሳይሆን፣ ምንም ሳልሆን በጤና መመለሴ ነበር:: ከአቢ አዲ በደከመኝ በቅሎ ወጥቼ፣ ከአምስት ቀን በኋላ የለበስኩት ልብስ በራሴ ላይ አልቆ፣ ጠንካራው የቱሪስት የተራራ ጫማዬ እንኳን የት ተቆራርጦ እንደ ወደቀ ሳላውቅ ባዶ እግሬን በእግሬ እየተጓዝኩ፣ መላ ሰውነቴ በደም ተጨማልቆ ወደ አቢ አዲ ተመለስኩ::

ሁሌም ደግነት የማይለያቸውና ሰውን ማበረታታት የሚያውቁበት ሽማግሌው ራስ ካሣ "አይ ፈረንጅ! እንዲያው ምክሬን አልሰማ ብለህ" ብለው ስቀው ተቀበሉኝ:: ከዚያም "አይዞህ፣ ምንም አይደል አታስብ፤ ዋናው ጤናና በህይወት መኖርህ ነው" ብለው ካበረታቱኝ በኋላ ወደደጃዝማች አበራ ሰፈር ወርጄ እንዳርፍ ላኩኝ:: ወዲያው አጋፋሪያቸውን ጠርተው የሚያስፈልገኝን ነገር ሁሉ በእስቸኳይ እንዲያሟላ አዘዙት:: ለኔም የግላቸውን አንድ ብርድ ልብስና ከፈረሶቻቸው መሀል፣ አንዱን ቆንጆና ጠንካራ ሰንጋ ፈረስ መርጠው ሸለሙኝ::



30

የራስ ሙሉጌታ ሞት

ከመቀሌ በስተደቡብ ምዕራብ በኩል ለማንም ለምንም እንደማይበገር እየተናገረ በ2,756 ሜትር ቁመቱ ላይ የተፈጥሮ ደኖቹንና ቋጥኞቹን ደራርቦ ለብሶ የአምባራዶም ተራራ ተኮፍሷል። ከዚህ አይበገሬ ተራራ ጫፍ እስከ እግሮቹ ድረስ የኢትዮጵያ የጦር ሚኒስትር የራስ ሙሉጌታ ወታደሮች የተፈጥሮ ዋሻዎችን ቤቴ ብለው፣ ድንጋዩን ትራሴ ብለው መሽገዋል።

ከየካቲት ወር መጀመሪያ ላይ ጀምሮ የጣልያን አውሮፕላኖች ያለማቋረጥ ከጠዋት እስከ ማታ ራስ ሙሉጌታን ከሙቶ ሺ በላይ ከሚቆጠረው ሰራዊታቸው ጋር ይደበድባሉ። እነዚህ የራስ ሙሉጌታ ወታደሮች ከጠዋት ጀምረው ጀንበር እስክትጠልቅ ድረስ በዋሻዎች ውስጥ ተጨናንቀው ይውሉ ነበር። ራስ ሙሉጌታ ማርሻል ባዶሊዮ በታንኮችና በመድፎች ምትክ በአውሮፕላኖች ድብደባ ጦራቸውን ፊታ ሊነሳባቸው ማሰቡን ዘንግተውታል። ይኼ የማርሻል ባዶሊዮ የጦርነት ስልት፣ የራስ ሙሉጌታ ጦር ሞራሉ ላሽቆ ወኔው ሲሰበር አምባራዶምን ለመያዝ ለሚጠባበቀው ሰራዊቱ በር ከፋችና መንገድ ጠራጊ ነበር።

ምንም እንኳን የራስ ሙሉጌታ ሰዎች በተከታታይ የማርሻል ባዶሊዮን ሰራዊት እንቅስቃሴ የሚጠቁሙ መረጃዎች በተደጋጋሚ ቢያቀርቡም፣ እነዚህ ባላገሮች ሰብስበው የሚያመጧቸው መረጃዎች የተቆራረጡና ዝብርቅርቃቸው የወጣ፣ ትርጉም የማይሰጡ ስለነበሩ፣ ራስ ሙሉጌታ ስለ ማርሻል ባዶሊዮ ሰራዊት እንቅስቃሴ ምንም አይነት ግምት አልነበራቸውም ማለት ይቻላል።

ራስ ሙሉጌታ ከነሰራዊታቸው ቀኑን በዋሻ ውስጥ ሲያሳልፉ፣ ማርሻል ባዶሊዮ የተንቤኑ ሽንፈት እንዳይደገምበት በጥንቃቄ የጦር ስልቱን ነድፎና ሰራዊቱን አደራጅቶ አምባራዶምን ለመያዝ በተጠንቀቅ ቆሞ ነበር።

አንደኛውንና ሁለተኛውን ክፍለ ጦሩን ከበርካታ ብረት ለበስ ተሽከርካሪዎችና ከባድ መሳሪያዎች ጋር፣ 40 ሻለቃ ጦርና 170 መድፎች ጋር፣ በመቀሌ በተጠንቀቅ አቁሞ፣ ጠቅላላውን የኤርትራ ተወላጆችን ሰራዊት ከ30 ሻለቃ ጦርና 76 መድፎች ጋር ወደ ተንቤን ልኮ አደራጅቷል። ገና አሁን ከጣልያን ወደ አፍሪካ የገባውን ትኩሱን ጦሩን 44 ሻለቃ ጦር ከ173 መድፎች ጋር አክሎበት 4ኛውን ክፍለ ጦር ወስዶ በስተምዕራብ በሱዳን ድንበር በኩል አቆመው።

ከዚህ ሁሉ ፍጹም ጥንቃቄ ከተሞላበት የማርሻል ባዶሊዮ ዝግጅት በኋላ መደራጃ ቀርቶ ደጅ መውጫ ካልነበረው የራስ ሙሉጌታ ጦር ጋር አምባራዶምን ለመያዝ፣ በትኝ ገገርዎች ታሪክ ተወዳዳሪ የሌለው ከፍተኛው የሞት ሽረት ውጊያ ተካሄደ።

የካቲት 10 ቀን ንጋት ላይ ጨለማንና የጠዋቱን ጉም ጥላ በማድረግ እጅጉን በከባዱ የተጠናከሩት ሁለቱ የጣልያን ክፍለ ጦሮች፣ 3 ዲቪዥን ሙሉ የጣሊያን ወታደሮች፣ ከሁለት ሻለቃ በላይ የኤርትራ ተወላጆችና በ2 ሜካናይዝድ መድፈኛ ብርጌዶች እየተረዳ ከመቀሌ ተነስቶ ወደ አምባራዶም ተራራ ድምጹን አጥፍቶ ተጠጋ።

በሚቀጥሉት ሁለት ቀናት ውስጥ ይኼ ዘመናዊና በጣም ጠንካራ ጦር አምባራዶምን ከበባት። ደፋሮቹና ጀግኖቹ ቀዳሚዎቹ የራስ ሙሉጌታ ወታደሮች በሹሞቻቸው እየተመሩ ወደፊት በመግፋት ላይ ያለውን የጠላት ጦር ለመግታት ቢጥሩም ሊያቆሙት አልቻሉም። ከሚቻላቸው በላይ ሆነባቸው። አንዳንድ ቆራጥና ጀግና ሹሞች ከጥቂት ወታደሮቻቸው ጋር የዘመናዊውን የጣልያን ወታደሮች ደካማ ጎን እየፈለጉ ወገቡን እየሰበሩ ወደ መሀል መግባት ቢቻላቸውም፣ ከኋላ እሳት የሚተፉት መድፎችና መትረየሶች አላነቃንቅ አሏቸው። እንዲህም ሆኖ ጀግኖቹ ቀዳሚዎቹ የራስ ሙሉጌታ ወታደሮች በመጀመሪያው ቀን ጦርነት በዘመናዊው የጠላት ጦር ላይ ከፍተኛ ጉዳት አደረሱ።

ከአንድ ቀን እረፍት በኋላ ማርሻል ባዶሊዮ እረፍቷን በመጠቀም በመጀመሪያው ቀን ጦርነት ከባድ ጉዳት የደረሰበትን ጦሩን እንደገና አሰባስቦ የካቲት

ለመያዝ በሁሉም አቅጣጫ የማጥቃት ውጊያ 15 ቀን ማለዳው ላይ አምባራዶምን ከፈተ።

ምንም እንኳን ጣሊያኖች በቁጥርም ሆነ በመሳሪያ ጥራት ኢትዮጵያውያንን ቢበልጡም፤ በተለይ ሁለቱ ጦሮች የተጠቀሙትን መሳሪያ ማወዳደር ባይቻልም፤ ጀግኖቹ ምርጥ የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጆች ያለ አንዳች ፍርሃት በታላቅ ጀግንነት የጠላትን ጦር ወጥረው ሲያርበደብዱት ዋሉ። በተለየዩ የጦር አውድማዎች ወንድ ለወንድ የጨበጣ ውጊያዎች ተካሄዱ። በዚህ የጨበጣ ውጊያ ሁሌም ጀግኖቹ የራስ ሙሉጌታ ወታደሮች ይረቱ ነበር። የጠላትን አንገት በጎራዴያቸው ሲቀሉት ወደር አልነበራቸውም።

ከእንዲህ አይነት ፍጹም ጀግንነት ከተሞላበትና ናላ ከሚያዞር ውጊያ በኋላ ለአጭር ጊዜም ቢሆን ጣሊያኖች ማፈግፈግ ጀመሩ። ውዶቹ የራስ ሙሉጌታ ወታደሮች ሽሽት የጀመረውን የማርሻል ባዶሊዮ ወታደር እያባረሩ ቂጡን በጦር ወጉት። ይኼንን ሁኔታ ቀድሞ የገመተው ማርሻል ባዶሊዮ፣ የሚሸሸውን ወታደሩን ቀድሞ በአዘጋጀው የደጀን ጦር ተካው። ድካም የማያውቁት፣ እስከመጨረሻዋ ደቂቃ ድረስ ሽንፈትን የማይቀበሉት፣ የራስ ሙሉጌታ ወታደሮች ምርጦቹ የኢትዮጵያ ልጆች በውጊያ፣ በጦርነቱ አውድማ፣ እስከምሽቱ ድረስ ቆዩ። ከረፋዱ ጀምሮ ቀኑን ሙሉ ከሰማይ እንደ ነሐሴ ዝናብ ቦምብ ሲወርድበት፣ በምድር የመድፍና የመትረየስ ጥይት ሲቀጠቀጠው ለዋለውና ላመሸው ጦራቸው፣ ራስ ሙሉጌታ ምሽቱ ላይ ጦሩ አምባራዶምን ለቅቆ እንዲወጣ ትዕዛዝ ሰጡ።

ራሳቸው ራስ ሙሉጌታ የሚመሩት ጦር እንደዚያ ደክሞ እኩለ ሌሊት ግድም ላይ በደቡብ በኩል የጣልያንን ጦር ወገብ ሰብሮ በር በማስከፈት ከተከበበት አምልጦ ወደ አምባላጌ ወረደ።

ማርሻል ባዶሊዮ በአምባራዶሙ ጦርነት ከ15,000 ወታደሮች በላይ አጣ። የራስ ሙሉጌታም ጉዳት እንደ ማርሻል ባይሆንም፣ በአምባራዶም ከ12,000 እስከ 20,000 የሚደርሱ ውድ ኢትዮጵያውያን ጀግኖች የህይወት መስዋዕትነት ከፍለዋል። "Affidavo all'aviazione il proseguimento della battaglia mediante l'inseguimento del nemico" ሲል ማርሻል ባዶሊዮ ማስታወሻውን ፅፎ፣ በዚያው ቀን ምሽት ለአየር ኃይል አዛዡ ባስተላለፈው ትዕዛዝ፣ "ሰብሮ የወጣውንና ወደ አምባላጌ በማምራት ላይ ያለውን የራስ ሙሉጌታን ጦር እየተከታተለ ያለምንም ምህረት በቦምብ እንዲደበድብ" ጥብቅ ትዕዛዝ ሰጠ። የሚሸሹትን የራስ ሙሉጌታን ወታደሮች፣ በማርሻል ባዶሊዮ ልዩ ትዕዛዝ፣ በሚፈነጣጠሩ፣ እሳት በሚተፉና በጭስ መርዝ ቦንቦች ሳይቀር እየተከታተሉ ደበደቡት።

ከእንዲህ አይነቱ ናላ ከሚያዞር አድካሚ ጦርነት በኋላ አበሳቸውን ሲያዩ የዋሉና በድካም ሰውነታቸው የዛሉ የራስ ሙሉጌታ ወታደሮች አምባራዶምን ለቅቀው

በሁለት መንገድ ወጡ። የመጀመሪያው በራሳቸው በራስ ሙሉጌታ የሚመራው ቡድን በስተደቡብ በኩል ሰብሮ ከወጣ በኋላ ወደ አምባላጌ አመራ። ሁለተኛው ቡድን ደግሞ በዚያው ትይዩ ከከፍተኛ ተጋድሎ በኋላ የጣልያንን ሰራዊት ወገብ ሰብሮ ከወጣ በኋላ የጠላትን 1ኛ ክፍለ ጦር በጀርባው አዝሎ ወደ ሰቆጣ የሚወስደውን መንገድ ያዘ።

በሁለቱም አቅጣጫ በመሸሽ ላይ ላለው የራስ ሙሉጌታ ጦር የኋላ ደጀን ሆኖ ሽፋን የሚሰጠው ጦር በጥሩ ሁኔታ 1ኛውን የጠላት ክፍለ ጦር ወጥሮ በመያዝ አላንቀሳቅስ ቢለውም፣ በሰማይ እየበረሩ ፈጣሪን እንኳን ሳይፈሩ የቦንብና የጢስ መርዝ ከሚያወርዱበት ለመከላከል ግን ፈጽሞ አልተቻለውም ነበር። ቢያንስ ከነዚህ አውሮፕላኖች ለመትረፍ የነበረው ብቸኛ አማራጭ፣ በጋራ ተሰልፎ ጠላትን መግጠሙን ጥሎ በፍጥነት ተበታትኖ ወደ ጫካው፣ ወደ ዱሩ ውስጥ መግባት ብቻ ነበር። ይኼ ደግሞ ለበለጠ መጥፎ አውሬ ጠላት አሳልፎ ሰጣቸው።

የራስ ሙሉጌታ ወታደሮች የጣልያን አውሮፕላኖች እንደደፍ ከሚያወርዷቸው ቦንቦችና የጢስ መርዞች ለማምለጥ በቻሉት ፍጥነት በየጫካውና በየጢሻው እየገቡ ሲበተኑ፣ቀድሞ መሽጎ ይጠብቃቸው የነበረው የራያና አዘቦ አረመኔ ሽፍታ በጣልያን መሳሪያ እያለመ ለቀማቸው።

ገና ጦርነቱ ከመጀመሩ በፊት ጣልያኖች በወኪሎቻቸው አማካኝነት ሰርጎ ገቦችን እየላኩ የራያና አዘቦን ሰዎች ገንዘብ እየሰጡና ዘመናዊ መሳሪያ እያስታጠቁ በነዛ ወንድሞቻቸው ላይ እንዲዘምቱ አደረጋቸው።

እነዚህ የራያና አዘቦ ከሀዲ ሽፍቶች ጦርነቱ በተጀመረ ሰሞን ጀምሮ ከመሀል ሀገር ተነስቶ ወደ ጦር ሜዳ የሚገሰግሰውን የኢትዮጵያ ጦር አሳቻ ቦታ እየጠበቁ ዘረፉት፣ ገደሉት። እነሆ ዛሬ ከስድስት ወር በላይ በሰሜን ኢትዮጵያ ፍዳውን ሲያይ ኖሮ፣ በትናንቱ ጦርነት ተሸንፎ፣ በመሸሽ ላይ ያለውንና ነፍሱ እስክትወጣ የደከመውን የራስ ሙሉጌታን ሰራዊት እንዲህ ተበትኖ አገኙት። በጥይት ኢላማቸው ያልገባላቸውን፣ ደክሞት በየዛፉ ጥላ ስር ያረፈውን፣ በንቅልፍ እጦት ሲሰቃይ ሰንብቶ ለአፍታ ጋደም ያለውን ሰራዊት ድምፃቸውን አጥፍተው እየተጠጉ፣ በጩቤ ከጊዳው እየወጉ ገድለው የመጨረሻ ንብረቱን ዘረፉት።

ሽማግሌው የጦር ሚኒስትር ራስ ሙሉጌታ ከልጃቸው ጋርና በመቶዎች ከሚቆጠሩ የመጨረሻዎቹ ታማኝ ወታደሮቻቸው ጋር አምባላጌ በሰላም ደረሱ። የአይን ምስክሮች እንደተናገሩት ራስ ሙሉጌታ በዚህ ጦርነት እንደማንም ተራ ባላገር ወታደር ሁሉ በታላቅ ጀግንነት በግንባር ከነልጃቸው በጦርነቱ ተሳትፈዋል። ራስ ሙሉጌታ ከኋላ እንደጥላ እየተከተለ ከሚያድናቸው 1ኛው ክፍለ ጦር፣ ከሰማይ ላይ ሆኖ እያንገበበ እንደመርፌ ከሚፈልጋቸው አውሮፕላን ሁሉ አምልጠው! የአሸንጌን ሐይቅ በመሻገር ላይ እንዳሉ እድል ፊቷን አዞረችባቸው።

ይኼንን ሁሉ መከራና ፍዳ ተወጥተው፣ ስራዊታቸውን በታላቅ ጀግንነት መርተው፣ በግንባር ከጠላት ጋር ተፋጠው እንዳልተዋጉ ሁሉ የአሸንጌ ሐይቅ አትሻገሩኝም አለች፡፡ ከፈረንሳይ ሀገር የጦር-ታደራዊ ትምህርቱን አቋርጦ በመጣው ልጃቸው ታጅበው የአሸንጌን ሐይቅ በፈረሳቸው ላይ ተቀምጠው በመሻገር ላይ እንዳሉ፣ ታልመው በተተኮሱ ሁለት የራያና አዘቦ ሽፍቶች ጥይት ተመተው ወደቁ፡፡ ከፊት ለፊቱ ከፈረሳቸው ላይ ዘንበል እያሉ የወደቁትን አባቱን ለመርዳት ከፈረሱ ላይ ዘሎ በመውረድ አባቱን ለመደገፍ ጎንበስ ያለውንም ልጃቸውን ታልመው፣ ተደጋግመው የተተኮሱ ጥይቶች በአባቱ ራሳ ላይ ጣሉት፡፡

እድለቢሱ የጦር ሚኒስትር "ራስ ሙሉጌታ" የአሸንጌን ሐይቅ ለመሻገር ሲሞክሩ ቀድሞ መሽጎ ይጠብቃቸው የነበረው የራያና የአዘቦ ጦር ወደ 15,000 ገደማ ይደርስ እንደነበረና፣ በጣልያኖች መሳርያ ጥሩ ሆኖ ታጥቆና ተዘጋጅቶ እንደነበረ በኋላ የአይን ምስክሮች ተናግረዋል፡፡ ሆነም ቀረ ከዚህ አስከፊ ጦርነት የተረፉት ወታደሮቻቸው፣ ራስ ሙሉጌታን ለመርዳት ከኮረም ተነስቶ ከነበረው ከራስ ጌታቸው ጦር ጋር ከተወሰኑ ቀኖች በኋላ ተቀላቀሉ፡፡

ከዚህ ሁሉ በኋላ 1ኛው የጣልያን ክፍለ ጦር ያለብዙ ችግር የካቲት 28 ቀን ባንዲራውን በአምባላጌ ተከለ፡፡

31

የራስ ካሣ ጦር ወጥመድ ውስጥ

ከየካቲት ወር አጋማሽ ጀምሮ እነዚያ የተረገሙ የጣልያን አውሮፕላኖች ከንጋቱ ጀምሮ እስከ ማምሻው ድረስ እየተመላለሱ በሚጥሏቸው ቦንቦች የአቢ አዲ ከተማ ህጻናት፣ እናቶች፣ አሮጊቶች ልክ በረዶ እንደወረደበት አበባ እዚህም እዚያም በየቀኑ ይረግፋሉ፡፡

እነዚህ ጨካኝ አረመኔ፣ አውሬ የአውሮፕላን አብራሪዎች ሁለቱን ጥንታውያኑን የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያናት እንኳ ሳይቀር አልማሯቸውም፡፡ አቢ አዲ ከምድር ገጽ ለመጥፋት ተቃርባለች፡፡

አቢ አዲ እንዲህ በቦንብ እሳት ስትነድ፣ ለወታደሮቻችን፣ ለሚስቶቻቸውና ለልጆቻቸው፣ በጠቅላላው ለራስ ካሣ ጦር የነበረን አንድ አውሮፓዊ ዶክተር ብቻ ነበር፡፡ እሱም ዶክተር ሹፕለር ሲባል ዜግነቱ ኦስትሪያዊ (ነምሳዊ) ነበር፡፡

ከዚሁ የኦስትሪያ ተወላጅ ከሆነው ዶክተራችን ቀጥሎ እንደነገሩ የተደራጀችና እምብዛም የሚረባ የህክምና መሳሪያ ያልነበራት የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ከአንድ ህንዳዊ፣ አህመድ ከሚባል ዶክተር ጋር በአየርላንዳዊው ካፒቴን ሄስኬይ (Cap. Hickey) እየተመራች የካቲት 8 ቀን አቢ አዲ ገባች፡፡

በዚሁ ቀን ማምሻው ላይ በጦር ሜዳ ጀግንነታቸው ወደር የሌላቸውና የማይገኝላቸው ወደ 15,000 ገደማ የሚሆኑት የከንባታ ተወላጆች በጀግናው መሪያቸው በደጃዝማች መሸሻ እየተመሩ ከ900 ኪሎ ሜትር በላይ በእግራቸው ተጉዘው አቢ አዲ ገቡ።

በዚቹው ቀን ምሽት ደጃዝማች መንገሻ ሂልሚና ደጃዝማች በየነ ከነጦራቸው ተጉዘው ከከንባታ ልጆች ጋር በዚያው ምሽት እስካሁን በልጁ ስለደረሱ፤ ደከመኝን ከማያውቁት የከንባታ ልጆች ጋር በዚያው ምሽት እስካሁን ጦር ብቻ ሲጠበቅ የነበረውን ቦታ በስተሰሜን በደብረ አምባ በኩል የጽኚን የወንዝ ዳርቻ ይዘው መሸጉ።

በዚሁ ሰሞን ለራስ ሙሉጌታ ጦርም አነስተኛ የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ከሁለት የፖላንድ ተወላጅ ዶክተሮች ጋር ተልከላቸው ነበር። ይሁን እንጂ፣ ሁለቱ የፖላንድ ዶክተሮች በመጀመሪያው ቀን የአምባራዶም ጦርነት ስራቸውን እንኳን ሳይጀምሩ በጣሊያኖች ምርኮ ስር ወደቁ።

ጣሊያን በእንግሊዝና በፈረንሳይ ሙሉ በሙሉ ተደግፋ በማን አለብኝነት ኢትዮጵያን በወረረችበት ሰሞን፣ በጠቅላላው በሰሜኑ የጦር ግንባር አራት ፈረንጆች ብቻ ነበርን፤ 3 አውሮፓውያን (ስሎቫንያውያን) እና አንድ ኩባዊ፣ አሁን ወደ ጦርነቱ ፍጻሜ ስንቃረብ ቁጥራችን ወደ ዘጠኝ አደገ። አምስት ስሎቫንያውያን፤ ሁለት ቼኮዝሎቫኮች፣ እኔና ቪሌም ብረየር። ሁለት የፖላንድ ዶክተሮች በጣልያኖች ተማርከዋል። አንድ ህንድ አህመድ የሚባል ዶክተር፤ አንድ ኦስትሪያዊ የነምሳ ሰው ሹፐለር (Dr. Schuppler)፤ ብቸኛው የሰሜኑ የጦር ግንባር ዶክተር። አንድ አየርላንዳዊ ካፒቴን ሄስኬይ (Capitain Hickey)። አንድ ኩባዊ፣ አሌሳንድሮ ዴል ቫል፣ "ቀይ አንበሶች" የሚል መጽሐፍ ጽፏል፤ ወደ አማርኛም ተተርጉሟል። አንድ ሩሲያዊ ፌኦዶር የቭገኒቪች ኮኖቫሎቭ፣ የኢትዮጵያም ዜግነት አለው፤ Con le armate Del Negus የሚል መጽሐፍ ጽፏል።

ገና ጦርነቱ እንደተጀመረ ግድም ከ200 በላይ የውጭ ሀገር የጦር ሜዳ ዘጋቢ ጋዜጠኞች ወደ ኢትዮጵያ ቢገቡም፣ በሰሜኑ የጦር ግንባር ግን አንድም የጦር ሜዳ ጋዜጠኛም ሆነ ዘጋቢ አልነበረም። ከነዚህ የጦር ሜዳ ዘጋቢዎችና ጋዜጠኞች ውጪ ንጉሠ ነገሥቱ የኢትዮጵያን ሰራዊት ይረዱ ዘንድ የተቀበሏቸው ለቁጥር የማያስቸግሩ በጎ ፈቃደኛ ከፍተኛ የጦር መኮንኖችና የጦር አማካሪዎች ወደ አዲስ አበባ ቢገቡም፣ በጣት ከሚቆጠሩ በደቡብ ግንባር ከተሰለፉት የጦር መኮንኖችና አማካሪዎች በስተቀር የቀሩት ያለምንም ስራ አዲስ አበባ ወይም ደሴ ከጦር ግንባር በመቶዎች ኪሎ ሜትር ርቀው ይንደላቀቁ ነበር።

በዘመናዊ መልኩ የተደራጁ በርካታ ዶክተሮችንና አስታማሚዎችን ከበቂ መድሀኒት ጋር ያቀፉ በርካታ የአውሮፓ ቀይ መስቀል ማህበሮች ኢትዮጵያን በጦርነቱ ሊረዱ ወደ ሀገር ውስጥ ገብተዋል።

የሲዊዲን፣ የፊንላንድና የግብፅ ቀይ መስቀል ማህበሮች በደቡብ የጦር ግንባር ስራቸውን ቢጀምሩም፣ ምን ያህል ከጦር ሜዳ ርቀው እንደሆነ ግን አላወቅም። በብዛትም ሆነ በጥራት ኢትዮጵያ ውስጥ ከገቡ ቀይ መስቀል ማህበሮች መካከል ተወዳዳሪ የሌለው የእንግሊዞቹ ቀይ መስቀል ማህበር ከንጉሠ ነገሥቱ ጦር ጋር ደሴ ነበሩ። አፄ ኃይለ ሥላሴ ከነጦራቸው ከደሴ ድንኳን ነቅለው ወደ ኮረም ሲያመሩም የእንግሊዞች ቀይ መስቀል ማህበር እንዳጀባቸውም ሰምተን ነበር።

የሆላንድ (ኔዘርላንድ) ቀይ መስቀል ማህበር ደግሞ በደሴና በኮረም መካከል መሀል መንገድ ወልዲያ ላይ ድንኳኑን ጥሎ ተቀምጧል። በትክክል በሰሜኑ የጦር ግንባር የነበሩት ግን ሁለቱ የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማህበሮች ሲሆኑ ስለነበራቸው የህክምና መሳሪያም ሆነ መድሀኒት ግን ባይወራ ይሻላል። እዚህ ግባ የሚባል አልነበረም። ቁምነገሩ ምንም እንኳ ምንም የረባ የህክምና መሳሪያም ሆነ መድሀኒት ባይኖራቸውም በጦር ግንባር ደርሰው ስራቸውን ጀምረው ነበር።

በኛ የጦር ሰፈርም ዶክተር ሹፐለር ገና ከመድረሱ ስራውን ጀምሯል። ወታደሮቻችን ከአቢ አዲ በስተደቡብ ከተራራው ጥግ አንድ ሰስት የሚሆኑ አነስተኛ ቆሻዎችን አጽድተውለት በጣት የሚቆጠሩ ከፉኛ የተጎዱ ቁስለኞች ተኝተውበታል። አብዛኛው ቁስለኛና በሽተኛ ግን የአርባ ቀን እድሉን እያሰበ ለነዚያ ምትዜሮ አውሮፕላኖች አውላላ ሜዳ ላይ እንደብቅል ተሰጥቷል።

ዶክተር ሹፐለር ወደ ሰሜን ጦር ግንባር ጉዞውን ሲጀምር በመንገድ ላጋጠሙት ቁስለኞችና በሽተኞች ከያዘው መድሀኒት ሲቀንጥር፣ የመድሀኒቱ ክረጢት ጦር ግንባር ሲደርስ እጅጉን ሳስቶ ስለነበር፣ ያለብዙ ህመም ማስታገሻ መድኃኒት እጅግ በጣም አስቸጋሪ የሆኑ ቀዶ ጥገናዎችንና ታክመው ሊድኑ የማይችሉ አጥንታቸው የደቀቁ እግሮችንና እጆችን የመቁረጥ ስራውን፣ ከዋሻዎቹ ደጃፍ ላይ ባስተከላት ሰፋ ያለች ድንኳን ውስጥ ህይወቱን አደጋ ላይ ጥሎ ደከመኝ ሳይል ከጠዋት እስከ ማታ ያለ እረፍት ይሰራ ነበር።

ጣልያኖች እንዲህ አቢ አዲን ከታሪክ ገጽ ላይ ለማጥፋት ከጠዋት እስከማታ የቦንብ ውርጅብኝ ሲያወርዱባት "ለምን ድንኳኗ ላይ የቀይ መስቀል ምልክት እንደማያደርግባት" በመጀመሪያው ቀን ጉብኝቴ ዶክተር ሹፐለርን ጠየኩት። ዶክተር ሹፐለር "አይ አንተ፣ አሁን ይኼ ጠፍቶህ ነው?" አለና፣ "ጣልያኖች ሆን ብለው የቀይ መስቀል ምልክት ያለባቸውን ጎጆዎች፣ ቤቶችና ድንኳኖችን አሳድደው ይደበድባሉ" አለኝ። የጣልያን ፕሮፓጋንዳ ለዓለም ህዝብ ሲዋሽና ይኼን አሳፋሪና አረመኔያዊ የአብራሪዎቹን ድርጊት ሲሸፋፍን፣ የኢትዮጵያ ወታደሮች ሆን ብለው በድንኳኖቻቸውና በመሳሪያ ግምጃ ቤቶቻቸው ላይ የቀይ መስቀልን የተቀደሰ ምልክት ይቀባሉ ሲል ዋሸ።

በኋላ ላይ የተለጠፉ የአውሮፓ ሀገሮችን የቀይ መስቀል ማህበር ድንኳኖች በቦንብ ሲደበድቡ፤ ለአረመኔያዊ ድርጊታቸው ማስተባበያ በነዚህ የቀይ መስቀል ማህበር ድንኳኖች ውስጥ ጤነኛ የኢትዮጵያ ወታደሮች ተደብቀው አግኝተን ነው ሲሉ በድጋሚ የዓለምን ህዝብ በተለመደ ውሸታቸው ለማታለል ሞከሩ።

ከጦርነቱ ጅማሬ እስከ ፍጻሜው ድረስ በሰሜኑ የጦር ግንባር አንድ እንኳን የራስ ካሣና የራስ ሥዩም ወታደሮች ድንኳን በቀይ መስቀል ምልክት ተቀብቶ ቢገኝ አንገቴን እሰጣለሁ ስል በንጹህ ልብ እምላለሁ። የኢትዮጵያ ወታደሮች እንዲህ አይነት ተራና ርካሽ የማታለል ተግባር አይፈጽሙም። በጣም ሲበዛ ኩሩና ጀግኖች ነበሩ። እርርትም ቢባሉ አያደርጉትም።

ይሁን እንጂ በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል የጣልያን አብራሪዎች ከትላልቅ ከተሞች እስከ ትናንሽ መንደሮች ድረስ ቀይ መስቀል የተቀቡ ቤቶች ሲገጥማቸው እንደሚጥሉ አጠራጣሪ አይደለም። ሁላችንም እንደምናውቀው ጣልያኖች ስለኢትዮጵያ ከኢትዮጵያውያን በላይ፣ ስለአኗኗራቸውና ስለባህል ታሪካቸው አሳምረው ያውቃሉ። በከተማና በገጠር መኖሪያቸውን በቀይ መስቀል ማስጌጥ በኢትዮጵያ ከጥንት ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ባህል እንደሆነና፣ እነዚያ ቤቶች ለዓለም ህዝብ ሲዋሹት እንደሚሞክሩት የመሳሪያ ግምጃ ቤቶች ሳይሆኑ ተራ የሴተኛ አዳሪዎች ቤቶች መሆናቸውን ልባቸው እያወቀ ያለምንም ርህራሄ በቦንብ እሳት አንድደዋቸዋል።

ከየካቲት 21 በኋላ ወደ ጦር ሰፈራችን በቡድን በቡድን እየሆኑ፣ ሸማቸው በላያቸው ላይ ከመበጫጨቁም በላይ እስኪሞቱ የደከሙ የራስ ሙሉጌታ ወታደሮች የከበባቸውን የጠላት ጦር ጥሰው በመውጣት ወደተንቤን በመጉረፍ፣ ከሁለቱ ራሶች ጦር ጋር መቀላቀል ጀመሩ።

እነዚህ የደከሙ ወታደሮች በተመሳሳይ ሁኔታ የራስ ሙሉጌታ ጦር በጠላት ጦር መሸነፉንና አምባራዶም በጠላት እጅ መቶ በመቶ መውደቁን መስክረዋል። ወደአቢ አዲ የሚወስዱ ሁሉም መንገዶች በጣልያን እጅ እንደገቡም አከለው ተናግረዋል። ከዚህ ምስክርነታቸው በተጨማሪ የሁለቱ ራሶች ጦር አደገኛ ሁኔታ ላይ መሆኑንና የጣልያን ሰራዊት ከደቡብ ወደተንቤን እየገሰገሰ መሆኑን አስጠንቅቀዋል። እነዚህ ምስኪኖች ከድካማቸው እንደነገሩ ከአረፉና እህል ውሃ ከቀማመሱ በኋላ በራስ ካሣ ጦር ስር እንዲመጣጣቸው ተመድበው፣ ከአንድ የጦርነት እሳት አምልጠው፤ ለሌላ ጦርነት፣ ለሌላ ውጊያ ምሽጋቸውን ያዙ።

በጦር ሰፈራችን ሁለቱ ራሶች ከሹማምንቶቻቸው ጋር ጠዋትና ማታ ይመክራሉ። ይኼ የጦር ሜዳ ምክር ቤት አንዴ ተራራውን ተጠግተው ካሉ ዋሻዎች ውስጥ ሌላ ጊዜ ደግሞ እታች አቢ አዲ ውስጥ ያለማቋረጥ ቦታ እየተቀያየረ ይካሄዳል። የኢትዮጵያው የጦር ሹማምንቶችና የጦር አበጋዞች እንዲህ ያለማቋረጥ ቦታ እየለዋወጡ ሲመክሩ፣ የጣልያን ጦር ወደተንቤን እየተቃረበ መጣ። በእያንዳንዷ

ምሽት የጠላት ሰራዊት የሚያበራው መብራት በያንዳንዷ ምሽት ወደ ጦር ሰፈራችን መቃረብ መጀመሩን እያስተዋልን፣ አሁንም ሳናሰልስና ሳንሰላች እንዴት የጠላትን ጦር መመከት እንዳለብን እንመክራለን። የሁለቱ ራሶች ጦር አደጋ እየመጣበትና በጣም በአስከፊ ሁኔታ ላይ እየወደቀ ነው።

ሁሉም ወታደሮቻችን መሳሪያ አልታጠቁም። መሳሪያ ለታጠቁትም በአማካኝ ለየአንዳንዱ ባለጠመንጃ ቢበዛ 20 ጥይት ቢደርሰው ነው። ሌላው የጦራችን መሳሪያዎች በጣም የተወሰኑ፣ በጣት የሚቆጠሩ አርጀት ያሉ መትረየሶች፣ አራት እርሊኮን (Oerlikon) አውሮፕላን መቃወሚያዎችና በታላቁ የአደዋ ድል ጊዜ በ1896 ዓ.ም. ከዚሁ ዘመናዊ ጠላት እጅ የተነጠቁ ወደ ሙዚየም መግባት የሚገባቸው መድፎች ናቸው። በጥቅሉ ለነዚህ ሁለት አሮጌ መድፎች የነበሩት 27 ጥይቶች ብቻ ነበሩ። እነዚህን ጥይቶች መቁጠር ከባድ አልነበረም። እያንዳንዷን ጥይት በስልቻ ከትቶ በአንድ አህያ ጭኖ የሚሮጠውን የኢትዮጵያ የገበሬ ወታደር ስቃይ ለአምስት ወራት ስላየሁ፣ 27ቱን ጥይቶች ከመቁጠሬም በላይ፤ አንድ ሹም ጥር መጀመሪያ 20ዎቹን ጥይቶች ደብረ አምባ አፋፍ ላይ መድፉን ተክሎ፣ በወቅቱ ወራዶ ላይ ሰፍሮ የነበረውን ጠላት ለመደብደብ ተኩሷቸዋል። ሁሉም መሀል መንገድ ላይ ኢላማቸውን ሳይመቱ ፈንድተዋል።

በተቃራኒው ማርሻል ባዶሊዮ ለወሳኙ ውጊያ ከራስ ካሣ ጦር የማያንስ ብዛት ያላቸው ወታደሮቹን አሰልፏል። ይሁን እንጂ የማርሻል ባዶሊዮ ጦር ፍጹም በዘመናዊ መልኩ የተደራጀና ዘመኑ ያፈራቸውን ዘመናዊ መሳሪያዎች ቁጥር ስፍር ከሌለው ጥይት ጋር የታጠቀ፤ በምድር በታንኮች፣ በረጅምና አጭር ርቀት አልመው የሚመቱ መድፎች፣ መትረየሶች እንዲሁም ከባድ ብረት ለበስ ተሽከርካሪዎች ያሉት ሲሆን፤ በሰማይ ደግሞ በእነዚያ ስፍር ቁጥር የሌላቸው የሞት ዝናብ አዝናቢዎቹ አውሮፕላኖች ቀድመው መንገድ የሚጠርጉለት ጦር ነው። ይኼ የማርሻል ባዶሊዮ ጦር እንዳይራብና እንዳይጠማ ስንቅና ትጥቁን ጭነው ከኋላ የሚከተሉት በርካታ የጭነት መኪኖች አሉት። እንግዲህ የማርሻል ባዶሊዮ ጦር በዚህ መልኩ ተደራጅቶ፤ ተሰልፎና ሞራሉን ገንብቶ፣ ሆዱን ሞልቶ፣ ወደፊት ሲል፤ እኛ ከዋሻዎች ወደ ዋሻዎች እየተዘዋወርን የጦር ምክራችንን ቀጥለናል።

ከኛ ብዙም ሳይርቅ በአጎራባች ቀበሌዎች በወራዶና በአባሮ የጦር ሰፈር ስምንት ዲቪዥን ሙሉ የኤርትራው ጦር ሰፍሮ ምሽግ ከያዘ ሰነባብቷል። ይኼው የፋሽስቱ የሚሊሺያ ጦር በ3 ሻለቃ ጦር የተከፈለ ሲሆን፣ በርካታ ብረት ለበስ ተሽከርካሪዎችና ታንኮች ይዞ፣ ወደ 76 የሚጠጉ መድፎቹን ከጠመደባቸው ሰንብቷል። በሚቀጥሉት ቀናት ስንቅና ትጥቅ የጫኑ በርካታ የጭነት ተሽከርካሪዎች መጉረፍ ጀመሩ። እነዚህ በተሰራላቸው ጥርጊያ መንገድ ላይ የሚያዘግሙ ከባድ የጭነት መኪናዎች ሁለት ጊዜ በልጁ ጦር ከመዘረፋቸው በስተቀር ያለብዙ ችግር ለጠላት ጦር ከስንቅ በተጨማሪ 48,000 የመድፍ ጥይቶችና 7,000,000 ለተለያዩ ጠመንጃዎች የሚሆኑ ጥይቶችን

ለማድረስ ተችሏቸዋል። በሃውዜን እንደተጠባባቂ ጦር ካሰፈረው ሰራዊት በተጨማሪም፣ አዲስ ከጣልያን የተላከለት ትኩስ ጦርም ወደ ኢንጢቾ እየገሰገሰ ነው።

የጠላት ጦር በዚህ መልኩ ሲደራጅ ከአቢ አዲ በስተደቡብ ማምሻው ላይ አዲስ ጠላት ብቅ አለብን። ይኼው አዲስ ጠላታችን ገና ደንገዝገዝ ከማለቱ አይን ሊያጠፉ የሚደርሱ እንፀባራቂ (የሪፍሌክቶር) መብራቶቹን ያበራብናል።

ይኼን ከባድ መብራት በየምሽቱ የሚያበራብን የፋሽስቱ 3ኛው ክፍለ ጦር ሲሆን፣ በማርሻል ባዶሊዮ ጥብቅ ትዕዛዝ ከአምባራዶሙ ጦርነት በኋላ 3 ሻለቃ ጦር ያለው ብርጌድ ፊቱን አዙር ከ3ኛው ክፍለ ጦር ጋር በመቀላቀል ወደ አቢ አዲ ጉዞ ጀምሯል። 4 ዲቪዥን ሙሉ ጦር ደግሞ በጠቅላይ መምሪያው ስር ሆኖ እንደተጠባባቂ ጦር በመቀሌ፣ እንጣሉና፣ ሙጂ መካከል ሰፍሯል።

በዚህ መልኩ የራስ ካሣ ጦር በተንቤን በጠላት ጦር ዙሪያውን ተከበበ። የጠላት አውሮፕላኖች በየቀኑ ያለማቋረጥ ድብደባቸውን ቀጥለዋል። እንደ ሁልጊዜው ሁሉ የመጀመሪያዎቹ አውሮፕላኖች ከጠዋቱ ጀምረው ጀንበር ከመጥለቋ አንድ ሰዓት ቀደም ብለው የእለት ተለት የግድያ ተግባራቸውን አጠናቀው ይመለሳሉ። ከሰማይ በዚህ መልኩ እሳት ሲወርድብን ከምድር ደግሞ ከአቢ አዲ በስተደቡብ የፋሽስቱ ጦር መድፎች ያለማቋረጥ ያጓሩብናል። በዚህ መልኩ በአቢ አዲ ዙሪያ ያሉ ተራ የምስኪን ገበሬ ጎጆዎች ሳይቀሩ እንደመስቀል ዳመራ ሌሊቱን ሙሉ ሲጨሱና ሲነዱ ያድራሉ።

የካቲት 27 ቀን ማለዳ ገስግሰን ወደ ራስ ካሣ ዋሻ በደጃዝማች አበራ የጦር ሰፈር [ደብረ አምባ አፋፍ] ስናመራ ከርቀት የነዚያን የቆርቆሮ አሞራዎች ጩኸት ሰማን። ይሁን እንጂ የዛሬዎቹ የቆርቆሮ አሞራዎች የጦር ሰፈራችንን ወደ ጎን በመተው አልፈውን በረሩ። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ የቦንብ ፍንዳታዎችን ያለማቋረጥ መስማት ጀመርን። አዎ እነዚህ የተረገሙ አውሮፕላኖች ዛሬ ቀዳሚውን ጦራችንን በጾኚ ወንዝ ዳርቻ ላይ የቦምብ እሳት እያወረዱበት ነው። ሌሎች በርከት ያሉ አውሮፕላኖች፣ ከአቢ አዲ በስተሰሜን ባለችው የተራራ ቀበሌ፣ በወርቅ አምባ የሰፈረውን የደጃዝማች አድማሱ፣ የደጃዝማች በየነ ሂልሚንና የደጃዝማች መሸሻ የከንባታውን ጦር እየዞሩ ይደበድባሉ።

ዛሬ በራስ ካሣ ዋሻ ራስ ካሣን ምንጊዜም ከአጠገባቸው ከማይለየው ከትንሹ ልጃቸው ከደጃዝማች አስፋወሰን፣ ከወንድሙ ከደጃዝማች አበራና ከጥቂት መኳንንት ጋር ተቀምጠው አገኘናቸው። ራስ ካሣ ልጠይቃቸው ያሰብኩት የገባቸው ይመስል፤ ገና ሳልጠይቃቸው ራስ ሥዩምና ትልቁ ልጃቸው ደጃዝማች ወንድወሰን ጦራቸውን ይዘው በሌሊት ወደ አምባ ጸለሪ መሄዳቸውንና፣ በአምባ ጸለሪ ወደ አቢ አዲ በመግፋት ላይ ያለውን የፋሺስቱን ጦር ለማገድና እዚያው ቢቻል እንዳይንቀሳቀስ አድርገው ሊያስሩት መሄዳቸውን አስረዱኝ። የጠላት ጦር ያለብዙ ችግር የጊባን ወንዝ

ተሻግሮ በአምባ ጸለሪ በኩል አድርጎ ወደ አቢ አዲ ለመግባት ጉዞ ጀምሯል። የጠላት ጦር በአንድ ራስና በአንድ ደጃዝማች ጦር አምባ ጸለሪ ላይ መገታት አለበት።

ከራስ ካሣ ጋር በነዚህ ጉዳዮች ላይ እየተወያየን እያለ ወደ ዋሻው ውስጥ በጣም የሚቻኮልና በሩጫ ብዛት ደክሞ ትንፋሹ ቁርጥ ቁርጥ የሚል የደጃዝማች በየነ መልክተኛ መጥቶ ከራስ ካሣ እግር ስር ወደቀና የመጣበትን ጉዳይ ማስረዳት ጀመረ። የደጃዝማች በየነ መልክተኛ፣ ዛሬ አጥቢያ ሌሊት ላይ ጣልያኖች በሁለት ረድፍ የወርቅ አምባን ተራራ ለመቆጣጠር ጦርነት መክፈታቸውን አስረዳ። ወርቅ አምባ፣ ከአቢ አዲ በስተሰሜን በኩል ጥቂት ኪሎ ሜትሮች ርቃ የምትገኝ ተራራ ነች። ከተራራዋ በስተሰሜንና በስተደቡብ በኩል ሆኖ በሁለት ረድፍ ተሰልፎ ተራራዋን ለመቆጣጠር የሚጣደፈውን የጣልያን ጦር፣ የደጃዝማች በየነ ወታደሮች በግራ በኩል፣ ደጃዝማች መሸሻ ከንባታውና ደጃዝማች መንገሻ ሂልሚና ደጃዝማች አድማሱ በቀኝ በኩል የጠላትን ጦር ወጥረው ይዘው፣ ፋታ ሳይሰጡ የመትረየስ ጥይት እያዘነበባቸው መልሶ የማጥቃት ርምጃ ወስደው፣ ጣልያኖቹን ወደ መጡበት ወደወረዱ የጦር ሰፈራቸው የመለሷቸው መሰለ።

በኢትዮጵያውያን ታልማ በተተኮሰች ጥይት በሚወድቀው የጠላት ጦር ምትክ አዲስ ጦር እየተተካና ከላይ በአውሮፕላን፣ ከመሬት ደግሞ በከባድ መሳሪያዎች እየተረዳ ጦርነቱ ቀጥሎ መሬት ቁና ሆነች። በዚህ መልኩ ሁለተኛው የተንቤን ጦርነት በወርቅ አምባ ተጀመረ።

አሽከሮች በቅሎዎቻችንን ጭነው ስለመጡ ጊዜ ሳናጠፋ ከራስ ካሣና ከልጃቸው ከደጃዝማች አበራ ጋር ወደላይ ወደተራራው አሻቅበን ወጣን። እሁንም እሁንም ፍጥነታችንን እየጨመርን በፍጥነት ተጉዘን ከ13ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ከሆነችው ጥንታዊቷ የዋሻ ቤተክርስቲያን ደረስን፤ የደብረ አምባ ቤተ ክርስቲያን። በዚችው ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ደጃፍ ላይ ድንኳናችንን ጥለን ከዚችው አፋፍ ላይ ሆነን የውጊያውን ሂደት መከታተል ጀመርን።

ራስ ካሣ ከተራራዋ ጫፍ ላይ ቆመው በጦር ሜዳ መነጽራቸው የጦርነቱን ሂደት እየተከታተሉ አልፎ አልፎ በእጃቸው ምልክት ሲሰጡ፣ ከጀርባቸው በተጠንቀቅ የቆሙ ወታደሮች ይቀርቡና፣ አፋቸውን በሻማቸው ጫፍ ሸፍነው ከራስ ካሣ ወታደራዊ ትዕዛዞችን ይቀበላሉ፤ ከዚያም እታች እጦር ሜዳ ላሉ የጦር መኮንኖች ትዕዛዙን ለማድረስ እየተንደረደሩ ይወርዳሉ።

ምንም እንኳን የጠላት አውሮፕላኖች ያለምንም ርህራሄ በኢትዮጵያው ሰራዊት ላይ የቦምብ ናዳ ቢያወርዱበትም፣ አይበገሬው የኢትዮጵያ የገበሬ ወታደር ወደፊት ገፋ። እንደ እሳት የሚነደው የተንቤን አሸዋማ መሬት ቃጠሎ በባዶ እግሩ ለሚሄደው የኢትዮጵያ የገበሬ ሰራዊት ከሚችለው በላይ ቢሆንበትም፣ ወርቅ አምባን ለመያዝ የመጣውን የጣልያን ጦር ወጥሮ ያዘው።

ቀትን ሙሉ ሰማዩን ወርረው የሞት እሳት የሚያዘንቡት የጣላት አውሮፕላኖች የኢትዮጵያው ሰራዊት እንደልቡ ወደፊት እንዳይገፋ የብረት አጥር ቢሆኑበትም፣ በቦምብ እሳት የነደዱ የትግል ሜዳ ወንድሞቹን እየዘለለ ወደፊት ገፋ። በጀግናው ደጃዝማች መንገሻ ሂልሚ በወርቅ አምባ የጦር አውድማ የግራ ክንፍ፣ በጀግናው ደጃዝማች መንገሻ ሂልሚ የሚመራው ጦር ደረጃ በደረጃ፣ ሜትር በሜትር የጠላትን ጦር እያንበረከከ፣ ድል እየመታ ወደፊት ገፋ።

የደጃዝማች መንገሻ ሂልሚና ቀዳሚው ጦር በጠላት እጅ የወደቀቼውን የወራዩን ቀበሌ እጁ ሊያስገባ ወደፊት ገሰገሰ። የደጃዝማች መሸሻና የደጃዝማች አድማሱ ወታደሮች ወደፊት ገፍተው በወራዩ የጣልያኖች የመከላከያ ምሽግ ደጃፍ ላይ ደርሰው ጣልያኖች ከምሽጎቻቸው እንዲወጡ እየኮረኮሯቸው ነው።

በዚች ቅጽበት የጣሊያን ጦር የአርባ ቀን እድል የተፈጸመች መስላ ነበር። በአለቀ ሰዓት ጣልያኖች ወደፊት በሚገፋው የደጃዝማች መንገሻ ሂልሚ ጦር ላይ ባለ12 ባትሪ መድፎቻቸውን ከፈቱበት። በወርቅ አምባ የጦር አውድማ የግራ ክንፉን ይዞ ወደፊት የሚገፋውን የደጃዝማች መንገሻ ሂልሚን ጦር ባለ12 ባትሪ መድፍ ባያቆመውም፣ ከስር የመጣው አዲስ የጣልያን ጦር አላንቀሳቀስ አለው።

በዚችው የወርቅ አምባ የጦር አውድማ የደጃዝማች በየነ ወታደሮች ከጠላት ጦር ጋር ተፋጠዋል። ይኼ የጠላት ጦር የመጀመሪያው ብርጌድ የኤርትራ ተወላጆች ጦር ነበር። ይኼው በመጀመሪያው ረድፍ የሚጓዘው የኤርትራ ተወላጆች ጦር ከኢትዮጵያውያን ወንድሞቹ ጋር ሲገናኝ እጆቹን ወደ ሰማይ እያነሳ "በምኒልክ፣ በምኒልክ አምላክ፣ በምኒልክ!" ሲል ኢትዮጵያውያን የደጃዝማች በየነ ወታደሮች ኤርትራውያን ወንድሞቻቸውን እየዘለሉ በሁለተኛ ረድፍ ተሰልፎ ከሚጠብቀው የጣልያን ጦር ጋር ለመግጠም ወደፊት ገፉ። ኤርትራውያን በምኒልክ ስም እየማሉ ወደኢትዮጵያውያን ወንድሞቻቸው ያልገቡበት አንዲት ቀን አልነበረችም። እናም ደጃዝማች በየነም ሆነ ወታደሮቹ፣ ኤርትራውያን እጃቸውን እንደሰጡና ጠላቶቹ እንዳልሆኑ አምኖ ከጣልያኖቹ ጋር ለመግጠም ወደፊት ሲገሰግስ፣ ያመናቸው፣ በምኒልክ ስም የተማጸኑት ኤርትራውያን ወንድሞቹ ከጀርባው ተኩስ ከፈቱበት። ከፊት ለፊቱ የጣልያን ፋሽስቶችን እየተዋጋ ከጀርባው የከዳውን ወንድሙን እየመከተ ከገባበት ወጥመድ ለመውጣት የሞት ሽረት ትግሉን፣ ውጊያውን ገፋበት። የዚህ ውጊያ ውጤት አስከፊ ነበር። የደጃዝማች በየነ ወታደሮች ከገቡበት ወጥመድ ለመውጣት በታላቅ ጀግንነት ተዋጉ። የዚህ ጀግና ጦር መሪ ጀግናው ደጃዝማች በየነም በዚህ አንጎል በሚያደርግ ውጊያ በታላቅ ጀግንነት ቀኑን ሙሉ ሲዋጋና ሲያዋጋ ውሎ የመጨረሻዋን መስዋዕትነት ከፈለ። ከወራዩ የጦርነት አውድማ ጀግናው ደጃዝማች በየነ አልተመለሰም።

መሪ አልባ የሆነው ይኼው ሰራዊት ተስፋ ሳይቆርጥ ሲዋጋ ውሎ ማምሻው ላይ ከተከበበበት ሰብሮ በመውጣት ወደሰሜን ወርቅ አምባ አፈገፈገ። በዚህ መሀል የግራ ክንፉ የደጃዝማች መንገሻ ሂልሚ ጦር በድል አድራጊነት ወደፊት ገፋ። ይሁን እንጂ ጣልያኖች በዚያው በኩል በርከት ያሉ ወረዩን ለመያዝ ከወርቅ አምባ ተራራ ጫፍ ላይ ማጓጓዝ በመቻላቸው፣ ይኼንኑ በድል አድራጊነት ወደፊት በመግፋት ላይ ያለውን የደጃዝማች መንገሻ ሂልሚን ጦር ከጎኑ ሰቅስቀው ገብተው፣ በመትረየሶቻቸው ወደፊትም ወደኋላም አላንቀሳቅስ አሉት። የዚህ ጦርነት ውጤት፣ መሪው ደጃዝማች መንገሻ ክፉኛ ሲቆስሉ ወታደሮቹ ደግሞ ማፈግፈግና ወደ ኋላ መመለስ የግድ ሆነባቸው።

እስከ ከሰዓት በኋላ ድረስ የጣልያን አውሮፕላኖች ከመቼውም ጊዜ በላይ ፋታ ሳይሰጡ እነሆ ከጠዋት ጀምሮ የጦር ሰፈራችንን አቢ አዲን በቦምብ ይደበድባሉ። በተደጋጋሚ በደቂቃዎች ልዩነት ከምንሰማው የቦምብ ፍንዳታና የአውሮፕላኖች ጩኸት በተጨማሪ፣ አልፎ አልፎ የምትንጣጣው የራስ ካሣ አየር መቃወሚያ ድምጽ ትሰማ ነበር።

ይቺኑ የምትንጣጣ የራስ ካሣ አየር መቃወሚያ ያዩ የጣልያን አውሮፕላኖች ዝቅ ብለው በመብረር በተደጋጋሚ በጣሉባት የቦንብ ናዳ የሳት ራት አደረጓት። ማምሻው ላይ የመጀመሪያዎቹ ቁስለኞች ወደጦር ሰፈር መመለስ ጀመሩ። በቀላሉ የቆሰሉ ወታደሮች የጦር ሜዳ ጓዶቻቸውን ትከሻ ተደግፈው በእግራቸው እያዘገሙ ሰፈር ሲደርሱ፣ በከባዱ ክፉኛ የቆሰሉ ወታደሮች ደግሞ በፍጥነት በባፍ ቅርንጫፎች ዝንጣፊዎች እንደነገሩ በልጥ ታስረው በተሰሩ ቃሬዛዎች ላይ የትግል ጓዶቻቸው ተሸክመው አመጧቸው። በእግራቸው እያዘገሙ ጦር ሰፈር ከደረሱት የጦር ሜዳ ቁስለኞች መካከል የደጃዝማች በየነ የጦር መኮንን አንዱ ነበር።

ይህ የደጃዝማች በየነ የጦር መኮንን በጦር ሜዳ ውሎው ከጠላት የተተኮሱ አምስት ጥይቶችን በሆዱ ይዞ፣ በእግሩ እያዘገመ መጥቶ በጦር ሰፈር እንደ ሆስፒታል ከምታገለግለው አንዲት አለታማ ዋሻ ደጃፍ ላይ አንገቱን ሰብር አድርጎ ተቀምጧል። በአምስት የጠላት ጥይት ተመትቶ ህመሙንና ስቃዩን ጥርሱን ነክሶ በሆዱ ውጦ እንደማንኛውም ወታደር ከብጤኛው ዶክተራችን የቀዶ ጥገና ድንጋይ ላይ እስኪተኛ ድረስ በታላቅ ትግስት ይጠብቃል።

ቀኑን በዚህ መልኩ አሳልፈን ማምሻው ላይ ሰላም ወረደ። ሌሊቱ በቁስለኞች የህመም ጣር፣ ዋይታና ጩኸት ተሞልቶ ሊነጋጋ ሲል፣ ገና ጎህ ከመቅደዱ እነዚያ የተረገሙ የሰማይ ላይ የቆርቆሮ አሞራዎች ጩኸት ከርቀት መሰማት ጀመረ። እነዚህ ጣረሞቶች ገና ጦር ሰፈራችን ከመድረሳቸው ትላልቅ የሚበታተኑና የሚነዱ ቦንቦችን በጦር ሰፈራችን ላይ ጣሉብን። እንዲህ ያለ ማቋረጥ በቦምብ ናዳ ሲደበድቡን ትላልቅ

ተሰባብረው እንዲሁ መሰለ በተላቀ ኩራት ከቆሙበት አስፈሪ ተራራ ላይ እንደ ገደሉት እንዲሁ በዛባቸው ወረዱ። ጎመን ቅጠል እየተቀነጠሰ ወረዱ::

ከሰዓት በኋላ በግምት ለአንድ ሰዓት ያህል እነዚህ ሞት አዝናቢዎች ከሰማይ ላይ ተሰጠሩ:: በአቢ አዲ የጦር ሰፈር ለተወሰነች ጊዜ ፀጥታና ሰላም ሰፈነ:: ከደብረ አምባ አካባቢ ብቻ በተወሰኑ ደቂቃዎች ልዩነት የከባድ መሳሪያዎች ጩኸትና ፍንዳታዎች ከርቀት እንሰማለን:: ይቺን ጊዜያዊ ሰላም ተጠቅመን ከመሸግንባት ዋሻ ወጥተን ምንም መከላከያ የሌላትን ሜዳ በፍጥነት እየሮጥን፣ እየወደቅንና እየተነሳን ወደ ድንኳናችን ተፈተለክን:: ከዚያች ተንቀሳቃሽ የመኖሪያ ድንኳናችን ውስጥ ያሳችን እዚህ ግባ የማትባል ንብረታችን ቡጭቅጭቁ ከወጣው ድንኳናችን ስር አመድ ሆና አገኘናት:: ባፋጣኝ ዋጋ ያላቸው እቃዎችን ሰባስበን እንዳመጣጣችን በፍጥነት ተመለስን:: ከኛ ድንኳን ብዙም ሳይርቅ ገደሎችን ተገን አድርገው በትናንሽ ዋሻዎች ውስጥ የተደበቁ ቁስለኞች፣ እናቶች፣ ሴቶችና ህጻናት በትላልቅ ቦንቦች ፍንዳታ የሚደረመሱ ገደሎች ከነህይወታቸው ቀብረዋቸዋል::

ከኛ የጦር ሰፈር ብዙም ሳይርቅ ካለ ሌላ የጦር ሰፈር ወታደሮች እንደሰማነው እነዚያ የተረገሙ አብራሪዎች በብዙ የጦር ሰፈሮች ላይ ባለ መርዘኛ የጋዝ ጭስ ቦምቦች (Yperit) ሳይቀር በጭካኔ ጥለዋል:: ከሰዓት በኋላ አሁንም ከራስ ካሣና ከባለሟሎቻቸው ጋር ምክር ስንቀመጥ፣ እታች እጦር ሜዳ የአርጌ ጠመንጃ፣ የጦርና የጎራዴ ታጣቂው የገበሬ ወታደር ከባለታንኩ፣ ከባለአውሮፕላኑ፣ ከባለመትረየሱና ከባለ መድፉ የጠላት ጦር ጋር የሞት ሽረት ውጊያውን ቀጥሏል::

ማምሻው ላይ ወደ ጦር ሰፈር ተመለስን:: ወደ11 ሰዓት ገደማ ሆኗል። አሁንም ከርቀት የመትረየሶች የማያቋርጥ መንጣጣት ይሰማናል:: የጦር ሜዳው ሽለላና ፉከራ ልክ ከርቀት እንደሚሰማ የገበያ ጩኸት ይሰማል:: የጠመንጃ ጩኸቶችን መለየት ያስቸግራል:: የመትረየሶች ጣጣታ በጣም ፈጣንና ተደጋጋሚ ስለነበር ከምድር እንጂ ከአውሮፕላኖች ላይ እንደማይተኮስ ያስታውቃል:: ጣልያኖች በደብረ አምባ ተራራ ጫፍ ላይ ደርሰው ይሆን?

በዚህ መሀል እንደ ደራሽ ውሃ ልጆችና በጀርባቸው ቅርጫት፣ ጋን፣ እንስራ ወይም ሌሎች ቅራቅንቦዎች የተሸከሙ ሴቶች መዓት አጥለቀለቀን:: ከሴቶችና ከልጆች ኋላ ቁስለኞች፣ በሽተኞችና አዛውንቶች ተከታትለው ያዘግማሉ:: ሁሉም ግራ በተጋባ ሁኔታ እንዱ ከሌላው አፍ እየተቀበለ እየነጠቀ፣ "ጣልያኖች መጡ! ጣልያኖች መጡ!" እያሉ ይጮሀሉ:: ይኼው አቢ አዲ ስር ደርሰዋል::

በግራ በኩል ከደብረ አምባ ተራራ አንድ ፈረሰኛ ጦር እየወረደ ነው:: ይህ ፈረሰኛ ጦር እየቀረበ ሲመጣ የራስ ካሣ አጃቢዎች መሆናቸውን አወቅን:: አዎ ራስ ካሣ ከታማኞቹ አጃቢዎቻቸው ጋር ወደታችኛው የጦር ሰፈር እየወረዱ ነው:: ምክንያቱም የላይኛው የጦር ሰፈር አሁን የጣልያኖቹ ጦር እይታ ውስጥ ገብቷል::

ምን ተፈጠረ? ጣልያኖች ወደፊት ገፍተው በምዕራብ በኩል አቢ አዲን ሊወጉ ነው የሚባለው እውነት ነው?" ስል ራስ ካሣን ጠየኳቸው::

"ምንም ነገር አልተፈጠረም!" ሲሉ ራስ ካሣ መለሱልኝና ፍጹም በተረጋጋ መንፈስ በመቀጠል፣ "ይኼ የምታየው ራስ ሥዩም ከወንድወሰን ጦር ጋር ዛሬ ጠዋት አምባ ጸለሪ ላይ ድል ያደረገው የጣልያን የተረፈ፣ የተፈታ ጦር ነው:: ይኼ እንደምታየው አቢ አዲን ዞሮ ከጦሩ ጋር ለመቀላቀል የሚጥር ትራፊ የተበተነ ጦር ነው:: ድል አድራጊው የሥዩም ጦር ወደሰሜን እያባረረው ነው" አሉኝ::

ቆየት ብሎ ነው ራስ ካሣ ስለ ሁኔታው ምንም አይነት ግንዛቤ እንደሌላቸው የገባኝ:: ነው ወይስ ራስ ጦሩን አጉል ላለማረበሽና ከግርግር ለማዳን የፈጠሩት ዘዴ ይሆን? አልገባኝም:: ከተወሰኑ ቀናት በኋላ በአጋጣሚ ከአንድ የራስ ሥዩም የጦር መኮንን ጋር በተገናኘን ጊዜ ነበር በትክክል አምባ ጸለሪ የሆነውን ሁሉ የሰማሁት:: የራስ ሥዩምና የደጃዝማች ወንድወሰን ጦር ማለዳ ላይ ከወታደራዊ ስልት አንጻር በጣም ቁልፍና ወሳኝ የሆነ የተራራ ጫፍ ይዞ ይመሽጋል:: የራስና የደጃዝማቹ ጦር ወሳኝ ቦታ ይዞ ሲመሽግ የጣሊያኑ 3ኛ ክፍለ ጦር በዝግታ ወደ ሰሜን እያዘገመ ነበር::

ልክ ጎህ እንደቀደደ ራስ ሥዩም ሹማምንቶቻቸውን ለጦር ምክር ይጠራሉ። አንዳንዶቹ ወደሰሜን በማዝገም ላይ ባለው የጣልያን ጦር ላይ አሁኑኑ ጥቃት ይሰንዘር አሉ:: ይሁን እንጂ አመዛኙ ይኼን ሀሳብ ተቃወመው:: በምትኩ በትግዕስት መልካም አጋጣሚ መጠበቅ አለብን አሉ::

ይኼን የኢትዮጵያውያንን አለመግባባት የተጠቀመውና የትግራይ ሰላዮች ምን እየተደገሰለት እንደሆነ ወሬ ያደረሱለት የጣልያን ጦር፣ ከመቀሌ አስራ ስምንት አውሮፕላኖች መጥተው ጊዜ ስለገዙለት፣ ተበትኖ ያዘግም የነበረውን 3ኛ ክፍለ ጦሩን በፍጥነት አጠናክሮ በጥንቃቄ ወደ አምባ ጸለሪ መጠጋት ጀመረ:: እነዚህ አስራ ስምንት አውሮፕላኖች ግን የሥዩምንና የወንድወሰንን ጦር በመደብደብ ፈንታ በሶስተኛው ክፍለ ጦርና በሥዩምና በወንድወሰን ጦር መካከል ያለውን ባዶ መሬት መደብደብ ጀመሩ::

እነዚህ አስራ ስምንት አውሮፕላኖች ይኼንን የማንም ያልሆነ ባዶ መሬት የሚደበድቡት ሆን ብለው ነበር:: አውሮፕላኖቹ ያንን ባዶ መሬት ሲደበድቡት የኢትዮጵያው ሰራዊት በተራራው ላይ እንደመሸገ በጣልያኖች ላይ እየሳቀ ተቀመጠ:: እንዲህ የነሥዩም ጦር ተቀምጦ ሲስቅ 3ኛው ክፍለ ጦር ድምጹን አጥፍቶ ወደ ተራራው ተጠጋ::

አዎ የጣልያን አውሮፕላኖች ሆን ብለው የማንም ያልሆነውን መሬት ሲደበድቡ ለጦራቸው ጊዜ ከመግዛታቸውም በላይ የነስዩም ጦር ተዘናግቶ እንዲቀመጥ

ይመስላሉ። እንደልማዳቸው የሥዩምንና የወንድወሰንን ጦር ቢደበድቡት ኖሮ፣ ያ ጦር ቆርጦ እንደ ተኳ ንብ ከመሸገበት ወጥቶ ያንን የተበተነና የተዝረከረከ 3ኛውን ክፍለ ጦራቸውን ልክ ያስገባው ነበር። አዎ ኢትዮጵያውያን በአለም ልዩ የሚያደርጋቸው ነገር ቢኖር፣ በጦር ሜዳ ውሏቸው ጤነኛ መሆናቸው እስኪያጠራጥር ድረስ እንደአብድ መድፉን፣ መትረየሱን፣ ታንኩንና የአውሮፕላን ቦምቦችን ከመጤፍ ሳይቆጥሩ እየፎከሩና እየሸለሉ የጠላትን ጉሮሮ አንቀው ይወድቃሉ እንጂ ወደ ኋላ አለመመለሳቸው ነው።

የሥዩምና የወንድወሰን ጦር በአምባ ጸለሪ ተራራ ውስጥ መሽጎ የ3ኛውን ክፍለ ጦር መምጣት ሲጠባበቅ እነዚያ አስራ ስምንት አውሮፕላኖች የገዙለትን ጊዜ ተጠቅሞ እግራቸው ስር ደርሶ ጥቃት ሰነዘረባቸው፣ ወጋቸው። ከዚህ በኋላ ነበር፣ ያ ብዙ ደም የፈሰሰበት የአምባ ጸለሪ ጦርነት የተደረገው። በዚህ ጦርነት ጣልያኖች ብረት ለበስ ተሽከርካሪዎቻቸውን ሳይቀር አሰልፈው ነበር። ይኼ መኰንን "ምን ያደርጋል፣ እንዲያ እንደ ወፍ ዘር ተበትኖ ብናጠቃው ኖሮ ለወሬ ነጋሪም አናስተርፈውም ነበር" እያለ በቁጭት አጫውቶኛል።

በኃይል ሚዛን የተረታው የራስ ሥዩምና የደጃዝማች ወንድወሰን ጦር በመጨረሻ ማፈግፈግ ግድ ሆነበት። በዚህ ጊዜ ራስ ካሣ 3ኛው የጣልያን ክፍለ ጦር ወደ ሰሜን አቢ አዲ እየገሰገሰ እንደነበረ ምንም አይነት ግምት አልነበራቸውም። ራስ የገመቱት ትንሽ ቁራጭ ጦር ከነራስ ሥዩም እየሸሸ የሚበረግግ የጣልያን ጦር ነው ብለው አምነው ነበር።

የካቲት 28 ቀን ማምሻው ላይ በወታደራዊ ሰዓት አቆጣጠር ልክ በ17:00 ላይ ጣልያኖች በስተምዕራብ አቢ አዲ በኩል ጦርነት ከፈቱ። ጣልያኖች በኛ ላይ ጦርነት ሲከፍቱ፣ በርካታ የራስ ካሣ የግል ዘቦች በአቢ አዲ ከተማ በፍጥነት በመዘዋወር የጦር ሰፈሩን ለማረጋጋት ሞከሩ። በዚህ ሰበብ በአቢ አዲ ሊፈጠር የሚችለውን ግርግርና ጩኸት በአጭር ጊዜ ተቆጣጥረን በአቢ አዲ እኛም ሶስት ፈረንጆች ስንቆይ፣ በመሃሉ አንድ ሹም እየሮጠ መጥቶ፣ “ዋይ ዋይ! ጣልያኖች! የከፉ ነው። ዋይ ዋይ! ጣልያኖች ወደ አቢ አዲ እየገቡ ናቸው። ጣልያኖች ብዙ በጣም ብዙ ናቸው። የኛዎቹ አልቻሉም እያፈገፈጉ ነው” እያለ ያለ ማቋረጥ በሀዘንና በድንጋጤ ስሜት ተናገረ፣ “እንጎራጎረ።”

ከዚህ ሹም የሀዘን ንግግር በኋላ ጊዜ ሳናጠፋ እየተጣደፍን ወደ ራስ ካሣ ድንኳን አመራን። ከድንኳኗ በራፍ ስንደርስ ራስ ካሣ በተንቀሳቃሽ ዙፋናቸው ላይ ተክዘውና አዝነው ተቀምጠዋል። ራስ እኛን ሲያዩ ራሳቸውን እያወዛወዙ የጦር ሜዳው ውሎ አስከፊ እየሆነ መምጣቱን እዝን ብለው ገለጹና በመቀጠል፣ “ያለንበት ሁኔታ ብዙም ተስፋ የሚጣልበት አይደለም። ቢሆንም ተስፋ ሳንቆርጥ እየተዋጋን ማፈግፈግ አለብን። ግን ወዴት ነው የምንሸሸው? ወደ ደቡብ የሚወስዱት ሁሉም

መንገዶች በጣልያኖች ተይዘዋል። እንግዲህ ያለን አማራጭ ወደላይ ወደ ተራራው መሸሽ ብቻ ነው። ከዛስ?” ራስ ንግግራቸውን ሳይጨርሱ አንጠልጥለው ተውት። ለዚህም ራስ መልስ የላቸውም።

“በሉ እቃችሁን ሰባስቡና ከሰራዊቱ ጋር ተደባለቁ” አሉ ጥቂት ትክዝ ብለው ቆይተው። ከራስ ካሣ ዋሻ ውስጥ አሽከሮቻቸው ሊሸከሟቸው የማይችሉትን መዛግብት ያቃጥላሉ። አዎ ሁኔታው በጣም አስጊ ነው። ተስፋ አስቆራጭ ነው ማለትም ይቻላል።

ከሰሜኑ የጦር ግንባር በርካታ የደከሙ ወታደሮች ወደጦር ሰፈር መመለስ ጀመሩ። ጣልያኖች ደረጃ በደረጃ ይኼንንም የተራራ ወገብ በቁጥጥራቸው ስር እያደረጉት ነው። የደብረ አምባን የተራራ ጫፍ ሊይዙ ተቃርበዋል። ከተራራው ስር ትልቁ የራስ ካሣ የጦር ሰፈር ተዘርግቷል።

በፍጥነት ወደ ድንኳናችን ተመለስን። እዚያው ድንኳናችን የቆመበት ቦታ አንበሳ ጓዛችንን በሁለት አህዮች ጭኖ ጠበቀን። ወዲያው ጊዜ ሳናጠፋ መጨረሻ በሌለው የሰውና የእንስሳ መንጋ ጋር ተቀላቅለን የሽሽት ጉዟችንን ጀመርን። ወዴት እንደምንሸሽ ለጊዜው የሚያውቅ ማንም የለም። የእግሬ አውጪኝ ጉዞ ግን አላቆመም። ወንዙን ተከትለን ዙሪያ ጥምጥም ስንጓዝ አምሽተን ትንሽ ለማረፍ ወሰንን። ጫማችንን እንኳን አላወለቅንም። ጊዜ የለንም። ሌሊቱን ከፈረሶቻችን ላይ ወርደን በእግር መጓዝ ግድ ሆኖብን ነበር። እንስሳዎቹ እርስ በርስ እየተጋፉ ንቅንቅ ማለት አልቻልንምና አንበሳን ከጭነት ከብቶች ጋር ትተነው እኛ በሌሊት ተነስተን በሁለቱ ገደሎች መሀል ያለቺውን ስርጣማ መንገድ መረጥንና ሽቅብ መውጣት ጀመርን። ሌሎች መንገዶች በጣልያኖች ተዘግተዋል። ተይዘዋል። እናም ከመንጋቱና እነዚያ መዘዘኛ አውሮፕላኖች መጥተው ሳይደበድቡን በፊት ከአይናቸው መሰወር አለብንና ፍጥነታችንን ጨምረን ወደፊት በሽሽታችን ገፋንበት።

በርከት ያሉ የሀበሻ ወታደሮች የተጠረበ የሚመስለውን ገደል እንደ ዝንጀሮ ሲወጡ አየንና እኛም ከነሱ ጋር ተቀላቅለን ገደሉን እየቧጠጥን መውጣቱን ተያያዝነው። ያቺን የተረገመች ገደል ወጥተን እንደጨረስን፣ ሰፋ ያለች ለሁለት የተሰነጠቀች ገደል አገኘንና ወደዛችው ገደል ውስጥ ገብተን ተሰወርን እንጂ በዚያችው ቅጽበት እነዚያ ርጉም አውሮፕላኖች ሰማዩን ወርረውት ነበር።

እዚያ እታች ሜዳው ላይ ግን በሺዎች የሚቆጠሩ እንስሳዎች፣ ልጆች፣ አሮጊቶችና ሽማግሌዎች ከጥቂት ወታደሮች ጋር ይተራመሱ ነበር። ማምለጫ በሌለው በብረት በታጠረ ግቢ ውስጥ እንደሚተረማመስ አይነት ነገር። ይህን እንዲህ ማምለጫ አጥቶ የሚተረማመሰውን ምስኪን እነዚያ የተረገሙ አውሮፕላኖች አዩትና በጣም ዝቅ ብለው እየበረሩ፣ ምንም እንኳን ተራ ሲቪል ህዝብ መሆኑን ቢያውቁም፣ ያለአንዳች ርህራሄ ቦምባቸውን አዘነቡበት። ይኼን አረመኔያዊ ጭፍጨፋ ማየት አልቻልኩም፣

እያንዳንዷ በጣልያኖች የምትወረወር በምብ ፈረሱን፣ አህያውን፣ ልጅ አዋቂውን፣ ትገረርደው ጀመር።ያቺ ሜዳ ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ደም ለበሰች። እነዚያ ርጉሞች እየተመላለሱ የቦንብ ሸክማቸውን አውርደውበት ከመሄዳቸው፣ እነሱ ያወርዱት የነበረው የቦንብ ፍንዳታ ድምጽ በአድለቢስ ቁስለኞች ለቅሶና ዋይታ ይተካል፤ ሞት በስንት ጣሟ።

ከሰዓት በኋላ በመንገዳችን ቀጥለን ወደአርበ ዶሮ አመራን። ምንም እንኳ የምንጓዘው በገላጣ መንገድ ቢሆንም እነዚያ ርጉሞች ዛሬ ሰላም ሰጥተውናል። ምናልባት የዛሬውን ጭካኔያዊ ጭፍጨፋቸውን በደብረ አምባ ላይ አዙረው ይሆናል። በደብረ አምባ በታላቅ ጀግንነት ትግሉ፣ ጦርነቱ ተጧጡፏል። የደጃዝማች አበራ ጀግኖች የጣልያኑን ጦር ወጥረው ይዘውታል። የነዚህ ጀግኖች ግዳጅ፣ የጣልያኑን ጦር ወጥሮ ይዞ ለዋናው የራስ ካሣ ጦር የማፈግፈጊያ ጊዜ መግዛት ነው።

በጉዟችን ቀጥለን ወደአርበ ዶሮ በሩጫ ቀረሽ ርምጃ ገሰገስን። እንዲህ ስንጣደፍ ካንድ ሸለቆ ውስጥ ገብተን ተገትረን ቀረን። የህዝብ መዓት ከእንስሶች ጋር ሆኖ ወደፊትም ወደ ኋላም በማይንቀሳቀስ ሁኔታ ተጨናንቆ ቆመ። እያንዳንዷ ደቂቃ ውድና ለህይወት አደገኛ በሆነችበት ሰዓት ህዝቡ ለምን እንደቆመ ግራ የሚያጋባ ነበር። እንደምንም በህዝቡ መሀል እየተሸሎከለክን ወደፊት ቀደምን። ከፊት የነበሩት ኢትዮጵያውያን፣ ወደፊት መሄዱ አደገኛ እንደሆነና ከፊት ለፊት በተዘረጋው አሸዋማ መሬት ላይ የመድፍ ጥይቶች በተደጋጋሚ እንደሚወድቁ ነግረው አስጠነቀቁን። በአሸዋማው መሬት ላይ ያንን የጣልያን መድፎች ለማለፍ የሞከሩ ደፋር ኢትዮጵያውያን ወታደሮች ሬሳ ወድቀው ይታያሉ። ከፊታችን የጣልያኖቹ መድፎች ካጓሩ በኋላ "ወደፊት!" ስል ትዕዛዝ ሰጠሁ።

እዚህ እንደሚታረድ ከብት ታጉረን መጠበቅ አንችልምና አሁንም ድምጼን ከፍ አድርጌ "ወደፊት!" አልኩና ወደፊት መሮጥ ጀመርኩ። እድለኞች ነበርን፤ ያቺን ደም የጠገበች አሸዋማ ሜዳ ተሻገርናት። ከዚያ በኋላ ያ የታጎረው ህዝብ ይከተለን ጀመር። የጣልያን አውሮፕላኖች ይቺኑ ብቸኛ የማምለጫ መንገዳችንን አገኟት መሰለኝ እየዞሩ መንገድ ሊዘጉብን ሲጣጣሩ ጀንበር መጥለቅ ጀመረች።

በዚህ መልኩ እኛ ስንሸሽ ደጃዝማች መሸሻ የራስ ካሣን ጦር የቀኝ ክንፍ በታላቅ ጀግንነት ሲከላከል፣ የግራውን ክንፍ ሽፍቶችና ባንዳዎች አስፍስፈው ሲወጉት የሚጠብቁትን የአቢቹ ጦር እየተከላከለ ጦሩ መስመር ይዞ ከተከበበት የብረት አጥር ሰብሮ ወጣ። የደጃዝማች መሸሻ ጦር ጣልያኖቹን ወጥሮ ቢይዝም ጦሩ አነስተኛ ስለነበር፣ ከኛ መሀል ጥቂት ወታደሮች፣ "ነበዝ፣ ደጃዝማች መሸሻን እንርዳው!" ብለው ከጦር ሜዳ ሸልከው እንደገና ወደ ጦር ሜዳ ሲሮጡ፣ ወዲያው በመቶዎች የሚቆጠሩ ህይወታቸውን ወደማትረፉ የተቃረቡ ጀግኖች እየፎከሩና እየሸለሉ ከደጃዝማች መሸሻ ጦር ጋር ተቀላቅለው የጣልያኑን ጦር ገጠሙት።

እንዲህ እነዚህ ጀግኖች ከጀግናው የደጃዝማች መሸሻ የከንባታው ጦር ጋር ተቀላቅለው የጣልያኑን ጦር መግቢያ መውጫ ሲያሳጡት፣ እኛ በየት በኩል መንገዳችንን መቀጠል እንዳለብን እናስባለን። አንዳንዶቹ ወደ ሲዳን ምህረቱ እንሂድ እና ከራስ ስዩም ጦር ጋር እንቀላቀል ሲሉ፣ ሌሎች ዝም ብለን ወደፊት ተጉዘን የራስ ካሣን ጦር እንፈልገው እያሉ ስንወያይ አቢ አዲ በነበረችበት ቦታ የተለያዩ ደማቅ ቀለም ያላቸው የመብራት ጥይቶች እየተተኮሱ የአቢ አዲን ሰማይ አደመቁት። እነዚህ መብራቶች ለነዚያ የተረገሙ የጣልያን አውሮፕላኖች አቢ አዲ በጣልያን ጦር ስር መውደቋን የሚጠቁም ምልክት ነበር።

ከኛ በታች እታች ረባዳው ስፍራ ላይ በርካታ የኢትዮጲያ ወታደሮች በጉዞ ላይ እያሉ አየንና በፍጥነት ወደታች እየተንደረደርን መውረድ ጀመርን። የኛን ከተራራው ወደታች መውረድ ያዩ ወታደሮች ተኩስ ከፈቱብን። ከነዚህ ወታደሮች ጋር ተኩስ የምንገጥምበትም ሆነ እኛ መሆናችንን የምናስረዳበት ጊዜ ስላልነበረን አንዲት ጥይት ሳንተኩስ ተመልሰን ወደ ተራራው ወጣን። እኛ የብረት ቆብ ደፍተን ስለነበር ምናልባት ጣልያኖች መስለናቸው ይሆናል። የኛን የመልስ ተኩስ ያለመከፈትና ተመልሰን ወደ ተራራው መውጣታችንን ያስተዋለው ወጣት ሹማቸው በፍጥነት ወደኛ እየገሰገሰ ወታደሮቹን ተኩስ እንዲያቆሙ. ድምጹን ከፍ አድርጎ፣ "አትተኩሱባቸው፣ የኛ ፈረንጆች ናቸው" ብሎ ወደኛ መጥቶ እንደ ኢትዮጵያውያን ባህልና ወግ አቅፎ ከሳመን በኋላ፣ አብረነው እንድንጓዝ ይቅርታ ጠይቆ ጋበዘን። "ወይ ጉድ! ጌቶች! ምንም አይደል ተሳስተን ነው። ዋናው ነገር ምንም ያለመሆናችሁ ነው ጌቶች።" ይኼው ወጣት ፊታውራሪ ሹም "እንዴት እንደምክላችሁ አላውቅም። ፈረስ እንዳልሰጣችሁ የኔን የመጨረሻ ፈረስ አንድ ክፉኛ ለቆሰለ ወታደሬ ሰጠሁት" አለ፤ እሱም እንደኛው በእግሩ ነበር የሚጓዘው።

በድካምና በውሃ ጥም ብቻ ነፍሳችን ልትወጣ ስትቃረብ ካንዲት ጥቂት ዛፎች ካሉባት ለምለም ቦታ "እንዳ ማሪያም" ደረስን። በእንዳ ማሪያም ከአንዲት ለምለም ዋርካ ስር አንዲት ምንጭ ቡልቅ ቡልቅ እያለች ትፈሳለች። ግን ለዚያ በሺህ ለሚቆጠረው ሰራዊት ጥም የሚቆርጥ ውሃ አልነበራትም። ከዚያቺው ዋርካ ስር በደረቁ መሬት ላይ ጋደም ብለን ማረፍ ጀመርን። እንዲያው ወገባችንን ለማሳረፍ ያህል ጋደም አልን እንጂ፣ እንቅልፍ ወስዶን መተኛት አንችልም። እኩለ ሌሊት ላይ የሆነ ሰው ቀሰቀሰን።

"የተወሰኑ ሹሞች ጉዞ ሊጀምሩ ነው። እና አብራችሁን መሄድ የምትፈልጉ ከሆነ ተነሱ" አለን፣ የቀሰቀሰን ሹም። ይኼ ደግ ሹም በዚህ የመከራ ጊዜ፣ ለጉዟችን ይረዳን ዘንድ ከራሱ ፈረሶች መርጦ ለሁላችንም እየሰጠን፣ "ወዴት ነው የምንሄደው?" አልኩት አይኔን እያሻሸሁ። "ራስ ካሣ የሰፈሩበትን ፍለጋ" አለኝ።

ወዲያው ተነሳንና ተቀላቀልናቸው። ይሁን እንጂ አንዳቸውም ራስ ካሣ የት እንዳሉ የሚያውቅ አልነበረም። እንዲሁ በጭፍኑ፣ መንገዱ በማይታወቅ ጨለማ፣ የአውር ጉዞ ጀመርን። ቶሎ እንኳን ማብራት አንችልም፣ ጣልያኖች ቅርብ ሊሆኑ ይችላሉና። ትናንት ማታ እነዚህ ሹሞች እንደነገሩን ጣልያኖች ኪዳነ ምህረቱንና እምባ ጸለረን በእጃቸው አስገብተዋል። ከአምባ ጸለሪ አካባቢ ሰፊ ብርሃን ይታየናል። እዎ ጣልያኖች የአምባ ጸለረን የሳር ጎጆዎች እሳት ለቀውባቸዋል።

ከሁለት ሰዓት በላይ ዝም ብለን እንዞራለን። በሰማይ ኮከቦች እንደሚየው እነዚህ ሹሞች በቀጥታ ወደምስራቅ እየወሰዱን ነው። ምስራቁ ክፍል ደግሞ ሙሉ በሙሉ በጣልያኖቹ እጅ ገብቷል። እነዚህን ሹሞች ከተከተልናቸው ደግሞ በቀጥታ በጣልያኖች እጅ መውደቃችን ነው። ይህ ደግሞ ፈጽሞ ሊሆን አይገባም፣ መሆንም የለበትም። እና እስኪነጋ ድረስ ባለንበት ለመቆም ወሰንን። የተወሰኑ ሹሞች ወዴት እንደሚወስዱቸው እንኳን በማይታወቀው መንገድ በጉዟቸው ቀጠሉ።

ገና ድሮ ሳይጮህ ተነስተን ትናንት ማታ የመጣንበትን መንገድ ተከትለን ወደኋላ ተመለስን። ጥሻውን እየጣስን ስንጓዝ በነዚህ ጥሻ ውስጥ እዚህም እዚያም በርካታ ቀለሀዎች፣ የጥይት ካርታዎች፣ የተለያዩ የጦር ሜዳ ቁሳቁሶች ተበታትነው ይታያሉ።ከጥቂት ቀናት በፊት ከባድ ውጊያ ተደርጎ እንደነበር ጥርጥር የለውም።

በዚህ መልኩ ስንጓዝ ቆይተን በመንገዳችን ላይ በርካታ በመሸሽ ላይ ያሉ ኢትዮጵያውያን አገኘን። አብዛኞዎቹ ሴቶች ሲሆኑ ከፍ ከፍ ያሉት በጀርባቸው ቅርጫት፣ እንስራና ሌሎች ቅራቅንቦዎችን ተሸክመዋል።

"ጌታህ ማነው?" ስል መጀመሪያ ያገኘሁትን ወታደር ጠየኩት።

"ደጃዝማች መሸሻ" ሲል በኩራት መለሰልኝ።

"ደጃዝማች መሸሻ የት ነው ያለው?" ስል አጥብቄ ጠየኩት።

"አላውቅም ጌቶች፣ በጣም ቆስሎ ስለ ነበር ወደ ኋላ ቀርቷል" አለኝ።

ደጃዝማች መሸሻ ቆስሎ ከወታደሮቹ ጋር ወደኋላ በመቅረቱ፣ ደጃዝማቹን መጠበቁ ለጊዜው ምንም ጥቅም የለውምና ከነዚህ ተበትነው ከሚሄዱት የደጃዝማች መሸሻ ወታደሮች ጋር ተቀላቀልን፣ ቀኑን ሙሉ ከዛሬ ወር በፊት ጣልያኖች በዘረጉት ጥርጊያ መንገድ ስንጓዝ ውለን ካንዲት ትንሽ መንደር ደረስን። የዚች መንደር ነዋሪዎች ከየጎጆቻቸው ግር ብለው ወጥተው ተቀበሉን። የዚች መንደር ሹም አንድ ሽበቶ ሽማግሌ፣ "ወዴት እየሄዳችሁ ነው ጌቶች?" ሲል በትህትና ጠየቀን።

"ራስ ካሣን እየፈለግን ነው። አታውቅም ራስ ካሣ የት እንዳሉ? በየት በኩል እንደሄዱ?" ስል አከታትዬ ጠየኩት። "ጌቶች እኔ በትክክል አላውቅም። እንደሰማሁት በጊባ ወንዝ ዳርቻ ሰፍረዋል አሉ። እናንተ ግን ጌቶች፣ በዚች መንገድ ከሄዳችሁ በቀጥታ መቀሌ መግባታችሁና በጣልያኖች እጅ መውደቃችሁ ነው። በየቀኑ መኪናውና ታንኩ ይመላለሳል፣ አደጋ ላይ ናችሁ። ጌቶች ይቺን መንገድ ለቃችሁ

ወደቀኝ ታጥፋችሁ ወደ ተራራው ውጡ" እያለ የዚች መንደር ሹም ለጣልያኖች በፍቃዱ ያደረ ቢሆንም፣ የጠላት ጦር ሳያገኘን የምንገዝበትን መንገድ መራን። እዎ ምንም እንኳ ለጣልያን ቢያድርም ኢትዮጵያዊነቱን አልረሳም። ጥሩ መንገድ ነበር ያሳየን።



32
የብረቱ አጥር መስበር

እነሆ ሶስተኛ ሌሊት በሽሽት አሳለፍን። ሁላችንም ከሚገባው በላይ ደክሞናል። የግድ ትንሽ ማረፍ አለብን። እኛ ለማረፍ በደረቁ መሬት ላይ ጋደም ስንል ዋናው የስደተኞች ጎርፍ በመንገዱ ቀጠለ። እኛ በተኛንበት መንገድ ከኋላ ከጦር ሜዳ የሚሸሸው ስደተኛ እንደደራሽ ውሃ ቁጥሩ አሁንም አሁንም እየጨመረ ይጓዛል። ወዴት እንደሚሄዱ ግን እግዜር ይወቀው።

ግማሹ ስደተኛ የስደት መስመሩን ወደ ምስራቅ አድርጓል። እነዚህን ወደምስራቅ የሚሄዱትን ስደተኞች "ኧረ በቀጥታ ወደ መቀሌ እየሄዳችሁ ነው። በቀጥታ በጣልያኖች እጅ መውደቃችሁ ነው" እያልኩ በነዚህ በተበተኑ የገበሬ ወታደሮች ላይ ብጮህም፣ መላው በጠፋ ሁኔታ ቆም ብለው ያዩኝና በጉዟቸው ይቀጥላሉ። የሚሰማኝ አጥቼ ስጮህ አንዱ ወታደር ቆም ብሎ፣ "ጌቶች እኛ አገራችን ከአዲስ አበባ በታች ርቆ ነው። እዚያች አገራችን እያንዳንዷን መንገድና ድንጋይ እናውቃታለን። እዚያ እንዲህ መላው ባልጠፋብንና ባልጠፋን፣ እዚህ ሀገር ምንም ጊዜም አልነበርንም። የዚህ አገሩን ዳገት ቁልቁለቱን፣ መንገዱን፣ ቋንቋውን፣ ወገን

እና ሰውን አናውቀውም። ያው በጠላት እጅ መውደቃችን ነው። ይኼንንም እግዜሩ ያውቀዋል። ፈቃዱ ትፈጸም፤ እንውደቅ" አለኝና በጉዞው ቀጠለ። አሳዘኑኝ ።

ምንም የምናነጥፈው አንሶላም ሆነ ብርድ ልብስ ስላልነበረን በደረቁ መሬት ላይ ከነልብሳችን ጫማችንን እንኳን ሳናወልቅ በተከፈተው ሰማይ ላይ የተዘረጉትን ኮከቦች ደርበን ተኛን። በመንገድ ብዛት የደከመና የዛለውን ሰውነታችንን ለማሳረፍ ያህል ጋደም ብለናል እንጂ እውነተኛ እንቅልፍ አልወሰደንም። ያንን እውነተኛውን እንቅልፍ ለማንቀላፋት ጊዜውም፣ ሀሳቡም የለንም። እንዲህ ጋደም እንዳልን አልፎ አልፎ የሚተኮሱ ብቸኛ ጥይቶች ድምጽ ይሰሙናል። አሁን ባለንባት ሰፈር እያንዳንዷ የተተኮሰች ጥይት የአንድ ምስኪን ኢትዮጵያዊ የገበሬ ወታደር ሞት ማለት ነች።

የተወሰኑ ወታደሮች ትንሽ ቡድን መስርተው ወደኋላ በመመለስ እነዚህን ጨካኝና ከሀዲ፣ ባንዳ ሽፍቶችን ማሳደድ ጀመሩ። እነዚህ አረመኔ ሽፍቶች፣ ከጣልያኖቹ የጦር ከበባ ባሳሩ የወጣውን የተበታተነ ምስኪን ወታደር አጉል ቦታ ተደብቀው እየጠበቁ እየገደሉ፣የቋጠራትን የመጨረሻ ንብረቱን ይዘርፋታል። የሰው ልጅ ህይወት ዋጋ ቢስ ሆኗል።

የተኩሱ ጩኸት አሁን ከበፊቱ በጥቂት ደቂቃዎች ልዩነት የተደጋገመ በመሆኑ እዚህ መቆየቱ ራስን አደጋ ላይ መጣል ስለሆነ ጋደም ካልንባት ተነስተን ጉዞ ቀጠልን። ወዴት? እግዜር ይወቀው። የማይታወቀውን እድላችንን ልናይ ወደፊት ሄድን።

ንጋት ላይ እሳተ ገሞራ ከደረመሳት ገደል ጫፍ ላይ ደረስን። ከዚች የገደል ጫፍ ላይ ቁልቁል በአሞራ አይን የጊባ ወንዝ ትታያለች። እታች ከጊባ ወንዝ ዳርቻ ካሉ ቁጥቋጦዎችና አልፎ አልፎ እዚህም እዚያም ጉች ጉች ካሉ የደረቁ የግራር ዛፎች ስር የተቀመጡና ወዲያ ወዲህ የሚሉ የደከሙ፣ የደኸዩ የኢትዮጵያ የገበሬ ወታደሮች ይታያሉ።

ከገደሏ ጫፍ ወደ ጊባ ወንዝ ስንወርድና ወደ እነዚያ የገበሬ ወታደሮች እየቀረብን ስንመጣ አንዳንዶቹን ወታደሮች እያወቅኋቸው መጣሁ። የሰላሌዎቹ የደጃዝማች አበራ ወታደሮች ናቸው። ስለዚህ ራስ ካሣም ሆኑ ሁለቱ ልጆቻቸው ደጃዝማቾቹ ወንድወሰንና አበራ፣ ከራስ ሥዩም ጋር ሩቅ እንዳልሆኑ ገመትኩ። ይህንን ግምቴን መጀመሪያ ያገኘሁት የደጃዝማች አበራ ወታደር አረጋገጠልኝ። ራስ ካሣ ከዚህ ብዙም ሳይርቅ ካንዲት ዋሻ እንደመሸገና ምናልባትም ብዙ ሳይቆይ ወደፊት ሳይኼድ እንደማይቀር ጭምር አስረዳኝ።

እዎ ራስ ካሣ ከቀረው ወታደሮቻቸው ጋር በብረት አጥር አስሮ የያዛቸውን ሁለቱን የጣልያን ክፍለ ጦሮች በኃይል ሰብረው ለመውጣት ወስነዋል።

ስለዚህ በአስቸኳይ ከራስ ካሣ ምሽግ መድረስ አለብን፡፡ ግን ኮሎኔል ኮኖቫሎብም ሆነ ወዳጄ አቶ ብረየር እጅግ በጣም ከመድከማቸው የተነሳ እግሮቻቸው ሰውነታቸውን በመከራ ይዘው ይንቀጠቀጡ ስለነበር፣ ከአንዲት የቋጥኝ ጥላ ስር እንዲያርፉ ትቻቸው እኔ እንደምንም እግሮቼን እየጎተትኩ ራስ ካሣን ፍለጋ በኢሊ እርምጃ ወደፊት አልኩ፡፡

በሰማይ ላይ እነዚያ የተረገሙ የቆርቆሮ አሞራዎች ጥንብ እንዳየ አሞራ ይዞራሉ፡፡ አንዳንዶቹ አውሮፕላኖች ከ100 ሜትር ባነሰ እርቀት በጣም ዝቅ ብለው ይዞራሉ፡፡ እንዳንዶቹ አውሮፕላኖች በጣም ዝቅ ብለው በጉራ የሚበሩ አውሮፕላኖች ለኢትዮጵያ ይበራሉ፡፡ እነህ እንዲህ በጣም ዝቅ ብለው በጉራ የሚበሩ አውሮፕላኖች ለኢትዮጵያ ወታደሮች ኢላማ በቀላሉ የሚገቡ ቢሆንም፣ አንድም የኢትዮጵያ ወታደር የመሸገበትን ቦታ ለነዚያ የተረገሙ አብራሪዎች ላለማጋለጥ አንዲት ጥይት እንኳን አይተኩስም ነበር፡፡ ርጉሞቹ አብራሪዎች ስላሳ ጊዜ ቢዞሩም ጥቂት የተበታተኑ የወታደር ሰፈሮች ከማየት በስተቀር ያ ሁሉ የራስ ካሣ ጦር የገባበትን ሳያውቁ ወደ ቤታቸው ወደ መቀሌ ይመለሳሉ፡፡

ጓደኞቼን ከቋጥኟ ጥላ ስር ጥዬ፣ ራስን ፍለጋ ወደፊት ተጓዝኩ፡፡ ብዙም ሳልርቅ "ዋይ ዋይ! ወይኔ ወይኔ! ዋይ ዋይ" እያለ የሚያጣጥር የጣር ድምጽ ሰማሁና ቆምኩ፡፡ በቆምኩበት ሆኜ አካባቢዬን መቃኘት ጀመርኩ፡፡ ያ የዋይታ ድምጽ አሁንም ይሰማል፡፡ ይኼን የዋይታ ድምጽ ወደምሰማበት አቅጣጫ መራመድ እንደጀመርኩ አንድ ቁጥርጥር ፀጉር ያለው በጣም ጥቁር ልጅ ካንዲት ድንጋይ ስር ብቅ ሲል አየሁና እርምጃዬን ገታ ቼ ስቆም፣ ከዚያች እንደ ከለላ ከቆመች ትልቅ ድንጋይ ስር አንድ በደረቱ የሚሳብ ወጣት የሀበሻ ወታደር አየሁ፡፡ ያ ቆፍጣና ወታደር በደረቱ እየተሳበ እኔ ወደ ቆምኩበት ቦታ መጣ፡፡ ይኼ ጆግና ልጅ ማለዳ ላይ ሰማዩን እየዳሰሰች የቦምብ ዝናብ ታወርድ የነበረቺው አውሮፕላን የጣለችው ቦምብ አንድ እጁን እጅጌው ድረስና አንዱን እግሩን ከጉልበቱ በላይ ሞኝ የጨፈጨፈው ዛፍ አስመስላ ቆርጣ ጥላቸዋለች፡፡ ከዚህ ትልቅ ዘግናኝ ቁስሉ ነፍሱ እያመለጠች ነው፡፡ ይኼ ወጣት ወታደር የቀረቺውን አንዱን እጁን ወደኔና ወደሰማዩ ጌታ ዘርግቶ፣ "ጌታ፣ ጌታ እባክህ ስለ እግዚአብሔር ብለህ እርዳኝ፤ ጌታ እኔን የሚያስታምምና በቀረችኝ ጥቂት ጊዜ ስቃዬን የሚካፈል ጓደኛ የሌለኝ ብቸኛ ነኝና ይኼው ስቃዬን ብቻዬ ተሸክሜ መሞቴ ነው፡፡ እባክህ ጌታ ስለ እግዚአብሔር ብለህ ወኃ አጠጣኝ፡፡ ውሃ ጥም ሞትኩ" አለኝ፡፡ አሁን እኔ እንዴት አድርጌ ነው የምረዳው?

ለራሴ በመከራ ነው በሁለቱ እግሮቼ የምቆመው፡፡ ምናልባትም ከዚህ ምስኪን በላይ ውሃ ጠምቶኝ ይሆናል፡፡ ባለፉት ሶስት ቀን ጉዞዬ አንድ ጊዜ ብቻ ነው አንዲት ኩባያ አሸዋና ጭቃ ቅልቅል ቆሻሻ ውሃ የጠጣሁት፡፡ ወደፊት በጉዞዬ ለመቀጠል ፈለኩና እግሮቼን አንቀሳቀስኩ፡፡ ግን ብዙም ሳልሄድ እርምጃዎቼን ገታ ቼ ቆምኩ፡፡ ወዲያው ፊቴን አዙሬ ወደዚያ ምስኪን ተመለስኩ፡፡

እስከሞት ድረስ ያንን ለማኝ፣ ተማጻኝና አሳዛኝ ገጽታውን አልረሳውም፡፡ ምንም ልረዳው ባልችልም፣ እንደረዳሁት ቆጥሮ መሞቱ አይቀርም፡፡ ባልረዳውና ዝም ብዬው ብሄድ ግን ልክ ልረዳው ሳድነው ስችል፣ ልረዳውና ሳድነው ባለመፈለግ ጥዬው እንደሄድኩ ቆጥሮ እያዘነብኝ መሞቱ ነው፡፡ ተመለስኩ፡፡

ወዲያው ያንን በእድፍና በደም የተጨማለቀ ሸማውን ተለተልኩና እነዚያን ዘግናኝ ቁስሎቹን ግጥም አድርጌ አሰርኩለት፡፡ ከዚያ ኪሴን ስዳብስ አንዲት ባፈር የተለወሰች ኪኒን ከኪሴ ስላገኘሁ አፉን ክፈት አድርጌ ከምላሱ ላይ አደረኩለትና "ዋጠው" አልኩት፡፡ ቀጥዬም "በአንድ ሳምንት ውስጥ ትድናለህ፡፡ አይዞህ" እያልኩ አጽናናሁት፡፡

ምስኪን አመነኝ፡፡ ልክ ኪኒኗን ሲውጥ ያ አሳዛኝ ፊቱ በፈገግታ ተሞላ፡፡ እንደሚሞት እያወቅሁ ለምን እንደዋሸሁት ሳሰላስል፣ በዚያች ቀሪ አንድ እጁ ጉልበቶቼን ትርቅም አድርጎ ይዞ በምስጋና ጫማዬን ሳማት፡፡ አዎ ይኼ ሚስኪን እንደሚድን አምኗል፡፡ ወይም ደግሞ ፈረንጅ ትድናለህ ብሎታል፡፡ ፈረንጅ አንዳንዴ ተዓምር ይሰራልና ለምን እንደሚድን አያምን፡፡ ምስኪን፣ እንዲያ ጉልበቴን አቅፎ ጫማዬን ሲስም ለዚህ ጆግና ምስኪን የሀበሻ ወታደር መታሰቢያ የወጣቱ ደም በጫማዬ ላይ ተለውሳ ረግታ ቀረች፡፡

አሁን የዚያን ምስኪን የመጨረሻ ሰዓቶች እንዳቀለልኩለትና ጥሩ ነገር እንደሰራሁ እየተሰማኝ ኃይል ጨምሬ ወደፊት ተጓዝኩ፡፡ ብዙም ሳልሄድ አንዲት ቋጥኝ ስር ምሽግ ሰርተው ሁለቱ የራስ ካሣ ልጆች ደጃዝማቾቹን አበራንና ወንድ ወሰንን አገኘዋቸው፡፡ በስማም፣ እንዴት ተለውጠዋል፡፡ ሳገኛቸው እነዚያ ደጃዝማቾች የማውቃቸው የማውቃቸው አልመስል ብሎኝ በመከራ ነው እነሱ መሆናቸውን ያወቅሁት፡፡ ያ ምርጥ በወርቅ የተሽቆጠቆጠ የወታደር ልብሳቸው በራሳቸው ላይ ተቦጫጭቆ ከማለቁም በላይ በጭቃና በረጋ ደም ተለውሶ ልዩ አድርጎቸዋል፡፡

"አይ... ፈረንጅ....." እያሉ የደስታና የመደነቅ ፈገግታ እየታየባቸው፣ ሁለቱ ወንድማማቾች ከምሽጋቸው ወጥተው በየተራ እያቀፉ ሳሙኝ፡፡ "አይ...ፈረንጅ..." አሁንም እየሳቀ፣ እየተደነቀ ወንድወሰን ወደምሽጉ ተመለሰ፡፡ አበራ በመደሰት በድጋሚ አቅፎ ሳመኝና እዝን ብሎ፣ "ብዙ ወታደሮችን ስለናንተ ስጠይቅ" አለና አሁንም ካቀረቀረበት አንገቱን ቀና አድርጎ እኔን እያየ፣ "ሁላችሁንም ሽፍቶች ጨፍጭፈው እንደገደሏችሁ ነበር የነገሩኝ፡፡ አሁን እንዲህ ሳይህ እንዴት ደስ እንዳለኝ ልነግርህ አልችልም፡፡ ና፣ ና ጌታ" አለና ወደ ምሽጉ ሲያስገባኝ ወንድወሰን ጀርባዬን እየቸበቸበ በመሃላቸው እንድቀመጥ ጋበዘኝ፡፡ በዚያች ጠባብ ምሽግ ውስጥ እንደተቀመጥን አበራ ኪሱን ዳብሶ አንዲት ቆሎ የያዘች ትንሽ ከረጢት አቀበለኝ፤ "ዋሽንብራ ቆሎ፡፡"

የመጨረሻው ድሀ የሀበሻ ወታደር ምግብ፣ ቀለብ፣ ሽንብራ ቆሎ። ምንም እንኳን ሁለቱ ደጃዝማቾች ለራሳቸው የሚበሉት ባይኖራቸውም ትንሿን የሽንብራ ቆሎ ከረጢት ተዉሉኝ። ወዲያው አበራ የጦር ሜዳ ኮዳውን አቀበለኝ። በዚያች የጦር ሜዳ የወታደር ኮዳ ውስጥ የቀረችውን እንጥፍጣፊ ድፍርስ ውሃ ጭልጥ አድርጌ ጠጣኋት።

በዚች የመከራ ጊዜ እፍኝ የሽንብራ ቆሎና አንዲት ጉንጭ ቆሻሻ ድፍርስ ውሃ በዚች የመከራ ጊዜ እፍኝ የሽንብራ ቆሎና አንዲት ጉንጭ ቆሻሻ ድፍርስ ውሃ ፓሪስ ከተማ ውስጥ ካለ ምርጥ ሆቴል ውስጥ ከሚዘጋጅ ምርጥ ምግብና ምርጥ ሻምፓኝ በላይ ይጥማል፣ ይጣፍጣል። ጥቂት ቆየት ብለው ኮሎኔል ኮኖቫሎቭና ወዳጄ አቶ ብረየር ከጃጥኗ ስር አርፈው ሲያዘግሙ ቆይተው መጥተው ከሁለቱ ደጃዝማቾች ምሽግ ተቀላቀሉ።

ከነዚህ ወንድማማች ደጃዝማቾች ምሽግ በታች ከጊባ ወንዝ ማዶ ያለውን ጭልጥ ያለ ሜዳ በግልጽ ማየት ይቻላል። በርቀት የከብቶች፣ የአጋሰሶች፣ የታንኮች፣ የብረት ለበስ ተሽከርካሪዎችና የጠላት ጦር ወታደሮች ኮቴ የሚያስነሳው አቧራ እንደ ዳመና ሲቋጠር ከሩቅ ይታያል።

ሁለቱ ደጃዝማቾች በጦር ሜዳ መነጽሮቻቸው ወደዚያ አቧራ ወደሚጨስበት አቅጣጫ ሲመለከቱ ቆይተው ለወታደሮቻቸው ትዕዛዞችን ይሰጣሉ። ወዲያው አበራ ወደኔ ዞር ብሎ፣ "ጣልያኖች በቀጥታ ወደኛ እየመጡ ነው። እዚህ የረባ ጦር ስለሌለን ቆሞ መጠበቁ ዋጋ የለውም። በፍጥነት ወደ ራስ ካሣ ጦር መሄድ አለብን" አለኝ። ወድያው የደጃዝማቾቹ አሽከሮች ሁለት ፈረሶች ጭነው ስለመጡ ሁለቱ ደጃዝማቾች በፈረሶቻቸው ላይ ተቀምጠው እየጋለቡ ወደ ፊት ሄዱ። ዋናው የሰሜኑ ጦር፣ የአባታቸው የራስ ካሣ ጦር ወደ ሰፈረበት አቅጣጫ። እኛም ሁለቱን ደጃዝማቾች ከሚያጅበው እግረኛ ጦር ጋር ተቀላቅለን ጉዞ ጀመርን። የዚያን እግረኛ ጦር ፈጣን ሩጫ ቀረሽ እርምጃዎች መመጠን ግን ከአቅማችን በላይ ሆነ፣ ወደኋላ ቀረን።

እነሆ ሶስት ቀንና ሶስት ሌሊት ባይናችን እንቅልፍ ሳትዞር እየሸሸን ነው። እንዲህ ወደኋላ ቀርተን ስናዘግም፣ በአናታችን ላይ አንድ ባለሶስት ሞተር ግዙፍ አውሮፕላን ሲበር መጥቶ አይቶን ከሄደ በኋላ እንደገና ተመልሶ የቦምብ ናዳውን ያወርድብን ጀመር። እንዲህ እየተመላለሰ ቦምብ ሲያወርድ ቆይቶ፣ እንደገና እየዞረ በአውሮፕላኑ ላይ በተጠመዱ መትረየሶች ሰራዊታችንን ሲረሽን፣ ወታደሮቻችን አሮጌ ጠመንጃቸውን ማናገር ጀመሩ። እንዲያም ሆኖ በነዚያ አሮጌ ጠመንጃዎች ያንን የሰማይ ላይ ንጉሥ አንበሳ ጎትተው ከመሬት ጣሉት። ያ የሰማዩ ላይ ብቸኛ ገዢ፣ አቅመ ቢስ ሆኖ በሜዳው ላይ ሲገላበጥ ኢትዮጵያውያን ጀግኖች ከያቅጣጫው እየፎከሩና እየሸለሉ ግዳያቸውን ሊያዩ ወደዚያ ግዙፍ አውሮፕላን ሮጡ።

በዚህ መሀል የሁለቱ ደጃዝማቾች ጦር በጣም ርቆን ሄደ። የደከሙ እግሮቻችንን እየጎተትን ወደፊት ማዝገም ግድ ነበርና ያለ የሌለ ኃይላችንን

አጠራቅመን ወደፊት ሄድን። እጅግ በጣም ሲበዛ ተጠምተናል። አልፎ አልፎ የምናገኛቸውን ወታደሮች ውሃ እንዳላቸው ብንጠይቅም፣ እራሳቸው ከሶስት ቀን በላይ ባፋቸው ጠብታ ውሃ እንኳን ገብታ እንደማታውቅ እያስተዛዘኑ ነገሩን።

እንዲህ ተጠምተንና ደክመን ወደፊት ስንሄድ ኮሎኔል ኮኖቫሎቭና አቶ ብረየር ወደኋላ ቀሩብኝ። ለሁለቱም ከሚችላቸው በላይ ሆኗል። በጣም ደክመዋል። ስለዚህ ቢያንስ ጥቂት ውሃ እንኳን ይገፍላቸው ብመጣ ብዬ፣ ሁለቱን ወዳጆቼን ከጥላ ስር አስተኛቼ እኔ ወደፊት ተንገዝኩ። ከወታደሮቻችን እንደሰማሁት ሁለቱ ወንድማማች ደጃዝማቾች ምናልባትም ሁለቱ ራሶች ሳይቀሩ የመሸጉባት ዋሻሩቅ እንደማትሆን በልቤ እያሰብኩ ወደፊት ሄድኩ።

ነፍሴ አፌ ደርሳ እየተጎተትኩ የግዴን እየተራመድኩ ራሶች መሽገውበታል ወደተባለችው ዋሻ ተቃረብኩ። እኔ እንዲህ በመከራ የገዛ እግሮቼን እየጎተትኩ ስራመድ ከርቀት የራስ ካሣ የክብር ዘብ ዋና አዛዥ ቀኛዝማች አበበን ወደኔ ሲሮጥ አየሁት። ቀኛዝማች አበበ ወደኔ እየቀረበ ሲመጣ ብዥርዥር እያለብኝና ቀኛዝማች አበበ ከአካባቢው ጋር እየተመሳሰለ ገጽታው እየጠፋብኝ መጣ። ብዙም ሳይቆይ አይኖቼ የሚያዩት ጨለማ ብቻ ሆነ። ከባድ ጨለማ። በዚህ መሀል ተዝለፍልፌ ወደቅኩ። ብዙም ሳልቆይ ቀኛዝማች አበበ ከወታደሮቹ ጋር ተሸክሞ ወስዶኝ ኖሮ ሁለቱ ራሶች ከመሸጉባት ቀዝቃዛ ዋሻ ውስጥ ተኝቼ ነቃሁ። ራስ ካሣ እኔ እንደተኛሁ ከጎኔ ተቀምጠው በሀዘን ቁልቁል እያዩኝ ገና አይኔን ስገልጥ "አይ ...ፈረንጅ" አሉና በደስታ ሲያዩኝ ቆይተው፣ወዲያው ቀጥለው "ሌሎቹስ ፈረንጆች ጌታ?" አሉኝ።

"የኔ ጓደኞች?" አረፍተ ነገሯን አልጨረስኳትም። መናገር አልችልም፤ በውሃ ጥም አፌ ደርቋል፣ ምላሴ አብጧል። ስለዚህ እንደምንም ብዬ በእጆቼ ሁለቱ ጓደኞቼ ከዚህ ራቅ ብለው ከጥላ ስር መተኛታቸውን ላስረዳ ሞከርኩ። ራስ ካሣ ግን በትክክል አልተረዱኝም። ወደ ራስ ስዩም ዞር ብለው "ዋይ ዋይ !ዋይ ዋይ ! ሁሉም ፈረንጆች ሞተዋል" አሉ። በዚህ መሀል ቀኛዝማች አበበ ቀዝቃዛ ውሃ የያዘቹውን የጦር ሜዳ ኮዳውን ስላቀበለኝ አፌን አረጣጥቤ "አልሞቱም" አልኳቸው።

ከዚህ ብዙም ሳይርቅ ከአንዲት የዛፍ ስር ጥያቸው ውሃ ፍለጋ ብቻዬን እንደመጣሁ አስረዳሁ። ወዲያው ወታደሮች ሄደው ይዘዋቸው መጡ። ብዙም ሳይቆይ ማታ በጨለማ የተጠፋፋነው ዶክተር ሹፐለርና ካፒቴን ሄስኪም ስለመጡ ሁላችንም እንደገና በአንድ ላይ ሆንን። ከዚያ በዛች ዋሻ ለሁለት ሰዓታት ያህል ጤናማና ጥልቅ እንቅልፍ ወሰደን። ከሁለት ሰዓት በኋላ በራስ ካሣ ትዕዛዝ ተቀስቅሰን ተነሳን።

ራስ ካሣ "በጣሊያን ጦር ተከበናል። እና እንደምንም ብለን ከዚህ ከከበበን የጠላት ጦር ሰብረን መውጣት ይኖርብናል" ካሉ በኋላ "በቀጥታ ወደ አምባላጌ

በሚጠበቀው መንገድ በኩል፣ በብረት አጥር አጥሮ የያዘንን ጣልያን ተዋግተን ማምለጥ አለብን። እግዜሩም ይረዳናል" አለ።

አዎ አምባላጌ የንጉሠ ነገሥቱ ጦር ይጠብቀናል። ከእግዚያብሔር እርዳታ ጋር ከዚህ የብረት አጥር ሰብረን መውጣትና ከጃንሆይ ጦር ጋር መቀላቀል ከቻልን፣ ጣሊያንን ሳንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ወሳኝ በሆነ ቦታ ላይ ገጥመን ድል እንመታው ይሆናል።

በዚህ መሀል ለረጅም ጊዜ ያላየሁት ወዳጄ ልጅ ወልዴ በራሶች ቀኝ ፊተግታው ሳይለየው ብቅ አለ። ልጅ ወልደ ገብርኤል፣ ከዛሬ ሁለት ሳምንት በፊት ወደ ራስ ሙሉጌታ የጦር ሰፈር ለመዝለቅ ባደረኩት ጉዞ አብሮኝ የነበረውና ነፍሴን ያዳነኝ ልጅ ወልደ ገብርኤል፣ "አየኸሁ! ዛሬስ አንዱን የጣልያን አውሮፕላን ከሰማይ ጎትተን አውርደን ከመሬቱ ከስከስነው" አለ። ቀጥሎም "ጉዱን ልይ ብዬ ወደወደቀበት ቦታ ሄጄ ነበር። ጉድ ነው፣ በዚያ በተከሰከሰ አውሮፕላን ውስጥ ከአራቱ ደብዳቢዎች በተጨማሪ ሞታም እንኳ የምታምር ቆንጂዬ ልጅ ነበረች" አለ።

ሌሎችም ወታደሮች በተከሰከሰው የውጊያ አውሮፕላን ውስጥ ከአራቱ ወታደሮች በተጨማሪ፣ ወታደራዊ ልብስ የለበሰች መልከ መልካም ወጣት ሴት ልጅ ሬሳም ማየታቸውን መስክረዋል። ማን ትሆን ያቺ ወጣት?

ጣልያኖች አንድም ጊዜ ሴቶች በዚህ ጦርነት ስለመካፈላቸው ትንፍሽ ብለው አያውቁም። ይቺ በኋላ ቀር ጠመንጃ ተመትቶ በወደቀው አውሮፕላን ውስጥ ሞታ የተገኘች ሴት፣ በዚህ ጦርነት የተገደለች ሁለተኛዋ ሴት መሆኗ ነው። የመጀመሪያዋ በጥር ወር በወራዩ አምባ በተደረገው ጦርነት ግንባራዋን ተመታ የተገደለቺው ናት።

ቀሪውን ቀን የኢትዮጵያ ወታደሮች ሌሊት ለሚደረገው "የብረቱን አጥር ሰብሮ የመውጣት ጉዳይ" ዝግጅታቸውን ሲያደርጉ ዋሉ። የራስ ካሣም አሽከሮች የጌታቸውን ሳጥኖች እየከፈቱ በጣም አስፈላጊ የሆኑትን ብቻ እየመረጡ ካስቀሩ በኋላ አቢ አዲ ላይ ያላቃጠሏቸውን መዛግብት ጭምር እዚህ አቃጠሏቸው።

ጀንበር ከመጥለቋ፣ ሁለቱ ራሶች ጥንታዊውን ወታደራዊ የጦር ልብሶቻቸውን ለብሰው መሳሪያዎቻቸውን ይፈታትሻሉ። ራስ ሥዩም ከነጠረ ብረት የተሰራውን ምርጡን ሰይፋቸውን እያገላበጡ ስለቱን በጣታቸው ይዳስሳሉ።

ጀግናውና ደፋሩ ደጃዝማች መሸሻ የከንባታውን ጦር እየመራ እንደቀዳሚ ጦር ከጦር ሰፈራችን መጀመሪያ ወጣ። ዋናውን ጦር የቀኝ ክንፍ ለመከላከል ፊታውራሪ ዘውዴ ጦሩን ይዞ እሱም ከምሽጉ ወጥቶ ሄደ። የዋናውን ጦር የግራ ክንፍ ለመከላከል የሰላሌው ጦር መሪ ደጃዝማች አበራም ከምሽግ ወጥቶ ሄደ። በመጨረሻ ዋናውን ጦር ደጃዝማች ወንድወሰን እየመራ መሀል ለመሀል፣ ፊት ለፊት ወደ ጣልያኖች ገሰገሰ።

ቀዳሚው ጦር ድምጹን አጥፍቶ፣ ሳይታሰብ በድንገት ደርሶ ከጣልያኖች ጋር መግጠሙን የሚያበስር ዜና ከአንድ ሰዓት በላይ እየጠበቅን እያለ፣ በመጨረሻ አንድ ትንፋሹን መዋጥ የተቸገረ መልክተኛ መጣ። አዎ ቀዳሚዎቹ ጦሮች ደጃዝማች መሸሻ፣ ደጃዝማች አበራ፣ ደጃዝማች ወንድወሰንና ፊታውራሪ ዘውዴ ከጣልያን ጦር ጋር ግብ ግብ ገጥመዋል። ጀግኖቹ የኢትዮጵያ ልጆች የጣልያኑን ጦር ከተለያየ አቅጣጫ ከበው እየጠዘጠዙ ለዋናው የራሶቹ ጦር መንገድ እየከፈቱ ናቸው።

አሁን የኛ ሰዓት ደረሰች። በሁለቱ ራሶች የሚመራ ያ ሁሉ ሺህ ጦር አንዲት ኮሽታ ሳያሰማ ወደ ታች ወደ ጊባ ወንዝ መውረድ ጀመረ። ራሶች ባስተላለፉት ጥብቅ ትዕዛዝ መሰረት ማንም ወታደር ምንም አይነት አላስፈላጊ ግርግርና ድምጽ ሳያሰማ በተቻለ ፍጥነት ወደ ጊባ ወንዝ መውረደ አለበት። አንድ ጊዜ በሺዎች የሚቆጠሩ ነጭ ሸማ ለባሽ ወታደሮች ብቅ ይሉና በቅጽበት ይሰወራሉ። ወዲያው ደግሞ በሺዎች የሚቆጠሩ ዝምተኛ ወታደሮች ይከቡንና ከጥቂት ቆይታ በኋላ በዚያች ቁልቁለት ላይ ብቻችንን እንቀራለን። ልክ እንደመንፈስ ወታደሮች ዱካቸው ይጠፋል። እንዲህ ባለ ፍጹምነት ነበር የኢትዮጵያ ወታደሮች የመሪዎቻቸውን የራሶችን ትዕዛዝ የሚያከብሩት።

ሁለቱ ራሶች ጦራቸውን በግንባር እየመሩ ወደ ጊባ ወንዝ የወረዱት አንድም የኛ ሰላዮች ባመጡት ወሬ "የጣልያኑ ጦር ደካማ ጎን የጊባ ወንዝ በመሆኑ፣ ሁለተኛና ዋናው ምክንያት ውሃ በማስፈለጉ ነው። አብዛኛው ወታደር ከሶስት ቀን በላይ ጠብታ ውሃ አልቀመሰም። ስለዚህ ያለቀው አልቆ ከጊባ ወንዝ መድረስ አለብን። ያለ ውሃ ጦራችን ለጦርነትም ሆነ ለሽሽት ብቁ አይደለም። እኩለ ሌሊት ግድም ላይ ከጊባ ወንዝ ዳርቻ ደረስን። በመካከላችን ያ አስፈሪ፣ ከሞት በላይ አስፈሪ፣ ከጦር ሜዳ ጩኸት፣ ፉከራና ሽለላ በላይ የዘገነነ ፀጥታ እንደሰፈነ ነው።ይህ አይነት ፀጥታ ማለት ጀግናውና ቀዳሚው ጦራችን የጣልያንን ጦር ገትሮና ወጥሮ ይዞታል ማለት ነው።

የጊባን ወንዝ፣ በዝግታ ድምጹን አጥፍቶ የሚፈሰውን ውሃ ስናይ የራሶችን ጥብቅ ትዕዛዝ ጥሰን ራሱን እንደሳተ ሰው ምንም ነገር ሳናግደን ወደ ወንዟ ሮጥን። ጎን ለጎን ተኝተን እንደከብት በቀጥታ ባፋችን መጠጣት ጀመርን። ከኔ በስተቀኝ በኩል ሁለት ፈረሶች ይጠጣሉ። ከኔ ከፍ ብሎ ከወንዟ ማዶ አንድ የኢትዮጵያ ወታደር በጉዞ ብዛት የደከሙ እግሮቹን ይታጠባል። እና ግን ምን ይሁን? ውሃ ጠምቶኛል፣ ተቃጥያለሁ። ይቺ ወንዝ በመርዝ የተበከለች መሆኗን ባውቅ እንኳን እጠጣ ነበር። ብቻ ሆዴ እስኪቀዘር ጠጣሁ።

እየነጋ ነው። በዚህ መሀል አንድ ጥይት ተተኮሰች። ምናልባት የተዘናጋ የኢትዮጵያ ወታደር የባረቀበት ስለመሰለን ተዘናግተን እንደተቀመጥን በተደጋጋሚ የተኩስ መዓት ይወርድብን ጀመር። እስር፣ ሀያ፣ ኀምሳ፣ መቶ ጥይቶች በአናታችን ላይ እያፏጩ አለፉ። እዚህም እዚያም ወታደሮቻችን ሳይተኩሱ ወደመሬት መውደቅ

ጀመሩ። ወዲያው በማናየው ጠላታችን ላይ የመልስ ተኩስ ከፈትን። መሽጎ ተኩስ የከፈተብን ጠላታችን ከጥቂት ደቂቃዎች ውጊያ በኋላ ፀጥ አለ።

እዎ የትግራይ ሽፍቶች ነበሩ። የተቆረጠ፣ የደከመና በሽሽት ላይ ያለ አነስተኛ ቁጥር ያለው የኢትዮጵያን ወታደር ያገኙ መስሏቸው የቋጠሩትን የመጨረሻ ንብረቱን ገድለው ሊዘርፉት ያሰፈሰፉ የትግራይ ሽፍቶች፣ ዋናውን የራስ ካሣን ጦር እንደገጠሙና እንደደፈሩ ሲረዱ እግራን አውጪኝ ፈረጠጡ።

እነዚህን ሽፍቶች ተከታትሎ ለማሳደድ ጊዜ የለንም። በተጨማሪ ራስ ካሣ በተቻለ መጠን ያለ ብዙ በተቻለ መጠን ከአጉል ግጭቶች መራቅ አለብን ስላሉ፣ በተቻለ መጠን ያለ ብዙ በተቻለ መጠን ከአጉል ግጭቶች መራቅ አለብን ስላሉ፣ ከሚጠብቀን የንጉሡ ጦር ጋር መቀላቀሉ መስዋዕትነት ወደ አሸንጌ ሐይቅ መውረድና ከሚጠብቀን የንጉሡ ጦር ጋር መቀላቀሉ ቀዳሚ የጦሩ አላማ በመሆኑ፣ የንጉሡን ጦር አጠናክረን የመጨረሻውን ወሳኝ ጦርነት ልናደርግ ወደ አሸንጌ ሐይቅ ወረድን።

ለዚያም መሰለኝ መንገዳችንን ለማሳጠር የጊባን ወንዝ ለቀን የተራራውን መንገድ የመረጥነው። የጊባ ወንዝ ትንሿን ተራራ አንድ ጊዜ ዞራ ስለምትመለስ ተራራውን ከመዞር ተራራውን ወጥተን እንደገና ወርደን ተመልሰን ከጊባ ወንዝ የገባነው። በዝግታ በምትፈሰው የጊባ ወንዝ ውስጥ ጫማችንን አውልቀን፣ በትከሻችን አንግተን፣ የጠጣነውን ውሃ እያንቦጫረቅን ወንዟን ተከትለን ጉዟችንን ቀጠልን። አሁን የምር እየነጋ ነው። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ከባለግርማ ሞገሱና አስፈሪው የሰሜን ተራራ አናት ላይ ፀሐይ ብርሃኗን ትፈነጥቃለች።

ይሁን እንጂ የአርባ ቀን እድላችን እንዳሰብነውና እንደተመኘነው በቀላሉ ያለ ብዙ ጉዳት ከዚያ በብረት አጥር አጥሮ ከያዘን የጠላት እጅ ልናመልጥ አልቻልንም። ጫማችንን እንኳን እስክንጫማ እድል ሳይሰጥ ከጊባ ወንዝ ማዶ የጣልያን መትረየስ ያንራብን ጀመር። ከጊባ ወንዝ ወደላይ ወደ ሜዳው ለመውጣት የሞከሩት ወታደሮቻችን አንድ እግራቸው ሜዳውን ከመርገጡ በጣልያን መትረየስ ደረታቸውን እየተመቱ ተመልሰው ወደ ጊባ ወንዝ ወደቁ። የጀግኖቹ ወንድሞቻችን ደም ከጊባ ወንዝ ውሃ ጋር መቀላቀል ጀመረ። አዎ ጣልያኖች ወሳኝ የሆኑ ወታደራዊ ቁልፍ ቦታዎችን ሁሉ ተቆጣጥረዋል። ጣልያኖች እያንዳንዷን የሚጠረጠር እንቅስቃሴ በመትረየሶቻቸው ያናግራሉ፤ ይደበድባሉ። አዎ የጊባን ወንዝ ጭቃ እያጠነ፣ የጣልያን መትረየሶች የሞት እሳት እያፏጩብን ነፍሴን አውጪኝ ሩጫችንን እንንዛለን ገፋንበት። እኛ እንዲህ አቀርቅረን ስንሮጥ ጀግኖቹ የኢትዮጵያ ልጆች የጊባን ወንዝ ተሻግረው የጣልያንን ጦር የጨበጣ ውጊያ ገጠሙት። እኒያ ጀግኖች ጦራቸውን እየሰበቁ፣ ሰይፋቸውን እያወናጨፉ የነዚያን መድፎች አፍ ለመዝጋት ወደፊት ሄዱ። ብዙም ሳይቆይ እነዚያ ሞት የሚተፉ መትረየሶች አፋቸው ተዘጋ።

ይሁን እንጂ ይቺ በኢትዮጵያውያን እጅ የገባች ድንቅና ሙሉ ጀግንነት የተሞላባት የድል ውጊያ ሌሎች ጠላቶቻችንን ጠራችብን። አሁን የራስ ካሣ የኋላ

ደጀን ጦር የምር የሞት ሽረት ትግል ውጊያ ማድረግ አለበት። ይቺን ምንም መከላከያ ወይም መደበቂያ የሌላትን ወንዝ ሁለት ጊዜ የጠላት መትረየሶች የሞት እሳት እየረጩብን መሻገር አለብን። ረፋዱ ላይ ለጥ ያለ አሸዋማ ሜዳ ላይ ደረስን። አልፎ አልፎ ከሚታዩ ከፍ ከፍ ካሉ ግራሮች በስተቀር ምንም መደበቂያ የሌለው ሜዳ ነበር። ጣጣችን ገና አላለቀም።

በዚች አሸዋማ ሜዳ ውስጥ ተጋልጠን ስንጓዝ እነዚያ የሰማይ ላይ ንስሮች ብቅ ማለት ጀመሩ። የመጀመሪያዋ አውሮፕላን አልፋን በረረችና ብዙም ርቃ ሳትሄድ የቦምብ ሸክሟን ማውረድ ጀመረች። ከፊት ለፊታችን በግምት 200 ሜርት ርቀት ላይ ወድቃ ቀይታ የፈነዳች አንድ ቦምብ ያስነሳችው የአሸዋ አቧራ ፊታችንን ገረፈን። ከዚያ በተከታታይ በተወሰነ የጊዜ ርቀት በተደጋጋሚ እየዞረች ደበደበችን። እንዲህ በተወሰነ ደቂቃዎች በዛች አሸዋማ ሜዳ ላይ የሚወድቁት ቦምቦች ያችን ሜዳ ጉድጓድ በጉድጓድ አደረጓት። ይኼም አነሳቸው መሰል የጣልያን መድፎችም ለክፉ ስላምታ ላንቃቸውን ከፈቱብን።

ከዚች ምንም መሸሸጊያ ከሌላት ገላጣ ሜዳ በፍጥነት መውጣት አለብን፤ እናም የመድፎቹ ድንፋታና የቦምቦቹ ድብደባ ሳይበግረን ወደፊት አልን። ይሁን እንጂ ይቺ ገላጣ ሜዳ መጨረሻ እንደሌላት ሁሉ በጣም ረዘመችብን። ጥቂት ሜትሮች እየሮጥን ወዲያው ወድቀን እንተኛና፣ በፍጥነት ተነስተን እየሮጥን ከፊታችን የወደቁትን የትግል ጓደኞችን እነዚያ ቦምቦች በቆፈሩት ጉድጓድ ወስጥ ገፍትረን እንደነገሩ አፈር እያለበስን ወደፊት አልን።

እንዲህ ፍዳችንን እያየን ከዚች አደገኛ አሸዋማ ሜዳ ብዙም ሰው ሳናጣ በጥቂት መስዋዕት ብንወጣም፣ መከራችን ግን ገና አላለቀም ነበር። ከረፋዱ ጀምሮ እስከ መሽ ድረስ በኢትዮጵያ ወታደሮች ላይ የሚወርደው የቦምብ ዝናብ ሳያባራ መሸና እነዚያ ርጉሞች ወደ መቀሌ ተመለሱ።

በትናንሽ ተራሮች ጫፍ ላይ የተሰቀሉት የጣልያን ባንዲራዎች እንደሚጠቁሙን ቀኑን ሙሉ ስንጓዝ የዋልነው ቀድሞ ብለው በጣልያኖች እጅ በወደቁ ቀበሌዎች ውስጥ ነበር። እንዲያውም ለተወሰኑ ጊዜያት ጣልያኖች በየድልድያ በስሩት የጥርጊያ መንገድ ተጓዝናል። ምንም እንኳን ጣልያኖች ዘመኑ ያፈራውን ምርጥ መሳሪያ የታጠቁ፣ በቁጥሩ ሁለት እጥፍ የሚሆን ጦርና በብረት ለበስ ተሽከርካሪዎች፣ በታንኮች፣ በመድፎችና በአውሮፕላኖች የሚታገዙ ቢሆንም እንዳሰቡት የራስ ካሣን ጦር በተንበረ በብረት አጥር አስሮ ብትንትኑን ለማውጣት ሳይቻላቸው ቀርቷል።

የኢትዮጵያው ጦር ወደኋላ ሲያፈገፍግ በትንንሽ ቡድን ተከፋፍሎና ተበታትኖ የራሱን ቀኛዝማች፣ ግራዝማች፣ ባላምባራስና ሹም ተከትሎ ወደ ዋናው አላማው ወደ አሸንጌ ሐይቅ በራሱ ጥረትና ሀላፊነት መድረስ ነው። ለዚህም አላማው ከጣልያኖች፣

ከሽፍቶችና ከራያዎች ጋር የሞት ሽረት ትንቅንቅና ትግል እያደረገ፣ እየወደቁና እየተነሳ ወደ አሸንጌ ሐይቅ ገሰገሰ፤ ወረደ።

የልጁ (አቢቹ) ጦር አሁን ከምንጊዜውም በላይ ተጠናክሯል። በርከት ያሉ ሹምቻቸው በየጦር ሜዳው የወደቁባቸው ወጣት ወታደሮች ከጀግናውና ከጀብደኛው የአቢቹ ጦር ጋር ከመቀላቀላቸውም በላይ በርካታ ምርጥ የትግራይ ልጆችን ያቀፈ ጦር ስለነበረ ያለምንም ካርታ በቀላሉ የሚንቀሳቀስና ሴቶች፣ ልጆችና አዛውንቶች የሌሉበት፤ ከግማሽ በላይ የሚሆነው ጦሩ በራሱ ፈረስ የሚንቀሳቀስና፣ በጣሊያኑ ጦር ላይ ድንገት ባልታሰበ ሰዓትና ቦታ ደርሶ አደጋ የሚጥልና እንዳመጣጡ የሚሰወር ጦር በመሆኑ ጣልያኖች ክፉ ቂም ከያዙበት የኢትዮጵያ ጦር አንዱ ነበር።

የደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ሰዎችማ ይኼን አንበሳ ጦር እንዴት እንደሚንቀጠቀጡለት እግዜር ብቻ ነው የሚያውቀው። ምንም እንኳን ይኼ የከፋው ጦር ማለትም ዋናው የልጁ አቢቹ ጦር ታማኝነቱ ለሰላሌው ጦር ደጃዝማች አበራ ቢሆንም፣ ይኼ ጦር፣ ጦር ከሆነበት ቀን ጀምሮ እስካሁን ከማንኛውም ደጀዝማችም ሆነ ከሁለቱ ራሶች ምንም አይነት ትዕዛዝም ሆነ መመሪያ ተቀብሎ የማያውቅ፣ ከጣልያኖችና ከደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ሰራዊት በሚዘርፈው ንብረት ሰራዊቱን የሚያስተዳድር ጦር ነው።

ይኼ የአቢቹ ጦር ለሁለቱ ራሶች "ተራ የጥጋበኛ ሽፍቶች ክምችት" ነው። ጃንሆይም ቢሆኑ "ይኼ በአንድ ባለጌ ወጣት የሚመራ ጦር" ለሁለቱ ራሶች በተለይም ለራስ ካሣ በተደጋጋሚ ባስተላለፉት ትዕዛዝ አሻፈረኝ በማለቱና ሁለቱ ራሶች ልጁን ወደ እናት ጦሩ ለመመለስ ያደረጉት ያላሰለሰ ጥረት ውጤት አልባ በመሆኑ፣ ጃንሆይ በአቢቹና በጦሯ ላይ ሳይቆጡ አልቀሩም።

በኋላ ላይ እንደሰማሁት ይኼ ጀግናውና ጀብደኛው የአቢቹ ጦር አወቃቀር ይፋ ባይሆንም በአራት ጀነራሎች የሚመራ ነበር።

1ኛ በጀኔራል ሀብቶም የሚመራ የሀማሴን ልጆች ጦር፣
2ኛ በጀኔራል ተሰፋጺዮን የሚመራው የትግራይ (የመቀሌ) ልጆች ጦር፣
3ኛ በጀኔራል ጋሹ የሚመራው የጎጃም (የዳሞት) ልጆች ጦር፣
4ኛ በጀኔራል ወርቁ የሚመራው ዋናው የሰላሌ ልጆች ጦር ሲሆን እነዚህ አራት ጀኔራሎች ከነጦራቸው ታማኝነታቸው ለልጁ ለአቢቹ ነበር።

እናም እነሆ ለመጀመሪያ ጊዜ ይኼ ጦር ወደ አሸንጌ ሐይቅ እንዲወርድ ከደጃዝማች አበራ ቀጭን ትዕዛዝ ሲደርሰው ትልቅ ፈተና ላይ ወደቀ። እነዚህ አራት ጀኔራሎችና መሪያቸው አቢቹ አንድ ሌሊት ሙሉ ሲመክሩ አድረው በመጨረሻ ባለአራት ነጥብ ውሳኔ ላይ ደረሱ።

1ኛ የትግራይ ልጆች ጦሩን እያገዙና መንገድ እየመሩ ወደ አሸንጌ ሐይቅ ወርደው ከዚያ ወደየቀበሌያቸው እንዲመለሱ፤
2ኛ የጎጃም (የዳሞት) ልጆች ከአሸንጌ ሐይቅ በኋላ ወደዳሞት የሚመለሱበትን ሁኔታ አሸንጌ ሐይቅ ላይ እንዲመከርበት፤
3ኛ የሰላሌ ልጆች ጦር የደጃዝማች አበራን ጦር ተከትሎ ወደ ሰላሌ እንዲመለስ
4ኛ፤ መመለሻ የሌለው የሀማሴኑ ጦር ከሰላሌው ጦር ጋር ተቀላቅሎ የዚህ ጦር እጣ ፈንታ ተካፋይ እንዲሆን ተስማምተው፣ የደጃዝማች አበራን ትዕዛዝ ተቀብለው ከደጃዝማች መሸሻ የከንባታው ጦር መሪ ጋር ጎን ለጎን የጠላትን ጦር እያርበደበዱ ወደ አሸንጌ ሐይቅ ወረዱ።

ከቀትር በኋላ ነው። ፀሐይዋ ግን አሁንም እንደ እሳት ትፋጃለች። አንድዳ አንድዳ ነፍሳችንን ልታወጣው ነው። ይኼው 10 ሰዓት ሙሉ ያለ ውሃ በመንገድ ላይ ነን። አስር ሰዓት ሙሉ በዚች በረሀማ ቀበሌ ለአፍይታ ያህል እንኳን ወገባችንን ሳናሳርፈው የደከሙ እግሮቻችንን እየጎተትን በጉዞ ላይ ነን። ብቸኞች፣ ሁለትም ሶስትም ሆነው በጎድ ያሉ፣ በቡድን በቡድን ሰብሰብ ያሉ መንገዱና ጉዞው ካቅማቸው በላይ ሆኖባቸው አንዲት እርምጃ ወደፊት ማለት ያልሆነላቸው ወታደሮች፣ በዚያች በረሀማ ቀበሌ ተበትነው በበቀሉ የግራር ዛፎች ጥላ ስር ጋደም ብለዋል።

እነዚህ ምስኪን ወታደሮች እንዲህ በየግራሩ ጥላ ስር ጋደም ሲሉ እንቅልፉ ይዟቸው ጭልጥ ይልና ራሳቸውን አደጋ ላይ ይጥሉታል። ብዙ ጊዜ እንዲህ እንደማሽላ ቆሎ ተበትነው በየግራሩ ስር ባረፉበት የጨካኞቹ ሽፍቶች ካራ ለዘላለም አስተኝቷቸዋል። ይኼ አረመኔያዊ የሽፍቶች ጭካኔ ሊደርስበት እንደሚችል ቢገምትም እድሉን በፈጣሪ ላይ ጥሎ ጋደም ይላል። በዚህ መልኩ ስንኪትን ውለን በአንድ ወጣት ፊታውራሪ ከሚመራ ጦር ጋር ተቀላቀልን።

ከዚሁ ወጣት ፊታውራሪ ጦር ጋር ስንጓዝ ውለን ማምሻው ላይ ከአንድ ከደረቀች ወንዝ ዳርቻ ደረስን። ወታደሮቻችን እዚያች የደረቀች ወንዝ መሀል ገብተው በእጃቸው ትልቅ ጉድጓድ ቆፈሩ። በዚች ጉድጓድ ውስጥ ትንሽ ውሃ እስኪጠራቀም ድረስ እንደ እድሜ ልክ የፈጀ ጊዜ ፈጀ። እኛ ቁጥራችን ብዙ ነውና ከዚያች በመከራ የተጠራቀመች የደፈረሰች ውሃ ለመጨረሻው ወታደር የደረሰው ነገር ቢኖር ውሃ ሳይሆን ጭቃ ብቻ ነበር።

ብዙም ሳናርፍ በአንዲት ጠባብ መንገድ ውስጥ ገብተን መጨረሻው ወደማይታወቅ መንገድ ጉዞ ጀመርን። ቀበሌው ተመሳሳይ ነው። ዳገት፣ ቁልቁለት፣ ገደል፣ ሜዳ፣ ግራር፣ ቁልቋል። መጨረሻ የሌለው በሽማው ተጠቅልሎ መደዳውን የተኛ፣ ቆስሎ በሽታውን በዝምታ የሚያስታምም፣ የሞተ የኢትዮጵያ ወታደር፤ ብቻ ሁሉም በዚያች መንገድ ዳር አንዱን ካንዱ መለየት እስኪያስቸግር ድረስ በሽማው ተጠቅልሎ ተኮልኩሏል።

ጀንበር ጠልቃ ብዙም ሳይቆይ ብዙም ውሃ ከሌላት የተንቤን መጨረሻና የአበርጋሌ አዋሳኝ ከሆነችው የአረንቋ ወንዝ ዳርቻ ደረስን። ብርቱዎች እድልና

ኢትዮጵያውያኖች ሊያጠምቁቸው ከአርንቋ ወንዝ ደርሰው ጥማቸውን ቆርጠው ከድካማቸው እረፍት ለማድረግ እዚህም እዚያም ጋደም ብለዋል። አንዳንዶቹ እሳት እንድደው ሽንብራ ይቆላሉ። ከትናንት ከሰዓት በኋላ ጀምሮ ባፋችን እህል አልገባም። በአረንቋ ወንዝ ዳርቻ ትናንት ቀድመውን ከሄዱት ከሁለቱ ራሶች ጋር ተገናኘን።

ይሁን እንጂ ዛሬ ቀኑን ሙሉ በገዛ ላይ ስንመኘው የነበረው፣ ትንሽ ተኝተን የማረፉ ሀሳባችን፣ ምኞታችን፣ ሳይሳካልን ቀረ። ጠንካራ የጣሊያን ጦር ከኋላችን እየተከተለን ሲሆን ከፊታችን ደግሞ ሌላ የጣሊያን ጦር መንገዳችንን ቆርጦ ሊዘጋብንና ሊያደቀን እየታገለ ነው።

ስለዚህ ጊዜ ሳናጠፋ በጉዟችን መግፋት ስለብንና እፍኝ የሽንብራ ቆሎዬን በልቼ ሳልጨርስ፣ ጉንጭ ውሃዬን አጣጥሜ ሳልጨልጥ ነጋሪቶች መጎሰምና ጡሩንባዎች መነፋት ጀመሩ። ይኸ ደግሞ ወደፊት በል ማለት ነውና እኛም ከጦሩ ጋር ተቀሳቅሰን የደከሙ እግሮቻችንን ወደፊት አልናቸው።

ወንዟን ተሻግረን ውሃ ከሌለው የአበርጋሌ ጫካ ውስጥ ገባን። የሰው ልጅ ሊያደንቀው ሊያፈቅረው የሚገባ ገደል፣ ተራራና ሸንተረር ከፊታችን ተጋረደ። ግን ምን ያደርጋል ጊዜው የመከራ፣ የጦርነት ጊዜ ነውና ይኼን የተፈጥሮ ውበት ማድነቂያም፣ ማጣጣሚያም ጊዜ የለንምና እንደሚታደን አውሬ እየተሽሎከለክን እግሬ አውጪኝ መሮጥ ጀመርን። የሰው ልጅ ጥንካሬ የሚያስገርም ነው። በኔ ባይደርስ ባላምንኩ ነበር። ከአቢ አዲ የነቁት 4 ቀን ተነስተን፣ ከጥቂት ሰዓታት እረፍትና እንቅልፍ በስተቀር ሳናርፍ እንደሮጥን ይኼው አሁን ከመጋቢት አራት ወደ መጋቢት አምስት ልንሸጋገር ነው። አንድ ወር ሙሉ የሰው ልጅ ጥቂት እርፎ፣ እፍኝ ሽንብራ ቆርጥሞ፣ ጉንጭ ውሃ ጠጥቶ፣ ተራራ ወጥቶ፣ ቁልቁለት ወርዶ፣ ገደል ዟጦ፣ መሮጥ መቻሉ ተዓምር ነው እንጂ ሌላ ምን ይባላል?

ዛሬ ደሞ እድለኞች ነን። ራስ ካሣ ፈረሶች ላኩልን። ያለ ፈረስ በቀጣዩ ቀን ጉዞ በእግር መቻላችንን እግዜሩ ነበር የሚያውቀው። ሁለቱ ራሶች ልክ ነጋሪት ከመነፋቱ ከጠንካራው ሰራዊታቸው ጋር በፍጥነት ጉዞ ቀድመው ይኼዳሉ። በዚህ ማለቲያ በሌለው ሩጫ ደካሞቹ ቀስ በቀስ ደረጃ በደረጃ ወደኋላ ይቀራሉ። የኛም የፈረንጆቹ አጃቢ ጦር ከምንጊዜውም በላይ ቀንሶ አብረውን የቀሩት በጣት የሚቆጠሩ፣ ጥቂት ጠንካሮች ብቻ ናቸው።

እኩለ ሌሊት ግድም ላይ ጨረቃዋ ከጠራው ሰማይ ላይ ሮጣ ከሰሜን ተራራዎች ጀርባ ገብታ ተሰወረች። ያስገባት ቀበሌ ወዲያው ጥቁር ድንኳን የለበሰች መሰለች። በዚች ጥቁር መጋረጃ የሸፈናት በምትመስለው መንገዳችን ከአንድ ሜትር በላይ ርቆ ያለን ነገር ለይቶ ማየት የማይቻል ነገር ነው። ከፊታችን ደግሞ አስቸጋሪ ቢርጥና የተራራ መንገድ ይጠብቀናል። ከተራራው ስር ያሉ መንገዶች ሁሉ ዞሮ ዞሮ የሚያደርሱት ወደ ተራራው ጫፍ በመሆኑ፣ ከፊታችን የነበሩ ወታደሮች ደረጃ በደረጃ

እየተከፋፈሉ በተለያየ መንገድ ከዚህ አስቸጋሪ ጨለማ ውስጥ ለመውጣት እየተጣደፉ ገደሉን መቧጠጥ ተያያዙት። ጥቂት እንደገፉን ጨለማዋ እየጨከነች መምጣት አንድ ሜትሯም በዛች ብላ ነው መሰል፣ የአንዷን ሜትር እይታም ነፈገችን።

ከፈረንጆቹ እኔ እንደመጨረሻ ፈረሰኛ እጓዝ ስለነበር ከፊቴ የነበረውን ፈረሰኛ ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት ተሰውሮብኝ፣ አሁን ከፊቴ የማየው ነገር ቢኖር እግረኛ ሰው የሚመስሉ ነገሮች ውልብ እያሉ ሲጠፉብኝ ብቻ ነው። ይችም በዛች መሰል የነዚያም እግረኞች ዱካ ጠፉ። አሁን በዚህ በሚያስፈራ ድቅድቅ ጨለማ አስቸጋሪ በሆነውና በወጉ በማላውቀው በተራራ መንገድ ብቻዬን ቀረሁ።

ምንም ነገር አላይም፤ በትክክለኛ ወታደሮቻችን ቀድመው በሄዱበት መንገድ እንኳን እንደምሄድ እርግጠኛ አይደለሁም። አሁን ሁሉንም ነገር ለፈረሴ ተውኩለት። በነጻነት ወዳሻው ቦታ እንዲወስደኝ። ከዚህ ጨለማ እንዲያወጣኝ ሙሉ ነጻነቱን ሰጠሁት። በዚች የቁርጥ ቀን መንገድ እድሌን በፈረሴ ላይ ተውኩት።

ብልጡ ፈረሴ በጥንቃቄ በዚያች አስቸጋሪ መንገድ ይዞኝ ይኼድ ጀመር። አልፎ አልፎ ፍንጥቅ በምትለው ብርሃን ፈረሴ በገደሎች መሀል አስቸጋሪውን መንገድ በጥንቃቄ እየረገጠ ይዞኝ እንደሚጓዝ ተረዳሁ። ግን ፈረሴ ጦራችን በሄደበት መንገድ ይዞኝ እንደሚሄድ የተረዳሁት አልፎ አልፎ ደክመው መንገድ ዳር የተኙትን ወታደሮች ላለመርገጥ በጥንቃቄ ሲራመዳቸው ቢሆንም፤ ዋናው ጦራችን በሄደበት መንገድ እንደሚወስደኝ ግን እርግጠኛ ሳልሆን የሰጠሁትን ነጻነት ሳልቀማውና ሳልጋፋው፣ እንደ ሁልጊዜው ሁሉ አስቸጋሪውን መንገድ በጥንቃቄ እየረገጠና፣ በየመንገዱ ዳር ጥቂት እርፈው ለመሄድ ቁጭ ባሉበት እንቅልፍ የወሰዳቸውን ወታደሮች እየተራመደ በመንገዱ ቀጠለ።

እንበሳው ፈረሴ ንጋት ላይ ከፈረሰኛው ጦራችን ጋር ወስዶ ቀላቀለኝ። የራሶችን ጦር እንዳገኘሁ በጣም ተደሰትኩ። "አለቃህ ማነው?" ስል መጀመሪያ ያገኘሁትን የሀበሻ ወታደር ጠየኩት። "ደጃዝማች ጨቡዴ" ሲል በታላቅ ኩራት መለሰልኝ። ወዲያው ከሩቅ ደጃዝማች ጨቡዴ ሊቀበለኝ ሲመጣ አየሁት። ከተያየን ሰንብቶ ነበር። አሁን ያለሁበት ጦር አዛዥ ደጃዝማች ጨቡዴ መሆኑን ተረዳሁ። ከደጃዝማች ጨቡዴ ጋር የተለመደውን ረጅሙን የሀበሾቹን ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ ደጃዝማች ጨቡዴ "ወዳጄ ጌታ፣ አሁኑኑ መመለስ አለብህ! እዚህ አደጋ የበዛበት ቦታ ነው። ባይሆን ጥቂት ወታደሮች እሰጥሃለሁ። አሁኑኑ ወደ ዋናው ጦር መመለስ አለብህ!" ሲል አዘዘኝ።

"ለምን ደጃች?" ብዬ ላቀረብኩለት ጥያቄ፣ "ጌታዬ፣ ከፊታችን ምንም የኢትዮጵያ ጦር የለም። ከፊታችን ያለ ነገር ቢኖር የጣሊያን ጦር ብቻ ነውና ጌታዬ፣ ከዚህ ተመለስ" አለኝ። እውነትም ከርቀት ቁጥር ስፍር የሌላቸው እነዚያን አመዳም አስጠሊታ የጣሊያን ወታደሮችን ድንኳን አየሁ። ጣሊያኖች ያለምንም ሀሳብ

ድንኳኖቻቸውን ተክለው፣ በድንኳኖቻቸው ዙሪያ እሳት አንድደው ጨዋታቸውን እየደሩ አርፈው ተቀምጠዋል። የጣሊያን ጀነራሎች በአንድ ሌሊት አስቸጋሪውን የተራራ መንገድ አልፈን ከሰፈሩባት የጦር ሰፈር ደጃፍ መድረሳችንን ፈጽሞ አልተገነዘቡም። እንዱም የአውሮፓ ሀገር ጦር እንኳን በሌሊት ለዚያውም በድቅድቅ ጨለማ፤ እንዲህ አይነት በቀን እንኳ የሚያስፈራ መንገድ ለመጓዝ አይደፍርም።

ደጃዝማች ጨቡዴ በተደጋጋሚ ወደኋላ እንድመለስ ቢያዘኝም፣ ቢለምነኝም፣ ሳልቀበለው ቀረሁ። በኋላ ደጃችን ወደሌት እንደምንሄድ ጠየኩት። "ጌታ፣ መጀመሪያማ ወደ እምባላጌ ነበር መስመራችን። እምባላጌ ግን በጠላት እጅ ወደቀ። ስለዚህ አሁን ወደ ኮረም ለመገስገስ መጣር አለብን" አለኝ።

ኮረም!ኮረም! በነዚህ አስቸጋሪ ቀኖች ውስጥ ብዙ የደረቁ ከንፈሮች በደረቁ ወንዞች ዳርቻ ጠብታ ውሃ ፍለጋ የሚቆፍሩ በሺዎች የሚቆጠሩ ወታደሮች፣ በስክስክታ ኮረም፣ ኮረም ሲሉ ሰማን። ኮረም፣ ከአሸንጌ ሐይቅ በስተደቡብ በኩል ያለች ትንሽ ቀበሌ። በኮረም ጃንሆይ ከነጦራቸው ይጠብቁናል። አዎ በኮረም የመጨረሻውን ውጊያ፣ የመጨረሻውን ፍልሚያ አድርገን ቢያንስ ጣልያኖችን እዚያ ላይ እናቆማቸዋለን። የሁሉም የኢትዮጵያ ወታደር ምኞት ነበር።

አሁን ከደጃች ጨቡዴ ጋር በፈረሶቻችን ላይ ተቀምጠን በግንባር ጦሩን እየመራን ነው። በመንገዳችን ላይ ደጃች የቆየ ጨዋታ እያወራኝ ትንሽ አሳቀኝ። የምንሄድባት መንገድ በሁለት ገደሎች መሀል በመሆኑ ጨለማው ጠንከር ያለ ነበርና የዚህ ጦር መሪ ደጃዝማች ጨቡዴ ከገደሎቹ መሀል ብርሃን ፍለጋ ወደ ላይ እንድንወጣ አደረገ። ከገደሎቹ መሀል ስንወጣ ደግሞ በጣም መሽቶ ስለነበርና እላይ የተቀበለን ጫካ የበዛበት ሜዳ ስለሆነ ከሸለቆውም መንገድ የባሰ ሆነብን። ይኼን የተረዳው ደጃዝማች ፈረሱን አቁሞ ዙሪያ ገባውን ቀበሌዋን ከቃኘ በኋላ ከፈረሱ ላይ ወርዶ "ከዚህ ጨለማ ወደፊት መሄድ አንችልም። እስኪነጋ መጠበቅ አለብን" አለ።

ይቺን የግዳጅ እረፍት አብዛኛው ወይም ጠቅላላው ጦር ማለት ይቻላል በደስታ ተቀበላት። እያንዳንዱ ወታደር ባጋጣሚ በቆመበት ቦታ ያገኘውን ድንጋይ፣ ግንድ፣ ጉቶ ብቻ ያገኘውን ነገር ተደግፎና ተንተርሶ ጋደም ማለት ጀመረ። እኔም የነሱን ፈር ተከትዩ በቆምኩበት ቦታ ከፈረሴ ወርጄ አንድ ከፍ ያለ ድንጋይ ተደግፌ የቅምጥ ጋደም አልኩ። ይሁን እንጂ ብዙም ሳልቆይ የሆነ ነገር ፊቱን ሲልሰኝ ባንኜ ነቃሁ። ፈረሴ ነበር። ቡሁ የደከመው ፈረሴ አንገቱን ወደኔ አስጠግቶ ካጠገቤ ተኝቶ፣ ልፎ ልፎ እያሻሸኝ ከነዚያ በደረቅ ሌሊት በዚያ አስጠሊታ ጨኸቶታቸው የተኛን እየቀሰቀሱ ከሚያዋክቡት ልክስክስ ጅቦች እንድጠብቀው የሚማጸነኝ መሰለኝ። እስብ ካሴ ማን አለው። አንገቱን አቅፌ ጋደም አልኩ።

እየነጋ ነው፤ እናም ብዙ ጊዜ ሳናጠፋ በመንገዳችን መቀጠል አለብን። አሁን ደግሞ ቀኑ መጨረሻ በሌለው አይነት ሁኔታ በዚያ እሾሃማ ጫካ ውስጥ ስንሽሎከለክ

ቆልን። ፀሐይ በምድር ላይ ኃይለኛውንሙቀቷን በለቀቀችበት እኩለ ቀን ላይ ከዚያ ጥላማ ጫካ ውስጥ ወጥተን ምንም መጠለያ ከሌለው ገላጣ ሜዳ ላይ ደረስን። ይኼን እደጋ ብቻ የሞላበትን ገላጣ መሬት በፍጥነት ለቅቀን ወንዝ ነገር ወደምትመስል ጎድጓዳ ቦታ እንድንገባ የጦሩ መሪ ደጃዝማች ጨቡዴ ስላዘዘ፣ በፍጥነት ወደዚያች ረባዳማ ቦታ መንገዳችንን ቀይሰን ገሰገስን።

ብዙም ሳንሄድ በግማሽ ከደረቀች ወንዝ ደረስን። በዚች በግማሽ በደረቀች ወንዝ ውስጥ ያለው ውሃ፣ ውሃ የሚመስል የተበጠበጠ አፈር ብቻ ነበር። ግን የተጠማን ሰው ምን ያቆመዋል። እኔም ከፈረሴ ጎን ተንበርክኬ አጎንብሼ እንደፈረሴ ባፌ ከፈረሴ ጋር አብረን ጠጣሁት።

ደጃዝማች ጨቡዴ ብዙም ጊዜ ሳያጠፋ በጉባው ሊገሰግስ እኔ በዚያች በደረቀች ወንዝ ዳርቻ ከቀሩት ወታደሮች ጋር ቀረሁ። ሁሉም እሳት አንድዶ የሚበላ ነገር ለማብሰል ይጣጣራል። አንድ አበሻ እሳት አንድዶ፣ በኩባያ ድፍርስ ውሃ ጥዶ፣ ውሃው ሲፈላ ወደ ኮቱ ኪስ ገብቶ፣ ቆሻሻ የሞላበት ዱቄት መሳይ ነገር በጁ እያፈስ ወደ ኩባያዋ ከጨመረና ጥቂት ደቂቃዎች ካማሰለ በኋላ ከእሳቷ ላይ አወረዳት። እጅጉን በጣም ጣፋጭ የሆነች ገንፎ አብረን በላንና በላዩ ላይ ያቺኑ ድፍርስ ውሃ ቸለስንባት።

ረፋዱ ላይ ለጉዞ ተሰናዳን። አሁን የያዝናት መንገድ ካለፈቺው የደረቀች ወንዝ ጋር ተመሳሳይ ናት። ልዩነታቸው ይቺኛዋ ጠለቅ ያለች ስንጥቅ መሬት ናት። በዚች ስንጥቅ መሬት ውስጥ ለረጅም ሰዓት ስንጓዝ ቆልን።

አዎ በክረምቱ ወራት በዚች ስንጥቅ መሬት ላይ የጋይላ ወንዝ ትፈሳለች። ይቺ የጋይላ ወንዝ ዛሬ የደረቀች ቢሆንም፣ አንድ ስንዝር ያህል ጫር ጫር ማድረግ ይበቃል። ከአሸዋማው መሬት ያለብዙ ድካም በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ንጹህና በጣም ጣፋጭ ውሃ ማግኘት እንችል ነበር። አዎ አድኔለሁ፣ ስልጥኛለሁ በሚለው ሀገር የሚኖር፣ ሌሊቱን በየመሸታ ቤቱ ሲፈነጥዝ የሚያድር ሰው፣ የውሃን ውድነትና ብርቅነት ምንጊዜም አይረዳውም።

መሸና ጋደም አልን። ካለፉት ሌሊቶች ማለትም ቢድንጋያማው መሬት ላይ ካሳለፍኳቸው ከእያንዳንዷ ሌሊት፣ ምንም እንኳን ለጥቂት ሰዓታት ብቻ እንኳን ቢሆንም፣ የዛሬውን ሌሊት ጋር ሳወዳድረው የዛሬው አዳሬ በአውሮፓ ካለ ምርጥ ሆቴል አልጋ ጋር አይተናነስም። በለስላሳው አሸዋ ላይ ለጥቂት ሰዓታት ቢሆንም ጋደም ብሎ ወገብን ማሳረፍ እጅግ ደስ የሚል ስሜት ይሰጣል። ለዛሬዋ አዳሬ የኢትዮጵያ ወታደሮች በአሸዋማው መሬት ላይ እንጥፌ እንድተኛበት በርከት ያሉ ቡሉኮዎች ቢሰጡኝም፣ ትንሳ ተራመድ የሚለው ጡሩንባ ቀስቅሶኝ ስነሳ መላ ሰውነቴ ውሃ በውሃ ሆኖ ነበር።

ከነልብሴ አጥባ ካሣደረቺኝ ሆቴሌ የጋይላ ወንዝ ሳንወጣ በጉዟችን ገፋንበት። በዚች በደረቀች በጋይላ ወንዝ ውስጥ ስንጓዝ በመጠኑም ቢሆን ከነዚያ የሰማይ ላይ የሞት ቀርቀሮዎች እይታ አምልጠናል። የጋይላ ወንዝ በደረቀ ወገቧ ላይ እንድንጓዝ፣ በሆዷ ቋጥራ ከያዘቺው ውሃ እንድንጠጣ መፍቀድ ብቻ ሳይሆን ከጠላትም የሞት አሞራዎች አይንም ደበቀችን። ጋይላ ምስጋና ይገባታል።

በዚቺው በደረቀች የጋይላ ወንዝ ጉያ ውስጥ ተደብቀን ወደኋላ የቀሩትን የትግል ጓደቻችንን፣ በተለይም ክፉኛ የቆሰለውን የከንባታ ልጆችን መሪ ደጃዝማች መሸሻን እየጠበቅን ነው። የጀግናው የከንባታ ልጆች ጦር መሪ ደጃዝማች መሸሻ፣ የራስ ካሣ ጦር ከተንቤን የብረት አጥር ሰብሮ እንዲወጣ ሽፋን ሲሰጥ የነበረው፣ የራስ ካሣ ጦር የብረት አጥሩን ሰብሮ ከወጣ በኋላ ወደኋላ እያፈገፈገ ሲዋጋ፣ ጀግናው የከንባታ ልጆች መሪ ደጃዝማች መሸሻ በአንድ የእጅ ቦንብ ከመመታቱም በላይ በሶስት የመትረየስ ጥይቶች ሆዱን ተመትቶ በወደቀበት ቦታ እንደሞተ ሰው ተኝቶ ውሎ ሲመሽ በጨለማ እንደእባብ እየተሳበ ከዋለበትና ከቆሰለበት የጦርነት አውድማ ወጥቶ ወደጫካ ይገባል። ከዚያች ጫካ የትግል ጓዶቹ አንስተው የተረፈ ጦራቸው ወደሰፈረበት የጦር ሰፈር ወሰዱት።

ይህ ጀግና ሰው ሶስት የመትረየስ ጥይቶች በሆዱ ይዞ፣ አብዛኛው ሰውነቱ በተወረወረበት የቦንብ ፍንጣሪ ተበሳስቶ፣ ሌላ ሰው ወዲያው የሚሞትበትን፣ ጭጭ የሚልበትን መከራ ተሸክሞ፣ ኋላ ቀር በሆነ በቡቱቱ ቁስሉን ታስሮ፣ ሶስት ቀንና ሌሊት በፈረስ ተጉዞ፣ እነሆ ዛሬ ከዋናው የራሶች የጦር ሰፈር ደረሰ። ይኼ ቆራጥ ጀግና ከራስ ካሣ የጦር ሰፈር ሲደርስ ከፈረሱ ለመውረድ አቅም ስላልነበረው በወታደሮቹ እርዳታ ከፈረሱ ወርዶ ራስ ካሣ ካስነጠፉለት አልጋ ላይ በጀርባው ተኛ። የጀግኖቹ ጀግና ደጃዝማች መሸሻ በከባዱ ከመቁሰሉም በላይ ያለ እንዳች የሀኪም እርዳታና ያለ እንዳች እረፍት ያደረገው ጉዞ ከፍተኛ የደም መፍሰስ ስላስከተለበት፣ ራስ ካሣ ካስነጠፉለት አልጋ ላይ ሁለት ሰዓት ያልሞላች ጊዜ ካረፈና የትግል ጓዶቹንና አለቆቹን ከተሰናበተ በኋላ ከዚያች ስቃዩ ተገላገለ።ምስኪን ኢትዮጵያ፣ አንድ ደፋር ድንቅ ጀግና ዛሬ አጣች። የጀግኖቹ፣ የደፋሮቹ የከንባታ ልጆች መሪ የደጃዝማች መሸሻ ሞት ሁላችንንም አሳዘነን።

ይገርማል ካሁኑ የዋናው የጦር ሰፈራችን ጋይላ ለብዙ ጊዜ ያላየኋትን ወፍራሟን፣ ሳቂታዋን የራስ ካሣ ዋና ወጥ ቤት አገኘኋት። አዎ ይቺ የደስ ደስ ያላት ደግ ሴትዮ ለብዙ ቀናት የደረሰችበት ጠፍቶ ነበር። ገና ከተንቤን ሽሽት ስንጀምር ይቺው ባልቴት ከወጥ ቤቶቿ ጋር እቃዋን ስትቋጥር ወደ ኋላ ቀርታ ኖሮ አንዱን እቃ ስትጭን፣ አንዱን ስታወርድ፣ ስትንጎዳጎድ ድንገት ጣልያኖች ደርሰውባት ከነንብረቷና ከጠቅላላው የወጥ ቤቶቿ ሰዎች ጋር በጣልያኖች ምርኮ ስር ትወድቃለች።

በቁጥር ወደ መቶ ከሚሆኑት ወጥ ቤቶቿና /ልጆችም አሉበት/ ከተንቀሳቃሽ ማድቤቷ ጋር የተማረከቺው ይቺ ደግ ባልቴት ለምርመራ ከአንድ የጣልያን መኮንን ፊት ስትቀርብ ለነጻነት ያበቃትን አቤቱታዋን ደጋግማ አቀረበች። እኔም ወሬ አልጠግብ ብዬ እንደምን ከጣልያኖች እጅ አምልጣ ከዋናው ጦራችን ጋር መቀላቀል እንደቻለች ጠጋ ብዬ ለጠየኳት ጥያቄ ይቺ ሳቂታና ሞኛሞኝ መሳይ ባልቴት ያወጋችኝ ባጭሩ እንዲህ የሚል ነበር።

ከወጥ ቤቶቿ ጋር ከአንድ ከፍተኛ የጣልያን መርማሪ መኮንን ፊት ቀርባ ስትመረመር፣ መኮንኑ በተደጋጋሚ የሁለቱ ራሶች ጦር የት እንደተደበቀ እንድትናገር አጥብቆ ይጠይቃታል። ያስፈራራታል። ታማኟ ወጥ ቤት ግን ብትገሉ ግደሉኝ እንጂ ለማንም አልናገርም ብላ ድርቅ ከማለቷም በላይ፣ ለጣሊያኑ ከፍተኛ መርማሪ መኮንን አሁኑኑ ከነወጥ ቤቶቿና ከነሙሉ ጓዟ ካለቀቃት ሁለቱ ራሶች የሚበሉት ነገር እንደማይኖራቸውና እንደሚቆጧት በተደጋጋሚ ለዚያ መኮንን አቤቱታዋን ታቀርባለች።

ያ መርማሪ መኮንን የባልቴቷን አቤቱታ እሺ ብሎ እንደጠየቀችው ከነሙሉ ወጥቤቶቿና ማድቤቷ ጋር በነጻ ለቀቃት። አገዞላት ሳይሆን ሊከታተላት፣ እሷ ሳታውቅ ወደ ሁለቱ ራሶች የጦር ሰፈር እንድትመራው አስቦ ነበር በነጻ የለቀቃት። ብልጧ ወጥ ቤት ግን ከጣሊያኖቹ እጅ እንደወጣች ወጥቤቶቿን በብዙ ቡድን ትከፋፍልና በተለያየ አቅጣጫ ሄደው የራሶችን የጦር ሰፈር እንዲፈልጉ አዝዛ የወጥ ቤቷን ጦር በተንቤን ትበትነዋለች። እሷም የራሷን ቡድን እየመራች ወደጫካ ገብታ በአሳቻ መንገድ እየሄደች፣ ተራራ እየወጣች፣ ቁልቁለት እየወረደች፣ ዋናውን መንገድ እየተወች፣ ዱር ለዱር እየሄደች፣ ከሚከታተሏት የጠላት ሰላዮች አይን ትሰወርና አረሳስታ እርግጠኛ ስትሆን ወደ ጌታዋ ተመለሰች። ድንቅና ብልህ ባልቴት!

የከንባታውን ደጃዝማች መሸሻን የቀበርንባትን የጦር ሰፈራችንን እኩለ ሌሊት ላይ ለቅቀን ወደፊት እንድንሄድ ራስ ካሣ ትዕዛዝ ሰጡ። ለኛ ለአምስቱ ፈረንጆች የቀረን አንድ የደከመ፣ የተራበና ለራሱም የግዱን የሚሄድ ፈረስ ብቻ ስለነበር፣ ቀጣዩን ጉዞ በእግር መግፋት ግዴታ ነውና ለረጅም ሰዓታት በእግር ተጉዘን ከመኪከላችን በጣም የደከመውና መሄድ ያልሆነለትን ተጋግዘን በዚያ በሞተ ፈረሳችን ላይ ጥቂት እግሮቹን እንዲያሳርፍ እያደረግን እንሄዳለን። ያ ፈረስ በቁሙ እንዳይሞት እንደገና ተፈናጣጩን አውርደን የደከመውን ፈረሳችንን እየጎተትን ወደፊት እንሄዳለን። ማለቂያ የሌለው ጉዞ።

እንዲህ እየተጓዝን ቀዳሚውና ጠንካራው ጦር ከሰፈረበት የጦር ሰፈር ደርሰን አይን ለመጨፈን የማትበቃ ጊዜ እንኳን ሳናርፍ ያ መከረኛ ነጋሪት ይጎስም ጀመር። ካረፍንባት መሬት በመከራ ተነስተን ጉዞ ስንጀምር ያንን የደከመ ፈረሳችንን ለእድልና

እጣፈንታው በዚያው ጥለነው ሄድን:: በተቀደሰች ሀገር ፈረስ አይበሳ ነገር፣ እናም እሱን መጎተቱ ፋይዳ አልነበረውም::

በመሆኑም ለሚቀጥሉት ረጅም ሰዓታት እግሮቻችን የአሸዋ አቧራ እያቦኑ ስንጓዝ ውለን እንደገና ያቺኑ አጭር እረፍትና የደሮ እንቅልፍ ወስደን፣ እንደገና ነጋሪቱ ይጎሰም፣ ጡሩንባው ይነፋና፣ የደከሙ እግሮቻችንን እየጎተትን ተራራ ስንወጣ፣ ቁልቁለት ስንወርድ፣ የደረቁ ወንዞችና ጅረቶች ስንሻገር፣ ማለቂያ የሌለው በሚመስል ሜዳ ስንሄድ እናመሽና እንደገና ሌላ አጭር እረፍት እናደርጋለን:: ከዚያም እፍኝ ሽንብራ ባፋችን እንልና ጉንጭ ውሃ ተጎንጭተን፣ ያ ነጋሪት ሲጎሰም እንደገና ማለቂያ በሌለው መንገድ ቀይ አሸዋ ስናቦን፣ ከመድረቁ የተነሳ የፈራረሰ አስፓልት የሚመስለውን፣ ጢጠር በጠጠር የሆነውን፣ የውሃ ዘር የሌለውን ወንዝ እየተሻገርን ብቻ መንገድ ይሁን አይሁን ወደፊት እያልን እንገሰግሳለን:: ያለፍናቸው ቅቤ የተቀቡ የሚመስሉ ገደሎች፣ አስደናቂ ተራሮች፣ የሚያስገርምና የሚያስደንቅ ውበት ያላቸው ሸለቆዎች፣ ፒራሚድን የሚያስንቁ ቋጥኞች፣ ብቻ በምድር ሳይሆን በጨረቃ ላይ የምንሄድ እስኪመስለን ድረስ ተጓዝን::

መጋቢት 9 ቀን ማምሻው ላይ ከሳምሬ ወንዝ ዳርቻ ደረስን:: ሳምሬ ውሃ በውሃ ነች። እንዲህ የሚያጓጓ ውሃዋን የሳምሬ ወንዝ ከምላጭ በሰሉ ሁለት ገደሎች መሀል ደብቃ ይዘዋለች:: ሳምሬ ተስፋችን ነች:: ቢያንስ እነዚያን ገደሎች ወርደን፣ ጥማችንን ቆርጠን፣ ጥቂት እናርፍ ይሆናል:: የሳምሬ ገደሎች፣ ድንጋዮች እግሮቻችንን እየሸረከቱት ወርደን፣ የውሃ ጥማችንን ቆርጠን፣ ኮዳችንን ሞልተን፣ ሁለት ሰዓት እንኳ ያልሞላ ጊዜ ሳናርፍ መከረኛው ነጋሪት ተጎሰመ:: ወደፊት ማለቱ የማይቀር ጉዳይ፣ ግዴታ ነውና በስለት ድንጋይ የተሸረካከቱ እግሮች በቡቱቱ ታስረው፣ ማለቂያ ከሌለው አግረኞች መሀል ገብተው ወደፊት አሉ::

መጋቢት 15 ማምሻው ላይ ከ14 ቀን በላይ ቀን ከሌት ጉዞ በኋላ፣ ደጃዝማች መሸሻን ቀብረን ሁለት ቀን በጋይላ ወንዝ ዳርቻ ከማረፋችን በቀር ያለምንም የረባ እረፍት (በየቀኑ ከ2 እና 3 ሰዓት በላይ አላረፍንም) ከፊታችን የሚነድ ከተማ የሚመስል የጣልያኖች የጦር ሰፈር ተዘርግቶ እይታችን ውስጥ ገባ:: ይቺ ዛሬ ጣልያኖች አንድደው ድንኳኖቻቸውን የተከሉባት ቦታ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ሰቆጣ በመባል የምትታወቅ ትንሽ ከተማ ነበረች::

ከሰማይ ላይ የሚወረወሩ የጣልያን ቦምቦች ያቺን ገና በማበብ ላይ ያለች ትንሿንና ውቧን ሰቆጣ ወደ አመድነት ለወጧት:: አንድም የጦር ሰፈር ምልክት እንኳ የሌላትን ትንሿን ሰቆጣን፣ የቦምብ ናዳቸውን አውርደውባት አመድ መድፊያ እንኳ ገና በማበብ ላይ ያለች፣ የነበረች ሰቆጣ መሆኗን የሚጠቁም ምልክት አሳጥተዋታል።

የሰቆጣ ጎጆ ያፈራቻቸው ወንዶች አንዳቸውም ሳይቀሩ ወደ ጦር ሜዳ ሲሄዱ በሰቆጣ የቀሩት ሴቶች፣ ልጆችና አሮጊቶች ብቻ ነበሩ:: በሮማ ከፓላዞ ቬኔዛ መስኮቱ በረንዳ ላይ ቆሞ "በኢትዮጵያ ስልጣኔ አመጣለሁ፣ አስገባለሁ" እያለ የሚደነፋው ሞሶሉኒ፣ የሱ የስልጣኔ መንገድ ምን እንደሚመስል፣ የሰቆጣ አመድ ዝምተኛ ምስክር ነች::





33

ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር በኮረም

የዋግ መዲና ሰቆጣ የሞተች ያልተቀበረች ከተማ ነች። ነዋሪዎቿ ከዚያ እሳት አምልጠው መሸሽ ችለው ከሆነ ከሰቆጣ በላይ ባለ ተራራ ተደብቀው በጠራ ሰማይ ላይ እያፈጠጡ ናቸው፤ ምናልባት በህይወት አምልጠው ከሆነ። በጊዜ ከጎጇቸው ወጥተው ማምለጥ ያልቻሉ የሰቆጣ አባውንቶች፣ ሴቶችና ህጻናትማ ያው ከሰቆጣ ጋር አመድ ሆነዋል።

ድምጥማጧ በጠፋው ሰቆጣ ብዙም ሳንቆይ ወደፊት ሄድን። ሌሊቱን ሙሉ ሲዘንብ ነው ያደረው። ንጋት ላይ ቀዝቃዛው ንፋስ ቀሰቀሰን። ያደርንባት ቤት ጣሪያ ሲያፈስ ነው ያደረው። አሁን ያለነው ተራራማ በሆነ ቀበሌ ሲሆን እዚህ ቀን ቀን ሐሩሩ ሲለበልብ፣ ሌሊት ሌሊት ደግሞ ቁሩ ብርዱ መድረሻ የሚያሳጣ ቦታ ነውና አጼራችን አጥር አያብለው። በብርድ ስንንቀጠቀጥ፣ ጥርሳችንን ስናፏጭ ነው ያደርነው። እንደዚያ በሚያንቀጠቅጥ ብርድ እንደፈሳ ተኝተን ዋናው የራስ ካሣ ጦር ንጋሪት መትቶ ሲንቀሳቀስ እንኳን አልሰማንም ነበር። ቢሆንም የኋላው ደጀን ጦር ሰገዞ ሲሰናዳ እኛም ተነስተን ንጉሡን ፍለጋ ወደፊት ሄድን።

አሁን የምንሄደው እስከዛሬ ብዙም ባልተጠኑ ሁለት ተራሮች መሀል ነው። ከአንዲት የጸለሬ ወንዝ ገባሪ ጅረት ዳርቻ ስንቃረብ መንጋት ጀመረ። ብዙም ሳይቆይ ከብዙ ቀናት እፎይታና ሰላም በኋላ ያልተጋበዙት፣ ያልተጠሩት እንግዳ ባለሶስት ሞተር የጣልያን ሰላይ አውሮፕላን ባናታችን ላይ መዞር ጀመረች። ከሰዓታት ጉዞ በኋላ በየቦታው ጋደም ብለው የሚያርፉ ወታደሮችን ማየት ጀመርን። ይህ ማለት ደግሞ በትክክልና በእርግጠኛነት ወደ ዋናው ጦራችን የጦር ሰፈር እየተቃረብን ነው ማለት ነው።

ብዙም ሳንቆይ በውሃ ልክ የተሰሩ ከሚመስሉ ሁለት ገደሎች መሀል ባለች ዋሻ ሁለቱ ራሶችና እሉ የሚባሉ የሰሜኑ ጦር የጦር አበጋዞች ሰፍረው አገኘናቸው። ከነዚህ ከፍተኛ የጦር ጄኔራሎች መሀል ጀግናው ደጃዝማች መሸሻ የከንባታው ሲቀር፤ የዋጉ ገገርና ወራሽ ራስ ከበደን ጨምሮ አሁን ራሶች ሶስት ሆነዋል። እንዳልኩት አሁን ራሶች ሶስት ናቸው። ሙግቱ ጦፏል። የዋግ ተወላጆች የራስ ካሣ ጦር በዋግ ግዛት ቆይቶ ከሰቆጣ የሚወርደውን የጠላት ጦር እንዲከላከል፣ ግዛታቸውን፣ ልጆቻቸውን፣ ንብረታቸውን እንዲታደግላቸው አጥብቀው ይማጸናሉ።

ከወታደራዊ ስልት አንጻር የዋጎችን ጥያቄና ምኞት የራስ ካሣ ጦር ሊፈጽመው አይቻለውም። ራስ ካሣ ጠቅላላ ጦራቸውን ይዘው ወደ ኮረም በመውረድ የንጉሡን ጦር አጠናክረው፣ ኮረም ወይም ማይጨው ላይ ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ከፋሺስቱ ጦር ጋር ገጥሞና የአንባላጌን ተራራ ወርዶ፣ ቢያንስ ወደአዲስ አበባ እንዳይዘልቅ መሞከር አለበት። የራስ ሙሉጌታ ጦር በተሸነፈ ጊዜና ደጃዝማች ወልደ ማሪያምና ደጃዝማች አውራረስ የተረፈ ጦራቸውን ይዘው በዋግ በኩል ሲያልፉ ተመሳሳይ ችግር ገጥሟቸው ነበር።

በዚሁ አንድ ቀን ሙሉ በፈጀ ሙግት በመጨረሻ ላይ ዋጎች እንዳሰቡትና እንደተመኙት ባይሆንም በሙግቱ አሸንፈው የአንድ ደጃዝማች ጦር በዋግ እንዲቆይ ሆኖ ሙግቱ አለቀ። የዋግ ድንበር፣ ህዝብ፣ ንብረት ከክፉው የጠላት ጦር ጠባቂ ሆኖ ከሙሉ ሰራዊቱ ጋር በዋግ እንዲቆይ ደጃዝማች ኃይሌ ከበደ፤ የዋግ ሹም፣ የራስ ከበደ ልጅ እና ወራሽ ተመረጠ፤ ተሾመ፤ ወይም ደግሞ ተፈረደበት። አሁን ማ ይሙት የአንድ ደጃዝማችን ጦር ብቻውን ከጠላት ጦር ጋር ግጠም ማለት የሞት ፍርድ እንጂ ሹመት ነው? ደጃዝማች ኃይሌ ከበደን ከጀግኖቹ፣ ከአንበሶቹ ሰራዊቱ ጋር ብቻውን በዋግ ጥለነው በዚያው ምሽት ንጉሡን ፍለጋ ወደ ኮረም ወደፊት ሄድን።

ከሰቆጣ ተነስተን ኮረም እስክንደርስ አምስት ቀን ፈጀብን። በሰቆጣና በኮረም መሀከል ያለውን አስቸጋሪ መንገድ እንሄድ የነበረው ጨለማን ተገን አድርገን ብቻ ነበር። በተለይ እንዚያ የተረገሙ የጣልያን የቅርቻ የሰማይ ላይ አሞራዎች ሰማዩን

ወርረው መርፌ እንደሚፈልጉ ሁሉ ስንገር መሬት እንድንሄድ፣ እንድንራመድ አይፈቅዱልንም ነበር:: እና ቀኑን በተገኘው ቦታ ሁሉ ከለላ ይዘን እንውላለን::

ሶስቱ ራሶች በተገኘችው ዋሻ መሳይ የቀበሮ ጉድጓድ ውስጥ ገብተው ይደበቃሉ፣ አሊያም በዘቦቻቸው ታጅበው የትልልቅ ዋርካዎችን ጥላ ተገን አድርገው ቀኑን ይውላሉ:: እንዲህ አምስት ሌሊት ሙሉ በዚያ በሚያንቀጠቅጥ ብርድ ሰውነታችንን ለማሞቅ ጭምር ስንሮጥ፣ ቀኑን በተወሸቅንባት ጉድጓድ በጠራራ ፀሐይ ስንወገር ሰንብተን መድረስ አይቀርምና ኮረም ደረስን:: ምናልባት ከዛሬ 2,000 ዓመት በፊት የኤክስፎኖት ወታደሮች በዚያ ተስፋ በሚያስቆርጥ ትንሿን ኤሺያ ዙረታቸው መጨረሻ ላይ የጥቁር ባህርን ዳርቻ ባገኙ ጊዜ የተሰማቸውን የደስታ ስሜት አይነት ነገር እየተሰማን፣ መጋቢት 19 ቀን ማለዳ ከሶስት ሳምንት ሽሽት በኋላ ትልቁን ግባችንን መታን:: ኮረም:: ትልቁ አላማችን ግቡን ይምታ እንጂ ጣጣችን፣ መከራችን ግን ገና አላለቀም ነበር::

ከሰዓት በኋላ በምስራቅ ከአዘቦዎችና ከራያዎች ጋር ከሚያዋስኑት የድንበር ተራሮች ላይ ወጣን:: እታች ኮረም የንጉሠ ነገሥቱ መለዮ ለባሽ ወታደሮች ሲርመሰመሱ በግልጽ ይታያሉ:: እንዲህ አይነት ወታደራዊ ልብስ የለበሱ ወታደሮች ያየሁት አዲስ አበባ ብቻ ነበር:: በተንቤን ከራስ ካሣ ወታደሮች መካከል ወታደራዊ ልብስ ለብሶ የሚታይ ከሺዎች አንድ ቢገኝ ነው:: ሁሉም የሰሜኑ ጦር አባል ነጭ ሸማ ለባሽ የገበሬ ወታደር ብቻ ነበር:: ወደ ኮረም ስወርድ በመንገዴ በርካታ ወታደራዊ ልብስ የለበሱና የወታደር ጫማ የተጫሙ የንጉሠ ነገሥቱን ወታደራዊ መኰንኖች አገኘሁ:: አብዛኛዎቹን በንጉሠ ነገሥቱ ቤተ መንግሥት አዲስ አበባ አግኝቻቸው ነበር:: ይኼ ማለት ደግሞ በትክክል ንጉሠ ነገሥቱ ወደ መሸጉበት ዋሻ ተቃርበናል ማለት ነው::

ብዙም ሳንቆይ በንጉሠ ነገሥቱ ዋሻ ውስጥ በንጉሠ ነገሥቱ ፊት ራሳችንን አገኘነው:: ጃንሆይ ልክ ኮረም እንደገባን ያለምንም ፕሮቶኮል ወዲያውኑ ተቀበሉን:: ምንም እንኳን ልብሳችን በራሳችን ላይ አልቆ በጭቃ የተለወሰ ሁለመናችን ከለማኝ የከፋ ገጽታ ቢኖረውም፣ ጃንሆይ ያለአንዳች ጣጣ በዋሻ ቤተ መንግስታቸው ተቀብለው አስተናገዱን:: አዲስ አበባ በጃንሆይ ለራስ ካሣ የጦር አማካሪ ሆኜ ተሹሜ፣ ከፍተኛውን የኢትዮጵያ የመኰንን ማዕረግ ተሰጥቶኝ ወደ ደብረ ታቦር ከሄድኩ ወራቶች አልፈዋል:: በነዚህ ወራቶች ውስጥ ኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ ለውጥ አለ::

በአዲስ አበባ ቤተ መንግሥት ያየሁት ምርጥና ድንቅ በወርቅ የተሸቆጠቆጠ ጌጣጌጥና ማራኪ ነገር ሁሉ እዚህ የለም፣ ጠፍቷል:: የንጉሠ ነገሥቱ ዋሻ ተራ ዋሻ ነች:: በዚች ዋሻ የኢትዮጵያው ንጉሠ ነገሥት እንደሚኖር የሚጠቁም ምንም ነገር የለም:: የንጉሠ ነገሥቱ ዋሻ በመጠኑም ቢሆን ሰፋና ጠራ ያለች ብትሆንም፣ በውስጧ ግን የኢትዮጵያው ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ እንደሚኖሩ የሚጠቁም

አንዳች ነገር የለም:: በዚያች ዋሻ ያለ ነገር ቢኖር አንድ መናኛ ወታደራዊ ታጣፊ ጠረጴዛ፣ አራት ታጣፊ የሸራ ወንበሮችና ከዋሻዋ የቀኝ ክንፍ ላይ በተራ የወታደር ብርድ ልብስ የተሸፈነ አንድ ተራ የወታደር አልጋ ብቻ ነበር:: ከዚህ ሌላ ወለሏ በተደጋጋሚ ተረጋግጣ ወደ መመላለጥ በተቃረበች የአበባ ምንጣፍ ከመሸፈኑ በቀር ሌላ ምንም ነገር የለም::

የዋሻዋን በር ታማኞቹ የንጉሠ ነገሥቱ የክብር ዘቦች በርካታ የአውሮፕላን መቃወሚያ መትረየሶች ጠምደው፣ ከጠላት አውሮፕላኖች አዬውን ለመከላከል በተጠንቀቅ ቆመዋል:: ጃንሆይ በዚች የዋሻ ቤተ መንግስታቸው እንደጥንት ጓደኛ በደስታ ከልባቸው ተቀበሉን:: ጃንሆይ ዛሬ የማርሻል ማዕረግ የተከተበበት ወታደራዊ የደንብ ልብስ ለብሰው፣ በተራ የመኰንን ቀበቶ ወገባቸውን ሸብ አድርገውታል:: የብርቱካን ቀለም ያለው ረጅም ወታደራዊ ጫማቸውን ተጫምተው፣ ፈገግታ ሳይለያቸው በዋሻዋ ውስጥ ባሉ አራት ወንበሮች ዙሪያ እንድንቀመጥ ጋብዘውን፣ እሳቸው በዚያች ደረቅ የወታደር አልጋቸው ላይ ተቀመጡ::

ከሁሉም በላይ ያስገረመኝ ነገር ቢኖር የጃንሆይ ፍጹም የተረጋጋ መንፈስ ነበር:: በየቀኑ የሚደርሳቸው ዜና እንኳን እሳቸውን ቀርቶ ከሳቸው በአካል ብዙ የሚበረታን ሰው ጭንቅላት አዙሮ የሚጥል ሆኖ ሳለ፣ ፍጹም በተረጋጋና ቁርጠኛ በሆነ መንፈስ ፈገግታ ሳይለያቸው ሲቀበሉን የመንፈስ ጥንካሬያቸውን አደነኩኝ::

ያኔ ከአዲስ አበባ ተሰናብቻቸው ወደ ሰሜን ጦር ግንባር ስሄድ ፊታቸው ላይ ያልወሰኑ፣ ርግጠኛ ያልሆኑ ሰው አይነት ነገር ይነበብባቸው ነበር:: ዛሬ ግን ከእያንዳንዷ ካፋቸው በምትፈልቅ ቃላቸውና እንቅስቃሴያቸው ፍጹም ርግጠኛና በራሳቸው የሚተማመኑ፣ ብርቱ፣ ጠንካራና ቆራጥ ሰው መሆናቸው ይነበባል::

አዎ ጃንሆይ በስተመጨረሻ የአውሮፓውያን ሻጥር ገባቸው:: አሁን የመንግስታቱ ህብረት የሰላም ድርድር ምንም እንደማይፈይድ ተረድተዋል:: ያ በመንግስታቱ ህብረት ስር ይፈጸማል ብለው ያመኑት የሰላም ድርድር፣ ጀግናውን የኢትዮጵያ ሰራዊት በእጁ የገባን ድል እንዲያጣ አድርጎታል::

ቢዘገይም ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የጠላትን ጦር ለመግጠም እነሆ ዛሬ ድሎት የበዛበትን ቤተ መንግስታቸውን ጥለው እንደማንም ተራ የገበሬ ወታደር ሁሉ በጦር ግንባር ሰራዊታቸውን ሊመሩ ተሰልፈዋል::

አዎ ጃንሆይ ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ለጥንታዊው የኢትዮጵያ ታሪክ፣ ባህልና ወግ ታማኝ ሆነው፣ እንዳለፉት የኢትዮጵያ ነገስታት ሁሉ ጦራቸውን ይዘው፣ እነሆ መትረየሳቸውን ጠምደው፣ ሽጉጣቸውን ታጥቀው፣ ጠመንጃቸውን አንግተው፣ በጦር ግንባር ከጠላት ጋር ገጥመው፣ ለእናት ሀገራቸው ለመሞት ተሰልፈዋል:: "ሀገር ወይም ሞት!"

በዳንሆይ ገጽታ ላይ የሚታይ ነገር ቢኖር እነዚያ የሚያበሩ አይኖቻቸው ፈዘዝ ማለታቸው ብቻ ነበር። እግዜር ይወቅ በዚች ዋሻ ለደቂቃዎች እንኳን አርፈው ተኝተው ከሆነ? አራታችን እንዲህ በዳንሆይ ዋሻ በሸራዎቹ ወንበሮች ላይ ተቀምጠን፣ ኮሎኔል ኮኖቫሎቭ በተጠንቀቅ እንደቆሙ፣ እሳቸው በዚያች ደረቅ አልጋቸው ላይ እንደተቀመጡ፣ ለሰዓታት ባለፉት ስድስት ወራት በሰሜኑ የጦር ግንባር ስላሳለፍነው ነገር እየንዳንዱን ጥቃቅን ነገር ሳይቀር ሳይሰላቹ በታላቅ ጉጉት ጠየቁን።

ከእንዲህ አይነቱ ውይይት በኋላ ዳንሆይ ኮስተር ብለው "በቅርብ ቀን እንሰነዝራለን" አሉ። ኮሎኔል ኮኖቫሎቭ በጣልያን ጦር ላይ በማይጨው ጥቃት እንሰነዝራለን" አሉ። ኮሎኔል ኮኖቫሎቭ በቀመበት በተጠንቀቅ ቆሞ፣ "ዳንሆይ ሆይ፣ ጣልያኖች እኛ ካለን ጦር እጥፍ ድርብ በላይ ጦር ያላቸውና በታጠቁት መሳሪያ ፍጹም የማንመጣጠናቸው ስለሆነ፣ የማይጨው የማጥቃት ጦርነት ራስን የማጥፋት ዘመቻ ነው" ሲል ለዳንሆይ ይቺን ሀቅ ማስረዳቱንና መጠቀሙን እንደግዴታው ወስዶ አስረዳ። ቀጥሎም "የሚሻለው ሠራዊታችንን ውጊያ ወደታች ወደደቡብ ገቶ ብሎ ማድረግ ነው። እኛ ወደ ደቡብ ወደ ሸዋ ሠሳችን ወሬቱን አብቶች ተደራጅተን ስንጠብቅ፣ ጣልያኖች ተዝረክርከው ስለሚመጡ ራያዎችም ወርደን፣ ተደራጅተን ስንጠብቅ፣ ጣልያኖች ተዝረክርከው ስለሚመጡ ራያዎችም ደፍረው ወደሸዋ ስለማይዘልቁ በቀላሉ ልናጠቃቸው እንችላለን።" ከወታደራዊ ስልት አንጻር ሌላም ሌላም ብዙ ብዙ መደረግ ያለበትን ነገር ሁሉ እንደቆመ ለዳንሆይ አስረዳ። በታላቅ ትግስትና በንቃት ሲያዳምጡ የነበሩት ዳንሆይ "እናውቃለን፣ ሀሳባችን ባይሳካ ሁሉም ነገር አለቀ ማለት ነው" ሲሉ ለኮሎኔል ኮኖቫሎቭ መለሱለት። ዳንሆይ አሁን እንዲህ ሲናገሩ በዓይናቸው ውስጥ ጥልቅ ሀዘን ይታይ ነበር። ወዲያው የንግግር መስመራቸውን ለውጠው፣ "ልጄን አይታችሁት ታውቃላችሁ?" ሲሉ ጠየቁ።

አሁንም ቆሞ የነበረው ኮሎኔል ኮኖቫሎቭ ከአፋቸው ነጥቆ፣ "ዳንሆይ ሆይ፣ ይቅርታ ያድርጉልኝና ስለ ልጁ ወዳጄ ካፒቴን ጋርለሳክ የበለጠ ስለሚያውቅና ከሁሉም በላይ የልጁ የጥብቅ ወዳጅ ስለሆነ የበለጠ ሊያብራራልዎት ይችላል" አለ። እንዲህ ኮሎኔል ኮኖቫሎቭ ስለኔና ስለ አቡቹ የጥብቅ ወዳጅነት በልበ ሙሉነትና በኩራት ሲናገር፣ እኔ በሆዴ ወይኔ እኔም እንደአቢቹ ሁሉ አለቀልኝ አያልኩ፣ ከየት ጀምሬ ለዳንሆይ ማስረዳትና ማብራራት እንዳለብኝ ሳሰላስል ዳንሆይ ገላገሉኝ።

"ግዴለም፣ እንደናንተም ባይሆን ይቺ አንድ ፍሬ ደጃዝማች ከኛም በላይ ትልቅ ጀብዱ እየሰራች እንደሆነ እንሰማለን። ይልቅ እርግጠኛ ነኝ፣ ለረጅም ጊዜ ፍራፍሬ በልታችሁ አታውቁምና እንካችሁ" ብለው ለራሳቸው ከተረበው ፍራፍሬ እንድንበላ ጋበዙን። እንዲህ ከዳንሆይ ፊት በሸራ ወንበር ላይ ተቀምጬው ያነሳኒትን ብርቱካን ለመላጥ እየታገልኩ በሀሳብ ወደ አቢቹ ነጎድኩ።

በኩረም የጦር ሰፈር መሸትሸት ሲል የገባሬው ወታደር ማለትም አባቱን፣ ወንድሙን፣ ጓደኛውን፣ በተንቤኑ የጦር ግንባር የመቅበር እድል እንኳን ያልገጠመው

የከፋው፣ ሆድ የባሰው ወታደር፣ እሳት አንድዶ እየሞቀና የቆላትን ሽንብራውን እየቆረጠመ፣ በማሲንቆ እየተደገፈች የምትንጎራጎረውን የአንድ የሰላሌ ልጅ ሙዚቃ ማዳመጡን ተያይዞታል። እንጎቱ የምትበላዋ የማሲንቆ እንጉርጉሮ ስለ ልጁ ስለ አቢቹ ነበረች።

አቢቹ ደራ ደራ
አቢቹ ደራ ደራ

ዛሬ አዝማሪው ሳይቀር ስለራሶች ጀግንነት፣ ስለ ንጉሠ ነገሥቱ ታላቅነት ማንጎራጎሩን ርግፍ አድርጎ ትቶታል። ብቻ የዳንሆይን ብርቱካን እየላጥኩ ዳንሆይ ስለልጁ፣ ስለአቢቹ በመጨረሻ ላይ የተናገሯትን ቃል ማሰላሰል ውስጥ ገባሁ። "ይቺ አንድ ፍሬ ደጃዝማች! ከኛ በላይ ጀብዱ እየሰራች መሆኑን እንሰማለን!" ሲሉ ምን ማለታቸው ነው?

እስከማውቀው ድረስ አቢቹ ምንም እንኳን በዚህ ጦርነት በጦር ሜዳ የወደቁት ሁለት ወንድሞቹ ብቸኛ ወራሽና በማዕረግም ፊታውራሪ ቢሆንም፣ ምንጊዜም ህጋዊውን የማዕረግ ስሙን ተጠቅሞ አያውቅም። አቢቹ በደጃዝማች አበራ የሚመራው የሰላሌው ጦር አባልና ለመሪው ለደጃዝማች አበራ ታማኝ ቢሆንም፣ የራሱን ጦር እየመራ ከሰላሌው ደጃዝማች አበራ የጦር ሰፈር ርቆ ከጠላት ጦር በሚዘርፈው ንብረት ጦሩን የሚያስተዳድር፣ በብዙዎቹ ዘንድ በሁለቱ ራሶች ሳይቀር እንደ ተራ ሽፍታ የሚቆጠር፣ ለከዳተኛውና ለባንዳው ለደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ጦር የእግር እሳት የሆነ፣ ምንም እንኳን በርከት ያሉ በሁቡዩም የሚመሩ የኤርትራ ልጆች የተቀላቀሉበትና የትግራይና የዳሞት ልጆችንም ያቀፈ ጦር ቢሆንም፣ አብዛኛው ጦሩ የሰላሌ ልጆች የሞሉበት መሆኑንና እስካሁን ጦሩ ምንም አይነት የማዕረግ ስም የማይጠቀም መሆኑን አሳምሬ አውቃለሁ።

ግን ዳንሆይ "አንድ ፍሬ ደጃዝማች!" ሲሉ ማዕረግ መስጠታቸው ይሆን? አቢቹ ይኼን ያህል በዳንሆይ ልብ ውስጥ ገብቶ ይሆን? ይኼን እያሰላሰልኩ ሳላስበው ሶስተኛዋን ብርቱካን ልጬ ስበላ ዳንሆይ ሳይታዘቡኝ አልቀሩም። ብቻ በሀሳብ ስለ አቢቹ እያሰብኩ እያሰላሰልኩ ያኔ ይልክልን የነበረው ሲጃራ፣ ቪኖ፣ የጣሳ ምግብ፣ ወዘተ. ብቻ የአቢቹ የዘረፋ ስጦታዎች አይኔ ላይ መጡብኝና ላየው ተመኘሁ። ግን ስለ አቢቹ ጦር እንቅስቃሴ ጋይላ እያለን የከንባታ ልጆች እንዴት ከጠላት ጦር ጓንቻ ውስጥ ፈልቅቆ እንዳወጣቸው ካወሩኝ ወሬ ውጪ ሌላ ወሬ ከሰማሁ ሰንበቻለሁ።

ከከንባታው መሪ ከደጃዝማች መሸሻ ቀብር በኋላ አንድ የከንባታ ልጅ ስለ አቢቹ ያጫወተኝ ባጭሩ የሚከተለውን ይመስላል። "የከንባታው ጦር በጣልያን ሰራዊት ተከቦ፣ መውጫው ጠፍቶት፣ እጥፍጥፍ ጥፋ አይነት ውጊያ ላይ እያለ ከየት መጡ ሳይባል እነዚያ የአቢቹ ፈጥኖ ደራሽ ደቦል አንበሶች ከጣልያኑ ጦር ብብት ውስጥ ገብተው ሲኮረኩሩት፣ደመሰስኩ ብሎ የሚኩራራው የጣልያኑ ጦር ሲያስብ

የከንባታውን ጦር ከዚያ ካስቀሰት ውጊያ ውስጥ አደጋ ደርሶበትና በተራው ሲያፈገፍግ እነሱ መንጥቀው አወጡት።"

አሁንስ እኔም እንደ ባለማሲንቆዎቹ ስሟን እየጠራሁ ሳንጎራጉር መሰለ። ጃንሆይ ፍራፍሬውን አቅርበውልን ቢያንስ ለሁለት ሰዓት ያህል በተንቤን ምን እንሰራ እንደነበረ ያስመሰልችት ጠየቁን። እሳቸው ሲጠይቁ እኛ ስንመልስ ብዙ ብዙ አወጋን። ጃንሆይ ሌላው ቀርቶ በጦር ሜዳ የኢትዮጵያው ሰራዊት ምርጥ ምግብ ስለሆነው ስለ "ጥሬ ስጋ" እንኳን ሳይቀር ጠየቁን። "እንዴት ነው ጥሬ ስጋ መብላቱን ተላመዳችሁት?" ሲሉ ሳነሱት ጥያቄ ኮሎኔል ሲመልስ "እንዴታ ጃንሆይ፣ሙዳ ስጋ ተበልቶ ሲሆን ጠጅ፣ ጠጅ ከጠፋም ካቲካላ ምናምን" እያለ አሳቃቸው።

ከዚች የጥሬ ስጋና ካቲካላ ወሬና ሳቅ በኋላ መቼ እንኳን እንዳበዙ ሳናስተውል፣ አሽከሮች መሶብ ሙሉ ጥሬ ስጋ ከሁለት ጠርሙስ ያገር ተወላጅ አረቄ "ካቲካላ" ጋር ቀረበልንና በጃንሆይ ትንሿ ዋሻ እንደአሞራ ከበን ከሰከስነው። ትናንት እፍኝ ሽንብራ በቆረጠመች ጥርስ ያላንዳች እፍረትና ይሉኝታ እንዳንበሳ እየተሻማን ጥሬ ሥጋውን አስነካነው።

ማዕዱ ሲነሳ አሽከሮች በርካታ ወታደራዊ ልብሶችንና ጫማዎችን ይዘው መጥተው ከፊታችን ደረደሩልን። ጃንሆይም እንድንመርጥ ገፋፉን፣ አበረታቱን። ይቺ የጃንሆይ የመጨረሻ ስጦታ ከሰማይ የወረደች ያህል ደስ አሰኘችን። ያኔ ከአዲስ አበባ ስነሳ የኢትዮጵያው ከፍተኛ ማዕረግ ካለው በወርቅ ከተሸቀጠቆጠው ወታደራዊው ልብሴ በሰውነቴ ላይ የቀረ ነገር ቢኖር ብጣሽ ቡቱቱ ብቻ ነበር።

ጃንሆይ ከቀትር በኋላ እስከ ምሽቱ ድረስ በጦር ሰፈራችን ዙሪያ የሚኖሩትን የአገሬውን ተወላጅ ትናንሽ ሹማምንቶች እየተቀበሉ ሲያነጋግሩ፣ ሲደራደሩ፣ ሿሞ እየሸለሙ ሲሾሙ፣ ማዕረግና ሹመት ለሚሻ ማዕረግና ሹመት፣ ገንዘብ ለሚፈልግ ገንዘብ፣ ጠመንጃ ለሚፈልግ ጠመንጃ እየሰጡ ሲሾሙና ሲሸልሙ፣ እነዚህ አዲስ ሹሞች ደግሞ ለንጉሠ ነገሥታቸው ታማኝነታቸውን እየማሉና እየተገዘቱ ሲያረጋግጡ ቀኑ አልቆ መምሸት ጀመረ። እነዚህ እንዲህ በንጉሠ ነገሥቱ ፊት ቀርበው የተሾሙና የተሸለሙ የአካባቢው ሹሞች መሀላቸውን አፍርሰው፣ ንጉሣቸውንና አገራቸውን ከድተው፣ ለጥቂት ብሮችና አዲስ ጠመንጃ ለጣልያን ባርነት፣ ባንዳነት አደሩ።

ማይጨው

በዚቺው ዕለት ምሽት ጃንሆይ በክብር ዘቦቻቸው ታጅበው፣ ወደሰሜን ወጥተው፣ ከአሸንጌ ሐይቅ በስተሰሜን በኩል ያለችውን የተራራ ቀበሌ "አያን" ያዙ። አያ ከመካነ በስተደቡብ በኩል ያለች ቀበሌ ነች።

ከወታደራዊ ስልት አንጻር አያ ደህና ቦታ ብትሆንም ከአያ አጅጉን በጣም ወሳኝ የሆነችውን የተራራ ወገብ ጣልያኖች ገና ዱሮ በጃቸው አስገብተው፣ ምሽጋቸውን ቆፍረው በተጠንቀቅ ይጠብቃሉ። የኢትዮጵያው ንጉሠ ነገሥት ለወሳኙ ጦርነት ያዘጋጀው ለዚህ ጦርነት ብቁ የመዋጋት ኃይል ያለው የወታደር ቁጥር ከ50,000 አይበልጥም።

ከዚህ አንጻር የጣልያኑ ጦር የታጠቀውን የመሳርያ ጥራት፣ ታንኩን፣ መድፉን፣ ከሁሉም በላይ ደግሞ እነዚያን መካች የሌላቸውን የሰማይ ላይ ጠላቶች አውሮፕላኖች እንኳን ወደ ጎን ትተን፣ በእግረኛ ወታደር ደረጃ ማርሻል ባዶሊዮ ለዚህ ወሳኝ ጦርነት ጥሩ ሆኖ የተዘጋጀና ቀድሞ የመሸገ ሁለቱ ክፍለ ጦሮቹ ላይ ሁለት ሻለቃ ጦር ጨምሮ በጠቅላላው ከ70,000 እስከ 80,000 የሚደርሱ ወታደሮቹን አሰልፏል። ምናልባትም ሊበልጥ ይችላል።

ጃንሆይ በማይጨው ስለሚደረገው የመጨረሻ ወሳኝ ጦርነት በገበሬ ሰላዮች፣ ለዚያውም ስለ ዘመኑ ወታደራዊ አሰላለፍም ሆነ አወቃቀር ምንም እውቀት ከሌላቸው ሰዎች፣ በተገኙ ቁርጥራጭ መረጃዎች መሰረት እቅድ ሲያወጡና ሲነድፉ ቢውሉም፣ እድሜ ለነዚያ የሰማይ ላይ የቆርቆሮ አሞራዎች እያንዳንዷን የኢትዮጵያ ወታደር እንቅስቃሴ የሚቆጣጠረው ማርሻል ባዶሊዮ እያንዳንዷን ከንጉሠ ነገሥቱ የምትተላለፍ ትዕዛዝ ለተላለፈለት ራስ፣ ደጃዝማችም ሆነ ፍታውራሪ ሳትደርስ በፊት እጁ ትገባ ነበር።

የጣልያን ራዲዮ ቴሌግራፊስቶች ያለማሰለስ ከንጉሡ በሬዲዮ የሚተላለፉትን መልክቶች፣ ትዕዛዞች አንዷንም ሳይተዉ ጠልፈው ይከታተሉ ነበር። እንዲህ ባለ ያለገመድ የሚተላለፍ የራዲዮ ቴሌግራም አደገኝነቱን ያኔ ተንቤን እያለን ለራስ ካሣ በተደጋጋሚ ባሳስብም፣ አይዞህ አንበሳዬ ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር በምስጢር ቃል ነው የምንነጋገረው እያሉ ሲሸነጋግሉኝ፣ ጣልያኖች የምስጢር ቁልፏን ያለ አንዳች ችግር እየፈቱ ለእያንዳዱ ራስ፣ ደጃዝማች፣ ፊታውራሪና ቀኛዝማች የተላለፈ ትዕዛዝና መመሪያ እየከተቡ ለማርሻል ባዶሊዮ ያጎርሱት ነበር።

ጃንሆይ ልክ እንደራስ ካሣ ሁሉ ትልቅ ስህተት ሰሩ። ለማርሻል ባዶሊዮ የማይጨው የማጥቃት ዘመቻ ምስጢር አልነበረም። ማርሻል ባዶሊዮ እልገረመውም ወይም መጋቢት 24 ቀን ከጃንሆይ ለራስ እምሩ የተላከውን ደብዳቤ የያዘው ፈረሰኛ መልክተኛ፣ በደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ሰዎች ተይዞ፣ የደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሣ ሰዎች ደብዳቤዋን ለጣልያኖች ሊያደርሱ ሲጣደፉ፣ በልጁ ጦር ክፉኛ ቢመቱም፣ የልጁ ጦር ያቺን የጃንሆይ ደብዳቤ ከጣልያኖች እጅ እንዳትገባ ያደረገው ትግል ውጤታማ አልነበረምና ያቺ ደብዳቤ ከማርሻል ባዶሊዮ እጅ ገባች።

ጃንሆይ ለራስ እምሩ በዚያች በጣልያኖች እጅ በገባች ደብዳቤያቸው ሲጽፉ "ጦራችንን ይዘን ወደፊት ሄደናል። አሁን እነሆ የአያን ቀበሌ ይዘን ሰፍረናል።"

ከወታደሮችዎ ጋር ሊያደርጉት የሚችሉት ነገር አለ ብለው ቀጥለው ጃንሆይ ሲጽፉ፣ "ከወታደሮችዎ ጋር ሊያደርጉት የሚችሉት ነገር አለ ብለው የሚገምቱ ከሆነ ያድርጉት። ይሁንና ጦርዎ ለሌላ ውጊያ የማይመችውና የማይሆንለትም መስሎ ከታየዎት፣ ምንም ተስፋ የሌለው ነገር ከሆነና ፈቃድ ቢሆን ወደኛ መጥተው ከኛ ጋር ለመሞት ከወሰነ ከዚያው ከዳባት ባስቸኳይ በቴሌግራፍ ያሳውቁኝ" ይላል።

ሌላው የጣሊያን ራዲዮ ቴሌግራፊስቶች ከጠለፉት መልእክት መካከል ጃንሆይ ለእቴጌ መነን ያስተላለፉት መልእክት ይገኝበታል። በዚሁ ያለገመድ በተላለፈው መልእክት መጋቢት 27 ቀን ጃንሆይ፣ "ከጠላት ጦር ሰፈር ተቃርበን ተፋጠናል፤ ሰዎች እንደሚሉት ከኛ ጋር ጦርነት እርስ በርስ በጦር ሜዳ መነጽር እየተያየን ነው። ሰዎች እንደሚሉት ከኛ ጋር ጦርነት ሊገጥም የተዘጋጀው የጠላት ጦር ከ10,000 አይበልጥም። የኛ ሰራዊት በትክክል 51,000 ነው። ግን እንዲያው ወደ ጠላት የጦር ሰፈር ስንቃኝና ስንመረምር በኛ ግምት የጠላት ጦር ወደ 20,000 ይሆናል እያልን እናስባለን። የኛ እምነት በፈጣሪ ላይ ነውና እንደሚረዳን በጽኑ እናምናለን" ይላል።

ሌላው አሳዛኝ ነገር አሁንም በጣልያኖች እጅ ሌላ ጥብቅና ወሳኝ መረጃ ገባ። በዚህ በጣልያኖች እጅ በገባና በገመድ የለሽ ራዲዮ ሲተላለፍ የተጠለፈ መልእክት እንዲህ ይል ነበር። "ቅዳሜ መጋቢት 28 ቀን በጠላት ላይ ዘመቻ እናደርጋለን። ቅዳሜ ባይሆንልን ሰንበትን ውለን ሰኞ ማለዳ የማይቀር ጉዳይ ነው" ይላል።

ለዚህም ነበር ማርሻል ባዶሊዮ ብዙም ሳይጨነቅና ሳይደነቅ የንጉሡ ጦር በቁርጥ መቼ እንደሚዘምትበት አውቆ በምሽጉ ተቀምጦ ና ግጠመኝ እያለ በትግዕስት ይጠብቅ የነበረው። እዎ ማርሻል ባዶሊዮ ዝግጅቱ የንጉሡን ጦር በምሽጉ ሆኖ ለመከላከል ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያን ጦር ብትንትኑን ለማውጣት ጭምር ነበር። መጋቢት 31 ቀን ልክ ጎህ ሲቀድ የኢትዮጵያው ሰራዊት እየተኮሰ፣ እየፎከረና እየሸለለ በሺዎች ረድፍ ተሰልፎ እየሮጠ በጣልያኖች ላይ ዘመተ። ባገኘው መረጃ መሰረት እንደሚዘመትበት አሳምሮ የሚያውቀውና በጥሩ ሁኔታ የመሸገው የጣልያን ጦር አጥብቆ በሰራው ምሽጉ ተኝቶ የኢትዮጵያውን ወታደር በመትረየሱ ያረግፈው ገባ።

ወሳኙ ስለ ኢትዮጵያ የወደፊት እድል የሚወስነው ጦርነት በዚች ማለዳ ጀመረ። በዚህ ወሳኝ ጦርነት የመትረየስና የመድፍ ጥይት እየወረደበት በሶስት ረድፍ ተሰልፎ ህይወቱን ለእናት ሀገሩ ሊሰዋ እየፎከረና እየሸለለ የኢትዮጵያ ጦር ወደፊት ሄደ። በሶስቱ ራሶች መሪነት (በራስ ካሣ፣ በራስ ሥዩምና በራስ ጌታቸው) በሶስት ረድፍ ተሰልፎ የጠላትን አንገት በጎራዴው ሊቀላ፣ በጦሩ ደረት ሊበሳ፣ በጥይቱ ግንባር ሊበረቅስ በሶስት መንገድ እንደጎርፍ የሚወርደው ጀግናው የኢትዮጵያ ሰራዊት የመጀመሪያውን የጣልያኖችን ምሽግ ሰብሮ ገባ።

በአራተኛው ረድፍ ተሰልፎ የነበረው በደጃዝማቾች ብቻ የሚመራውና የልጅና የክንባታ ልጆች ያሉበት ጦርም ትልቅ ውጤት አስመዘገበ። የአራተኛው ረድፈኛ ዋና

ግዳጅ የነበረው ጣልያኖቹን ኮርኩሮ ከምሽጋቸው አስወጥቶ ለሶስቱ ራሶች ሰራዊት ሁኔታዎችን ማመቻቸትና በር መክፈት ነበር። እዎ አራተኛው ረድፈኛ ይኼን የተሰጠውን ግዳጅ መቶ በመቶ ከግብ አድርሷል።

ከማለዳ ጀምሮ ከጣልያኖች ብብት ውስጥ ገብቶ እየኮረኮረና እየቆነጠጠ ረፋዱ ላይ የአምባ በሆራን ተራራ በእጁ አስገባ። ከአምባ በሆራ ተራራ ላይ ሆኖ የጣልያኑን ጦር ቀኝ ክንፍ ጥሩ አድርጎ ነረተው። ቀጠቀጠው። እርር...ሪ አስባለው። ቀትር ላይ ቁጥር ስፍር የሌላቸው አውሮፕላኖች እየዞሩ የቦምብ ናዳቸውን በኢትዮጵያው ሰራዊት ላይ አወረዱበት። እንዲህ ከሰማይ እንደበረዶ ቦምብ እየወረደበት፣ ከምድር የመድፍና የመትረየስ ጥይት እያጨደው፣ በታላቅ ጀግንነት እምቢኝ ለሀገሬ እያለ በጣልያኖች መሀል ገብቶ በሚቀናውና በሚመቸው በጎራዴው የጣልያኖችን አንገት ይቀላ ጀመር።

በዚህ ጦርነት ኢትዮጵያውያን ጦረኝነት በእግዚያብሔር ተመርቆ የተሰጣቸው ብርቅና ድንቅ ተፈጥሮ መሆኑን በድጋሚ አረጋገጡ። ኢትዮጵያውያን እንዲህ አንጎል በሚያዞር የጦርነት አውድማ ውስጥ በፍጹም ቆራጥነት ያለ አንዳች ፍርሃት በታላቅ ጀግንነት የጣልያኑን ጦር ወጥረው ይዘው፣ አላስቆም አላስቀምጥ ይበሉት እንጂ፣ የተሻለ መሳሪያ የታጠቀው የጠላት ጦር በጀግናው የኢትዮጵያ ሰራዊት ላይ ከፍተኛ ጉዳት አደረሰበት።

ጀግኖቹ አንበሶቹ የኢትዮጵያ ልጆች ዋናውን የጠላት ጦር ምሽግ ሰብረው ለመግባት ያደረጉት ሙከራ ሁሉ በእጅ በሚወረወሩ ቦምቦች ከምሽጎቹ በራፍ ላይ አስቀራቸው። የመጀመሪያው ዘማች በእጅ ቦምብ ተመትቶ ሲወድቅ ሁለተኛው የወደቀ ወንድሙን ዘሎ ወደፊት ሲል፣ እሱም የመጀመሪያው ወታደር እጣ ፈንታ ሲደርሰውና ሲወድቅ፣ ሁለት ሲወድቅ ሌላ አምስት እየተተካ፣ አምስቱ ሲወድቁ ሌሎች አስሮች እየተተኩ፣ ቢታገሉም የጣልያኖችን ምሽግ በሬሳቸው አጥር ከመስራት ውጪ ሰብሮ መግባት ሳይሆንላቸው ቀረ። አራተኛው ረድፈኛ ጦር የቀኝ ክንፉን የጣልያኑን ጦር ክፉኛ ጎድቶ ጣልያኖች ይዘውት የነበረውን በበርካታ ምሽጎች የታጠረውን መሬት በእጁ ቢያስገባም፣ በሶስቱ ራሶች ለሚመራው ጦር የጣልያኖችን ምሽግ መስበሪያ በር ከፍቶ ቢጠብቅም፣ የሶስቱ ራሶች ጦር የተሰጠውን ግዳጅ መፈጸም ሳይሆንለት ቀረ። በመሆኑም ወደ ኋላው ተመለሰ። አምባ በሆራን ይዞ የሶስቱን ራሶች ወደፊት መግፋት ይጠብቅ የነበረው አራተኛው ረድፈኛ ሰራዊት ብቻውን የጠላትን ጦር በአምባ በሆራ ተራራ ላይ አግዶ ብዙ መቆየት ስላልቻለ እሱም አምባ በሆራን ለቅቆ ወደኋላው መመለስ ተገደደ።

በ16:00 ሰዓት ላይ የሶስቱ ራሶች ጦር እንደገና በሶስት ረድፍ ተሰልፎ ለሶስተኛ ጊዜ ማይጨውን ለመያዝ ወደፊት ሄደ። ለሶስተኛ ጊዜ የተደረገው ይኼው ማይጨውን የመያዝ ጦርነት እድሜ ለአራተኛው ረድፈኛ ጦረኞች የጣልያኑን ሰራዊት ወገቡ ላይ ሰብረው የሚገባበት ሲያሳጡት፣ የሶስቱ ራሶች ጦር የጣልያኑን

ዋና ምሽግ ሰብሮ ገባ። ድል በኢትዮጵያውያን እጅ የገባች መሰለች። በዚች ቅጽበት ደግም አድዋ ሊደገም የሰዓታት ልዩነት ሲቀረው እነዚያ ከሀዲዎች፣ ራያዎችና አዘቦዎች ድልን በእጁ ሊያስገባ የተቃረበውን የገዛ ወንድማቸውን ከጀርባው ገብተው ጨፈጨፉት። ድልን በእጁ ሊጨብጥ ወደፊት የገሰገሰውን የእናታቸውን ልጅ ድል ነሱት።

አዎ ዛሬ እነዚህ ከሀዲዎች ጦርነቱን ወስነዋል። ታሪክም ሰርተዋል። ታሪኩ ግን የክህደት ታሪክ ነው። ለሰላሳ ሽልንግና ለአዲስ የጣልያን መሳሪያ ሲሉ ለጣልያን ባንዳነት አድረው የገዛ ወንድማቸውን ክደውታል። አሁን የኢትዮጵያ እድል ተወስኗል። ተሸንፈናል። ኢትዮጵያውያን በማይጨው ጦርነት ተሸነፉና በያቅጣጫው ወደየትውልድ መንደራቸው መሸሽ ጀመሩ።

ጃንሆይ በዚህ ታሪካዊ የማይጨው ጦርነት ላይ በቤልጂየሞች ጥሩ ሆኖ የሰለጠነውን የክብር ዘበኛ ጦራቸውን በግንባር እየመሩ ከበርካታ ምኒስትሮቻቸው ጋር በዚህ ጦርነት ተካፍለዋል፤ ተዋግተዋል። ጃንሆይ ከዚህ ድል ከእጁ አፈትልኮ ከወጣች ታሪካዊ ውጊያ በኋላ ወደ ቀኻቸው ሲመለሱ ያ በወርቅ የተንቆጠቆጠ የማርሻል ወታደራዊ የደንብ ልብሳቸው በደም ፍንጣቂና በጭቃ ተለውሶ ነበር። በራያዎች ክህደት ድል ተነስቶ ድል የሆነው የኢትዮጵያ ሰራዊት ማይጨው ላይ ተፈትቶ ተበተነ።

እኔ ራሴ የተሳተፍኩበት አራተኛው ረድፈኛ ከጣልያኖች ጋር ያደረገው ጦርነት እጅግ በጣም የሚገርም ነበር። 4ኛው ረድፈኛ ወይም 4ኛው ክፍለ ጦር ከንባታዎችን ጨምሮ የበርካታ የሸዋ ደጃዝማቾች ጦር ህብረት ነበር። ከመሪዎቹ አንጋፋዎቹ ሽማግሌው ደጃዝማች ወንድይራድ፣ ወጣቱ ደጃዝማች አበራ የሰላሌው፣ ደጃዝማች ኃይሉ ከበደ የዋጎች ወራሽ ሲገኙበት፣ መሪያቸውን ያጡት የከንባታ ልጆች ከጀግናው የአቢቹ ጦር ጋርና የሌሎችም ደጃዝማቾችን ጦር ያካተተው ጠንካራ ጦር፣ በዚህ ጦርነት ኢትዮጵያ በጦር ግንባር ካሰለፈቻቸውና በጦርነት አውድማ ካዋለቻቸው፣ በጦርነት እሳት ከማገደቻቸው ምርጥ ልጆቿ፣ የደጃዝማች አበራ፣ የደጃዝማች ወንድይራድ፣ የደጃዝማች ኃይሉ ከበደ፣ የልጁና የከንባታ ልጆች በታላቅ ወኔና ቆራጥነት ታላቅ ጀብዱ ሲሰሩ ለማየት ታድያለሁ።

ይኼው የበርካታ ደጃዝማቾች የህብረት ጦር በጣልያኖች ብቻ ሳይሆን በራያዎችም ጭምር ክፉኛ ተጎድቷል። በዚች የመጨረሻዋ ቀን ወሳኝ ጦርነት የአቢቹ ጦር ጄኔራል ወርቁ አባቱን አጥቷል። ቀኛማች ሼክ ሁሴን አባወርቁ ከልጃቸው ጋር ጎን ለጎን ከጠላት ጋር ሲዋጉ ከጀርባቸው ከራያዎች በልጃቸው ላይ የተተኮሰችን ጥይት በደረታቸው ተቀብለው ልጃቸውን አድነው እሳቸው ወድቀዋል። የጀግና ሞት ሞተዋል።

አባቱን ያጣው ወርቁ የቆሰሉ የትግል ጓዶቹን ሲደግፍ፣ ሲረዳና ሲያስተባብር ማየት እጅጉን በጣም ያኮራል። በዛሬው ጦርነት አምስት ምርጥ ጀነራሎችን በጦር ሜዳ ሲዋጉና ሲያዋጉ ማየት ብቻ ሳይሆን ከጎናቸው ተሰልፎም ጠላትን የመውጋቱ እድል ገጥሞኝ ነበር።ሀብቶም፣ ተሰሩ ጽዮን፣ ጋሹ፣ ወርቁ እና አቢቹ። ምናልባትም የነዚህ ወጣት ጀነራሎች የህብረት ጦር ህይወቴን አትርፎታል። እንዲያ ምድር ቀውጢ ሆና አሸናፊውና ተሸናፊው ባልታወቀበት ሰዓት፣ ፈረሴ አንገቱን በጥይት ተመቶ ሲወድቅ እኔን ከኮረቻው ላይ አስፈንጥሮ ጣለኝ። እኔ ራሴን ስቼ በወደኩበት መስመር ራያዎች ገፍተው እየገቡ ነበርና አለቀልኝ እያልኩ ለመነሳትና ለመሮጥ ስጣጣር እስከዛሬ ማንነታቸውን የማላውቀው ሁለት የአቢቹ ፈረሰኛ ጦረኞች ጎን ለጎን ሽምጥ ጋልበው መጥተው ማንጅራቴን ጨምድደው እየጎተቱ ወስደው ከአስተማማኝ ቦታ ጣሉኝ። ብዙም ሳልቆይ በዋናው የጦር ሰፈር ራሴን አገኘሁት።

ወርቁ በዛሬው ጦርነት በጣም የሚወዳቸውን አባቱን ቢያጣም የቆሰሉና የደከሙ የጦር ሜዳ ወንድሞቹን በመርዳቱ አልቦዘነም። ሀብቶም ግራ እግሩን ቢመታም በጠፍር ግጥም አድርጎ አስሮ የተረፉ ወታደሮቹን ያሰባስባል። አቢቹ በሁለት ጥይት ትከሻዋን ብትመታም ቁስሏን እንኳ ለማሰር ሳትሞክር ጭላሸት በሚመስለው ጥቁር ፈረሷ ላይ ሆና ወዲህ ወዲያ እየተዘዋወረች ጦሯን ታሰባስባለች። ተሰፋ ጽዮንና ጋሹ በማይጨው የዛሬው ጦርነት ታሪክ ሊጽፈው የሚገባ ጀብዱ ሰርተው በአምባ በሆራ የጦርነት አውድማ ወድቀዋል።

በዛሬው ጦርነት ብዙ ቂም የተያዘበት የአቢቹ ጦር እጅጉን ተጎድቷል። ሁለት ምርጥ አዋጊና ተዋጊ ጀነራሎቹን ከማጣቱም በላይ ሁለት ሶስተኛው የሰራዊቱ አባል በማይጨው የጦርነት አውድማ ለእናት ሀገሩ አጥንቱን ከስክሶ፣ ደሙን አፍስሶ፣ አዳውን ከፍሏል።

ማምሻው ላይ የሁለቱን ደቦል አንበሶች ሬሳ ጀግኖቹ ከጦር ሜዳ አምጥተው ከአንዲት በጣልያኖች ቦምብ ግማሽ አካሏ ካረረች ዋርካ ስር በታላቅ ክብር ቀበሯቸው። ጎን ለጎን ከጠላት ጋር እንደተዋጉ ሁሉ ጎን ለጎን እስከመጨረሻው ተቀበሩ። በዚች አንድ ሰዓት ባልሞላች ዋይታና ለቅሶ በሌላት የቀብር ስነ ስርአት ላይ እኔ፣ ደጃዝማች አበራና ኮሎኔል ኮኖቫሎብ ተገኝተን ነበር። በዚች ትንሽ የቀብር ስነ ስርአት ላይ የግል አገልጋዬ አንበሳም ተገኝቶ ነበር። ምንም እንኳን ራስ ካሣ እንዲያገለግለኝ ቢሰጡኝም አንበሳ ግን ሙሉ በሙሉ የአንበሳው የአቢቹ ጦር አባል ነበር።

ታዲያ አንበሳዬ ካንዲት ድንጋይ ላይ ቁጭ ብሎ ድምጽ ሳያሰማ ዝም ብሎ እንባውን ሲያወርደው አገኘሁት። እሱ በአለቆቹ ሞት አዝኖ፣ እኔ በህይወት ተርፎ ስላገኘሁት ተደስቼ እንደልጄ አቅፌ ሳምኩት። በተስፋና በጋሹ ሞት እጅጉን አዝኜ አንበሳዬ ከዚያ ቀውጢ ጦርነት በመትረፉ ፈጣሪዬን እያመሰገንኩ ወደ ጦር ሰፈር

ስመለስ ኮሎኔል ኮኖቫሎቭ እንደ ህጻን ልጅ ሲያለቅስና ሲንፈቀፈቅ አገኘሁት።
"ኢይዞን ኮሎኔል! ኢይዞን!" አልኩት ከጎኑ እየተቀመጥኩ።

"እየሀ የእግዜሩን ተንኮል፣ እኔን ሽማግሌውን ከዚህ ጦርነት አትርፎ እነዚህ ህጻናት ሲሞቱ፣ እግዜሩ እያየ ዝም ማለቱ አያስለቅስህም ትላለህ?" አለኝ። እዎ እግዜሩ ስለመኖሩ መፈላሰፍ ይቻላል። ጠቅላላው የኢትዮጵያ ሰራዊት በጦርነቱ እግዜሩ እንደሚረዳውና እንደሚያሸንፍ ያምን ነበር። ተሸነፈ። እግዜሩ ግን ምንም አላለም። እንዲህ ከሽሜው ጎን ተቀምጬ ሳባብል ደጃዝማች አበራ መጣና እሱም ከጎናችን ተቀመጠ፤ ቃላት ግን አልተለዋወጥንም።

የደጃዝማች አበራ የሰላሌው ጦር በዛሬው ጦርነት ሶስት ጊዜ የጣልያኖቹን ምሽግ ሰብሮ ገብቶ እጅ እያስገባ፣ እንደገና ሶስት ጊዜ እንደዚያ ያንን ከባድ መስዋዕትነት የከፈለበትን ለትቆ መውጣት ተገዷል። በዚህ ጦርነት ሶስት አራተኛው የሰላሌዎቹ አሉ የሚባሉት ቁራጦቹ፣ ጀግኖቹና ደፋሮቹ ልጆች ከማይጨው የጦር ሜዳ ከአምባ በሆራ አልተመለሱም። እስከመጨረሻው ድረስ ከጠላት ጋር ጉሮው ለጉሮሮ ተናንቀው በየምሽጉ ወድቀዋል።

ደጃዝማች አበራ ጥቂት ሲተክዝ ቆይቶ፣ "በሉ ተነሱ ጃንሆይ ለምክር ጠርተውናል" አለንና ብድግ ሲል እኛም በፍጥነት ተነስተን ተከተልነው። ከጃንሆይ ዋሻ ስንደርስ በማይጨው የጦር ሜዳ ከወደቁት ትልልቆቹ የጦር አበጋዞች በስተቀር ሁሉም ተገኝቶ ነበር፤ ያቺን ዋሻ ሞልተዋታል።

ገና ከዚያች የጃንሆይ ዋሻ እግራችን ከመግባቱ የኢትዮጵያን ሰራዊት የወደፊት እድልና እጣ ፈንታ የሚወስነው የጦረኞች የምክር ሸንጎ ጀመረ። ጀግናው የኢትዮጵያ ሰራዊት በማይጨው ጦርነት ድል ከፏ አምልጣ ድል ከተነሳና ከተሸነፈ በኋላ ጃንሆይ በአያዋ የዋሻ ቤተ መንግስታቸው ተመልሰው ከትልልቆቹ የጦር አበጋዞቻቸው ጄኔራሎቻቸው ጋር ለምክር ተቀመጡ።

እንዲህ በጃንሆይ የአያ የዋሻ ቤተ መንግሥት ለምክር ከተሰበሰቡት የኢትዮጵያ ከፍተኛ ሹማምንትና የጦር መሪዎች ከግማሽ በላዩ ያህል የሚሆኑት ከፋኛ ቆስለው ነበር። አንዳንዶቹ በሁለትና በሶስት ጥይት ተመትተው በቃሬዛቸው ላይ ተኝተው፣ ምርኩዝ ይዘው፣ ድንጋይ ተደግፈው፣ ህመማቸውን ውጠው፣ እነሆ ከንጉሣቸው ጋር በዚያች ትንሽ ዋሻ እንደ ከብት ታጉረው በታላቅ ትግስት ምክሩን እየመከሩ ናቸው።

በዚች ታሪካዊ የጦር ምክር በአያ የጃንሆይ የዋሻ ቤተ መንግሥት ያልተገኙ አውቅና ምርጥ ጀግና የጦር ጀነራሎች ቢኖሩ፣ ጀግኖቹ እነደጃዝማች መንገሻ ሂልማና ባላምባራስ አበራ ተክሌ የማይጨው አገረ ገገር፣ ከሁሉም በላይ ደግሞ ሽማግሌው ደጃዝማች ወንድይራድ ይገኙበታል።

ሽማግሌው ደጃዝማች ወንድይራድ ከዛሬ አርባ ዓመት በፊት ከአፄ ምኒልክ ጦር ጋር በአድዋ የጣልያንን ጦር ድል የመቱ ጀግና፣ ለሁለተኛ ጊዜ ተመሳሳይ ጠላትን በማይጨው ገጥመው በጎራዴያቸው አንገት ቀንጥሰው፣ በጦራቸው የጠላት ደረት በስተው ቢወድቁም፣ ከዚህ በላይ አስደሳች ሞት የለምና ጀግናው አዛውንት ደጃዝማች ወንድይራድ የጀግና ሞት ሞተዋል።

በአያ የጃንሆይ የዋሻ ቤተ መንግሥት የተሰበሰበውና ሌሊቱን ሲመክር ያደረው የጦር ሸንጎ ንጋት ላይ ባለሁለት ነጥብ ስምምነት ላይ ደርሶ ተበተነ።

1ኛ ራስ ስዩም መንገሻ የቀረ ጦራቸውን አሰባስበው ወደፊት በመግፋት ላይ ባለው የጣልያን ጦር መሀል ቀዳዳ እየፈለጉ ወደ ሰሜን እንዲመለሱና በሰሜን የአርበኝነት ትግሉን እንዲቀጥሉ፣

2ኛ ጃንሆይ ከቀረው ሰራዊታቸው ጋር ከራስ ሥዩም መንገሻና ከሚያጅቧቸው ጥቂት ደጃዝማቾች በስተቀር የሌሎችን ራሶችና ዳጃዝማቾችን ጦር ይዘው ወደደቡብ እየወረዱ አመቺ በሆነ ቦታ ላይ ሁሉ ወደደቡብ በመውረድ ላይ ያለውን የጠላት ጦር እያገዱና እየመከቱ ወደአዲስ አበባ እንዲመለሱ፣

ይኼ የጦር ሸንጎ ቢስማማና ቢወስንም ወደፊት የሚሄደውን የጣልያንን ጦር ግን የሚያግደው አልነበረም። እንዲህ በሚያሳዝን ሁኔታ የኢትዮጵያው ሰራዊት ተሸነፈ።

34

የእንግሊዞች ቀይ መስቀል

How do you do እያለ ዶክተር ጆን ሜሊ /Dr. John Melly/ የእንግሊዞች ቀይ መስቀል ማህበር መሪ በደስታ ከልቡ ተቀበለን።

ይኼ የእንግሊዞች ቀይ መስቀል ማህበር የንጉሡ ነገሥቱን ጦር አጅቦ በየካቲት ወር አጋማሽ ላይ ኮረም ገብቶ፣ በሰሜኑ የጦር ግንባር ይኼ ነው የሚባል ነገር ሳይሰራ ከርሞ እነሆ ዛሬ በደሴ በኩል አድርጎ ወደ አዲስ አበባ ለመመለስ በዝግጅት ላይ ነው።

እንዲህ የእንግሊዞች ቀይ መስቀል ማህበር በደሴ በኩል መንገዱን አቅንቶ ወደ አዲስ አበባ ለመመለስ ጓዙን ሲቋጥር ከአሸንጌ ሐይቅ በስተሰሜን በኩል በእግር የጥቂት ሰዓታት መንገድ ርቀት ላይ አሁንም ከፍተኛ ውጊያ እየተካሄደ ነው።

አዎ ይኼ የእንግሊዞች ቀይ መስቀል ማህበር፣ ብቸኛው በርካታ ዶክተሮችንና አስታማሚዎችን ያቀፈ፣ በመድሃኒትና በህክምና መሳሪያዎች ጥሩ ሆኖ የተደራጀ፣ በሰሜኑ የጦር ግንባር ንጉሠ ነገሥቱን አጅቦ እጅግ በጣም ዘግይቶ የደረሰ ማህበር ነው።

ለራስ ሙሉጌታ የተላኩት ሁለቱ የፖላንድ ዶክተሮች አንድ የራስ ሙሉጌታን ቁስለኛ ወታደር እንኳን ሳያክሙ ነበር በጣልያኖች ምርኮ ስር የወደቁት። ለራስ ካሣ የተላከው የነምሳው ዶክተር በኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማህበር ታጅቦ፣ የረባ መድሃኒት እንኳን ሳይኖረው በሰሜኑ የጦር ግንባር ጥቂት ዘግይቶ ቢደርስም፣ ሌት ተቀን ህይወቱን አደጋ ላይ ጥሎ፣ የሰው ልጅ የማይችለውን መከራ ሁሉ ተሸክሞ፣ ደክመኝ ሰለቸኝ ሳይል የራስ ካሣ ወታደሮችን ሲያክም ከርሟል። የእንግሊዞችን የተደራጀ መድሃኒትና መሳሪያ አንድ አስረኛውን ያህል ቢኖረው ኖሮ ስንት ህይወት ባተረፈ ነበር።

ረጅምና ቀጭን ቁመና ዛሳው ወጣቱ እንግሊዛዊ ዶክተር ሜሊ ከጥቂት ሳምንታት በኋላ በሽፍቶች በመሀል አዲስ አበባ ተገድሏል። ከልብ በመነጨ እውነተኛ አቀባበል በድንኳኑ ተቀበለን። ዶክተሩ እኛ በተነቤን ፍዳችንን ስናይ እሱ የተደራጀውን ማህበሩን ይዞ ያለ ምንም ስራ በደሴ መቀመጡ እጅጉን በጣም እንደቆጨው በፊቱ ላይ እየተነበበ፣ ከሱ ጋር በመኪና ወደ ደሴ አብረነው እንድንሄድ ጋበዘን።

በዶክተር ሜሊ የሚመራው የእንግሊዞች ቀይ መስቀል ማህበር ከሰላሳ በላይ ዶክተሮች፣ በርካታ ረዳቶች እና አስታማሚዎች በተጨማሪም ብዙ የሱማሌና የህንድ ሾፌሮችንና መካኒኮችን የያዘ፣ 16 በጥሩ ሁኔታ ላይ ያሉ ስንቅ፣ ትጥቅና መድሃኒት የተጫኑ ከባድ የጭነት ተሽከርካሪዎች ያሉት ድርጅት ነው።

በነዚህ የእንግሊዙ ቀይ መስቀል ማህበር ዶክተሮች፣ ረዳቶች፣ አስታማሚዎች፣ ሾፌሮችና መካኒኮች መካከልም የሚገርሙ፣ አለምን መዞር የሚወዱ ጀብደኞችም አሉበት። ከነዚህ ተንኾ ጀብደኞች መካከል ካፕቴን ስሚዝ /Cap. M. Smith/ እንደ ቀዳሚ ምሳሌነት ሊጠቀስ ይገባዋል። ካፕቴን ስሚዝ እድሜውን በትክክል መገመት የማይቻል ቢሆንም በ40ዎቹና በ50ዎቹ ውስጥ የሚገመት ሲሆን ማንም ሰው በመቶ ዓመት እድሜ ውስጥ እንኳን ሊያካብተው የማይችለውን ልምድ ያለው ሰው ነው። ካፕቴን ስሚዝ በዚች ምድር ላይ ያልዳሰሳት፣ ያልረገጣት ሀገር አለች ብሎ ማመን እጅጉን ያስቸግራል።

ይኼ እንግሊዛዊ ተንኾ ጀብደኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ ፖርቱጋልኛ፣ ስፓንሽኛ፣ ጣልያንኛ፣ ሩሲያኛ፣ ሰርቢያኛ፣ አረብኛና አማርኛ ልክ አፉን እንደፈታበት እንግሊዝኛው አቀላጥፎ ይናገራል።

አብዛኛውን ፈረንጅ የሚያስቸግሩትን የአማርኛ ድምፆች እንደ ፀ፣ ቀ፣ ጸ፣ ኀይነቶችን ሳይቀር ልክ እንደ ሀገሬው ሰው አስተካክሎ ይናገራል። አረብኛም ቢሆን ከነዚህ ቋንቋዎች ከእውነቶቹ የበረሃ ልጆች ባልተለየ ሁኔታ በትክክል ይናገራል። በጫወታ መሀል በተጨማሪ ህንድኛና የማሌዥያን ቋንቋ ሳይቀር አቀላጥፎ ይናገራል። "እዛያ ነበርኩ" ብሎ ሙቹ አፍጋኒኛ /ፓሽቶና ዳሪ/ እንደ ተማረ በጠየኩት ጊዜ በቀላሉ "እዛያ ነበርኩ" ብሎ መለሰልኝ። ካፕቴን ስሚዝ ወደ ኢትዮጵያ የመጣው ከቦሊቪያ በቻኮ /Chaco/ ጦርነት

ማለት በቦሊቪያና በፓራጓይ መካከል በ1932-1935 ዓ.ም. በተደረገው ጦርነት ተካፍሎ ነው።

በአውሮፓውያን እምብዛም ባልተጎበኙ የደቡብ ቻይና ግዛቶች ከሃያ ሁለት ዓመት በፊት እንደነበርኩ አንስቼ ባጫወትኩት ጊዜ፣ እኔ የረገጥኳቸውን የደቡብ ቻይና ግዛቶች ተወልዶ እንዳደገበት ሀገር ትንንሿን ነገር ሳይቀር ገላልጦ ሲያወጋኝ አፌን ከፍቼ ቀረሁ። እዎ ከዚህ እንግሊዛዊ ተጓዥ ጀብደኛ ሰው ጋር ባሳለፍኳት አጭር ጊዜ ውስጥ፣ ከዚህ በፊት በተለያዩ የአረብ ሀገሮች ስላሳለፍኩት ህይወት በተዝታ ተመልሰን አስታውሰናል። ልክ ትናንት እንደነበርን ሁሉ ስለ ሲንጋፖር፣ ስለ ዒደን፣ ስለሳይጎን፣ ስለ ባርሴሎና፣ ስለ ፖርትሳይድ፣ ስለ ቦምቤይ፣ ስለ ማድሪድ፣ ስለ ቶኪዮ፣ ስለ ካይሮ፣ ስለ ሄልሲንኪ፣ ስለ ሎንዶን፣ ስለ ፓሪስ፣ ስለ ኢስታንቡል እና ስለሌሎች ዘርዝሬ ስለማልገፋቸው ከተማዎች አንስተን ብዙ ብዙ ተጫወትን።

ይኼው ጀብደኛ ሰው በጨዋታው ቀጥሎ «ወዳጄ ካፕቴን ፓርለሳክ፣ እነዚህ ከብቶች (ጣሊያኖችን ማለቱ ነው) በመላው አለማችን የተከበረውንና የተቀደሰውን የቀይ መስቀል ማህበር ድንኳን፣ የምስኪኖቹን የኢትዮጵያውያንም ይሁን የሌሎችን አገሮች፣ በአውሮፕላኖቻቸው በሚያቃጥል ቦምብ እንደሚደበድቡ ታውቃለህ?» ሲል በንዴት ጠየቀኝ።

የማውቀውን በሰሜኑ የጦር ግንባር በተንቤን ጣሊያኖቹ በአውሮፕላኖቻቸው ስለደበደቧቸው አንድ የራስ ካሣ ወታደር እንኳን ስላልሰፈረባቸው መንደሮች ስነግረው በንዴት «ከብቶች! ከብቶች!» እያለ ጮኸ። ስለ ጣሊያኖቹ አውሮፕላኖች የቀይ መስቀልን ድንኳን በቦምብ ስለመደብደባቸው ዶክተር ሜሊና ሙሉ የድርጅቱ ሰዎች በአንድ ቃል እውነቱን አረጋግጠውልኛል። ለዚያም መሰለኝ የእንግሊዞች ቀይ መስቀል በምዕራባዊው የኮረም ገደላማ ቀበሌ የሆነ ውሸቅ ቦታ ላይ ድንኳኖቻቸውን ተክለው፣ ከባድ ተሽከርካሪ መኪኖቻቸውን በተፈጥሮ ደን ለመሸፋፈን የሞከሩት።

ከተረገሙት የጣልያን የቆርቆሮ አሞራዎች እይታ እንኳን እነዚህን ዘመናዊ ከባድ የጭነት ተሽከርካሪዎች ቀርቶ ትንሽዬ የቤት መኪናም መደበቅ መከራ ነው። እዎ ጣልያኖች ከሰማይ ላይ ሆነው በአሞራ አይን ሁሉንም ነገር ብጥልጥል አድርገው የማየትና የመመርመር ብቸኛ መብት አላቸው። እኛ በምድር ያለን ከአግዜሩ በማይተናነስ ሁኔታ እይታ ካላቸው የጣልያን አውሮፕላን አብራሪዎች አይን መሰወር እንደ ታምር በሚቆጠርበት ጊዜ፣ ትልልቅ የጭነት መኪኖችን ዛፍ ዝንጣፊዎች ሸፋፍኖ ከእይታቸው ውጪ ማድረግ፣ መኪኖቹን ዝም ብሎ ለአርባ ቀን አድላቸው እንደመተው ይቆጠራል።

ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ሊሆን የሚችለው ከስካንዴቪያን አገሮች የአንዷ ሀገር ተወላጅ (በትክክል ከየትኛው ሀገር እንደሆነ ማወቅ አልቻልኩም) የሆነ አንድ ልዑል አውሮፕላን አብራሪ ያደረገውን ማንሳት ይበቃ ይሆናል። ይኼ የንጉሣውያን ቤተሰብ

የሆነ ልዑል ንጉሠ ነገሥቱን በኮረም ለመጎብኘት ይወስንና፣ የግል አውሮፕላኑን ከአዲስ አበባ አስነስቶ ኮረም በሰላም ይገባና፣ አውሮፕላኗን በትላልቅ የዛፍ ቅርንጫፎች ሸፋፍኖ ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ይኼዳል። ታዲያ እነዚያ ሁሌም ሰማዩን ወረውት የሚውሉት የጣልያን አውሮፕላኖች በኮረም የንጉሠ ነገሥቱን ጦር ፍለጋ ሲዞሩ በአንድ ሌሊት በቅላና አድጋ፣ እንዲህ በርካታ ለምለም ቅርንጫፎችን ያፈራች ውብ ዛፍ ሲያዩ በጣም በመገረማቸው፣ በተደጋጋሚ እየዞሩ ይቺን በአንድ ጨረቃ የተፈጠረች ለምለም ዛፍ ሲመረምሩ፣ ዛፏ ዛፍ ሳትሆን አንዲት ትንሽዬ የግል አውሮፕላን መሆኗን በመረዳታቸው በተደጋጋሚ እየዞሩ የእሳት ቦምብ ጭነታቸውን እያወረዱባት የእሳት ራት አደረጓት።

እዚህ ላይ ጣልያኖች ስለ ኢትዮጵያ መልክአ ምድር ከማንም በላይ ጠንቅቀው ያውቃሉ። እናም ያቺ በአንድ ጨረቃ በቅላ ያደገች ዛፍ በቀላሉ በእይታቸው ውስጥ መግባቷ እምብዛም ሊያስደንቀን አይገባም።

ምስኪኑ ልዑል ከአዲስ አበባ እስከ ኮረም ሁለት ሰዓት ያልሞላ ጊዜ ቢፈጅበትም፣ የመልስ ጉዞ ያደረገው ግን ከሳምንት በላይ ነበር። ለዚያውም እድለኛ ነበር። ከአንድ የንጉሠ ነገሥቱ መኳንንት (ከብላቴን ጌታ ህሩይ) ጋር በሰላም በደሴ በኩል አድርጎ ወደ አዲስ አበባ መመለስ ችሏል።

እንግሊዞች የንጉሠ ነገሥቱን ጦር ተከትለው ከደሴ ወደ ኮረም ሲዘልቁ ሁሌም አካሄዳቸው ከጦሩ ኋላ ነበር። እነሆ በማይጨው ጦርነት ተሸንፍንና መሸሽ ግዴታ ሲሆን፣ ይኼው የእንግሊዞቹ የቀይ መስቀል ማህበር ቀኝ ኋላ ዞር እንደተባለ የወታደር ሰልፈኛ የሽሽቱ ቀዳሚው እሱ ነበር።

ምንም እንኳን ወደኋላ ለመመለስ ከንጉሠ ነገሥቱ ፈቃድ ያገኘው ማለዳ ላይ ቢሆንም፣ እነዚያ እርጉም የጣልያን አውሮፕላኖች ከመጨረሻው ሽሽቱ እንዳያስቀሩት ጉዞ የጀመረው ግን ከመሸ በኋላ ነበር።

እንዳልኩት የመልሱን ጉዞ አብረናቸው በመኪና እንድናደርግ ስለፈቀዱልን በመኪና ውስጥ ተቀምጠን ሄድን ይባል ይሆን እንደሆን እንጂ ጉዞው በጣም ቀርፋፋ ነበር። ጉልበቱ ቢኖረኝ በእግሬ ወይም በፈረስ ብሄድ ይሻለኝ ነበር። ይህም የሆነበት ምክንያት በጣም ቀላልና ግልጽ ነው። ጣልያኖች የት እንዳሉ ስለማናውቅ መብራት ማብራት አንችልም። እናም ያው ፊት ቀድሞ የሚሄደውን መኪና ከኋላ ዱካውን እየተከተሉ፣ ጭሱን እየጠጡ ተከታትሎ በጣም በዝግታ መንዝ ግዴታ ነው።

ይቺን አሁን እንዲህ በጨለማና በጣም በዝግታ የምንጓዝባትን የጥርጊያ መንገድ የጉራጌ ልጆች ሰርተው የጨረሷት ከወር በፊት ሲሆን፣ ርዝመቷም ማለት ከደሴ እስከ ኮረም ወደ 250 ኪሎ ሜትር ገደማ ያህል ይሆናል። መንገዷም ያው ጉራጌ የሰራት መንገድ ናት።

በግመል ተጉዞ ለማያውቅ ሰው ጉራጌ በሰራው መንገድ፣ ሱማሌ በሚነዳው መኪና ሂድ ማለት ግፍ ነው። ግን ምን አማራጭ አለ? ፈረስ ቀርቶ አህያ የለኝ። እግሮቼም ቢሆኑ እኔን ተሸክመው መሄድ ከሰገሙ ሰነባብተዋል።

በዚህ መልኩ ስናዘግም አድረን ሊነጋጋ ግድም ላይ ከአንዲት አፋፍ ላይ ደረስን። ከዚች የገደል ጫፍ በታች፣ እታች እቆላው ውስጥ የጨኸኞቹ የራያዎችና የአዘቦች መሬት ተዘርግቷል። እንግዲህ ከዚች የገደል ጫፍ ላይ ወርደን በራያዎች መሬት ላይ ማለፍ ግድ ነው።

እታች እቆላው ውስጥ ራያና አዘቦዎች እንደሚጠብቁን፣ መሬታቸውን ረግጦ ማለፉ ቀላል እንደማይሆን ሁላችንም ብናውቅም፣ አሁን ከዚች የገደል ጫፍ ላይ ወደታች የምንወርድበትን መንገድ ማስላቱ ላይ አተኮርን። የጉራጌ መሃንዲስ መንገዷን ሲቀይስ ምናልባት ለፈረሰኞች፣ ቢበዛ ለቤት መኪኖች እስቦ ሳይሆን አይቀርም እንጂ፣ ይቺ መንገድ ለትላልቅ የጭነት መኪኖች የተሰራች ሆና አልታይ አለችኝ። መንገዷ በጣም ቀጭን ከመሆኗም በላይ አሁንም አሁንም የሚጠማዘዝ፣ ገደል የሚበዛባት ናት። እናም ምናልባት አንዱ ሾፌር ግማሽ ሜትር ቢሳሳት ከነጫነው ጓዝ ገደል መግባቱ የማይቀር ነው።

ይኼንኑ በመፍራት ይመስላል እንዲህ ዓይነት ጠመዝማዛና ቀጫጭን መንገዶች ሲገጥሙን ተሳፋሪዎቹ ወርደን መኪናውን ለሱማሌው ሹፌርና የአርባ ቀን እድሉ የሚሰጥበት አጋጣሚ በጣም ብዙ ነው። የመጀመሪያዋንም የጭነት መኪና በዚች ዓይነት ጠመዝማዛና ቀጭን መንገድ ላይ አጣን።

እዎ እንዳልኩት እንዲህ ዓይነት ጠመዝማዛና ቀጭንና አስቸጋሪ መንገዶች ሲገጥሙን ተሳፋሪዎች ወርደው መኪናው ከጫነው ውድ እቃ ጋር ለሶማሌው ወይም ለህንዱ ሾፌር ይሰጣል። (እዚህ ላይ ሾፌርነት ለኢትዮጵያውያን የተከበረ ሥራ አይመስልም።) ታዲያ ይኼ የሶማሌ ወይም የህንድ ሾፌር ህይወቱን አደጋ ላይ ጥሎ መኪናውን በእዚያች የሞት መንገድ ላይ ለማሳለፍ ይሞክራል። ይኼ አሁን ገደል የገባው መኪና ሱማሌ ሾፌር ለምናልባቱ ብሎ በከፈተው በር በጊዜ ባይዘል ኖሮ አጥንቱም አይገኝም ነበር።

ብዙም ሳንሄድ ሌላ አደጋ ገጠመን። ከፊት ለፊት ይኼድ የነበረው መኪና መንገድ ዘግቶ ቆመ። በዚህ ጊዜ ቀጭኑ፣ ረጅሙና ቀልጣፋው ዶክተር ሜሊ፣

«ምን ተፈጠረ?» እያለ ከኋላ እየሮጠ ወደፊት መጣ።

«ሞተሩ ጠፋ» ሲል የሶማሊው ሾፌር መለሰለት።

«መስራት ይቻላል» አሁንም የሶማሊውን ሾፌር አፍጥጦ እያየ ጠየቀ።

«አላውቅም» ሲል ሾፌሩ ራሱን እየነቀነቀ ሲመልስለት፣

«ጥሩ፣ በዚህ ውድ ጊዜያችንን እናጠፋም። ጠቃሚ እቃዎችን ብቻ አውርዱና ወደ ገደል ወርውሩት» አለና ቀጭን ትዕዛዙን ዶክተሩ አስተላለፈ።

በርካታ ሰዎች ከመኪናው ውስጥ ይጠቅማል የሚሉትን ነገር አውጥተው ከጨረሱ በኋላ እነዚያው ሰዎች ከመኪናው ጀርባ ዞረው ተጋግዘው ወደ ገደል ውስጥ ማሰት። በዚህ መልኩ በጉዟችን ቀጥለን ከራያዎች፣ ከአዘቦች ድንበር ደረስን። የእንግሊዞቹ ቀይ መስቀል አሁንም ገና 14 መኪኖች አሉት።

አሁን ወደ ቆቦ እየተቃረብን ነው። በዚች የራያዎች ግዛት እንኳን የውጭ ዜጎች ቀርቶ ዋናዎቹ የሸዋዎቹ ጦረኞች እንኳን ሳይቀሩ ተንቀጥቅጠው፣ በኃይል ብዛት ተዋግተው ነው የሚያልፉት።

በእንግሊዞቹ ቀይ መስቀል ማህበር መሪ ዶክተር ጆን ሜሊ ጥብቅ ትዕዛዝ ሁላችንም መሳሪያዎቻችንን በተጠንቀቅ ይዘናል። እኔ በተቀመጥኩበት መኪና ጋቢና ውስጥ ለኔና ለሾፌሩ መሳሪያዎቻችንን ማስቀመጫ በቂ ቦታ ሲኖር፣ በሌሎች መኪናዎች ጋቢና ውስጥ ለሶስት ለአራት የተቀመጡት ግን መሳሪያዎቻቸውን በጉልበቶቻቸው መሀል አቁመው መያዝ አለባቸው። እኔ በተሳፈርኩበት የጭነት መኪና ውስጥ ከንጉሠ ነገሥቱ ለቀይ መስቀል ማህበር የታዘዙ (የተሰጡ) በርካታ ታማኝ አጃቢ ኢትዮጵያውያን ወታደሮች ተጨናንቀው ተቀምጠዋል። ጥቂቶቹን በተንቤን አውቃቸዋለሁ፤ እነሱም ደግሞ እኔ የራስ ካሣ ፈረንጅ መሆኔን በደንብ ያውቃሉ።

እንዲህም ሆኖ ከፊታችን በር ዘግቶ የሚጠብቀንን የራያና አዘቦ ጦር ተዋግቶ ለማለፍ መሞከሩ ፈጽሞ የማይታሰብ ጉዳይ ነው። እንደ ኢትዮጵያውያን ውስጥ አዋቂዎች ግምት ከፊታችን በቀላሉ ከ10,000 በላይ የሚሆኑ የራያና አዘቦ ጦረኞች ይጠብቁናል።

ምሳ ሰዓት ግድም ላይ መንገድ ቀዳጁ መኪና ሲቆም ሌሎችም መቆም ጀመሩ። እንደ ሁልጊዜው ሁሉ መኪናው ቀላል ብልሽት ገጥሞት ከሆነ ለተወሰኑ ደቂቃዎች ቆመን መኪናው ተጠጋግኖ በጉዟችን እንቀጥላለን። አሁን ስንቆም ምን እንደገፋፋኝ ሳላውቅ እስቲ እግሮቼን ላፍታታ ብዬ የተበላሸውን የመኪናውን በር በመከራ ታግዬ ከፈትኩና፣ ከመኪናው ውስጥ ወርጄ ጥቂት ርምጃዎች እንደተራመድኩ አንዲት ደረቅ ጥይት ጮኸች። በፍጥነት ወደ መኪናው ብመለስ ከጥቂት ሰከንዶች በፊት ተቀምጬበት የነበረው የመኪናው መቀመጫ በጥይት ተበድሶ አገኘሁት። ምናልባት ከኋላ ከተቀመጡት አጃቢ ወታደሮች አንዱ ባርቆበት ሊሆን ይችላል። የሆነው ሆኖ ከጥቂት ሰከንዶች በፊት በሆነ ምትሃታዊ ኃይል ተገፋፍቼ ከዚያች መኪና ውስጥ ባልወርድ ኖሮ እስከመጨረሻው አንቀላፍቼ ነበር። ብቻ እትሙቼ ያላት ነፍስ ዓይነት ሆኖ በዕድል ተረፍኩ። የሞት ጽዋዬ ገና አልሞላችም ነበር።

በዚህ መልኩ እድሌ አንድ ጨዋታ ካሣየችኝ በኋላና የጣሳ ምግብ ምሳ ከተበላ በኋላ በአዝጋሚው ጉዟችን ቀጠልን። አሁን አንድ ወጣት እንግሊዛዊ እኔ

ሰላምና ጤና ውስጥ ስለገባ ሶስት ሆነናል፡፡ ይኼ ወጣት በተጎዳበት መኪና ጋቢና ውስጥ ስለገባ ሶስት ሆነናል፡፡ ብቻ ይኼ ወጣት እንግሊዛዊ እንግሊዛዊ ክብረስቶል አካባቢ ነው የመጣው፡፡ ብቻ ይኼ ወጣት እንግሊዛዊ ጨዋታ አመጣና ስለ ሆላንዶቹ ዶክተሮች ገጠመኝ ያወጋኝ ጀመር፡፡

ወደ ስሜን ጦር ግንባር እንዲሄድ የታዘዘውና ምንጊዜም በሰሜኑ የጦር ግንባር ያልደረሰው የሆላንዶቹ የቀይ መስቀል ማህበር እድል እጣ ፈንታ በጣሙን የሚገርም ነው፡፡

ምንም እንኳን የሆላንዶቹ የቀይ መስቀል ማህበር በጥሩ ሁኔታ የተደራጀ፣ በርካታ ዘመናዊ መኪኖች፣ የህክምና መሳሪያዎችና መድሃኒቶች ከበርካታ ዶክተሮችና አስታማሚዎች ጋር ያሉት ቢሆንም፣ ያለምንም ስራ ከአሉጋ ወራሽ ጋር በደሴ ተቀምጦ ወርቅ ጊዜውን በከንቱ አሳለፈ፡፡

ለዚህም መሰለኝ በደሴ ያለምንም ሥራ የተቀመጠው የሆላንዶች ቀይ መስቀል ማህበር መሪ ቢያንስ በበርካታ የጭነት ከብቶች መድሃኒቶችን አስጭኖ ከሁለት ዶክተሮች ጋር በሰሜኑ የጦር ግንባር ለሚፋለመው የራስ ካሣ ጦር የተላከው፡፡ እነዚህን ሁለት ዶክተሮችና ጭነቶቻቸውንም 50 የሚሆኑ ታጣቂ የደሴ ልጆች አጅበዋቸው ነበር፡፡

አሁን በምናልፍበት መንገድ ማለት በዋድላና በቆቦ መካከል እነዚህን ሁለት ዶክተሮችና አጃቢዎቻቸውን የደሴ ልጆች፣ ዘመናዊውን የጣልያን መሳሪያ የታጠቁ አዘቦዎች ያገኟቸውና ጦርነት ይገጥሟቸዋል፡፡ 50ዎቹ ታጣቂ የደሴ ልጆች ከአዘቦዎች ጋር ጦርነት ገጥመው ወደመረታቱ ሲቃረቡ ይሸሻሉ፡፡

በሽሽቱ አንዱ ዶክተርና ጥቂት ታጣቂ የደሴ ልጆች ነፍሳቸውን ሲያተርፉ ሌሎቹ እስከመጨረሻው ተዋግተው ወደቁ፡፡ ሁለተኛው ዶክተር በሁለት የአዘቦዎች ጥይት ተመትቶ እየተንፏቀቀ ወደ ቁጥቋጦዎች ውስጥ ገብቶ ለመሰወር ቢሞክርም፣ የጊዜ ጉዳይ ይሁን እንጂ አዘቦዎቹ እንደሚያገኙት ርግጠኛ ነበር፡፡ በተለይ ቆስለው የወደቁትን አጃቢዎቹን የደሴ ልጆች በወደቁበት አንገታቸውን በካራ እያረዱ ብልቶቻውን ሲቆርጡ ባየ ጊዜ ሞት እይቀሬ መሆኑን አውቆ፣ ሽጉጡን ሊጠጣ ቢፈልግ ሽጉጡን ተመትቶ በወደቀበት ቦታ ላይ እንደጣለው ስለተረዳ አይቀሬውን ሞት መጠበቁን ተያያዘው፡፡ ብዙም ሳይቆይ አዘቦዎቹ ዶክተሩን አገኙት፡፡ ግን በዚያ ወሊጋዳ ካራቸው አንገቱን አርደው አላገደሉትም፡፡ ብልቱንም አልነኩበትም፡፡ ብቻ ለራሱም ግር በሚያሰኝ ሁኔታ በተራ ቃሬዛ ተሸክመው ወደ ሰፈራቸው ወስደው ቁስሉን አከሙው፣ እስኪጠግብ አብልተውና አጠጥተው፣ ከቁስሉ አገገሞ ትንሽ ጠንከር ሲል በቃሬዛ ተሸክመው የኢትዮጵያ ወታደሮች ጠዋት በተከከሉ ሊያገኙት በሚችሉበት ቦታ ላይ በሌሊት ወስደው በቃሬዛው ላይ አስተኝተው ጥለውት ሄዱ፡፡

ወጣቱ እንግሊዛዊ ይኼንን አስደናቂ ታሪክ ገና ሳይጨርስ ሶማሌው ሾፌራችን የመኪናው ማቆሚያ በድንገት ረግጦ ቆምን፡፡ እስካሁን ከፊት ይኼዱ የነበሩት ሶስቱም መኪኖች ቆመዋል፡፡ ከኋላ የሚከተሉንም በየተራ እየመጡ ተደርድረን ቆምን፡፡

በርካታ ፈረንጆች መሳሪያዎቻቸውን በተጠንቀቅ እንደያዙ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ይከራከራሉ፡፡ ኢትዮጵያውያን አጃቢ ወታደሮቻችንንም እየተጠራሩ በቡድን በቡድን እየሆኑ ይመክራሉ፡፡

«ምን ተፈጠረ?» ሁሉም የሚያነሳው ጥያቄ ነበር፡፡

በንጉሡ ትእዛዝ በራሳቸው የእንግሊዙን ቀይ መስቀል ማህበር መንገድ እንዲመራና በታጣቂ ወታደሮቹ ከአደጋ እንዲጠብቅ ጥብቅ ትዕዛዝ ተሰጥቶት የተሾመው ጊማሙ የኮረሙ ቀኛዝማች፣ ከፊት ለፊታችን ከተዘረጋው ሜዳ ማዶ ላይ ወዳለው ጫካ መሳይ ቁጥቋጦ በእጁ እያሳየ፣

ናአዘቦ! ራያን! አለ፣ ቀኛዝማቹ እነዚህን ሁለት ቃላት ሲናገር ከሁኔታው በቃላት ልገልጸው የማልችለው ጥላቻ በገጽታው ላይ ይታይበታል፡፡ በአንዲት ቃል፣ በአንዲት የኮረሙ ቀኛዝማች ቃል፣ ሁላችንም ከፊት ለፊታችን ታግለን የማንወጣው አደጋ እንደሚጠብቀን ተረዳን፣ ተገነዘብን፡፡ እኔ፣ ለሰው ሀገር ሰው «ራያ! ወይም አዘቦ!» የነዚህ ሁለት ጎሳዎች ልዩነትም ሆነ አንድነት ግልጽ ብሎ ባይታየኝም፣ ሁለቱም ግን አደጋዎች፣ ለዚያውም ከአደጋዎች ሁሉ የከፉ አደጋዎች መሆናቸውን አሳምሬ አውቃለሁ፡፡

እነዚህን ራያዎችና አዘቦዎች የትግራይ፣ የጎንደር፣ የዋግ፣ የጎጃም፣ የወሎና የሸዋ ሰዎች «አረመኔዎች» ይሏቸዋል፡፡ ምናልባትም እንዲህ በአንድነት «አረመኔዎች» ናቸው ብለው ሲሏቸው፣ የራሳቸው የሆነ ምክንያት ሊኖራቸው ይችላል፡፡ በማይጨው ጦርነት በዚያች ቀውጢ ሰዓት በሰሩት ስራ ግን እኔም «አረመኔዎች» ናቸው ከማለት ወደኋላ አልልም፡፡

ምንም እንኳ አዘቦዎች በቁጥቋጦዎች ውስጥ በደንብ ተደብቀው ቢመሸጉም ለጦረኛው ለኮረሙ ቀኛዝማች አይን ግን መሰወር አልተቻላቸውም ነበር፡፡ "ናአዘቦዎች መጥፎ ሃሳብ ባይኖራቸው ኖሮ አይደበቁም ነበር" እያለ የኮረሙ ቀኛዝማች ወደፊት እንዳንሄድ አገደን፡፡

አዘቦዎቹም እንዳያናቸው ገባቸው መሰለኝ፣ ቀስ በቀስ፣ ደረጃ በደረጃ ከተደበቁበት ቁጥቋጦ ውስጥ እየወጡ በሜዳው ላይ ተደርድረው "ወንድ የሆንሽ ጨጋ በይ" በሚል ጎይላ በንቀት ያመለክቱን ጀምር፡፡ አብዛኛዎቹ ዘመናዊ የሚባለውን የጣልያን መሳሪያ ታጥቀዋል፡፡ ረጃጅም ጦር የያዙትም አሉ ገድለው መሳሪያዎቻችንን ሊታጠቁ ሳይቆርጡ አይቀርም፡፡ ብቻ ተፋጠናል፡፡

በመኪኖች መካከል እየተዘዋወረ ለውጊያ ብቁ የሆኑ ሰዎችን ሲሰበስብ የቆየው ዶክተር ሜሊ "በሉ ቦታ ቦታዎቻችሁን ያዙ" ሲል ቆራጥ መመሪያ አስተላለፈ። ሁላችንም ጠመንጃችንን አቀባብለንና ወድረን ለመከላከል ይመቻል የምንለውን ቦታ ይዘን፣ በተጠንቀቅ በቆምንበት ሰዓት፣ ካፒቴን ስሚዝ እንደ ሁልጊዜው በግዴለሽነት ጠመንጃውን ዘቅዝቆ እንደያዘ በግራ እጁ የጨበጣትን ያለቀች የውስኪ ጠርሙስ አንጠፍጥፎ ከተጎነጨ በኋላ ባዶዋን ጠርሙስ ወረወራት። ከዚያም ከመኪናው ውስጥ አዲስ የውስኪ ጠርሙስ አውጥቶ፣ ቡሹን በጥርሱ ከፍቶ ከወረወረ በኋላ በረጅሙ አንዴ ተጎንጭቶ መንገዱን በቀጥታ ወደ አዘቦቹ አቀና።

ይኼ ጀብደኛ ሰው፣ ካፒቴን ስሚዝ፣ በቀኝ እጁ ጠብመንጃውን ዘቅዝቆ እንደያዘ በግራ እጁ ከጨበጣት የውስኪ ጠርሙስ ደጋግሞ ከተጎነጨ በኋላ "እስቲ ምን እንደሚፈልጉ እንጠይቃቸው" ብሎ በቀጥታ ወደ አዘቦቹ ሲሄድ፣ ጢማሙ የኮረሙ ቀኛዝማች፣ "እባክህ ልጄ፣ ይኼን ጂል ፈረንጅ ቁም በለው" አሉኝ።

በኮረሙ ቀኛዝማች አነጋገር የሳቅሁትን ያህል ስቄ ይኼ "ጅል ፈረንጅ" እንዲቆም ባፏጭለትም፣ ወደ ኋላ እንኳን ለመዞር ሳይሞክር ውስኪ የጨበጠቸውን ግራ እጁን ብቻ ወደላይ አንስቶ "አይዞን" ዓይነት ነገር ምልክት ሰጥቶኝ በጉዞው ቀጠለ።

ካፒቴን ስሚዝ ወደ አዘቦች እየቀረበ ቢሄድም አዘቦች ምንም ዓይነት የጠብ ምልክት አላሳዩትም። አንዲት ጥይት ሳትጮኽበት ጀብደኛው ካፒቴን ወደ አዘቦች ሰፈር ተቃረበ። አዘቦች ይኼን ጀብደኛ ሰው ሊገድሉት ቢፈልጉ ኖሮ ገና ዱሮ በሩምታ ተኩስ ብትንትኑን ባወጡት ነበር። ግን አንዲት ጥይት ሳይተኩሱበት በሰላም ከመሃላቸው እስኪያስገቡት ድረስ አፍጥጠንና ትንፋሻችንን ውጠን ተከተልነው፣ በአይናችን።

ብዙም ሳይቆይ ጀብደኛው ካፒቴን ስሚዝ እንደ አካሄዱ በቀኝ እጁ ጠብመንጃውን ዘቅዝቆ እንደያዘ፣ በግራ እጁ አሁን እያለቀች ያለቺውን ውስኪውን አሁንም አሁንም እየተጎነጨ፣ በሄደበት ፍጥነት ተመልሶ መጣ። የሁላችንም ጥያቄ የነበረውን ጥያቄ "ምን አሉህ?" ብሎ ዶክተር ሜሊ በጉጉት ጠየቀው። አሁን ካፒቴን ስሚዝ ጠርሙሷን በንዴት ወርውሮ ሌላ አዲስ ጠርሙስ ከመኪናው ውስጥ አውጥቶ ሊከፍታት እንኳን ሳይሞክር "ፈረንጆች ከነመኪኖቻቸው፣ ከነንብረታቸው ማለፍ ይችላሉ። የሸዋ ወታደሮች ግን አንዱም ማለፍ አይችልም!" ብለዋል፤ አለና ያቺን ሙሉ የውስኪ ጠርሙስ ወርውሮ ከአለቱ ጋር ሊከሰክሳት ካሰበ በኋላ መልሶ በጥርሱ ቡሿን ከፍቶ ባፉ ወረወራት። ቀጥሎም አንድ ጊዜ በረጅም ተጎንጭቶ ጠርሙሷን ለኔ አቀበለኝ።

እኔም የቻልኩትን ያህል ተጎንጭቼ ስለ አዘቦች፣ በተለይ ራያዎች፣ በሸዋ ሰው ላይ ስላላቸው ጥላቻ ወደ ማሰላሰሉ ገባሁ። የሸዋ ልጆች በአመሃኙ ኦሮሞዎችና

አማራዎች ናቸው። ራያዎችም በዘር ኦሮሞዎች ናቸው ይባላል። ታዲያ በዘር አንድ ከሆኑ ይኼን የመሰለ ጥላቻ በመካከላቸው እንደምን ሊፈጠር ቻለ?

ወደ ደብረ ታቦር ከመብረሬ በፊት አንድ ስለኢትዮጵያ ውስጥ አዋቂ የታሪክ ተመራማሪ ፈረንጅ፣ በአዚያች የግሪክ ቡና ቤት ውስጥ ተቀምጠን የዚያን የግሪኩን የውሸት ውስኪ ስንጠጣ እንደቀልድ ያለኝ ነገር ትዝ አለኝ።

"የምኒልክ ልጆች (የሸዋ ልጆችን ማለቱ መሰለኝ) ወደር የማይገኝላቸው ተዋጊዎች ናቸው። ግን ጥሩ ህዝብ አስተዳዳሪዎች አይደሉም" ነበር ያለኝ።

ይኼ ሁሉ ጥላቻና ቂም በቀል ከአስተዳደር ጉድለት የመጣ ይሆን? እኔ እንዲህ በሀሳብ ርቄ ስሄድ፣ ዶክተር ሜሊ ንጉሠ ነገሥቱ እንዲያጅቡት በኮረሙ ቀኛዝማች አዛዥነት የሰጡትን ጦር እዚህ ለአዘቦች ጠመንጃ ኢላማ መምቻ እንዲሆኑ በትኖ መሄዱ ክብዶት ለመወሰን ተቸግሮ አስር ጊዜ ፀጉሩን እንደመንጨት እያለ ሲንቆራጠጥና ሲጨነቅ፣ "አይዞን ዶክተር፣ አንተ ሰዎችህን ይዘህ ሃሳባቸውን ሳይቀይሩ በፊት ሂድ። እኔ ከነዚህ ምስኪኖች ጋር እቆያለሁ። እስከ ነገ ጠንክረን ከቆየን ምናልባት ቀዳሚው የንጉሠ ነገሥቱ ጦር ይደርስልናል ወዘተ" እያልኩ ላግባባውና አዘቦቹ በከፈቱለት በር ቢያንስ በሃላፊነት ያመጣቸውን ሰዎቹን በሰላም ይዞ እንዲያልፍ አደፋፈርኩት።

የኔን ከኮረሙ ቀኛዝማች ወታደሮች ጋር የአርባ ቀን እድላቸውን ለመካፈል መወሰኔን የሰማው እብዱ፣ ጀብደኛው ካፒቴን ያችኑ የውስኪ ጠርሙሱን እንደጨበጠ እኔ ተደግፌአት ወደነበረች ቋጥኝ መጣ።

"ካፒቴን ጋርለሳክ! እባክህ ከዚህ እብደትህ ጋር አብሬህ እንድሞት ፍቀድልኝ?" ብሎ በሳቅ ፈረሰና ቀጥሎ፣ "ታውቃለህ ካፒቴን? በዚህ ምድር ላይ ከኔ በላይ እብድ ያለ አይመስለኝም ነበር። በርግጥም የለም። ግን አንተ ወንድሜ እየደረስክብኝ ነው" እያለ ቀይቶ፣ "እኔም ከካፒቴን ጋርለሳክ ጋር እቀራለሁ" አለ።

የዚህ እብድ ሰው ከኔ ጋር በዚች የቀበ ድንበር ላይ መቅረት ባይገርመኝም "ለመሆኑ በምን ቋንቋ ተግባባችሁ?" ስል ከአዘቦች ጋር በምን እንደተግባባና እንደተደራደረ ጠየኩት። አሁንም ያቺን ውስኪውን ሁለት ጊዜ በረጅሙ ከተጎነጨና ውስኪው ያረደውን ጉሮሮውን እንደመሞረድ እያደረገና ጠርሙሷን ለኔ እያቀበለ "በአንድ ወቅት እዚህ ነበርኩ" አለኝ።

ምንም እንኳን ይኼ እብድ ካፒቴን ስሚትህ ከኔ ጋር አብሮ ለመቅረት ቢወስንም፣ አንተ ካልሄድክና መንገዱን ካላስከፈትክልን አንዳችንም አንሄድም ስላሉት፣ "አዝናለሁ ካፒቴን ጋርለሳክ! ካንተ ጋር መሞት ክብር ነበር" እያለ እየተለደብኝ እሱ ከመኪኖቹ ፊት ቀድሞ እንደ ሁልጊዜ ሁሉ ጠመንጃውን በቀኝ እጁ

ዘቅዝቆ ይዞ፣ ከግራ እኛ ሁሌም የማትለየውን የውስኪ ጠርሙስ እሁንም እሁንም እየጎመ ቀጥ ብሎ ወደ አዘቦዎች ሄደ።

እኛም እርሳችን ፈነክና አልጨክንንችብንም። የተቀራረጡ ጦረኞች ቀስ በቀስ መጠራቀቀም ሲጀምሩና ኃይላችን እየተበራታ ሲመጣ አዘቦዎች የዘኑትን በር ከፍተው ተበታተኑ። እኛ የአዘቦዎችን መሬት ስንሸገር የነዶክተር ሜሊ መኪኖች ገና ዱሮ ደሴ ገብተው ነበር።

የአዲስ አበባ ወሬኞች ስለ ካፒቴን ስሚዝ ብዙ ብዙ ሲያወሩ ሰምቡተዋል። እርግጠኛ ነኝ ይኼ ጀብደኛ ሰው በሁለቱ የተንበጌን ጦርነቶች የመሳተፍ እድል ቢኖረው ኖሮ፣ ታሪክ ሲጽፈው የሚገባ ጀብድ በሰራ ነበር። ግን እኛ በተንቤን የጦር እውድማዎች ስንዋጋ፣ እሱ በደሴ ድኳን ከብተኛዋ ጓደኛው ከውስኪዋ ጠርሙስ ጋር እለሙን ይቆጭ ነበር።

የአዲስ አበባ ወሬኞች ስለዚህ እንግሊዛዊ ካፒቴን ሳይሆን ስለ ልጅም ጦር በሰሩው ብዙ ብዙ እያጋነኑ ያወሩ ነበር። እነዚህ የአዲስ አበባ (የሸገር) ወሬኞች ልጅ ሙሪም ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር እደተገናኙና በሰሜኑ የጦር ግንባር ስላሳየው ወደር የማይገኝለት ጀግንነት የደጃዝማችነት ማዕረግ ስጡት፣ ሾሙት፣ ሸለሙት፣ እንደ ልጃቸው አቅፈው ሳሙት፣ እያሉ አይን ያወጣ የውሸት ወሬ ሲያወሩ ተሰምተዋል።

ርግጥ ንጉሠ ነገሥቱ ለልጁ ያላቸውን አድናቆት በኛ በሰው ሀገር ሰዎች ፊት እንኳን ሳይደብቁ ተናግረዋል። ከዚያም አልፈው "ይቺ አንድ ፍሬ ደጃዝማች ከእኛም በላይ ጀብዱ እየሰራች እንደሆነ እንሰማለን" ብለው በኔ ፊት ተናግረዋል።

ግን ንጉሠ ነገሥቱ እንኳን አቅፈው እንደ ወለዱት ልጃቸው ሊስሙት ቀርቶ ትከለኛ በሙ እንኳን ማን እንደሆነ ማምቱም የላቸውም። ለነገሩ ምናልባት ደጃዝማች አበራ ካሣ ያውቅ እንደሆነ እንጂ ሌላ የሚያውቅ ማንም ትልቅ ሹም የለም። የሆነው ሆኖ ትልቁ ቁም ነገር ሁላችንም በዚህ መልኩ የራያና የአዘቦዎችን መሬት ተሻግረን በሰላም አዲስ አበባ ገብተናል።

35

ተስፋ ቢስ ቀኖች፣ የግዳጅ ፍጻሜ

በማይጨው ስለደረሰብን ሽንፈት አዲስ አበባ ውስጥ መጀመሪያ የተረዳው ሰው የአዲስ አበባው ቴሌግራፊስት ነበር። አዎ የአዲስ አበባው ቴሌግራፊስት በተለመደው ሰዓት ከኛ ጋር ለመገናኘት ቢሞክርም የኛ ራዲዮ ደንቁሮ ነበር። እናም ያ ቆፍጣና ወጣት ቴሌግራፊስት በማይጨው የደረሰብንን ሽንፈት ለመረዳት ጊዜ አልፈጀበትም። የራስ ካሣ ጦር በተንቤን ሲሸነፍ የራስ ካሣም ራዲዮ ደንቁሮ ስለነበር፣ ያ ልጅ በማይጨው መሸነፋችንን ተረድቶት ነበር።

ከዚህ በተጨማሪ ከማይጨው ጦርነት ሽንፈት በኋላ ጃንሆይ አንድ የመጨረሻ ቴሌግራም ለእቴጌ መነን አስተላልፈው ነበር። በቴሌግራፋቸው መልክት፣ "የኛ ጀግኖቹና ታማኞቹ ወታደሮች በማይጨው የጦር እውድማ ወድቀዋል። ጀግኖቹን የመቅበሪያም ጊዜ አልነበረንም። የተረፉትም በአብዛኛው ቆስለዋል።" በዚች የጃንሆይ ቴሌግራፍ እቴጌ መነን የኢትዮጵያው ሰራዊት በማይጨው መሸነፉንና መረታቱን አውቀው ለወትቱ የአዲስ አበባው መሪ፣ ለሽማግሌው የጃንሆይ የውጪ ጉዳይ ምኒስትር ለብላቴን ጌታ ህሩይ ሳያስታውቁ አልቀሩም መሰል፣ ብላቴን ጌታ ህሩይ አዲስ አበባ አደጋ ላይ እየወደቀች እንደሆነች ተረድተው፣ በጦር ግንባር ካልተሰለፉት

ምኒስትሮቻቸው ጋር ሌሊቱን ሲመክሩ አድረው፣ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ ከአዲስ አበባ ወደ ነቀምቴ እንዲዛወር አደረጉ። አሁን የኢትዮጵያ ዋና ከተማ ነቀምት ናት።

ብላቴን ጌታ ህሩይን የኢትዮጵያን ዋና ከተማ ወደ ነቀምቴ እንዲያዛውሩ ያስገደዳቸው ምክንያት በማይጨው በኢትዮጵያው ሰራዊት ላይ ስለደረሰው ሽንፈት ያገኙት የተቆራረጠ ወሬ ብቻ ሳይሆን፣ ሰሞኑን በአዲስ አበባ አናት ላይ የሚያንገርበሱት የጣልያን የስለላ አውሮፕላኖች ቁጥር ከፍ መሆኑን እሳምኗቸው ነው። የኢትዮጵያ ዋና ከተማ ውሎ ሳያድር ወደ ነቀምቴ እንዲዛወር ወስነው፣ በጦር ሜዳ ካልዋሉ ምኒስትሮቻቸው ጋር ለነቀምቴው ጉዞ ዝግጅት ጀመሩ።

አዎ እንዲህ አዲስ አበባ አናት ላይ ቁጥራቸው በርከት ያሉ የስለላ አውሮፕላኖች ብቅ ባሉ ቁጥር የአዲስ አበባ ነዋሪዎች መላ ቅጡ በጠፋ ሁኔታ ተደናግጠው በየባህር ዛፉ ውስጥ ገብተው ሲደበቁ ሲሸሸጉ፣ የውጭ ዜጎች በየኤንባሲው ውስጥ ቀድመው በተገነቡ ከአውሮፕላን ቦምብ ፍንዳታ መከላከያ ጉድጓዶች ውስጥ ይገቡ ነበር። የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ስለጦርነቱ አስከፊነት ቅንጣት ያህል ግንዛቤ ያላቸው አይመስልም። ግንዛቤው ቢኖራቸው ኖሮ ከነዚያ የተረገሙ አውሮፕላኖች፣ ጀግናውን የኢትዮጵያ ወታደር በመሽገበት ዋሻ ገደል ንደው ከነህይወቱ ከቀበሩ ርጉሞች፣ በባህር ዛፍ ጫካ ውስጥ ገብቶ መሸሸጉ ምንም ፋይዳ የሌለው ነገር መሆኑን በተረዱት፣ በተገነዘቡት ነበር።

የውጭ ዜጎች ኤንባሲዎች በግቢዎቻቸው ውስጥ ባስቆፈሯቸው ከአየር ድብደባ መከላከያ ጉድጓዶች ውስጥ ለመግባት ሲራወጡ ስለጦርነቱ አስከፊነት ቢያንስ በመጠኑም ቢሆን የተረዱ ይመስላሉ። ይኼ ጭንቀትና ፍርሃት ግን ዋጋ ቢስ ነበር። እንዲህ በርከት ብለው በአዲስ አበባ አናት ላይ የሚያንገርብቡት አውሮፕላኖች በአዲስ አበባ ከተማ ላይ በቦምብ ምትክ ወረቀቶች ብቻ ነበር የበተኑት። እንዲህ ቀኑን ሙሉ የጣልያን አውሮፕላኖች አዲስ አበባን እየዞሩ የጣልያን ባንዲራዎችንና በአማርኛ የተፃፉ በራሪ ወረቀቶችን ሲበትኑ፣ በየባህር ዛፉ ጫካ ውስጥ ገብቶ በፍርሃት ሲንቀጠቀጥ የዋለው ሰው ወደየጎጆው መመለስ ጀመረ። ማርሻል ባዶሊዮ በበራሪ ወረቀቶቹ ለአዲስ አበባ ህዝብ እንዲህ ሲል የሰላም ጥሪውን አስተላልፏል።

"የኢትዮጵያ ወታደሮች በአሸንጌ ሐይቅ ዙሪያ በተለይም በማይጨው እንዳይሆን ሆነው ስለተሸነፉ አዲስ አበባን ያለምንም ደም መፋሰስ እንዲያስረክቡና፣ ይኼንን የሰላም ጥሪ ተቀብለው በትላልቅ ህንጻዎች አናት ላይ ባለ ሶስቱን ቀለም የጣልያን ባንዲራ እንዲሰቅሉ ያዛል።"

መጋቢት 16 ቀን በአዲስ አበባ ነዋሪዎች መካከል በሰፊው ይወሩ ከነበሩት ትኩስ ወሬዎች መካከል "ጣልያኖች ሶስት ቀን ባልሞላ ጊዜው ውስጥ አዲስ አበባ ይገባሉ" የምትለዋ ወሬ ትገኝበት ነበር። ምንም እንኳን ይቺ ወሬ የጣልያን ሰላዮችና አዋሻኪዎች እጅ እንዳለባት ቢታወቅም፣ የጣልያኑ ጦር ከአዲስ አበባ ርቆ ያለና ሌት

ተቀን መንገድ እያሰራ ስለሆነ፣ በሶስት ቀን ውስጥ እንኳን ባይሆን በቅርቡ አዲስ አበባ መድረሳቸው ጥርጥር የለውም።

ይቺን የሶስት ቀኗን ወሬ አብዛኞዎቹ የአዲስ አበባ ሰዎች አላመኗትም ነበር። በተለይም የአምባላጌን ተራራማ መንገድ አስቸጋሪነት አሳምረው የሚያውቁት ሰዎች ሽንጣቸውን ገትረው "ሊሆን አይችልም" ሲሉ ተከራከሩ። እነዚህ ሰዎች ያላወቁትና ያልተገለጠላቸው ነገር ቢኖር ጣልያኖቹ አስቸጋሪውን የአምባላጌን ተራራ በድማሚት እያፈረሱና እየናዱ መንገድ (ጥርጊያ መንገድ) እየሰሩ በፍጥነት መጓዝ መጀመራቸውን ነበር። በኋላ ላይ አልጋ ወራሹ ከጥቂት ወታደሮች ጋር ከደሴ ተመልሰው አዲስ አበባ ሲገቡ ሁሉም ሊሆን ይችላል ሲሉ አመኑ።

በነዚህ በማይታመኑ ቀኖች ማናቸውም የአዲስ አበባ ሰው የኢትዮጵያው ንጉሥ የት እንዳሉ እንኳን አያውቅም ነበር። እና ሁሉም፣ በተለይም ወሬኞች፣ ስለጃንሆይ የአርባ ቀን እድል እየፈጠሩ ሲያወሩና ሲተነብዩ፣ የአዲስ አበባ ህዝብ መላው ጠፍቶት ሲጨነቅና ሲጠበብ፣ ቀድመው ከጦር ሜዳ የተመለሱ ወታደሮች የተለያዩ የስማ በለው አይነት ወሬዎች ይዘው አዲስ አበባ ገቡ።

ከነዚህ ከጦር ሜዳ ከተመለሱ ወታደሮች መካከል አንዳንዶቹ "ጃንሆይ ጦራቸውን እየመሩ የአሸንጌን ሐይቅ ሲሻገሩ በራያ ሽፍቶች ጥቃት ደርሶባቸው ጦራቸው ከፍተኛ ጉዳት ደርሶበት፣ እሳቸውም በአሸንጌ ሐይቅ ወድቀዋል" ሲሉ፣ ሌሎች ደግሞ "ጃንሆይ በራያ ሽፍቶች ጥይት ተመተው ሲወድቁ በአይኔ በብረቱ አይቻለሁ" እያሉ ምስክርነታቸውን በመስጠታቸው አዲስ አበባ አሁን ሌላ አደጋ ላይ ለመውደቅ ተቃረበች።

በሰሜኑ የጦር ግንባር የጠላትን ጦር ገጥመው ሲዋጉ፣ ሲመክቱና ሲከላከሉ ቆይተው በማይጨው ጦርነት ድል ተመተው፣ ደህይተውና ተርበው ወደ ትውልድ አገራቸውና መንደራቸው የሚመለሱት እነዚህ ጀግኖች አዲስ አበባ ሲገቡ፣ አዲስ አበባዎች በወጉ እንደጀግና ከመቀበል ይልቅ እንደቀማኛና ሌባ ይቆጥሯቸው ጀመር። በዚህም ምክንያት እነዚህ ረሀብ ያንገላታቸውና የሽሽት ሩጫ ክፉኛ የጎዳቸው አንበሶች ቁጡዎችና ብስጩዎች መሆን ጀምረዋል። ይኼም አዲስ አበባን ለሌላ አደጋ እየጋበዛት፣ እየገፋፋት ነው።

አዲስ አበባ በዚህ መልኩ አደጋ አርግዛ ቀኗን ስትጠብቅ በርካታ ንዝ የተጫኑ አህዮችና አጋሰሶች ወደ ነቀምቴ መንገድ ጀመሩ። ይኼ ማለት ደግሞ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ በትክክል ወደ ነቀምቴ እየተሸጋገረች ነው ማለት ነው።

በርካታ አውሮፓውያን ገና ጦርነቱ ሊጀመር ግድም በጊዜ ወደሀገራቸው ሄደዋል። ወደ አገራቸው ያልሄዱት ጅቡቲ ተቀምጠው የሚሆነውን እየጠበቁ ናቸው። ሚያዝያ 18 እና ሚያዝያ 19 ቀን "ጣልያኖች በሶስት ቀን አዲሳባን እንደሚይዙ እርግጠኛ ነው" እየተባለ በሰፊው ስለተወራ፣ በአዲስ አበባ ያሉ በርካታ የውጭ ሀገር

ቤተሰቦቻቸውን ጥለው በባቡር እንደክብት ቤቶች ግዛቸውን እንኳን በቅጡ ሳይቋጥሩ፣ ኮተታቸውን ጥለው በባቡር እንደክብት ቤቶች ግዛቸውን እንኳን በቅጡ ሳይቋጥሩ፣ ከሚፈረጥጡት አመዛኞቹ እየተጎዱ ወደ ጅቡቲ ፈረጠጡ። እንዲህ አግሬን አውጪኝ ከሚፈረጥጡት አመዛኞቹ ለጃንሆይ ወታደር ያሰለጥኑ የነበሩ መኰንኖች ነበሩ። እነዚህ መኰንኖች በንጉሠ ነገሥቱ ቤተ መንግሥት ከፍተኛ ገንዘብ እየተከፈላቸው የንጉሠ ነገሥቱን ጦር ሲያሰለጥኑ ለረጅም አመታት በኢትዮጵያ በተድላ ቢኖሩም፣ ጦርነቱ ሲጀመር ግን እግራቸውን ከአዲስ አበባ አላነሱም ነበር። እንዲህ የቁርጧ ቀን ስትቃረብ ግን እግሬን አውጪኝ ወደ ጅቡቲ ፈረጠጡ።

የንጉሠ ነገሥቱን ጦር ሲያሰለጥኑ እስከ መጨረሻው ቀን ድረስ ከሥራ ገበታቸው ላይ ሳይነሱ የመጣው ይምጣ ብለው በአዲስ አበባ የቀሩ ቢኖሩ የስዊድን ተወላጅ መኰንኖች ብቻ ነበሩ። የመጣው ይመጣል፤ ያበጠው ይፈነዳል እንጂ፣ ከኢትዮጵያ አንወጣም! ያሉ የውጭ ዜጎች የተለያዩ አገሮች ኤንባሲዎች ያቀረቡላቸውን ጊዜያዊ መጠለያ ተቀብለው፣ ከአራዳ ወጥተው፣ በየኤንባሲው ጓሮ የድንኳን ከተማ ከትመው ተቀመጡ። እዎ ኤንባሲዎች በአብዛኛው በትላልቅ የድንጋይ ግንቦች ከመገንባታቸውም በላይ በበርካታ ታጣቂዎች ሌት ተቀን ይጠበቁ ነበር።

በፈረንሳይ ኤንባሲ ከፈረንሳውያን በተጨማሪ ቼኮዝሎቫኮች፣ ፖላንዶች፣ ሩሲያውያን፣ ግሪኮችና የሌሎችም ሀገር ዜጎች ስደት ገብተው፣ ያንን በአበባ ያጌጠና የተሽቆጠቆጠ ግቢ ወደትልቅ የድንኳን ከተማነት ለወጡት። ይቺ በፈረንሳይ ኤንባሲ ግቢ የተከተመች የስደት የድንኳን ከተማ ምናልባት ጣልያኖች አዲስ አበባ ቢገቡና ጥቃት ለመሰንዘር ቢሞክሩ፣ ይኼን መሰሉን ጥቃት ለመከላከል ከተሰለፉት አልሞ ተኳሽ የሴኔጋል ወታደሮች በተጨማሪ በድንኳን ከተማ በስደት የሚኖሩት ወንድ ሴት ሳይባል ከኤንባሲው መሳሪያ ታድሏቸው ሁሉም በተጠንቀቅ ቆመዋል። ይቺ በኤንባሲዋ ግቢ ውስጥ ያለች ትንሽ ጦር በመጠኑም ቢሆን አለማቀፋዊነት ያላት ጦር ትመስል ነበር።

የጣልያን ጦር እንደተወራለት በሶስት ቀን አዲስ አበባ ባይገባም፣ አዲስ አበባ አፋፍ ላይ ግን ደርሶ ነበር። አዲስ አበባን ቀድሞ ሄዶ እንዲይዝ የታዘዘው የጣልያን ጦር ከደሴ የተነሳው ሚያዝያ 24 ቀን ነበር። አራት ቀን ቀደም ብሎ ሚያዝያ 20 ቀን ማርሻል ባዶሊዮ ዋና የጦር መምሪያውን ከመቀሌ ነቅሎ ደሴ ከተከለና ከሰፈረ ከአራት ቀን በኋላ፤ ክፍለ ጦሩን አዲስ አበባን እንዲይዝ አዘዞ ላከው።

እንዲህ የጣልያኑ ጦር ያሰበዉ ከልካይና አጋጅ አዲስ አበባን ለመያዝ እየገሰገሰ ወደአዲስ አበባ ሲቃረብ፣ ቢያንስ አዲስ አበባን ከጠላት ጦር ለመከላከልና፣ የጣልያኑን ጦር መንገድ ላይ አግዶ ከማይጨው ተበትኖ ወደአዲስ አበባ የሚመጣውን ጦር እድል ለመስጠት የመጨረሻ ሙከራ ለማድረግ፣ በተወሰኑ ጀግኖች ወደ 5,000 ገደማ የሚሆን ወታደሮችን ያቀፈ አነስተኛ ጦር በአጭር ጊዜ ውስጥ ተዘጋጅቶ አዲስ አበባን ለመከላከል ከአዲስ አበባ ተነስቶ ወጣ። ይኸ ወደ 5,000

ገደማ የሚሆነው ጦር የተሰበሰበው ከሆለታ ወታደራዊ ትምህርት ቤት ተማሪዎች፣ ከንጉሠ ነገሥቱ የቤተ መንግሥት ታጣቂ አሽከሮች፣ ከጦር ግንባር ከተመለሱ፣ በአዲስ አበባ ዙሪያ ካሉና እንዲሁ አዲስ አበባ ውስጥ ከሚንገላወዱ ወዶ ገባዎች ሲሆን የዚህ ጦር መስራችና መሪ በሆነው ስዊድናዊ መኰንን ጦሩ እየተመራ ወደ ጣርማ በር ገሰገሰ። ይቺ ወሳኝ የሆነች ቦታ ግን ገና ዱሮ በጣልያኖች እጅ ወድቃ ነበር። ከጣርማ በር በኋላ የጣልያኑ ጦር ወደ አዲስ አበባ ያደረገው ጉዞ ግን በሁለመናው ወታደራዊ ሰልፍ ይመስል ነበር።

የመጀመሪያው ሜካናይዝድ ጦር 1,725 ተሽከርካሪዎችን ይዞ በጣርማ በር በኩል አድርጎ በደብረ ብርሃን አልፎ ወደ አዲስ አበባ ያለ ችግር ገሰገሰ። ሶስተኛው ክፍለ ጦር ደግሞ በአስቸጋሪው መንገድ በፊቼ በኩል ወደ አዲስ አበባ ሄደ። በዚህ መልኩ ወደ አዲስ አበባ የሚጎርፈውን የጠላት ጦር ሊያቆመው የሞከረ ምንም ኃይል አልነበረም። የአዲስ አበባ መንገድ ክፍት ናት።

ከዛሬ ነገ ጣልያኖች አዲስ አበባ ገቡ እየተባለ ሲሰጋ ሚያዝያ 30 ቀን ጃንሆይ በጣት ከሚቆጠሩ ታማኝ ወታደሮቻቸው ጋር አዲስ አበባ ቤተ መንግሥት ገቡ። ጃንሆይ የአሸንጌን ሐይቅ ሲሻገሩ፣ እንደዚያ በጣልያን አውሮፕላኖች ቦምቦችና በራያና አዘቦዎች እየታለሙ በሚተኮሱ ጥይቶች የኢትዮጵያ ሰራዊት ሲረግፍ፣ ከሁሉም በላይ ከጣልያኖች የጭስ መርዝ መትረፋቸው ራሱን የቻለ ታላቅ ተዓምር ነው። እድለኛ ናቸው። ጣልያኖች በጥሩ መረጃ ተከታትለው በቦምብና በጭስ መርዝ ሆን ብለው ያጋዩት ጃንሆይን አጅቦ ይኼድ የነበረውን ሰራዊት ነበር። ከየፐራት የቦምብ ዝናብ ያመለጠ ሰው በእውነት በጣም እድለኛና እግዜሩ የሚጠብቀው ሰው ነው።

ጃንሆይ እንዲህ መላው በጠፋ ቀውጢ በሆነ ሰዓት የአሸንጌን ሐይቅ የመሻገሩን ሀሳብ ቀይረው፣ ተገንጥሎ ብቻውን በራያዎች፣ በአዘቦዎችና በጣልያኖች ተከቦ ፍዳውን የሚያየውን የአራተኛውን ረድፈኛ ጦር ለመርዳት ዞረው ቆርበቱ ላይ ለመግጠም የወሰኑትን ውሳኔ በትላልቆቹ ሹሞቻቸው ውትወታ ትተው እያዘኑ አሸንጌን ተሻገሯት። በቆርበቱ የጦር አውድማ በሺዎች የሚቆጠሩ ምርጥ የኢትዮጵያ ልጆች የጠላትን አንገት እያነቁ ጥለው ወደቁ።

በነዚህ ሹማምንቶቻቸው ውትወታ ጃንሆይ ሚያዝያ 5 ቀን እንደገና ሰራቸውን አሰባስበው ብዙም ጣልያኖች በማይዳፈሩት መንገድ በላሊበላ በኩል አድርገው ወደ ደሴ ጉዞ ጀመሩ። ከሰባት ቀን አድካሚ የእግር ጉዞ በኋላ ላሊበላ ገቡ። ከዛሬ ሰባት መቶ ዓመት በፊት ሆዷን ቆፍራ፣ ከአንድ ወጥ ድንጋይ ልጇን ፈልፍላ፣ ውብ ቤተ ክርስቲያኖችን ሰርታ፣ በሆዷ አቅፋ በምትኖረው ላሊበላ ለሁለት ቀናት ያህል አረፉ። ከዚያ በኋላ በሚቀጥሉት ሰባት ቀናት ተጉዘው ወደ መቅደላ አፋፍ ሲቃረቡ፣ መቅደላ በጣልያኖች እጅ መውደቋን ሰሙ።

እንዲህ ሽፍታ በሽፍታ በሆነው ሀገር ውስጥ ኢጅጉን የደከመውንና ቁጥሩም እሽቆልቁሎ የወረደው ሰራዊታቸውን እየመሩ ወደ ወረኢሉ ሄደው፣ ቢያንስ በስልክ ከአዲስ አበባ ጋር ለመገናኘትና አለም ምን እያለ እንደሆነ ለመስማት ከፍተኛ ተጋድሎ በማድረግ ወረይሉ አፋፍ ላይ ደረሱ። ጠማማ እድል ወረኢሉም (ወረ ኃይሉ) በጣሊያኖች እጅ ወድቃለች።

ጃንሆይ አሁን ሌላ ምንም አማራጭ አልነበራቸውም። ያላቸው ብቸኛ አማራጭ ጣሊያኖች ለጊዜው የማይደፍሩት አስቸጋሪው የፊቼው መንገድ ብቻ ነው። ይህን ለዝንጀሮ እንኳን የሚታክት መንገድ እንደማንም ተራ ወታደር ተጉዘው ሚያዝያ 29 ቀን ፊቼ ገቡ። በዚያው ቀን ከአዲስ አበባ በርካታ ተሽከርካሪዎች መጥተው ወደ አዲስ አበባ ወሰዷቸው። የኛም ግዳጅ በፊቼ ተጠናቀቀ።

36
የልጁ ጦር ፍፃሜ

ጃንሆይ አዲስ አበባ ከመግባታቸው በፊት ከመኳንቶቻቸው ጋር የመጨረሻውን የጦር የምክክር ሸንጎ ያካሄዱትና የመከሩት ፊቼ፣ ሰላሌ ውስጥ ነበር። የኛም የፈረንጆቹ ግዳጅ በሰላሌ ሜዳ ፊቼ ላይ ቢጠናቀቅም ልጁን ሳልሰናበተው መሄዱ ሆዴን በላኝና የአየርላንዱ ካፒቴን ከኦስትሪያው ዶክተር ጋር የጃንሆይን ጦር ተከትለው ወደ አዲስ አበባ ሲሄዱ፣ እኔ፣ ብረየርና ሽማግሌው ኮሎኔል ኮኖቫሎቭ በፊቼ ቀረን።

ሽሜው ይኼው ቀኑን ሙሉ ከአንዲት ጉብታ ላይ ተቀምጦ ዙሪያ ገባውን ሲያማትር ነው የዋለው። ሽሜው የሰላሌን ሜዳ እያደነቀ ሳይሆን የአቢቹን የተበተነ ጦር በአይኑ እየፈለገ እንደሆነ ገብቶኝ ወደተቀመጠባት ጉብታ ሄጄ፣ "ታዲያስ ኮሎኔል፣ አቢ የምትመጣ ይመስልሃል?" ብዬ ላቀረብኩለት ጥያቄ፣ ከተቀመጠባት ጉብታ ላይ እየተንፏቀቀ ወርዶ ቆመና አሁንም እየዞረ ዙሪያ ገባውን መጨረሻ የሌለው የሚመስለውን የሰላሌን ሜዳ እየት አድርጎ፣ "ይመስለኛል፤ መምጣትም አለበት! የሱ እግረኛ ወታደሮች እኩለ ቀን ላይ በትንሽ በትንሹ ቡድን እየሆኑ ወደ ጃርሶ መስመር ሲወርዱ አይቻለሁ። ምናልባትም እስኪመሽለት እየጠበቀ ሊሆን ይችላል እንጂ ይመጣል። እንዲህማ ከዚህ ሁሉ መከራ በኋላ በትውልድ ሀገሩማ ሳይሰናበተን" ብሎ ኮሎኔል ሊናገር የፈለገውን አልጨረሰውም። ሊል ያሰበው እኔም ስለገባኝ አላስጨነኩትም። በዚህ መሀል የጃንሆይ መልክተኛ መጥቶ ጃንሆይ እንደጠሩን ስለነገረን ጊዜ ሳናጠፋ ወደ ጃንሆይ ሄድን።

ከጃንሆይ ጋር ባሳለፍናት ጥቂት ቆይታ ጃንሆይ እኛ ለአሳቸውና ለምስኪኗ ኢትዮጵያ የዋልነውን ውለታ ምንጊዜም የማይረሱትና ከፍለው የማይዘልቁት ባለውለታቸው እንደሆንን አመስጋግነው ተሰናበቱን። ከዚች ከመጨረሻዋ ከጃንሆይ ጋር ካሣለፍናት ጥቂት ቆይታ በኋላ እኛም ለቀረው የሽሽት ጉዟችን ልንሰናዳ ወደ

ድንኳኖችን አመራን። በዚቹው ሌቱ ላይ ጥያት በምሄደው ድንኳኔ በራፍ አጠገብ ደጃዝማች አበራን ቆሞ አገኘሁት።

የሰላሌው ገበሬ ደጃዝማች አበራ ለንጉሡ ካደረገው ግብዣ በተጨማሪ እኛን ፈረንጆቹን በሀገሩ፣ በግዛቱ የምሽቱ እንግዶቹ እንድንሆንለት ሲጋብዘን ነበር አመጣው። አሽከር መላክ ሲበቃ ራሱ ደጃዝማች፣ የሰላሌው ገበሬ መምጣቱ ከልብ አስደሰተን። ከረጅም የረሀብና የውሃ ጥም በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ የጤፍ እንጀራ በቆይ ወጥ፣ ጥሬ ስጋ፣ መጠጥ በየይነቱና እየረሳኋት የመጣኋትን ክፉ አመሌን ማስታገሻ ሲጃራም ጭምር ቀረበልንና ከሰከስነው። እንደወጉና ባህሉ ማዕድ ተነስቶ ጠጅ እየተቀዳ ጨዋታው ሲጀመር ጠጄን በአንድ ትንፋሽ ጨልጠው ከተቀዳልኝ በኋላ የሁላችንንም አንጀት የሚበላውን የአቢቹን ነገር ያናራ አነሳሁት።

የአቢቹ ጦር በቀርበተው ጦርነት በአዘቦቻችና በራያዎች ከፍተኛ ጉዳት እንደደረሰበት ሁላችንም ሰምተናል። ጃንሆይ ሳይቀሩ አሻፈረኝ ልጅን ብቻውን ጥለን እንሄድም እስከማለት ደርሰው ነበር። እንደዚያም ሆኖ ጦሩ ከፍተኛ የሚባለውን መስዋዕትነት ከፍሎ ከቀርበቶ እሳት ውስጥ እንደወጣና መሪው አቢቹም በህይወት እንደተረፈ ሰምተናል።

ይኼን ጥያቄ ደጃዝማች የጠበቀው ጉዳይ ነው መሰለኝ፣ "መልክተኛ ልኬብታለሁ፤ እዚህ ብዙ ሳይርቅ ሰፍሮ ከጀግኖቹ የትግል ጓዶቹ የከንባታ ልጆች ጋር እየተሰናበተ ነው" አለን። እዚች ላይ ደጃዝማች አበራ ለነአቢቹና ለከንባታ ልጆች መስዋዕቶች አንድ ሰንጋ፣ እንጀራና ጠጅ ማስላኩን ሳይነግረን እንዲሁ በደፈናው መልክተኛ ልኬብታለሁ፤ መልክተኛዬን በያንዳንዷ ደቂቃ እየጠበኩት ነውና አይሂችሁ ይመጣል፣ ይልቅ ከጠጁ ይጋግሙ እያለ አበረታታን። እዎ ነገ በማለዳ ተጓዦ ነንና ስመተኛትም ሳንሞክር ጠጃችንን እየንደቀደቅን መልክተኛውን በተስፋ መጠባበቁን ተያያዝነው። መልክተኛው ግን የውሃ ሽታ ሆኖ ቀረ።

እንዲያይነጋ የለም ሲነጋጋ ሲል ግድም ኮሎኔል ኮኖቫሎቭና አቶ ብረየር አሸለቡ። እኔና አበራ በረንዳ ላይ በሉኮምቻችንን (ድርብ ጋቢ) ተከናንበን በወርጨሜማዎች ላይ ተቀምጠን ሰፍወጋ፣ እንዴት የውሃ እንስራ የተሸከመች ሴት በትንግርት እንስራዋን እንደተሸከመች አንድ ቦታ ላይ ቆማ ለረጅም ጊዜ ፊዛ ወደምትያይበት አቅጣጫ ተመለከትኩ። ምንም የሚታይ ነገር የለም። እኛ ካለንበት በጣም ብዙ እርቀው የሆኑ ፈረሰኛ የሚመስሉ ነገሮች ቀመዋል። ወዲያው ደጃዝማች ፈረሰኛ ወደሚመስሉት ነገሮች በጦር ሜዳ መነጽሩ እንጣጥሮ ጥቂት ከተመለከተ በኋላ ሳቅ እያለ የጦር ሜዳ መነጽሩን እንዳያበት አቀበለኝ። እነዚያ ፈረሰኞች ወርቁ፣ አቢቹና ሀብቶም ነበሩ። "ለምን ወደዚህ አይመጡም?" ብዬ አበራን ጠየኩት። አሁንም እንደመሳቅ ብሎ፣ "እንበሳዋ ከራሶችም ሆነ ከሌሎች ደሊዎቻቸው ጋር መገናኘት የፈለገች አልመሰለኝም። እስቲ ሌሎችንም እንቀስቀሳቸውና እነሱው ወደመረጡት ቦታ

እንሂድ" አለና ወደ ውስጥ ገባ። እኛ ስንለባበስ አሽከሮች ፈረሶቻችንን ጭነውልን ስለነበር ጊዜ ሳናጠፋ እነአቢቹን ወዳየንበት ቦታ በፈረስ ሄድን። እነ አቢቹ ግን በቦታው አልነበሩም።

ብዙም ሳንቆይ ለጉዞ ተሰናድቶ የነበረው ከዚያ አስከፊ የቀርበቶ እልቂት የተረፈው ፈረሰኛው ጦር ጉዞ ሲጀምር አየነው። እግረኞቹ ወደኩዩ፣ ወደ አቦቴና ጃርሶ ከሄዱ ቆይተዋል። ከነዚህ ፈረሰኞች ሶስቱ የመንገድ መስመራቸውን ለውጠው እኛ ወደቆምንበት አቅጣጫ በዳለቻ፣ በግራጫና በጥቁር ፈረሶቻቸው ላይ ተቀምጠው ሽምጥ ሲጋልቡ አየናቸው።

ጋላቢዎቹ ፈረሰኞች ግማሽ ርቀት ሲቀራቸው ፈረሶቻቸውን ገትተው ካቆሙ በኋላ፣ ጥቂት ሲነጋገሩ ቆይተው ባለ ጥቁሩ ፈረስ ፈረሰኛ ብቻውን ወደኛ መጋለብ ጀመረ። ባለጥቁሩ ፈረስ ጋላቢ ወደኛ እየተቃረበ ሲመጣ ማን እንደሆነ ሁላችንም ለየነው። ባለ ጥቁሩ ፈረስ ፈረሰኛ የኛዋ ትንሿ ጀግና አቢቹ ናት።

ልክ እኛ የቆምንበት ቦታ ሲደርስ ፈረሱን ቀልጠፍ አድርጎ ከፈረሱ ላይ ዱብ ብሎ ወርዶ ከደጃዝማች አበራ እግር ስር ለጥ ብሎ ወድቆ ሰላምታውን ሲያቀርብ ሲል፣ ደጃዝማች አፈፍ አድርጎ አንስቶ እንደታናሽ ወንድም፣ እንደጓደኛ እቅፍ አድርጎ ሳመው። በእቅፉ አስገብቶ ጀርባውን ቸብ ቸብ ካደረገ በኋላ ወደኛ ሲለቀው የደጃዝማች አበራ አይኖች እንባ አርግዘው ነበር። እናም ዞር ብሎ በሸማው አበሳቸው። ሁላችንም እያቀፍን ከሳምነው በኋላ በርቀት ወደሚጠብቁት ወንድሞቹ የሆነ ምልክት ከማሳየቱ ሁለቱ አንበሶች የትግል ጓዶቹና ወንድሞቹ እየጋለቡ ወደኛ ገሰገሱ።

በዚች የሰላሌ ሜዳ በዚች ውርጭ፣ በጣም የምወደውን፣ የምኮራበትንና የማደንቀውን፣ ትምህርት ቤት እንጂ ጦር ሜዳ መዋል የሌለበትን፣ ስም የለሹን የወረ ጃርሶውን ደቦል አንበሳ፣ ጀግናውንና ታላቁን የጦር መሪ "ልጅን" ተሰናበትኩት።

እኔ፣ ኮሎኔል ኮኖቫሎቭ፣ አቶ ብረየር፣ ደጃዝማች አበራና ልጁ (አቢቹ) ሆነን በዚያች ገላጣ ሜዳ ላይ ተቀምጠን ስንጫወት ሁለቱ ወንድሞቹ ወርቁና ሀብቶም መጥተው ተቀላቀሉን። የደጃዝማች አሽከር ለሁላችንም ቡና ሲኒ ካቲካላ ቀዳልን። ለዚች ውርጭ ፍቱን መድሀኒት ናትና በደስታ ተቀበልናት።

"እሺ አቢ፣ ምን ታስባለህ?" ስል የሞኝ ጥያቄ ጠየኩት። ምናልባት የወደፊት አላማውን ቢነግረኝ ብዬ። "ጣልያኖች ትምህርት ቤት የመግባቱ ሀሳብ የለኝም" አለኝ። ቶኔ መሆኑ ሁላችንም ገብቶናል። የነዚህ አንድ ፍሬ ልጆች እጣ ፈንታ ተወስኗል። "ቀን ሲያልፍ ወደ ትምህርት ገበታህ ትመለሳለህ። አይዞህ" አለው ደጃዝማች አበራ የአቢቹን ጎፈሬ እያሻሸ።

"በስተርጅና ትምህርት ይሆናል ብለው ነው ጌቶች?" ብሎ መለሰ፤ ምናልባት ጣልያኖችን በቀላሉ ከሀገር ማስወጣት እንደማይቻል ታይቶት፣ ታስቦት ይሆናል።

መለሰ። "ወዴት መሄድ አስበሃል?" አሁን ብቻ እሁንም በተለመደችው አማርኛው መለሰ። "እንጃ ጌቶች፣ ምናልባት ጃርሶ ወደቀላው እንወርድ ይሆናል። ደግሞ ሸሜው ጠየቀ። "እንጃ ጌቶች፣ ምናልባት ጃርሶ ወደቀላው እንወርድ ይሆናል። ደግሞ ሸሜው ጠየቀ። አሁን ግን ትክዝ ብሎ። ከስፋም ወደ ማንደብረት መዝለቃችን አይቀርም" አለ፣ አሁን ግን ትክዝ ብሎ። ከስፋም ወደ ግንደብሬት መዝለቃችን አይቀርም" አለ፣ ትዕዛዝም ልመናም ጌጥማን ሳታዮቸው እንዳትወርድ፤ አደራ" አለው ደጃዝማች፣ ትዕዛዝም ልመናም በተሳበሰ ቃና።

አሁን አቢቹ አዝን ብሎ ቆይቶ፣ "ጌቶች፣ ትልቁ መከራዩም እሱ ነው። እንደምን ብዬ አይናን እያለሁ። ሁለት ልጆቿን በተንቤን አንዱን ቀብሬ ሁለተኛውን ሊጫብራ ራት ጥዬ፣ እኔ ብቻ ተርፌ ፊቷ ስቀርብ ምን ትለኛለች?" አለ። "አይዞህ፣ የጀግኖች እናት ነችና ሁሉንም ትችለዋለች። ሂድና እያት። ብዙ ቀን ግን አትሰንብት። እኔም እንደነገሩ የቀረኝን ጦር አሰባስቤ ወደበረሃ መውረዴ አይቀርምና እንገናኛለን። ጥሩ ዋሻ ይዘህ ጠብቀኝ" አለ ደጃዝማች በማብራራት አይነት። ቀጠል አድርጎም ከኪሱ አንዲት የተጣጠፈች ወረቀት አውጥቶ "ለእማማ ስጣቸው" አለው።

የደብዳቤዋን ይዘት ባላውቅም ለአቢቹ እናት ስለ ሁለቱ ልጆቻቸው አሟሟት የተጻፈ የማጽናኛ ደብዳቤ እንደሆነ ሁላችንም ገምተናል። ግን አበራ ምን እንደጻፈ ሊያውቅ የሚችለው፤ ለእናቱ የሚያነብላቸው አቢቹ ብቻ ነው። አቢ "እሺ ጌቶች" ብሎ ደብዳቤውን ተቀብሎ ወደ ኪሱ ከተተው። በዚህ መልኩ ብዙ ስንጫወት ቆይተን መሄጃቸው ሲቃረብ ለስንብት ጀግኖቹ ተነሱ። አንበሶቹ እኛን ለመሰናበት ተደርድረው ቆሙ። ማን እንደሚጀምር ስንተያይ ወርቁና ሀብቱም የሆኑ በራፊ በቱቶዎች የተጠቀለሉ ነገሮች ይዘው ቀረቡ።

አቢ መጀመሪያ ከወርቁ እጅ የተተጠቀለለውን ነገር ተቀብላ ጨርቁን ከጣለች በኋላ አንድ ሽጉጥ ይዞ ለደጃዝማቹ፣ ለጦር አለቃው ስጦታ እያቀረበ፣ "ጌቶች፣ ከአንድ ከገደልኩት የጣልያን መኮንን እጅ ፈልቅቄ ያወጣሁት ነው። እነሆ ለማስታወሻ፤ ለወደፊት የነጻነት ትግላችንና ታማኝነታችን ይቀበሉኝ" ብሎ አተርትሮ ሽጉጡን የያዙትን ሁለት እጆቹን ለደጃዝማች ዘረጋቸው።

ደጃዝማች አበራ ሽጉጡን አገላብጦ ካየ በኋላ፣ "አመሰግናለሁ የኔ አንበሳ" ብሎ እቅፎ ሳመው። ቀጣዩ ባለ ተራ ኮሎኔል ኮኖቫሎብ ነበርና አሁንም እራፊውን ጨርቅ ጥሎ የሚያብረቀርቅ ስለታም ሰይፍ ይዞ፣ "ኮሎኔል፣ ይኼ ደግሞ የወንድማችን የተሰፋ ጸዮን ሰይፍ ነው፤ እባክዎትን ለመከራ ጊዜ ማስታወሻ ይሆንዎት ዘንድ ይቀበሉኝ" ብሎ እንደ ኢትዮጵያውያን ወግ ሁሉ አንገቱን ሰብሮ ሰይፍ የያዙ እጆቹን ዘረጋ። ኮሎኔል ኮኖቫሎብ እንባ እየተናነቀው ሰይፉን ተቀብሎ አቢቹን መተንፈስ እስኪያቅታት ድረስ አቀፈት።

ቀጥሎ የብረየር ተራ ነበርና እሱም በተመሳሳይ ሁኔታ በተመሳሳይ ቃላት የጋሹ ሰይፍ ለመከራ ጊዜ ማስታወሻ ስጦታ ተሰጠው። የመጨረሻው ባለ ተራ እኔ ነበርኩና አሁን አቢቹ በእጁ ምንም ነገር ሳይዝ መጥቶ ከፊቴ ቆመ "ጌቶች፣ ለእርሶ

ምንም የምሰጠው ነገር የለኝም። እዚህ አብረውን ቢሆኑና ቀሪውን ጊዜዎን ከኔና ከወንድሞቼ ጋር ቢያሳልፉ ምንኛ ደስ ባለኝ። ግን የሽሽት ኑሮ ይበቃዎታል" ብሎ ትክዝ አለና፣ በተንቤን ሀ ብሎ የተዋጋበትን ሰይፉን መዝዞ እንድቀበለው በሁለት እጆቹ ይዞ ለመነኝ። የገዛ ሰይፉን ለኔ መስጠቱ አግባብ እንዳልሆነ ለማስረዳት ብሞክርም አሻፈረኝ ስላለኝ ተቀበልኩት።

በመጨረሻ ተቃቅፈን እንባ ተራጭተን ተለያየን። ለዎ አቢቹ ሌላ አንድ ሰይፍ አለው። በጣም የሚወደው፣ ወደ ጦር ሜዳ ሲሄድ አሻፈረኝ ብሎ የተከተለው፣ በመጀመሪያው ቀን ጦርነት በጀግንነት ሲዋጋ ወድቆ በዚያች ትንሽ ዋርካ ስር የቀበረውና ለትልቁ ትግል ያደፋፈረው የወንድሙ ሰይፍ። ሁሌም ግራ ያጋባኝ የነበረው የአቢ ሁለት ሰይፍ መታጠቅ ምስጢር በዚች ቅጽበት ተገለጠልኝ።

በሞት አልጋ ላይ ያለቺው ኢትዮጵያ ምርጥ ምርጥ ጀግኖቿን በየጦር ሜዳው አውድማ፣ ማግዳና ቀብራ፤ የቀሩትንና የተረፉትን በየቆላው፣ በየበረሀው፣ በየተራራው፣ በየሸለቆው ብቻ ሊተርፉላት፣ ሊጠነክሩላት፣ ሊበረቱላት በሚችሉት ቦታ ሁሉ በተነቻቸው። እኛም የማንወለዳት፣ ሳትወልደን ፍቅሯን የለገሰችን፣ እንደ ልጇ የተቀበለችን እናት ኢትዮጵያን ያቅማችንን ታግለንላት፣ ልንሰናበታት፣ ህይወታችንን ልናተርፍ ተነሳን።

ሶስቱ ፈረሰኞች ከአይናችን እይታ እስኪርቁ ድረስ በሰላሌ ሜዳ ላይ ስናፈጥ ቆይተን ወደ ደጃዝማች አበራ ሰፈር ተመለስን። ቁርስ ካደረግን በኋላ ደጃዝማች አበራን ተሰናብተን ወደ ሸገር ጉዞ የሰላሌን ሜዳ ተያያዝነው።

37

የአዲስ አበባ (የሸገር) እሳት

አዲስ አበባ ራስ ካሣና ሌሎች ክፍተኛ ሹማምንቶች ጃንሆይን አጅበው ገብተዋል። የቀሩት ክፍተኛ የጦር ሹማምንቶች፣ ምርጥ ምርጦቹ የኢትዮጵያ ልጆች፣ በተንቤን፣ በማይጨው፣ በአሸንጌ ሐይቅ ዙሪያ ወድቀው የአሞራ ራት ሆነዋል። ከዚህ የተረፉትን ሽፍቶች፣ ራያዎችና አዘቦዎች አጉልና አሳቻ ቦታ እየጠበቁ ከአዲስ አበባው ጉዟቸው ለዘላለሙ አስቀርተዋቸዋል።

በቤተ መንግሥት በጃንሆይ መሪነት ሌሊቱን ሙሉና እስከሚቀጥለው ቀን የምሳ ሰዓት ድረስ የተረፈው የጦር ሸንጎ መከረ። ከምሳ በኋላ ጃንሆይ መጀመሪያ በቤተ መንግስታቸው የእንግሊዙን አምባሳደር ቀጥሎም የፈረንሳዩን አምባሳደር ተቀብለው ለረጅም ሰዓቶች አናገሯቸው።

ከዚህ በኋላ ግንቦት አንድ ቀን የጣልያን ሜካናይዝድ ጦር አዲስ አበባን ሊይዝ 25 ኪሎ ሜትር ብቻ እንደቀረው በሰፊው ሲወራ አዲስ አበባ ተበጠበጠች። ባለፉት ሳምንታት በአዲስ አበባ ያሉ ሱቆች ተዘግተው ነበር። የመኖሪያ ቤቶችም ወና መሆን ከጀመሩ ሰንብተዋል።

በየመስቀለኛ መንገዶች መሀል ላይ ያሉት እነዚያ የበርሜል ቤቶች እንኳን ሳይቀሩ እነዚያ በባዶ እግራቸው የሚኳትኑትን የአዲስ አበባ ፖሊሶች ጠረን ካጡ ሰንብተዋል። እናም አዲስ አበባ ባዶ ሆናለች።

በዋናው የራስ መኮንን አደባባይ (ሰፈር) ወይም መንገድ ባለች አንዲት ትንሽ የግሪክ ሆቴል ብቻዬን ነኝ። የሆቴሏ ባለቤት ድራሹ ከጠፋ ሰንብቷል። ኢትዮጵያውያን የሆቴሏ ሰራተኞች ጓዛቸውን ጠቅልለው ጠፍተዋል። እንዲሁ ምክንያቱ በማይታወቅ ምትሃታዊ ምክንያት የሆቴሏ ቁልፍ ቤት ብቻ በቦታው ተቀምጧል።

ማታ ከእንጨት በተሰራችው የሆቴሏ በረንዳዬ ላይ ተቀምጬ ጭር ያለችውን የራስ መኮንንን ሰፈር ስቃኝ አመሸሁ። አልፎ አልፎ ውልብ እያሉ ከሚያልፉ ሽማ ከተከናነቡ እግረኞች በስተቀር የራስ መኮንን ሰፈር ፀጥ ረጭ ብላለች። አዲስ አበባ ነገ ከነገ ወዲያ ቀውጢ ልትሆን ዛሬ ፀጥ ብላለች።

ከዚህ የአዲስ አበባ እይታዬ በኋላ ወደ አልጋዬ ሄጄ ጋደም እንዳልኩ እንቅልፍ ወሰደኝና ግር የሚያሰኝ ህልም ይታየኝ ጀመር። በህልሜ እንደገና ወደሰሜን ጦር ግንባር ተንቤን ተመልሻለሁ። ወይም ደግሞ አሁንም እዚያው ጦር ግንባር ያለሁ ይመስለኛል። የመትረየስ ጥይት ጩኸት፣ የአውሮፕላን ጩኸት፣ በታላቅ ጀግንነት

እየፎከረ፣ እየሸለለና እያቅራራ የጠላትን አንገት ሲቀላ የሚጮኽ የሽማ ለባሹ የገበሬ ወታደሮች ድምጽ፣ ጩኸት፣ ብቻ ሁሉም ተቀላቅሎ ይሰማኛል።

በጭንቀት ባነንኩ። ከዚያ አስከፊ በዛዙ የሚቆጠሩ ሰዎችን ደም ካፈሰሰው አስቃቂ ጦርነት መሀል እንደምንም ወጣሁ። ግን አሁንም የአውሮፕላን ድምጽ የሚመስል ነገር ይሰማኛል። እናም ከአልጋዬ ላይ ተስፈንጥሬ በመነሳት ወደ በረንዳዋ ተንደርድሬ ወጣሁ። አሁንም የራስ መኮንን ሰፈር ጭር እንዳለች ነው። ወደ ዋናው የራስ መኮንን መንገድ ተመለከትኩ።

ምንም ነገር ማየት ባልችልም አልፎ አልፎ ተከታትለው የሚተኮሱ ጥይቶች ጩኸት እሰማለሁ። መጀመሪያ ጣልያኖች አዲስ አበባ እየገቡ እንደሆነ ገመትኩ። በደንብ ስነቃ ግን የምሰማው ከኢትዮጵያ ወታደር የሚተኮስ የአሮጌ ጠመንጃ ጥይት መሆኑን ስረዳ ተመልሼ አልጋዬ ላይ ተፈነገልኩ።

አልጋዬ ውስጥ እንደገባሁ በጣም ቀርቦ የሚሰማ የሞተር ድምጽ ሰማሁና ወደዚያችው የእንጨት በረንዳ ተመለስኩ። አሁን ደግሞ ጣልያኖች አዲስ አበባን በሌሊት ሊደበድቧት የመጡ መሰለኝ ነበር። ግን ከበረንዳዋ ላይ ሆኜ ወደ ዋናው አደባባይ ሳፈጥ ከጨለማው መሀል እየቃሰተ ዳገቱን የሚወጣ፣ ካቅሙ በላይ ጓዝ የተጫነ የጭነት መኪና እያንራ አለፈ። ብዙም ሳይቆይ ተከታትለው ሌሎች የጭነት መኪናዎችና አውቶሞቢሎች አለፉ። አዎ ጃንሆይ እየሄዱ ነው። ሀገር ለቀው እየወጡ ናቸው።

38

ስደት

ማታ ዘበኛውን በጠዋት እዲቀሰቅሰኝ ነግሬው ነበር። እንዲህ አዲስ አበባ አደጋ ላይ እየወደቀች ባለችበት ሰዓት ወደ ባቡር ጣቢያ ሄጄ ወደ ጂቡቲ ለመሄድ አስቤ፣ ዘበኛውን እንዲቀሰቅሰኝ ደጋግሜ ጉርሻም ሰጥቼ ብነገረውም፣ ምስኪኑ ዘበኛ እኔን ሊቀሰቅሰኝ አልቻለም። እኔው ራሴ ነቃሁ። ከሆቴሏ ብዙም ሳይርቅ የሚተኮሱ የመትረየስና የጠመንጃ ጥይቶች ጩኸት እንኳን እኔን የዶሮ እንቅልፍ የለመድኩትን ሰው ይቅርና የሞተም ሰው ይቀሰቅስ ነበር።

አዎ ከየቦታው የተጠረቃቀሙ ሽፍቶች አዲስ አበባን ዙሪያዋን ከበው ለዝርፊያ ማነፍነፍ ጀምረዋል። ለጊዜው ባለቤቶቻቸው ጥለዋቸው የሄዱ ቤቶችን፣ የተዘጉ ሱቆችን ያለ አንዳች አጋጅ እየዘረፉ ናቸው። እነዚህ ሽፍቶች የሚዘርፏቸውን ንብረቶች እየተሸከሙ ወደ ምሽጋቸው በጠራራው ፀሐይ ያለ ይሉኝታ ያግዛሉ። የጠርሙስ መጠጥ መጋዘኖችን ሰብረው እየገቡ፣ እዚያው በቦታው መጠጣት ይጀምሩና ሲሳከሩ፣ ተሸክመው መሄድ የማይችሉትን ሁሉ ሰባብረው መጋዘኗንም አቃጥለው ይኼዳሉ።

አሁን አዲስ አበባ በጠላት ሳይሆን በራሷ ደደብ ልጆች እጅ መንደድ፣ መቃጠል ጀምራለች። ይቺ የሽገር እሳት ለጊዜው የምትጨሰው በከተማዋ ዳርቻ ቢሆንም እነዚህ ደደብ የሽገር ዘራፊዎች ወደ አራዳ ብቅ ማለታቸው የማይቀር የጊዜ ጉዳይ ብቻ ነው። ትልቁና ብቸኛው ሸገርን ለዘራፊዎቿ ጥሎ ነፍስን ማዳኛ ጊዜ አሁን ነው። እናም ወደ ባቡር ጣቢያ ለመሄድ ወስኜ ሆቴሏን ለምስኪኑ ዘበኛ ብቻ ጥዬ ወጣሁ።

በአጋጣሚ ከሆቴሏ ብዙም ሳልርቅ አንድ የሚከራይ መኪና ሲሄድ አየሁና ሾፌሩን እንዲያቆምልኝና ወደባቡር ጣቢያ እንዲወስደኝ ስጠይቀው፣ ሾፌሩ ፍጥነቱን ብቻ ቀንሶ አንገቱን በመስኮቱ ወጣ አድርጎ፣ "ጌታ ዛሬ አልሰራም። መንግሥት የለም። ዛሬ ማንም አይሰራም። መሞት የሚፈልግ ብቻ ነው የሚሰራው" እያለ ጥሎኝ ሄደ።

አዲስ አበባ በሚያስገርም ፍጥነት ወደ እብደት እያመራች ነው። ለሁለት ጠብደል ጎረምሶች ቅድሚያ ትልቅ ጉርሻ ሰጥቼና ቀሪውን ባቡር ጣቢያ ልጨምርላቸው ቃል ገብቼ፣ የቀሩኝን እቃዎች አሸክሜ በዚያች ሌሊት ወደ ባቡር ጣቢያ ሄድኩ። አሁን ባቡር ጣቢያ ደርሻለሁ። ባቡር ጣቢያዋ በጂቡቲ የፈረንሳይ ወታደሮች ስለምትጠበቅ ለጊዜው እነዚያ ልክስክስ የአዲስ አበባ ዘራፊዎች ጣቢያዋን አይዳፈሯትምና እዚህ የሽፍቶች አደጋ እምብዛም አያሰጋም፣ ቢያንስ ለጊዜው።

በሀዲዶቹ ላይ እግሮቹን ዘርግቶ ለጉዞ የተዘጋጀ ባቡር ቆሟል። እስከፍንጫው ድረስ ሰው ስለጫነ አንዲት ዶሮ እንኳን ማስገቢያ፣ መስቀያ ቦታ የለውም። በለገሀር

የባቡር ጣቢያ ስድስት የሲዊድን አየር ኃይል ወታደራዊ የደንብ ልብስ የለበሱ ወጣት አውሮፕላን አብራሪዎች ወዲያ ወዲህ ይራወጣሉ። እነሱም እንደኔው በዚህ ለጉዞ በተዘጋጅ ተራ ባቡር ቦታ አላገኙም። ስድስቱ የሲዊዲን ተወላጆች ኢትዮጵያውያንን አውሮፕላን ማብረር ሲያስተምሩ እስከ መጨረሻዋ ቀን ድረስ በአዲስ አበባ ለንጉሡ የገቡትን ቃል በታማኝነት ሲፈጽሙ ቆይተው፣ እነሆ አዲስ አበባ አደጋ በአደጋ ሆና ፈረንጅ በመሆኑ ብቻ አደጋው እጥፍ ድርብ በሆነበት ሰዓት ነፍሳቸውን ለማዳን ይኼው እንደኔው በለገሀር የባቡር ጣቢያ ቆመዋል።

እነዚህ ስዊዲናዊ የጦር መኰንኖች ሶስት ቀን በሚፈጀው በዚህ ተራ ባቡር ጂቡቲ መድረስ አስቸጋሪ መሆኑን አሳምረው ያውቃሉ። እናም ከፈረንሳዊው የአዲስ አበባ የባቡር ጣቢያው ሀላፊ ጋር ሙግት ገጥመዋል። እነዚህ ልጆች ሰውዬው ልዩ ባቡር እንዲያዝላቸው አጥብቀው ጠየቁት። እኔም በሙግቱ ገብቼ ከብዙ ውትወታና ጭቅጭቅ በኋላ ይኼው የሸገር ባቡር ጣቢያ ሀላፊና ፈላጭ ቆራጭ ፈረንሳዊ 20,000 የፈረንሳይ ፍራንክ ጉቦውን ከተቀበለ በኋላ ልዩ ባቡር ፈቀደልን።

ይሁን እንጂ ይኼንን ባለአንድ ፉርጎ ፈጣን ባቡር አሙቆ ለጉዞ ለማዘጋጀት ረዘም ያለ ጊዜ ስለሚፈጅ በተራውና የሰው መዓት በታጨቀበት በዚያ ቀርፋፋ ባቡር ቀድመን እንድንሄድና፣ ፈጣኑ ባቡር በመንገዳችን እንደሚደርስልን አሳምኖን ለመቆሚያ የምትሆን ቦታ አስያዘን። አማራጭ አልነበረንምና እኛም በዚህ ተስማምተን ከአዲስ አበባ ተነስተን ረጅሙን የጂቡቲ መንገድ ተያያዝነው።

ይኼ ቀርፋፋ ባቡር በሚያስደንቅ ሁኔታ በተወሰነለት የጊዜ ገደብ ያለ አንዳች ችግር በደቂቃዎች ልዩነት በየፌርማታው ይደርስ ነበር። ከአዲስ አበባ ወጥተን በእያንዳንዷ ፌርማታ ደርሰን በቆምን ሰዓት አዲስ አበባ የገዛ ልጆቿ በሚጭሩት እሳት እየነደደች፣ እነዚህ የፌርማታ ከተሞች በሰላምና በመረጋጋት የእለት ከእለት ስራቸውን ሲያከናውኑ ይታያሉ። ምናልባት እነዚህ ሰዎች ኢትዮጵያ ዓመት ሙሉ ስላየችው ፍዳና መከራ አልሰሙ ይሆናል። ወይም ደግሞ መዲናዋ አዲስ አበባ በገዛ ልጆቿ እሳት እየነደደች በጠላት ጦር እጅ ለመውደቅ መቃረቧን አልገመቱ፣ አልሰሙ ይሆናል። ብቻ ማን ያውቃል ? በሰላም በስራ ገበታቸው ላይ ናቸው።

ሞጆ ስንደርስ የሞጆው ፌርማታ ስልከኛ የኛ 20,000 የፈረንሳይ ፍራንክ ጉቦ የተከፈለበት ልዩውና ፈጣኑ ባቡር ከአዲስ አበባ መነሳቱን አበሰረን። አዲስ አበባ ግርግር በግርግር ሆናለች። ድብልቅልቋ ወጧል። መንግሥት የለም። ወታደር የለም። ፖሊስ የለም። ከሌባና ከዘራፊዎች ጋር ጤነኛው ሰው እንኳን ሳይቀር ተደባልቆ ይዘርፋል። አዲስ አበባ በጠላት ሳይሆን በገዛ ልጆቿ እጅ ወድቃ እሳት በእሳት ሆና እየነደደች ነው።

በአዲስ አበባ የባቡር ጣቢያ ያሉ የኢትዮጵያ ሰዎች በሙሉ ተበትነዋል። በባቡር ጣቢያ ይሰሩ የነበሩት የፈረንሳይ ዜጎች ከጂቡቲ በመጡ የጅቡቲና የሴኔጋል

ስልም ተኳሽ ወታደሮች ታጅበው ፈረንሳይ ኤንባሲ ገብተዋል። አሁን በለገሀር የባቡር ጣቢያ በስራ ገበታው ላይ ያለ ሰው ቢኖር ብቸኛው የባቡር ጣቢያዋ ራዲዮ ቴሌግራፊስት ስልከኛ ብቻ ነው።

አዋሽ በደህናው፣ በሰላሙ ጊዜ ባቡሮች ሌሊቱን አርፈው በሰላም የሚያሳልፉበትና ለቀሪው ጉዞ የሚዘጋጁበት ከተማ ነበረች። ምን ያደርጋል፣ ጊዜው የመከራ፣ የጦርነት ጊዜ ነውና ሌሊቱን አዋሽን ለቀን የምንሄድበትን መንገድ ስናሰላስል ገና ደንገዝገዝ ከማለቱ በተስፋ ይጠበቅ የነበረው ፈጣኑ ባቡራችን አዋሽ ገባ። በዚህ ባለ አንድ ፉርጎ ፈጣን ባቡር ውስጥ አራት ወታደሮች ሁለት መትረየሶች ጠምደው፣ በርካታ የመትረየስ ጥይቶች የታጨቁባቸው ሳጥኖች ላይ ቁጭ ብለው አዋሽ ባቡር ጣቢያ ከች አሉ።

በጉዟችን ላይ እንዳጫወቱኝ እነዚህ አራት ኢትዮጵያውያ አውሮፕላን አብራሪዎች ሲሆኑ፣ በአውሮፕላን ጣቢያ የቀረችውን አንድ አውሮፕላን አስነስተው ለመብረር ቢሞክሩም አውሮፕላኗን ከመንደርደሪያው ጣቢያ ማድረስ ሳይቻላቸው ቀርቶ፣ አውሮፕላኗን ለሽፍቶች በጣቢያዋ ብቻዋን ጥለዋት ይኼው ለቀሪው መንገዳችን ብረት ለበሱን ባቡራችንን በሁለት መትረየሶች አጅበው በደስታ ተቀበሉንና በጉዟችን ጊዜ ሳናጠፋ ቀጠልን።

እነዚህ ኢትዮጵያውን አውሮፕላን አብራሪዎች አዲስ አበባ በመንደድ ላይ እንዳለችና፣ አንዳንድ በግድየለሽነት በሸገር ይንዘላዘሉ የነበሩ ፈረንጆች በቀማኛ ሽፍቶች መገደላቸውን ጭምር አረጋገጡልን።

በመጀመሪያውና በመጨረሻው የኢትዮጵያ ብረት ለበስ ተሽከርካሪ ባቡር ወደፊት ገሰገስን። የሌሊት ጉዞ ለዚያውም በጨለማና ፊዕሞ በማይጠበቅ የባቡር መንገድ እንዲህ በፍጥነት መጓዝ እጅግ አደገኛ መሆኑን ጠንቅቀን ብናውቅም፣ በጣልያኖች እጅ ከመውደቅ የከፋ ነገር የለምና ብረት ለበሱን የባቡር ፈረሳችንን ቼ ብለን ወደ ጂቡቲ ገሰገስን። ከሁሉም በላይ ደግሞ ከደቡብ ጦር ግንባር ወደሰሜን በመገስገስ ላይ ያለው የጣልያን ጦር መንገዳችንን ቆርጦ ሊያቆመን ይችላል።

ገና 500 ኪሎ ሜትር ያህል መንገድ ይቀረናል። የጣልያን ፈጣን ተሽከርካሪዎች ከኛ ቀድመው ፊርማታዎችን ከመያዛቸው በፊት እኛ ቀድመን ለማለፍ በኛ ፈጣኑ፣ የብረት ለበሱ ባቡር ነጂና በጣልያኑ ፈጣን ብረት ለበስ የጦር ተሽከርካሪ መካከል ያለው እሽቅድምድሞሽ ጦፏል። እስካሁን አሸናፊዎች ነን። ሁሉም፣ በምትቀጥለዋ ፌርማታ ለጥቂት ደቂቃዎች ቆም እንልና የምትቀጥለዋ ፌርማታ ነጻ መሆኗን እንጠይቃለን።

እነሆ አሁን ዘቆምንባት ፊርማታ ከፊታችን የምትጠብቀን አፍደም ነጻ መሆኗን ጠየቅን። ስልከኛው አፍደም ነጻ መሆኗንና እስካሁን በጣልያኖች እጅ

እንዳልወደቀች ሲነግረን ትልቅ እፎይታ፣ ደስታ ተሰማኝ። ከሳምንት በፊት አዲስ አበባ ውስጥ አፍደም በጣልያኖች እጅ ገብታለች እየተባለ ይወራ ነበር።

አሁን ወደቆምንባት ፌርማታ በመግባት ላይ ያሉ ሶማሌዎች እንደሚሉት ብዛት ያላቸው የጣልያን ተሽከርካሪዎች ወደ አፍደም በመብረር ላይ እንደሆኑ ተናገሩ። እንግዲህ ጣልያኖች ሩቅ አይደሉም ማለት ነው። እናም ጊዜ ሳናጠፋ በጉዟችን ገፍተን እኩለ ሌሊት ግድም ላይ ከጣልያኖች ቀድመን አፍደምን አለፍናት።

ሁሌም ለጥቂት ደቂቃዎች ቆም ብለን የምትቀጥለዋ ፌርማታ ነጻ መሆኗን እና ሌላም ሌላም ወሬ መቃረሙን ልማድ አድርገነዋልና በቃረምነው ወሬ እስካሁን እድለኞች ነን። እስካሁን በቃረምናት ወሬ መሰረት ጠቅላላው የጣልያኑ የደቡብ ክፍለ ጦር ብቸኛዋን የኢትዮጵያ የባቡር መንገድ ለመቆጣጠር መንቀሳቀሱንና፣ አንድ ፈጣን ቀዳሚ ጦር ገፍቶ መሄዱን ነው። ያ ማለት ደግሞ አሁንም ከአደጋ አልወጣንም ማለት ነበርና ያለ ምክንያት በየቦታው ሳንቆም፣ ወሬ ለመቃረሚያ የምትሆን ጥቂት ደቂቃዎች ብቻ እያባከንን፣ ጊዜ ሳናጠፋ ሌሊቱን በዚያ ጨለማ በብረት ለበሱ ፈረሳችን (ባቡራችን) ወደፊት ገሰገስን። ልክ ሲነጋ ምንም አይነት አደጋ ሳይደርስብን በሰላም ድሬደዋ ገባን።

እዚህ ድሬ የሚኖሩ ፈረንጆች ብዙም ሳይጨነቁ ተረጋግተው እንደሰላሙ ጊዜ ሁሉ ያለ ሃሳብ ይኖራሉ። ሁኔታው ግራ እንዳጋባኝ የተረዳ አንድ ፈረንጅ ጠጋ ብሎ "በድሬደዋ ላሉ ፈረንጆች የጂቡቲው ገገር ወደ 200 ገደማ የሚሆኑ የጂቡቲና የሴኔጋል ተወላጅ የሆኑ ወታደሮች ለጥበቃ ስለላከላቸውና፣ እስካሁን ምንም አደጋ እንዳለ የሚጠቁም ነገር ስለሌለ በድሬደዋ ጥቂት ቀናት አርፌ ወደ ጂቡቲ ባሻኝ ጊዜ መሄድ እንደምችል" ወዘተ. አይነት ነገር ነግሮ ጋበዘኝ። ስለ ግብዣው አመስግኜ በሆዴ ግን "ምንህን ፈልግ" ብዬ ወደ ፈጣኑ ባቡራችን ተመለስኩ።

ሌላው ትኩሱ የድሬደዋ ወሬ ደግሞ ጃንሆይ በልዩ ባቡራቸው ከነቤተሰባቸው ከሁለት ሰዓት በፊት ከድሬደዋ ወደ ጂቡቲ መሄዳቸው ነበር። ጃንሆይ በድሬደዋ አንዳንድ አንገብጋቢ መንግስታዊ ጉዳዮችንና አንዳንድ ውሳኔ የሚያስፈልጋቸውን ነገሮች ለመፈጸምና ለድሬደዋም ሁነኛ ሰዎችን ለመሾም የሚፈጅ ያህል ጊዜ ነበር በድሬደዋ የቆዩት። እኛም ወሬ ለመቀራረምና ለፈጣኑ ባቡራችን ውሃ ለመቅዳት የሚፈጅ ጊዜ ብቻ አባክነን በፈጣኑ ጉዟችን ቀጠልን።

ይኼ በኛ ፈጣን ብረት ለበስ ባቡር ነጂና በጣልያኑ ፈጣን ብረት ለበስ ወታደራዊ ተሽከርካሪ ሾፌር መካከል ያለው እሽቅድምድሞሽ ቀጥሏል። እሽቅድምድሙ ይቀጥል እንጂ እኛ ሁለት ሰስተኛውን የውድድር ርቀት በሰላም ፈጽመናል። በቀረችን አንድ ሰስተኛ መንገድ የሚያሰጋን አደጋ ቢኖር ምናልባት የጣልያኑ የደቡብ ጦር አባኸር ቀድሞ የላከው መንገድ ጠራጊ ቀዳሚ ጦር ቢሆን ነው።

ከዚህ ቀዳሚ የጣልያን እግረኛ ጦር ለመከላከል ደግሞ ከታጠቅናቸው መሳሪያዎች ውጪ ሁለት መትረየሶች ጠምደናል።

ወደ ኢትዮጵያ ድንበር በተቃረብን ቁጥር ጭንቀታችን እጥፍ እየሆነ መጧል። በእንዷ ፌርማታ እንደተለመደው ለወሬ መቃረሚያ ያህል ጊዜ ቆም እንዳልን በአንዲት ሱቅ አንድ ፈረንጅ ሚስቱን እየጎተተና እየሮጠ የባቡራችን ነጂ እንዲያቆምለት፣ ቆሞ እንዲጠብቀው ደጋግሞ ምልክት ሰጠው። የኛም ባቡር ነጂ የፈረንጁን የአቁምልኝ የልመና ምልክት በጊዜ አይቶትኖሮ አቅመለትና በድንጋጤ ነፍሱ ልትወጣ የደረሰች አንድ የግሪክ ነጋዴ ከነሚስቱ በባቡራችን ውስጥ ገባና ቀሪውን ጉዞ አብሮን ወደፊት ወደ ጅቡቲ ሄደ።

ታሪኩን ሲያጫውተን፣ ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት በርከት ያሉ የታጠቁ ሱማሌዎች ወደሱቁ ይገቡና እቃ ማገላበጥ ይጀምራሉ። በዚህ መሀል የኛን ነፍስ አድኗን ባቡራችንን ድምጽ ሲሰሙ የታጣቂ ሶማሌዎች አለቃ ለጓደኞቹ፣ "ጠብቁ፣ ባቡሩ ከዚህ ሲሄድ ይኼንን መናጢ ፈረንጅ ከነሚስቱ ገድለን ንብረቱን በሙሉ እንዘርፈዋለን" ይላቸዋል። እነዚህ ሶማሌዎች ምናልባት ራቅ ካለ ጎሳ የመጡ መሆን አለባቸው እንጂ፣ ይኼ ግሪክ ለረጅም ዓመታት በዚች ቀበሌ ሱቅ ከፍቶ የሚኖርና ሶማሊኛም አቀላጥፎ የሚናገር መሆኑን ባላጡትና እንዲህ አፉቱ ያ የታጣቂዎች መሪ ባልደነፉ ነበር። ብቻ ይኼን የሰማው ብልጡ የግሪክ ነጋዴ ሚስቱን ጎትቶ፣ ለዓመታት የለፋባትን፣ የተቃጠለባትን ብቸኛዋን ንብረቱን ገድለው ሊዘርፉት ለነበሩት ለዘራፊ ነፍሰ ገዳይ ሶማሌዎች ጥሎላቸው፣ ባዶ እጁን ይኼው ከኛ ጋር ወደ ጂቡቲ እየተሰደደ ነው።

እኩለ ቀን ላይ የኢትዮጵያ የድንበር ፌርማታ ከሆነችው ደወሌ ደረስንና መሳሪያዎቻችንን በሙሉ ለኢትዮጵያ የድንበር ጠባቂ ወታደሮች አስረክበን ለ20 ደቂቃ ያህል ከዚያች ፌርማታ አሁንም በኢትዮጵያ ሉአላዊ መሬት ግዛት ላይ ተንዝን። ከዚያ ግራጫና የወይን ጠጅ ቀለም ባላቸው ገደሎች ውስጥ ገብተን ብዙ ተጉዘን ስንወጣ፣ ንፋስ በሌላት አየር ላይ ብዙም የማትውለበለብ የፈረንሳይ ባንዲራ ተገትራ አየናት። አሁን ነፍሳችን በትክክል ተረፋለች። ከጣልያኖች እጅ አምልጠናል።

ከተገተረቺው የፈረንሳይ ባንዲራ ስር አንድ ፈርጠም ያለ ጥቁር ወታደር ነጭ የሴኔጋል አልሞ ተኳሽ ወታደሮችን ወታደራዊ የደንብ ልብስ እንደለበሰ በተጠንቀቅ ቆሟል። ደረቱ ላይ በቀይ ቀለም "የሴኔጋል ወታደር" የሚል ተጽፎበታል። አናቱ ላይ ቀይና ረጅም፣ ሹል፣ አስቂኝ ቆብ ደፍቷል። በቀኝ እጁ ሰደፉን መሬት ላይ አስገድፎ በጠመንጃው አፈሙዝ ላይ የሰካውን ሳንጃ እንደያዘ እንደመያዝ ብሎ በግራ እጁ አይኑንና ግንባሩን አሁን ጊዜ እየጠራረገና አይኑን ከፀሐይ ለመከላከል እየሞከረ ወደፊት አርቆ ያያል።

ብዙም ሳንቆይ በነጭ ድንጋይ (ቦረንቅ) የተሰሩ ከሚመስሉ የወታደር ካንፖች መሀል ማለፍ ጀመርን። አሁን የፈረንሳይ ጂቡቲ ግዛት ውስጥ ገባን ማለት ነው። በመጀመሪያዋ የጂቡቲ የባቡር ጣቢያ አሳዛኙን፣ የመጨረሻውን የአዲስ አበባ ወሬ ሰማን። የአዲስ አበባው የባቡር ጣቢያ ራዲዮ ከሁለት ሰዓታት በፊት ደንቁሯል። ከዚያች ሰዓት ጀምሮ ከአዲስ አበባ ጋር በራዲዮም ሆነ በቴሌግራም መገናኘት አለመቻሉን እያዘነ የመጀመሪያዋ የጂቡቲ ባቡር ጣቢያ ስልከኛ ነገረን። ዘራፊ ሽፍቶች የአዲስ አበባን ባቡር ጣቢያ ጥሰው በመግባት የዘረፉትን ዘርፈው የቀረውን አቃጥለውታል።

ማምሻው ላይ ወደ 17:00 ሰዓት ገደማ በዋናው የጂቡቲ ባቡር ጣቢያ ደረስን። ጃንሆይ ከነቤተሰቦቻቸውና አጀበዋቸው ከመጡት መሳፍንት ጋር ከሁለት ሰዓታት በፊት በጂቡቲው ዋና የባቡር ጣቢያ "ለአንድ ሀገር ንጉሥ" የሚገባው ምንም ነገር ሳይጎድል፣ በታላቅ ክብር የጂቡቲው አገረ ገዢ ተቀብለው በክብር ወደጂቡቲ ቤተ መንግሥት እንደወሰዷቸው ሰማን።

እኛ ጂቡቲ ከገባን ከአንድ ሰዓት በኋላ አንድ ረጅም ባቡር የሴኔጋል አልሞ ተኳሽ ወታደሮችን ከፈረንሳዊው ነጭ አዛዥ መኰንን ጋር ይዞ ከጂቡቲ ተነስቶ በአዲስ አበባ ያሉ ፈረንጆችን ለመርዳት ወደ አዲስ አበባ አቀና።

ይኼ ባቡር ወደ አዲስ አበባ እንዲሄድ ያስገደደው አንድ ያለገመድ የተላለፈ ቴሌግራም ነበር። ይኼው ከአዲስ አበባ የፈረንሳይ ኤንባሲ በአንባሳደሩ የተላለፈ መልእክት እንዲህ ይል ነበር። "የአዲስ አበባ ዘራፊ ሽፍቶች ከተማይቱን አንድደው ከጨረሱ በኋላ አሁን የውጭ ሀገር ኤንባሲዎችን ለመዝረፍ አሰፍስፈዋል። ስለሆነም አደጋ እየመጣብን ነውና በአስቸኳይ ርዳታ ይላክልኝ" ይላል።

በሚቀጥለው ቀን ማለዳ በታላቅ ጥንቃቄ የምትጠበቀዋንና ወደ ጂቡቲ ቤተ መንግሥት የምትወስደዋን መንገድ አልፌ ጂቡቲ ቤተ መንግሥት ገባሁ። በቤተ መንግስቷ ግቢ ውስጥ ብዙ የጭነት መኪናዎች ቆመው አሽከሮች ሻንጣዎችን ይጭናሉ። ጣሪያ በሌለው የቤተ መንግስቷ ሰፊ አዳራሽ ውስጥ ከፍተኛ የእንግሊዝ የባህር ኃይል መኰንኖች (ትናንት በጂቡቲ ወደብ ካረፈች የእንግሊዝ የጦር መርከብ የመጡ መሆን አለባቸው) ወዲያ ወዲህ ይንቆራጠጣሉ።

ብዙም ሳይቆይ በአንድ ነጭ ፈረንሳዊ መኰንን የሚመራ የሴኔጋል ወታደሮች ሰልፈኛ መጥቶ በአዛዡ ቀጭን ትዕዛዝ በሚያስደንቅ ፍጥነትና ቅልጥፍና ሁለት ረድፍ ሰርተው በተጠንቀቅ እንደቆሙ፣ ጃንሆይ ከአቴጌ መነን ጋር የቤተ መንግስቷን ደረጃ በዝግታ መውረድ ጀመሩ። ከኋላቸው ጥቂት ወደኋላ ቀረት ብሎ የጂቡቲው ገዢ ተከትሏቸዋል። ቀጥለው በርካታ የአውሮፓ ሀገሮች ከፍተኛ የጦር መኰንኖች አጅበዋቸዋል፤ ጃንሆይ ተራ ካባ ደረብ አድርገዋል። ከዚህ አሳዛኝ ዓይናቸው አሳዛኙ የኢትዮጵያ ውድቀት ምንኛ እንዳሳዘናቸውና እንደጎዳቸው በግልጽ ይነበባል። ከጃንሆይ

ኋላ የሚሄዱት ራስ ካሣም ያ ሳቂታ ፊታቸው በሀዘንተኛ ሽማግሌ ፊት ተለውጧል። የለሜኑ ጦር ሽንፈትና የኢትዮጵያ ውድቀት እሳቸውንም ክፉኛ ጎድቷቸዋል።

እንዲህ ጃንሆይ ደረጃውን ሲወርዱ እኛ በደረጃዎች ላይ መስመር ሰርተን ከአራቱ ኢትዮጵያውያን አውሮፕላን አብራሪዎች፣ ማለትም ብረት ለበሱን ባቡር ይዘውልን ከመጡትና፣ ስድስቱ ሲዊድኖች ጋር ተደርድረን ቆመናል። ጃንሆይ ለትጽበት ቆም አሉና ሁላችንንም በየተራ ጨበጡን። ከዚያ የሆነ ነገር ለመናገር ከንፈራቸውን አንቀሳቅሰው መልሰው ተዉት። መሪሩ ሀዘናቸው ቃላት እንኳን እንዲናገሩ አላስቻላቸውም፤ አንጀት የሚበላ ስንብት።

ከቤተ መንግስቷ ግቢ ውጪ የሴኔጋሎቹ ወታደሮች ሰልፈኛ ኃይል ለቅቆ ወደ ስደት ለሚሄደው የኢትዮጵያው ንጉሠ ነገሥት የክብር የስንብት ሰላምታ ሲሰጥ ይሰማል። ብዙም ሳይቆይ መርከብ ላይ የተጠመዱ መድፎች ሲተኮሱ ሰማን። እነዚህ ውስን ቁጥር ያላቸው ግዴታዊ የመድፍ ጥይቶች የሚተኮሱት ለበዓል ወይም የአንድ ሀገር መሪ ወደ መርከቧ ሲገባ ለክብሩ፣ ለደስታ የሚተኮሱ የክብር የመድፍ ጥይቶች ናቸው። አሁን የተተኮሱት ጥይቶች ግን ባዶ ጩኸት ሆነው ታዩኝ፤ ልክ ኢትዮጵያን በሬሳ ሳጥን ውስጥ ከትቶ ከቀበሩ በኋላ ለሀዘኗ የሚተኮስ አይነት ነገር።

........................../// ተፈጸመ ///..............................

Mapa č. 1. Přesuny armády rasa Kassy

የራስ ካሣ ጦር የጉዞ መስመር

Mapa 1: የራስ ካሣ ጦር አካሄድ

የኢትዮጵያው ጦር አሰፋፈር፣ 1. ራስ ካሣ 2. ራስ ሙሉጌታ 3. ራስ እምሩ

በአውሮፕላን ከአዲስ አበባ ደብረ ታቦር በረ

የራስ ካሣ ጦር ወደ ጦር ሜዳ ይኼደበት መንገድ

የራስ ካሣ ጦር ከጦር ሜዳ የተመለሰበት መንገድ



Mapa č. 2. Prvni bitva u Tembienu

Mapa 2: የመጀመሪያው የተንቤን ጦርነት

የኢትዮጵያውያን የጦር ሰፈር

1. ራስ ካሣ
2. ራስ ስዩም
3. ደጃዝማች አበራ
4. ደጃዝማች ወንድወሰን
5. ደጃዝማች ወርቅነህ
6. በጅሮንድ ለጥይበሉ እና ደጃዝማች ኃይሉ ከበደ
7. ደጃዝማች አድማሱ
8. ፊታውራሪ አንዳርጌ

የጣልያኖች የጦር ሰፈር

I. የወራዩ የጦር ሰፈር
II. አዲ ዙሃባ አጠገብ
III. አባሮ አካባቢ

Mapa 3: ሁለተኛው የተንቤን ጦርነት

የኢትዮጵያው ጦር እንቅስቃሴ

የጣልያኑ ጦር እንቅስቃሴ

የራስ ካሣ ጦር ሲያፈገፍግ

የኢትዮጵያው ጦር

1. ደጃዝማች ወንድወሰን
2. ደጃዝማች አበራ
3. ራስ ስዩም
4. ደጃዝማች አድማሱ
5. ደጃዝማች መሸሻ
6. ደጃዝማች በየነ
7. ደጃዝማች መንገሻ



Mapa č. 3. Druhá bitva u Tembienu

ሁለተኛው የተንቤን ጦርነት

አዶልፍ ፓርለሳክ ከአደን በኋላ

የአዲስ አበባ ገበያ



አዲስ አበባ፣ ጎራዴ ገበያ



መሀል አዲስ አበባ ከዘመናዊ ሆቴሎቿ ጋር



ዋናው የአዲስ አበባ አደባባይ። አብዛኞዎቹ ሱቆች በግሪክ ነጋዴዎች እጅ ነበሩ።

አዲስ አበባ፣ የጥላ ገበያ

አበዳሪና ተበዳሪ (በርኖስ ከለበሰው በስተጎላ) እጆቻቸውን በነጠላቸው ተሳስረው ዳኛ ፍለጋ ሲሄዱ

ችሎት፣ ተከሳሽ እግዚአብሔርን ምስክርነት ሲጠራ

የአዲስ አበባ የኮረኮንች መንገድ

ወደ አዲሱ ቤተ መንግሥት
የሚወስደው የጌጋር መንገድ (አርባ ደረጃ)

አዲስ አበባ፣ የእንጀራ ገበያ

አዲስ አበባ ዙሪያ፣ የኢትዮጵያውያን መኖሪያ ቤቶች



ንጉሠ ነገሥቱ በዘርን ከመጀመሩ ጥቂት ቀደም
ብሎ ከገርጌሳው ባልኮን ላይ ሆነው
ለእንደራሴዎች ንግግር ሲያደርጉ

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት
ዘኢትዮጵያ በሻሽ ፈረሳቸው

ንጉሠ ነገሥቱ ከአልጋ ወራሹና ከሐረሩ መስፍን ጋር

ራስ ካሣ ኃይሉ ዘዳርጌ የሰሜኑ ጦር ጠቅላይ አዛዥ

ታሪክ ምንጊዜም የማይረሳቸው አፄ ምኒልክ

የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡
የውጭ ፡ ጉዳይ ፡ ሚኒስትር ።

ሙሴ ፡ ሲ. ኦ. ፓርሰንስ

በነሐሴ ፡ ፲፱ ፡ ቀን ፡ ከማታው ፡ በ፱ ሰዓት ፡ ወደቤታቸው ፡ መጥተው ፡ ራት ፡ እንዲጋብዙላቸው ፡ ይለምናሉ ።

ነሐሴ ፡ ፲፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፳፪ ፡ ዓ ፡ ም ።

ልብስ ፡ ፍራክ ፡

የቤተ መንግሥት የእራት ግብዣ ወረቀት

ንጉሠ ነገሥቱ ከሚኒስትሮቻቸው ጋር፤ ከንጉሡ በስተቀኝ ራስ ካሣ (ጥቁር ካባ የለበሱት) ከፊታቸውም የሚታየው ልጅ የሐረሩ መስፍን ልዑል መኮንን ናቸው። ከንጉሡ በስተግራ የቆሙት ካባ ደርበው ጥቁር ቆብ የደፉት ሹም ብላቴን ጌታ ህሩይ ሲሆኑ ከእሳቸው ቀጥሎ ራስ ሥዩም (ባለነጭ ቆቡ) ናቸው።

ወደ አዲስ ቤተ መንግሥት የሚያስገባው ዋናው በር

ጦርነቱ እንደተጀመረ ወታደሮች ሹሞቻቸውን ተከትለው ወደ ጦር ሜዳ ሲገሰግሱ

በማይጨው ጦርነት በጀግንነት የተዋጋው የንጉሠ ነገሥቱ የክቡር ዘበኛ በልምምድ ላይ



የንጉሠ ነገሥቱ ፈረሰኛ ጦር

በደብረ ታቦር ጊዜያዊ አውሮፕላን ማረፊያ
በፊተኛው ረድፍ የቆሙት ከቀኝ ወደግራ ብረየር፣ በጅሮንድ ለጥይበሉ ደጃዝማች ወንድወሰንና ፓርለሳክ

ደብረ ታቦር፣ ጦርነቱ የተጀመረ እለት በራስ ካሣ ቤተ መንግሥት ግቢ



ደብረ ታቦር፣ የራስ ካሣ ቤተ መንግሥት

ሹሞች ... በጦር ሜዳ ልብስ

አዶልፍ ፓርለሳክ ከራስ ወታደሮች ጋር



ደብረ ታቦር፣ ራስ ካሣ በመስቀል በዓል ላይ

በዋድላ ሜዳ ሰራዊቱ ወደ ሰሜን ጦር ሜዳ ሲገሰግስ መሪዎቹ በጅሮንድ ለጥይበሉ (ከፈረሰኞቹ ከግራ ወደቀኝ የመጀመሪያው) ደጃዝማች ወንድወሰን (ከመሃል) እና አዶልፍ ፓርለሳክ በቀኝ አብረው ሲጓዙ

በመጀመሪያው የተንቤን ጦርነት ራስ ካሣ ከጀርባቸው ደጃዝማች ወንድወሰን እና ሌሎች ጀነራሎች ወረድ ብሎ አዶልፍ ፓርለሳክ

ከኮረም በስተደቡብ ሰራዊቱ ለመስፈር ቦታ ሲያማርጥ

ወታደሮች በጦር ሜዳ ፋታ ሲያገኙ ... ችግሮቻቸውን ሲፈቱ

በጦር ሜዳ ወታደሩ በማሲንቆ ስለ ትውልድ አገሩ ሲያንጎራጉር

የመቀሌ ከተማ ዋና አደባባይ

የማርትሬዛ ብር

ንጉሠ ነገሥቱ ከወሳኙ ጦርነት አንድ ቀን ቀደም ብለው ለማስታወሻ ለጋርለሳክ ፈርመው የሰጡት ፎቶግራፋቸው

የአዶልፍ ጋርለሳክ የጋዜጠኝነት መታወቂያ

የቼክ ሪፐብሊኩ ተወላጅ የዚህ መጽሐፍ ደራሲ አዶልፍ ፓርለሳክ ቀደም ሲል ኢትዮጵያን ጨምሮ ብዙ አገሮችን የጎበኙ ሲሆን፣ እ.ኤ.አ በ1935 ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው በመምጣት ከንጉሠ ነገሥቱ ፊት ቀርበው የኢትዮጵያን መኰንንነት ማዕረግ ከተሾሙ በኋላ የስሜኑ ጦር ጠቅላይ አዛዥ ለነበሩት ራስ ካሣ ኃይሉ የጦር አማካሪ በመሆን አገልግለዋል፡፡ በዚሁ ወቅት በመቶ ሺዎች ከሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ጎን ሆነው ታግለዋል፡፡ መጽሐፉ፣ ሃበሽስካ ኦዴሳ (Habešská Odyssea) - የሃበሻ ጀብዱ፣ የዚያን የገበሬ ጦር ጀግንነት ለመዘከር የጻፉት ነው፡፡

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ ISBN 978-99944-52-36-1

ብራና ማተሚያ ድርጅት

ዘጠና ስድስት ብር ብቻ